

# ኤቶዮጵ

4ተኛ ዕትም

ኤቶዮጵም ከራማ ተራራ ይመጣል፤
በግዮን ወንዝ ዙሪያ ይሰፍራል።

ዶ/ር ኢልያስ ገብሩ አዕምሮ

# ኤቶዮጵ

‹‹ኤቶዮጵም ከረርማ ተረርረ ይመጣል››

……… ከዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አዕምሮ

……… (ነሐሴ፤ 2010 ዓ.ም)

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

Elation© 2018/ All Rights Reserved!

™Nebadan Publishers
0911124769, 0911035035, 0911351840
*Addis Ababa, Ethiopia.*



አንደ **ዮጵ** ወርቅ ያማረ ስጦታ ቢኖር
፤ጥሩ መፅሐፍ ነውና……………

ከ______________

ለ______________ የተሰጠ***

*1ኛ/እትም ነሐሴ 2010*
*2ኛ/እትም ጳጉሜ 2010*
*3ኛ/ እትም ሐምሌ 2011*
*4ኛ/ እትም ጳጉሜ 2011*

የደራሲው ቀደምት ስራዎች

1/ ኮሜንት (ወጎችና ግጥሞች ለወጣቶች፣ 2008 ዓ.ም፣ አ.አ)

2/ The Pursuit of Unity in Time of Separation, (Spiritual Fiction, 2016, London)

**ﻣﻣﻣ የሽፋን ከቨር ዲዛይን፤ ኢ/ር ሳሮን አሸቱ**

## ....................ምሲጋና፤

ከመጀመር እስከ መጨረስ፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ፣ አልፋና ኦሜጋ... ከዘላለም እስከ ዘላለም ምስጋናዬ ከሁሉም እጅግ ልቆ ከፍ ላለው፣ ለሁሉም ደግሞ እጅግ ቅርብ ለሆነው፤ እስትንፋስን ፈጥሮ በቃሉ ይሁን ላለው፣ ይህንን መፅሐፍ እንድፅፍ በጎ ፍቃዱ ሆኖ፤ የእኔ የምላትን ነፍስ ለለገሰኝ፣ ቀለም መከተቢያ ጣቶቼን አርቃቂና ሰሪ፣ የልቦናዬ አነሳሽ ብፁዕ መንፈስ፣ የአዕምሮዬ መሪ፤ ምሉዕ አዋቂ ለሆነው ሃያል ፍቅር፤ በተለያዩ ቋንቋዎች፣ በተለያዩ ስሞች፤ እግዚአብሔር/ ረቢ/ አዶናይ/ ኤልሻዳይ/ ኤሎሄ/ አላህ/ ኦላ / ኢላህ/ ዋቃ/ ዋካ/ ጋድ/ ጌታ/ ጎይታ/ ያህዌ/ ጃህ/ ራህ/ ዣህ... እየተባለ በእልፍ ስሞች ቢጠራም እርሱነቱ ግን ለማይለዋወጠው አሐዱ የምህረት አምላክ ይሁንልኝ፡፡

***››››ጃንሆይ ዘመን በነበሩት ፀሐፍት አባቶቻችን ወግ ንጉሦቻችንን እናመሰግናለን።***






*ለጠ/ ሚ ዶ/ ር ዐብይ አህመድና ኦቦ ለማ መገርሳ... **"የንጉሥ ልብ እንደ ውኃ ፈሳሾች በእግዚአብሔር እጅ ነው፤ ወደ ወደደውም ያዘነብለዋል።"**(መጽሐፈ-ምሳሌ፤ 21:1)*
*እንዲል ቅዱስ ቃሉ በእናንተ ቡድን በኩል ፈጣሪ ትልቅ ውለታን ውሎልናልና እናመሰግናችኋለን፡፡ እነሆ የሙሴ እማት ዮቶር የአገዛዝ መንፈስ ዳግም ተላከችልን!!*

***

*ለዚህ መፅሐፍ እውን መሆን ከእኔ እኩል ለለፋችሁ እንዲሁም "ቢየደከምም፣ ቢዘገይም፣ በርታ ጊዜውን ጠብቆ ያልፋል፡፡" ብላችሁ በሞራል ሊደገፋችሁኝ፣ ዋና አርታዒ ገሊላ ዳንኤል፣ ለገ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ፣ ለዶ/ር ዴቪድ ሻትዝ፣ ጉና ማህታሪ፣ ለተመስገን ስሜነህ፣ ለዶ/ር አሸናፊ ካሳሁን፣ ለሙቡ፣ለበረከት ዓለም፣ ለዶ/ር ጀን፣ ራስ ጃራማይ፣ ለአባ አስጢፋኖስ፣ ለሼህ ከድር፣ ለጋዜጠኛ አዜብ ወርቁ፣ ለጋዜጠኛ ሃይለመለኮት አሰፋ፣ ለፀሐይ ሀይሉ፣ ለማርታ ገዛኸኝ፣ ለአረፋት መሐመድ፣ ለዶ/ር ዓወት አለማና ለዶ/ር ራስ አማኑዔል ተፈሪ የከበረ ምሲጋናዬን አቀርባለሁኝ፡፡*

*(☛ ደራሲው)*

"እስመ እልቦ ዘይኩብር እምፍኖተ ምሒር ወእስንዩ ወፀዊረ ትዕግስት፤"

"ከእርስዋ የሚበልጥ የለምና እርሷ የፍፁምነት የመጨረሻ ህግ ናት፡፡ ከርህራሄና መልካም ከማድረግ ትዕግስትንም ከመያዝ የበለጠ ህግ የለምና!"

"ኢ-ኦላህ ማዓ ሳቢሩን፤" --------- "አምላክ ከታጋሾች ጋር ነው፡፡"

… ይህንን መፅሐፍ ጀምሮ የመጨረሱ ትዕግስት እንዲኖራችሁ ጽኑ መሻቴ እንደሆነ ከወዲሁ እየገለፅኩኝ መፅሐፉ ላይ ስለሚኖራችሁ ማንኛውም አይነት አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ አስተያየቶች፥


የደራሲው አድራሻ

- 0913714275
-Elationunifire@gmail.com
- Elias Gebru Aimero
- Elation Unifire
ፖስታ፡ (ኤልያስ ገብሩ አዕምሮ - 24741
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

## ማውጫ


ርዕስ , , , , , , , , ገፅ

ተግባቦት - - - - - - - - - - - - 6

ምዕራፍ አንድ............. ♎ዘ-ፍጥረተ አውትት ---------------- 9

ምዕራፍ ሁለት............... ጽዮን ---------------------------- 33

ምዕራፍ ሦስት............. ♛ መልዓከትና ኢጋንንት ☿ ---------- 55

ምዕራፍ አራት ............... ≐ ጭላንጭል ጮራ --------------- 83

ምዕራፍ አምስት ............... ባህታዊው ከላሲታ --------------- 113

ምዕራፍ ስድስት ................ ዝህ...ራህ...ውሃ... ❢ ------------- 159

ምዕራፍ ሰባት .................... ወሎየው ወልዩ ----------------- 202

ምዕራፍ ስምንት ................ ሳባውያንና ኡቢያት ------------ 223

ምዕራፍ ዘጠኝ .................. ጥቁር አክሱም ◚ --------------- 263

ምዕራፍ አስር ------------ ቁሮ ቃሮ ♞ ጉዳ ፋኖ ——— 285

ምዕራፍ አስራ አንድ ............. የሮማ ከፍታ ------------- 315

ምዕራፍ አስራ ሁለት ............ ኤ ቶ ዮጵ ---------------- 346

ምዕራፍ አስራ ሦስት .......... አንድ ፍቅር ♥ ------------ 366

## ተግባቦት...

ጠቅለል አድርገን ስንተምን የኢትዮጵያ ዋና ዋና፣ ባለብዙ ተከታይ ሃይማኖቶች ክርስትናና እስልምና ናቸው:: ይህም መፅሐፍ ሁለቱን ሃይማኖቶች በጥልቅ መርምሮ፣ የሚስጥሩን ፍቅር መዞ አውጥቶ፣ ሌሎች ሀገር በቀል ሰማያዊ ወጎችን አካቶ፣ ለሁሉም ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን ማሕበረሰባዊ ታአማኒነት እንዲኖረው የእነዚህ ሃይማኖቶች ታላቅ ማስረጃ የሆኑት ቅዱስ መፅሐፍቶችንም በሰፊው ያጣቅሳል::

በአይን የማይታዩ ነገሮችን ማመን የሃይማኖቶች መሰረት ከመሆኑም ባሻገር ሳይንስ ለፍጥረት ጅማሮ የሚያቀርበውን መላምት ጨምሮ ብዙ እንደ ግራቪቲና የአስትሮ ፊዚክስ፣ ብሎም ኬሚካል ቀመሮች ባልታዩና ባልተዳሰሱ መረጃዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: የሚታየውን ከማይታየው ማቀራረብ፣ የሚፃረሩ የሚመስሉ ሀሳቦችንም ማስማማት አንዱና ዋነኛው የዚህ መፅሐፍ አላማ ነው:: በሃይማኖቶች መሃልም ይሁን በኢትዮጵያዊነት ዙሪያ ተሸሽገው የነበሩ ድንቅ ድንቅ እውነታዎችን በታሪኩ ውስጥ ዳሰስ አድርጊያለሁኝ:: ስናጣብቀው እየተበጣጠሰ ያስቸገረንን የዚህ ዘመን ኢትዮጵያውያን ፖለቲካዊ ቀውስ፣ ምጣኔ-ሀብታዊ ድህነትም ይሁን የስነ-አዕምሮ ንቃተ-ህሊና ደረጃ በመግለጥ፣ ከጥንቱ የሊቃውንት ቅም-ቅም ኢያቶች ጥበብ ላይ ተመርኩዤ አሁን ላለው ነባራዊ ሁኔታችን ስር-ነቀል መፍትሔዎችን ለማመላከትም ሞክሪያለሁኝ::

አብዛኛው የመፅሐፉ መልዕክቶች ከእውነተኛ ታሪክነትም በላይ ከነተጨባጭ መረጃዎቻቸው የተጠቀሱ መለኮታዊ ዳራዎች ናቸው:: በእርግጥ አንባቢው እንዳያሰለችና ስነ-ፅሑፋዊ ውበት እንዲላበስ እውነተኛ ታሪኮቹ ልቦለዳዊ ቀለም ተቀብተው ውብ ኒሻን ተሸልመዋል:: ዞሮ ዞሮ "ህይወት ራሷ የፈጣሪ ልብ-ወለድ ነች" እንዲሉ ይህም መንፈሳዊ ታሪክ ቀመስ ረጅም ልብ-ወለድ መፅሐፍ የኛን የተቀደሰ ጥንታዊ ማንነት አሁን ካለንበት ውጥንቅጡ የወጣ ዓለም ጋር እንዴት መቃኘት እንዳለብን ትንሽም ቢሆን አቅጣጫ ይጠቁማል ብዬ አምናለሁኝ::

*በተለይ ባለፉት የተወሰኑ አመታት ውስጥ የቅድስት ኢትዮጵያን ትክክለኛ ምንነት የሚያሳዩ እውነተኛ ታሪኮቻችን ላይጠፉ ከተዳፈኑበት በብዛት እየወጡ ይገኛሉ:: እነመሪራስ አማን፣ ፕ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ፣ ዲ/ን ዳንኤል ክብረት፣ መጋቢ ሐዲስ እሸቱ፣ በእውቀቱ ስዩምን መሰል ቅን፣ ቱባ ፀሐፍት ምስጋና ይግባቸውና:: ይህን መፅሐፍ ግን ለየት የሚያደርገው ነገሮቻችንን ብዙም ባልተሞከሩ ግን ተጨባጭ በሆኑ አዳዲስ በሆኑ መንገዶች ማየቱ፤ ተሸፋፍነው የሚታለፉ ግን በማንነታችን ላይ ትልቅ አሻራ ያላቸውን እሴቶች ደፍሮ መበርበሩ፣ የጥንቱን የነገረ-ጥበብ ልቅናችንን አሁን ባለንበት ዘመን እንዴት መተግበር እንዳለብን ጥሩ ራዕይ አመላካችነቱ፤ በተለይ ደግሞ በቁጥር ወደ ግማሽ ገደማ የሚጠጋውን የሀገራችንን ሙስሊም ማህብረሰብ ታሳቢ አድርጎ በመከተብ፤ በእነ ቀዳማዊ ሙፍቲ ሐጂ ዑመር ኢድሪስ፣ ኡስታዝ አቡበከር አህመድ፤ አህመዲን ጀበል፣ ሐሰን ታጁና ኡስታዝ ያሲን ኑሩን መሰል አሊም ፀሐፊዎች ቢገለፅም ከሙስሊሞች አልፎ ለሁሉም ያልተዳረሰውን ማንነቱን የመረመረና የሃይማኖት ግንብ ያለያየውን የእውቀት ባህር ለማቀራረብ እንደ አቅሚቲው የሞከረ መፅሐፍ መሆኑ ነው::*

*መፅሐፉ በእውነተኛ ክስተቶች ላይ የተመሰረተ ታሪክ ይዞ ቢቀርብም የተጠቀሱት ስሞች ከገሀዱ አለም ጋር የመመሳሰል ነገር ቢኖር አጋጣሚ ብቻ እንደሆነ ከወዲሁ ለማሳወቅ እወዳለሁኝ::*

*።። እንግዲህ ውድ አንባብያን እስካሁን በኖርኩባቸው አመታት ያገኘሁትን መንፈሳዊ መገለጥ ከአዕምሮ ንጥረ-ሃሳብ ጋር በጥበብ አዋዝቼ አቅርቢያለሁኝ፣ ማንም እውነትን የሚሻ ቢኖር እውነትን አውቃታለሁኝ ብሎ በራሱ መብቃቃቱን ያቁም፤… "ራሳችሁንም ፈትኑ፣ ሁሉንም መርምሩ፣ ከከፉ ሽሹ፣ የሚበጃችሁን ያዙ፤" (2ኛ ቆሮ 13፥5:: 1ኛ ተሰ ፤ 5፥20) እንዳል ወርቃማ ቃሉም፣ ነብዩም "ኢልምን ፍለጋ ቻይናም ድረስ ቢሆን ሂዱ፤" ብለዋልና በቅን ልቦናና አዲስ እውነትን ለመቀበል ዝግጁ በሆነ አዕምሮ መፅሀፉን እንድታነቡት እመክራለሁኝ::*

☛ *ዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አዕምሮ*

**** ቶ – ቶ ****

“ንባብ ያውቃልና አንብብ ይሉታል፡፡ ‘እኔስ አትሮንስ አቀርባለኊ፤ መፅሐፍ አወጣለኊ፤ መብራት አበራለኊ፤ እናንተ አንብቡ’ ይላል፡፡”

*(አረጋዊ መንፈሳዊ)*

“(1)አንብብ ያ ሁሉን በፈጠረው ጌታህ ስም፡፡ (2)ሰውን እንደአልቅት በመሰለ በፈጠረው (3)አንብብ ጌታህ እጅግ ቸር ሲሆን፤ (4)ያ በብዕር ያስተማረ፤* (5) ለሰውም ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ነው፡፡” *(ለሄኖክ)

*(ቅዱስ ቁርዓን፡ 96፡ ሱረቱል-አለቅ, የአልቅት ምዕራፍ)*

# ምዕራፍ - ፩

## Ω እውነተ ዘ-ፍጥረት Ω

✍ ተጀመረ እንዳልል - ቀድሞ ተጨርሷል

ተፈፀመ እንዳልል -ሲቆረጥ ቀጥሏል፥
አልፋና ኦሜጋ-ሊከፈት ሚዘጋ
የፍቅር ጎዳና በሁለት -ጫፍ ሚላጋ፤
አንድም ከላይ ወርዶ -ከመሬ ይፈለቃል
ከግራ እየተኛ-በቀኝ ጎን ይነቃል፡
ሞተ አበቃ ሲሉት -በሞት ላይ ይኖራል
ለተሻለ አሟሟት- ዳግም ነፍስ ይዘራል።

የመጨረሻው ግጥሙ፣ የመጨረሻ ስንኝ መዝጊያ አራት ነጥቦች ከኢትኤል ብዕር ተንጠባጥበው አረፉ። የሚወደውን የግጥም መፃፊያ ደብተሩን ከደነና ከጎኑ አስቀመጠው። ድፍን 5 ዓመታትን የፈጀበት የጥበብ ስራው፣ የበኩር ልጁ አልቋል፤ የ'ሱ የህይወት መንገድ፣ የፍቅሩ ጥማት፣ የኑሮ ፈተናው ውጤት ግን ገና አላበቃም... ጥፋቱ አልተሻረም፣ ፍቅሩንም አልገለፀምና!

*** ፉ – ፉ ***

*…2010 ዓ.ም/ ኢ.ኢ.ትዮጵ.ኦ*

*ጥር ወር፣ ዕለተ ሰኞ -› ወሎ- ጨለማ ዱር…*

**እ**ኩለ ሌሊት… ፅዮን፣ ዝምተኛዋ ልጅ - ከድቅድቁ ጨለማ ጋር ተፋጣለች፤ የት እንዳለች ፤ እንዴት እዚህ እንደመጣችም አታውቅም፡፡ ከጥግ እስከ ጥግ የተዘረጋ ፅልመት፣ ፀጥ ረጭ ያለ ሌሊት ውስጥ ብቻዋን ነች! ማንም፣ ምንም የለም! መርፌ ካየ ህፃን የበለጠ ፈርታለች፤ ቢያንስ እርሱ መርፌውን አይቷልና፡፡ የገዛ ትንፋሿ ከጆሮ ግንዷ ስር እንደሚነፋ የእድር ጥሩንባ ይጮኽባታል፡፡ የእድር ጥሩንባ ለሷ ትርጉም ነበረው… አሁን ግን ትርጉሙን ረስታዋለች፡፡

ከአንታርክቲክ የበረዶ ግግር የመጣ ያህል የቀዘቀዘ ንፋስ እያፏጨ መጥቶ ጉንጮቿን ይላተማል፣ ውስጧ ግን ታላቅ ንዳድ ወርሶት በጥማት ይቃጠላል፡፡ በቁጥቋጦው ላይ በባዶ እግሯ እንደቆመች የታወቃት የቆንጥሩ እሾኽ ውስጥ እግሯን በስሱ ሲጠረቁሳት ነበር፡፡ ሲወጋት ከውጭ ቆዳዋ ላይ የተሰማት ህመም ግን ከውስጧ ስቃይ ጋር ቢወዳደር የስፖንጅ ጭቤ ይሆናል፡፡ ውስጧ እጅግ ታሟል! አንድ ነገር በነርቮቿ ውስጥ ሰርፆ ገብቶ የስሜት ህዋሶቿን ሲደቁስ ይታወቃታል፡፡ እንዴት እዚህ መጣሁኝ?… እዚህስ ማለት የት ይሆን? የጨለማ ቋንቋ፣ መልስ አልባ ትንቅንቅ ከራሷ ጋር ገጠመች፡፡ ለማይሆን ነገር መባዘን፣ ከድፍን በርሜል ውስጥ ያለች ጥቁር ሲኒ… አይኗን በትግል ገልጣ አካባቢውን ለማስተዋል ሞከረች፤ ፀሐይን ፈለገቻት… ከሃጂዋ ፀሐይ ቦታ ለቃለች፤ የከሃጂዋ ዘመድ አዝማዶች፣ ኮከቦች አኩርፈዋል፤ ጨረቃ ድንቡልቦቃ በጥቁር ደመና ተጋርዳ፣ ተደብቃ ተከዛለች… ህይወት አልባ የመሰለ፣ ሙትቻ ሰማይ በተራው በጨለምተኛ አይኖቹ መልሶ ቁልቁል አፈጠጠባት፡፡ አንገቷን ሰበረች፣ ያላወቀችውን ቀን ረገመችው፣ ያላወቀችውን ቦታ ጠላችው፡፡

ከፊሷን ጨረቃ የጋረዳት ዳመና እንደ ዘገምተኛ አውሮፕላን በዝግታ ቦታውን ለቀቀ፡፡ የፅዮን አይኖች ቀስ በቀስ ጭለማውን እየለመዱላት ሲመጡ ወደ ምድር ፊቷን መልሳ አሻግራ ለማየት ጣረች፡፡ ዳኑ ግን

ከጨለምተኛው ሰማይ ጋር የተነካኩ የሚመስሉ የረጃጅም ዛፍ ቅርፆች እንደ መጋረጃ ተሰድረው አይታዋን ጋረዱት:: ከሚደንሱት የዛፎቹ ቅርንጫፎች ላይ የቅጠል ዝናብ ሲረግፍ በብዥታ ይታያታል:: የአይኖቿን አጉሊ መስታወቶች አስተካከላ ወደፊት አሻግራ ለማየት ተንጠራራች፤ ሆኖም ከቁመቷ እጅግ ረዝመው ከሰማዩ ጋር የተነካኩ የሚመስሉ ዛፎች ዳግም አይታዋን ጋረዱት፡ ለእነርሱ እሷ ከግዙፍ ሰው እግር ስር ተንጠራርቶ እንደቆመ የጉንዳን ወታደር ነበረች:: ሸውው… ሸውው… ከሚሉት ቅርንጫፎቻቸው ላይ እንደ ዝናብ የሚረግፉት ቅጠሎች ፍርሀትን ይዘው የሚወርዱ ይመስል የሰራ አካላቷን ፍርሀት ውርር አደረጋት…

ጥቋቁር ቁራዎች ከጨለማው ሰማይ ይበልጥ ጠቁረው በአናቷ ሽቅብ ከብ ሰርተው ያንዣብባሉ፤ እየተርበተበተች እንደቆመች ድንገት ከዛፎቹ በአንዱ ማማ ላይ ቅፅበታዊ እንቅስቃሴ ታየ! የቅርንጫፍ ውዝዋዜ አልያም የቅጠል መርገፍ አልነበረም… የሰው ቅርፅ ያለው ነገር ከአንዱ ዛፍ ወደሌላኛው ሽምጥጧል! ጮኸች… ጩኸቷ ግን ለራሷም አልተሰማትም… ድምፅም ብርሃን ይፈልግ ይመስል፤ ከፋትም ልማትም ካልታየ እንዳይሰማ ሁሉ ጉሮሮዋ ጠበበባት:: ተንቀሳቃሹ አካል አሁንም ውልብ ብሎ ከአንደኛው ዛፍ ጫፍ ወደሌላኛው ዛፍ ተሸጋገረ::

ብቸኛዋ ፅዮን ፍርሀትና ጭንቀት ደረቷን ሰንቅረው ይዘዋታል፡ ልቧ እንደ ከበሮ ይመታል! አንድ ሐኪም የልብ-ምት ማዳመጫውን (stethoscope) ከመደበኛ ሰው የግራ ደረት ላይ አኑሮ ቢያዳምጥ ለብ ደብ… ለብ ደብ… የሚሉ ሁለት የደም-ቅዳና ደም-መልስ ድምፆችን ያዳምጣል:: የፅዮን ልብ ግን በዚህ ውጥረት ተውጦ ልብ ዱብ…ዱብ፣ ልብ ዱብ ዱ..ብ…. ዱ..ብ እያለ ሲጮህ ለመስማት ጆሮ ከበቂ በላይ ነበር:: የፍርሃቶች ሰምሶማ ይሶመሱማል!… ዳሩ፣የሚገርመው ፍርሃትና ጭንቀት ባይሰማት፣ ልቧ እንደከበሮ ባይመታ… የፍርሃቱ ደረጃ እንደየሰዉ ቢለያይም አንድ ነገር ግን ግልፅ ነው፤ ይህ አይነት አስፈሪ ሁኔታ ውስጥ ማንም ቢሆን የሚደርስለትን ረዳት እጅጉን እንደሚሻ… ዘመድ አዝማዱንና ወዳጆቹን ማየት ቀርቶ የሰው ዘር የሆነ ማንም ዝር ቢል ታላቅ ተስፋን እንደሚቸረው…ብርታት እንደሚሆነው… ሳይታለም የተፈታ ሀቅ ነው! ቢታለምም የማይታሰር እውነታ!

*** ፉ – ፉ ***

‹ጨለማ ዱር› ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ በሚገኘው ጫካ ውስጥ ካሉት አጅግ ግዙፍ ዋርካዎች መካከል በአንዱ ላይ የሰው ቅርፅ ያለው አካል ተሰይሟል… ለዚህ አካል ሰዎች በዘመን ሽግግር ውስጥ በጅምላ ብዙ ስምን ሲሰጡት ኖረዋል… እሱ ግን ከአለቃው ዲያቢሎስ ጋር በሚለየው፣ ገና ከጅምሩ በወጣለት ስሙ ቢጠራ ይመርጣል… ‹ሱቃኤል›* እየተባለ፡፡

ሱቃኤልም ሆነ ሌሎቹ አጋሮቹ ብዙኀኑ እንደሚስላቸው ቀንዳቸው የተሾለ፣ አይናቸው የቀላ፣ አፍንጫቸው እንደ ድንኳን የተወጠረ፣ ጥርሳቸው የተሳለ፣ ቆዳቸው የተሸበሸበ… ጥቁር ሰውነት ያላቸውና ገላቸው በሙሉ በጉድፍ የተሞላ ባለአስፈሪ ገፅታዎች አይደሉም፡፡ እንዲያውም ሱቃኤል በአካል መገለጥን የሚመርጠው በዘንካታ ሰውነት ነው፡፡ ዛሬም በምርጫው የዘነጠ ወጣት ሆኖ… ሙሉ ልብሱን ለብሶ፣ ሽክ ብሎ… ከላይኛው ቅርንጫፍ ተቆናጧል፡፡ የብቻ መፈንጫው በሆነው ፩ኛው የህቡዓን ስፍረታዊ ቦታ ውስጥ ሆኖ የፅዮንን ጭንቀት በደስታ፣ ቁልቁል ያስተውላል፡፡

የከፋት ሊቀ-መንበሩ ሳጥናኤል የሰው ልጅ ተስፋ ሲቆርጥ ከማየት የበለጠ የሚያስፈነጥዘው ነገር እንደሌለ ስለሚያውቅ ምን ያህል እንዳኮራው እያሰበ በየመሀሉ ለየት ያለች ፈገግታን ይፈግጋል፡፡ ይህችን ሃይማኖቷን አጥባቂ የነበረች ብላቴና ሴት እንደዚህ እያቅበዘበዘ በዚህ ሰዓት፣ እዚህ ቦታ እንድትገኝ አድርጎ በፍርሀት ስለናጣት ኮርቷል ፡፡ እሷን ለማሸነፍ ከሁለት አመታት በላይ ለፍቷልና፡፡ ቢፈልግ ኖሮ ሌላ ከእምነት የራቁ ሰዎችን ከፍተታቸውን በቀላሉ እየተጠቀመ ወደ መከራ መከተትና ማሰቃየትን በቻለ ነበር፡፡ ያን ከማድረግ ይልቅ ግን እንደ ፅዮን አይነቷን ታታሪ ጧሚና ፀላይ፣ ለማሳሳትም አስቸጋሪ የሆነችን ሴት ተፈታትኖ ወደጥርጣሬና ፍርሐት መከተት የበለጠ የአሸናፊነት ስሜትን እንደሚሰጥ ያውቃል፤ ከባድ የደርቢ ተጋጣሚን እንዳማሸነፈ ያለ ልዩ ፌሽታ እንዲሰማው ያደርገዋል!

"ሰዎች «እግዚአብሔር የሚወደውን ነው የሚፈትነው» የሚሉት የኛ የኢጋንንቶችን የማሸነፍ አባዜ በእጅ አዙር ተጠቅሞ ይሆን እንዴ?" ሲል ራሱን ጠየቀ ሱቃኤል… ጠይቆም መልሱን በማሰላሰል ላይ ሳለ ነበር ትልቅ ርኩስ-መንፈስ ወደሱ ሲቀርብ የተሰማው! የመልዕክት መቀበያ አንቴናዎቹን አጎነ… የበርካታ ሺህ ዓመታት የስራ ልምዱን መሰረት አድርጎ እንደተረዳው

*ሱቃኤልና ሳቁኤል የተለያየ ግብርና ማንነት ያላቸው መላዕክት ናቸው፡፡ ሳቁኤል በመልካምነት የሚገለፅ የሳቅና ደስታ ቅዱስ-መልዓክ ሲሆን ሱቃኤል ግን ለሰው ልጅ ሲቃርና መከራ አምጪ የእርከሰና ፍጡር ነው፡፡

የቅርብ አለቃው ሀልውና ወደእሱ እየቀረበ እንደሆነ መገመት አላደገተውም… ከባድ የሆነ ዕልመትን የተሸለመው አዛዝኤል አጠገቡ ደርሶ ቆመ፡፡

"ገ! የተከበረው የሰው ልጅ እንዲህ በፍርሀት ሲርድ ከማየት በላይ ምን የሚያስደስት ነገር ይኖር ይሆን ጓድ?" አለውም… ረጅም ጥቁር ካፖርቱን እንደቁራ ክንፍ እያንሳፈፈ፤

"እውነት ብለዋል የተከበሩ አለቃ… ቂቂቂቂ…" መለስ ሱቃኤል የፌዝ ሳቅ እያስረቀረቀ፤ "አለቃ ብዬ ስጠራኽ ሌላ አጋንንት 'ኮ ነው የምትመስለኝ አለቃ አዛዝኤል¡" አብረው እንደ እባብ ተሸሽሸ እያሉ ተፍነከነኩ፡፡ ምንም እንኳን አዛዝኤል የሱቃኤል ዋና አለቃ ቢሆንም እነርሱ ግን የአለቃና ሰራተኛ ሳይሆን የቅርብ 'ጓደኛ' አይነት ቀርርብ ነው ያላቸው፡፡ መቼስ ብዙ ሺህ አመታትን አብረው ከሰሩት የቅርብ አለቃዎ ጋር በጊዜ ሂደት እንደወዳጅ ቢተያዩ ምንም የሚያስገርም ነገር አይኖርም፡፡

"እኔ ግን ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እነዚህ ሰዎች የሚባሉ ፍጥረታት ደካማና እርባና ቢስ እንደሆኑ ገብቶኝ ነበር" አለ አዛዝኤል…

"ታዲያሳ… እያት እስኪ እንዴት እንደምትርበደበድ!… አሁን የዚህች ሚጢጢ ነፍስ የታላቁን የሰራዊት ጌታን ቅዱስ-መንፈስ መሸከም ይችላል ቢባል ማን ያምናል?" ብሎ ሱቃኤል ትንሽ እንደመተከዝ ካለ በኋላ "እኔ ግን…" አለ፣ በስሜታዊነት ወሬውን እየቀጠለ "እኔ ግን ሁሌም ሚስጥር የሚሆንብኝ ነገር ይሄው ነው… 'ከኛ ከእሳት ልጆች አብልጦ እነዚህን ጭቃዎች ያከበረበት ምክንያት ምን ይሆን?' ብዬ ራሴን ሳልጠይቅ ውዬ አድሬ አላውቅም፡፡ ከሊቀ-መንበሩ ሳጥናኤል እና ከበላይ አለቆች በስተቀር ከሌሎቻችን ተደብቆ የተያዘውን የእውነተ ዘ-ፍጥረትን ሚስጥር ለማወቅ እንደጓጓሁት አለሁት፡፡ አንተም «ከዛሬ ነገ እነግርሀለው» እያልክ ይሄው ስንት ሺህ አመታት አለፉ? ስንትና ስንት ሰዎችን በማሳሳት ብቃቴን ባስመሰከርም መቼ የስልጣን ደረጃዬ እንደምትጨምርልኝና ሚስጥሩን እንደማውቅ ምልክት እንኳን ሰጥተኸኝ አታውቅም… አሁንማ ተስፋ መቁረጥ ጀምሬያለሁኝ!"

*አዛዝኤል የሱቃኤልን የተጠራቀመ ብሶት ለመረዳት አላዳገተውም ነበር፡፡ ይህንን ደረጃ ለመስጠት ብዙ እንዳስጠበቀው በደንብ ያውቃል፡፡ እርግጥም ለሱቃኤል የስልጣን እድገት ለማድረግና የዘ-ፍጥረት እውነትን ሚስጥር ለመግለፅ ትክክለኛው ጊዜ አሁን ነው!*

*"እንግዲያውስ በሚያስፈነጭህ ዜና ላበስርህ ነው ጓድ ሱቃኤል… ከዚህች ደቂቅ ሰዓት ጀምሮ አንተ የመቶ-ሺህ ጋኔሎች አለቃ፣ የርኩሰ-ህቡዓን አበጋዝ ሱቃኤል ሆነሃል!"*

*ሱቃኤል ይህንን ብስራት በሺዎች ለሚቆጠሩ ዘመናት ሲጠብቀው ኖሯል፣ ሲመኘውና ሲያልመው ከርሟል… 1ኛና 2ኛ የዓለም ጦርነቶች ላይ ስንቱን ደም እያፋሰሰ ሲፈነጭ እንኳን ይህ ክብር አልተሰጠውም ነበር፡፡ ዛሬ ግን ያለመው ተፈታ፣ የተመኘው ደረሰ፣ ደስም አለው፡፡ ደስታው ግን እሱ እንደወጠነው ሰማይ የሚነካ ፈንጠዝያ አልነበረም፣ በልኩ የተመጠነ አዎንታዊ ስሜት እንጂ፡፡ ምንአልባትም ለዘመናት የተመኙትን ነገር የሚያገኙት ለነገሩ ተገቢ ሲሆኑና ቢያገኙትም የማይገረሙበት ደረጃ ላይ ሲደርሱ ይሆናል፡፡ አልያም ህይወት በራሷ እስኪያገኟት እየጓጉ የቋመጡለትን ነገር ሲያገኙ ደግሞ ከንቱነቱን እየተረዱ የሚኖሩባት የወረት መድረክ ስለሆነች ይሆናል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን ሱቃኤል የማዕረግ እድገት ማግኘቱ የጠበቀውን አይነት ደስታ አልሰጠውም፡፡ ግና ከላይ ሲታይ ስልጣን ዕውቀትን የሚገዛ ቢመስልም በንጥረ-ጥበብ ውስጥ ዕውቀት ለመኖር የተሻለ ትርጉም ይሰጣልና ሱቃኤልም የጓጓለትን የስነ-ፍጥረት ሚስጥር ማወቁ ያስፈነጥዘው ይሆናል፡፡ እርሱም ቢሆን ይህንን ነገር ተገንዝቧል፡፡ የስነ-ፍጥረትን እውነት ለማወቅ ቀጠሮ መስጠትን አልፈለገም፡፡*

*"አሁን ሚስጥሩን ለማወቅ በቂ ስልጣን ላይ ደርሻለሁኝ፣ ስለዚህ ጊዜ ሳትፈጅ «እውነተ ዘ-ፍጥረትን» ንገረኝ?!" አለ ሱቃኤል… የጨቅጫቃ ህፃን ጉጉት እየተነበበበት፣*

*አዛዝኤል ከሊቀ-አጋንንቱ ሳጥናኤል ወርዶ ተዋርዶ የመጣለትን ታሪክ ወደሱቃኤል ለማሳለፍ ጉሮሮውን ሳለ፡፡ ወትሮም የማመንና የመታዘዝ እንጂ የእውቀትና አሳምሮ የማቅረብ ችግር አልነበረበትምና ጀመረ…*

*"ሁሉም የሆነው አሁን ካለንበት ጊዜ እጅግ ርቆ በሚገኝ ወቅት ነበር... ለነገሩ እሱ እንደሚለው ሳይሆን ያኔ ወቅትም አልነበረም...*

""""""""" """"""""""" """"""""""" """""""""""""" """""""""""""" """""""""""""

*** ፍ – ፍ ***

# እውነተ ዘ-ፍጥረት .......... O Ω ❄

...ያኔ "ወቅት" የሚባል ነገር አልነበረም!

ያኔ ፊትና ኋላ አልነበረም!

ያኔ ጥሩና መጥፎ አልተፈረጀም!

ያኔ ህይወትና ሞት፣ መኖርና አለመኖር አልነበረም፤

አምላክ ለብቻው፣ ከሁሉም ጋር ነበርና!!!

ድቅድቅ ጨለማና ጥልቅ ፀጥታ ብቻ፣ ለውጥ የሌለው ስክነት፣ ተረጋግቶ የተዘረጋ ውሀ ከበላዩም የተንሳፈፈ ቅዱስ መንፈስ (ዘፍ-1:2)

*"ኤርጋ ዱፍታን ዱፍቴ ኡሜን ወላቡ ባተ ዱቢ አካና ኢርግኔ ሀንቤከኦ"* (*ምፅአት* ከመጣ በኋላ ፍጥረት ከውሀ ወጣች፤ እንዲህ ያለ ነገር አይተንም አናውቅ!) እያሉ ኢሬቻን በውሀ ዙሪያ ማከበራቸው፤ ምስጋና የሚያቀርቡበት ሚስጥር ሲፈታ... እነ‹ማይ› ማለትም ከውሀ የተገኙ ሰዎች እንዲባሉ ሁሉ፤ በንሰሓ ጥምቀት፤ በፀበልና በዘምዘም ህይወት እንደምትታደሰው ሁሉ!

ከዚሁ የህይወት ምንጭ ውሀ (አል-አንቢያ 21፤32) ላይ የተንሰራፋው ሐያል መንፈስ (ዘፍ-1:26) እምቅ ሐይል መንቃትን ሻተ (ሱራ ሁድ- 11፤7) ፡ ረቂቅ እውነትም በማወቅ ሰረገላ ፊት እየጋለበ ካልተኛበት ሽለብታ፤

***ሊታላቅ ውጥን፣ ሊታላቅ ድርሰት፣ ሊታላቅ ቃል፣ ሊታላቅ ስራ! ነቃ!***

በመጀመሪያ ቃል፤ እንደ ሰይፍ የሰላ ምሉዕ-ሐይል ነበረ! (ዮሐ1፤1)፣ እርሱም ማድረግን በሻተ ጊዜ ‹ሁን› ሲለው/ ሲሆነው/ ይሆን ነበር! (ሱራ-ያሲን፤82)... እናም መሆን፣ መደረግ (Action) ቀጠለ... ከመጠነ-ቁስ ያነሰ ከብደትና መገኘት ያለው ነገር ቢኖር የድምፅ ሐይል (Sound Energy) ነበርም፣ ነውምና ቅንጣቶች ተርገበገቡ፡፡

ሰማይና ምድርን እንደ ሀሳቡ፣ በቃሉ፣ በተግባር ይፀና ዘንድ፣

ከድምፅም የፈጠነና የቀለለን አንድ ሐይል አስገኘ(ዘፍ1፤3)፤ የብርሀን ጨረርን ፈነጠቀ፤ ጨለማና ብርሀንን ለየ፤ ንፋሳትን ከማዕበል አዋጀ፤ ከዋክብትን በጥልቁ ላይ በተነ፤ ይህም ለስራው መልካም እንደሆነ አየ፡፡ መልዓክትና ኢጋንንትንም ከብርሀንና እሳት ፍልቃቂ፣ በረቂቅ ሚስጥር ሰራቸው፡፡ የእሱ የሆኑ ሁሉንም ቅንጣቶች (Atoms & Photons) እንደየባህሪያቸው እያጣመረ ለነገሮች ቅርፅ ሰጠ!

ምድርም ዝናብና ንፋስ፣ ፀሐይና እሳተ-ጎመራን በመሰሉ ውስጣዊና ውጫዊ ተፈጥሯዊ ሀይሎች ለዘመናት ታሽታ ለህይወት አመቺ ትሆን ዘንድ አደላደላት፤ በእሱ ዘንድ አንድ ደቂቃ በእኛ ዘንድ 10.000 ዓመታትን ይወከላል እንዲል ቃሉ፤ አምላክ በዝግመታዊ ለውጥ ውስጥ ባዮሎጂካል ህይወትን ፈጠረ፤ እነዳርዊንን መሰል «ኢቮሊሽን ቲዮሪ» ተከታዮች ባልተፈታላቸው ቅኔ ውስጥ ሁሉን ሰራ፡፡ እነርሱ "ከአምላክ በፊት ምን ነበር?" እያሉ ቢደናገሩም ፊትና ኋላ የሌለው አምላክ ግን ጊዜንም፣ የጊዜ ተገቢዎችንም ፈጠረ፡፡

*ዋናተኛ፣ ተሣቢም፣ ዳሂም፣ ቋሚም፣ ተራማጅም፣ ሯጭም፣ ዘላይም እንስሳትን በወገን በወገናቸው ፈጠረ፡፡ እፅዋትንም በየዘራቸው አበቀለ፣ አሰረገ፣ አፈካ...*

*ጥንትም ውሀ የህይወት ምንጭ ነበርና በፍጥረቱ ሳሎን በኤደን ገነት ውስጥ አራት ታላላቅ ወንዞችን አመነጨ፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱና ዋነኛው የግዮን ወንዝ (አብይ፣ታላቅ) ወንዝ ነበር፡፡ የኤደን ገነትን በከበረ ወርቅ ሊያካብብ ወደልና የ‹ፊሶን› ወንዝ ፈሰሰ፡፡ የሦስተኛው ወንዝ ስም ጤግሮስ ነው፣ የአራተኛው ደግሞ ኤፍራጥስ...*

*በመጨረሻም የፈጠረው ነገር ሁሉ ውብና እንከን አልባ እንደሆነ ተመለከተ... ዳሩ ግን ይሄ ሁሉ ውበት ለ'ሱ ትርጉም አልባ ነበር፡፡ ሁሉን*

ቀድሞ የሚያውቅ… ሁሉም ከርሱ ሆኖ የተፈጠሩ ነበሩና ፍጥረታት በሙሉ ለሱ ከወትሮው ለየት ያለ ስሜትን ሊፈጥሩለት አልተቻላውም፡፡

ቅዱስ-አምላከም የገዛ ፍጥረቱ አካል ሆኖ የሰራውን ሁሉ መመልከትን አቀደ፤ የህይወትን ፍሬ ያጣጥምና ያጣጥል ዘንድም የራሱን ምሳሌዎች በመሬት ላይ መፍጠርን አሰበ፡፡ አሰቦም አልቀረ የፈጠራቸውን መልዓከቶች በሙሉ ሰብስቦ እንዲህ አላቸው፡፡

“እነሆ በገነት ምድር ውስጥ ከኔ የሆነ ነፃ ፍቃድ ያላቸው፤ የኔን ምትክ (ምሳሌ) ተከትለውም ምድርን የሚገዙ እንደ'ራሴዎቼን ልፈጥር ነው!” (ዘፍ፤ 1:26-28) (ሱረቱል-በቀራህ፤ 2:30)

“ምነዋ ጌታዬ…?” ሲል ጥያቄውን ጀመረ የመልዓከት የበላይ ተደርጎ የተፈጠረው ሳጥናኤል፤ ፍም ፊቱ መሬት እስኪነካ እጅ እየነሳ፣

“ምነዋ ጌታዬ? እኛ ያለማቋረጥ እያመለከንህ… እያመሰገንህ… እየታዘዝንህ… ለምን እነዚህን ነፃ ፍቃድ አግኝተው በምድር ላይ ጥፋትና መከራን የሚያበዙ፣ የማይታዘዙ፣ የሚያጠፉ፣ ከንቱ ፍጥረታትን ትፈጥራለህ?”

የረቂቁ አምላክ ጥበባዊ ድምፅ ወደነሱ ተመለሰ፤

“እኔ የማውቀውን እናንተ አታውቁምና ይህን ብነግራችሁ ከመረዳት አቅማችሁ በላይ ነው፡፡” አላቸው፤ እነሆም ከአፈሮች ሁሉ የነጠረው የኤደን አፈር ከህይወት ምንጭ ግዮን ውሃ ጋር ተዋሃደ፡፡ ጥሩና መጥፎ መዓዛን የሚቀያይር ቡኮ እስኪሆንም ለረጅም ጊዜያት ታሸ፡፡

ያ አካል! ጥሩና መጥፎን በኑሮው እንደሚያየው ሁሉ በጊዜው እጅግ ተውቦ ተገንባ፣ ከኃጢያቱም በኋላ እንደሚሞት ደግሞ በጊዜውም እጅግ አስጠልቶ እንዲፈርስ ተገነባ፤ በአርያም ፀጋው እጅግ በሚስብ መዓዛ ታውዶ፤ ስለኃጢያቱም በሚከረፋ ሽታውም ጠርንቶ፣ ኗሪም ሟችም ተደርጎ ከተቦካ በኋላ በፀሐይ ነበልባልም የሚፀና ለባዊ-አዕምሮ ተሰጠው አምላከም የሚያንቀሳቅሰውን ነፍስ በእስትንፋሱ ሞላበት፡፡ እንደ ንፋስ በምርጫው ቅዱሱን ወይም ርኩሱን መንፈስ መርጦ በምድር እንዲንቀሳቀስ ታቅዷልና!

እነሆም ይህ ረቂቅ ውህድ እንደ ተዋህዶ/ተውሂድ ፦ ምሳሌ፤ ከህሊና እስከ ስሜት፣ ከአምላካዊ ባህሪ እስከ አውሬ ከፋት በሰባት መሰረት ተቀይጦ፤ “የሰው ልጅ” ተባለ… በስውር ለፈጣሪው ሊሰዋ ተፈጥሯልና!

*** ፉ – ፉ ***

አዛዝኤል የስነ-ፍጥረት ትረካውን ድንገት አቁሞ ወደ ግራው አርቆ ሲያማትር አድማጩ ሱቃኤልም አብሮት ዞረ፡፡ ሁለቱም እኩል የሚመጣባቸውን ቅዱስ ግብረ-ሓይል ተመለከቱ፡፡

በአካል ሶስት በመንፈስ የትየለሌ ናቸው፤

አመጣጣቸው ያስደነግጣል… ግርማቸው ያስፈራል!

በህያው መንፈስ ተሞልተው… በመታዘዝ ቅዱስ ግብር-ኤል፣ "እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም!" ብሎ በታጠቀው ሚካ-ኤል ታጅበው እየነጎዱ ነው፡፡ ለማዳን ጥሪው ጫካውን እየሰነጠቁ ወደነአዛዝኤል ገሰገሱ፡፡… "ሱቃኤል ፍጠን! ፍጠን! ይህችን ልጅ እየሳብክ ከዚህ ቦታ አርቃት!" አለ አዛዝኤል በተረበሸ መንፈስ፤

"ምነው አዛዝኤል እነዚህንማ ፈርተን መሸሽ የለብንም!… ተዋግተን ማሸነፍ አያቅተንም"፤ ሱቃኤል ለከባድ መንፈሳዊ ፍልሚያ ራሱን አዘጋጀ፤

"ተው ሱቃኤል!" አለው አለቃው፣ ለእርክስና መልዓክት እጅግ አስቸጋሪ የሆነው ትዕግስት እየተነበበበት፤ "ትተን መሄድ አለብን፣ የማትጨርሰውን ጦርነት አትጀምር፡፡ የዚህች ልጅ ጉዳይ ላንተ ማዕረግ ከማሰጠትም ሆነ እኔ ከተጎናፀፍኩት ስልጣን እጅግ የላቀ እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ ቶሎ ብለን ከዚህ እንራቅና ለአለቃዬ ዲያቢሎስ መልዕክት እንላክ!"

"ካልክ ይሁን" አለና ሱቃኤል ይዞታውን ለቆ ከዛፉ ጫፍ ወደምድር ቁልቁል ወረደ፡፡ አዛዝኤልም ተከተለው፤ የአወራረዱ ፍጥነት የፈጠረው ሰበቃ ከንፋሱ ጋር ተደምሮ በተዋጊ ጀት ወደታች የተተኮሰ ተምዘግዛጊ ሮኬት አስመስሎታል፡፡

*** ፉ – ፉ ***

*(ከ፤ ዓመት በፊት፤)*

*ጅማ ዩንቨርሲቲ የጤና ማዕከል፣ የህፃናት ህክምና ንዑስ ክፍል፦*

የተለምዶ የምሳ ጊዜ ካለፈ ከሁለት ሰዓታት በላይ ቢሆንም ጥዋት 4፡00 ሰዓት ላይ የተጀመረው በሽተኞችን እየዞሩ የመከታተል ስነ-ስርዓት (Round) ግን እንደቀጠለ ነው:: በርካታ በነጭ ካባ የተጀቦኑ ሰዎች ከአልጋ አልጋ እያለፉ የበሽተኞቹን ሁኔታ ይገመግማሉ፡ አርስበርስ ይወቃቀሳሉ፡ እንኪያ ሰላምታ እስኪቀራቸው ይተያየባሉ!

አብዛኛዎቹ የ4ኛ ዓመት የህክምና ተማሪዎች ሲሆኑ ጥቂት ተመራቂ ሐኪሞች፣ ሁለት የህፃናት ህክምና የሚያጠኑ ብላቴና ሬዝደንቶችን ጨምሮ ፋርማሲስቶችና ጤና መኮንኖችም ይገኙበታል:: የዙረቱ ዋነኛ ዘዋሪ ደግሞ የህፃናት ህክምና ሊቀ-ጠበብት (Pediatrician) ዶ/ር አበራ (እሳቱ) ነበር:: የቁመቱ መመዘዝና የቦርጩ መወጠር ከትንሽዬ ፊቱ ጋር ተደማምሮ አራት ረጃጅም እግሮች ያሉት ሸረሪት አስመስሎታል:: ትናንሽዬ አይኖቹን በባለ ቡናማ ቀለም ፍሬም መነፅር በኩል እያቁለጨለጨ በዙሪያው ያሉትን ሰዎች ይገረምማል:: ለማሳወቅ ሳይሆን ለማሳቀቅ በሚመስል መልኩ ከተማሪው አቅም በላይ በሆኑ ጥያቄዎች እያፋጠጠ ሁሉንም ያሸማቅቃል:: እነርሱ ሲሸማቀቁ እሱ ደግሞ ይረካል::

ዶ/ር አበራ ከጅማ ምናልባትም በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ታዋቂ የህፃናት ሐኪሞች የሚመደብ ነው:: የህፃናት በሽታዎች እሱ ካጋጠማቸው ዳኛ ፊት እንደቀረበ ወንጀለኛ ይርበተበታሉ:: በዘመናት እውቀትና ልምድን ያካበተ ሐኪም ነው:: በሌላ በኩል ግን ዶ/ር አበራ ከመከበር ይልቅ መፈራትን የሚፈልግ እንደመሆኑ በስራ ባልደረቦቹ፣ በተለይ ደግሞ በተማሪዎቹ ዘንድ ጥላቻን አትርፏል:: ይኸው ዛሬም ሆን ብሎ እነርሱን ለማድከም በሚመስል መልኩ በየአልጋው ጎን ከሚገኙ ወንበሮች አምር ብሎ እየተቀመጠ ረጅም ሰዓት በመቆየት ዙሩን እያጓተተው ነው::

ሁሉም ተማሪ በድካምና መሰላቸት ውስጥ ቢሆንም የኢትኤል ግን ይለያል፡፡ ትናንት ሌሊቱን ሙሉ ሲያነብ አድሮ ጥዋት እንቅልፍ ጥሎት ስለረፈደበት ቁርሱንም ሳይበላ ነበር የመጣው፡፡ የጨጓራውን የይድረሱልኝ ጥሪ 'ሆዴ ዳባ ልበስ' ብሎ እንዳልሰማ እያለፈ ለመማር ቢሞክርም "የራበው ሰው ቢያወሩት የሚሰማው በሆዱ ነው፡፡" እንዲሉ፤ ዶ/ር አበራ አልፎለት ከሚያፈሰው የሳይንስ ወንዝ ውስጥ አንዲት ጠብታ እንኳን መቃመስ አልተቻለውም፡፡ ከርሀቡ እኩል ሌላ ያስጨነቀው ለሰዓታት በመቆሙ የተነሳ እወደ-ባቱ ግድም ዘልቆ የሚሰማው የእግር ህመም ነበር፡፡ ፊትለፊት ላይ ቆሞበት የነበረውን ቦታውን ለቆ ቀስበቀስ ወደኋላ እያፈገፈገ.. እያፈገፈገ… ወጣና የሌላ ታካሚን የእልጋ ዘንግ ደገፍ ብሎ ከሌሎቹ ተማሪዎች ጀርባ ቆመ፡፡

ሆዷ በሚያሳዝን መልኩ ውጥር ብሎ የተነፋባትን የ14 ዓመት ታካሚ ህመምተኛ ሆድ እየጠቆመ ስለ ልብና ጉበት ህመሞች ግንኙነት ሲያብራራ የቆየው ዶ/ር አበራ ድንገት ወደ ኢትኤል አገጩንና አውራ ጣቱን እኩል እያሾለ…

"ማነው ስምህ አንተኛው?" ቢለው ኢትኤል ድንግጥ አለ፡፡ ጥያቄው ለሱ እንደሆነ እስኪያረጋግጥ ድርስ እየተደናበረ፤ ተጠያቂው ሌላ ተማሪ ቢሆንስ ብሎ ሲዞር፤ ዶክተር አበራ በድጋሚ፤

"አዎ አንተኛው!… ምን ወደኋላ ታያለህ?" ብሎ ይባስ አስበረገገው፡፡

"ኢትኤል" አለ በለሆሳስ፤ አያይዞም በደረቱ ላይ የተለጠፈ የስሙን መለያ በግራ እጁ ከፍ አድርጎ ለማሳየት እየሞከረ፤

"‹ራሴን ማጥፋት እፈልጋለሁኝ› የሚል ፊት እያሳየኸኝ እንደሆነ ይታወቅሃል?" አለና ዶ/ር አበራ ቁጣና ፌዝ በቀላቀለ ድምፅ… "ና እስኪ ጠጋ በል ወደፊት… ከማጠሩ መደበቁ!" ብሎ አፌዘበት፤

ኢትኤል ፈራተባ እያለ ወደፊት ተጠጋ… ከወዲያኛው ጫፍ የቆመው ጓደኛው ዮሴፍ ሳቁን ለማፈን ሲጣጣር ይታየዋል፡፡ ናዖድ፣ ቶላና ዘይኔ ደግሞ የዶርም ልጃቸው ችግር ውስጥ መግባት አሳስቧቸው ይሁን እርቧቸው በማይለይ ሁኔታ ፊታቸውን ቡዝዝ አድርገው ቆመዋል፡፡ ማታ አብሮት ሲያጠና ያደረው አብርሃም ደግሞ ወገቡ እንደጎበጠ፣ ቸልተኝነትና ድካም በቀላቀለ ፊት ያየዋል፡፡ የባቹ ስቃይ ቀለሜው ወጋየሁ ፊት ላይ ግን ‹አፍሬብሐለሁኝ!… ታሳዝናለህ!› የሚል ገፅታ ነው የሚነበበው፡፡

ኢትኤል ከፊት ደርሶ፣ ለዶ/ር አበራ ተጋልጦ ቆመ::

*"እሰኪ "Tell me a differential diagnosis for a girl presenting with abdominal swelling?* (ሆዷ አብጦ ለመጣች ልጅ-ገረድ ምክንያት ሊሆን የሚችል ነገር ንገረኝ?)" ጠየቀው ዶ/ር አበራ ፤ ኢትኤል መልስ ይሆናሉ ብሎ ካመነባቸው አማራጮች መካከል አንዷን መርጦ እየፈራ ወደ ቃላት ቀየራት…

*"Pregnancy.* (እርግዝና)"

ዶ/ር አበራ ፊት ላይ ንዴትና ሳቅ ሲዋሀዱ ተስተዋለ…

"ምንአልከ አንተ ደደብ! ትንሽ ቆይተህ ቦርጭ ማለትህም አይቀርማ!" አለና ቦርጩን እያሻሸ ተንቆራጠጠ … ሊማታም መሰለ፡ ኢትኤል ራሱን ለመከላከል ወደኋላው አፈገፈገ፤

ዮሴፍ አፍኖ የያዘውን ሳቅ ለቀቀው፤ ሌሎቹም ተማሪዎች እሱ የቀደደላቸውን ፈር ተከትለው ተፍነከነኩ::

"ዝም በሉ!" ሲል ጮኸ ዶ/ር አበራ… በቅፅበት ፀጥታ ሰፈነ!

"ከናንተም ብሶ ትስቃላችሁ:: እናንተ ናችሁ የዛሬ ዓመት ሁለት ዓመት ሐኪሞች ተብላችሁ ሰው የምታክሙት?… የማትረቡ!" አምባረቀባቸው፤ ሁሉም ተማሪዎች አንገታቸውን ወደ መሬት ደፉ፤ በክፍሉ የሚገኙት ታካሚዎች በሙሉ ዞረው በትዝብት እየተመለከቷቸው ነበር::

…የማያልቅ ነገር የለምና በተማሪዎቹ፣ በተለይ ደግሞ በኢትኤል ላይ በርካታ የስድብ ናዳዎች ከወረዱ በኋላ ለምሳ ተለቀቁ:: "ዛሬ ሰውዬው ምን ሆኖ ነው?" አለ ዮሴፍ፣ እሱ ኢትኤልና አብርሃም ከሆስፒታሉ አብረው ሲወጡ፤ "ራውንዱን እንደ ሕንድ ፊልም አረዘመው እኮ… ኤጭ!"

"እኔማ ካፌ ራሱ ተዘጋብኝ… ምሳ ከየት እንደማገኝ አላውቅም::" አለ አብርሃም በደከመ ድምፅ፤

"አዎ ወላሂ… እኔ ራሱ የዝሁር ሶላት አመለጠኝ!" ዘይኔ በምሬት አጀበው፤

"እንዴ እኔማ እግሬ ተቆርጦ የወደቀ እስኪመስለኝ ድረስ ነው የደከመኝ፤" አለ ናዖድ ነጭ ካባውን አውልቆ እያጣጠፈ፤

"ድካም ቢሉ ድካም ነው እንዴ!?" ብሎ ዮሴፍ ለሐሳቡ ተጨማሪ ግነትን ከለገሰ በኋላ ለጠቅ አድርጎ፤ "አንቺ ኢትኤል ደግሞ ዛሬ እሳቱ ወረደብሽ ኮ… አላስተረፈሽም… እኔ የምልሽ የሆነ በቤተሰብ የመሬት ይገባኛል ምናምን ክርክር አለባችሁ እንዴ?" *(እሳቱ ማለት ለዶ/ር አበራ ተማሪዎች ያወጡለት ቅፅል ስም ሲሆን ከዋናው ስሙና ከባህሪው ተቀይጦ የተገኘ ነው፡፡)*

"አንተ ቀልድ ጀሲ… ሰውዬው ያጠቆረኝ እኔን፤ አንተ ምን አለብህ!"

"አዎ! በጣም አካብደል! የሚረሳህ አይመስለኝም…" አለ አብርሃም ቀበል አድርጎ፤

"ኧረ እባካችሁ ዝም ብላችሁ አትተሽኑ! (አትንቦቅቦቁ)፤ ይልቅ እሱን እርሳውና ሄደን በርጫችንን እንግዛ… ገብተን ማንበብ አለብን!" አለና ዮሴፍ ጊዜም ሳይፈጅ ፈጠን ፈጠን እያለ ቀድሟቸው ወደ ታክሲ መያዣው ሄደ፡፡ አብርሃምና ኢትኤል ከኋላ ሆነው ያዩታል… በቀጫጫ ሰውነቱ ላይ እንደ ስቲኪኒ የተሰኩትን እጆቹን እዚህና እዚያ አንሰራፍቶ ሲሄድ ሊበር የሚያኮበኩብ ቀጭን የጦር ጀትን ይመስላል፡፡ እንደ ደረሰ ፈንጠር ብሎ ከተረኛው ታክሲ ላይ ጥልቅ አለ፡፡

"ከምሳ በኋላ ወዴት ነሽ አብርሽ?"አለ ኢትኤል ወደ አብርሃም ዞሮ፤ ለአመሉ ነው እንጂ የጠየቀው ወደ ዶርሙ ተመልሶ እንደሚያነብ ልቡ ያውቀዋል፡፡

*"ምሳውም ከተገኘ ነዋ!" አለ አብርሃም፤ ሳቅ እያለ፡፡*

*"የምሳ ብር የለሽም እንዴ አብርሽ?" አለ ኢትኤል፤ መልሱንም ሳይጠብቅ እጁን ወደኪሱ እየከተተ፡፡*

*"ሃምሳ ብር ይበቃል" አለ አብርሃም፣ አንገቱን እየደፋ፣ ኢትኤል ሃምሳ ብር አውጥቶ ሰጠው፡፡*

"በቃ ምሳ ልብላና ዶርም ገብቼ ትንሽ እቸከላለሁኝ፡፡ ወደ ማታ ግን ቤተ-ክርስቲያን መሄዴ አይቀርም፡፡ ከፈለግክ ደውልልኝና አብረን መሄድ እንችላለን፡፡" አለው አብርሃም፤ እሱም ይህንን ጥያቄ ለምን-አልባት ያህል ነው እንጂ የጠየቀው ምላሹን ቀድሞ ገምቷል፡፡ ኢትኤል ቤተ-ክርስቲያንም ሆነ መስጂድ እንደማይሄድና "አምላክ የለም፣ ሃይማኖትም አስፈላጊ አይደለም!" ብሎ እንደሚያምን ሁሉም ጓደኞቹ ያውቃሉ፡፡ አብርሃም ግን አብረን ቤተ-ክርስቲያን እንሂድ ብሎ ሳይታክት ከመጠየቅ ወደኋላ ብሎ አያውቅም፡፡

“አይ አልሄድም፤ ግን ማታ ላይብረሪ ስትገባ ደውልልኝ፡ አብረን እናነባለን::” አለ ኢትኤል፤

“እሺ እደውልልሃለሁኝ::” መለሰ አብርሃም፤ ለስንብት ትከሻውን በትከሻው በስሱ እየገጨ፤

“«ፒስ» በቃ ይመችሽ!”

“ቻው!”

ኢትኤል አብርሃምን ተሰናብቶ ወደ ታክሲው ሲገባ ዮሴፍ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ነበር የጠበቀው::

“እኔ ላንተ ቦታ ይዤ ስጠብቅህ አንተ ከዛ ሰገጤ ጋር ቆመህ ትቀዳለህ እንዴ?”

“ጆሲ ምንድነው ወከባ የምትፈጥረው? አስር ሰከንድ አይሆንም እኮ ያወራሁት...”

“ለነገሩ አንተ ችግር አለብህ:: ከማንም ካገኘከው ሁሉ ጋር ጉንዳን ይመስል ሰላምታ ማብዛት፣ እንደ ስራ-ፈት ቆመህ ማውራት ይመችሃል::”

“ምን ማለትህ ነው? አብረሃም እኮ ማንም አይደለም!... የአምስት ዓመት ጓደኞችንን ማንም ትላለህ እንዴ?”

“አቦ አትጨቅጭቀኝ! ለራሴ እርቦኛል...” አለ ዮሴፍ ሂሳብ ለረዳቱ እየሰጠ፤

“እሱን እንኳን ተወው ሰዓቱ ነው የሚያነጫንጭህ!” አለ ኢትኤል፤ ሁለቱም እኩል ተያይተው ፈገግ አሉ:: ታክሲው ቆጪ ሰፈር ደርሶ ሲቆም ቀጥታ የጫት ደንበኛቸው ወደሆነው አሩሲ ነበር ያቀኑት:: ኢትኤል ኪሱን ዳበስ አደረገ:: ዛሬ ብዙ ማንበብና ለነገ የእሳቱ ጥያቄዎች መዘጋጀት ስላለበት ጫቱም ጨመር ተደርጎ መገዛት ነበረበት:: የ50 ብር ገዝተው፣ ምሳቸውን በልተው ወደ ተከራዩት ጠባቡ የማንበቢያ ክፍላቸው እየተጣደፉ ሲገቡ ስምንት ሰዓት ተኩል ሆኖ ነበር::

*** ዩ – ዩ ***

ቢታንያ… በግቢው ወንድ ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን በሴቶችም ጭምር "ቆንጆ" እየተባለች የምትሞካሽ አይነት ተማሪ ናት፡፡ ቆንጆ የሚያመርት ፋብሪካ ያለ ይመስል የዩንቨርስቲው ቅጥር ግቢ በውብ ተማሪዎች ቢሞላ እንኳን ከፉከከሩ ነጥራ መውጣት የቻለች… የተመሰከረላት "ቆንጆ" ነች!

እርግጥ ውበት እንደተመልካቹ ነው፤ ከፊቱ ስትመጣ የተመለከታት አብዛኛው ወንድ ግን አንገቱን ጠምዝዞ እስከ ጀርባው ሲሸኛት ውሎ ላልተገባ የማጅራት ህመም መጋለጡ ግን የተለመደ ነው፡፡ በቁምጣም ይሁን በተቀዳደዱ ጂንስ ሱሪዎች ተነስታ ፌስቡክ ላይ በምትለጥፋቸው ፎቶዎች ከሁሉም የግቢው ሴቶች በልጣ በሺዎች የሚቆጠሩ ላይክና ኮሜንቶችንም ታገኛለች፡፡ ብዙ ብዙ የግቢው ተማሪና የከተማው ኗሪ አፍ አውጥቶ ስለውበቷ ሲመሰክር ተሰምቷል፡፡ ይህንን እሷም ጠንቅቃ ታውቃለች፤ በግሏ ግን እንደ መስታወቷ ስለውበቷ የሚመሰክር፣ ውበቷን የሚገልፅላት ነገር አግኝታ አታውቅም፡፡ በመልኳ ሌሎች ብቻ ሳይሆን እሷ ራሱም ትመሰጥበታለች፡፡ ገፅታዋን ትክ ብላ ለረጅም ደቂቃዎች በመስታወት ማየትና ‹ሜካፕ› መቀባባት በየቀኑ የተወሰኑ ሰዓታትን የሚወስድባት የሰርክ ስራዋ ነው… ዛሬም እንደ ልማዷ ቁጭ እያለች ፊቷን፤ እየቆመች ቁመናዋን እየተመለከተች ነው፡፡

*በሀገራችን መለኪያ ረጅም የምትባል አይነት ሴት ናት፡፡ ጠቃጠቆ አልባ፣ ቀላ ያለች ሴት… የዶልፊን ቆዳ የሚመስል ጥርት ያለ ወዛም ቆዳ ያላት… ለግላጋ ወጣት… የነብር ጣት… ግነት ብቻ ሳይሆን ተሹለው ተቆርጠው ግራጫማ ቀለም የተቀቡት ጥፍሮቿ እውነትም የነብር ጣት የሚመስሉላት፤ ተቀንድበው… ተቀንድበው… አንሰው በኩል ከደመቁት ቅንድቦቿ ስር የተቀባችው የአይን ሻዶዋ የነብር አይንን የሚገዳደርባት… ነብር ናት!*

በኩል እያሰመረች አይኖቿን በከደነች ቁጥር ‹ሻዶዋ› ይረግፋል፤ በ‹ማስካራ› የደመቁትን ሽፋሽፍቶቿን አላቃ ስትከፍታቸው ደግሞ… በሁለት ቀዳዶች በኩል የአይን ብሌኖቿ ይፈነጥቃሉ፡፡ ብርሃናቸው ዘልቆ የስጋዊ ስሜትን ድብቅ መሻት የሚመረምሩ የሚመስሉት ቀስተኛ የአይኖቿ ጨረሮች ተመልካቾቿን የማፍዘዝ አዚም አላቸው፡፡ ትንቡክ ትንቡክ የሚሉ ድልህ ጉንጮች አሏት፡፡ በጉንጮቿ መሀል ስልክክ ብሎ ቁልቁል

ከሚወርደው አፍንጫዋ ታች፣ ብዙም ሳይርቁ...ብዙም ሳይቀርቡ... እግድም የተሰየሙት፣ በሊፒስቲክ ያበዱ፣ እንቡጥ ከንፈሮቿ ሳሚት ሳሚት የሚል ስጋዊ ርሐብን ይፈጥራሉ:: ከብ ሙልሙል ወይም ሶስት ማእዘን እንባሻ ነገር ቆረስ አድርገው በከንፈሯ እያጣቀሱ መብላትንም ይወስውሳል::

ይህን ሳቢ ፊቷን ደግፎ የቆመው መቃ አንገቷ... የሩብ ሩብ ጨረቃ ቅርፅ እየሰራ በግራና በቀኝ ወደ ትከሻዋ ይቀላቀላል:: በተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን በቅንጦተኛ ‹ሎሽኖች› ርሰው ጥርት... ልስልስ... ካሉት ኢጆቿ መገንጠያ በታች የተሰየሙት ጡቶቿ አንዳች ነገር እንደተሞሉ ሁሉ ጉብ ጉብ ብለው ደረቷ ላይ የተኙ ተራሮች ይመስላሉ:: የምትለብሳቸው ስስና ጥብቅ ያሉ ልብሶች የማይበግሯቸው የጡቶቿ ጫፎች ባልረገበ ቾካል እንደተወጠሩ ሁሉ ቀጥታ፣ ከአይኖቿ እኩል ፊት ለፊት ያፈጣሉ:: እንደአይኖቿ የስሜት ጨረር እየተኮሱ የተባዕትን ልብ ያርዳሉ:: የወገቧ መቅጠንና የዳሌዋ መስፋት የብርሌ ቅርፅ ቢሰጣትም የባቶቿ ልኬታማ አፈጣጠር ደግሞ ተፋልመው የሚያገኙትን ዋንጫ ያስመስላታል:: በዚህ ላይ የዘውትር ባለትልል..ቅ ገደላማ-ሶል ‹ሂል› ጫማዎችና ድመትማ እርምጃዋ ‹ካት ዎክ› ተጨምሮበት ከፍ ዝቅ፣ ዝቅ ከፍ እያለ ዳሌዋ ሲተረማመስ እውነትም ወንዶች በሙሉ ተወዳድረው፤ በስተመጨረሻ አሸናፊው ጭምቅ አድርጎ የሚይዛት አጓጊ ዋንጫ ሆና ትታያለች::

... ዛሬም እንደወትሮዋ ገና ‹ፍሬሽ› ተማሪ እያለች በግል ወጪዋ ገዝታ ዶርም ባስገባችው የ21 ኢንች ቴሌቪዥን ስፋት ያለው መስታወቷ ፊት ቁጭ ብድግ እያለች እየተመሰጠች ነበር:: ይሄ መስታወት ለቢታኒያ ትልቅ ቦታ አለው:: በየቀኑ በሻምፖና ውሃ ትወለውለዋለች:: ጥግ ጥጉ ላይ የምትወዳቸውን የአሜሪካ ዘፋኞች ትናንሽ ፎቶዎች ለጣጥፋበታለች:: ከታች በግራ በኩል ጀስቲን ቢበርና ሪሃና ጎን ለጎን ተሰይመዋል፡ ከመስታወቱ የቀኝ ጠርዝ ደግሞ ክሪስ ብራውን አየር ላይ ሲንሳፈፍ የሚያሳይ ምስል አለ:: ማይሊ ሳይረስ፣ ቢዮንሴ እና ሌሎችም ዘፋኞች የመስታወቱን መሃል ትተው ተመሰቃቅለው ተለጣጥፈዋል::

ለቢታኒያ መስታወቱ ከመልክ መመልከቻም በላይ ነው፡ እንደግል ጣዖቷ ነው የምትንከባከበው! ሌሎቹ የዶርሙ አባላት በመስታወቱ እንዳይመለከቱ ለብዙ ጊዜ ብትከለክልም መጨቃጨቁ ስለሰለቻት አሁን ቢያዩበትም የሆዷን በሆዷ ይዛ በዝምታ ታሳልፋለች:: መስታወቱን ግን እንድች ብሎ በእጅ መንካት ቢታኒያ ላይ ጦርነት እንደማወጅ ተደርጎ ስለሚወሰድ ማንም አይዳፈርም::

የሆነ ቀን ፅዮን የአልጋዋን ቦታ ልትቀይር ብላ የቢታንያን መስታወት አንስታ ከሎከር ጀርባ አኖረችው:: የቢታንያን ለምሳ መውጣት ጠብቃ ነበር ይህን ያደረገችው:: ስልኳን ዶርም ረስታ በደቂቃዎች ውስጥ የተመለሰችው ቢታንያ ግን የመስታወቷን ከቦታው መነሳት ባየች ጊዜ ከፉኛ ቱግ አለች::

“ማነው መስታወቴን ከቦታው ያነሳው?” አለች ‹ለፀብ ዝግጁ ነኝ› በሚል ቅላፄ፤ ዶርሙ ውስጥ የነበሩት መርየምና ቦንቱ እኩል ፊታቸውን ወደ ፅዮን አዞሩ:: ፅዮንም አልጋዋን መግፋት አቁማ፣ በድንጋጤ ቆማ የቢታንያን አይን አይን እያየች፤“እኔ ነኝ ቢታን...” አለች የጭንቀት ፈገግታን እየፈገገች፤

ቢታኒያ በንዴት ቀይ'ይ ሆና ፀሐይ ላይ የተሰጣ ፈረንጅ መሰለች:: ወደ ፅዮን ራመድ ራመድ ብላ ቆመች፤ ፅዮን በት/ት ደረጃም ይሁን በእድሜ ቢታንያን የምትበልጣት ቢሆንም በቁመትና በድፍረት ግን ቢታንያ ትበልጣታለችና አጠገቧ ቆማ ቁልቁል አይኖቿን አጉረጠረጠችባት:: አንዳንዴ ከዚህ አይነቱ ነፍስን አስጨናቂ አስተያየት ቡጢ ይሻላል... ፅዮን ድመት አባሯት የምትገባበት ጉድጓድ ያጣች አይጥን መሰለች::

ቢታንያ በቁጣ መንተክተክ ጀምራለች፣ “መስታወቴስ አንቺ መናጢ?” አለች፤ ጉሮሮዋ ደርቋል፣ ጠቧል... ድምጿ ቀጥኗል::

“ያ... ያ... ያውና” አለች ፅዮን፤ ከመንተባተቧ እኩል ጣቶቿን አርበትብታ ወደ ሎከሩ ጀርባ እየጠቆመች::

ቢታንያ ጥድፍ ጥድፍ ብላ መስታወቷን አንስታ፤ ምንም አይነት ጉዳት እንዳልደረሰበት አረጋግጣ፤ በቀድሞው ቦታው ካስቀመጠች በኋላ ወደ ፅዮን ተመለሰች::

“ትሰሚያለሽ?... የዚህ መስታወት ዋጋ እነዚህን የቻይና ጫማዎችሽን በሙሉ ጠቅልሎ እንደሚገዛ ታውቂያለሽ?”

“ይቅርታ ቢታን... አልጋዬን ሳስተካክል እንዳይሰበር ፈርቼ እኮ ነው”

“ብትሰብሪው ኖሮማ አሳይሽ ነበራ!”... ከንግግሯ እኩል አስፈራርታ፣ ሞባይሏን ብድግ አድርጋ እየተመናቀረች ወጣች:: መርየም፣ ቦንቱና ፅዮን እርስበርሳቸው ተያዩ:: አንዳቸውም ቃል ትንፍሽ ባይሉም ሳይነጋገሩ ተግባብተዋል:: ከዚያች ቀን በኋላ ግን የቢታንያን መስታወት የነካች አንዲትም የዶርሙ አባል አልነበረችም::

*** ፶ – ፶ ***

"ሜሩዬ፤ ዛሬ ከዛ ከነገርኩሽ ልጅ ጋር ቀጠሮ አለኝ!" አለች ቢታንያ፣ ከመስታወቷ ፊት ቆማ፤ ተጠማዛ ሸንጧን እያየች::

"ከማን?… ከዚያ ‹ኢንጅነሪንግ ተማሪ ነው› ካልሽኝ ልጅ ጋር ነው?"

"አዎዋ… ደሞ ‹ጂሲ› እኮ ነው!"

"እና ቢሆንሳ?"

"እንዴ መላ ይኖረዋላ… ተመራቂ ተማሪ ብር በገፍ እንደሚላከለት አታውቂም?"

"እስኪ አላህ ያድርግልሽ::" አለች መርየም በቸልተኝነት፣

"ታያለሽ ዛሬማ ከባድ እራት ካልጋበዘኝ… ወይኔ ሽከላ ጥብስ ቢያበላኝ… ወይ ደ'ሞ… እ… ስፔሻል በርገር… ወይ ፒዛ… በዚያ ላይ ደግሞ ተኪላ ወይ አማሩላ ቢከለስበት… ዋው!" ቢታኒያ ምላሷን አጣጥፋ፣ ምራቋን አጣፍጣ ዋጠች::

"ምኗን ሳታውቅ እጇን ታጠበች' አሉ…" ብላ መርየም መሳቅ ስትጀምር፣ ቢታንያ እንደመናደድ እየቃጣት "እሱን በኋላ እነግርሻለሁኝ!" ብላ ተመናቅራ ወጣች::

… ቢታንያ ተመልሳ የመጣችው ማታ 3 ሰዓት ገደማ ነበር:: መርየም አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ እያነበበች፤ ሃኒ ሌሊት ለመ·ነት የስልክ ማንቂያዋን ሞልታ ተኝታ፤ በአንድ አመት የምትበልጣቸው ቦንቱ ደግሞ የጆሮ ማዳመጫ አድርጋ ዘፈን እየሰማች፤ በጠረጴዛዋ ላይ እያነበበች ነበር የጠበቋት:: ገና ከመግባቷ በሩን ከኋላዋ አሽቀንጥራ ዘጋችና አልጋዋ ላይ በቁሟ ወደቀችበት፣

"ችጋራም፣ የችጋራም ልጅ…" አጉተመተመች::

መርየም አፏን በትራሷ ሸፍና በሳቅ ተንሰቀሰቀች:: በሆዷ 'ሙብላቷን ሳታውቅ እጇን ታጠበች' ያልኩት እውን ሆነ እያለች ተንከተከተች:: አፍናው ግን አልቀረችም ሳቋ ከትራሷ አምልጦ ወጣ…

"ኤጭ አንቺ ደግሞ ምን ያስገለፍጥሻል?" አለች ቢታንያ በምሬት ድምፅ::

"አይ ወላሂ ላናድሽ አስቤ አይደለም:: ብቻ ቅድም ስትሔጂ የነበረሽ ጉጉት ትዝ ብሎኝ ነው የሳቅኩት… እና በርገሩ እንዴት ነበር በአላህ?" አለች መርየም በሰፊው ፈገግ እያለች:: መርየም ስትስቅ የረመዳን 28ኛውን ምሽት ጨረቃ ትመስላለች:: በጥቁሩ ሂጃቧ ተከቦ የሚያበራው ፍም፣ ክብ ፊቷ በነጫጭ፣ ትልልቅ የአይን ብሌኖቿና ሀጫጭ በረዶ ጥርሶቿ ሲታጀብ በሌሊት ውስጥ ንጋት ልፍጠር የምትል ጨረቃን ውበት ያላብሳታል::

"አሂሂሂ… ተይኝ እስኪ!" አለች ቢታንያ ሆዷን እያሸች::

“ምነው?” አለች መርየም፤ አሁንም ያ ውብ ሳቋ ቀጥሏል፡፡
“ባከሽ አንድ በያይነት ለሁለት ነው የበላነው… እንዴት እንደተናደድኩኝ አትጠይቂኝ፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ አስሬ ብዱ እያለ ነፍሴን አወጣት እንጂ”
“ተኪላስ አልጠጣችሁም?”
“አውቀሽ ነው አይደል ሜሩ ‹ሙድ› ምትይዝብኝ?… በያይነት አዞ ለመከፈል የተንቀጠቀጠ ልጅ ጭራሽ መጠጥ አዝዤ ራሱን ቢያጠፋ ማን ተጣያቂ ሊሆን ነው?”… ሁለቱም ሳቁ፤
“እና ግን እንዴት ነበር ምሽቱ?… ልጁስ ጥሩ ልጅ ነው?” ጠየቀች መርየም ሳቋን ገታ አድርጋ፤
“ኧረ በፈጠረሽ በቅጡ እንኳን አላዋራሁትም፡፡ ምግቡንም ሳልጨርስ በቃኝ ብዬው ቶሎ ነው ወደ ዶርም የመጣሁት፡፡ ውይ! እስክለየው ነው የጨነቀኝ!”
“ለምን ወሬው ደስ አይልም ነበር?”
“ቂቂቂ… በናትሽ አታስቂኝ… ሆዴ በቅጡ ሳይሞላ የ'ሱን ወሬ ልስማ? ለነገሩ አንቺ ስለ ወንድና ሪሌሽን ምን ታውቂና?” … ቢታንያ በረጅሙ ተነፈሰች፡፡
“አይ ያንቺ ነገር!” አለችና መርየም ወደ ንባቧ ተመለሰች፡፡
“ምን እያጠናሽ ነው?” አለች ቢታንያ፤ ጫማዋን አውልቃ ከአልጋዋ ጋደም እያለች፡፡… “ነገ እኮ ‹ፋርማኮሎጂ ኤግዛም› አለ… አላወቅሽም?”

“እንዴ! ነገ ነው እንዴ ፈተናው በናትሽ!?” ቢታንያ ተደናገጠች፡፡ ከአልጋዋ ተስፈንጥራ ተነሳችና ላፕቶፕ ከፍታ ጥናቱን መታገል ጀመረች፡፡

መርየም ያነበበችውን በእርጋታ እየከለሰች፤ ቢታንያ በውጥረት እንዳዲስ እያነበበች 3 ሰዓትታ ያክል እንዳጠኑ የዶርሙን በር ገርበብ አድርጋ ፅዮን ገባች፡፡ ፅዮን ከቦንቱ በአንድ አመት፤ ከመርየምና ቢታንያ ደግሞ በሁለት ዓመት የምትበልጥ የህክምና ተማሪ ናት፡፡ ቦንቱ አየቻትና “አንቺ ልጅ በሌሊት እዚህ ግቢ ውስጥ ስትዞሪ ደቼዋ እንዳታገኝሽ” አለች፣ የጀሮ ማዳመጫዋን አውልቃ እየተንጠራራች፡፡ “‹ሎው ላይብረሪ› ነበርኩኝ፡፡” አለች ፅዮን አንገቷን እንደ ደፋች፤

“እሱማ መቼ ጠፋን፣ ግን ካልጠፋ ላይብረሪ እላይ ‹ሎው ላይብረሪ› ድረስ መሄድሽ ነው እኮ የሚገርመን… ወይስ እዛ የጠበስሽው ሰው አለ?” አለችና ሳቀች ቢታንያ፤ የፅዮን ፊት በሃፍረት ተሞላ፡፡ ፅዮን እንደዚህ አይነት ነገር የማታውቅ ልጅ ናት፡፡ እውነታው እንዲያውም የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ ከሌሎቹ ይልቅ የህግ ተማሪዎችን ቤተ-መፅሐፍት (ሎው ላይብረሪን) የመረጠችው

ብዙ ተማሪ በተለይም የግቢው ወንድ ተማሪዎች ስለማያዘወትሩት ነው:: እያነበበች የሚያዋራት ቀርቶ ከምታነብበት ጠረጴዛ በሩቁ ተቀምጦ የሚያያት ወንድ እንኳን ውስጧን በጭንቀት ይሞላዋል::

"ግን ይህቺ ደቼ የምትባለው መንፈስ የእውነት ነች እንዴ?" አለች ሃና እንደቀልድ አድርጋ::
"እንዴ በደንብ እንጂ... ባለፈው ባይገርማችሁ አንዷን ‹ባይሎጂ› ተማሪ ባዶ ‹ስፔስ› ውስጥ ስታነብ ስሟን ጠርታ አናግራት ልጅቷ ሦስት ቀን ሙሉ እየተንቀጠቀጠች ትርጉም የሌላቸው ቃላትን ስትዘባርቅ ነበር" ... ቦንቱ ለቃላቶቹ ሞቅታ እየጨመረች ነበር ያወራችላቸው::

"በእናታችሁ ዝም በሉ እኔ እፈራለሁኝ!" አለች ፅዮን ይዛ የመጣቻቸውን ደብተሮች ከሎከሯ እየከተተች:: "መፍራትማ ሃቅሽ ነው... ቂ..ቂ..ቂ.." ቢታንያ ተስረቀረቀች፤ ወደ ቦንቱም ዞራ፤ "እቦ ባከሽ ቦኒዬ ቀጥዪ... እና ይህቺ ደቼ ተብዬ ከየት ነው የመጣችው?" አለቻት::

ቦንቱ ህፃናትን ሰብስባ የሚያስፈራ ተረት እንደምትነግር አሮጊት ሴትዮ ድምጿን ዝግ አድርጋ ቀጠለች... "እዚህ ግቢ ውስጥ ከ20 ዓመታት በላይ በጥበቃ ካገለገሉት ጋሽ ዲኖ እንደሰማሁት ከሆነ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ከተቋቋመ ከጥቂት አመታት በኋላ ነበር አንዲት ዳቼላ የምትባል ልጅ ግቢውን የተቀላቀለችው:: የመጣችው ራቅ ካለ አካባቢ ሲሆን የምትማረው ደግሞ ‹ሳይኮሎጂ ፊልድ› ነበር:: ከቁመቷ በጣም መርዘምና የቆዳዋ ከሰል የመሰለ ጥቁረት ምክንያት አብረዋት በአንድ ዶርም የተመደቡት ሴት ተማሪዎች ይፈሯት፣ ይጠየፏትና ያንጓጥጧት ነበር:: ከእነርሱ በመልከና አቋም ለየት ብላ በመታየቷ ብቻ ከማግለል አልፈው ሴቶቹ ስሟን እያጠፉ ይዘባበቱባት ነበር:: እሷም እያዘነች ለብቻዋ ጨለማ ቦታዎች ውስጥ ሆና ታለቅስ ነበር፤"

ቦንቱ በዚያን ጊዜ ኖራ ሀዘኗን የተመለከተች ያህል ፊቷ ጭፍግግ ብሏል::

"ታድያ ዳቼላ መገለሉና የሴቱ ሃሜት የፈጠረባት ሃዘኗ ተጠራቅሞ ብስጭትና የበቀል ስሜትን ወለደ:: ወደ መጣችበት ስትመለስም በአካባቢዋ የሚገኝ ኃይለኛ ጠንቅ-አዋይ ዘንድ ሄዳ ሴቶቹን እንዲበቀልላት ተለማመነችው:: ጠንቅ-አዋዩም የፈለገችውን ፈፀመላት:: ዋና ዋና ያናደዷትንና ስሟን ያጠፉ የነበሩ ሴቶች እንዲያብዱና ካለማቋረጥ እንዲለፈልፉ አደረገላት:: ይህንን አድርጋ ስታበቃ በሰላም ት/ቷን ምትከታተል መስሏት ወደ ትምህርቷ ተመለሰች:: ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስትመለስ ግን ያበዱት ሴቶች "ዳቼላ አሳበደችን" እያሉ ይለፈልፉ ኖሮ

የግቢው ተማሪ በሙሉ ጠላት:: እሷ ክፍል ልትማር ስትገባ ሌላው ተማሪ ጥሎ እስከመውጣት ድረስ አገለላት:: በስተመጨረሻም በብቸኝነት ውስጥ ትሰቃይ የነበረችው ዳቼላ ሎው ላይብረሪ አካባቢ ከነበረ ፎቅ ላይ ወጥታ፤ ያገለሏትን በሙሉ ተራግማ፤ ቁልቁል ተምዘግዝጋ ወድቃ ሞተች::"… ብላ ቦንቱ አፈ-ታሪኳን ስታገባድድ የዶርሙ አባላት በሙሉ ተመስጠው እያዳመጡ ነበር::

"የሚገርመው ግን!" አለች፤ ቦንቱ ለትረካዋ አዲስ ሓይል እየደረበች "የሚገርመው ግን ዳቼላ ከሞተች ከሳምንታት በኋላ ብቻቸውን ስፔስ፣ ላይብረሪና ግቢው ሰዋራ ስፍራዎች ላይ የሚገኙ ሴቶችን በስማቸው እየጠራች፤ 'አቤት' ብለው የሄዱትንም "ቆንጆ ነኝ ወይ?" ብላ ጠይቃ የምታስጨንቅ፣ ዝም ካሉም በጥፊ የምታጠናግር አንዲት ረጅም ጥቁር ሴት በተደጋጋሚ መታየት ጀመረች:: የዳቼላን ታሪክ በቅርብ ያውቁ የነበሩ አንዳንድ ተማሪዎችም "ይህ የሷ የሙት መንፈስ ለበቀል መጥቶ ነው!" በማለት መንፈሷን "ዳቼላ" ሲሉ ስም ሰጧት:: በአመታት ሂደት ውስጥም «ደቼ» ለብዙ ሴቶች እንደተገለፀችና ጥቂት የማይባሉትንም እንደለከፈች ጋሽ ዲኖ ምለው ነግረውኛል::" አለች ቦንቱ ትረካዋን ስታገባድድ:: ሁሉም እየፈሩ ትረካዋን ቢያዳምጡም ከፍተኛው የፍርሃት ገፅታ የሚነበበው ግን ከፅዮን ፊት ላይ ነበር::

*** ፉ – ፉ ***

በማግስቱ እኩለ ሌሊት አካባቢ ፅዮን የምታነባቸውን ‹ሃንድ-አውቶች› *(አስተማሪ ለተማሪዎች የሚሰጣቸው የፅሁፍ ጥራዞች)* ሰበሰበችና ከህግ ተማሪዎች ቤተ-መፅሐፍት ወጣች:: ካፌ አተር ከኳን በልታ፤ ቤተ-ክርስቲያን ተሳልማ፤ ምሽት 2 ሰዓት ገደማ ነበር ቤተ-መፅሐፍት የገባችው::

ከቤተ-መፅሐፍቱ ወጥታ ለብቻዋ ወደ ዶርም ስትሄድ ትናንት ቦንቱ የነገረቻት የደቼ ታሪክ ትውስታ ላይ በጅማ ዩንቨርሲቲ ግቢ ውስጥ የሰፈነው ፀጥታና ጨለማ ተጨምሮበት ልቧ በፍርሃት እየራደ ነበር::

›››ያኔ ባይታወቃትም… ባይገለፅላትም… ይህቺ ምስኪን ነፍስ፤ ደብተርና ‹ሃንዳውቶቿን› ከደረቷ ልጥፍ አድርጋ ድክ ድክ እያለች ስትሄድ ጨረቃ ቁልቁል እያየቻት ትመሰጣለች:: ከፊደል ለቀማ የመጣች የእውቀት ቃራሚ ወፍ ጋር እያመሳሰሏት ኮከቦች ያበሩላታል:: ከህይወት የጭለማ ሸለቆ ውስጥ በሚደረግ ጉዞ ላይ መልዓክት ብርሃን ይፈነጥቁላታል:: በአጀባ፣ ካለችግር ዶርሟ ትደርስ ነበር::

*** ☥ – ☥ ***

…2010 ከ.ክ.ል.በኋላ/ኢ.ኢ.አ

ጥር ወር፣ ዕለተ ሰኞ → ጨለማ ዱር…

አኩለ ሌሊት… ፅዮን ከድቅድቁ ጨለማ ጋር ተፋጣለች፤ የት እንዳለች አታውቅም፤ እንዴት እዚህ እንደመጣችም አታውቅም። ከጥግ እስከ ጥግ የተዘረጋ ፅልመት፣ ፀጥ ረጭ ያለ ሌሊት ውስጥ ብቻዋን ነች! የገዛ እስትንፋሷ ከጆሮ ግንዷ ስር እንደሚነፋ ጥሩንባ ይሬጮኽባታል። ከአንታርክቲክ የበረዶ ግግር የቀዘቀዘው ንፋስ እያፏጨ መጥቶ ጉንጮቿን ይላተማል።

ከቁጥጥሯ ውጪ በሆነ ሃይል እንደተለጎመች፤

እየሆነ ያለው ሁሉ ቅዠት ሆኖባት ደንዝዛ ቆማለች፤

እንዴትና ለምን እዚህ ተገኘች?

አዕምሮዋ ከሷ ትዕዛዝ ውጪ ለምን ሆነ?

የትኛው የህይወቷ እርምጃ ነው እዚህ ያደረሳት?

ፅዮን አስተሳሰቧን ከጋረዳት ነገር ጀርባ ባለው ማንነቷ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ትጥራለች። በየመሐሉ ደግሞ የእናቷ በፍቅር የተሞላ ገጽታ፤ የልጅነት ፍካት ንፁህ ፈገግታዋ፤ የኢትኤል ጨዋታ ከፊቷ ድቅን ይልባታል።

«ይህ ሁሉ እንዴት ሆነ?» ልትፈታው ያልቻለችው ሚስጥራዊ ጥያቄ ነፍሷን ወጥሮ ይዞታል።

*** ☥ – ☥ ***

*** ፉ – ፉ ***

*“እንዲገለጥ ባይሆን የተሰወረ የለምና፤ ወደ ገሃድ እንዲመጣ እንጂ የተሸሸገም የለም።”...... (የማርቆስ ወንጌል - ምዕ.4፡22)*

*** ፉ – ፉ ***

# ♣ ምዕራፍ ፪ - ፅዮን ♣

*(ቀጨኔ፤ 1987 ዓ.ም/ አ.አ.እ)*

በቀይ ጭቃ ጠፍጠፍ... ጠፍጠፍ ተደርጋ የተሰራች፤ በመጠን ከሻይ ብርጭቆ የምትቀራረብ፣ ሚጢጢ ጀበና ከመሃል ተሰይማለች፤ በዙሪያዋ 6 ቆርኪዎች አፋቸውን ከፍተው ተደርድረዋል:: አንዲት ፊቷ ላይ ሰላም ብቻ የሚነበብባት፣ ባለዛጎልማ ጥቁር ቆዳ፣ በሎቄ የሚመስሉ አይኖች ያሏት ህፃን በሚገርም ኩስትሪያ ሚጢጢውን ጀበና ብድግ አድርጋ በአፈር የደፈረሰ ውሃ በጥንቃቄ ቀዳች:: በዙሪያዋ ከበው ቁጭ ያሉት 5 ህፃናት እየተቁነጠነጡ 'ቡናቸውን' እየጠበቁ ነበር።

ሙልት አድርጋ እየቀዳች... የየድርሻቸውን ቆርኪ ስትሰጣቸው አጅ እየነሱ ተቀበሉ:: መዕዛው እንደሚያውድ፣ ቃናው እንደሚጣፍጥ ልዩ የሐረር ቡና ቆሻሻውን ውሃ ፉት እያሉ ማጣጣሙን ተያያዙት::

የእቃቃ ቡናው ዋና አዘጋጅና አቅራቢ፣ ፊቷ ላይ ሰላም ብቻ የሚነበብባት፣ ባለዛጎልማ ጥቁር ቆዳ፣ በሎቄ የሚመስሉ አይኖች ያሏት ህፃን ‹ፅዮን› ትባላለች::

የቆርኪው ቡና በመጀመሪያ የተሰጠው፣ ከፅዮን በአንድ ዓመት የሚያንስ፣ ካሉት ልጆች መካከል በትንሽዬ አዲዳስና ካኪ ልብስ ዘንጦ የሚታየው ኢትኤል ሲሆን፤ በቀጨኔ ሰፈር አሉ ከሚባሉት ሃብታሞች መካከል ዋነኛው የሆኑት የአቶ ሳአልና ወ/ሮ እመቤት አንጋፋ ልጅ ነው:: ከእድሜ እኩዮቹ ለየት ባለ መልኩ አዳዲስ ልብሶች ስለሚለብስና ውድ ውድ መጫወቻዎች ስለሚገዛለት የሰፈሩ ህፃናት በሙሉ ይቀኑበታል፤ ሁሌም ከሱ ጋር ለመጫወት ይጓጓሉ:: የኢትኤል ቤተሰቦች ግን አንድም ልጅ ግቢያቸው

እንዲገባ አይፈቅዱም፡፡ እሱንም ከልጆች ጋር ተቀላቅሎ እንዳይጫወት ቢከለክሉትም ተደብቆ እየወጣ ሲጫወት ይውላል፡፡ በተለይ ደግሞ ከጎረቤቱ ልጅ ፅዮን ጋር በጣም የሚዋደዱ ጓደኛሞች ስለሆኑ ተደብቆ፣ እሷ ጋር እየመጣ መዋልን የሁልጊዜ ልማዱ አድርጎታል፡፡

ኢትኤል... ወርቅ የመሰለ የቀይ-ዳማ ቆዳ፣ ጥቁር ሉጫ ፀጉርና ድንቡሽዬ ሰውነት ያለው፤ ላየው የሚያሳሳ ልጅ ነው፡፡ እንደወትሮው ሁሉ ዛሬመወ ፅድት ያለ ልብስና አዲዳስ ጫማ ገድግዶ፣ ተውቦ ነበር ለቡና ስነ-ስርዓቱ የተገኘው፡፡ ከጎኑ ሌላ የቆርኪ ቡናውን የሚያጣጥመው ጩጩዎ ደግሞ ዋሲሁን ይባላል፤ ጓደኞቹ ግን ዋሴ እያሉ ነው የሚጠሩት፡፡ በተቀቀለ ቶፓዝ ምላጭ ሙልጭ ተደርጎ የተላጨው ጭንቅላቱ በዜኒት ቅባት ተወልውሎ፤ ፀሐይ እንዳንፀባረቀ ስፖኪዮ ያብለጨልጫል፡፡ በግንባሩና አናቱ መሃል በጥበበኛ ወ/ሮ የተቀረፀው ቁንጮው ደግሞ ገብስማ አውራ ዶሮ አስመስሎታል፡፡ በመላጣው ላይ እዚህም እዚያም የመፈንከትና የመውደቅ ጠባሳዎች ይታያሉ፡፡ ለፀብና ፍንከቻ ቋሚ ተሰላፊ መሆኑ ከእነዚህ ጠባሶች ባሻገር በሌሎች ልጆች የሚፈራ እንዲሆንም አድርጎታል፤ ቢጫ የተበጫጨቀች ሹራብና አሮጌ ጥብቆ ለብሷል፡፡

ሌሎቹ የቡናው ስነ-ስርዓት ላይ የታደሙት ልጆች ደግሞ አልቃሻዋ ጩኒ፣ ዝምተኛው ዳኒና ሁሌም ካፍንጫው ንፍጥ የማይለየውና ከማውራት ይልቅ "ኡሁ.. ኡሁ.. ኡሁ.." እያለ ማሳል የሚያበዛው ቀኬያሙ ስኢዶ ናቸው፡፡

የቡናው ስነ-ስርዓት ካበቃ በኋላ ፅዮን ቆርኪዎቿንና ሚጢጢ ጀበናዋን ሰብስባ በጥንቃቄ ወደቤት አስገባቻቸው፡፡ ከቤቷ ተመለሳ ስትወጣ ሁሉም ልጆች አባሮሽ ለመጫወት ተስማምተው አቦ-ሰንበቴ ሲጥሉ ነበር የደረሰችው፡፡

"ፅዮን! ቶሎ ነይ አቦስም አትጫወቺም?" አለ ኢትኤል በጉጉት፤ ...ትርር ብላ ሮጣ ተቀላቀለች፡፡ ሁሉም ልጆች ትከሻ ለትከሻ ገጥመው፣ ክብ ሰርተው ቆሙ፡፡ ሁለቱ አባራሪዎች እና አራቱ ተባራሪዎች መለየት ነበረባቸው፡፡ ስድስቱም ቀኝ እጃቸውን ከጀርባቸው ደበቁ... "አ...ቦ... ሰንበቴ!" ብለውም እኩል መዳፎቻቸውን ወደመሃል ዘረጉ፡፡ አራት አይበሉባዎች እና ሁለት የውስጥ መዳፎች ታዩ፤ የፅዮንና ኢትኤል እጆች ነበሩ፡፡ ከአባራሪነት

ሃላፊነት ነፃ ወጥተው ተባራሪነታቸውን አረጋገጡ። ቀጥሎ በተደረገው አቦሰንበቴ ደግሞ አልቃሻዋ ጩኒም ነጻ ወጥታ ከነፅዮን የተባራሪ ቡድን ጋር ተቀላቀለች። አሁን ጉልቤው ዋሴ፣ ጉንፋናሙ ሰኢዶና ዝምተኛው ዳኒ ለመጨረሻው አቦሰም ተፋጠዋል። ከሦስቱ አንዱ ብቻ ራሱን እልህ ከሚያስጨርሰው አባራሪነት ሊያገል ይገባዋል፣ ሁሉም ያን ሰው ለመሆን አሰፍስፈዋል።

ሦስቱም ፊት ለፊት ተፋጠው ቆሙ። የጥንቱ የ‹ቴከሳስ› የሸጉጥ መዘዛ ፍልሚያን ይመስል የሁሉም እጆች ከጀርባቸው ተንቀጠቀጡ። ከባድ መፋጠጥና ውጥረት ሰፈነ። ሰኢዶ፣ ዋሴ ወይስ ዳኒ?

"አ… ቦ… ሰንበቴ!"… ሶስት መዳፎች ተዘረጉ፤ አንዲት ጥቁር አይበሉባ በሁለት ነጭ የውስጥ መዳፎች ታጅባ ደመቀች። ዳኒ በደስታ ዘለለ፣ ዋሴ በንዴት የዘረጋውን መዳፉን ቡጢ አስጨብጦ የሚማታ መሰለ፤ ሰኢዶ ከፍተኛ የሆነ ሳል ያጣድፈው ገባ። "ይሄማ አይቻልም!"… ጉልቤው ዋሴ እጆቹን እያወናጨፈ ተቃወመ፤

"ለ… ለምን?" ጠየቀ ዳኒ፤ የፊቱ ላይ ገፅታ ከደስታ ወደ ፍርሃት እየተለወጠ፤
"እኛ ከጣልን በኋላ ጠብቀህ ነው እጅህን የጣልከው!"… ዋሴ ቀወጠው፤
"ኧረ… ዋሴ አታፋፍር! እኩል አይደል እንዴ የጣልኩት?!" አለ ዳኒ ፈራ ተባ እያለ፤
"በቃ አሁን ና!… እና በድጋሚ እንጣል፤" …ዋሴ ቀጭን ትዕዛዝ ሰጠ!
"እም…ቢ"… የፈሪ ተቃውሞ ከዳኒ ተሰማ፤
"አንተ እናትንና ከኔ ጋር መሳፈጥ ጀመርክ እንዴ?!" እያለ ዋሴ ከመሬት ምን የሚያህል ድንጋይ ብድግ አድርጎ ወደ ዳኒ ተጠጋ። ዳኒ ፊቱን በእጆቹ ከልሎ ወደኋላው አፈገፈገ። ኢትኤል እየሮጠ መጥቶ ዋሴን ለማቆም መሃላቸው ገባ። ሰኢዶ ከኋላ ቆሞ በተለያዩ ስልቶች ያስላል። ዳሩ ኢትኤል ባይደርስለት ኖሮ እርግጥም ዳኒ የሚፈነከትባት ቀኑ ዛሬ ነበረች።

ዳንኤል ካለፍላጎቱ፤ እያለቃቀሰ ለድጋሚው አቦሰም ከዋሴና ሰኢዶ ጋር ተሰለፈ። ድጋሚ የዕድል እጆች ተዘረጉ። አሁንም ግን "የእውነት አምላክ ለእውነታኛው ሰው ይፈርዳል!" እንዲሉ ተለይታ የወጣቸው የእሱ እጅ ነበረች። ዋሴ ባይዋጥለትም ለሁለተኛ ጊዜ የእድሉን መጥመም እያማረረ ከጉንፋናሙ ሰኢዶ ጋር አባራሪ ሆኖ ለመጫወት ተስማማ።

ፅዮን፣ ኢትኤል፣ ጬኒና ዳኒ ዘርዘር ብለው ቆመው ለሰዶ ማሳደዱ ተሰናዱ:: ዋሴ ተስፈንጥሮ ወደ ዳኒ ገሰገሰ:: ዳኒ ነብር እንዳየ ሚዳቆ ፈረጠጠ:: እርግጥም የዋሴ አመጣጥ ይዞ የአቦሰም እስረኛ ሊያረገው ሳይሆን ሊደበድበው ነው የሚመስለው፤ በእልህ እየተገፋ ከኋላ አሳደደው…

የዳኒና ዋሴን አባሮሽ አፏን ከፍታ ስታይ የነበረችው ጬኒ ወደራሷ የተመለሰችው ሰኢዶ ሳሉን ዋጥ አድርጎ መጥቶ ከኋላዋ ጋማዋን ሲይዛት ነበር:: ከመታሰር ሌላ አማራጭ አልነበራትም:: ሰኢዶ ጬኒን አስሮ እየሮጠ ሲመጣባቸው ፅዮንና ኢትኤል በተለያየ አቅጣጫ ሮጡበት:: ሰኢዶም ፅዮንን ትቶ ኢትኤልን ያባርረው ገባ:: ግና ትኪ..ትኪ.. የሚያስብለው ሳሉ ተነስቶ ትንፋሹን እያሳጠረበት ደርሶ ሊይዘው አልቻለም ነበር:: በሌላ በኩል ዋሴ ቁንጮው እስኪነቃቀል ድረስ ጥርሱን ነክሶ ሮጦ፤ እንደተመኘው ዳኒን ይዞ፤ የግራጫ ሸሚዙን ኮሌታ ጨምድዶ፣ እንደሚታረድ ዶሮ አንጠልጥሎ አምጥቶ አሰረውና ኢትኤልን መያዝ ያቃተውን ሰኢዶን ለማገዝ ሄደ:: ጬኒና ዳኒ ጎን ለጎን ተያይዘው ቆሙና ነፃ የሆኑት እጆቻቸውን ውጥር አድርገው ዘርግተው የሚስፈታቸውን ልጅ በጉጉት ይጠብቁ ጀመር::

ሰኢዶና ዋሴ እሷን ትተው ኢትኤልን እያባረሩ እንደሆነ ያየችው ፅዮን ጬኒና ዳኒን ለማስፈታት ቀስ ብላ ተጠጋች:: የጬኒን የተዘረጋ የእጅ መዳፍ ተንጠራርታ ለመንካት ከጫፍ ደርሳ ሳለች ግን ዋሴ አይቷት ኖሮ፤ ከየት መጣ ሳይባል ደርሶ እጇን ለቀም አድርጎ ያዘው፤ ሳታስበው ነበር የደረሰባት:: እሷንም ወስዶ ከነጬኒ ጋር ሰልሶ አሰራት:: “አንቺም ከተያዝሽማ በቃ ተሸንፍን ማለት ነው::” አለች ጬኒ በማለቃቀስ… “ኧረ አልተሸነፍንም! ግና እኮ ኢትኤል አለ… እሱ ያስፈታናል!” አለች ፅዮን በእርጋታ፤ እንደምትፈታ እርግጠኝነቷ ልክ የዋስ መብቷ እንደተጠበቀላት እስረኛ ነበር::
“ባክሽ አያስፈታንም!” መለሰች ጬኒ ተስፋ በቆረጠ ሰው ለዛ፤ “እነርሱ እኮ ሁለት ናቸው… እሱ ብቻውን ነው::”አለች…ለማልቀስ እየዳዳት ነበር::
ፅዮን “እምኘኝ ያስፈታናል::” አለችና “ኢትኤል አስፈታን!” ብላ ጮኸች፤ ትንፋሽ ያጠረውን ሰኢዶ ከወዲያ ወዲህ እያንገላታ ሲደስት የነበረው ኢትኤል ድምጿን ሰምቶ ዞረ:: ከሁሉም በተለየ ደግሞ የፅዮንን መታሰር አየና ደነገጠ::

ዋሴ በበኩሉ ለፍቶ የያዛቸው እስረኞቹ እንዳይፈቱ ሰግቷል:: እናም ሰኢዶን ጠርቶ ሦስቱን እስረኞች እንዲጠብቅ ቀጭን ትዕዛዝ ሰጠው:: እሱ ደግሞ ባለ በሌለ ሐይሉ ኢትኤልን አባሮ ለመያዝ ተንደረደረ:: … ኢትኤል በበኩሉ በሩጫ ዋሴ እንደሚቀድመው ያውቃል:: ከዚህ በፊት አሽቅድድም ሲጫወቱ በተደጋጋሚ አሸንፎታል:: ስለዚህም ዋሴ ወደ'ሱ ጋር እየተንደረደረ ሲመጣ ሸሽቶ ከመሮጥ ይልቅ ቆሞ ጠበቀው:: ልክ አጠገቡ ሲደርስ ወደግራ የሚሮጥ አስመስሎ ዞረበት:: ዋሴ አገኘው ብሎ ሲመነጠቅ ግራ ቀኝ ብሎ አሸማቀቀው:: ዋሴም ፊጥኖ የመጣበትን አቅጣጫ በቅፅበት ሊቀይር ሲሞክር ሚዛኑን ሳተና ወደቀ:: ኢትኤል በመግነጢሳዊ ሽምጠጣ ወደነፅዮን ሮጠ::

ቀና ብሎ ሲያይ የጥበቃ አደራ የተሰጠው ሰኢዶ እጆቹን እንደ አሞራ ዘርግቶ ይጠብቀዋል፡፤ ከእሱ ጀርባ ደግሞ ሦስቱም ታሳሪዎች እጆቻቸውን ውጥር አድርገው ዘርግተው ለመፈታት ተዘጋጅተዋል:: ፅዮንን አያት፣ ፊቷ ላይ ደስታ፣ ጉጉት፣ ፍርሃትና ጭንቀት ተደበላልቀው ይነበባሉ:: በማይክሮ ሰኮንዶች ውስጥ ሰኢዶን እንዴት ሊያልፍ እንደሚችል ማጤን ነበረበት:: ሰኢዶ በቁመት ይበልጠዋል፤ በዚያ ላይ እጆቹን ሽቅብ ከፍ አድርጎ ነው እየጠበቀው ያለው፡ ኢትኤል እየሮጠ በመጣበት ፍጥነት፣ ካለምንም ማወላወል በሰኢዶ ግራ እጅ ስር ወደኋላው ተለጥጦ፣ በጉልበቶቹ መሬቱን እየታከከ ተንሸራተተ:: ጉልበቶቹ መሬቱን እንደያዙ ከስሩ አለፈ:: በዝቅታውና ፍጥነቱ ምክንያት ሰኢዶ ሊይዘው አልቻለም ነበር:: ኢትኤል ተንገዳግዶ ቆመና በጉጉት ትጠብቀው የነበረችውን ፅዮን መዳፍ ቶብ አደረገው:: ሁሉም ተፈቱ፤ ነፃ ወጡ! በሩጫ ተበተኑ:: ዋሴ ጭንቅላቱን በንዴት ይዞ ከአፈሩ ላይ ተቀመጠ፤ የሰኢዶ ሳል በረታ::

… የተፈታችው… ሰንሰለት ያላሰራት ፅዮን በነፃነት በታጀበ አባሮሽ ጨዋታዋ እየቦረቀች ነበር፤ እናቷ ጠርታ ወደ ቤት እስከታስገባት ድረስ::

*** ፉ – ፉ ***

ካዘመመ የጭቃ ቤት፣ አንዲት ኮስማና አሮጊት “ፅዮን… ፅዮን…” እያሉ እየተጣሩ ወጡ፡፡

ወ/ሮ ቤዛዊት ግን የእድሜ አሮጊት አይደሉም፣ እንዲህም አልነበሩም፤ በመንሳቀል አርጅተዋል፡፡ የወጣትነታቸው ይቅርና ከሁለት አመት በፊት የነበራቸው የእናትነት ድባብም አሁን ላይ ጠፍቷል፡፡ ትርንጎ ይመስል የነበረው ጉንጫቸው ማድያት አጥልቶበት፤ ወደ ውስጥ ሰርጉዶ ፤የጉንጫቸው አጥንት ፈጦ፣ ጠውልጎ ይታያል፡፡ የእናት ፍቅር የሚረጭ የነበረው አይናቸው በለቅሶ ብዛት ጠጅ ሲገለብጥ እንዳደረ ሰው ድፍርስ ብሎ ትካዜን ይተፋል፡፡ ተተኩሰውም ይሁን ተሽርበው ሲለቁት ከጀርባቸው የሚንዘላፈል ፀጉራቸው በሻሽ ተጀቡኖ ማበጠሪያ እንኳን ካየ ወራት አልፎታል፡፡

ከሚታየው ገፅታቸው ይበልጥ የተንሳቀለው ቅስማቸውን መግለፁ ከቃላትም አቅም በላይ ነው፡፡ አሁን ያሉበትን ሁኔታ ከወጣትነታቸው ጋር ማነፃፀር ደግሞ የህይወትን ረጋፊነት ባጭር ማስቀመጥ ይሆናል፡፡ ህይወትም ትርጉሟ እንደ ወ/ሮ ቤዛዊት ኑሮ በሁለት ተቃራኒ፣ የተገላቢጦሽ ገፅታዎች የተሞላች ናትና፡፡ አለማዊ ትሩፋቶች ምን ቢጥሙም መምረራቸው፣ ያማረ መደበሩ፣ የሳቀ ማልቀሱ፣ ያለቀሰ መሳቁ፣ የተበላ በሰገራ መውጣቱ፣ የተጠጣ መሸናቱ፣ የተራበ መጥገቡ፣ የተወጠረ መርገቡ፣ አዲሱ ማርጀቱ፣ የተወለደ መሞቱ አይቀርምና፤ ዪስሪን ዪስራ ነው፡፡

የዚህች አለም ነገር ከሰማይ የምትወርድ የ‹ውሀ ጠብታ›ን ይመስላል፡፡ ከሰማይ የምትወርድ የዝናብ ጠብታ በሺህ የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን ቁልቁል ገስግሳ ከደረቀ ምድር ላይ ታርፋለች፡፡ አርፋም በአፈሩ ላይ ተጠምታ ልትሞት የነበረች ፍሬ ላይ አዲስ ህይወትን ትዘራባታለች፡፡ በአበባው ውስጥ አድራም ትዋህዳለች፣ ተዋህዳም አንድ አካሏ ትሆናለች፡፡

አበባዋ በተራዋ የፍካት ዘመኗ ሲደርስና ዕንቡጧን ስታፈነዳ፣ ቅጠሎቿን ዘርግታ፣ ማዕዛዋን ለቃ፣ ፀዳሏ ደምቆ አምራ ትታያለች፡፡ ንቦች ይቀስሚታል፣ ቢራቢሮዎች ከበዋት ይደንሳሉ፣ ሰዎች በውበቷ ተማርከው ይገጥሙላታል… ተቀኝተውም ያዜሙላታል፤ ቀለሞችን በብሩሻቸው እያዋዙ.. እየሳሉ ያቀናጧታል፤ በካሜራ መስኮታቸው እየቀረፁ ለነገ

ያሳድሯታል፡፡ ሲያሻቸው እያቀፉ ደስታና ፍቅራቸውን ይገላለፁባታል፣ ሲያሻቸው ደግሞ በሸከላና መስታወት እየደገፉ የቤታቸው ማጌጫ ያደርጓታል፡፡ አድናቂና ፈላጊዋ እንደጉድ ይበዛል!

እነሆ የጊዜ እንጂ የሰው ጀግና የለምና፤ ለዝናብ የተሰጠው የጊዜ ገደብ ያበቃና ፀሐይ ከነሙሉ ሙቀትና ድምቀቷ ሰማይን ለወራት ትነግስበታለች፡፡ ያኔ አፈር ያጠራቀመችውን እርጥበት በሙሉ ሳትወድ በግዷ ትነጠቃለች፡፡ ኢምንት የውሃ ጠብታዎች በበራሪ ግለቶች እየተንተቱ ወደ ሰማይ ይጎናሉ፡፡ ያለረዳት የቀሩት አበባዎችም የፀሐዩ ቃጠሎ ለጋ ቅጠላቸውን እየመጠጠ ያጠወልግባቸዋል፡፡ ቀለማቸው ይደበዝዛል፣ ልስላሴያቸው ይቆረፍዳል፣ መዓዛቸው ይበናል፡፡ ፅጌረዳዋን የወደዳት ሁሉ ይጠላታል፣ ያደንቃት የነበረ ሁሉ አሁን ግን ከጫማው ታኮ ስር ረግጧት ያልፋል፡፡ እንደ ሄዋን ስጋ አፈር ናትና ወደ አፈር ትመለሳለች፡፡ ውቧ የውሃ ዘለላ በጊዜዋ ወርዳ ዳግም ህይወትን እስክትዘራ ድረስ፤ ቡቃያም ሳይበሰብስ እንደማይበቅል እንዲሁ የሰው ልጅም ሞተ በሰበሰ ሲባል በጌታ ሃይል ዳግም ተነስቶ ለፍርድ መቅረቡን ቢክድም እንደማይቀርለት ሁሉ የመሞትና የመነሳት ዑደቱ . . . . . . . ይቀጥላል፡፡

አዎ! ወ/ሮ ቤዛዊትም እንዲህ አልነበሩም፤ ተጎሳቅለዋል፡፡ የወጣትነታቸው ይቅርና ከሁለት አመት በፊት የነበራቸው የእናትነት ድባብም አሁን ላይ ጠፍቷል፡፡ ባለቤታቸው ጋሽ ጀምበሬ ታመው ከአልጋ ከዋሉ አሁን 2 ዓመታቸውን ከድነዋል፡፡ ያልተሞከረ መድሐኒት፣ ያልተቆፈረ ጉድጓድ፣ ያልተፈነቀለ ድንጋይ፤ ያልተጎበኘ ሐኪም፣ ያልተለማመኑት አዋቂና ባለውቃቢ አልነበረም፤ የህመማቸው ምክንያትና ፈውሳቸው ግን ሚስጥር እንደሆነ ቀርቷል፡፡ ይለፈልፋሉ፣ ያቃስታሉ፣ ሲያሻቸው ዘልዬ እሳት ውስጥ ካልገባው ይሉና ደርሶ ደግሞ ሰውነታቸው ግትርትር ብሎ፣ ከእንጨት እንደተሰራ አሻንጉሊት ድርቅ ብለው አንድ ቦታ ላይ ብቻ አፍጠው... ተቀምጠው ይውላሉ፡፡

ወ/ሮ ቤዛዊት ከድሮም የወጣትነት ፍቅራቸው፤ አሁንም ውድ ባለቤታቸውና የአንዲት ሴት ልጃቸው አባት ለሆኑት ጋሽ ጀምበሬ ጤና ሲሉ ተንገላተዋል፡፡ የቋጠሩትን ጨርሰው የቤት እቃዎችን ወደ መሸጡ

ገብተዋል፡፡ ባለቤታቸው በአልጋ ከመዋላቸው በፊት ጎበዝ አንጥረኛ ስለነበሩ ቢያንስ ለምግብና ልብስ ተቸግረው አያውቁም ነበር፡፡ ከዚያም አልፈው በዕቁብና ቁጠባ ማጠራቀምም ችለዋል፡፡ አሁን ግን ጊዜ ለኩሉ ነገሮች ተቀይረዋል፡፡ በእርግጥም ይህ የመከራ ወቅት ነበር፡፡ የሚላስ የሚቀመስ እስኪጠፋ ድረስ አንጀታቸውን አስረው እስከ መተኛት ድረስ ህይወት ፈተን አዙራባችዋለች፡፡

አንዳንዴ ሁሉ ነገር ሲጨልምባቸው በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ውስጥ የደስታን ጭላንጭል ያገኙ ዘንድ ከቤታቸው ደጃፍ ባለ 3 እግር በርጩማቸው ላይ ቁጭ እያሉ ገና ዋጋ ያልተተመነለትን ነፃ የጥዋት ፀሐይ ይሞቃሉ፡፡

የሚያልፍ የሚያገድመው የሰፈር ሰው "ደህና አደሩ ወይዘሮ ቤዛዊት?" ካለ በኋላ ሁሉም…

"ጋሽ ጀምበሬ ተሻላቸው?" አልያም… "ዛሬስ እንዴት ናቸው፤ በጎ አደሩ?" የሚሉ ጥያቄዎችን ያስከትላሉ፡፡

ወ/ሮ ቤዛዊትም "እግዚአብሔር ይመስገን!... አሁን ምንም አይሉም!" እያሉ ሳይሰለቹ ለሁሉም ተመሳሳይ መልስ ይሰጣሉ፡፡ ጠያቂዎቹም የእርሳቸው መልስና ከውስጥ የሚሰሙት የጋሽ ጀምበሬ ማቃሰት ባይስማማላቸውም ለይምሰል ያህል አንገታቸውን አወዛውዘው፤ እግዚአብሔር ምሕረቱን እንዲያወርድላቸው ተመኝተው ያልፋሉ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ ቀኑም ያልፋል፡፡ የህይወት ዑደትም እንዲሁ ይቀጥላል፡፡ በወ/ሮ ቤዛዊት ዓለም ፀሐይ ሳትወጣ ትጠልቃለች፡፡

***

*✍ አለኝ ብለህ አትኩራ - የለኝም ብለህ አትፍራ፥*

*ዓለም ተለዋዋጭ - እድል ተገላባጭ*

*ሀብት ረጋፊ - መልክ ጠፊ ነውና*

*በራስህ ተማመን… በዘመንህ አዘን፤ (ተፍሲረ ኪዳር ሰተቴ፣*

*(«ከጠ/ሚ፣ ዶ/ር አብይ አህመድ ሰተቴ መፅሐፍ፣ ገፅ 28-29 የተወሰደ)*

*** ☥ – ☥ ***

"አንቺ ልጅ አትመጪም እንዴ?" አሉ ወ/ሮ ቤዛዊት፤ ከበር ላይ ቆመው ልቧ እስኪጠፋ ድረስ የምትጫወተውን ፅዮን አሻግረው ተጣሩ፡

ፅዮን ካልተያዘችበት የአባሮሽ ጨዋታ ላይ መጠራቷ እንባዋን እያመጣባት፤ ንጭንጭ እያለች መጣች፡፡

"ከዚያ የከይሲ ልጅ ጋር አትጫወቺ ብዬ ስንቴ ነው የነገርኩሽ!"

"እማ እሱ ግን ምን ስላደረገሽ ነው ከሱ ጋር አትጫወት የምትይኝ?... ኢትኤል እኮ ጓደኛዬ ነው!" አለች ፅዮን ግራ በመጋባት፤

"ዝም በይ! አንቺ ልጅ ነሽ! ብዙ የማታውቂው ነገር አለ፡፡ ይልቅ አባትሽ እየፈለገሽ ነው... አቤት በይው፡፡" አሉ ወ/ሮ ቤዛዊት እጇን እየጎተቱ ወደ ውስጥ እያስገቧት፡፡

የነ ፅዮን ቤት-ሁለት ክፍል ቤት ነች፡፡ በኮንተርሳቶ ሁለት የሆነች አንድ ክፍል ማለቱ ይቀላል፡፡ ከበር እንደገቡ የሚያገኙት የመጀመሪያው ክፍል መሃሉ ላይ መለስተኛ፣ ከርካሳ ጠረጴዛ ተቀምጧል፡፡ ዙሪያውን ቀለሙ የተላላጠውን የጭቃ ግድግዳ ተደግፈው የተቀመጡ አራት በርጩማዎች ይታያሉ፡፡ በግራ ጥግ ትልቅ የእንጀራ መሶብ ሌማት፣ በቀኝ ጥግ ደግሞ ዳንቴል ለብሶ በክብር የተቀመጠ ‹ናሽናል› ራዲዮ አለ፡፡ ከራዲዮኑ በላይ ካለው ግድግዳ ላይ...

***"በመንፈስ፤ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤ መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና!" ... (ማቴ-5፤3)*** የሚለው የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በደማቁ ተፅፎ ተለጥፏል፡፡ ማንኛውም ከቤቱ ገብቶ ከአራቱ በርጩማዎች አንዱ ላይ የተቀመጠ፣ ማየትና ማንበብ የሚችል ሰው ይህንን ደማቅ ጥቅስ ሳያነብ መውጣት አይቻለውም፡፡

ይህን ክፍል አልፈው ወደ ውስጥ ሲገቡ በጊዜ ብዛት ያልወደቀ አሮጌ ቁም-ሳጥን እንደ ከቡር-ዘበኛ ቀጥ ብሎ ቆሞ ይቀበሎታል፡፡ ከጎኑ ደግሞ በብረት ዳንቴል ተጠልፎ የተሰራ ትልቅ የሽቦ አልጋ ተኝቶ፣ 4በ 4 ሜትር የምትጠጋዋን ክፍል ግጥም አድርጎ ሞልቷታል፡፡ ጋሽ ጀምበሬ ከዚሁ የሽቦ አልጋ ላይ ነው የአልጋ ቁራኛ ሆነው 2 ዓመታትን የተቆጠሩት፡፡

"ፀ...ፀዮኔ የ...የ..ት ጠፋሽብኝ?" አሉ፣ ቁርጥ..ርጥ ባለ፣ ደካማ ድምፅ፣

"አለሁኝ ጋሼ... ውጭ እየተጫወትኩኝ ነበር፡፡"

"ጨዋታ ከሆነ ጥሩ ነው... እነዚያ ከፉ ሰዎች ቤት እንዳትሄጂ እንጂ!"

"የትም አልሄድኩኝም... በር ላይ እኮ ነው ስጫወት የነበረው" መለሰች ፀዮን፣ ድንግዝግዝ ባለው ክፍል ውስጥ ከስራቸው የማይለየው ውሻቸው አላዛር አይን ሲቁለጨለጭ ይታያታል፡፡ አልጋው ጎን መጥታ ከስራቸው ተቀመጠች፡፡ ከራሷ ላይ እጃቸውን ጣል አድርገው ፀጉሯን እየደባበሱ፡፡

"እ...እሺ... አሁን እስኪ ሂጂና ያቺን የምወዳትን የሀበሻ አረቄ አምጪልኝ፤" አሏት፣ ከፊታቸው ከጠፋ የቆየው ብርቅዬ ፈገግታ በስሱ እየተነበበባቸው፤

"ግን እንደባለፈው እማ አይታኝ ደግሞ ብትቆጣኝስ?" ... ቁልጭ ቁልጭ ከሚሉት አይኖቿ ላይ የልጅነት ፍርሃት ይንፀባረቃል፡፡

"ች... ችግር የለውም ልጄ... ቀስስ ብለሽ ሳታይሽ፤ በፌስታል ደብቀሽ አምጪልኝ፤" አሉ ጋሽ ጀምበሬ፡፡

ፀዮን ፌስታሏን አጣጥፋ ሹልክ ብላ ወጣች፡፡ እናቷ ወ/ሮ ቤዛዊት ከደጃፉ ላይ በባለ ሶስት እግር በርጬማ ቁጭ እንዳሉት አሉ፡፡ ምንም ሳይናገሩ ዝም ቢሏትም የት እንደተላከች ግን ልባቸው ጠንቅቆ ያውቀዋል፤ ባላቸው ከሚከፋ ግን እንዳላወቁ ማለፉን መርጠዋል፡፡

"እንደምን አረፈዱ ወ/ሮ ቤዛዊት?" አሉ አቶ ለማ፣ ኮፍያቸውን ከአናታቸው ከፍ አድርገው ከወደ ወገባቸው እያጎነበሱ፤

"ደህና እግዚአብሔር ይመስገን!"

"ጋሽ ጀምበሬስ እንዴት ናቸው?... ተሻላቸው?..."...ተመሳሳይ ጥያቄና መልስ ቀጠሉ፡፡

*** ፃ – ፃ ***

በጅማ ከተማ ውስጥ የዩንቨሪሲቲ ተማሪዎች መጠጫና መጨፈሪያ እንደሆኑ ተለይተው የታወቁ ገናና ሆቴሎች አሉ፡፡ በርካታ ሴትም ሆኑ ወንድ ተማሪዎች በተለይ አርብና ቅዳሜ እነዚህ መሸታ ቤቶች ውስጥ ይከትማሉ፡፡ እስከ ውድቅት ሌሊት ብሎም እስከንጋት ድረስ እየጠጡ፣ እየጨፈሩ ሲላቸው ጆሮ ከሚሰነጥቀው የሞንታርቦ ድምፅ በላይ እርስበርሳቸው እየጮሁ ያወራሉ፣ ይሳሳቃሉ፤ የሚወዱትን ሙዚቃ ዲጀው ከለቀቀ ደግሞ ሃገር ምድሩ ይያዝልኝ እያሉ ይጨፍራሉ፣ ይዘላሉ… ይፈነጥዛሉ፡፡

ሞቅ ሲላቸውም ወንዱ ከሴቱ፣ ሴቱ ከወንዱ እየተጎነታተለ፣ እየተሻሸ፣ እየተሳሳመ፤ ሌላም ሌላም እየሆነ ዓለሙን ይቀጫል፡፡

ከእነዚህ ሆቴሎች አንዱ የጅማ ‹አጂፕ› ሰፈር መድመቂያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ‹አጂፕ› ሰፈር ማለት ማንኛውም ከአዲስ አበባ የመጣ ተጓዥ ጅማ ከተማ ሲገባ በመጀመሪያ የሚያገኘው ሞቅ ያለ ሰፈር ነው፡፡ ከጅማ ወደ መሐል ሐገር የሚወጣም መኪና ለረጅሙ ጉዞው ነዳጅ ይሞላ ዘንድ የተዘጋጀ ሲሆን ታክሲም ይሁን ባለ 3 እግር መኪና አጂፕ ማደያ ጎራ ማለቱ የተለመደ ነው፡፡

ኢትኤልና ዮሴፍ በተለይ የዚህ የአጂፕ ክለብ የአልፎ አልፎ ደንበኞች ናቸው፡፡ ቢያንስ በወር አንዴ ወይ ሁለቴ ይሄዳሉ፡፡ ሁለቱም የሬጌ ሙዚቃ አድናቂ ናቸው፡፡ በተለይ ግን የኢትኤል የሬጌ ፍቅር ይለያል፤ ሙዚቃው ምት ውስጥ ዱብ ዱብ እያለ መጨፈር ልዩ ሃሴት ይሰጠዋል፡፡

*"አርማው የኢትዮጵያ አንበሳ ¶¶… ቦብ… ቦብ ማርሊይ!*
*ምቶም ዛሬም አይረሳ ¶¶… ባም… ባም… ቦብ ማርሊይ"*

የሙዚቃው ጥበበኛ፣ የፍቅር ቀስተኛው አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን ሳልሳዊው ያዜማል፤ የሚሰብከውም ስለሬጌ ንጉሱ፣ የአንድ ፍቅር ሳተናው፣ ኢትዮ-ጃማይካዊው ዘማሪ ቦብ ኔስታ ማርሊይ ነው፡፡ ኢትኤል በሙዚቃው ምት ውስጥ እየዘለለ አብሮ ይነሰነሳል፡፡ ግራና ቀኝ እግሮችን እያፈራረቀ ይወዛወዛል፡፡

ዮሴፍ በበኩሉ ከሙዚቃው ምት ውስጥ ገብቶ ከመደነስ ይልቅ ከጎኑ የቆመችው መቀመጫዋ ግብድዬ ሴት ላይ ቀልቡን ጥሎ ተገትሯል:: በስካር መንፈስ ውስጥ ሆኖ በስሜት እየነሆለለ ከዳሌዋ ጋር በሃሳቡ ይተረማመሳል:: እሷም እያያት እንደሆነ ገብቷታል፤ ከወገቧ በታች ያለውን አካሏን ከፍ ዝቅ እያደረገች ማንቀጥቀጡን ተያይዛዋለች::

የቴዲ አፍሮ ሙዚቃ ሲያበቃ ኢትኤልም መደነሱን አበቃና ወደ ዮሴፍ ዞረ:: ዮሴፍ ለሀጩን ማዝረክረክ እየቀረው አፍጥጦ ያቺን ልጅ ሲያይ ተመለከተው:: የጓደኛውን ፀባይ ጠንቅቆ ያውቀዋል:: ነገሮችን በጊዜ አቋርጦ ይዞት ካልሄደ ትንሽ ቆይቶ 'እዚሁ ማደሬ ነው' ማለቱ አይቀርም:: ቀስ ብሎ ለአስተናጋጇ የእጅ ምልክት አሳይቶ ጠራት… እጆቿን ወዲህና ወዲያ እያወዛወዘች፣ እንደ መደነስም እየቃጣት መጥታ ከጎኑ ቆመች::

"ሂሳብ!" ብሎ ጮኸ፣ የሞንታርቦውን ድምፅ ለማሸነፍ ወደ ጆሮዋ በጣም እየተጠጋ:: ሌባ ጣቷን እንደ ዳከዬ አንገት እያጠፈች በጠረጴዛው ላይ የተደረደሩትን የቢራ ጠርሙሶች አንደ በአንድ ቆጠረች::

*"540 ብር!"* በተራዋ ወደ ኢትኤል ጆሮ ተጠግታ ጮኸች:: ኢትኤል ወደኋላ እንደመውደቅ ብሎ ተንገዳገደ:: በእርግጥ ኪሱ ውስጥ 1000 ብር ገደማ ቢኖረውም ሂሳቡ ከ200 ብር ይበልጣል ብሎ ጭራሽ አላሰበም ነበር:: ሳያስቡት ብዙ ጠጥተው ኖሯል! የኪስ ቦርሳውን አወጣና ከጨለማው ጋር እየታገለ 600 ብር ቆጥሮ ሰጣት::

ኢትኤል 60 ብር መልሷን ታመጣለች ብሎ ቢጠብቅ… ቢጠብቅ… አስተናጋጇ ግን የውሃ ሽታ ሆና ቀረች:: በመጨረሻም ባንኮኒው ድረስ ራሱ ሄዶ መልሱን መቀበል ነበረበት:: ተመልሶ ሲመጣ ዮሴፍ የቅድሟ ባለ ግብድዬ ዳሌ ሴት ጭኖች መሃል ሆኖ ሲደንስ ነበር ያገኘው:: ገላዋ ላይ እንደ አልቅት ተለጥፎ ስለነበር እጁን ይዞ ቢጎትተውም ሊያላቀው አልተቻለውም:: ወደ ጆሮው ተጠግቶ…

"እባክህን እንውጣ!" ብሎ ጮኸበት፤ ከዮሴፍ ጋር ያለችው ሴት በክፉ አይን ወጋችው::

"አቦ አልሄድም!... ትንሽ እንቆይ!" አለ ጥንብዝ ብሎ የሰከረው ዮሴፍ፣

"በናትህ እንውጣ፣ 5 ሰዓት ሊሆን ነው... የግቢ በር ይዘጋብናል!" አለ ኢትኤል በምሬት፣ ከዚያም እጁን ይዞ በሓይል ጎተተው... ዮሴፍ ላማሚቀችው ባለ ግብድዬ ዳሌ ሴት ልቡን ጥሎ በግድ እየተጎተተ ወጣ::

"ዛሬ በጣም ሙዴን ከንተከዋል!" አለው ኢትኤልን፣ ወደግቢ የሚያደርሳቸው ባጃጅ ውስጥ ገብተው ገና ጉዞ ከመጀመራቸው፣

"አንተ ዝም በል... ሰከረሃል፣ ዛሬ በሌለን ብር ውጭ ልታሳድረኝ ነበር እቅድህ..."

"በቃ አታካብድ!" አለ ዮሴፍ በቸልተኝነት፣ ኢትኤል መልስ አልሰጠውም:: ቢናደድም ንዴቱን ለራሱ ማስቀረቱን መርጧል:: ከጎኑ ባለችው ትንሽዬ መስኮት በኩል የምትገባውን ብርድ ለመከላከል የጃኬቱን ኮሌታዎች በጆሮዎቹ ትይዩ ውጥር አድርጎ ይዞ ተቀመጠ:: ወደፊትና ወደኋላ እያለ ቅዝቃዜውን ለመቋቋም ይወዛወዛል:: ምሽቱ በመጠኑ ቀዝቀዝ ያለ ቢሆንም የባጃጁ መፍጠን ከአየሩ ጋር የሚፈጥረው ስበቃ ብርዱን እያበረታው እነኢትኤልን ያርበተብታቸው ገባ:: ..................................
ጅማ ከተማም እንደነኢትኤል በርዷት ነው መሰል ጭር ብላለች:: አልፎ አልፎ ከመንገዱ ዳር ላይ ከሚታዩት ብርድ ቀርቶ ድሪል የማይበሳው ካፖርት ከራስ ፀጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ከለበሱ የሌሊት የጥቢቃ ሰራተኞች በቀር ወፍ ዝር አይልም:: ፀጥ ያለው ሌሊት ላይ አንድ ዜማ ተከፈተ...

*"♫እምዬ ኢትዮጵያ ይመርልሽ ሰብሉ፣*

*አውድማው ጎተራው ይሁንልሽ ሙሉ*

*በቸር ውሎ ይደር ጋራ ሸንተረርሽ..*

*...ወንዝ ወንዝሽ ሁሉ!"*

የሚለው ስሜት ኮርኳሪ፣ ብርር ብላችሁ በእናት ሀገር እቅፍ ውስጥ ግቡ እያለ የሚጎተጉት የዜማ መዋዕሉ አርቲስት ቴዎድሮስ ታደሰ ዘፈን ከባጃጁ ሞጁሌተር አልፎ ይሰማል:: ከብርዱ ጋር ተደምሮ እነኢትኤልን ያልጠበቁት ትካዜ ውስጥ ከተታቸው:: ሳያስቡት ኢትኤልና የባጃጁ ሹፌር አብረው እኩል ይዘፍኑ ጀመር...

♪♫ "ይመስከር አካሌ ጉያሽ ያደረጀው

የእናትነት ጠዓምሽ ውለታሽ ያበጀው፣
በማጀትሽ ወተት በጤፍሽ እንጀራ
በማር በወለላሽ በጓሮ ሽንኮራ፣
ብድር አለብኝ ልከፈልና ልኩራ
ከብርሽ ከፍ ይበል ከሰላምሽ ጋራ፤
…የወለደኝ ምድርሽ… በቸር ይደር
ያሳደገኝ ቀዬሽ… በቸር ይደር…"

"እስኪ አንድ ላይ!" አለና ዮሴፍም በስሜት የመጨረሻውን ስንኝ አጀባቸው፤

*"♫በቸር ይደር… ዙሪያው በቸር ይደር ያሳደገኝ ሃገር…"*

ኢትኤል አንዳች ስሜት ሰውነቱን ሲወረው ይታወቀዋል:: ስላደገበት የልጅነት መንደሩ እያሰበ በምናብ ወደኋላ ተመለሰ… በልጅነት ትዝታው ውስጥ የነገሰችውን ፅዮን በዚያው ቅፅበት ሲያስታውሳት ነበር ከደወለላት በጣም እንደቆየ የገባው:: ስልኩን አወጣና ፅዮን የሚለውን ስም ፈልጎ አግኝቶ አረንጓዴውን የመደወያ ቁልፍ ሊጫን ሲል…

"ደርሰናል!" አለ የባጃጅ ሹፌሩ፣ ቡዝዝ ብለው በሃሳብ ወደነጎዱት እነኢትኤል እየዞረ::

የተስማሙትን ሂሳብ ለባለባጃጁ ከፍለው ከወርዱ በኋላ ወደ ግቢ ሊገቡ ሲሉ፣ "ቁሙ!" አለ፣ አንድ እንቅልፍ ሲያንጎላጀው የነበረ የጥበቃ ሰራተኛ እግሩን አነፋሮ ከታኛበት ወንበር ብንን ብሎ እየተነሳ፤

ኢትኤልና ዮሴፍ እንደ ወታደር ቀጥ ብለው ቆሙ::

"ከየት ነው የምትመጡት?" አላቸው ሌላ ባለጎርናና ድምፅ ረጅ…ም ጥበቃ ከማደሪያው የቆርቆሮ ቤት እየወጣ::

"አይ ትንሽ ፕሮግራም ነበረችን… ሳናስበው መሽቶብን ነው::" አለ ዮሴፍ እየተቅለሰለሰ… መስከሩ እንዳይታወቅበት የአቅሙን እየሞከረ ነበር::

"ቦ..! ሂድና የምትፎግረውን ፎገር ባክህ፣ እኛም የደርግ አራዳ ነን!"... ረጅሙ ጥበቃ የሚሸወድ አልሆነም፡፡ ሁለቱም ጥበቃዎች በተራ ተራ እየቆሙና እየተቀመጡ ለብዙ ደቂቃዎች አስለመኗቸው፡፡ የኋላ ኋላ ግን የነኢትኤል በብርድ መኮራመት ሃዘኔታ ቢጭርባቸው እኩለ ሌሊት ገደማ በሩን ከፍተው እንዲገቡ ፈቀዱላቸው፡፡

ግቢ ውስጥ ገብተው ከበር ጠባቂዎቹ አይን እንደራቁ "ምድረ አካብዴ ሁላ... ሲያናዱ!" አለ፤ ቅድም የሚያሳዝን ፊት እያሳየ ሲለምን የነበረው ዮሴፍ.. "ማስገባታቸው ላይቀር ማስለመን ምን ይሉታል?"

"አትፍረድባቸው ጆሲ!" አለ ኢትኤል "በዚህ በዚህ ካልተዝናኑ ሌሊቱን በሙሉ በብርድ ቆሞ ማሳለፍ ምን ያህል አታካች እንደሆነ አስበኸዋል?"

"ባክህ ተወኝ... አትጨቅ... ጭ... ቀኝ" ... ዮሴፍ መስማት አልፈለገም፡፡ ለብቻው በምሬት እያጉተመተመ ዚግዛግ ይራመድ ገባ፡፡

*** ቶ – ቶ ***

መርየም ከሰሞኑ ያመጣችው ለየት ያለ ባህሪ በፅዮንም ሆነ በሌሎች የዶርም ጓደኞቿ ዘንድ ጥያቄ የሚፈጥር ሆኗል፡፡ ያ ሳቂታነቷ ጠፍቶ ትካዜ ወርሷታል፡፡ የባጥ የቆጡን እያወራች የተከዘን ሁሉ ፈታ ታደርግበት የነበረው ጨዋታዋ ጠፍቶ በዝምታ ተተክቷል፡፡

"ሜሩ ግን ምን ሆነሻል?... እያስጨነቅሽኝ እኮ ነው?" አለቻት ፅዮን፤ አንድ ምሽት ዶርም ብቻቸውን ሳሉ፤ ምክንያቱን ለማወቅ ጥሩ አጋጣሚ ያገኘች ስለመሰላት...

"ምን ሆንኩኝ?... ምንም አልሆንኩም ፂያ!" አለች መርየም ትንሽ እንደመቆጣት እያለች፡፡

"እንዴት ምንም አልሆንኩም ትይኛለሽ?... አፍሽ ተለጉሞ እያየሁሽ፡፡ ወይስ ከእኔ የምትደብቂው ነገር አለ ማለት ነው ሜሩ?" አለች ፅዮን በእርጋታ፤

"ካንቺ ለመደበቅ ፈልጌ አይደለም ወላሂ"

"ምኑን ነው የምትደብቂው?" አለች ድንገት በሩን ከፍታ የገባችው ቢታንያ፤

"እ... እ... ምንም..." አለች መርየም ያደረገችውን ሻርፕ ጠቅለል አድርጋ በስፒል እያያያዘች፤

"ሜሩ ስትዋሺ አያምርብሽም፤" አለች ቢታንያ፤

"እኔ እንደማልዋሻችሁ ልባችሁ ያወቀዋል፤ ግን ብነግራችሁም ይሄን ያህል ለውጥ ታመጣላችሁ ብዬ ስላላሰብኩኝ ነው፡፡"

"ግድየለሽም አንቺ ብቻ ንገሪን" ብላ ፅዮን አበረታቻት፤

መርየም በረጅሙ ተነፈሰችና "እሺ ካልሽ ምን አደርጋለሁኝ፤" ብላ ጀመረች፤ "ምን ብዬ እንደምገልፅላችሁ ባላውቅም ሰሞኑን በህይወቴ ተሰምቶኝ የማያውቅ ልዩ ስሜት እየተሰማኝ ነው፡፡"

"ምን አይነት ስሜት ሜሩ?... ለምን በግልፅ አትነግሪንም?"... ፅዮን ተቀበለቻት፤

"ፍ... ፍ... ፍቅር ሳይዘኝ አይቀርም፡፡" አለች መርየም ከረጅም ማመንታት በኋላ፤ . . . ቢታንያ ጆሮዋን ማመን አቃታት፣ ፅዮን በአግራሞት ፈዘዘች፡፡ እየቀለደች ነው እንዳይሉ ፊቷ ላይ የሚያነበት ጭንቀት የእውነት ነበር፡፡ መርየም ወንድ መውደድና ፍቅረኛ መያዝ ቀርቶ ለመጨበጥ እንኳን ‹ውዱዬ ይጠፋል› የምትል፤ በሙሉ ዓይን ወንድን የማታይ በጣም ቁጥብ ልጅ ናት፡፡ ታድያ የነገረቻቸውን ለማመን ጥቂት ጊዜ መውሰዱ አልቀረም ነበር፡፡ ከደቂቃዎች በኋላ...

"ግን ልጁ ማነው?... የትስ ተገናኛችሁ?... ጠይቀሽዋል?..." የሚሉ ጥያቄዎችን ያዘንቡባት ጀመር፡፡ መርየም በበኩሏ እንኳን ለሰው ለመናገር ቀርቶ ለራሷም በቅጡ ስለማታውቀው ልጅ ምንም መናገር አቃታት፡፡ በተለይ ቢታንያ ጉዳዩን ለማወቅ በጣም ጓጓታ ጨቀጨቀቻት፡፡ የምታደርገው ቢጠፋት ያ አንገት ደፊ ልጅ የሚያነብበት ቤተ-መፅሐፍት ድረስ አብረው ሄደው ልታሳያት ተስማማች፡፡

*** ቶ – ቶ ***

ኢትኤልና ዮሴፍ፤ የማይደረስ ነገር የለ በድካምና በስካር እየተንገላጀጁ የዶርማቸው በር ጋር ደረሱ።

ኳ ኳ ኳ ኳ... የዶርሙን በር አንኳኳ ኢትኤል፡ መልስ የለም... ደገመው፤ ጠበቀ፣ መልስ የለም...

ጓ ጓ ጓ ጓ. . . አንጓጓ ዮሴፍ፡ መልስ የለም... ደገመው፡ ጠበቀ...

ደግሞ በሩን ሊነርተው ሲዘጋጅ ዘይኔ በሩን ከፈተላቸው።

ዮሴፍ፤ "ለ... ለምን ቶሎ አትከፍቱም?" እያለ እየተነጫነጨ ገባ፡

"እናንተስ ምን ያስቸኩላችኋል?... ሶብር የሚባል ነገር አልፈጣረባችሁም?" ዘይኔ በምሬት መለሰ፤ "እዚያ የትም ስትጠጡ ታመሹና ከዚያ እኛን ትረብሻላችሁ... ወላሂ ይሄን አላህ አይወደውም።"

"እሱ ምን?... ምንድነው የሚወደው?" አለ ዮሴፍ፡

ዘይኔ ዮሴፍ እያፌዘ መሆኑ ገብቶታል፤ በውስጡ ቢናደድም ባልሰማ ወደ አልጋው ተመልሶ ንባቡን ቀጠለ።

"ቲሽ አንተን ብሎ አማኝ... ድሮም መልስ እንደሌለህ አውቃለሁኝ። አላህ፡ እግዚአብሔር... እ... ጌታ ምናምን የምትሉትን ነገር አላየሁት አልሰማሁት..." አለ ዮሴፍ እየተንጀዋረረ...

"ኧረ በፈጠረክ ጆሲ... እኛን መበጥበጥህ ሳያንስ የእግዚአብሔርን ስም አታጉድፍ፤" አለ አብርሃም፡ ረብሻውን እንዳልሰማ ሆኖ ለማንበብ ቢሞክርም ትዕግስቱ ግን እየተሟጠጠ ነበር።

ዮሴፍም መልሶ "ቄሱ ደግሞ ተነሳበት!" አለ፤ አብርሃም ላይ ሌባ ጣቱን ጠቁሞ እየሳቀ፤

መልስ አልሰጠውም፤ የአብረሃም ፊት በንዴት እሳት ሲለብስ ግን ኢትኤል አስተውሏል።

"አይ እንግዲህ መስመር አትለፍ፤ ስርዓትህን ብትይዝ ይሻልሃል!" አብርሃም ለመጣላት የተዘጋጀ ይመስላል።

"አብርሽ በቃ ተረጋጊ" አለና ኢትኤል፣ ከአልጋው ወርዶ ሄዶ ያዘው፤

"ኧረ ልቀቀው! ይምጣና ይምታኝ!... ና ምታኝ!... ምታኛ ና!.." ዮሴፍ መጮኽ ጀመረ:: ዘይኔም ከአልጋው ዘሎ ወርዶ መሃል ገባ:: ኢትኤል አብርሃምን እንደያዘ ሲዞር ዮሴፍም ለመማታት ሲወራጭ አየው:: እየሆነ ያለው ነገር በሙሉ ግራ እያጋባው ነበር፤

"በእየሱስ ስም ምንድነው ይሄ ሁሉ ረብሻ?"... ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ውስጥ የነበረው ናዖድ በጫጫታቸው ባንኖ ነው የተነሳው:: በድንጋጤ ሱሪ እንኳን ሳይታጠቅ በፓንት ቆሟል::

"በጌታ ስም ይገሰፅ ይሄ የጥል መንፈስ! ምንድነው ይሄ ሁሉ ፀብ?" አለ፤ ቃላቶቹ ‹አፍሬባችኋለሁኝ› የሚል ፍካሬያዊ ለዛ ነበራቸው::

"አቦ አንተ ሚጢጢ ‹ፓስተር› አርፈህ ተኛ!"... አለ ዮሴፍ በንቀት፤ "ብለሽ! ብለሽ! አንቺም እኔን ልታስፈራሪ አማረሽ... ወይኔ ጀሲ!"... ዮሴፍ የእውነትም የተናደደ መሰለ፤

"ምን አቅም አለንና እንመታሃለን... ጉልበተኛው አንተ..." አለ ዘይኔ እልህ እየተናነቀው::

አብርሃም፣ ዘይኔና ናዖድ ሁሉም ዮሴፍ ላይ ጥርሳቸውን ነክሰው ቆመዋል::

"ጭራሽ ለሦስት ልተደበድቡኝ ነው እንዴ?... ጉድ እኮ ነው::" ዮሴፍ ፍርሃት ቢጤ የተሰማው ይመስላል:: ከአልጋው ላይ ተመልሶ ቁጭ ብሎ ጫማውን እየፈታ፣ ድምፁን ዝቅ አድርጎ ሲያጉረመርም ቆየና ቀና አለ፤ "ቆይ.. ቆይ.. ቆይ.. ግን ዛሬ እንዴት ነው እንደዚህ የተባበራችሁት? ሌላ ጊዜ እኮ ቢሆን እየሱስ ሲነካ ደስ ነበር የሚልህ!" አለ ወደ ዘይኔ ዞሮ::

"ወላሂ ደስ ብሎኝ አያውቅም::" መለሰ ዘይኔ፤

"ኧረ ባክህ... እየሱስ ላንተ ምንህ ነውና?" ዮሴፍ ጠየቀው::

"ሙስሊም እንደመሆኔ መሲሑ ኢሳ የማከብረው ነብይ ነው፤ ማንም ስለእሱ ክፉ ሲናገር ደስ አይለኝም::"

"ታዲያ ጌታና አምላክ አይደለማ?!" አለ ዮሴፍ በሬዝ፤

"እሱ የአላህ ባሪያ ነው እንጂ ጌታ አይደለም፡፡" መለሰ ዘይኔ፤

"እየሱስማ ባሪያ ሳይሆን ብቸኛው አዳኝ ጌታ ነው!" አለ ናዖድ በቁጣ ወደ ዘይኔ እየዞረ፤

"ማዳን የሚችለውና የእውነት ጌትነት የሚገባው ለአላህ ብቻ ነው!" ዘይኔም በግልፍተኝነት መለሰ፤

ዘይኔና ናዖድ ተፋጠጡ፤ የዮሴፍ ፊት ላይ ታላቅ ደስታ ይነበባል፡፡ በሱ መናደዳቸውን ትተው ወደሌላ የክርክር ርዕስ መዞራቸው ተመችቶታል፡፡ ወትሮም ፍላጎቱ እነርሱ በሃይማኖት ሲከራከሩ እየሰማ መዝናናት ነበር፡፡ አላማው በከፊል ተሳክቶለታል አሁንም ግን አልረካም፡፡

"ግን እኮ እየሱስ ብቻውን አዳኝ ከሆነ ድንግል ማርያም አታድንም ማለት ነው?" አለ አብርሃምን በቆሪጥ እያየ፡፡

"ድንግል ማርያም ባንተ አፍ የምትጠራ ሴት አይደለችም፣ ከዓለም ሴቶች በሙሉ የላቀች ብፅዕት ነች እሺ!" አለ አብርሃም እልህ ድምፁን አቅጥኖት እንባ እየተናነቀው፤

ከዚህ በኋላ ደስ የማይል ስሜትን የሚፈጥር የጦፈ የሃይማኖት ክርክር ተነሳ፡፡ መጨረሻው ግን ከማስማማት ይልቅ የሁሉንም ቀልብና ላንቃ ያደረቀ ፍፃሜ ነበር፡፡

በረጅሙ ክርክር ውስጥ አንዲትም ቃል ያልተነፈሰው ኢትኤል ብቻ ነበር፡፡ ስለሃይማኖት የተወሰነ እውቀት ቢኖረውም የሚነሱት የክርክሩ ነጥቦች በአዕምሮው ውስጥ ብዙ ጥያቄዎችን እየፈጠሩበት ነበር፡፡

ጥያቄዎቹ እየጠነከሩ መጥተው እንደዚያ ዳግቶለት የመጣው አልጋው ላይ እንቅልፍ ሊተኛ ከለከሉት፡፡ *«እውን አምላክ አለ? የት ነው ያለው? ምን አይነት ነው? ካለስ ለምን ፈጠረን? ፈጥሮንስ ለምን ስንሰቃይ ዝም ብሎ ያየናል? ሁሉም የኔ ልክ ነው ብለው ካስተማሩስ ትክክለኛው ሃይማኖት የቱ ሊሆን ነው? ኢትዮጵያስ የእውነት ቅድስት ሀገር ናት? ከሆነችስ ይሄ ሁሉ ሃይማኖተኛ እያለባት ችግር፣ ርሃብ፣ ጦርነት፣ በሽታና ስደት ለምን ይወርሳታል? ለሁሉም መፍትሔውስ ምን ይሆን? እምነትስ ምንድነው? እውነትስ?»* … በቃ ጭንቅላቱ በጥያቄ መዓት ተወጠረ፡፡ ከሌሊቱ 9:00 ሰዓት ገደማ ከአልጋው ወረደና የሚወደውን የግጥም መፃፊያ ደብተሩን ገለጠ፡፡ እንዲህ ሲልም ከተበ…

✍ አንደኛው ይሰግዳል - እጅ እግሩን ተጣጥቦ፣

ሌላኛው ያዜማል - ተጨንቆ ተጠቦ…
አይኖቹን ጨፍኖ - በቅኝት ተውጦ…
አንደየዋህ እርግብ - ሲያም ጥሬ ንቆ፥
ከአፉ እህል እርቆ - በአጣን ተጠምቆ፡፡
ሌላኛው ሊያስቀድስ ጎህ ሳይቀድ ይወጣል፤
እያሉ ቢያውጁም - ሁሉም "የ'ኔ ይበልጣል"
ልብሳቸው ቢለያይ - ቀኖና እና ባህል
አውነት ለመናገር፤
ጥልቅ ትርጉም ያለው - እምነት ግን ያስቀናል፡፡

---

ካላየሁ ማላምን- በወጉ ያላደግኩኝ
ለእኔ ግን አልገባኝ - የእነርሱ ሚስጥር፥
የትኛው ሃይማኖት… በምን በኩል ይጥራኝ?
ላየው ተመኘሁኝ - ሞት ደርሶ ሳይከዳኝ
ለዘላለም ኑዋሪ - ህያው መሆን ዳዳኝ፡፡
ታድያ…
የእውነቱን መንገድ ሳልኖረው እንዳልቀር፤
ይመጣ ይሆን ወይ የማውቅበት መስመር?
የሚመራኝ ነገር፣ የሚታይ ምስክር፥
ለተራ እኔነቴ - ይከፈት ይሆን ወይ ታላቅ የፅድቅ በር?!

ደብተሩን ዘግቶ ወደ ቦታው መለሰና ትራሱን ደገፍ አለ፡፡ የሆነ የተስፋ ብርሃን ውስጡን ሲሞላው እየታወቀው ወድያው ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰደው፡፡

*** ቶ – ቶ ***

ፕ/ር እሴ አሁን ሞቅ ብሏቸዋል፤ በላፕቶፓቸው የሚያነቡት ታሪክ ቀመስ መፅሐፍ ላይ ተመስጠው፣ ከዘመን ብዛት በማርጀቱ ምክንያት ዋጋው የተወደደውን የፈረንሳይ «ሴይንት-ኤሚሊዮን» ውስኪ ብዙ እንደተጎነጩለት አልተረዱም ነበር፡፡ ብዙ ብዙ ጥያቄዎቻቸውን ሊመልስ የቻለ መፅሐፍ እንዲህ በቀላሉ ከድህረ-ገፅ ላይ ስሙን በመፃፍ ብቻ ፈልገው አግኝተው፣ በነፃ አውርደው ማንበብ መቻላቸው በጣም ገርሟቸዋል፡፡

እሴ ፂማም ናቸው፣ የአይን ሽፋሽፍታቸው የሸለ፣ ቅንድባቸው እንደጎተራ የተከመረ፣ የደስ ደስ ላይ ግርማ ሞገስ የደረበባቸው ‹ፕሮፌሰር›፤

በአፍሪካ ታሪክ ዙሪያ ብዙ የጥናት ፅሑፎችን ለዓለም ያበረከቱና በዘርፉም አንቱ ከተባሉ አፍሪካዊ ምሁሮች መካከል አንዱ ናቸው፡፡ ይህንን መፅሐፍ ግን ታሪክን “ሀ” ብሎ እንደሚጀምር የ7ተኛ ክፍል ተማሪ እንግዳ ሆነው ነበር የሚያነቡት፡፡ በግላቸው ስለ አክሱምና ጥንታዊ ግብፅ ፒራሚዶች ትርጉምና የመሰራታቸው ትክክለኛ አላማ ለማጋለጥ ጥናት ከጀመሩ 13 ዓመታትን አስቆጥረዋል፡፡ እንደዚህኛው መፅሐፍ ግን ደም-ስራቸው ውስጥ ገብቶ የፈሰሰ፣ እስከዛሬ ‘አለኝ!’ ብለው የሚኩራሩበትን የታሪክ እውቀታቸውን እንዳዲስ የፈተነ፣ ብሎም የብዙ ዓመት ጥናቶቻቸውን ክፍት ቦታዎች እየሞላ እውቀታቸውን ምሉዕ ያደረገ መፅሐፍ የለም፡፡ ስለ አፍሪካ ቀርቶ እትብታቸው ስለተቀበረባት ሃገራቸው ኢትዮጵያ ብዙ የማያውቁት ነገር እንዳለ እየተረዱ ነበር፡፡ የሚያነቡት መፅሐፍ በኢትዮጵያ የታሪክ መማሪያ መፅሐፍት ውስጥ ያልተካተተ፣ ብዙዎቹ የምዕራብ ዘመነኛ የታሪክ ፀሃፍት ያልዘገቡት አዲስ ተዓምረኛ ድርሳን ነበር፡፡

“እስካሁን ይሄ ሁሉ ጉድ የት ተደብቆብን ነበር!?... ከፊታችን የተቀመጠን ተዓምር እንኳን ማየት የተሳነን ምን አይነት ከንቱዎች ነን!” አሉ በንዴት፤ ሲያነቡት የነበረውን ላፕቶፕ እየዘጉ፤ በልባቸውም ይህንን መንፈሳዊና ዓለማዊ የከፍታ እውቀት ለመላው ኢትዮጵያዊ ይፋ ለማውጣት ቃል እየገቡ፡፡

*** ☥ – ☥ ***

*** ቶ – ቶ ***

*"አሁን ያለው በፊትም ነበር፥ የሚሆነውም በፊት ሆኖ ነበር፤ እግዚአብሔርም ያለፈውን መልሶ ይሻዋል።"*

*(መፅሐፈ መክብብ፤ 3-15)*

*** ቶ – ቶ ***

# ምዕራፍ - ፫

## …♛ መልዓክትና አጋንንት ☿

አዛዝኤል በሸሸት ላይ እንዳለ የዘ-ፍጥረተ አውነትን ቀሪ ትረካ ግን በምናብ፣ በመናፍስት የመረጃ-መረብ ለሱቃኤል እየገለጠለት ነበር፡፡ እሱ ከሚያስረዳው ይልቅ እውነታው ግን ይህ ነበር›››

… ያኔ ነው!

ስነ-ፍጥረት ቀጥሏል፣ እነሆ የፍጥረታት የህይወት ዑደትም እንደዚያው!
ከመንግስተ-ሰማይ መቅደስ፣ በየቅፅበቱ!
ሚሊዮኖች ሲገቡ ፥ ሚሊዮኖች ይወጣሉ!
ሚሊዮኖች ሲሰግዱ፥ ሚሊዮኖች ያጎነብሳሉ! ባለቃል-ኪዳን ኮከቦች ያበራሉ!
ሚሊዮኖች ሲያመሰግኑ ፥ ሚሊዮኖች ያወድሳሉ! ሚሊዮኖችም ይዘምራሉ!

ሁሉም መልዓክት የፈጣሪያቸው ባለሟል ናቸው! ከበላይ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በአግባቡ ይወጣሉ፡ ሁሉንም ያስገኘ እርሱ ሁሌም ከብር ይገባዋልና ያለማቋረጥ በመተናነስ ይታዘዙታል!

በሁሉም የአርያን ዘውታሪዎች ዘንድ መከባበርና ህብረት ይታያል:: የስልጣን ተዋረድ ብቻ ሳይሆን የስልጣንና ትግበራ ትክክለኛ ከፍፍልም ነግሷል:: እንደሌሎቹ መልዓክት ሁሉ ሳጥናኤልም ኃላፊነቱን እየተወጣ ነበር:: ስራው እንደሀገር አለቃ የመንግስተ-ሰማይን ኑሮ ማስተናበር ነበር:: እሱ ከስሩ ያሉትን ሲያስተናብር የሁሉም አስገኚ ደግሞ እሱን ይቆጣጠራል::

የሁሉም አስገኚ ፈጣሪ ሁሉንም መልዓክት ይገዛል:: የመልዓክቱ የመኖር አላማ ደግሞ አንድና አንድ ብቻ ነበር፤ እርሱን መታዘዝ! የላይኛው ካዘዛቸው ውጪ አንዳች አያፈነግጡም፤ ከቶውንም ማፈንገጥ የሚባለውን ተግባር አስበውት እንኳን አያውቁም:: እግዚአብሔር እንዲያውቁ ከፈቀደላቸው ውጪ አንድም እውቀት አልነበራቸውምና!

«ያ ቀን፤ ግን እውነትም ‹የተቀደሰ ስብሰባ ነበር!> ሰደደ አዛዝኤል፤ ያቺን ቀን በምሬት እያስታወሰ "አዎ የተቀደሰ ስብሰባ ነበር! ለኛ ግን የእርግማን ቀን!…

ያን ቀን፤ ቅድስና እና ሰላም ሰፍኖ ነበር!

ከሰው ልጅ በስተቀር አብዛኛዎቹ ተሰብሳቢዎች የእኔ ነው የሚሉት ገፅታ አልነበራቸውም:: መልዓክቱ በጊዜያዊነት እግዚአብሔር በለገሳቸው ቅርፅ ተገልፀው በወገን በወገናቸው በረድፍ ተሰልፈዋል:: ሲወርዱና ሲጎኑ፣ ሲገቡና ሲወጡ ክንፎቻቸው ከክንፎቻቸው ይሳበቃሉ:: በየስራ ክፍሉ አለቃ ሆነው የተሾሙት ሊቃነ-መልዓክቶች በየመስመሩ ላይ ከፊት ከፊት ቆመው ይታያሉ:: ከሁሉም በእውቀትና አመራር የበላይ መሪ ተደርጎ የተሾመው ሳጥናዔል በበኩሉ እንደ አጥቢያ ኮከብ ፍላፃው በሚያስፈራ ነበልባል አካሉ እያበራ ከአሳት ፍጥረታት (ጂን/ ኢጋንንት) ፊት ተደቅኗል:: ውበቱ ከሁሉም ፍጥረታት የላቀ፤ ስራቱም ከሁሉም የነጠረ ነበርና ግርማው ሌሎቹን ፍጥረታት በሙሉ ይስባል፣ ይማርካል... ቢያዩት ቢያዩት አይጠግቡትም፣ እሱም ይህ ውበቱ ኩራት በልቡ ፈጥሮበታል::

ሁሉም ቦታ ቦታውን ይዞ ቢገኝም የሁሉ ነገር ቀዳሚ ወጣኝና ባለቤት ግን ሊገለፅ አልፈቀደም ነበር:: ዝምታው የበዛበት ሳጥናኤል የበላይነቱ ሳግና ትዕቢት ሲተናነቀው ተስተዋለ:: ከዚህ በላይ ትዕግስቱ የለውም - አለቃና ታዛዥ እንጂ ጥሩ ባሪያና ታጋሽ ተደርጎ አልተፈጠረም ነበርና፤

*ስኑ-ግኒታው ኢጋንንትነቱ የወለዳቸው ጭንግፍ ቃላቶቹን መናገር ጀመረ..."ዛሬ ታላቅ ስብሰባን የጠራን አምላክ ከዚህ ያለ አይመስለኝም... እኔም ስገምት መገኘትን ሳይችል ቀርቶ... አልያም ጠፍቶ ይሆናል..." ከሰው ልጅ በስተቀር ሁሉም የቀጭን ድምፁን ሀቡዕ መልዕክት እየተረዳ ነበር፡፡ የሰው ልጅ ግን ገና የእውቀት አይኑ አልበራም ነበርና አምላክ ካስተማረው እውቀት ውጪ አንዳችም አይረዳም ነበር፡፡ (ኢሳ 14፡13)*

*"ጓድ ሳጥናኤል፣ ይህን ከእውነታ የራቀ ቅጥፈት አቁም! ኃያል አምላካችን አይጠፋም፡ የማይችለውም አንዳች ነገር የለም፡ ጌታችን ሁሉን ቻይና ዘላለማዊ ነው!" አለ - ታዛገፍ - የመልዕክት ተቀባይ፣ አውራጅና ተግባሪዎች ሊቃነ-መልዓክት ገብረ-ኤል (ጀባር - ኢል)፡*

*"አንተ ማን ሆነህ ነው ስለ ስርአተ-መለኮት የምታስተምረኝ?" ጠየቀ ሳጥናኤል፤*

*"እኔ ከእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ!" ሲል መለሰለት፡*

*ወድያው ሳጥናኤል በከፍተኛ ድምፅ "አሁን አውጃለሁ..." ሲል ተሰብሳቢዎቹ በሙሉ ወደ ሳጥናኤል ዞሩ- እሱም ኮራ ኮራ እያለ "ከዚህ ቅፅበት ጀምሮ የሁላችሁም የበላይ አለቃ እንደመሆኔ መጠን ከአሁን በኋላ መሪያችሁም ጌታችሁ..." ብሎ ንግግሩን ከመጨረሱ በፊት አይንን የሚያንጠባርር የብርሀን ፍንጣቂ ከአድማስ እስከ አድማስ ጎለመሰ፡ በከብሩ ብዛት፣ ፈጣሪ በራሱና በፍጥረቱ መካከል ያቆመው ታላቅ፡ ረቂቅ መለያ ግንብ ተሰነጠቀ፤ በዚህም አራቱ የጠፈር አውታራትም ከባድ የሆነ ንቅናቄ አናወጣቸው፤ ሰባቱ ሰማያትና ሰባቱ ምድሮች ተርበደበዱ፡ ሁሉም በፍርሀትና ድንጋጤ ተርበተበቱ፡ ምንም አይነት ምድራዊ መብረቅ የማይወከለው ነጎድጓዳዊ ድምፅ ወደነሱ መጣ...*

*"እነሆ ታላቅ ነኝ የሚል ማነው? እስኪ ከእናንተ መሀከል ለፍጥረታቱ በሙሉ ስምን መስጠት የሚችልስ ከቶ ማነው?... የበላይ ነኝ ባዩ ሳጥናኤል እስኪ ተናገር?" ሁሉም መልዐክት በዝምታ ወደ መሬት አዘቀዘቁ፡*

ሳጥናኤል መልሱን ባለማውቁ ፊቱ በሀፍረት ተሞልቶ አንነበሰ፡፡ ፈጣሪም "አዳም ሆይ ወደመንበሩ ውጣና ለሁሉም የፍጥረታትን ስም ንገራቸው" ሲል አዘዘው፡ አዳምም የታዘዘውን አደረገ፡ አምላኩ ፈቅዶ በለገሰው እውቀት መሰረት የፍጥረታትን ስሞች ዘረዘረ፡፡ ነገሮችን በሙሉ ልብ አንድ ባንድ ሲያሚ ሰጣቸው፡፡

"እኔ የማውቀውን እናንተ አታውቁም ብያችሁ አልነበረምን? እነሆ! ሁሉን የሰማያትና የምድርን ሚስጥር፣ ድብቅም ይሁን ግልፅ አዋቂውና ጠቢቡ እኔ ነኝ!" አለ የዘላለም አምላክ ኤሎሄ!
የጌታቸውን ክብር ለመመስከር ሳጥናኤልን ጨምሮ ሁሉም መልዓክት ወደ ድምፁ አቅጣጫ ሊሰግዱ ሲያጎነብሱ፤ ድምፁ አሁንም ወደ'ነሱ መጣ፤

"እነሆ ወደ አዳም ዙሩና ለ'ሱ ስገዱለት!" ሲልም አዘዛቸው፤ ሁሉም ሰገዱ፤ ዲያቢሎስና ጭፍሮቹ ግን ከእሳት ወገን ሲሆኑ ወገባቸው ሳይታጠፍ ቀረ፤ (መፅሐፈ-መቃብያን፤ ሣልስ ምዕ-1፥15) (› ሱረቱል-በቀራህ 2፤34)

"እሳት ለጭቃ አይሰግድም!" አለ ዲያቢሎስ በእብሪተኝነት፤

"አንተ እርጉም የማይገባህን ኩራት ኮርተሃልና ሂድ ውጣ! አንተ የተባረርክ የተዋረድክ ነህና!" ተባለ፤ እጅግ ሰቅጣጭ እርግማንም በትዕቢተኛው ዲያቢሎስ ላይ ወረደ፡፡ ከብሩ ተገፈፈ፤ ብርሀኑ ደበዘዘ፤ መንሳፈፊያው ረገበ… ወደታች ሲጣል የተረፈው ነገር ቢኖር የተጣመመ መሰሪ አውቀቱና ተሰልቦ ከፍተትን የሚሞላበት ሰላቢ ጥላው ነበር፡፡

"እባክህን ፈጣሪዬ አንድ ነገር ብቻ ፍቀድልኝ?" አለ ዲያቢሎስ፣ ከበታች ሆኖ በእልህና ፀፀት እየተቃጠለ፤
"ምን?" አለው፣ የልቡን የሚያውቀው እግዚአብሔር ለሁሉም ጥያቄው ይሰማ ዘንድ፤
"እስከመጨረሻዋ የፍርድ ቀን ድረስ ሳልሞት ከእነርሱ ጋር እንድቆይ አድርገኝ?"
"ፈቅጄልሃለሁኝ፤ እስከ መጨረሻዋ ቀን ድረስ አብረሃቸው ትኖራለህ፣ አትሞትምም!" አለው ሲጋሱና ታጋሹ ኤሎሄ!
"እሱን ከፈቀድክልኝ ዘንድ ለእነርሱ ብለህ እኔን እንደተውከኝ እኔም በበኩሌ እኔን በማጥመምህ ይሁንብኝ እነርሱን እየተከታተልኩኝ አሳስታቸዋለሁኝ፡፡ በሁሉም አቅጣጫ እየወሰወስኩኝ ከትክክለኛው መንገድ ወደከፋት እመራቸዋለሁኝ፣ አንተንም አመስጋኝ አይሆኑም፡፡ በእኔ ወጥመድ እየጣልኩኝ ከኔ ያነሱ መሆናቸውን አስመስክራለሁኝ!" አለ ሳጥናኤል፤

"እንግዲያውስ በአንተ ጭፍሮችና በእነዚያ አንተን በሚገዙት ሰዎች ገሃነምን እንደምሞላት እኔም ቃሌን አጸናለሁኝ፤ ለስሜቱ ተገዝቶ የተከተለህን እንጂ እነዚያ ፃድቅ ባሮቼን ግን ልታሳስት አይቻልህም፣ ስልጣኑም የለህም!" አለውና ውሉ በዚሁ አበቃ፡፡

*እነሆም አዳም በክብርና ተድላ በኤደን ገነት ውስጥ ይኖር ነበር:: ሁሉንም ነገር ጥንድ ጥንድ አድርጎ የሰራ አምላክም የአዳም ብቸኝነት መልካም እንዳልሆነ ተመለከተ:: ከባድ እንቅልፍንም ጣለበትና ከግራ ጎኑ አንዷቷን አጥንት መዞ ስፍራውን በስጋ ዘጋው:: እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት አጋሩ አድርጎ ሰራትና ወደአዳም አመጣት:: አዳምም አለ "ይህቺ አጥንትዋ ከአጥንቴ ናት፣ ሥጋዋም ከሥጋዬ ናት፣ እርሷ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል!" እንደዚሁ ሰው እናቱንና አባቱን ይተዋል፣ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም እንደ አንድ ስጋ ይሆናሉ::*

እግዚአብሔር አምላክም ለአደም አለው፤ "ሴይጣን ላንተ በእርግጥም ጠላትህ ነውና ተጠንቀቀው:: በገነት ውስጥ በደስታና በተድላ ኑር፣ ከእነዚያ ሁለት ዛፎች ፍሬ ግን እንዳትበላ፤ ፍሬውን በበላህ ጊዜ ሞትን ትሞታለኸና፣" ተባለ... አዳም አሜን ብሎ ተቀበለ. . . . .

እነሆ! የፍጥረታት ሁሉ የህይወት ዑደት ቀጠለ!

ከመንግስተ-ሰማይ መቅደስ፣ በየቅፅበቱ!

ሚሊዮኖች ሲገቡ ÷ ሚሊዮኖች ይወጣሉ!

ሚሊዮኖች ሲሰግዱ ÷ ሚሊዮኖች ያጎነብሳሉ! ባላቃል-ኪዳን ኮከቦች ያበራሉ!

ሚሊዮኖች ሲያመሰግኑ ÷ ሚሊዮኖች ያወድሳሉ !

*አዳምና ሄዋንም በእፁብ ደስታና ሰላም ውስጥ አብረው ይኖራሉ:: ፀሐይ አይመታቸው፣ ዝናብ አያበሰብሳቸው፣ ሳይጨነቁ፣ ለሚበሉትም ይሁን ለሚጠጡት ሳይለፉ፤ በአይነት በአይነቱ ይቀርብላቸዋል:: ሁለቱም እርቃናቸውን ነበር እንቅስቃሴያቸው፣ እንዳችም ሃፍረት ግን አልነበረባቸውም:: ከፉና ደጉን የሚለየው ልቦናቸው ተጋርዶላቸው ነበርና በማመስገንና በእምነት ነፃነትን ተጎናፅፈው ይኖራሉ:: እርቃናቸውን እንዳሻቸው እየፈነደቁ... (ዘፍ 2፤ 15-25)*

*** ቶ – ቶ ***

"ትዝ ይልሻል ያኔ ራቁታችንን ወንዝ ወርደን የተያዝን ጊዜ?" አለ ኢትኤል ከፅዮን ጋር ጅሬን ሆቴል በረንዳ ላይ ቁጭ ብለው ሳለ ራቆቱን ያለፈ እብድ ነበር የልጅነት ትዝታውን የቀሰቀሰበት:: እብዱ አላፊ አግዳሚውን ያስጨንቃል... ትዕይንቱ ፈገግ ያስብላል፤ በመንገዱ የሚያልፉ ሰዎችም እያዩት ወይ ስቀው ወይ ፈርተው ሲያልፉ ሌሎች ተጓዦች ደግሞ ይተካሉ::

እልፍ ተራማጆች ይተራመሳሉ! መተራመሳቸውን የሚያውቁት ግን ከአንድ በረንዳ ወይም ስገነት ላይ በስክነት ቁጭ ብለው ትርምስምሱን ማስተዋል የቻሉ ቀን ብቻ ነው።

ኢትኤል በጥዋቱ ከጅሬን ሆቴል በረንዳ ላይ ቁጭ ብሎ የህዝበ-አዳምን ትርምስምስ አስተውሏል! «ዘንቢሏን በእጇ፣ ህፃን ልጇን በጀርባዋ ያዘለች እናት፤ የተቃቀፉ ባለዩኒፎርም ወንዶች፣ ፎቅ የሚያህል ሸክም የተሸከመ ሰርቶ-በላ፤ የላፕቶፕ ቦርሳ ያነገተ የግቢ ተማሪ፤ ከንዷ ላይ መስቀል የተነቀሰች ኮረዳ ውጥርጥር ያለ የቻይና ሱሪ ለብሳ፤ ባለፌስታል ወይዛዝርቶች፤ ኢማማ አገልዳሚዎች፣ ሂጃብ ጠምጣሚዎች፤ በእግር እየተራመዱ ጤና ጠባቂ ሽማግሌዎች… ይተረማመሳሉ! ትንሽ ራቅ ብሎ ትንንሽ ባጃጆች… ባለሶስት ጎማ ተሽሎክላኪዎች፤ ከላይ ደመናማ ነጭ ቀለም ከስር ሰማያዊ ተቀብተው የሰማይ ሳጥኖች የመሰሉ ነፍ ታክሲዎች ህብረ-ትርኢት ሲያቀርቡ፤ የሲፋን ነጠብጣብ፤ ባለ ራቫ-4፣ ቪ-8፣ ባለማርሴዲሱ፣ የጊዜው ባለዙፋን፣ ባለባዶ እግሩን ሎተሪ አዟሪ ተገላምጦ ይነዳል… እስኪያልፍ ድረስ በምቾት ይጋልባል! የሞተር አከተሮች በመሃል በመሃል ከንፍ ብለው እየመጡ ትርዒቱን ያደማምቁታል።

ሞተር የሳታቸው ደንባራ አሮጊት ይራገማሉ። በአንዳንዶቹ ሞተሮች ጀርባ ላይ ተደርበው የተጫኑ ሰዎች ደግሞ "እኔም ሞተር መንዳት እችላለሁኝ" በሚመስል ሁኔታ ዘና ብለው ለመታየት ይሞክራሉ። ወድያው ኩርባና መደረብ ሲመጣ ተቆጣጣሪ አለመሆናቸው ይታወሳቸውና የሞተሩን ጭራ ጥብቅ አድርገው ይይዛሉ… እንዳይወድቁ።» ኢትኤል ስቆ ይዞራል፤ «…3 ቅንጡ ወጣት ሴቶች እጅግ የዘነጡ፤ እጅ ለእጅ ተጠላልፈው እየተሳሳቁ፤ ፀሐይ ሳትበረታ ደመናም ሳይወርድ ዣንጥላ ያሰፋሉ። ነጠላ የለበሱ፤ እንገት ደፊዎቹ፤ በዝምታ መጥተው ደግሞ ይተካሉ። ከዚያም ትመጣለች ፊቷን የሸፈነች በጥቁር ኒቃሟ… ኢትኤል ያስተውላል፤ ፀጉሩን የሚጠቀልል ደረታም ፍንዳታ በተራው ይተካል… መሬትን መርገጥ ተጠይፎ እየዘለለ ያልፋል። ከኋላው በ30ዎቹ መባቻ ላይ የሚገመቱ ወፋፍራም ሴቶች እስከጉልበታቸው የሚደርሱ ቀሚሶችን ለብሰው፣ ረጃጅም ቡትስ (ቄንጠኛ ቦቲ) አድርገው እያወሩ በእርጋታ ይራመዳሉ… ይተራመሳሉ። ሜካፕ ያጎለመሳቸው ባለቅንጡ መኪና አሮጊት ሰላም ብለዋቸው ያልፋሉ።» የጫት ገረባ ያቀፈ፣ ባዶ እግሩ የተጋለጠ፤ የድሮ ደፉ ማድቤት ውስጥ የሚኖር የሚመስል አንድ ራቁታም ወፈፌ ሁሉንም ተራማጅና ነጂ በንቀት እያየ መሃል አስፓልት ላይ ይንጎራደዳል። እንደ ወልዩ ከድር ስተቴ ቅኔ መቀኘቱ ባይሆንለትም ወቀሳውን ግን ለጉድ ያዘንበዋል።

"ሌባ ሁላ!... ቆሞ ሲሄድ ሰው መሳይ... ሌ... ሌባ ሁላ!" እያለ ይጮኻል... "ሌባ ሁላ!... ልብስ የሸፈነው ጉደኛ ሁላ!" ይልና ዘሎ የመኪና ጎማ ስር ይገባል:: ታክሲዋን በግድ ሲጢጢ...ጥጥ አድርጎ ያቆመለት ሹፌር መስኮት ጋር ሄዶ... "ግጨኛ ወንድ ከሆንክ?!... ፈሪ! ሌባ ሁላ!" እያለ ይወራጫል:: የታክሲው ሹፌርም እብዱን ሳይሆን የእብዱን እናት ተሳድቦ፣ የመጫኛ ተራው ስላለፈው ተናዶ ያልፋል::

*** ፆ - ፆ ***

"ምነው ትዝ አይልሽም እንዴ ራቁታችንን ወንዝ ወርደን የተያዝንበት ቀን?" አላት ኢትኤል፣ ፅዮን ጥያቄውን ሳትመልስ ብትቆይበት፣

"አይ አይደለም... እብድ እንደምፈራ ታውቅ የለ? ሰውዬውን ገርሞኝ እያየሁት ነበር እንጂ ጀርባዬ እስኪላጥ የተገረፍኩበትን ቀንማ እንዴት እረሳዋለሁኝ ብለህ ነው ኢታዬ?" አለች በስሱ ፈገግ ብላ፣ ከፊቷ የተቀመጠውን ቡና በዝግታ እያማሰለች፣

"ያኔ እኮ ስታለቅሺ ድምፅሽ እኛ ቤት ድረስ ይሰማ ነበር:: ባይገርምሽ እኔን እኮ እነማዘር ብዙም አልተቆጡኝም:: ግን..." አለ ኢትኤል እሱም ፈገግ እያለ "ግን ያን ቀን እኔም አልቅሼ ነበር::"

"ካልተገረፍክ ለምን አለቀስክ?"

"ያንቺን አሳዛኝ ለቅሶ ስሰማ በጣም ነበር የደበረኝ፣ እልህ ሲተናነቀኝ ከነማዘር ተደብቄ አለቀስኩኝ::" አለ ኢትኤል በትዝታ እንደተዋጠ፣

"ወይኔ! የኔ ምስኪን ኢታዬ... የኔ ሆደ-ቡቡ!" አለች፣ ጉንጩን በጣቷ ነካ አድርጋ እየሳቀች:: ፅዮን ብዙ አትስቅም:: ከስንት አንዴ እንዲህ ኢትኤልን አግኝታ የልጅነት ትዝታቸውን ሲያወሩ ግን ጥርሷን አትከድንም:: እንደህፃን ልጅ ትፍለቀለቃለች:: ከልጅነቷም ጎላ ጎላ ብለው እንደ በሎቄ የተከረቡት አይኖቿ አሁንም ያ ፍካታቸውን አላጡም:: አሁንም ገፅታዋ ላይ ያ የድሮ ሰላሟ ይነበባል:: ልብ ብሎ ላየው ፊቷ የቸኮሌት ቀለም የተቀባ እንቁላል ይመስላል:: ከነጠላ የተረፈው የሹሩባዋ ረድፍ በጥቂቱም ቢሆን ተጋልጦ ይታያል:: የጉንጉኖቿ ፊተኛ ስድሮች እኩል የሆነ አግድም መስመር ከግንባሯ ላይ ይፈጥራሉ... ቸኮሌት ፊቷን አካበውም ልዩ የሆነ መስብ ይሰጧታል... በተለምዶ ወንዶች ለፀጉራቸው ቅርፅ ማስወጣት እንደሚሉት ሁሉ እሷን ተፈጥሮ ካለእንከን ቅርፅ አውጥታላታለች! ብዙ ጊዜ የምታዘወትረው ግራጫማ ቀሚስ እስከጉልበቷ ቢሸፍናትም ከጉልበቷ በታች

ያለው ባትና ተረከዟ ልዩ መስህብ አለው:: ከስር ዙሪያውን በጥንቃቄ ስውር የተሰፋው ሽራ ጫማ ቢያረጅም ውብ ባቷን ትቶ የሱን ማርጀት የሚያይለት አንድም ሰው አላገኘም ነበር::

"ባከሽ ሆደ-ቡቡ ሆኗ አይደለም፣ በጣም ነበር እኮ የምወድሽ ፂያ … አይ የልጅነት ነገር?!" አለ የድሮ ስራውን እስተውሶ በመገረም፤

"ማነው አንተ ብቻ ነበር የምትወደኝ ያለው?… ያኔ ትዝ አይልህም? 5ኛ ነው 6ኛ ክፍል ሆነን የታመምከ ጊዜ?"

"ትዝ ይለኛል! ብዙ የቤት ስራዎቼን ስሪልኝ ብዬ የሰጠሁሽ ጊዜ አይደል?"

"አዎ! … ያኔም እኮ ተገርፌያለሁኝ!" ተቅለሰለሰች… አይኖቿ አይኖቹን ለመተው አሻፈረኝ ያሉ ይመስላሉ፤ ስታወራም፣ ሲያወራም አይኖቿ አይኖቹን ማገት አልተዉም ነበር::

"ማ?… ማዘርሽ ናት የገረፈችሽ?"

"ኖ… ትምህርት ቤት ነው እንጂ የተገረፍኩት"

"ለምን?"

"ያንተን የቤት ስራዎች የሰራሁት እኮ የራሴን የቤት ስራ ትቼ ነበር፤" አለች ይብልጥ ቀና ብላ እያየችው፤

"እውይ የኔ እናት!" ብሎ ሳቀና የእጆቿን መዳፎች ያዛቸው:: የሰራ አካላቷን የሆነ ነገር ነዘራት፤ ልቧ እንደ ቀነኒሳ ጠንካራ የታፋ ጡንቻዎች የመጨረሻ ዙር ግልቢያ ሲፈጥን፤ ሪባኑን ሊበጥስ ሲሽመጥጥ ይታወቃታል::

"ልንገረው እንዴ?" ራሷን ጠየቀች፤ "ግን ይሄ ስሜት በእሱም በኩል ባይኖርና ቢጣላኝስ?… ፍቅሬን ልግለፅ ብዬ የእድሜ ልክ አብሮ አደግ ጓደኛዬን… ከጓደኛም በላይ ወንድም የሆነኝን ሰው ባጣውስ?" ልቧን ፍርሃት ገባው፤

"አይ አይሆንም!..የራሴ ጭንቀት ለራሴው ይቅር፤ ደብቆ መያዙ ይሻለኛል::"

"ኢታ…" ብላ ጠራችው፤…"ወዬ"

"በጣም ጨንቆኛል"

"ምነው?"

"ጋሼን አሞታል!"… እንደመተከዝ እያለች፤ እውነቱ ግን የውስጧን ሃሳብ ትታ ሌላ ወሬ ለመጀመር የፈጠረችው ርዕስ ነበር፤ እንጂማ የአባቷ የጋሽ ጀምበሬ መታመም አስራ አምስት አመታትን ያስቆጠረ፣ የተለመደ እውነታ እንጂ አዲስ ነገር አልነበረም::

"ምነው በጣም በረታባቸው እንዴ?"
"ይመስለኛል!" አለች በቸልተኝነት፤

መልሷ አጥጋቢ ባይሆንለትም ለማፅናናት ያህል ሁለት እጆቿን ይበልጥ ጥብቅ አድርጎ ያዛቸው፤ ጣቶቿን ነጣጥሎ አሻቸው:: አሁንም እንደቅድሙ ልቧ እንደቀነኒሳ ፈርጣማ እግር ጡንቻዎች ግልቢያ ሲፈጥን ይታወቃታል:: ጣቶቿን ሲያሻቸውማ የልቧ ፍጥነት እንደምሩፅ ማርሹን ቀየረ፤ ልክ የመጨረሻው ዙር ደውል የተደወለ ይመስል፤ ሽመጠጠ… የመጨረሻው መስመር ጋር ደርሶ አልፎ ልቧ የማሸነፊያውን ገመድ ከበጠሰ ቀጥ ብሎ መቆሙ ነው…… ራሷን አረጋጋች::

"እና በተረፈ ምን አዲስ ነገር አለ?… ከላስ እንዴት ይዞሃል?"
"አሪፍ ነው፤ ግን ባክሽ ይሄ ዶ/ር እሳቱ የሚባል ሰው አዛ እያደረገኝ ነው::"
"ውይ እሱ ሰውማ እኛንም የዛሬ ዓመት አሳራችንን አብልቶን ነበር፤ በምን ተገናኘታችሁ ነው?"
"ኧረ ምንም አላጠፋሁም፤ በቀደም እለት ደከሞኝ ከኋላ ቆሜ አይቶኝ ነው::"
"ብዙም አትጨናነቅ፤ በደንብ አንብብና የሚጠይቅህን ነገር በሙሉ ከመለስክለት ትታረቃላችሁ:: እኔ የምልህ አብርሽስ ደህና ነው? ቤተ ክርስቲያን ካየሁት ቆየሁኝ፤"
"ሰላም ነው ባክሽ እሱ ምን ይሆናል ብለሽ ነው…"
"ሰላም በልልኝ!… እ…እንሂድ አይደል ኢታ?… ቤተ-ክርስቲያን ተሳልሜ ወደዶርም መሄድ አለብኝ፤ ከሰዓት ሴሚናር አለን፤" አለች፤ እጇን ከጣቶቹ መካከል ምዝዝ አድርጋ እያወጣች::
"አዎ! የእኔም የዋርድ ሰዓት ደርሷል!" አለ ኢትኤልም፤

"እሺ ግን ከመውጣታችን በፊት አዲስ ግጥም ፅፈህ ከሆነ አንብብልኝ?" አለችው ፈገግ ብላ፤ ስልኩን አወጣና አንዲቷን አጭር ግጥሙን ከፈተ "ባይገርምሽ ላንቺ ነው የፃፍኩት፤" ብሎ አያት፤ ፈገግ አለች፤ ማንበቡን ጀመረ…

## «በሳቅ ፍሰሽልኝ፤

*እንደውሃው ጠበል - ነፍሰችን ሊያረካ፣*
*ሳር ምድሩ ያምራል - ያንቺ ፊት ሲፈካ፣*
*ፈገግታሽ አልፎ ነው ጥሜን ሚያርሰልኝ፣*
*ደስ... ደስ... ይበለሽ ህይወት ኢድሽልኝ፣*
*ሌላው ሁሉ ይቅር በሳቅ ፍሰሽልኝ።*

... በሳቅ ፍሰሺ ቢላትም ግጥሙ ግን ለፅዮን የሐዘን ስሜት ነበር የፈጠረባት፤ ይህን ስሜቷንም እንዳያይ ስልክ የተደወለላት አስመስላ ቀድማው ወጣች፤ እሱም አስተናጋጇን ጠራትና ሂሳባቸውን ከፍሎ ተከትሏት ወጣ። ከትርምስምሱ ዘው ብለው ገቡ። ለመሸኘት ያክል ትንሽ መንገድ አብሯት ተጓዘና ተቃቅፈው ተሰነባበቱ፤... ልትሄድ ስትል ግን"ፂያ?" ብሎ ጠራት እጁን ኪሱ ውስጥ እየከተተ፤ አይኗን አደራርጋ "ወዬ፤" ብላ ስትመለስ ከኪሱ ጥቂት የመቶ ብር ኖቶችን አውጥቶ ሰጣት።

"ምን ያደርጋል ይሄ ሁሉ?" አለችው ደስታዋን መደበቅ እጅግ እየተሳናት፤

"አዲስ ጫማ ግዢበት፤"

ብትከራከርም የሰጣትን ብር መልሶ እንደማይቀበላት ስለምታውቅ እቅፍ አድርጋ አመሰገነችው። ብሩን እንደያዘች ተሰናብታው ስትሄድ አይኗ በድጋሚ በእንባ ተሞልቶ ነበር። ወደ ኪዳነ-ምህረት የሚያስገባ የ‹ኮብል ስቶን› ቁልቁለት መንገድ እየተንደረደረች ስትወርድ ልቧን አስፓልት ዳር የቆመው ኢትኤል ጋር ጥላው ነበር። እሱ በበኩል ከበላይ ቆሞ ቁልቁል ምትወርደውን የልጅነት ጓዱን እያየ ውስጡ በተለያዩ ስሜቶች ሲደበላለቅ ይታወቀዋል።

ለዲታ ቤተሰቦቹ ብቸኛ ልጅ ነው። እህትም ወንድምም ባይኖረውም ፅዮን ግን ነፍስ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ልዩ እህት ሆናዋለች። በጣም ይወዳታል... ፈፅሞ ሊያጣት አይፈልግም። 12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናውን ሲጨርስ ቤተሰቦቹ በወር ብዙ ሺህ ብር የሚከፈልበት የግል ኮሌጅ እናስተምርህ ሲሉት እምቢ ብሎ፤ ጅማ ዩንቨርሲቲን መርጦ ሞልቶ ከመጣባቸው ምክንያቶች መካከል ዋነኛዋ አንድ አመት ቀድማው ጅማ ዩንቨርስቲ የገባችው ፅዮን ስትሆን ሌላዋ ደግሞ ጅማ ያለችው የሚወዳት አክስቱ ነች።

በሃሳብ እንደተዋጠ ቀና ቢል ፅዮን የተወሰነ መንገድ ወርዳ፤ ካንድ የኔ ቢጤ ፊት ቆማ ቦርሳዋን ስትከፍት አያት። ቀጥላም ከቦርሳዋ ውስጥ አንድ

ረጅም ዳቦ አውጥታ ለነዳያኑ ሽማግሌ ሰጠችው፤ የካፌ ምግብ ላይ ለተማሪው የሚሰጥ ዳቦ እንደሆነ አውቋል:: ከፍሬሽ ጀምሮ እንደሚያውቃት ፅዮን የካፌ ቁርስ ሩዝ በዳቦ በሚሆንባቸው ቀናት ሩዙን በማንኪያ በልታ ዳቦውን ግቢው አካባቢ ለሚቀመጡ የኔቢጤዎች ትለግሳለች:: ምን ያህል ታታሪና ደግ… በድህነቷም ውስጥ ለጋስ መሆኗን ቆም ብሎ ሲያስበው በእሱም አይኖች ውስጥ እንባ ግጥም አለ::

በረጅሙ ተነፈሰና ሰዓቱን ሲመለከት፣ ለዋርድ 30 ደቂቃ ይቀረዋል:: ሰአቱን ሊያይ ጎንበስ ባለበት የጫማውን አቧራ መልበስም አስተውሏል:: ዙሪያውን ሲያማትር በቅርብ ርቀት ላይ ከተደረደሩት ሊስትሮዎች መካከል ብቸኛ ሊስትሮ ለየና ሄዶ እፊቱ ተቀመጠ::

“እስኪ አሳምሪው…” አለው፤ በአዛዥነት ሳይሆን በወዳጅነት ለዛ::

ሊስትሮውም “ስራችን ነው!” አለ በግነት:: በትንሽዬ ባልዲ የተሞላ ውሃ ውስጥ ስፖንጁን ነክሮ አወጣና በሳሙና አሸት አሸት አድርጎ ጫማውን መወልወል ጀመረ:: ኢትኤል ቁልቁል ሊስትሮውን ልጅ አስተዋለው:: በአስራዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ፣ ከሌሎቹ ሊስትሮዎች በተለየ ጥሩ የሚባል ጫማ ያደረገ፣ ከስር የለበሰው ቡናማ ከሬሸን ዩኒፎርም ሱሪ ደግሞ ጥዋት ጥዋት እየሰራ በፈረቃ ከሰዓት እንደሚማር የሚያሳብቅበት፣ ጎንበስ ብሎ ቢሰራም ነገ ቀና እንደሚል ባለሙሉ ተስፋ ብላቴና እንደሆነ ያስታውቃል:: “ትማራለህ?” አለው ኢትኤል ዝምታውን ለመስበር ያህል፤

“አዎ” መለሰ ልጁ… እንዳቀረቀረ፤
“ስንተኛ ክፍል ነህ?”
“ስምንተኛ”
“እንዴ ሚኒስትሪ ተፈታኝ ነሻ!… እያጠናህ ነው?”
“አዎ ማታ ማታ አጠናለሁኝ”
“የት/ቤት ወጪ ማነው የሚሸፍንልህ?”
“ራሴ ነኝ!”
“ልብስና ጫማም ራስህ ነህ የምትገዛው?”
“አዎዋ”… ለኢትኤል የልጁ መልስ ሌላ ጥያቄን ፈጥሮበታል:: ከልጁ አጠገብ ያሉት አራት ሊስትሮዎች በሙሉ የቆሸሸ ልብስና የተቀደደ አልያም

የተላላጠ ጫማ ነው ያደረጉት፡፡ "እንዴት ከእናንተ ተለይቶ እሱ ዘነጠ?" ብሎ ከልጁ አጠገብ ያለውን ሊስትሮ እንደ ቀልድ ጠየቀው፤

"ይሄማ መርዝ ቋጣሪ ስለሆነ ነዋ!" አለ ሊስትሮውም፤ ወደ ሌሎቹ ሊስትሮዎች ዞሮ እየሳቀ... እነርሱም አጀቡት፡፡

"አይ እንዳንተ ብሬን በጆተኒና ፑል ቁማር ልጨርስ? ወይስ ሳይከል በሰዓት እየተከራየው ስነዳ ልዋል?" አለ የኢትኤል ሊስትሮ፤

ሌላኛው ሊስትሮ የረባ ምላሽ እንደሌለው በሚያስነቃ መልኩ ቱግ ብሎ አጠያፊ ስድቦችን ሰደበውና ዝም አለ፡፡ ኢትኤል በበኩሉ ለተፈጠረበት ጥያቄ ጥሩ ምላሽ አግኝቶ ነበር፡፡ ወድያውም ከአስፓልቱ ባሻገር በጥቂት ቤቶች ልዩነት ከአምስት በላይ ፑል ቤቶችና 2 ጆተኒዎች እንዳሉ አስተዋለ፡፡ በፑል ቤቶቹ መካከል ሁለት ግሮሰሪዎችና በሆቴል ሽፋን የሚሰሩ ሺሻ ቤቶችም አሉ፡፡ ታዳጊው ወጣት ለመለወጥ ቢለፋ እንኳን በየደረጃው፣ በአካልም ይሁን በኢኮኖሚ እንዳያድግ ብዙ እክሎች እንዳሉበት መረዳት አላዳገተውም ነበር፡፡... በዚህ ሃሳብ ውስጥ እንዳለ ድንገት ከቅርብ ርቀት ላይ ኡኡታ ቀለጠ፤ "ኡ!... ኡ!... ኡ!..."

"ኡ! ኡ! ኡ!" ቀወጡት አንዷት ሴትዮ፣ ነጠላቸውን ሸቅብ እንደ ፓራሹት አንሳፈው ወደ መሬት በአፍጢማቸው እየተደፉ፡፡ ኢትኤል እና የ8ኛ ክፍል ተማሪውን ታታሪ ሊስትሮ ጨምሮ ሁሉም ትኩረታቸውን ወደ ከሰቶቱ አደረጉ... "ኡ! ኡ! ኡ! ኧረ የሰው ያለ ድረሱልኝ!" በጩኸት ወከቡት፤ ሰፈሩን ረበሹት! "ያዙልኝ... ያዙልኝ... ያዙልኝ... ተዘረፍኩኝ!!!"

"ያውና ሌባው!" አለ አንዱ ሽምገል ያለ መንገደኛ ሰው፤ ሌባ ጣቱን ወደ አንድ ወጣት ቀስሮ፡፡ ወጣቱ መሮጥ ጀመረ፡፡ ኢትኤል ወጣቱን አየው፤ ፀጉሩን ያንጨፈረረ፣ አለባበሱም የተጎሳቆለ ልጅ እግር ነበር፡፡

"ሌባ! ሌባ! ያዙት!" ለፈፈ አዛውንቱ፤ ለሁሉም ነጋሪቱን ጎሸመ፤

"ያዘው... ያዘው!" እያሉ አዋጁን አስተጋቡ በአካባቢው የሚገኙ ጎረምሳዎች፤ "ቁም! አንተን ነው አትቆምም?" አስጠነቀቀ፤ ግርግሩን አይቶ በፍጥነት የመጣው ፖሊስ......ከሰኮንዶች የሰዶ ማሳደድ ድራማ በኋላ ልጁ በገዛ ፍቃዱ ቆመና ተያዘ! የሚወርድበትን ዱላ ቢያውቅ ኖሮ ባልተያዘ ነበር፡፡ ቡጢዎች ዘነቡበት፡፡ "ኧረ በማርያም እኔ አይደለሁም፤ ለምን አታምኑኝም?" ይማፀናል ተያዡ፤ ዱላው አስጨንቆት...

"ውሸታም ላቦሮ! ታድያ ምን አባትህ ያስፈረጥጥሃል?"

"ሰውዬው ሌባ ብለው ወደ'ኔ ሲመጡ ደንግጬ ነው… በማርያም ልቀቁኝ?"

"ውሸቱን ነው እንዳትለቀው!… እናቱን… በለው! በለው!" ያበረታታሉ በአካባቢው የሚገኙ ወጣቶች፤ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሌባ ተብዬው ላይ የምት አይነት እያሳረፉ:: ፖሊሱ ልጁን እየገፈተረ ተሰርቃለች የተባለቸው አሮጊት የወደቀችበት ቦታ ይዞት እየሄደበት በነበረበት ቅፅበት የአካባቢው ትናንሽ ልጆች አንድም ሳይቀሩ ግልብጥ ብለው ፈሰው መንገዱን ወረሩት::

"ሌሌሌ…ባ! ሌሌሌ…ባ! ሌሌሌ…ባ!" በሚል ዜማ እዘል የጋራ ማላዘን በድብደባ የተዳከመውን ወጣት ከኋላ እየተከተሉ አጀቡት::

አጀቡ እርሳቸው ጋር ሲደርስ፤ ሴትዮዋ "የት አባህ! አንተ ቦዘኔ!" እያሉ በፖሊሱ የፍጥኝ ተይዞ የመጣውን ወጣት ለመጠፍጠፍ ነጠላ ጫማቸውን ታጥቀው፤ በደረታቸው ከተዘረሩበት አቧራ እንደለበሱ ብድግ አሉ:: ተነስተው ሲያበቁ ግን ትንሽ ወደ ተደብዳቢው ወጣት ጠጋ ብለው አይኖቻቸውን እያቅበዘበዙ ግራ እንደ ተጋባ ሰው ተገትረው ቀሩ:: ነጠላ ጫማቸውንም ወደመሬቱ ጣል አድርገው በዝግታ ተጫሙት:: ኢትኤል ለመበቀል ጎምጅቶ የነበረው ንዴታቸው ሲበርድ በግልፅ ተመልክቷል:: ቀሚሳቸውን አራገፉና እልፍ ብለው ለፖሊሱ አንድ ነገር ሹክ አሉት:: ፖሊሱ ልጁን ለቀቀውና ከሴትዮዋ ጋር አብሮ ሄደ:: ምን እንደተፈጠረ ስላልገባው ወሬውን ሊያጣራ ቅድም የተሳደበው ሊስትሮ ተነስቶ ሄደ:: ከአፍታ በኋላም ሪፖርቱን አጠናቅሮ ተመለሰና አነበነበ::

በሪፖርቱ መሰረት ሴትዮዋ የተወሰደባቸው የሞባይል ቀፎ ነበር:: ላቦሮው ግን ያለ ጥፋቱ የተወገረው ወጣት ሳይሆን አንዴ ስልክ አስደውሉኝ ብሎ የተቀበላቸው የዘነጠ መላጣ ጎልማሳ ነበር:: አዛውንቱ ሰውዬ የወጣቱን ሌባነት የወሰኑት ከኮስማና አለባበሱና ጨፍራራ ፀጉር በመነሳት ብቻ ነበር:: ምስኪኑ ልጅም ያለ ሀጥያቱ የዱላ መዓት ተቀብሏል::

"አይ ይሄ ትውልድ!… መከራው መብዛቱ! ግን መቼ ይሆን? መፅሀፍ በሽፋኑ እንደማይለካ ሁሉ ሰውን በአለባበሱና ገፅታው መመዘን የምናቆመው?"… ሲል ኢትኤል ከራሱ ጀምሮ ሁሉንም ታዘበ:: ሰዓቱ ደርሶ ስለነበር ለሊስትሮው ቲፕ ጨምሮ ሰጠውና እንዳይረፍድበት ባጃጅ ተኮናትሮ ወደ ጅማ ሆስፒታል ገሰገሰ::

*** ዯ – ዯ ***

ኢትኤል ዋርድ እንደደረሰ የተመደበበት አልጋ ላይ የተኛችውን ህፃን የጥዋት የልብ ምትና አተነፋፈስ በደቂቃ ቆጥሮ ፃፈ፤ የሰውነት ሙቀቷንም ለከቶ መዘገበ፡፡ ቀጣዩ ስራው የደም ግፊቷን መለካት ነው፡፡ ለእሷ ትንሽ እጅ የሚበቃ የደም-ግፊት መለኪያ (Sphingomyometer) ለመቀበል ወደነርሶቹ ቢሮ መሄድ ነበረበት፡፡ ልክ ከዋርዱ በር ሲወጣ ዶ/ር ሳሙኤል የእለቱን ዙር ለመምራት ሲመጣ በቅርብ ርቀት አየው፤ የደም ግፊት ለመለካት በቂ ጊዜ እንደሌለውም ተገነዘበ፡፡ ተመልሶ ገባና ሌሎች ተማሪዎች ጋር ተቀላቀለ፡፡ የዛሬውን ራውንድ የሚመራው ዶ/ር እሳቱ አለመሆኑ ግን ትልቅ እፎይታን ሰጥቶታል፡፡ ከዶ/ር እሳቱ ተቃራኒ ሊባል የሚችል ባህሪ ያለው ዶ/ር ሳሙኤል ረጋ ያለና ቁጥብ ሰው ነው፡፡ በእርግጥ ከበሽተኛው የጤና ችግር ጋር ብዙም የማይያያዙ ነገሮችን እያወራ ጊዜ ይፈጃል ተብሎ ይታማል፡፡ በተለይ ከሃገር በቀል ህክምናዎች ጋር የተያያዙ ነገሮችን ማውራትም መለያው ነው፡፡

ዶ/ር ሳሙኤል ወደዋርድ ገብቶ የመጀመሪያ ታካሚው አልጋ ጎን ሲቆም ሁሉም ተማሪዎች፣ እጩ ዶክተሮችና ሬዝደንቶች መጥተው ዙሪያውን ከበውት ቆሙ፡፡ ፊሽካ ባይነፋም ራውንዱ ተጀመረ ማለት ነው፡፡

"ከተማሪዎች መካከል ይሄ የማን አልጋ ነው?" አለ ዶ/ር ሳሙኤል ከበሽተኛው ላይ ሙሉ ትኩረቱን አድርጎ እየመረመረው፤

"የእኔ ነው!" አለ አብርሃም… ወረቀቱን ከፍቶ የበሽተኛውን የጤና ታሪክና የምርመራ ግኝት ሊያቀርብ እየተሰናዳ፤

"እሺ ቀጥል!"… አብርሃም እርጋታና እውቀት በተሞላበት ሁኔታ የበሽተኛውን ሙሉ መረጃዎች ለሁሉም አነበነበ፡፡ ዶ/ር ሳሙኤልም "ጥሩ ነው" ብሎ አሞገሰውና አንዳንድ ጥያቄዎችን ጠይቆት ወደሬዝደንቶቹ ዞረ፡፡ ታካሚው አሁን ያለበትን ደረጃ ጠየቃቸው፡፡ እነርሱም ብዙም ለውጥ እያሳየ አለመሆኑን ስለነገሩት ከበፊቱ ጠንከር ያለ መድሃኒት እንዲቀየር አዘዘና ወደ ሁለተኛው ታካሚ አለፈ፡፡

ሁለተኛው አልጋ ላይም ሙሉ ትኩረቱን በለጋነቱ የስኳር በሽተኛ የሆነው ድንቡሽዬ ልጅ ላይ አድርጎ ከመረመረው በኋላ "ከተማሪዎች የማን አልጋ ነው?" ብሎ ቀና አለ፡፡ በደሙ ውስጥ ያለው የስኳር መጠን እጅግ ከፍ በማለቱ ራሱን ስቶ በሽክም የመጣ ልጅ አሁን ዘና ብሎ ሲስቅና ሲጫወት ማየት የመልካም ህክምናን መልካም ፍሬ በተግባር ይመሰክራል፡፡ "የእኔ ነው!" አለች ቦንቱ ወደ ዶ/ር ሳሙኤል ጠጋ እያለች፤

*"Have you assessed any risk factors?* (ለዚህ በሽታ ያጋለጠውን ነገር ለይተሽ አውቀሻል?)" ብሎ ጠየቃት፤

*"Yes, his aunt is a known diabetic patient and I believe it is inherited.* (አዎ፣ አክስቱም የስኳር በሽተኛ ስለሆነች በዘር የወረሰው ይመስለኛል፡፡)"

*"Okay...Have you tried to access other risk factors?* (እሺ ግን ሌላ ምክንያቶቹን ለማጣራት ሞክረሻል?)"...

ቦንቱ ሌላ ምክንያት ማከል አልቻለችም፡፡

"Have you accessed his nutritional history properly? (የአመጋገብ ሁኔታውን በትክክል ለማጣራት ሞክረሻል?)"

ቦንቱ በዝምታ ተውጣ ጣሪያ ጣሪያውን ማየት ጀመረች፡፡ የልጁን የአመጋገብ ሁኔታ በደንብ እንዳልጠየቀች ግልፅ ነበር፡፡

"አትጨናነቂ ማነሽ... እምም ቦንቱ... ለምን ጠይቀሻል እንዳልኩሽ ገብቶሻል?... አሁን የ‹ፔሽንቱ ኮንዲሽን› (የታካሚው ሁኔታ) እንደምታዪው እየተሻሻለ ይገኛል፡፡ ይሄን ልጅ ከአንድ ሁለት ቀናት በኋላ ወደቤቱ ስለምንልከው እሱና ቤተሰቡን የምንመከረውን ነገር ማወቅ አለብን፡፡ እስኪ ሲወጣ አንቺ ብትሆኚ ምን ምን እንደምትመከሪው ንገሪኝ?" አላት በአማርኛ፤

ትንሽ አሰብ አደረገችና "መድሀኒቱን በአግባቡና በጊዜው እንዲወስድ፣ አመጋገቡን እንዲያስተካከል ማለትም ጣፋጭ እንዲቀንስ፣ ጮማና መሰል ቅባታማ ምግቦችን እንዲያቆም እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንዲያደርግ እመከረዋለሁኝ፡፡"

"ጥሩ ነው፡፡ እኛ ዶክተሮች የእያንዳንዱ ታካሚያችን አመጋገብ ላይ ትልቅ ቦታ ሰጥተን መምከር አለብን፡፡" አለ ረገጥ አድርጎ! "የድሮ ጠበብቶች ‹የሰው ልጅ የሚበላውን ነገር ይመስላል› ይላሉ፡፡ ‹አመጋገብ ማለት በየቀኑ የሚወሰድ መድሃኒት ማለት ነው› ይሉም ነበር፡፡ ባይገርማችሁ..." አለ ለአዲስ ገለጻ እጆቹን ወደኪሶቹ ሰዶ እየተመቻቸ፤

"ባይገርማችሁ... አንድ ወዳጄ የሆነ የውስጥ-ደዌ ሐኪም በቅርቡ በሰራው ሪሰርች መሰረት እነዚያ፣ በየቦታው ያጥለቀለቁን ባለቢጫ ጀሪካን፣ የሚረጉ

የምግብ ዘይቶች ለልብ፡ የደም ቧንቧና መገጣጠሚያ በሽታዎች እንደሚያጋልጡ አረጋግጧል:: እንደእኔ፣ በእርዳታና ቅናሽ አገኘን ብለን የምንበላው ምግብ ውሎ አድሮ ልብና ኩላሊቶቻችንን ከጥቅም ውጪ የሚያደርግ ከሆነ ቢቀርብን ነው የሚሻለው፤ ኢኮኖሚካሊም ለልብ እና የኩላሊት ህክምና የሚወጣው ወጪ ከሺህ ሊትር ዘይቶች ይበልጣል:: ጥዋት እኮ አይቼው ደህና ነበር ምን አገኘው እየተባለ በደም ቧንቧ መዘጋት ድንገት የሚሞተው ህዝብ ቁጥር ማሻቀቡን እንኳን እኛ ህዝቡም እያስተዋለ ነው:: ማህብረሰባችን ውስጥ ያሉ እናቶቻችንን የማይረጉ የምግብ ዘይቶችን እንዲጠቀሙ ማበረታታት አለብን:: በአመጋገብም በኩል ብንመጣ፤ የእህል ዘሮችን ከአትክልትና ፍራፍሬ ጋር መመገብ ለዘለቄታዊ ጤንነት ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳለው ብታውቁ ትደነቃላችሁ! ‹ኢንተርኔት አከሰስ› ካላችሁ እስኪ <What the health> የተሰኘ የጥናታዊ ፊልም አውርዳችሁ ብትመለከቱ እመኑኝ ትገረማላችሁ... አንዳንዴ ሳስበው..." ብሎ ለአፍታ በዝምታ ከቆመ በኋላ... ወለል ወለሉን እያየ እንደ መተከዝ ብሎ ቀጠለ!

"አንዳንዴ ሳስበው እኛ እንደሞኝነት የምንቆጥረው ባህላችን የቀደመ የህክምና ጥበብ የነበረው ይመስለኛል:: በፆም ከስጋና መሰል ምግቦች እየራቁ ለወራት በሌሎች ምግቦች መቆየት ለጤና ያለው ጥቅም አልገባን ይሆናል:: ከልጅነት ጀምሮ ምንም ጥቅም እንደሌለው ሲነገረን የኖረው እንጀራ ዛሬ ለስኳር በሽተኞች ምርጥ መብል ሆኖ በፓስታና ማካሮኒ መልክ እየተሸጠ እንደሆነ የምናውቅ ስንቶቻችን ነን? አባቶቻችን ያልተዳቀሉና ያልደለቡ፣ ኬሚካል ያልበረዘውን መኖ እየበሉ ያደጉ በሬና በጎችን በጥሬውም ይሁን በንጹህ የኑግ ዘይትና ቅቤ ጠብሰው እየበሉ በ90 ዓመታቸው እንደ 25 አመት ጎረምሳ ጠንካራ ነበሩ:: እኛ ግን ይኸው ገና 20 ዓመት እንኳን በቅጡ ሳንደፍን ወገቤን፣ ጨጓራዬ፣ ልቤን... እንላለን:: ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ደም-ግፊትና ስኳር በሽታ ወሮን አሳራችንን እናያለን፤ አሁንማ ጭራሽ በርገር-ኪንግና ፒዛ-ሃት ብለው ሊከፍቱልን ነው! አበቃልን::" ብሎ ሁሉንም አንድ በአንድ እያቸውና ቀጠለ...

"እርግጥ ችግሮቹ ከእድሜ መጨመር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፤ ወጣት ሆነንም ጉዳታቸውን ላናስተውላቸው እንችላለን... By the way, I just remembered something, what is the major cause for heart failure in youth? (በነገራችን ላይ አንድ ነገር አስታወሰኩኝ፤ በወጣቶች ላይ የልብ-ድካም ከሚያስከተሉ ነገሮች መካከል ግንባር ቀደሙ ማነው?)" ብሎ ቦንቱን ጠይቃት::

"Rheumatic Heart Disease" (ተደጋጋሚ የጉሮሮና አንቃር ወይም ቶንሲል መመርቀዝን ተከትሎ የሚመጣ እንደ ሪህ ያለ የልብ በሽታን ጠራች) ... "ትክክል ጠርተሻል" አለና ገለፃውን ቀጠለ::

"*This is the cause for around 50% of young patients with heartfailure.* (ይህ በሽታ 50 በመቶ ለሚሆኑት በወጣትነት ለሚከሰቱ የልብ ድካም በሽታዎች ምክንያት ነው፤)... እንዴ በዚህ በሽታ የተጠቃና ‹Valvular Disease› (የልብ ውስጥ ፍሰትን ተቆጣጣሪዎች ብልሽት) ያጋጠመው ሰው በቀዶ ህክምና ለመዳን ከሃገር ውጪ ሄዶ መሰራት አለበት:: በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ብሮችም ያስፈልጉታል:: ለዚያውም በጊዜ ሄዶ ቀዶ ጥገናው ስኬታማ ሆኖ ነፍሱን ከታደገ ማለት ነው:: ካልሆነም ሙሉ ኪሳራው በእሱ ይሆናል:: እኛም ታማሚው ይህ ሁሉ ኪሳራ ውስጥ ሳይገባና የመዳን እድሉ ሳይመናመን በፊት ይህን በሽታ የሚያመጡትን ተደጋጋሚ የቶንሲል በሽታዎች መከላከል ዋነኛ መፍትሔ እንደሆነ እናምናለን:: የእነዚህን በሽታዎች የመከላከያ መድሃኒቶችን አሰጣጥም ጠንቅቃችሁ የምታውቁት ነገር መሆን አለበት::

ለኔም ጭምር ሁሌም ጥያቄ የሚሆንብኝ ነገር ግን ከመከላከያ ብሎም የማከሚያ አማራጮች መካከል ቶንሲልን ማስቆረጥ አንዱ መሆኑ ነው:: እናትና አባቶቻችን እኛ ጎጂ ባህል ነው ብለን ሳናስተዋቸው በፊት ቶንሲልና እንጥልን እየቆረጡ ግግን የሚቧጥጡት ምክንያትም ይህ ይሆን እንዴ ብዬ እጠረጥራለሁኝ:: ባይገርማችሁ የቅርብ ጥናቶች ራሱ እንደሚያሳዩት ቶንሲልን መቁረጥ ከዚህ መሰሉ የልብ በሽታ በተጨማሪ የላይኛው የመተንፈሻ አካላት በሽታዎችን ብሎም የመሃለኛው የጆሮ ክፍል በሽታዎችን እጅጉን እንደሚቀንስ ተረጋግጧል:: ድሮም ግብፅን ያስገበሩት አባቶቻችን አጤ-ፋሪስ፣ የጎላ ዘይት፣ የበለስ ፍሬና ጤና አዳም እየተጠቀሙ ወባንና መሰል በሽታዎችን የሚፈውሱ መድሐኒቶችን ይቀምሙ ስለነበር ይህንን ጥበብም ቀድመው አውቀውት ሊሆን ይችላል:: ... እኛ ግን ሞኞች ነን::" አለ ዶ/ር ሳሙኤል የተረብ ሳቅ እየሳቀ፤

"እንደ ሞኝ ይህ ነው የሚባል የረባ ጥናት እንኳን ሳናደርግ የአባቶቻችንን ባህል ‹ጎጂና ኋላቀር› ለማለት እንቸኩላለን:: ይህንን ስል ደግሞ ዶ/ር ሳሙኤል እንጥል አስቆርጡ ብሏል ብላችሁ የሁሉንም ህፃናት እንጥል እንዳትቆርጡ፤" አለ ሁሉንም ተራ በተራ እያየ፣ ይበልጥ እየሳቀ፤ "በመጀመሪያ ይህ ነገር ትክክል እንደሆነ ተገቢ ምርምር መደረግ አለበት:: ሲቀጥል ‹ስቴራይል› በሆነ መንገድ ቀዶ ህክምናውን ሊያደርጉ በሚችሉ የጤና ባለሙያዎች ብቻ ነው መደረግ ያለበት:: እናንተም ነገ የት ቦታ ላይ

ራሳችሁን እንደምታገኙ አይታወቅምና አቅሙና ሓይሉ ሲኖራችሁ በእንዲህ መሰል ነገሮች ላይ ሰፊ ጥናት አካሂዳችሁ ለሀገር ልትተርፉ ትችላላችሁ የሚል ተስፋ አለኝ፡፡ የተሰጠንን እየሸመደድን ከማከም በላይ የራሳችንን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህላዊ የህክምና ጥበብ የምንመረምር ባለሙያዎች መሆን አለብን ብዬ ስለማምንም ጭምር…" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ "እሺ እንቀጥል.." እያለ ወደቀጣዩ አልጋ ተሻገረ፡፡ ቀጣዩ አልጋ የኢትኤል ነበር፤ ተረኛነቱን ስለተረዳ ከተማሪዎቹ ፊት ወጥቶ ቆመ፡፡ "ያንተ አልጋ ነው?" ሲል ጠየቀው ዶ/ር ሳሙኤል፤… "አዎ፡፡" መለሰ ኢትኤል፤

"እሺ ቀጥል…፤" ሲሉት ኢትኤልም የታማሚዋን ህፃን ሙሉ ታሪክ ለሁሉም አቀረበና እሱ ደግሞ በምርመራ ያገኛቸውን ነገሮች መናገር ጀመረ፡፡ "Heart rate 118 per minute (የልብ ምት በደቂቃ 118), respiratory rate 22 (እስትንፋሱ በደቂቃ 22) temperature 37.3°c (የሰውነቱ ሙቀት 37.3 ዲግሪ ሴልሺየስ)" አለና ወደቀጣዩ ሊያልፍ ሲል፤ "*What about the blood pressure? (የደም ግፊቷስ?)*" አለ ዶ/ር ሳሙኤል፤

"ማለት ቅድ… ቅድም መለኪያውን ልቀበል ብዬ… ከ…ዚያ ቶሎ… ቶሎ….ተጀመረና…" ኢትኤል ተንተባተበ፤

"እ… ማነከ ኢትኤል!… ይሄማ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡" ዶ/ር ሳሙኤል የተቆጣ መሰለ፤ "እነዚህ አራት ልኬቶች እኮ በህክምናው ዓለም የህይወት ወሳኝ ኩነቶች (Vital Signs) ለምን እንደሚባሉ ማወቅ አለብህ…" አለና *በዝምታ ቆየት ብሎ ወደ ቀድሞው እርጋታው ተመልሶ ቀጠለ፤*

*"‹ቫይታል ሳይንስ›! የተባሉት የጤንነት ዋነኛ ሚዛኖች ስለሆኑ ነው! የጥንት የግዕዝ መፅሃፍቶቻችን አራቱ የፍጥረት ሃይሎች ማለትም ውሃ፣ አፈር፣ እሳትና ንፋስ መሆናቸውን ይዘግባሉ፡፡ እኔ እንደሚገባኝ እነዚህ አራት ኃይላት በሰው ልጅ አካል ላይ ሲገለጡ ደም ወይም ፈሳሽ፣ ስጋና አጥንት፣ ነርቭና ኬሚካል ቻርጅ እና አራተኛ አየር ወይም ኦክስጅን ናቸው፡፡ ተዋህደውም ተንቀሳቃሹን የሰው ልጅ ያቆማሉ፡፡ ስለዚህ የእነዚህ ኃይላት ዋነኛ መገለጫ የሆኑትን እነዚህን አራት ምልክቶች ማለትም የልብ ምት መጠንና የእስትንፋስ መጠን በደቂቃ፣ የሰውነት ሙቀትና የደም ግፊት መጠን በስርዓቱ መመዝገብ* አለባቸው!" አለና ንግግሩን አቁሞ ሰዓቱን ተመለከተ፤ 6:46 ይላል፡፡ "That is enough for today (ለዛሬ ይሄ በቂ ነው፤)… ተማሪዎች ካፌ እንዳይዘጋባችሁ መሄድ ትችላላችሁ… እኛ እንቀጥል" አላቸውና ከሬዝደንቶቹ ጋር ዙሩን ቀጠለ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በአንድነት ዋርዱን ለቀው ወጡ፡፡ አንድም የሚያማርር ተማሪ ግን አልነበረም፡፡

*** ፬ – ፬ ***

በራቸው እየተንኳኳ ነበር፤ ከእንቅልፋቸው ነቁ:: ከንባብ ጠረጴዛው ላይ እንቅልፍ ጥሏቸው እንደ ወደቁ ወደ አልጋቸው መሄጃያ ቅንጣት አቅም አጥተው እዚያው ጠረጴዛቸው ላይ እንደተደፉ ነበር የነጋባቸው:: እንደምንም ብለው ተነሱና ፂማቸውን አራግፈው፤ ከባኞ-ቤቱ ቧንቧ በፀሎት-መዳፋቸው ውሃ ሞልተው ፊታቸውን አብሰው፤ በፎጣ እያደራረቁ በሩን ሊከፍቱ ሄዱ:: በበሩ ላይ ባለች ቀዳዳ በኩል ሲያጮልቁ የፍሬድሪካ ቀይ ፀጉር ታያቸው:: ፈገግ አሉ::

በሩን እንደከፈቱላት ራመድ ብላ ተጠመጠመችባቸው:: ያልተበጠሩት ፂም ፀጉሮች ሳይኮሰኩሷት በፂሞቻቸው መሃል ያሉትን ከንፈሮች ጡት እንደናፈቀው ጨቅላ መጠመጠቻቸው:: በዚያው የስሜት ሰላምታ ላይ አንዲትም የቃል ልውውጥ ሳይወጣቸው ሁለቱም እኩል ግለው እኩል በረዱ::

ሁሉም ተፈፃፀሞ ትንሽ አረፍ እንዳሉ፤ እርሳቸው ከአልጋው ላይ እሷ ደግሞ እርሳቸው ላይ ተኝታ የመጀመሪያውን ቃል ተነፈሰች::

"I have missed *you my professor!* (ናፍቀኸኝ ነበር የኔ ፕሮፌሰር)"

"Me too my doctor (እኔም የኔ ዶክተር)" አሉ ፈገግ ብለው፤

"And someone had a lot of liquor last night (የሆነ ሰው ማታ በጣም ጠጥቶ ነበር)" አለች በፌዝ፤ ተከፍቶ ባዶውን የተጣለውን የፈረንሳይ ውስኪ ጠርሙስ እየጠቆመች::

"I was reading a great book and I was so excited that I didn't realize I was drinking too much! (በአንድ ግሩም መፅሐፍ ተመስጬ ስለነበር ብዙ መጠጣቴን ራሱ አላስተዋልኩም ነበር)" አሏት፤

"Was it a book about history? (የታሪክ መፅሐፍ ነው?)" አለች ፊቷ ላይ ጉጉት እየተነበበባት::

ፍሬድሪካ እስራኤላዊት የታሪክ አጥኚ መሆኗን ነግራቸው፤ በግብፅ የዛሬ አምስት አመት አገናኝቶ ያጣመራቸውም የዚሁ እየዞሩ ታሪክ የማጥናት አባዜያቸው ነበር:: የንጉስ ራምሴስ 5ኛ የመቃብር ስፍራ ሲቆፈር የተገኙትን

የድንጋይ ላይ ፅሁፎች ለመመርመር ጥላ አልባ ትላልቅ የግብፅ ፒራሚዶች ድረስ በሄዱበት ወቀት ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኙት፡፡ በአሁን ዘመን አሉ የሚባሉ ክሬን ማሽኖች የማያነሷቸው መቋሚያ አለቶች፤ ሳይንስ ምን እንደሆነ ባላወቀው ታላቅ ሃይል ተደራርበው ከተሰሩት ድንቅ የታሪክ ምስክሮች ስር ጎን ለጎን ቆመው ሳለ፤

ግዙፎቹን የግብፅ ፈረዖን ሃውልቶች ሽቅብ እያስተዋለች "I wonder why all the noses of these pharoas are broken? (ለምን ይሆን ሁሉም ሃውልቶች ላይ ያሉት የፈረዖን ንጉሶች አፍንጫቸው የተሰበሩት ብዬ አስባለሁኝ?" ብላ ፍሬድሪካ ራሷን ስትጠይቅ አጠገቧ ቆመው ዙሪያውን ያጤኑ የነበሩት ፕ/ር እሴ ግን ሰምተዋት ኖሮ እንደዘበት መለሱላት፤

"Your own people did this! (የእናንተ ሰዎች ናቸው እኮ የሰበሩት)"… ለመስከ ስራ የበረሃውን ጨረር ሊከላከል ታስቦ የተሰራው ሰፊ ኮፍያዋን ከፍ አድርጋ በጥያቄ አይን አስተዋለቻቸው፡፡ "What do you mean? (ምን ማለትህ ነው?") አለቻቸው ግራ መጋባት ሞልቷት፡፡

*"I will explain it for you. You see these pharoas were primarily of Kushitic origin. Particularly these over here were ancient Ethiopians who came from the source of Nile to establish and rule this great empire for long ages. (እሱን ቆይ ላብራራልሽ፤ ምን መሰለሽ እነዚህ የምታያቸው የፈረዖን ነገስታት በሙሉ መሰረታቸው የኩሽ የዘር ግንድ ነበር፡፡ በተለይ እነዚህ ከጎናችን የቆሙት ሀውልቶች ከአባይ ወንዝ መነሻ የመጡና ይህን ታላቅ ስልጣኔ አስገኝተው ለረጅም ጊዜ ያስተዳደሩ ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን ቅርጽ ነው፡፡)"*

"That might be true but what is your point? (ያ ምን አልባት እውነት ሊሆን ይችላል ግን ነጥብህ ምን እንደሆነ አሁንም አልገባኝም?)" አለች፤

*"My point is that these noses were all crushed down by European invaders who wanted to conceal this truth. Jealous people who don't want the world to know that once there were giant black kings, kushitic pharaos with big round nose who*

*established & ruled such a spectacular civilization"* (የኔ ነጥብማ እነዚህ ሃውልቶች ላይ ያሉት ሰፋፊ አፍንጫዎች በአውሮፓውያን ወራሪዎች መሰባበራቸው ነው:: ይህንን ያደረጉት ደግሞ ዓለም የዚህ ግሩም ስልጣኔ መስራቾች ግዙፍ ጥቋቁር የኩሽ ንጉሶች መሆናቸውን እንዳያውቅ ለማዳፈን ነው፤)" አሷት ቆፍጠን ብለው፤ ፍሬድሪካ ትንሽ አሰብ አደረገችና፤

"Wow! Is that for real... I have been here a couple of times but this never occurred to me & no one told me about it..." (ዋው! እውነት እኮ ነው! ከዚህ በፊት እዚህ ስፍራ ላይ በተዳጋጋሚ መጥቻለሁኝ ግን ይሔ ስውር እውነታ አንድም ቀን ውል ብሎብኝ ወይም ማንም ሰው ነግሮኝ አያውቅም::) አለች በነገሩ የእውነት እንደተገረመች በፊቷም ጭምር እየገለፀች:: አስከትላም T/C እሴን አተኩራ እያየች...

*"Frankly speaking, I liked your openness... you know what I mean? Even if I am a white woman you were firm about your truth!"* (እውነቱን ለመናገር ግልፅነትህን ወድጄዋለሁኝ፤ ምንም እንኳን እኔ ራሴ ፈረንጅ ብሆንም ያመንከበትን እውነት ከመናገር ግን ወደኋላ አላልክም::)

"Sorry if I offended you" (እንዲሰማሽ ካደረግኩኝ ይቅርታ እጠይቃለሁኝ!)"

"Don't feel sorry... I think we deserve more than that for what we did in those days of invasion and slavery... but I hope you won't cut my nose..." (ምንም ይቅርታ አያስፈልገንም፤ በቅኝ ግዛት ወቅት የሰራነው ስራማ ከወቀሳም በላይ ብዙ ሊያስቀጣን ይገባ ነበር፤ ቢሆንም አፍንጫዬን እንዳትቆርጥብኝ አደራ::) እንደሚያስነጥስ ሰው አፍንጫዋን ይዛ በስርቅርቅታ ሳቀች፤ እርሳቸውም አብረዋት ሳቁ... T/C እሴና ፍሬድሪካ ያኔውኑ ነበር በመሃከላቸው የሆነ መጠን የሌለው የመግባባት መንፈስ ሲፈጠር የታወቃቸው:: ዛዲያ ሁለት መሰረታቸው እጅጉን የተለያዩ ሰዎች እንዲህ ሲግባቡ ከጀርባ አንድ ነገር አለ ማለት ነው:: አንድ ነገር...

*** ዩ – ዩ ***

ጉጉት ፊቷ ላይ እየታየ ደግማ ጠየቀቻቸው "Was it a historical book? (የታሪክ መፅሐፍ ነው?)"

"Yeah, I was reading one remarkable book about Ethiopian history. (አዎን አንድ በኢትዮጵያ ዙሪያ የተፃፈ አስገራሚ መፅሐፍ እያነበብኩኝ ነበር።)

"That is exciting... but..." (ደስ የሚል ነገር ነው... ግን...) አለች አንድ ነገር ቅር እንዳለው ሰው አይኗን ቡዝዝ እያደረገች።

"*But what?* (ነገር ግን ምን?)" አላት፤

"Would you mind if I ask you something" (አንድ ነገር ብጠይቅህ ቅር ይልሃል?) አለች ትከሻቸው ላይ ቀኝ ጆሮዋን አንጥፋ ተኝታ የደረታቸውን ጸጉር እያሻሸች፤

"No problem Fredi, you can ask me anything" (ምንም ችግር የለውም ፍሬዲ የፈለግሽውን መጠየቅ ትችያለሽ።)

*"You know what I really like about you... you have a unique respect for your origin & identity. Before I met you I only knew Ethiopia by her athletes & reggae music. But after you came into my life Ethiopia became such an extraordinary country to me. I am always excited to study more.* (ስለአንተ በጣም የምወድልህ ነገር ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ስለማንነትህና ታሪክህ ያለህ ልዩ ክብር ነው። አንተን ከማግኘቴ በፊት ኢትዮጵያን የማውቃት በሬጌ ዘፈንና ታላላቅ ሯጮቿ ነበር። አንተን በህይወቴ ውስጥ ካገኘሁኝ በኋላ ግን ኢትዮጵያ ለኔ ልዩ ትርጉም የምትሰጠኝ ሃገር ሆናለች፤ ሁሌም ስለሷ ማወቅ ያጓጓኛል " ብላ በረጅሙ ተነፈሰችና "but (ግን)" አለች እያቅማማች፤

*"But what Fredi, Just tell me?! (ግን ምን ፍሬዲ?... ንገሪኝ እንጂ!)"*

*"But when I compare that great civilization with the socio-economic status of the current Ethiopia, I even doubt that they*

*are the same people. We both know what the media reports about the current Ethiopia; Poverity & food insecurity, Injustice & Political Instability, HIV and Malaria, Migration and more bad news as such... Seriosly professor! What happened to you guys through out the years?!* (ነገር ግን ያኔ የነበረውን ታላቅ ስልጣኔ አሁን ካለው የኢትዮጵያ ማህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ወቅታዊ ሁኔታ ጋር ሳነፃፅረው ያኔ የነበሩትና የአሁኑ ትውልድ አንድ አይነት ህዝብ መሆናቸውን ራሱ እጠራጠራለሁኝ:: ሁለታችንም የዘመኑ ሚድያ ስለአሁኒቷ ኢትዮጵያ ምን እንደሚዘግብ እናውቃለን፤ ድህነትና የምግብ እጥረት፣ የፍትህ መጓደልና የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ኤች አይ ቪና ወባ፣ ስደትና ሌሎች ከፉ ከፉ ዜናዎች፤ እውነቱን ንገረኝ እስኪ ፕሮፌሰር! በዘመን ሂደት ውስጥ ምን ኣጋጥሟችሁ ነው እንዲህ የሆናቹት?)"

ፕ/ር በአፅንኦት ሲያዳምጧት ቆዩና ተራቸው እንደደረሰ ሲያውቁ መመለስ ጀመሩ፤ *"You were afraid to ask me this; yet, you will be startled if you knew that it was a question which troubled me since my young age, a riddle I couldn't solve throughout my years. Even after I became a professor, it was my inner pain for which I couldn't find the remedy!* (ባይገርምሽ ዛሬ አንቺ ለኔ ለመንገር የፈራሽው ጥያቄ እኔን ገና ከለጋ እድሜዬ ጀምሮ ሲያስጨንቀኝ የነበረና ለብዙ አመታት በቅጡ ልፈታው ያልቻኩት እንቆቅልሽ ነበር:: የፕሮፌሰርነት ደረጃ ላይ እንኳን ደርሼ አንዳችም እሳማኝ ማርከሻ ያላገኘሁለት ውስጣዊ ህመሜ ነበር::)" ካሉ በኋላ ለአፍታ ዝም ብለው ቀጠሉ፤

*"But all of that changed after I read this book, and now I can confidently tell you that Ethiopia is still a great, chosen nation. These recent eras, paper based, accelerated civilization born from black magic of people like John Dee had considered Ethiopia a backward country. Yet she is still a crowned queen!* (አሁን ይሄን መፅሐፍ ካነበብኩኝ በኋላ ግን ደረቴን ነፍቼ የምነግርሽ አንድ እውነት ቢኖር ኢትዮጵያ ድሮ ብቻ ሳይሆን አሁንም ታላቅና የተመረጠች ሃገር መሆኗን ነው:: የዘመናችን የነጆን ዲ ጥቁር አስማት የወለደው ወረቀት አምራች፣ ፈጣን ስልጣኔ ውስጥ ያዘገመች መስላ ‹ኋላቀር› ብትባልም አሁንም የንግስትነቷን ዘውድ ያልተነጠቀች ሃገር ነች::)" አሏት አስረግጠው::

"How come? I mean on what bases you claim that? (እንዴት ሊሆን ይችላል?... ማለቴ በምን መስፈርት ላይ ተመስርተህ ነው እንዲህ ያልከው)" አለች ግራ እየገባት፤

ፐ/ር እሴ አንዲትም ቃል ሳይተነፈሱ ተነሱና ጠረጴዛው ላይ ሳይዘጉ ያሳደሩትን ላፕቶፕ ‹ሃይበርኔት› ከሚያረግበት አውጥተው ከፈቱት:: ትናንት ማታ ሲያነቡት ከነበረው ምዕራፍ ላይ አንዷን አንቀፅ አቅልመው ‹ስክሪኑን› ወደእሷ አዞሩና እንድታነብ ጋበዟት::

በቀይ ፊቷ ላይ ብዙ አይነት ስሜቶች እየተፈራረቁ አንቀፁን አንብባ ጨረሰች:: ለአፍታ በአግራሞት ስታያቸው ቆየችና... *"Oh my God! I can't believe this! So under the Axum stale is?.... (የአምላክ ያለህ! ይሄንንስ እኔ አላምንም... እና የአክሱም ሃውልት ስር...?)"* አለች ቃላቶቿ እያገቷት፤

*"Yes! (አዎ!)" አሉ ፐ/ር እሴ ቆጭም ብለው፤*
*"So what about the secret key to the treasure you discovered? (ድብቁን ሐብት መክፈቻ የሚስጥሩን ቁልፍስ አግኝተኸዋል?)"*
*"Yeah (አዎን)"*
*"So tell me then?... (ታድያ ንገረኝ)?" አለች በችኮላ፤*
*"Not yet, I will tell you when we get to the place. (ሚስጥሩን አሁን አልነግርሽም፤ ከቦታው ስንደርስ ነው የምነግርሽ)" አሏት ቆፍጠን ብለው፤*
"This means we are going to Ethiopia! ... By the way do other Ethiopians know about this secret? *(ይህ ማለት ኢትዮጵያ እንሄዳለን እያልከኝ ነዋ! በነገራችን ላይ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ስለዚህ ሚስጥር ያውቃሉ እንዴ?)"*

"I really don't think so. *(የሚያውቅ ሰው መኖሩን እጠራጠራለሁኝ)"* አሉ ፐ/ር እሴ በለዘብታ፤

"That is amazing; I believe we should leave for Ethiopia as soon as possible (ይህማ አስገራሚ ነገር ነው፤ በቻልነው ፍጥነት ወደ ኢትዮጵያ መሄድ እንዳለብን አምናለሁኝ!)" አለች ታላቅ መነሳሳት እየታየባት; የፐ/ር ፂማምና ሸበታም ፊት ላይ ግን ብዙ አይነት ስሜቶች ይፈራረቃሉ፤ ቃልም ሳይተነፍሱ ወደ ራሳቸው አስጠግተው እቅፍ አደረጓት::

*** ቶ – ቶ ***

ላለፉት ሁለት ቀናት እኩለ ሌሊት ጠብቆ መጮኽ የለመደው የጋሽ ጀምበሬ ውሻ አላዛር ገና ጀምበር ከመጥለቋ ማላዘኑን ጀምረ::

"አሄሄ… አላዛር ለቅሶዬን ቀድሞ ጀመረልኝ!" አሉ ጋሽ ጀምበሬ፤ ከአልጋቸው ስር የተቀመጠውን ውሻ በተስፋ መቁረጥ እየተመለከቱ…

"ኧረ አንቱ ሰውዬ ዝምብለው አያሟርቱ!" አሉ ወ/ሮ ቤዛዊት እጃቸውን በነጠላ ጠቅልለው አፋቸውን እየሸፈኑ፤

"እሱንስ ተይው አንቺዬ… ሟች መሆኔን ዑቃቢዬ ከነገረኝ ቆይቷል፣ ውሻ እኮ እንዲህ የሚያላዝነው የሞትን መልዓክ ሲያይ ነው::" አሉ::

"ምን አለ ከፉ ከፉውን ትተው መልካሙን ቢያስቡ" አሉ ወ/ሮ ቤዛዊት፤ አይናቸውን የሞላውን እንባ በነጠላቸው እያጎደሉ፤

"ለሟች ይታወቀዋል ሲባል አልሰማሽም… ውስጤ እየነገረኝ… አሄሄ" አሉ ጋሽ ጀምበሬ በተስፋ መቁረጥ ተውጠው፤

"የፈሩት ይደርሳል፤ የናቁት ይወርሳል!" እንዲሉ አበው፤ ወ/ሮ ቤዛዊት ምኑንም ያህል ውሸት እንዲሆን ቢመኙም ባለቤታቸው በደካማ ድምፃቸው የተናገሩት ትንቢት ግን መድረሱ አልቀረም:: ጋሽ ጀምበሬ ውለው ሳያድሩ ቅጭም ያለ ፊታቸውን እንደያዙ አረፉ::

በቀብራቸው እለት፣ ከቀኑ 10 ሠዓት ላይ፤ በርካታ ወዳጅ ዘመዶቻቸው፤ ወንዶቹ ጥቋቁር ካፖርታቸውን፤ ሴቶቹ ደግሞ ጥቋቁር ነጠላዎቻቸውን ለብሰው ተገኙ:: አፈር ተምሶ የሬሳ ሳጥናቸው ተሰተረ:: ከበላዩም ሁለት ሰፋፊ ጣውላዎችን በሚስማር በመምታት የተሰራ መስቀል ቆመ::

**"አቶ ጀምበሬ ዳኛቸው"**
**(ከ1943- እስከ 2010 ዓ.ም)**
**"አፈር ነበርኩና ወደ አፈር ትመለሳለሁ::"**

የጋሽ ጀምበሬ ቀብር ቆፋሪዎቹ አካፋና ዶማቸውን፤ ለቀስተኞች እምባቸውን፤ ጋሽ ጀምበሬ ትዝታቸውን ይዘው ከስፍራው ለቀቁ:: የፈረደባቸው ወ/ሮ ቤዛዊት ብቻ ቦታው ላይ ድፍት ብለው ቀሩ፤

አንዲት ሴት ልጅ ብቻ ያፈሩበት ትዳራቸው 27 ዓመታትን አስቆጥሯል:: እነዚህ አመታት ለባልና ሚስቲት የደስታም የሀዘንም ነበሩ:: ሲሞላ ጮማ ተጎራርሰው፣ ሳይሞላ ሲቀር የጠላ ቂጣ ተካፍለው በልተዋል:: ሕይወት ትከፋም ትልማም እነርሱ ግን ሁሉንም በአብሮነት አልፈዋል:: መለያየት ከቶውንም አማራጭ ሆኖ አያውቅም::

ይህው ዛሬ ግዴታ ሆኖ፣ ጥርሱን አግጦ እስኪመጣ ድረስ!

ወ/ሮ ቤዛዊት የህዘኑ በትር ክፉኛ ሲደቁሳቸው ይታወቃቸዋል:: ህመሙን ግን በምን መንገድ አስተንፍሰውት እንደሚቀላቸው አያውቁም:: የሆነ በሀዘን እየመዘመዘ የሚገድል አሲድ ውስጣቸውን እንዳለ ይታወቃቸዋል፤ እንዴት አድርገው ግን ከሰውነታቸው ስርዓት እንደሚያስወግዱት ብልሀቱ የላቸውም:: በጭንቅ ውስጥ ተደፍቶ ከመንሰቅሰቅ በስተቀር...

"በቃ ሄድክ ጀምበሬ? ሄድክ ማለት ነው?...በቃ ሄድክ ወይ?" የባለቤታቸው በድን ልሳን አውጥቶ ይመልስ ይመስል በጥያቄ መወትወት...

"በቃ ሄድክ ጀምቤ?... ላትመለስ አሸለብክ?... እሺ አንተስ አረፍከው... እኔስ ምን ልሁን? ማን አለኝ ጀምብዬ?... ባዶ ሜዳ ላይ ጣልከኝ? አላሳዝንህም? ያቺ ምስኪን ከርታታ ልጅህ ፅዮንስ አታሳዝንህም?" እምባቸው ጉንጫቸውን አርሶ አልፎ መሬቱን ማርጠብ ጀምሯል::

"አላሳዝንከም ወይ ጀምብዬ?...የኔ ጌታ!...አለቃዬ!"

በምሬት እያነቡ የመቃብሩን አፈር ይቧጥጡት ገቡ:: ኋላ ግን እጆቻቸው ሲላላጥ፣ አካላታቸውም ሲዝል ሁሉን ትተው መቃብሩ ላይ ተደፉ:: እዚያው እየተንሰቀሰቁ፣ እየደከሙ ሄደው ሳያስቡት እንቅልፍ ሸለብ አደረጋቸው:: እንደተኙ ጊዜው ነጎደ... ፀሐይቱም ለነገ ቀጠሮ ይዛ ጠለቀች::

ራቅ ብሎ ከሚገኘው የመቃብር ጠባቂ ማደሪያ የሚወጣው የአንፖል ብርሀንና የሙሉዋ ጨረቃ ነፀብራቃ ተደማምረው ምሽቱን ከሙሉ

ፅልመትነት ታድገውታል:: ወ/ሮ ቤዛዊት ሻሻቸውን ከላ አድርገው ከተደፉበት ቀና ሲሉ ምሽት ነበር የተቀበላቸው:: ድንግዝግዝ ካለው የሙታን መንደር ውስጥ ዝር የሚል ህያው ነገር ማየት አልቻሉም:: የልባቸው ትርታ ቀስበቀስ ሲጨምር ይታወቃቸዋል:: የእልፍ ሬሳዎች የሞት መንፈስ የሚጠራቸውም መሰላቸው::

በረጅሙ ተንፍሰው ለመረጋጋት ሞከሩና ምክንያታዊ ፍርሀታቸውን አከብረው ከዚህ ቦታ ለመራቅ ወሰኑ:: ለመሄድ ከተቀመጡበት ብድግ ሲሉ ግን ከጎናቸው የተኛ ነገር ተመለከቱ:: በመቃብሩ ስፍራ ብቻቸውን አልነበሩም:: ታማኙ ውሻቸው አላዛር ከመቃብሩ ግርጌ ጋደም ብሎ አዩት:: ሁሌ ከጋሽ ጀምበሬ ወንበር ስር እየተኛ ከእግራቸው ጋር መተሻሸትን ይወድ እንደነበር አስታወሱ:: አላዛር ላይ አይናቸውን እንደተከሉም በትዝታ ነጎዱ::

ከ10 አመታት በፊት ነበር፤ አንዲት ድክምክም ያለች ጥቁር ውሻ እያነከሰች መጥታ ወደነጀምበሬ አጥር የተጠጋችው:: እንኳን በሌላ በሽረሪትም የማይጨክኑት፣ እንዳሁኑ በፀና ያልደከሙት ጋሽ ጀምበሬ ውሻዋን አፈፍ አድርገው ወደቤት አስገቧት:: ምግብና ውሀ ከመስጠትም በላይ ቁስሎቿን ለማከም የተቻላቸውን ቢሞክሩም ከፉኛ ደከማ ስለነበር ውሻዋን ማትረፍ አልተቻላቸውም ነበር:: ገና የውሻዋ ትንፋሽ ተቋርጦ ከማሸለቧ ግን ትንሽዬ ቡችላ ከወደጭሯ ፈለቀ:: ጋሽ ጀምበሬ ፈጠን ብለው ቡችላውን ከሙት እናቱ ለዩና በጨርቅ ጠቀለሉት:: መገቡት፣ ውሀም ሰጡት፤ ሊያሳድጉት ወሰኑ:: ከሞት ጋር አብሮ ተወልዷልና "አላዛር" ብለው ሰየሙት:: የቤተሰቡ አባልም ሆነ::

"ሰውነት ማለት ፍጥረትን በሙሉ መውደድ ነው፣" ብለው እንደ አንድ የቤተሰቡ አካል ባላቸው አቅም ተንከባከበው አሳድገውታል:: እርሱም ይህንን ያውቅ ይመስል ከስራቸው አይጠፋም ነበር:: ዛሬም እንደለመደው ከእግራቸው ጋር ባይተሻሸም፣ ፀጉሩን እከክ እከክ አድርገው ባያጫውቱትም፤ ከመሰቡ ሙብል ቆረስ አድርገው ባያጎርሱትም ሊለያቸው ግን አልፈቀደም:: እንደነገሩ የፊት እግሮቹን አፈራርቆ ከመቃብራቸው ተቀምጧል::

ወ/ሮ ቤዛዊት ከትዝታ መንጎዳቸው ሲመለሱ ጨረቃዋን ጥቁር ዳመና ጋርዷት ነበር::

"በል ተነስ አላዛር ወደቤታችን እንሂድ፣ ከእንግዲህ በኋላ በቀናችን እኛ ወደሱ ብንሄድ እንጂ እሱ እንደሆን ወደ እኛ አይመለስም" አሉና ከእንብርክካቸው ተነሱ:: አላዛር ግን ወይ ፍንክች አለ:: ወ/ሮ ቤዛዊት ማስገደድን የቀላቀለ ተደጋጋሚ ልመና ቢያዳርጉም አላዛር ግን አሻፈረኝ ስላላቸው ትተውት ወደ ቤት መሄዱ የግድ ሆነባቸው:: ፈጣሪ ነፍሱን ከገሀነም፣ ስጋውን ከጅብ እንዲጠብቅላቸው ተማፅነው የባላቸውን መቃብር ለመጨረሻ ጊዜ በሀዘን ተሰናብተው ትንሽ እንደተራመዱ፣

በስፍራው "ቤዛዊት… ቤዛዊት…" የሚሉ ሁለት ጥሪዎች ተሰሙ፤ ወ/ሮ ቤዛዊት ባሉበት ቀጥ አሉ፣ ጀርባቸው ቀፈፋቸው:: እውን የእርሳቸው ስም ነው የተጠራው? ድምፁስ የጋሽ ጀምበሬ ነው ወይስ በቁማቸው እየቃዡ? እንደ ሎጥ ሚስት ሀውልት የሆኑ ያህል ዞሮ መመልከቱና ማረጋገጡ ፈተና ሆነባቸው:: ድምፁ ግን አሁንም ከጀርባቸው ተደገመ…

"ቤዛዊት… ምነው በአንድ ቀን ረሳሽኝ እንዴ?"

ቅዠት አልነበረም! ጥሪዎቹ የእውነት ናቸው:: ወ/ሮ ቤዛዊት የሞት-ሞታቸውን አንገታቸውን ወደኋላ አጠማዘዙ:: ከጋሽ ጀምበሬ የቀብር ቦታም ላይ አይናቸው ተተክሎ ቀረ:: ድንግጥ አሉ፤ አካላታቸው ወደብዙ ትንንሽ ንዑሶች የተሰነጣጠቀ ያህል ተሰማቸው::

በጋሽ ጀምበሬ ቁመት የረዘመ፤ በውፍረታቸው ስፋት የተመጠነ አንድ ሰው ከመቃብራቸው ላይ ቆሟል:: ከለበሰው ነጭ መጎናፀፊያ አሳልፎ ቀኝ እጁን መዘዘ:: ረጅም ሌባ ጣቱን ወደ ወ/ሮ ቤዛዊት ዘርግቶ እየጠቆመ… "ቤዛዊት…" ሲል ጮኸ፤ ድምፁም የጋሽ ጀምበሬን ቢመስልም ትንሽ ጎርነንና ጎተት ያለ ነበር::

"ቤዛዊት… ጥለሽኝ ልትሄጂ ነው? ደሜንም ሳታጥቢልኝ! አስተብትበው የገደሉኝንም ሳትበቀይ! ልትሄጂ ነው ወይ?… ነገር ግን ታገሺ በልጃችን በኩል የሚመጣ ከባድ የብርሀን ሰራዊት አለ!"

አላዛር በደስታ እየቦረቀ የጋሽ ጀምበሬን የሙት መንፈስ ሲዞረው ወ/ሮ ቤዛዊት ግን ብኽርኽር ብለውባቸው ተገትረው ቀሩ::… ትንሽ ነፍሳቸው ከድንጋጤ መለስ ሲልላቸው ግን…

"እማ" የሚል ጥሪ ከጀርባቸው ተሰማቸው፤ ዞሩ…

*** ፉ – ፉ ***

# ምዕራፍ - ፬ ፦ ጭላንጭል ጮራ…

-------------------------ውድቅት ሌሊት - ባህር-ሃጠራ

ፅዮን ማንነቱ ባልታወቀ በራሪ ፈረስ እንደሚገፋ እንደ ነፍስ-አልባ ጋሪ እየተጎተተች ከጨለማ ዱር ወደ ሰሜን አቅጣጫ 12 ኪ.ሜ ከነፈች:: ግፊቱ አብቅቶላት በእግሮቿ አንድ ስፍራ ላይም ቆመች፤ አሁን ያለችበትንም ቦታ ልክ እንደ ቅድሙ ለማስተዋል ሞከረች፤ ፀሐይን በፅኑ ፈለገቻት… ከሃዲዋ ፀሐይ ግን አሁንም ከሰማዩ ብራና ላይ አልተቀለመችም፤ የከሃዲዋ ዘመድ አዝማዶች ኮከቦችም አኩርፈዋል፤ ጨረቃ ድንቡልቦቃ በጥቁር ደመና ተጋርዳ፣ ከነነፀብራቋ ተደብቃ ተከዛለች… ህይወት አልባ የመሰለ፡ ሙትቻ ሰማይ በተራው በጨለምተኛ አይኖቹ ዳግም ቁልቁል አፈጠጠባት::

አይኗ በጭለማው ሓያልነት ቢንበረከክም ተረጋግታ ስታዳምጥ ከጀርዋ የውሃ ጨዋታ… የፈሳው የሿሿታ ድምፅ ተሰማት፤ በእርጋታ የሚፈስ ውሃ፡ የሰፊ ሰማይ ምሳሌ ሰማያዊ ውሃ ተፈጥሯዊ ጠረን ከአፍንጫዋ ገብቶ ነፍሷን በጥቂቱም ቢሆን ሲያረጋጋው፤ የጠል ጠብታ በፍርሃት የነደደ ደሟን ቀዝቀዝ ሲያደርገው ታወቃት::

ትንሽ አቅም አግኝታ ወደራሷ መለስ ስትል ከዚህ ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት ምን ማድረግ እንዳለባት ራሷን ጠየቀች፡፡ በኑሮ ለዛለና ተስፋው ለመነመነበት ሰው ብቸኛው መጠጊያው ጥሎ የማይጥለው አንድ አምላኩ እንደሆነ ታውቃለች፡፡ ለመፀለይ አይኖቿን ጨፈነች፤

…ምን ብላ እንደምትፀልይ ግራ ገብቷት ትንሽ እንደቆየች የመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ ሦስት ቃላት… እያንዳንዱ ፊደላት እንደ ወርቃማ እሳት ተሰልፈው ሲነዱ በምናቧ ታያት፤ አፏን እያንቀሳቀሰች ቃላቶቹን ማነብነብ ጀመረች፤

*"1፤ አቤቱ የሚያስጨንቁኝ ምንኛ በዙ! በኔ ላይ የሚቆሙት ብዙ ናቸው፡፡*
*2፤ ብዙ ሰዎች ነፍሴን ‹አምላክሽ አያድንሽም› አሏት፤*
*3፤ አንተ ግን አቤቱ መጠጊያዬ ነህ፤ ክብሬንና ራሴንም ከፍ ከፍ የምታደርገው አንተ ነህ፡፡*
*4፤ በቃሌ ወደእግዚአብሔር እጮሃለሁኝ፤ ከተቀደሰው ተራራውም ይሰማኛል፡፡*
*5፤ እኔ ተኛሁም አንቀላፋሁም እግዚአብሔር ግን ደግፎኛልና ነቃሁኝ!*
*6፤ የሚከብቡኝን እእላፋት አልፈራም፡፡*
*7፤ ተነሥ፥ አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ አድነኝ፤ አንተ የጠላቶቼን መንጋጋ መተሃልና፤ የከፉዎችንም ጥርስ ሰብረሃል፡፡*
*8፤ ማዳን የእግዚአብሔር ነው፥ በረከትህም በህዝብህ ላይ ነው፡፡"*
*(መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 3፤1-8)*

"እ… እ… አሜን፣ አሜን…. እ… አሜን!" አለች ብርዱ እያንዘፈዘፋት፡፡ ከዚህ አስፈሪ ክስተት በፊት የነበረው ማንነቷም ቀስ-በቀስ ይታወሳት ጀመረ፡፡ ከኢትኤል ጋር ጅሬን በረንዳ ላይ ቡና ስትጠጣ፣ መርየም "አፈቀርኩኝ" ስትል፣ ቦንቱ ስለዳቼላ ስትተርክላት… ‹የዳቼላ የሙት መንፈስ ወይስ የአባቷ የጋሽ ጀምበሬ?›… የቢታንያ ሴራ ወይስ የጎረቤት ድግምት… ሁሉም ይገላለጥላት ጀምሯል፡፡

*** ♀ – ♀ ***

አብረሃም ተቸግሯል . . . ያቺ ልጅ ደግሞ ዝም ብሎ ሲያያት ነንበስ ቀና እያለች ትሽኮረመማለች። የቀይ ፊቷ ሙሉ ጨረቃ ቅርፅ… ከጥቁር ሂጃቧ ሾልኮ አልፎ የሚንዘላፈል ዘለላ ፀጉሯ፤ … እንጆሪ ከንፈሯ… የቆዳዋ ወዛማ ቅላት ጋር ተደምሮ የአይን አባዜ ሆኖበታል። ሌላውን በቅጡ አላስተዋለውም። አይኗ እየገረፈው ሙሉ ውበቷን ማየት አላስቻለውም:: ግን ቢያያትም አያስተውላትም፣ ከልቡ አስተውሎም አያስታውሳትም:: የእሷነቷን መልክ እንጂ ጥቃቅን ገፅታዋን ለማስታወስ አዕምሮው ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ነበር:: ነገ ከእውቀት ዳገት ቆሞ ጥርሱን አግጥጦ የሚጠብቀው ፈተና ላይ የሚንከባለሉት ቋጥኝ ቋጥኝ የሚያህሉ ጥያቄዎች አሳስበውታል:: ታድያ የሷን ፊት ቢያስታውሰው ነገ ምን ሊጠቅመው?

ከመልኳ ይልቅ የትዝታ ምህዋሩን የሚዘውረው ፈረንጅ ያሸከመው የበሽታና የመድሃኒት ስም መዓት ነው። ነገ ማስታወስም የሚጠበቅበት እሱኑ ነው። ከልጅነት ጀምሮ ከተሸከመው የቤተሰቦቹ አደራ እና ከወደፊት የኑሮ መሰረቱ ደሞዝ ተመን አንፃር ካየው እኮ፤ እሷ ለሱ… ያቺ ቆንጅዬ ባለሂጃብ ልጅ… ምኑም ናት። ምን አልባትም ከዚያች ቀን በኋላ ‹ለዘላለም ላላገኛት እችላለሁም› ብሎ አስቧል::

ያቺ ቀን ግን አለፈች:: የፅሑፍ ፈተናው ውሽንፍርም ጥቂት በደንቡ ያልተወጠሩ ሽራዎችን በሳስቶ፣ በጣጥሶ ሲለውም ገንጣጥሎ - ጥሎ አለፈ:: ሆኖም ያቺ ቆንጆዬ ሙስሊም ልጅ ግን በማግስቱም ትውስ አለችው። ከእያንዳንዱ የሽምደዳ መፍዘዝ ጋር ከፊት ለፊቱ ተቀምጣ ስትፈግግ ትዝ ትለዋለች። ትዝ ስትለውም ፈተና የጨረሰበት ቀን ምሽት ላይ ማረፍም ሳያስፈልገው እራቱን 12:00 ሰዓት ካፌ መጀመሪያ ተሰላፊ ሆኖ በልቶ ወደ ላይብረሪው ከነፈ:: ትልል…ቅዬ መፅሐፍ ከፍቶ ትናንት ተቀምጦበት ከነበረው ቦታው ላይ ተቀመጠ::

ያቺ ቀይ ሙስሊም ልጅ ግን ትናንት የነበረችበት ቦታ ላይ ዛሬ አልተገኘችበትም:: ውስጡ እየጓጓ፣ ችቦ ለኩሶ እንደ ድንቢጥ እያስገገ ጠበቃት:: ደበበ ሰይፉ "አዱኛ ሰብስቤ ጠብቄሽ ነበረ" እንዳለው አዱኛም ባይኖረው አፈያውን ሰብስቦ ጠብቋታል፤ ሰዓቱ ይሄዳል… በእያንዳንዷ ደቂቃ ‹እሷን አያታለሁኝ› የሚል አዲስ ተስፋ አንገቱን እስኪያመው ዞሮ የመግቢያው በር ላይ ያፈጣል:: ‹የአንባቢ ያለህ› እያለ ከስሩ የተዘረጋው መፅሐፍ ሽቅብ ይታዘበዋል:: እሱ በተራው ከቤተ-መፅሐፍቱ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን ሰዓት ይታዘባል:: የግድግዳው ሰዓት በበኩሉ የአብርሃምን ትዝብት ከቁብም ሳይቆጥር ዝም ብሎ ይጓዛል… 2:30… 3:00… 3:30… መፅሐፉ አብርሃም ላይ፣ አብርሃም ሰዓቱና በሩ ላይ እንዳፈጠጡ 5 ሰዓት

ሞላ:: ያቺ ቀይ ሙስሊም ልጅ ግን የውሃ ሽታ ሆና ቀርታለች:: በስተመጨረሻ ተስፋ ቆርጦ ወደዶርሙ አዘገመ::

በቀጣዩ ቀንም እንዲሁ ጠብቋት ነበር፤ እሷ ግን አልመጣችምና ሳይሳካለት ተመለሰ:: ሦስተኛዋ ቀን ግን ለአብርሃም የተባረከች ነበረች:: ያቺ ልጅ አልቀረችም፤ መጥታለች! ሁለቱም መፅሐፋቸውን የሆነ ገፅ ላይ ከፍተው ተሰየሙ:: ሌባ አይኑ ከመፅሐፉ አፈትልኮ ከእሱ ትዕዛዝ ውጪ በሆነ ሁኔታ ከጠረጴዛው ማዶ ወዳለችው ልጅ ይሰደዳል:: እሷም እየሰረቀች ትመለከተው ኖሮ አይን ለአይን ይጋጫሉ:: ግጭቱ በሚፈጥረው መግነጢሳዊ ሃይል የሁለቱም ልብ እኩል ይርዳል:: በአይን መላተሙ ሁለቱም ላይ ሃፍረትን ፈጥሮባቸው፤ ይህን አስጨናቂ ደስታ የሚፈጥር ኀይል መቋቋም አቅቷቸው ባጎነበሱበት ሳያስቡት ንባባቸው ውስጥ ይመሰጣሉ::

አብርሃም ጭንቅላቱን ያጣበቡትን አስጠሊታ አስጠሊታ በሽታዎችና ከሌላ ፕላኔት የተገኙ የሚመስሉ ስሞቻቸውን እንብቦ ቀና ሲል የሷን ቆንጆ ፊት ያያል:: በረሃ ውስጥ ምንጭ እንዳየ ግመል ልቡ በሐሴት ይሞላል:: ደግሞ እኮ ናፍቃዋለች፤ እንደገና ግን ሳይታወቀው ወደ በሽተዎቹ ስም ዝርዝር አዕምሮውን መልሶ ይፍጨረጨራል።

ሳያስበውም ራሱን ‹እግዚአብሔር ግን ይሄን ሁሉ በሽታ ለምን ፈጠረ?› የሚል ሙግት ውስጥ ያገኘዋል:: ያኔ ህሊናው የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ይመስል መልስ ይሰጠዋል፤ *"እግዚአብሔር ለሁሉም በሽታዎችም መድሀኒታቸውን ፈጥሯል! ተመራምሮ ማግኘት የሰው ልጆች ፋንታ ነው"* እያለ:: *ስሜታዊነቱ የወለደው ድፍረቱ ይገለምስና... ‹በመጀመሪያ በሽታዎቹንስ መፍጠሩ ለምን አስፈለገ?› ብሎ ይጠይቃል:: ህሊናው ህፃን ልጅ እንደሚያዋራ ሽማግሌ ፈገግ ብሎ መልሱን ይሰጠዋል፤ ‹የኔ ልጅ!... በሽታ ከሌለ እኮ ጤና ትርጉም አይኖረውም› እያለ::* አብርሃም *የገዛ ህሊናው መልስ ግራ አጋብቶት ሲወዛገብ...*

"ቀና በል" ይለዋል ልቦናው በተራው፤ ...ቀና ሲል እሷን ያያታል። ሙግቱን ይረሳል:: "ይሄንንም ውበት የፈጠርኩት እኔ ነኝ" የሚል አይነት መልስ በደማቁ ይታየዋል። ወድያው እሷም ቀና ብላ ስታየው ሁለቱም ድንግጥግጣቸው ይወጣል። የአይን ዘረፋ እልፍ ጊዜ ይፈፀማል... "ልተዋወቃት እንዴ?" ... ከወንበሩ ሊነሳ ይዳዳዋል፤ ውጥረትና ፍርሃትን ለማምረት ሀላፊነት የተሰጠው የአዕምሮ ክፍሉ ግን ይዞ ያስቀረዋል:: እሷን ትተተህ ከህሳብህ አወጣና አርፈህ አንብብ እያለ ይገስፀዋል። ግና ዛሬ ትትቶ

ከአቅሉ ጓዳ ያወጣት ያቺ ቆንጆዬ ሙስሊም ልጅ በማግስቱ የትውስታ ጓዳው ውስጥ ገብታ የናፍቆት እንጀራዋን ስታሰፋ ትገኛለች።

አብርሃም ምን እንደሚሆን ግራ ገብቶታል፡፡ አያውቃት አታውቀው!... ምኑ ስለሆነች ነው ትዝ የምትለው? ሊረሳት በሞከረ ቁጥር ይባሱኑ የሚያስታውሳት ለምን ይሆን? እሷ 'ኮ ለእሱ ምኑም ነች!... ግን... እንደትናንቱ ዛሬም፣ ቅድምም... አሁንም ትዝ ትለዋለች... እንደገና...

ዛሬን እንደ ትናንቱ ይህ አዙሪት ይቀጥላል፡፡ አብርሃም እንደ ወትሮው የልቡንም የአዕምሮውንም ጥማት አንዲትም ሳያርስ ወደዶርሙ ሲመለስ 5፡30 ሆኖ ነበር፡፡ የዮሴፍ በር ላይ ሆኖ ስልክ እየተጃናጀነ ቆሟል፤ ውስጥ ደግሞ ኢትኤልና ናዖድ ቀድመውት ገብተው እያጠኑ ነበር፡፡ "ምነው አብርሽ ዛሬ በጊዜ?... አንድ ፈተና ጨረስን ብለህ ፈታ እያልክ ነው መሰለኝ አለ ናዖድ ከወዳደቁት ካልሲዎች መካከል የግሉ የሆኑትን እየመረጠ፤

"ዛሬ ምንም ማጥናት አልቻልኩም፤"

"የሆነ ሰው ተሸኗል!" አለ ኢትኤል፤ የፌዝ ሳቅ እየሳቀ፡፡

"መተሸን ብቻ ቢሆንማ ጥሩ ነበር፡፡" አለ አብርሃም ከሰባራው ወንበር ላይ መውደቅንም ሳይፈራ ዘፍ እያለ፡፡

"ምን ሆነክ ነው አብርሽ?" አለ ኢትኤል ጥናቱን አቁሞ ላፕቶፑን እየዘጋ፤

"ነገ ማታ ላይብረሪ አብረን እንሂድ ኢታ..." አለው አብርሃም በለዘብታ፤ ኢትኤል መልስ ለመስጠት ትንሽ ማሰብ ነበረበት፡፡

"ምን አልክ?" አለ ናዖድ፤ ከአልጋው ጀርባ የወደቀበትን አንድ እግር ካልሲ ለማውጣት ሲታገል ከነበረበት ዘሎ እየወጣ፤

"ማን አንተን አናገረክ?" አለ ኢትኤል፤ "ምነው ብቻህን ደበረኽ እንዴ?"፤ አለ ወደ አብርሃም ዞሮ፡፡

"አዎ በእናትህ አብረን እናጥና" አለ አብርሃም፤ አንገቱን ወደመሬት እንደደፋ የሆዱን በሆዱ ይዞ፡፡

"እሺ በቃ ነገ አብረን እንሄዳለን" አለ ኢትኤል ሃሳቡን አውጠንጥኖ ሲጨርስ፤ አብርሃም የሚሰማውን ስሜት ለሁሉም የዶርም አባሎቹ ቢናገር በተለይ ዮሴፍ ‹አብርሃም ፎንቃ ጠለፈው› ምናምን እያለ እንደሚዘባበትበት ስለሚያውቅ ሚስጥሩን ለኢትኤል ብቻ መናገሩን መርጧል፡፡ ልብሱን ቀያይሮ፣ የሆዱን በሆዱ ይዞ አልጋው ውስጥ ገብቶ ጥቅልል ብሎ ተኛ፡፡

*** ዩ – ዩ ***

በማግስቱ በማለዳ ቁራ ሲያቁራራ ተነስቶ፣ ቤተ-ክርስቲያን ደጃፍ ስሞ የቀን ውሎውን ቢጀምርም ቀኑን ሙሉ ግን ሃሳቡ ያቺ ልጅ ጋር ነበር:: አይደርስ የለ ምሽቱ ደርሶ ገና ለአይን ያዝ ማድረግ ሲጀምር ነበር የኢትኤልን ስልክ ያስጮኻት:: ኢትኤል በበኩሉ ቀኑን ሲዞር ውሎ ስለደከመው አረፍ ለማለት ከቤቱ ገብቶ ገና ከአልጋው ላይ መጋደሙ ነበር:: እረፍቱን መነጠቁ ቢያናድደውም የጓደኛ ነገር ነውና ተነስቶ ወጣ::

ማክሰኞ ዕለት ነበር፣ ኢትኤል ቤቱን ከተከራየበት የቆጪ መንደር ወደ ጅማ ሆስፒታል ለመውጣት ከተሳፈረው ታክሲ ውስጥ አንድ የት እንደሚያውቀው ውል ያላለለት ልጅ-እግር ረዳት የጉዞውን ሂሳብ ጠየቀው:: ብሩን እየሰጠው ትንሽ የጭንቅላት ሚሞሪ ካርዱን ሲያገላብጥ ግን ማንነቱ ወድያውኑ ታወሰው፤ ያ ምስኪኑ ካለሃጢያቱ የተደበደበው ‹ላቦሮው› ልጅ ኖሯል!

መልኩ ለጊዜው ለምን ግር እንዳለው ሲያስተውልም ጨፍራራ ረጅም ፀጉሩን ሙልጭ አድርጎ ስለተላጨው መሆኑን ተረዳ:: በእርግጥ መቆረጡ ፊቱን ቀለል ያደረገው ቢሆንም ፀጉሩን የተቆረጠበት ምክንያት ‹ውበትን ፍለጋ› እንዳልሆነ ግን ኢትኤል በቀላሉ ገምቷል:: የልጁ ለብዙ ጊዜ ያሳደገውን ፀጉር መስተካከል ከጥቂት ቀናት በፊት በገፅታው ብቻ ከደረሰበት የግፍ ድብደባ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ግልፅ ነበር:: ፀጉሩን መከርከሙ እንዳለ ሆኖ በራሱ ፍላጎት ሳይሆን በፍርሀት መሆኑ ግን ሲበዛ ኢትኤልን እየቆረቆረው በሀሳብ ሩቅ አነጎደው…

ከገዛ አባቱ አቶ ሳኦል ጀምሮ የልጅ ፀጉር መርዘም ለምን እንደ መርዛማ ዱርዬነት እንደሚታይ ሚስጥር እንደሆነበት አድጓል:: ገና ልጅ እያለ ቤታቸው ይመጣ የነበረውን ባለ«ድሬድ» ፀጉር ራስታው አጎቱን በጣም ይወደው ነበር:: በለጋ ጣቶቹ የዳበሳቸው ጉንጉን ፀጉሮቹ በልጅነት ልቡ ተቀርፀዋል:: የሚወደው አጎቱ አንዳች ምልክት ሳይሰጥ እንደወጣ ሲቀር የኢትኤል አይኖች ለቀናት አንብተዋል:: በውስጡ የጣለበትን የማይረሳ ትዝታ አዝሎ ሰባተኛ ክፍል ሲደርስ እርሱም ልክ እንደ አጎቱ ፀጉሩን ማሳደግ ጀምሮ ነበር:: ግና አንዳች ለዘብተኝነት ያልፈጠረበት ግትሩ አባቱ የፀጉሩን ማደግ ባየ ጊዜ እጅጉኑ ተቆጣ:: አንጠልጥሎ ወስዶ ሙሉ ለሙሉ ሙልጭ አስደርጎ አስላጨው::

ለኢ.ትኤል ግን ጸጉሩን የመቆረጡ ተጨባጭ ሰበብ እስከ ዛሬም ምንም ግልፅ ሆኖለት አያውቅም:: በአቅሙ የፀጉር ማሳደግን ትክክለኛ ትርጉም ለማወቅ በርካታ የንግል ንልጉለህ ፈልግ ቁልፎችን ተጭኗል፡ የተወሰኑ መፅሐፍትን አገላብጧል:: ፀጉርን ማሳደግ ከእርከስናና ንጢያት ጋር የሚያይዙ ሃይማኖታዊ ድርሳናት ይኖሩ ይሆን ብሎ ቢያነብም ከጥንት ከጥዋቱ ኖህ መርከቡን ሲቀልስ መላጣ እንዳልነበር አውቋል:: እንዲያውም በተቃራኒው ፈጣሪ የሳምሶንን ሀይል ያኖረው ከጡንቻው ሳይሆን ከተንዠረገገ ፀጉሩ እንደነበር አንብቧል:: ስለምንም ሲጠበብ ፀጉሩን ተቆርጦ እንዳልነበር ተረድቷል:: በክርስትናም ይሁን በእስልምና አስተምህሮ መሰረት ነብያት በሙሉ ማለት ይቻላል ፀጉራቸውን ያሳድጉ እንደነበር በቂ ማስረጃ አግኝቷል:: ከነብያት የተሻሉ የሃይማኖት ህግጋት ቋሚ ምሳሌዎች ደግሞ የትም አይገኙም::

ሆኖም ፀጉርን ማሳደግ አንዳንዴ ከስራ ቦታ ህግጋትና የሳይንስ መርሆዎች ጋር ሊጋጭ ይችላል ብሎም ደምድሞ ነበር:: "እኔ በሳይንስ አማኝ ነኝ!" ለሚል ማንም የዚህች ምድር ጠበብት ደግሞ ከእነ አርስቶትልና ሊዮናርዶ ዳቪንቺ ጀምሮ እስከ ፊዚክስ ሊቁ አልበርት አንስታይን ድረስ ያሉ ታላላቅ ሰዎችን ምስል ፈልጎ ቢመለከት ፀጉራቸው ረዝሞ ወርዶ አልያም አድጎ ተንጨባርሮ ማግኘቱ የማይታበይ ሀቅ ነው::

ፉሽኑ አልፎበት ነው የሚጠላው እንዳይለም፡ ከጥሌ ገፈሬ እስከ ማይክል ጃክሰን ዘማ፣ የቦብ ማርሌይ ድሬድ፡ ጆንትራ አለማየሁ እሸቴ ወዘተ ገፅታዎች ይሞግቱታል:: ብቻ በየትኛውም መስፈርት ፀጉር ማሳደግ የወንድነት፣ ብልህነትና ትልቅነት መገለጫ እንጂ የላቦሮነት መታወቂያ ነው የሚል መረጃ እስካሁን አላገኘም:: በእዚህም ማንኛውም ሰው ንፅህናውን ከጠበቀና የሙያ ስነ-ምግባሩን እስካልጣሰ ድረስ ፀጉሩን ቢያሳድግ ምንም ከፉት እንደሌለው አምኗል::

ሁሌም በዚህ ነገር ዙሪያ ሲወያይ በጭራሽ የማይዋጥለት ማብራሪያ ቢኖር ደግሞ ‹ባህላችን አይደለም› የሚለው ዲስኩር ነው:: በእሱ እምነት በባህሉ ረገድ የሀበሻነት ምርጥ መገለጫ ረጅም ፀጉር ነው:: ጥንታዊ ስዕሎች ምስክርነት አፍሮ ጠይሞችን እንደሚያሳዩ ሁሉ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መስራች የቋራው ጀግና ቴዎድሮስ ራሱ ቆንጆ ሹሩቤ ነበር:: በጦርነት የኖረው አፄ ዮሀንስም የትግሬ ሹሩባውን ግጥም አድርጎ የተሰራበትን ምስል በተደጋጋሚ አይቷል:: ሩቅ አሳቢው እምዬ ምኒሊክም ሻሽ ያሰሩት የኤርትራ ጉዳይ ራስ ምታት አስይዟቸው ሊሆን ይችላል እንጂ በራቸው ለመሸፈን

አልነበረም። ሲቀጥልም የብልኹ ግርማዊነታቸው ቋሚ ጎፈሬ መች ይረሳናል።

እናማ "የልበ ደንዳና አርበኞች ጎፈሬ፣ የአፋሮች በቂቤ የራስ ጉንጉን፣ የወላይታ ነጠላ ሸብ የተደረገበት አፍሮ፣ የአባ-ገዳዎች ረጅም ሸበቶ ሁሉ ባህል አይደለም ማለት ነው? ወይስ ባህል ሌላ ትርጉም አለው?" እያለ ከራሱ ጋር ሲሟገት፤ በአንድ ረዳት መቆረጥ ተመስጦ፤ በምናቡ ማጀት ውስጥ ጠንስሶ እራሱ ያብሰለሰለውን ሀሳብ ገና ከታክሲው ከመውረዱ አንድ ጥግ ጥላ ላይ ቆመና አባባል ቢጤ ደብተሩ ላይ ሞነጫጭሮ ቋጨው፤ እንዲህ ይላል ፅሁፉ…

*‹ከራስ ቅል ውስጥ ያለው አዕምሮ እሳቤ እንጂ ከራስ-ቅል በላይ የሚበቅለው ፀጉር የሰውን ማንነት አይገልፅም። ቢገልፅማ ኖሮ ፀጉር ማሳደግ የግርማ መገለጫ እንጂ የዱርዬ መለዮ ሊሆን አይገባም ነበር።›*

… ዶርም ሲደርስ በቀጠሮው መሰረት አብረሃም በጉጉት እየጠበቀው ነበር። ተያይዘው ወደ ጤና ቤተ-መፅሐፍት ሄዱ።

*** ༒ – ༒ ***

*"ነይ እንጂ ቢታን ቶሎ እንሂድ!" አለች መርየም ለመሄድ እየቸኮለች!*

*"ሜሩ ደግሞ አታጣድፊኛ… ቆይ አንዴ ኩሌን ላድምቀው፤ … ሆ! ሆይ! ምን ይሉታል አሁን እንዲህ ሰው መናፈቅ?" አለች ቢታንያ በሽሙጥ፤ ከዚያ ከትልቁ መስታወቷ ፊት ለፊት ቁጭ ብላ ፊቷ ላይ እየሳለች። በያንዳንዱ መበተን፣ በያንዳንዱ ማስመር መሃል በመስታወቱ ውስጥ ያለውን የራሷን ምስል እያየች ትደሳሰታለች። የውድ መስታወቷን ጠርዞች በስሜት ተውጣ ትደባብሳለች።*

"አቦ! ወላሂ ትቼሽ ልሄድ ነው… ቆይ አንቺ ነሽ እኔ ልጁን የወደድነው?" አለች መርየም ለመሄድ እያኮበኮበች፤

ቢታንያ በስተመጨረሻ መኳኳሏን ጨርሳ ስትወጣ ደንበኛ የግብፅ ሴት ጣኦት መስላ ነበር።
"እንዲህ ነፍስሽ እስኪወጣ የተንገበገብሽለትን ጉድሽንማ ሳላየው አልቀርም!" አለች የመርየምን እጅ ይዛ ጎትታ እየወሰደቻት…

*** ༒ – ༒ ***

ፅዮን ጅሬን ሆቴል በረንዳ ላይ ከኢትኤል ጋር ከተገናኘች 3 ቀናት አየነጉ መሹ:: የደበቀችው ሚስጥሯ እረፍት ቢነሳትም የግድ ማጥናት ነበረባትና በየቀኑ የህግ ላይብረሪ እየሄደች ማንበቧን አላቋረጠችም:: በንቱ የነገረቻት የዳቼላ ታሪክና የሙት መንፈስ ጉዳይ በጊዜው አስፈራርቷት ነበር:: ነገር ግን ይህ ነው የሚባል ተጨባጭ መረጃ የሌለው የግቢው ተማሪዎች የፈጠሩት አፈ-ታሪክ እንደሆነ ራሷን አሳምናዋለች::

ዛሬም እንደልማዷ ምሽት አንድ ሰዓት ተኩል አራቷን ቅፅል ስሙ ሸራተን እሚባለው የተማሪዎች ካፌ በልታ ህግ ላይብረሪ ውስጥ ተሰይማለች:: ከአራት በኋላ ከግቢው በር ፊትለፊት ከሚገኝ አንድ ዳስ ሁለት ሲኒ የጀበና ቡና ጠጥታ ስለነበር እንቅልፍ የሚባል ነገር ሲያልፍም አልነካካት:: የባህልና ኢኮኖሚ ጋር የተሳሰረን ተክል ሱስ ብሎ መጥራት ቢከብድም ፅዮን የቡና ሱስ አለባት:: ልክ ዮሴፍ ሜት ሲያጣ እንቅልፍ እንደሚያስቸግረውና እያዛጋ ሰፈሩን ጉም በጉም እንደሚያደርገው ሁሉ ፅዮንም ቡና ካልጠጣች ዱካክ ወዳጇ ይሆናል:: ቡናዋን ካገኘች ግን ነቃ ብላ ለረጅም ሰዓታት የማንበብ ችሎታ አላት::

ሌሊት ስድስት ሰዓት ሲቃረብ በህግ ቤተ-መፅሃፍት እያነበቡ የነበሩት ተማሪዎች 90 በመቶ የሚሆኑት ወደ ዶርማቸው ተመልሰው ነበር:: 7 ተኩል ሲሆን ደግሞ ሁሉም አንባቢዎች ለቅቀው ሶስት ተማሪዎች ብቻ ቀሩ:: ፅዮን ከእርሷ ጋር አብረው የቆዩትን የንባብ ተፎካካሪዎቿን ቀና ብላ አየቻቸው::

አንደኛው የትልቅ ሰውዬ ሰውነት ላይ የህፃን ልጅ ፊት ተተክሎበት የሚመስል አይነት አቋም ያለው ጉንጫም፣ ፂም አልባ፣ ላፕቶፕና ታብሌት የመሳሰሉትን የኤሌክትሮኒክሶች በገፍ ከፊቱ የደረደረ ድንቡሽቡሽ ያለ ወጣት ነው:: ሁለተኛዋ አንባቢ ግን ለፅዮን ጀርባዋን ሰጥታ ስለተቀመጠች የፊት ገፅታዋን ለማየት ባትችልም ጥቁር ሹራብ ለብሳለች፣ ጥቁር ሻሽም ሸብ አድርጋለች:: ከቅርጿ ገዘፍ ያለች ወጣት ሴት መሆኗን ገምታለች:: ወንበር ላይ ተቀምጣ እንኳን ረጅም መሆኗ ያስታውቃል::

ከ15 ደቂቃዎች በኋላ ድንቡሽቡሹ ወጣት ኢቃዎቹን ዘጋግቶ ወደ ቦርሳው አስገባና ወጣ:: አሁን ቤተ-መፅሐፍቱ ውስጥ የቀሩት ያቺ ረጅም ሴትና ፅዮን ብቻ ነበሩ:: ፅዮን እንቅልፏ ባይመጣም ከዚህ በላይ ማምሸቱ የነገ ውሎዋን እንደሚያበላሽ ስለገባት ቀጣዩን አንቀፅ ብቻ አጥንታ ወደ ዶርሟ ለመሄድ ወሰነች::

...ተመስጣ እንቀፁን ኢየነበበች ሳለ ድንገት ጠቅላላው የቤተ-መፅሀፍቱ መብራት ድርግም ብሎ ጠፋ:: ፅዮን ደነገጠች:: ያን የሚያክል ሰፊ ቤተ-መፅሐፍት ጨለማ ሲሞላው የሆነ ፍርሃት ይጭራል:: ደብተሮቿን በዳበሳ ዘጋጋችና ለመውጣት ስትዘገጃጅ መብራቱ በራ:: ዙሪያዋን ስታማትር ያቺ በቤተ-መፅሐፍት ውስጥ የነበረችው ባለጥቁር ሹራብ፣ ጥቁር ሻሽ ያሰረች ረጅም ሴት ከቦታዋ ላይ አልነበረችም:: "በምን ቅፅበት ከላይብረሪው ወጣች?" ብላ ለራሷ አጉተመተመች፤ አሁን በዚህ ትልቅ ቤተ-መፅሐፍት ውስጥ በእርግጥ ብቻዋን ቀርታለች:: ቶሎ ወጥታ ለመሄድ ወሰነችና ገና ከወንበሯ ብድግ ከማለቷ ድጋሚ መብራቱ ድርግምግም አለና አዳራሹ በሙሉ በጭለማ ተሞላ:: ምንም ጊዜ ሳትፈጅ ወጥታ ወደ ዶርሟ አቀናች::

የዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ ፀጥ ረጭ ብሏል:: የጠፋው ጠቅላላው የኤሌክትሪክ ሃይል ነበርና ግቢው ብዙ ሺህ ወጣት ተማሪዎች የሚገኙበት ስፍራ ሳይሆን ሰፊ የመቃብር ቦታ መስሏል:: ጥድፍ ጥድፍ እያለች የግቢውን ትንሿን ስታዲየም ዞራ ልክ እንደታጠፈች ከጀርባዋ "ፅዮን" የሚል የሴት ድምፅ ከቤተ-መፅሐፍቱ አቅጣጫ ሲጠራት ተሰማት:: ልቧ በድንጋጤ ለሁለት ተሰነጠቀ:: ማነው በዚህ ጭር ባለ ውድቅት ለይቶ የሚጠራት፤ ወደ ኋላዋ ዞሮ ለማየት ልቧ በጣም ሰግቷል:: የቦንቱ ማስጠንቀቂያ ጆሮዋ ላይ ያቃጭላል "ስማቸው ሲጠራ የሚዞሩ ሴቶችን ዳቼላ በመንፈስ ቆንጆ ነኝ አይደል?› ብላ እየጠየቀች በጥፊ ታጠናግራለች::" ብላ የነገረቻትን በፍርሃት ውስጥ ሆና አስታወሰች:: ወደኋላዋ ሳትዞር በፍጥነት ስትራመድ ልቧ እየራደ ነበር:: በየቀኑ አጥንታ የምትመላለስበት መንገድ አሁን ከጅማ እስከ አጋሮ በእግሯ የምትሄድ ያህል ርቆባታል:: የእውን ይሁን ምናባዊ ሃሳቧ የፈጠረው መገለጥ ባታውቅም ከኋላ ጀርባዋን የሆነ እጅ ቸብ ያደረጋት መሰላትና "ዋይ!" ብላ ጮኸች:: ደንግጣ ዙሪያዋን ስታስተውል የሰው ዘር የሚባል አልነበረም:: በዚሁ ውጥረት ውስጥ ሳለች ድንገት ስልኳ አቃጨለ:: አውጥታ ስትመለከት ‹ማማ› የሚል ስም ወጣላት፤ እናቷ ወ/ሮ ቤዛዊት በዚህ ሰዓት ለምን ደወሉ?... ውስጧን ፍርሃት ወሮት፣ ቅፍፍ እያላት ስልኩን አነሳችው::

"ሄሎ ልጄ" አሏት፣ ከወዲያኛው ሀዘን ያደባበት የምስኪን እናቷ ድምፅ፤

"ሄ... ሄሎ እማ" ተንተባትባ መለሰች ፅዮን፣ ፍርሃቷ ላይ ድንጋጤ ታክሎበት፤

"ልጄ... በቃ ልናጣው ነው! ... አባትሽን ልናጣው ነው!"

"ምን ማለት ነው እማ?..." አለች ፅዮን፣ ከመቅፅበት እንባ አይኖቿን ግጥም አድርጎ እየሞላው፤

"አባትሽ በጣም ደክሞብኛል ነው የምልሽ ልጄ…" ብለው መለሱላት፣ ደከም ባለ ድምፅ… "ከቻልሽ ቶሎ ነይና ከመሞቴ በፊት ብትሰናበቺው ብዬ ነው መደወሌ…" ዝም አሉ፤ ፅዮን የቀረቻትን አቅም አንጠፍጥፋ የሞት ሞቷን መለሰችላቸው፤

"እ… እሺ እ… እማ!"

*እንደዚያ በጥድፊያ ትራመድ የነበረች ልጅት በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆና መሃል መንገድ ላይ ቆመች፤ ሰማይ ምድሩ ተምታቶባታል:: ብቻዋን የምትቋቋመው አይነት ጭንቀት አልሆን ሲላት ስልኳን አወጣችና የኢትኤልን ቁጥር መታች:: ቢመሽም ኢትኤል በዚህ ሰዓት የመተኛት ልምድ እንደሌለው ታውቃለች:: ስልኩ ጠራ፣ ደጋግሞ ጠራ… አልተነሳም፤ በቴሌ የተቀዳች የአንዲት ሴት ድምፅ «የደወሉላቸውን ደንበኛ ማግኘት እንደማትችል» ነገረቻት:: በዚህች ደቂቃ ግን ኢትኤል ለቴሌዎች ደንበኛ ለፅዮን ደግሞ የነፍስ አድን መሲሕ ነበር:: ደጋግማ ደወለች፤ ኢትኤል ግን አላነሳም… ለጭንቋ አልደረሰም::*

*እንደምንም የህልም ተጓዥ ይመስል እያዘገመች ዶርሟ ገብታ ወደቀች:: በማግስቱ በማለዳ ተነስታ መሄድ ብትፈልግም ኢትኤል የሰጣትን ብር በሙሉ ጫማ ገዝታበት ምንም ብር ስላልተረፋት መርየምን እንድታበድራት ጠየቀቻት:: የአጋጣሚ ነገር ሆኖ መርየምም እጇ ላይ ብር አልነበራትም:: ለዚህም መርየምም ልብሷን ቀይራ አብረው ባንክ ሄደው ብር እስኪያወጡና ከዚያም መኪና እስኪታገኝ ድረስ ሰዓቱ ሄደባት::*

*ፅዮን የያዘችው ዶልፊንን መሳይ መኪና ወደአዲስ አበባ ጉዞውን ሲጀምር 4 ሰዓት ሞልቶ ነበር::*

*መንገዱ ሲጀመር ትልቅ የተስፋ ማጣት ስሜት ሁለመናዋን ወሮት ነበር:: እንደ ጅማ አዲስ አበባ መንገድ ጥምዝምዝ ያሉ ሃሳቦችን ስትጠመልል ስትፈታ ምኑንም ሳታውቀው አመሻሽ ላይ ሸገር አዱ-ገነት ገባች፤ ዉዲያውም መናኸሪያ ወርዳ የሰፈሯን የቀጨኔን ታክሲ ተሳፈረች::*

*** ☥ – ☥ ***

*አብርሃምና ኢትኤል ተያይዘው ወደቤተ-መፅሐፍት ሲሄዱ ቶላ ዶርም ውስጥ ለብቻው ቀረ፡፡ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርገው ዛሬም የባለፐዑም ዜማውን አብተው ከበደ ዘፈን ከፍቶ በነፃነት ማንበብ ጀምሯል፡፡*

*♫"ፈጌኛ ነ ዶዌፍ መሌ - ሱያዱ ሂንዲ'ፍኔ ሃደኮ*

*ማሊን ጎዳ ገሩ? - ፈጌኛቲ ሃ አማቱ - ነጋን ታኢ*
*ረከቱሲ ረቢን ጂራ - ቤሎፍቱስ አብቢ ታኢ*
*አኒ ሙጫን ኬ ነጋዳ - ሃደኮ ነን ያዲሂ"*

*(ርቀት ከልከሎኝ እንጂ አንቺን መናፈቅ አላቆምኩም እማ፥*
*ምን ማድረግ እችላለሁኝ ከአቅሜ በላይ ሆነማ*
*ለችግርሽ እግዚአብሔር አለ - ርሐቤን ታግሼ እቀመጣለሁኝ*
*እኔ ልጅሽ ደህና ነኝ - እናቴ አስብሻለሁኝ፡፡)*

*…ይላል እንጀትን አላውሶ፣ ልብን ሰርስሮ፣ ሃያሉን የእናትን ፍቅር እሳተ-ጎሞራ ቆስቁሶ የሚያፈነዳው ዘፈኑ፤ ቶላ በህሊናው አንድም ቀን ባይደላት አንድም ቀን መከፋቷን ሳታሳየው ለሱ ደስታ የኖረችውን ምስኪን እናቱን እየሳለ፤ በየመሃሉ አይኑቹን የሚሞላው እንባ ወደጉንጮቹ እንዳይወርድ ታግሎ ወደጉሮሮው እያስገባ ወደውስጥ ያነባል…ያነባል፡፡ ለእሱ ንባብ መጠጊያው ናት፡፡ ያኔ ገና በለጋነቱ እናቱ ያላትን ቆጣጥራ፣ እየጎተተች ወስዳ ት/ቤት ካስመዘገበችውና ‹አ ባ ጫ ዳ›… ‹አ ቦ ጊ ዳ›.. እያለ ፊደል መቁጠር ከጀመረበት ቀን አንስቶ፣ ‹ሔ ቢ ሲ ዲ› . . ‹ሰልፋ ቤታ ጋማ ዴልታ›፤ እያለ የፊዚክስና ሒሳብ ቀመሮችን ማብላላት እስከቻለበት የመሰናዶ እርከን ድረስ በት/ቱ ዋዥቅ አያውቅም፡፡ ከክፍሉ ሲለውም ከጠቅላላው ሴክሽን አንደኛ እየወጣ ጨርሶ፣ በማትሪኩም የከተማው አምቦን 1ኛ ትልቅ ነጥብ አምጥቶ ነበር ጅማ ዩኒቨርስቲን የህክምና ት/ት ክፍል የተቀላቀለው፡፡*

*ግቢ ከገባም በኋላ ሰቃይ ከሚባሉ ተማሪዎች ዘንድ የተመደበና ለማዕረግ የሚጠበቅ ተማሪ ነው፡፡ አጥንቶ… አጥንቶ ድካም ቢጤ ሲሰማው የእናቱን በደህነት የተጎሳቆለ ፊት አስቦ፣ ቶሎ ሊደርስላት ተልዕኮ አንግቦ ዳግም ይነቃቃል፡፡ ሚሞሪ እንኳን ከማትቀበለው ባለአነስተኛ ዋጋ ስልኩ ውስጥ ካሉት ጥቂት ሙዚቃዎች መካከል ይህችኑ የአብተው ዘፈን መርጦ ይከፍታል፡፡ በጥልቅ ስሜት ውስጥ ገብቶ ዳግም ወደ ንባቡ ይመለሳል፤ መድከሙ የማይቀረው ስጋው ‹በቃኝ› እስኪለው ድረስ ያጠናል፡፡*

የቶላ አጭር ጎፈሬ በየቀኑ ጥዋት ጥዋት በሙሽጥ በውኃ ይበጠራል፣ በየሳምንቱ በእኩል ደረጃ ተመጥኖ ተከርክሞ ቅርፅ ሲወጣለት አንከን አልባ የጥድ ከርከምም ይመስላል:: ከመቃ አንገትና ዘላጋ ፊቱ ጋር ተደምሮ የአዳ ዛፍን ቢጤ ግርማን ያላብሰዋል:: እሱም ይህን ያውቅ ይመስል ከአንገቱ ላይ የአዳ ባህላዊ ዛፍ ያለው ጨሌ ከአንገቱ አይለይም:: ከግራ ጉንጩ ላይ የተጫረች ጠባሳው ከዛጎል መሳይ ፊቱ ላይ ለየት ብላ ትታያለች::

ቢሊሱማ በሩን ብርግድ አድርጎ ሲገባ ቶላ ሙሉ በሙሉ በንባቡ ውስጥ ተመስጦ ነበር:: "አካም አልቴ? አንባቢው ወንድሜ!" አለው ቢሊሱማ፣ ተደራራቢውን አልጋ ደገፍ ብሎ ቆም ቁልቁል እያየው፣

"ሰላም ነኝ ባክህ... ምን አንባቢው ትለኛለህ፣ ይህው አንተ መጣኽ ማለት አላነብም ማለት ነው፤ አንተ እንጀራህን ጋግረህ እኔን ታዘናጋኛለህ::" አለ ቶላ፤ ቢሊሱማ ግማሽ ደምወዝ የሚከፈለው ተመራቂ ሐኪም ስለሆነ አሽሙር መናገሩ ነው::

"ለፍተህ አንብበህ ብትመረቅም፣ ለውጥ ለማምጣት የታፈንክበት ጨቋኝ አገዛዝ ስር እስካለህ ድረስ የማንበብ ጥቅሙ አይታየኝም" አለ ቢሊሱማ በሰለቸ ሰው ድምፅ፣

"ይሄ ነገርህ እኮ ነው የማይዋጥልኝ" አለ ቶላ፣ ለክርክር ራሱን ሊያዘጋጅ የሚያነበውን መፅሐፍ እየዘጋ፣

"ለነፃነት መታገል ሌላ ጉዳይ ራስን በትምህርት ማበልፀግ ሌላ ጉዳይ... ማልኮም ኤክስ እንዳለው ‹ብቻልነው መንገድ ሁሉ ራሳችንን ለሚጠብቀን ትግል ማዘጋጀት አለብን::› ለምሳሌ ቼ-ጉቬራ የህክምና ት/ቱን ጨርሶ ነው ወደ ትግሉ የገባው፤ የተማረው ት/ትና በንባብ ያካበተው እውቀት ደግሞ የትግል አጋሮቹ ሲጎዱ ህክምና ከመስጠት አንስቶ የተዋጣለት ተናጋሪና ተፅእኖ ፈጣሪ ትንታግ እንዲሆን ኢጅጉን ረድቶታል:: ..."

"ካንተ ጋር መከራከር የማልወደው እኮ ለዚህ ነው!" አለ ቢሊሱማ... "በድሮ ታሪክ ውስጥ የፃግኖር ይመስል ያነበብካቸውን ታሪኮች እንደ ምስክር እየደረደርክ ታደርቀኛለህ:: አሁን ያለንበትን ችግርና የተሸከምነውን የጭቆና ቀንበር ለመቀልበስ ስር ነቀል ንቅናቄ እንጂ ወሬና ታሪክ አይጠቅመንም:: ታሪክ በፍትህ እጦት ተረስተው የታሰሩ ወንድሞቻችንን አያስፈታም፣

በኢድሏዊ ኢኮኖሚ ለተራቡት ወንድምና እህቶቻችን ምግብ አይሆንም፡፡"
ስሜቱ እየጋለ ሲሄድ በግልፅ ያስታውቅ ነበር፡፡

"ተረጋጋ" አለው ቶላ፣ ነገሩን ለማብረድ እየሞከረ፣ "ታሪክ ዳቦ አይሆንም እንዴት ትላለህ አንተ?... የዳቦ አመጣጥ፣ ከመጠሪያ ስሙ ጀምሮ የስንዴ አዘራር፣ አስተሜጨጨድና አፈጫጨት፣ የእሳት አነዳደዱ፣ የመጋገሪያ ምጣድ ስሪቱ በሙሉ ከታሪክ ውርርስ የመጣ መሆኑን አታውቅምን?" አለው አሁንም እርጋታ ሳይለየው፣

ቢሊሱማ ለደቂቃዎች ዝም ብሎ ሲያሰላስል ቆየና "ለተረትና ምሳሌማ አትሰንፍም፣ ግን እኔም መተረት አያቅተኝም፣ ስማ..." ብሎ ትንሽ አሰብ አደረገና፣ "‹ታሪክ ዳቦ ነው› የሚል ያ ምኝ ሰው ነው፣ ስለትላንቱ ሙክት እጁን አጣጥፎ ሲያወራ ዛሬ የተራበው፣ የትናንት ቡኮውን ዛሬ ላይ ሳይጋግር ሸጋታ እየዋጠው፡፡" አለ በታላቅ የድል አድራጊነት ስሜት፣

ቶላ ቢሊሱማን በንግግር እንደማያሳምነው ያውቃል፣ "እሺ አሁን የመጣከው ጥናቴን አስቁመህ ለመጨቃጨቅ ነው ወይስ?..." አለ በስሱ እየሳቀ፣

"አይደለም ባክህ... ነገ ከንቅናቄው መሪዎች ጋር አንድ ድብቅ ስብሰባ አለን፣ እንዳትቀር ልልህ ነው አመጣጤ፡፡"

"እሺ እሞክራለሁኝ... ያው ነገ ፈተናው ከተራዘመ..."

"አይ! አይ! እንደዚያ ብሎ ነገር የለም መምጣት አለብህ፣ ‹ቶላ መምጣት አለበት› ብለው በስምህ ነው የነገሩኝ..." አለ ቢሊሱማ ቆፍጠን ብሎ፣

"እሺ በቃ ካልክ እመጣለሁኝ!" አለ ቶላ በቀዘቀዘ ድምፅ፣

ቢሊሱማ ተነስቶ ሲወጣለት ቶላ የአብተውን ዘፈን ዳግም ከፍቶ ወደ ጥናቱ ተመለሰ፡፡ መታገልና ትምህርት፣ ራስን መቻልና ለውጥ ማምጣት... አንድ የሚመስሉ ግን የተራራቁ እውነታዎች ውስጥ ራሱን አገኘው፡፡

♪ ♫ "ፈጌኛ ነ ዶዌፍ መሌ - ሰያዱ ሂንዲ'ፍኔ ሃደኮ

ማሊ ን ጎዳ' ገሩ? - ፈጌኛቲ ሃ እማቱ - ነጋን ታኢ...

*** ☥ – ☥ ***

አብርሃምና ኢ.ትኤል ከጤና ቤተ መፅሐፍት ሲደርሱ መርየምና ቢ.ታንያ ቀድመዋቸው ደርሰው ከፊት ለፊታቸው ቁጭ ብለው እየጠበቋቸው ነበር:: የጅማ ዩኒቨርስቲ የጤና ተማሪዎች ቤተ መፅሐፍት ግቢው ውስጥ ከሚገኙ ቤተ መፅሐፍቶች በሙሉ የሚለይባቸው ሁለት ነገሮች አሉት:: አንደኛው የተማሪው ፍርሀት ወልዶት አየሩን ያከበደ ጭንቀት (ቴንሽን) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መለስተኛ ‹ስቲም› ውስጥ የገባህ እንዲመስልህ የሚያደርግ ሙቀቱ ነው:: ኢ.ትኤል ለዚህና መሰል ምክንያቶች የጤና ቤተ መፅሐፍት ውስጥ ማንበብ ብዙም አይመቸውም:: ዛሬ ግን ለጓደኛው ሲል ተገኝቷል፣ ከለበሰው ጥቁር ፖሎ ቲሸርት የተረፈው ቢጫ ወርቅ የመሰለ የቀይ-ዳማ ቆዳው ማራኪ ገፅታ ለግሶታል:: ጥቁር ሉጫ ፀጉሩን በጄል አስተኝቶታል:: በቃሪያ ጂንስ ሱሪው ስር በውድ ዋጋ እንደተገዛ የሚያስታውቁት ጆርዳን ጫማዎቹ አይንን ይስባሉ:: ከኢ.ትኤል በቁመቱ ረዘም የሚለው አብርሃም ከቀጭን ገላው ላይ የለበሳት ባለካሬ መስመር ሰማያዊ ሸሚዝ ትውለበለባለች:: ብዙ ጊዜ የሚያዘወትረው ባለስስ ሶል ሸራ-ጫማ ቀለል ያለ ዘንካታ ውበት ያላብሰዋል::

"የትኛው ነው አብርሃም?" አለች ቢ.ታንያ ወደ መርየም ጆሮ አስግጋ፣

"ረጅሙ ልጅ!" አለች መርየም በለሆሳስ፤

"አብሮት ያለውንስ ታውቂዋለሽ?" አለች ቢ.ታንያ፤ ከኢ.ትኤል በሺዎች የሚገዛ ጫማ ላይ ሳንባ እንዳየ ድመት እያፈጠጠች፤

"አላውቀውም፤ ዛሬ ገና ነው አብሮት የመጣው..." አለች መርየም ዓይኗን አብርሃም ላይ እንደተከለች::

አብርሃም ከነመርየም ፊትለፊት ያለውን ወንበር ጎትቶ ሲቀመጥ ኢ.ትኤልም ከጎኑ ተቀመጠ:: መርየም ሙስሊም መሆኗን ስለሚያውቅ እሷን መለየቱ አልከበደውም፣ ከጎኗ በተቀመጠችው ቀይ ልጅ ቁንጅና ግን መደንገጡ አልቀረም::

"ቆንጆ ነች አይደል?" አለው አብርሃም እንደማፈር እያለ፣

"በጣም እንጂ" አለ ኢ.ትኤል አይኖቹን ቢ.ታንያ ላይ እንደተከለ፣

ጥቂት የይስሙላ ጥናት ከተካሄደ በኋላ ቢ.ታንያ ከወንበሯ ተነሳችና ወደእነ ኢ.ትኤል ከላይብረሪው ህግ ውጪ በሆነ አረማመድ፣ ቋ.. ቀጭ, ቋ.. ቀጭ፣ እያለች መጣችና ከኢ.ትኤል ጎን ያለውን ወንበር እየጠቆመች፣

"እምም... ይሄ ወንበር ተይዟል እንዴ?" አለች ዝቅ ባለ ድምጽ፣ በተቀመጣጠለ አማርኛ፤

"አል... አልተያዘም" ኢ.ትኤል መለሰላት፣ ተቀመጠች::

የተቀባችው ባለልዩ መዓዛ ሽቶ ከገላዋ ላይ እየተነነ የኢትኤልን አፍንጫ ማወዱን ተያያዘው:: የወንድነትን ስሜት የሚፈታተን ሃይል እያሸነፈው በቆረጣ ሰውነቷን ሲመለከት እጅ ከፍንጅ ያዘችውና ሳቅ አለች፤ ምንም ሳታወራም አንድ ቁራጭ ወረቀት በመዳፉ አስጨበጠችው:: ወድያውም ተነስታ ወጣች፤ ኢትኤል የሰጠችውን ወረቀት ገለጠው፤ ‹ውጭ ወጥተን እናውራ በር ላይ እጠብቅሃለሁ› ይላል ፅሁፉ፤ ጊዜ ሳያባክን ብድግ ብሎ ወደ ውጭ ተቻኮለ፤ አብርሃምና መርየም እየተካሄደ ያለው ነገር ግራ እንዳጋባቸው ትርዒቱን ይከታተላሉ::

ነፋሻማ ምሽት ስለነበር ቢታንያ ለስላሳ ገላዋን በሁለት እጆቿ እቅፍ አድርጋ ነበር በር ላይ የቆመችው:: ኢትኤል ገና እንደወጣ እጁን ለትውውቅ ዘረጋላት፤ “ኢትኤል እባላለሁኝ፤”

“እንተ በጣም የሚገርም ስም ነው ያለህ... ጭራሽ ሰምቼው አላውቅም!”

“አዎ አሁን የት እንዳለ የማላውቀው አጎቴ ነው ያወጣልኝ፤ እንደነገሩኝ ከሆነ የሆነ የድሮ የኢትዮጵያ ንጉስ ስም ነገር ነው፤ ያንቺሳ ማነው?” አለ...

“ቢታንያ” አለች በለሰለሰ ድምፅ፣ ጣቶቹን በለስላሳ ጣቶቿ እየዳበሰች፤

“የሚያምር ስም ነው!” አላት በግነት፤

“አዎ የራሴ ነው” አለች እንደቀልድ፤ ሁለቱም ሳቁ ...

“እኔ የምልህ” ... አለች ከአፍታ ዝምታ በኋላ “እኔ የምልህ በመርየምና ባንተ ጓደኛ አብርሃም መካከል ስላለው ነገር ታውቃለህ?” አለችው ቀለል አድርጋ፤

“አዎ... የሷን ባላውቅም እሱ ግን በጣም እንደወደዳት በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁኝ::” ... ቆፍጠን ብሎ መለሰላት፤

“እሷም እንደዚያው ነው ስሜቷ... ፍርሃት እየለጎማቸው ነው እንጂ ሁለቱም በፎንቃ ተጠላልፈዋል ማለት ነው፤” ... አሁንም ለሁለት ሳቁ:: በመሃላቸው የተፈጠረው ኬሚስትሪ ሙቀት የሚተፋ ውህደት ሲፈጥር ታውቋቸዋል::

“ታዲያ ምን ብናደርግ ይሻላል?” አለና ኢትኤል ወደመጡበት አላማ ተመለሰ፤

“እንዴ ምን ጥያቄ አለው፤ ሁለቱም ለብቻቸው ተገናኝተው የሚሰማቸውን ነገር በግልፅ መነጋገር አለባቸው::” አለች ቢታንያ፤

“መቼ ቢገናኙ አሪፍ ይመስልሻል?”

"ጊዜ ማርዘም አያስፈልግም! ለምን አሁኑኑ አንተም አብርሃምን ጠርተከው እኔም መርየምን ጠርቼያት እንዲያወሩ እናደርጋቸውም?" አለች ቢታንያ፤ ምንም አይነት ቀጠሮ የመያዙ ጥቅም ስላልታያት:: የተሻለ ሃሳብ ያልነበረው ኢትኤል በሃሳቧ ተስማማና ተያይዘው ወደ ውስጥ ገቡ:: ቢታንያ መርየምን ኢትኤል ደግሞ አብርሃምን ወደውጭ ይዘው ለመውጣት ጊዜ አልፈጀባቸውም ነበር:: እነርሱ ባሉበት ካስተዋወቋቸው በኋላ እንዲያወሩ ብቻቸውን ትተዋቸው ሊሄዱ ሲሉ፤

"ወዴት ልትሄዱ ነው?" አለች መርየም ፍርሃት ቢጤ እየተነበበባት፤

"አይ እኔና ኢትኤል የምናወራው ነገር ስላለ ወከ እያደረግን እናውራ ብለን... እእ... እናንተም አየር መውሰድ ከፈለጋችሁ ተከተሉን" አለች ቢታንያ የኢትኤልን እጅ ይዛ ወደዋናው መንገድ እየገባች:: እነአብርሃምም በሃሳቧ ተስማምተው፤ ኢትኤልና ቢታንያ ከፊት፣ አብርሃምና መርየም በተወሰኑ እርምጃዎች ዘግየት ብለው እየተከተሏቸው የዝግታ ጉዞው ተጀመረ:: ቢታንያ ብርዱ ያስቸገራት ይመስል ከኢትኤል ከንድ ውስጥ ውሽቅ ለማለት ጊዜ አልፈጀባትም:: የፍርሃት ድባቡ ሙሉ በሙሉ ያልለቀቃቸው አብርሃምና መርየም ቀስ በቀስ ሞቅ ወዳለ ጭውውት ገብተዋል::

"እና መርየም ማለት ማርያም ማለት ነው አልሽኝ?" አለ አብርሃም ቀድሞ የሚያውቀውን ነገር አዲስ የሰማ ይመስል እየተገረመ፤

"አዎ... በእናንተ ሃይማኖት በጣም ትልቅ ቦታ ነው ያላት አይደል?" አለች መርየም እንዳጎነበሰች፤ በሙሉ አይን እሱን የማየት ድፍረቱ ገና አልነበራትም::

"በጣም እንጂ... ቅድስት ድንግል ማርያም መድሐኒዓለምን የወለደች፣ ለእኛ ኢትዮጵያውያንም የምህረትና ፍቅር እናታችን፣ እፁብ ሃብታችን ናት::" አለ ስክነት በተሞላበት አነጋገር፤

"ደስ ይላል!" አለች መርየም ስሟን ስለምትጋራት ቅድስት እናት የምታውቀውን ነገር ለማስታወስ አብሰለሰለችና፣ "ባይገርምህ በእኛም ሃይማኖት እኮ ብቸኛዋ ስሟ በቅዱስ ቁርዓን የተጠራላት ሴት መሆኗ ሳያንስ በስሟ ሙሉ የቁርዓን ምእራፍ የተሰየመላት ሴት ነች:: እኔም ስሜን በጣም ነው የምወደው ወላሂ!" አለች፤ ሳታስበው ስሜታዊ የሆነችም መሰላት፣ "ምዕራፉ ስለምንድነው የሚናገረው?" አላት አብርሃም በሚወዳት ድንግል እናት ስም የቁርዓን ምዕራፍ መኖሩ እያስገረመው፣ መርየም በበኩሏ ያልጠበቀችው ጥያቄ ስላጋጠማት ትንሽ ተደናግጣለች::

"እውነት ለመናገር እኔ ምን እንደሚል በደንብ አላውቅም::" አለች የሃፍረት ፈገግታ እያሳየች፤

"እንዴ ስለቁርዓን አታውቂም እንዴ?" እሱም ፈገግ ብሎ ጠየቃት፤

"አው ቃለሁኝ...ማለት ቁርዓን አኽትሚያለሁኝ ግን ተፍሲር አልተማርኩም፤"

"ምን ማለት ነው አልገባኝም?... ምንድነው ልዩነቱ?"

"ቁርዓን ማኽተም ማለት ቁርዓን አንብቦ መጨረስ ሲሆን ተፍሲር ማለት ደግሞ ትርጉሙን በጥልቅ ማጥናት ማለት ነው::"

"ስለዚህ አንቺ ቁርዓንን አንብበሽ ጨርሰሻል ማለት ነው?"

"አዎ ግን ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም::"

"ይቅርታ አድርጊልኝና ምንም የምትይኝ ነገር እየገባኝ አይደለም!" አለ አብርሃም የእውነትም ግራ እየተጋባ፤

"ምን መሰለህ ቁርዓንን አንብቤ ጨርሼዋለሁኝ ግን በአረብኛ ስለሆነ ትርጉሙን ብትጠይቀኝ ምን ማለት እንደሆነ በደንብ ልነግርህ አልችልም::" አለችው::

"አው... ኬ፤ አሁን ገና ገባኝ!" ብሎ ትንሽ አሰብ አደረገና "ግን እኮ ይሄ መሆን የለበትም የምታነቢውን ነገር ትርጉሙን ካላወቅሽ እኮ የአንደበት ማነብነብ ነው:: በእውቀትሽም በእምነትሽም ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ እዚህ ግባ የሚባል አይሆንም:: ቆይ ግን አንቺ ብቻ ነሽ ወይስ ሁሉም ሙስሊም ልጅ ቁርዓንን የሚማረው በማያውቀው የአረብኛ ቋንቋ ነው?"

"አዎ! አብዛኛው የሚማረው በአረብኛ ነው::"

"ታድያ ከዚህ ውስጥ ምን ያህሉ ናቸው ከማንበብ አልፈው ትርጉሙን የማወቅ ደረጃ የሚደርሱት?"

"ውይ እውነት ለመናገር ብዙዎቻችን ቁርዓንን ከማኽተም ባለፈ ለተፍሲር አንበቃም፤" አለች መርየም አንገቷን አሁንም ወደ መሬት እንደደፋች ፤

"እኔንጃ ብቻ በእኔ በኩል ሁለቱም አስተምህሮ ጎን ለጎን መሰጠት ያለበት ይመስለኛል::" አለና መልስ ቢጠብቅም የመሽነፍ የሚመስል ዝምታዋ ሲቀበለው ወሬ መቀየር እንዳለበት ገባውና "ምነው ዝም አልሽ?... ይቅርታ ሳላስበው ሌላ ርዕስ ውስጥ ገብቼ አስደበርኩሽ መሰለኝ" አላት፤

"ወላሂ ደብሮኝ አይደለም ዝም ያልኩት፤ የምታወራኝ ነገር የእውነትም ስላስገረመኝ ነው:: ከልጅነታችን ጀምሮ ከነትርጉማቸው ብንማር ኖሮ ምን ያህል እንደሚጠቅመን እያሰብኩኝ ነበር::"

"እሺ ስለተቀበልሽኝ አመሰግኛለሁኝ፤ እንግዲህ የምዕራፉን ነገር ከየትም ብለሽ ትነግሪኛለሽ፡፡ የምረሳልሽ እንዳይመስልሽ..." አለና እየሳቀ እጆቹን እንደዘበት ትከሻዋ ላይ ጣል አደረገው፡፡ መርየም የኤሌክትሪክ ገመድ ያነቃት ይመሰል እንደ ዘመንኛ ሞባይሎች ቫይብሬት አደረገች፡፡

"ምነው በረድሽ እንዴ?"

"አይ አልበረደኝም" አለች እጆቿን የሹራቧ ኪሶች ውስጥ እየከተተች፤ ሁለቱም የሚወዱትን ሰው አግኝተው ከቁብም ባይቆጥሩት እንጂ ምሽቱስ ብርዳማ ነበር፡፡ በስስ ሸሚዙ ላይ እያሾፈ ከሚጠበጥበው ብርድ ጋር ተስማምቶ መርየም ጋር መሆኑ ባይከብደውም መንቀጥቀጧ የመጣው ስለበረዳት ስለመሰለው ወደ ዶርሟ ሊሸኛት ወሰነ፡፡

"በጣም ደስ ብሎኛል በአካል ተዋውቀን ለማውራት በመብቃታችን" አላት ከሸራተን ካፌ ትይዩ ጋር እርምጃውን ገቶ እየቆመ፤

"እኔም በጣም ወላሂ!" አለች መርየምም፤ ካንገቷ ቀና ብላ በመንገዱ ዳር አንፖል ድጋፍ የአብርሃምን ፊት ለመጀመሪያ ጊዜ በደንብ እያስተዋለች፡፡ የሁለት እጆቹን መዳፎች በቀስታ ጉንጮቿ ላይ አሳረፈ፡፡ መርየም ፍርሃት እንደዋጣት የሷንም እጆች እሱ እጆች ላይ ደረበቻቸው፡፡ በቀስታ ተጠጋትና ግራ ጉንጯን አንድ ጊዜ፣ ቀኝ ጉንጯን አንድ ጊዜ ሳማቸው፡፡ ቀጥሎም ወደደረቱ ለጠፋትና ጥብቅ አድርጎ አቀፋት፡፡

"እወድሻለሁኝ!" በጆሮዋ አንሾካሾከ፤

"እኔም እወድሃለሁ!" አለች መርየምም በለሆሳስ፤

ሁለቱም ተቃቅፈው፣ አይኖቻቸውን ከድነው ምን እያሰቡ እንደሆነ እንኳን በማያውቁበት ልዩ የሃሴት ስሜት ተውጠው፣ የአንጎል ህዋሶቻቸው የሚወዛወዙበት ዜማ ውስጥ ዘልቀው ተመስጠው ለረጅም ደቂቃዎች ቆዩ፡፡

"ወደዶርም ልሸኝሽ?" አለ አብርሃም አይኖቹን እየገለጠ፤

"እ... እሺ" አለች መርየም በደከመ ድምፅ፡ የእውነትም እንቅልፏ መጥቶ ነበር፡፡ ነገሩ የሰላም እንቅልፍ ከምቹ ቦታና ከተደላደለ አልጋ ይልቅ ንፁህ የአዕምሮ እረፍትን ነው የሚፈልገው፡፡

"መቼ ነው ድጋሚ የማገኝሽ"

"እንደዋወልና ‹ፍሪ› በሆንን ቀን እንገናኛለን፤... እኔ የምልህ አብርሽ... እነዚህ ልጆች የት ገቡ?" አለች መርየም በቅርብ ርቀት ሲከተሏቸው የነበሩት ኢትኤልና ቢታንያ ከአይናቸው መሰወራቸውን ድንገት አስተውላ፤

"እውነትም የት ገቡ?" አላት አብርሃምም፤ አጠፋፋቸው እያስገረመው፡፡

*** ፉ – ፉ ***

ቢታንያ የተቀባችው ጣፋጭ ቻፒስቲክ ከንፈሮቿን መሳሙን እንዳያቆም ኢትኤልን አስሮ ይዞታል:: ካንዱ ባዶ የጋራ ማንበቢያ ሲደርሱ እንዴት እንደገቡና እንዴት መሳሳም እንደጀመሩ ሁለቱም በቅጡ አያስታውሱትም:: ለምን ያህል ሰዓትም ሲሳሳሙና በስሜት ተውጠው ሲተሻሹ እንደነበርም አያውቁትም::

....ኢትኤል በስሜት ማእበል ውስጥ እያለ ስልኩ መጥራት ጀመረ:: እንዳልሰማ ሆኖ ሊያልፈው ቢሞክርም ጠርቶ በዘጋ ቁጥር ዳግም እየተደወለ እረፍት ነሳው:: ስልኩን አውጥቶ ሲያይ ‹**ፅዮን**› የሚል ስም በደማቁ ታየው:: ምን ፈልጋ ይሆን በዚህ ሰዓት የምትደውለው ብሎ ቢገረምም የቢታንያ ጣፋጭ ከንፈር ስላሸነፈው ስልኩን ዘጋና ሊስማት ወደ ቢታንያ ሲመለስ ወደኋላዋ ሸሽታ ከለከለችው፤ “ምነው?” አላት ግራ እየተጋባ፤

“ማናት ‹ፅዮን› በዚህ ሰዓት የምትደውልልህ?” አለች ቢታንያ ኩስትርትር ብላ፤

“አብሮ አደግ ጓደኛዬ ናት!” አለ ኢትኤል ነገሩን ቀለል ለማድረግ እየሞከረ፤

“ብትሆንስ ታድያ ለምንድነው በሌሊት የምትደውልልህ... ወይስ የደበቅኸኝ ፍቅረኛ አለችህ እንዴ?” አለች እጇቿን እያወናጨፈች፤

“ኧረ በፈጠረሽ! እንደሱ አይደለም ማሬ!” አለ ኢትኤል ሊያረጋጋት እየሞከረ፤ ያን ከመሰለ ጣፋጭ ከንፈር መነጠሉ እጅጉን እየቆረቆረው፤

“እንቺን ደስ ካላለሽ ሁለተኛ አላናግራትም::” አለ፤ በውስጡ የማይፈፅመውን ቃል እንደገባ እየታወቀው፤

“በሱ ብቻማ አልፋታህም” አለች ቢታንያ፤ አኩርፌ'ኻለሁኝ በሚመስል ለዛ፤ “እንድንታረቅ ከፈለግክ አሁን እያየሁኝ እሷን ከምባይልህ ብሎክ ታደርጋታለህ እና ደግሞ...”

“እና ሌላ ምን ልቀጣ?...” አለ ኢትኤል ፅዮንን ብሎክ ለማድረግ ስልኩን እያወጣ፤ ቢታንያ እያየች ፅዮን ብሎክ ከተደረገችላት በኋላ፤

“ነገ ቆንጆ እራት ትጋብዘኛለህ::” ብላ ሁለተኛ ትዕዛዟን አስተላለፈች፤ ብር በገፍ የሚላክለት ኢትኤልም እራት የመጋበዝ ችግር የለበትም፤ የፈለገችውን እራት እንደሚጋብዛት ቃል ገባላት:: ዘላ ከንፈሮቹ ላይ ሰፈረችባቸው::

*** ፉ – ፉ ***

ወ/ሮ ቤዛዊት "እማ" የሚለውን ድምፅ ሰምተው ሲዞሩ ፅዮንን ተመለከቷት፡፡ ተንደርድራ መጥታ በጉልበቷ ተንበረከከችና አንገታቸው ላይ ተጠመጠመች፡፡ እንባዋ መንታ መንታ እየሆነ ከእናቷ አንገት ላይ እንደ ጅረት ይፈስ ጀመር፡፡ ለረጅም ሰዓት አልቅሰው ሰውነታቸው ሙትት ያለባቸው ወ/ሮ ቤዛዊት የልጃቸው መምጣት ሀዘናቸውን አገርሽቶት እንደ አዲስ ዋይታውን ያቀልጡት ገቡ፡፡ የእናትና ልጅ ለቅሶ የመቃብር ስፍራውን ረብሾት ኖሮ የመቃብሩ ጠባቂ ዘብ መጣና ለማፅፅናናት እየሞከረ እስከ መውጫው ድረስ ሸኛቸው፡፡

ፅዮንና ወ/ሮ ቤዛዊት እርስ በርስ እየተደጋገፉ፣ አንዳንዴም እያረፉ ስላዘገሙ ቤታቸው ሲደርሱ እኩለ-ሌሊት ሆኖ ነበር፡፡ ወ/ሮ ቤዛዊት ሳምንታዊ የእድር መዋጮ መክፈል አቅቷቸው ከሰፈሩ እድር ከተሰናበቱ ቆይተዋል፡፡ ነገር ግን በጣም የቀረበ ጉርብትና የነበራቸው አስተዛዛኞች ጥቂት አግዳሚ ወንበሮችን ደርድረው ከቤታቸው ደጃፍ ለቅሶ ተቀምጠው ነበር፡፡ እነርሱም ቢሆኑ እነወ/ሮ ቤዛዊት በጣም ሲያመሹባቸው ወደየቤታቸው ተከተዋል፡፡ እናትና ልጅን የጠበቃቸው ባልና አባት የሌለበት ቀዝቃዛው እና ቤት ነበር፡፡ ቃላትም የነበሩበትን ትካዜ የመግለፅ አቅም ስላልነበራቸው ወ/ሮ ቤዛዊት እራት እንድትቀምስ ከመጠየቃቸውና ፅዮንም ለአመሉ ሁለት የእንጀራ በሽሮ ጉርሻዎችን ከሙብላቷ በስተቀር ምንም ሳያወሩ ከሽቦ አልጋቸው ላይ እንደተጋደሙ ነበር ሌሊቱን ያገባደዱት፡፡

ፅዮን የሌሊቱን አብዛኛውን ክፍል እንቅልፍ የሚባል በዓይኗ ሳይዞር በሀሳብ ስትንከላወስ ነበር የቆየችው፡፡ አባቷን ለረጅም አመታት የአልጋ ቁራኛ ያደረገው ህመም አንድ ቀን ይዟቸው እንደሚሄድ ሁሌም ልቧ ያውቀው ነበር፡፡ ግን አባቷ ሀብት ባይኖረውም፣ አምሮበት በጤንነት ባይታይም በህይወት መኖሩ ብቻ ለልጅ መመኪያ ነውና ስታጣው በጣም ተከፍታለች፡፡ የሁልጊዜ ምኞቷ፣ የምርቃት ቀኗ ላይ ያቺው የሚተኙበት አልጋ ድረስ ጥቁር የምረቃ ካባዋን ለብሳ መጥታ ግንባራቸውን መሳም ነበር፡፡ እቅዷ ሊሳካ ጫፍ ደርሶ መና እንደቀረ ስታስብ የእንባ ዘለላዎች አፍንጫዋን እየዘለሉ ወደትራሷ መንጠባጠብ ጀመሩ፡፡ እንባዋን ጠራረገችና በጀርባዋ ተኝታ ቅድም መቃብሩ ስፍራ ስላየችው ነገር ማሰብ ጀመረች፡፡ *ከጅማ የያዘችው ዶልፊን መሳይ መኪና ምሽት ላይ አዲስ አበባ እንዳስገባት ወዲያው የቀጨኔን ታክሲ ተሳፍራ ወደቤቷ ነበር ያመራችው፡፡*

ቤት ገብታ እናቷ ከቀብር አለመመለሷን ስትሰማ ነበር እየበረረች ወደ መቃብር ስፍራው ያመራችው:: እንደ ደረሰችም እናቷ አንድ አባቷን የሚመስል የሰው ቅርጽ ፊት ቆማ ስታወራ በብዥታም ቢሆን ከሩቅ ማየቷን እርግጠኛ ነች:: ያ… ሰው ግን ከቦታው ስትደርስ ወደየት እንደተሰወረ አላወቀችም:: ብዙ ብዙ ጥያቄዎች ውስጧን እንደሞሉት ሊነጋጋ አካባቢ እንቅልፍ ጣላት::

በበነጋታው የመርዶው ዜና ዘግይቶ የደረሳቸው አንዳንድ ሰፈርተኞች ከበር ላይ ሲያለቀሱ ለስሙ የተኙትን እናትና ልጅ ቀሰቀሷቸው:: ወ/ሮ ቤዛዊት በወጉ እንኳን ፊታቸውን ሳይታጠቡ፣ ሻሻቸውን ሸብ አድርገው ወጥተው ለቅሶውን ተቀላቀሉ:: ለተወሰኑ ደቂቃዎች ሙሾ ከወረደ በኋላ በርካታ የማፅናናት ጥረት ተደርጎ የተፈጠረው የለቅሶ ጡዘት ረገበ:: ወ/ሮ ቤዛዊትም ጋቢውን በወገባቸው ሸብ አድርገው ከልጃቸው አጠገብ ተቀመጡ:: ፅዮን ማታ ሲመላለሱባት የቆዩትን ጥያቄዎች ለማቆየት ትዕግስቱ አልነበራትም::

“እናቴ… እባክሽን ሃዘንሽን ገድቢው፤ አንቺ የሆነ ነገር ብትሆኚ እኔ አላሳዝንሽም?” አለች፣ ዘንበል ብላ ከትከሻቸው ላይ ጭንቅላቷን እያሳረፈች፤

“ምን ላድርግ ብለሽ ነው ልጄ፣ ባዶ ሜዳ ላይ ጥሎኝ ሲሄድ ታድያ ምን ልበል?” አሉ አሁንም ሳግ እየተናነቃቸው፤

“እኔ… እኔ አለሁሽ አይደል እማ!” አለች ፅዮን በቀለስታ፣ እናቷን ለማፅናናት እየሞከረች ቢሆንም እሷም እንባዋ እየታገላት ነበር::

“እሺ ልጄ… አንቺንማ ጥሎልኝ ሄዷል ቸሩ መድሐኒዓለም ይመስገን!” አሉና እቅፍ አድርገው ግንባሯን ሳሟት::

“እማ ግን አንድ ጥያቄ አለኝ?” አለች ፅዮን ካፍታ ዝምታ በኋላ፤

“ምን ልጄ?” አሏት፤ አሁን ትንሽ የተረጋጉ ይመስላሉ፤

“ትናንትና ከመቃብሩ ስፍራ ከማን ጋር ነበር የምታወሪው?…”

ወ/ሮ ቤዛዊት ድንግጥ ሲሉ በግልፅ ያስታውቅባቸው ነበር::

“እ… እንዴት… ለምን አለሽ?… ምን አይተሽ ነው?…” ተንተባተቡ፤

“አይ… ትናንት ከመቃብሩ ስፍራ ስደርስ ከአንድ አባቴን ከሚመስል ሰው ጋር እያወራሽ ከሩቅ አይቼሽ ነበር:: አጠገብሽ ስደርስ ግን ሰውዬው የት እንደገባ ሳላውቅ ጠፋብኝ::”

“በቃ ስለዚህ ጉዳይ ማታ እናወራለን::” አሏትና ብድግ ብለው ከለቀስተኛው ጋር ተቀላቀሉ::

ያ እለት የትኩሱ መርዶ ማግስት እንደመሆኑ ፅዮን በከንፈር መጠጣ፣ "የምታሳዝን ልጅ!"… "እይዞሽ ፅናቱን ይስጥሽ!" በሚሉና መሰል ማፅናኛና ማስተዛዘኛ ቃላት ታጅባ ነበር የዋለችው፡፡

*በእለቱ ከመጡት ለቅሶ ደራሽ ሰዎች መካከል የሩቅና የቅርብ ዘመዶች ዋነኞቹ ሲሆኑ ከኢትኤል አባት አቶ ሳአልና እናቱ ወ/ሮ አመቤት በቀር ሁሉም ጎረቤቶቻቸው መጥተዋል፡፡ እነአቶ ሳአል አለመምጣታቸውን የታዘቡት ወ/ሮ ቤዛዊት…"ድሮስ ማን ገደለውና ይመጣሉ! ለእነርሱማ የምስራች ነው!" እያሉ ሲያጉረመርሙ ፅዮን ሰምታቻዋለች፡፡ ምን ለማለት ፈልገው እንደሆነ ግን አልገባትም፡፡ ትናንት ወዲያ ስልኩን አለማንሳቱ አንሶት እስካሁን ድረስ መልሶ ያልደወለው የኢትኤል ጉዳይም አንቆቅልሽ ሆኖባታል፡፡… እንዲህ እንዲህ እያለ ቀኑ አለፈና ለቀስተኞች አንድ በአንድ ሄደው አበቁ፡፡ ሁሉም ተሰናብተው እናቷና እሷ ብቻ እስኪቀሩ ጠበቀችና ፅዮን ጥያቄዋን ደገመችው፤ ወ/ሮ ቤዛዊት ጥቁር የሃዘን ልብሳቸውን ሸብሸብ አድርገው ቆመው የሆነ ሰው እንደሚጠብቁ በር በሩን ያያሉ፡፡* "ትናንት ከማን ጋር ነበር የምታወሪው እማ? ንገሪኝ?!" *አለች ፅዮን፡፡*

ወ/ሮ በቀስታ ከጎኗ ተቀመጡና ትኩር ብለው አይኖቿን እያዩ "የአባታሽ የሙት መንፈስ ጋር ነው ያወራሁት" አሏት፡፡ ፅዮን ከው ብላ ከእናቷ አፈገፈገች፡፡

"ምን? … ይሄንማ አላምንም እማ… ተመሳስሎብሽ ይሆናል፣" አለች ለሚሉት ነገር ታእማኒ ምክንያት ሊኖረው እንደሚችል እያሰበች፤

"አልተመሳሰለብኝም ልጄ… ቃዡቼም አይደለም! እመኚኝ የአባትሽን የሙት መንፈስ አውርቼዋለሁኝ፡፡ የሞተው ድግምት ተሰርቶበት እንደሆነም ነግሮኛል፡፡" አሉ ወ/ሮ ቤዛዊት እርግጠኝነት እየተነበበባቸው፤

"የምትይውን ማመን ይከብደኛል እማ! አባቴ እኮ ለሁሉም አሳቢና ፀብ የማይወድ ሰው ነበር፤ ማነው እሱ ላይ ድግምት የሚያሰራው?… ይሄማ የማይመስል ነገር ነው!" ብላ ተሚገተች ፅዮን፣ የምትነግራትን ማመን ቢከብዳት፤ *"ያሰሩበትንማ ሰዎች ማንነት ልቤ ያውቀዋል፡፡ ሌላ ማድረግ የምንችለው ነገር ካለ እንዲረዱን አንድ የተከበሩ አዋቂ አሉ ተብሏል እስኪ ከሰምኑ እንሄዳለን"* አሉ ወ/ሮ ቤዛዊት፤

"እንግዲህ አንቺ ካልሽ ምን አደርጋለሁኝ" አለች ፅዮን አሁን ሃሳባቸውን ማስቀየር እንደማትችል ታውቃለች፡፡ በማግስቱ በማለዳ ተቀሰቀሰች ነገር ግን አዋቂ ነው የተሰኘው ሰው ጋር እንደምትሄድ ፍፁም አልጠበቀችም ነበር፡፡

*** ቶ – ቶ ***

በትላንትናው የጋሽ ጀንበሬ ለቅሶ ላይ ያልተገኙት አቶ ሳዖልና ባለቤታቸው ወ/ሮ አመቤት እራት ለመመገብ ከማዕዱ ጠረጴዛ ተሰይመዋል:: በጠረጴዛው ላይ የተደረደሩት ቀይና አልጫ፣ ጥብስና ዱለት ወ.ዘ.ተ የተሞሉት ጎድጓዳ ሳህኖች የምግብ ፍላጎትን ይከፍታሉ:: ‹ርሃብን የማያውቅ የምግብ ጠዓሙ አይታወቀውም› እንዲሉ ለአቶ ናዖልና ወ/ሮ እመቤት ግን ምንም ልዩ ስሜት የሚፈጥር ስነ-ስርዓት አልነበረም:: ይልቅስ የጎረቤታቸው መሞት ሁለቱንም የደስታ ስሜት ውስጥ ከቷቸው ነው የዋለው::

እራታቸውን እየተመገቡ ወደማጋመስ ላይ እንደደረሱ የአቶ ናዖል የሁለት ላፕቶፖች ዋጋ ያለው ሞባይል ስልክ አቃጨለ::

"እስኪ አንዴ ቴሌቭዥኑን ዝጉት አባታችን ነው የደወሉት" አሉና እየተቅለሰለሱ በግራ እጃቸው ስልኩን አነሱት፤

"ሄሎ አባታችን እንደምን ሰነበቱ?"

"እኛማ ዑቃቢያችን እያለልን ምን እንሆናለን ብለኸ ነው?... ይልቅ እናንተ እንዴት ናችሁ?... ‹ኮብራ›ስ እንዴት ነው በደንብ እየመገባችሁት ነው?" አለ በስልኩ ጫፍ ያለው ሰው በጎርናና ድምፅ፤

"እዎ ሁሉም ሰላም ነው፤ እድሜ ለእርስዎ!... ‹ኮብራ›ንም በሚገባ እየመገብነው ነው:: አሁንማ ደልቦ አምሮበታል" አሉ አቶ ሳኦል፤

"እንደዚያ ነው ወጉ፣ የገባችሁለትን ቃል-ኪዳን መዘንጋት አያስፈልግም:: ይልቅ አንድ ጉዳይ ነበራችሁ እኔ ዘንድ"

"ምን ጉዳይ ጌታዬ?" አሉ አቶ ሳኦል፤ አሁንም እየተቅለሰለሱ::

"እርሱን በአካል ስትመጡ ይነገራችኋል:: ነገ ከከሰዓት መጥታችሁ ጎብኙኝ፤ እንግዲህ የተለመደችውን እጅ መንሻችሁን ጨምሮ ጥቁር ፍየል ማምጣት እንዳትረሱ!!..."

"እሺ ጌታዬ ታዛዥ ነኝ!"... ስልኩ ተዘጋ::

በማግስቱ ረፋድ አንድ ሙሉ በሙሉ ጥቁር የሆነ ፍየል እነአቶ ሳዖል ቤት ተገዝቶ መጣ:: ከሰዓት ሲሆንም ባለ ድፍን መስታወቱ ‹ቪ. 8› መኪና ውስጥ ታስሮ ገባ:: ከደቂቃዎች በኋላ መኪናውን አቶ ሳኦል እያሾፈሩ ከግቢ ሲወጡ ወ/ሮ አመቤትም ከጎናቸው ነበሩ::

*** ቶ – ቶ ***

በቀጨኔ ሰፈር ለየት ብሎ የሚታይ፣ ብሎኬቶች በብሎኬቶች ላይ አለቅጥ ተደራርበው ያረዘሙት ረጅም ግንብ ያጠረው አንድ ግቢ አለ:: የግንቡ አናት በኤሌክትሪክና የብረት ምላጮች አዙሪት ከጫፍ እስከ ጫፍ ግጥም ተደርጎ ተሰናስሏል:: ዘራፊ ሌባን ብቻ ሳይሆን ጥሬ ለቃሚ ወፍም እንዳያስገባ ታስቦ የተሰራ የባቢሎን ግንብ ይመስላል:: እርግጥም እዚህ ግቢ ገብቶ ነፍስና ስጋ ሳያስይዙ በነፃ ፍሬ ለቅሞ መውጣት አይታሰብም::

አቶ ሳያልና ወ/ሮ እመቤት መኪናቸውን በርካታ ውድ ውድ ሞዴል መኪኖች አጠገብ ፓርክ አድርገው ሲወርዱ በእምነበረድ የተዋበ የተንጣለለ ግቢ ነበር የጠበቃቸው:: ግቢው አማካይ ላይ የተሰራው ግዙፍ ባለሁለት ፎቅ ቪላ ካለቃላት የፈሰሰበትን መዋዕለ-ንዋይ ይመሰክራል:: አንድ ቡራቡሬ ቀሚስ የለበሰ፣ ፎጣ ያገለደመ አጋፋሪ መጣና ጎንበስ ብሎ እጅ ነሳ::

*"ለሁሉ ደራሽ፣ በከራማቸው ሰረገላ ምድርን የሚያዳርሱት ታላቁ አባታችን መምጣታችሁን ቀድመው ያውቁ ነበርና አሁን እናንተን እየጠበቁ ነው... ግን አምጡ የተባላችሁትን ግብር አምጥታችኋል?" አላቸው::*

*"አዎ በሚገባ" አሉና አቶ ሳያል ከመኪናው የጀርባ ክፍል ጥቁር ፍየል እየጎተቱ አውጥተው አስረከቡ::*

*"እንግዲያውስ ተከተሉኝ" ብለዋቸው ወደ ውስጥ ዘለቁ፣*

*እነአቶ ሳያል ሁልጊዜ እዚህ ጠንቅ-አዋይ ቤት ሲመጡ እንደሚያደርጉት ጫማቸውን አውልቀው ገቡና ወለሉ ላይ እየተደፉ እየቆሙ ሁለት ጊዜ ሰገዱ:: ቤቱ አይንን በሚጋርድ፣ ለመተንፈስ በሚያዳግት ደረጃ በእጣን ጭስ ተሞልቷል:: ፊትለፊት በግዙፍ ወርቃማ የቱርክ መጋረጃዎች ከተጋረደው መደብ ላይ የተቀመጠ ሰው ቅርፅ ጥላ ይታያል:: ከመደቡ ስር መጋርጃው አጠገብ የተቀመጠው መለስተኛ ጠረጴዛ የሚያክል ረከቦት ላይ ሲኒዎች ተደርድረዋል:: የመጋረጃዎች ተቀጥያ የሚመስለው ቡኒ ምንጣፍ ግራና ቀኝ ላይ በተለምዶ አረቢያን መጅሊስ የሚባሉት እግር አልባ ሶፋዎች*

ተሰድረዋል፡፡ ከየት እንደታጨደ ማየትን የሚያጓጓ አገዳ የሚያካክል ቋጤማ ወለሉን አጥለቅልቆታል፡፡

"ተነሱና ወደዚህ ኑ!" የሚል ጎርናና ድምፅ ከመጋረጃው ጀርባ ተሰማ፤

በዝግታ ተነሱና ቄጤማውን እንዳይረግጡ እየተጠነቀቁ ተራምደው ከመጋረጃው በቅርብ ርቀት ላይ ካለው አረቢያ መጅሊስ ላይ ተቀመጡ፡፡

"በኛ በረከት ይዘናችሁ ህይወት በድሎት እየሄደላችሁ እንደሆነ እናውቃለን… "

"አዎ አባታችን! እርስዎ እያሉ ምንም አልጎደለብንም፣ በእርስዎ መጀን!" አሉ አቶ ሳሪል አንገታቸውን ወደመሬቱ እንደደፉ፤ ቤቱ በሙሉ በሙገሳና እልልታ ተሞላ፤

"እንግዲያውስ እናንተ ስተኙ እኛ ሳናሸልብ ለምንሰጣችሁ አገልግሎት ከፍያችን የታለ… ያልኩህንስ አመጣኸ?"

"አዎ አባታችን! እንዳሉኝ ጥቁር ፍየል አምጥቼያለሁኝ"

"እርግጥ ነው ተቀብለናል አባታችን" አለ አጋፋሪው መሬት እስኪነካ ድረስ እጅ እየነሳ፤ ቤቱ በምስክርነትና እልልታ ደመቀ፡፡

"ማለፊያ ነው፤ እንግዲህ ወደተጠራችሁበት ጉዳይ ሳልፍ ከሰሞኑ ከእናንተ ጋር በተያያዘ አንድ መልዕክት ውቃቢዬ አድርሶኛል፡፡"

"ምን አይነት መልዕክት አባታችን?"

"ከእውቀታችን ፈቅደን፣ ዓውደ-ነገስት ገልጠን፣ ዛራችንን እየላክን ጎረቤታችሁ ያሉትን ጋሽ ጀምበሬን እንዳሸመደመድንላችሁ የምትዘነጉት አይመስለኝም?"

"ውለታዎንማ እንዴት እንረሳለን?" አሉ አቶ ሳሪል፤ አሁንም እየተሸቆጠቆጠ፡፡

"ታድያስ የፈለጋችሁትን መሬት ወስዳችሁ፣ ሃብታችሁም በልፅጎ ሲያበቃ የሰካንበት መርፌ ጠዝጥዞ ጠዝጥዞ ሲገድለው ምነው ማመስገኑን ረሳችሁሳ!" ከመጋረጃው ጀርባ ያለው ሰው የቁጣ ድምፅ አሰማ፡፡

"ጌታዬ ይቅርታ ያድርጉልን እኛ አላዋቂዎች ነን!" አያሉ አቶ ሳዖል ወደ መሬት ተደፉ፣ ወ/ሮ አመቤትም እንደርሳቸው አደረጉ፤

"ከራማችን ምህረት አድርጎላችኋል ተነሱ፤ አሁን የተፈለጋችሁት በቅርቡ የሞቱት ጋሽ ጀምበሬ ባለቤትና ሴት ልጃቸው ፅዮን የምትባል ሴት ከሰሞኑ ወዳጃችን ከሆነ ‹አዋቂ› ዘንድ መሄዳቸውን ዑቃቢያችን ስለነገረን ነው፡፡ ‹አዋቂ›ውም ድግምቱን እናንተ እንዳሰራችሁባቸው ነግሯቸዋል፡፡ እንግዲህ ጠላቶቻቸውን ካወቁ ቀጣይ እርምጃቸው እናንተን መበቀል እንደሆነ አትጠራጠሩ፡፡"

አቶ ሳዖልና ወ/ሮ አመቤት በድንጋጤ ተያዩ፡፡ ሚስጥራቸው ከተጋለጠ ሌላው ቢቀር ስማቸው መጥፋቱ አይቀርም፡፡

"ምንድነው ማድረግ ያለብን ጌታችን፣ አዋቂው እርሶ እንጂ እኛ አይደለንም?" አሉ አቶ ሳኦል፤

"እኛ ቢያንስ ድግምቱን ማሳደስ እንዳለባችሁ እንነግራችኋለን፡፡ ነገር ግን ያለፈውን ብቻ ብታሳድሱ የያኔው ድግምት ልጅቱን አያካትትም ነበርና አሁን እሷ ልትበቀላችሁ ትችላለች፡፡ እናም አዲስ ትብታብ ብታሰሩ ይሻላችኋል፡፡" አለና ያ ከመጋረጃ ጀርባ ያለው ጠንቅ-አዋይ ወደኋላው ደገፍ ብሎ በወገቡ ተቀመጠ፡፡ አቶ ሳዖልና ወ/ሮ አመቤት ከጠንቅ-አዋዩ ጋር ከመስማማት በስተቀር የተሻለ የመፍትሔ መንገድ ሊታያቸው አልቻለም፡፡

*** ♀ – ♀ ***

መርየም ከአብርሃም ጋር ቆይታ ስትገባ ቢታንያ ዶርም አለመግባቷን አወቀች፡፡ ሰዓቷን ስትመለከት ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ይላል፡፡ ሁሉም የዶርም አባላት የሞት ታናሽ ወንድም ከሆነው እንቅልፍ ጋር ተሻርከው ነፍሳቸውን አያውቁም፡፡ አልጋዋ ላይ ጋደም አለች፡፡ ከአብርሃም ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ አብረው ያሳለፉትን ጊዜ በሃሳቧ ማዕድ ውስጥ ከለሰችው፡፡ ቀድማ በአይኗ ብቻ እያየችው የወደደችለትን አይናፋርነትና እርጋታ አሁንም በአካል ስታወራው አግኝተዋለች፡፡ ቃላት አመራረጡ፣ እርጋታውና ቁም-ነገሩ ማርኳታል፡፡ በቃ ፈልጋለች፤ አንድ ሦስት የቀይ ዳማ ልጆችን ልትወልድለት ፈልጋለች፤ እድሜዋን በሙሉ አብራው ብታሳልፍ ደስተኛ እንደምትሆንም አምናለች፡፡........〈ግን〉 አለች ፤ ድንገት ሳታስበው ፊቷ ላይ ተፈጥሮ የነበረው ፈገግታ እየደበዘዘ፤ "ግን ክርስቲያን እኮ ነው! እንዴትስ ሆኖ ይሆን የምንቀጥለው... እንዴትስ ብለን ነው የቤተሰቦቻችንን ፍቃድ አግኝተን አብረን የምንዘልቀው?... የዩኒቨርስቲው የሙስሊም ጀምዓ ጓደኞቼስ ምን ይሉኛል?... ተደብቀን ሳይታወቅብን ብንዘልቅ እንኳን እንዴት ነው የምንጋባው?" ቀስ በቀስ ጭንቀቷ ባሰ፡፡

ያልተመለሱ ጥያቄዎች አዕምሮዋን ውጥር አድርገው ቢይዟት አንድም ለመረጋጋት ሁለትም ለጭንቀቷ መልስ ከሰጠኝ ብላ ከሞባይሏ ላይ በድምፅ የተቀዳ ቁርዓን ከፍታ በጆሮ ማደመጫዋ ማዳመጥ ጀመረች፤ ውስጧ ቀስ በቀስ ሲረጋጋ ይታወቃታል፡፡ ከአረብኛ ቋንቋ የምታውቀውን ያህል እየተረጎመች ለደቂቃዎች ከሰማች በኋላ ቅድም ስለቅዱስ-ቁርዓን ትርጓሜ አብርሃም ያለው ትውስ አላት፡፡ ኢንተርኔት ከፈተችናም የቁርዓን አማርኛ ትርጉም ወደ ስልኳ ጫነች፡፡ ሱረቱል መርየምን ከፍታም ብዙ አነበበች፤ ብዙ አዳዲስ ነገሮችም አወቀች፡፡ ለአንድ ሰዓት ያህል ቁርዓን ስታዳምጥና ስታነብ ከቆየች በኋላ አጅሬ እንቅልፍ እርሷንም ጣላት፡፡

ሌሊት 9 ሰዓት አካባቢ ግን አንድ እጅ ትከሻዋን ይዞ ነቅነቅ፣ ነቅነቅ አደረጋት፡፡ "ሚሩ? ... ሚሩ? ... ተነሽ!" አለቻት ቢታንያ በለሆሳስ፤ መርየምም አይኖቿን በመከራ ገልጣ አየቻት፡፡
"ሳምኩት እኮ!" አለች ቢታንያ፤ ከዚህ በፊት ፊቷ ላይ ታይቶ የማይታወቅ ፈገግታ እየተስተዋለ... "ማ... ማንን?" አለቻት መርየም በእንቅልፍ ልብ፤

"ኢትኤልን ነዋ!"... "ማነው ኢትኤል?"

"የአብርሃም ጓደኛ ኢትኤል ነዋ!" መርየም መልስም ሳትሰጣት ወደ እንቅልፏ ተመለሰች፡፡

*** ፱ – ፱ ***

ፅዮንና ወ/ሮ ቤዛዊት ከአዋቂው ቤት ከመጡ ጀምሮ ፅዮን ከራሷ ጋር ሙግት እንደገጠመች አለች፡፡ አዋቂው ሰውዬ በልዩ ልሳን ቃላትን ካጉተመተመ በኋላ የአባቷ ገዳይ ጎረቤቶቻቸው እነአቶ ሳዖል መሆናቸውን ሲነግራት ከልጅነት እስከ አውቀት ያሳለፈችው ህይወት ትርጉም ተዘበራረቀባት፡፡ በእርግጥ እናቷ አንድ አዋቂ ሸማግሌ እሱ እናማከራቸው ብላ የወሰደቻቸው ጠንቅ-አዋይ ዘንድ እንደሆነ የተረዳችው በመጨረሻው ሰከንድ ነበር፡፡ ሆኖም የሰማችው ነገር ሃሰት ነው ብሎ ለመካድ አጅግ አዳጋች ሆኖባታል፡፡ እናቷም እንደነገሯት ገና በማህፀን ሳለች በእነርሱና በእነአቶ ሳዖል መካከል የተከፈተው የመሬት ይገባኛል ጥያቄ ከፍተኛ መቃረንን በሁለት ቤተሰቦች መካከል ፈጥሮ ለአመታት ቆይቶ ነበር፡፡ በስተመጨረሻ ግን የጋሽ ጀንበሬን መታመም ተከትሎ እነአቶ ሳዖል በአጅም ጭምር ሄደው የማይገባቸውን ሰፊ መሬት ወሰዱ፡፡ ስማቸውን አሳውጀው ያስከበቡትን ቦታ በታላቅ ግንብ ሲያሳጥሩ ፅዮን ነፍስ አውቃ ያልጨረሰች ትንሽ ልጅ ነበረች፡፡ እየተደረገ ያለው ነገር ባይገባትም የእናቷ መሪር ለቅሶና የታመመው አባቷ ከአልጋ ያልዘለለ መሪር ቁጭት ይታወሳታል፡፡

ልጅነቷ የዕድለኞች ልጅነት አልነበረም፡፡ በህመም፣ ድህነትና ብሶት በተሞላ ቤት ውስጥ አድጋለች፡፡ እናትና አባቷ ለእሷ ፍቅር ለመስጠት የሚያንሱ ሆነው አልነበረም፡፡ ከስንት ሙከራዎች በኋላ ለቅዱስ-ሚካኤል ስለት ተስለው ያገኟት ብቸኛ የስለት ልጃቸውንም ዋጋ ሳያውቁት ቀርተው አይደለም፡፡ ግና ያልታሰበው ሲሆን፣ የሰው ልጅም ለጠፊ ጥቅም ብሎ ከፋትና መጠፋፋትን ሲመርጥ ፍቅር በፍርሃት ይጋረዳል፡፡ ፅዮንም በዚህ ደስታ የራቀው ቤት ውስጥ ብትወለድም እግሯ ከደጃፍ እንደወጣ ግን ጥሎ የማይጥለው ጌታዋ የሚያስቃትን ምርጥ ጓደኛ ግን አልነፈጋትም … ኢትኤል ብቸኛው የፅዮን የልጅነት መልካም ትውስታ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

ቢሆንም አሁን ገና በገባት ምክንያት እነኢትኤል ቤት እንዳትሄድ ከእርሱም ጋር እንዳታሳልፍ በእናትና አባቷ ስትኮነን፣ ስትመከርና ስትገረፍ አድጋለች፡፡ ጓደኝነታቸው በሁለቱም ቤተሰብ ውስጥ የማይወደድ ነበር፡፡ አሁን እሷ ያለችበት ሁኔታ ግን ከጓደኝነት አልፎ የፍቅር ነበልባል በልቧ የሚነድበት ነው፡፡

አንድ ቀን… ከቀናት ሁሉ በተለየች አንድ ቀን ፍቅሯን ነግራው እሱም የቧን ስሜት ተጋርቷት ተጋብተው አብረው እንዲኖሩ ትመኛለች፣ ለማንም ያልነገረችው የህይወት ተልዕኮዋም ይህው ነውና ። ግን በእዚህ ውስብስብ ቅራኔ ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች እንዴት ብለው የሁለቱን አብሮነት እንደሚፈቅዱ ሲታሰብ ተስፋ አስቆራጭ ስሜት ተናንቃት፤ ግና ማድረግ የምትችለውን በሙሉ ታደርጋለች እንጂ ለእሱ ያላትን ፍቅር መፋቅ በፍፁም አትችልም። ከእናቷ ሌላ በህይወቷ ተለይታው ልትኖር የማትችለው አንድ ሰው አለ፣ እርሱም ኢትኤል ነው።

*** ☥ – ☥ ***

# ምዕራፍ ፳ ......... ባህታዊው ከላሲታ

በስጋ ስልል ያሉ አባት ከእንጦጦ ጫካ ረጃጅም ዛፎች ውስጥ አንዱን ዋርካ ደገፍ ብለው ተቀምጠው በገናቸውን ይደረድራሉ፡፡ ከፊት ለፊታቸው እንደነገሩ ያቀጣጠሉት እሳት ነበልባል ገፅታቸው ላይ ያበራል፣ አርያማዊ ቅባታቸው ያንፀባርቃል፡፡ የህፃን ልጅ የዋህነትና የጠቢብ እርጋታ የሚነበብበት ፊታቸውን ረጅሙ ፂማቸው ደግፎታል፡፡ የተገመዱት የባህታዊ ጉንጉኖቻቸው ከቆባቸው ስር ፈልቀው ወርደው አንገታቸው ላይ ግዙፍ መስቀሉን ካሰሩበት ቢጫ የዶቃ መቁጠሪያ ዙሪያ ያበቃሉ፡፡ የነተበ ብርቱካናማ የመነኩሴ ቀሚስ ታጥቀዋል፡፡ አፈናጠው ካጣጠፏቸው እግሮቻቸው መሀል በግራ ታፋቸው ላይ ነበር በገናቸውን አንተርሰው ያቆሙት፡፡

*♫ "እንዴህ አርገን*

*ስራውን ሁሉ አምነን... እናምናለን ዳግም ይመጣል ብለን*
*ነገር ግን ዳግም ይመጣል ስላልን*
*ከፃድቃንም ከመላዕክትም ቢሆን*
*የሚያውቅ የለም የሚመጣበትን ቀኑን*
*ባላወቅነው ባልመረመርነው ሠዓት*
*.... ይመጣል እንጂ ድንገት፡፡"*

12ቱን የበገና ቅኝት እየደረደሩ... በዝግታ... ሊጆሮ እንደሚጣፍጥ የፀበል ውሀ አወራረድ ድምጸት በቅዱስ ዜማ ውስጥ አብረው... ሸውው ብለው ይፈሳሉ፡፡ በዙሪያቸው ያለው ቁጠማ፤ ከበላያቸው ካጠላው ቅርንጫፍ ጋር እኩል ተስተናብረው በዝማሬያቸው የሚያሸበሽቡ ይመስል ወዲያ ወዲህ ይንዠዋዠዋሉ፡፡

… ከጀሮ አልፎ ልብና መንፈስን የሚያድሰውን ዜማ ለረጅም ደቂቃዎች ከተጫወቱ በኋላ በገናቸውን ከጎናቸው አኖሩት:: ቀጥለውም አንገታቸው ዙሪያ የነበረውን መቁጠሪያ አውርደው ያጉተለትሉት ገቡ:: እያንዳንዷ ዶቃ ጣታቸውን ዳብሳ ለቀጣዩ ዶቃ ቦታዋን ስትለቅ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማድረሻ በረከትን አስቆጥራ ታልፋለች:: እያንዳንዷ እስትንፋሳቸው ከዶቃዎች መቀያየር ጋር ተዋህዷል:: ሰላም ያልፋል… ሰላም ይተካል… ምስጋና ይቆጠራል!

ድንገት ከጫካው ውስጥ የእርምጃ ድምፅ የመሰለ ዳና ይሰማ ጀመር:: ባሕታዊው ቀሚሳቸውን ሰብሰብ አድርገው ከተቀመጡበት ብድግ አሉ:: ፀጥ ያለውን ጫካውን እየረበሸ ወደ'ርሳቸው አቅጣጫ የሚገሰግሰው ምን እንደሆነ ለማወቅ ተጠጉ… ልባቸው ግን የጠረጠረውን ጠርጥሯል… ለረጅም ግዜያት ሲጠብቁት ነበርና::

"አሁን ጊዜው ነው!" የሚል ነጎድጓዳዊ ድምፅ ተሰማቸው… ከፊታቸው እያነደዱት የነበረው እሳትም ሰማይ ሊነካ የቋመጠ ይመስል ተንበለበለ:: አካባቢው በሙሉ በታላቅ ብርሃን ተሞላ::

"አምላከ ይህንን ትውልድ አስቧልና" አሉ፤ ባህታዊው ወደ መሬት እየተንበረከኩ፣ "አዎን! መንገዱን የሳተን ትውልድ እሱ ወደመንገዱ ይመልስ ዘንድ ይገለጣል:: ከመሃከላቸውም እውነትን አስታዋሾች ይሾማል:: እነሆ ወደደቡብ ምዕራብም ታመራለህ፤ ህልም እስኪያዩ ድረስም ይታገሱ ዘንድ ለ5 ወጣቶች ታበስራለህ::" የሚል ድምጽ ተሰማቸው::

"እንኪያስ እሱ ይሁን ካለው የሚያፈነግጥስ ማነው?… ካለሱስ ፍቃድ ቅጠልም ከዛፍ አትወድቅምና ሁሉን በፀጋ እቀበላለሁኝ፤ ግና የልጆቹን ማንነት እንዴት ማወቅ ይቻለኛል?" አሉ ባህታዊው እንዳጎነበሱ፤ ረዘም ላለ ጊዜ ቢጠብቁም ምንም መልስ አልነበረም፤ ምንም ድምፅ አይሰማም:: ቀና ቢሉ ብርሃኑም ጠፍቶ ቦታው በጨለማ ተውጦ ነበር:: ተነስተው ልብሳቸውን አረጋገፉና ከቦታቸው ተመለሱ:: አሁን ተልዕኳቸውን አውቀዋል:: ነገ ወደ ጅማ ይጓዛሉ::

*** ☥ – ☥ ***

*>>>>ጥር ወር/ 2010- ኢ.ኢ.አ/*

ከምሽቱ 2:30/ ዶፍ ዝናብ የአዲስ አበባን ጎዳናዎችን እንደቦከሰኛው፣ ጥቁር ዲበ-ሰው መሐመድ አሊ ፈጣን ቡጢኞች ይደበድባል:: በዚህች ዓለም እድሉ የቀናለት ከሞቀ ቤቱ ውስጥ በአንሶላና በለስላሳ የብርድ ልብስ ተከናንቦ፤ እድል ፊቷን ያዞረችበት ደግሞ በጎዳና ጆንያ ለብሶ ዝናብና ብርዱን ያስተናዳል::

ፕ/ር እሴ ከፍሬድሪክ ጋር የቦሌ ዓለም-አቀፍ አየር ማረፊያ ሲደርሱ ዣንጥላ ይዘው የሚቀበሏቸውን ዘምድ አዝማዶች ባይጠብቁም ሽጉጥ የታጠቁ ደህንነቶችን ግን በጭራሽ አልጠበቁም ነበር:: ገና ሻንጣቸውን ከመጎተቻ ጋሪው ላይ ጭነው እየሳቡ ከዋናው በር ከመውጣታቸው ነበር፣ ጨርቁ ቆዳቸው ላይ የተሰፋ የሚመስል፣ ከሰውነታቸው ላይ ልከክ ያለ ጥቋቁር ሙሉ ልብሶችን የለበሱ ሦስት ሰዎች መጥተው የከበቧቸው:: ቁመታቸው ቢለያይም የሁሉም ደረትና ትከሻቸው ድልብ ጡንቻዎች በሱፎቻቸው አልተጋረዱም:: አይኖቻቸው ምን እያዩ እንደሆነ እንዳያስታውቅ ይመስል ሦስቱም ጥቋቁር መነፅሮችን አድርገዋል::

"ፕ/ር እሴ?" አለ ከሦስቱ ሰዎች መካከል አንዱ፣ አጠር ብሎ በአድሜም ታላቅ ይመስላል፤

"አዎ!" አሉ ፕ/ር እሴ በድንጋጤ አንዴ ሰዎቹን አንዴ ፍሬድሪካን እያዩ፤

"ፕ/ር እሴ እኛ ከማዕከላዊ የደህንነት ቢሮ ነው የመጣነው…" አለ፤ ከደረት ኪሱ መታወቂያ አውጥቶ ፊታቸው ላይ ደቅኖ እያሳያቸው "ለአንዳንድ ጥያቄዎች ስለምንፈልግዎ እባክዎን ይከተሉኝ::" አለና ምንም መልስ ሳይጠብቅ ፊቱን አዙሮ መሄድ ጀመረ::… "ይቅርታ አድርግልኝና፣ ለምን አይነት ጥያቄ እንደተፈለግኩኝ ማወቅ እችል ይሆን?" አሉ ፕሮፌሰር ወደፊት ራመድ ብለው እየተከተሉት፤

"ሁሉም ነገር እዚያ ስትደርሱ ይነገራችኋል!" የሚል ቁርጥ ያለ መልስ ተሰጣቸው፤ ምንም አማራጭ እንደሌላቸው የተረዱት ፕ/ር እሴ ከሦስቱ ሰዎች ጋር ተከታትለው ሲወጡ ኃይለኛው ዝናብ ነበር የተቀበላቸው:: ሆኖም ከአየር ማረፊያው መግቢያ በቅርብ ርቀት ላይ ቆሞ ይጠብቃቸው

የነበረው ፓትሮሎ ወደበሩ በደንብ ስለተጠጋላቸው ዝናቡ ብዙም ሳይመታቸው ወደውስጥ ገቡ::

*"Are you okay Fredi? (ፍሬዲ ደህና ነሽ አይደል?)"* አሉ ፐ/ር እሴ ገብተው ቁጭ ከማለታቸው:: ጠቃሚ የሆነ ትልቅ እውቀት ይዘው ከብዙ አመታት በኋላ የእናት ምድራቸውን ሲረግጡ ይህን መሰሉ ዱብዳ ይገጥመኛል ብለው በፍጹም አልጠበቁም ነበር:: ከእርሳቸውም አልፎ ከሌላ ሃገር ያመጧትን እንግዳዋን ፍሬድሪካን ችግር ውስጥ መክተታቸው አስጨንቋቸዋል::

"I am fine, don't worry about me. (እኔ ደህና ነኝ ስለኔ አትጨነቅ::)" አለቻቸው ወደኋላዋ ዘና ብላ ወንበሩን እየተደገፈች:: ድምጿም ላይ ሆነ ገፅታዋ ላይ ምንም አይነት ፍርሃትም ይሁን መጨነቅ አይነበብባትም::

"አይ ፈረንጅ! ፍርሃት ምን እንደሆነ ሳያውቅ፣ ካላንዳች ቁጣና ግርፋት አድጎ የፍርሃት ትርጉሙ የጠፋበት ህዝብ፤" አሉ በሃሳባቸው፤ የተከሰተው ነገር ጭንቀት ውስጥ እንዳይከታቸውም ምናባቸው ውስጥ ይህንን ሃሳብ ያመላልሱበት ገቡ::

"አይ ፈረንጅ! ድፍረቱ ለከት ያለፈ ጉደኛ፤ በአንድ በኩል ፍርሃትን አስወግዶ በድፍረት ብዙ ሙከራዎችን እያደረገ አሁን ያለንበትን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ደረጃ ያስገኘ፤ በሌላ በኩል አምላክን መፍራትም ስህተት መስሎት፣ በስሜት ህዋሳት ካልታየ፣ ካልተሰማ፣ ካልተዳሰሰ ውሸት ነው እያለ፤ ቁሳቁስን በሙሉ ፈጥሮ ያስገኘን ታላቅ ሃይል በላብራቶሪ ቁሳቁስ ተፈትኖ ካልተረጋገጠ ውድቅ ነው እያለ፤ የማይታይን ማመንን ሞኝነት አድርጎት በትዕቢት ህግጋትን የተላለፈ፤... አምላክን ከዶ ‹ከጦጣ ነው የመጣሁት› የሚል አዋቂ ተብዬ ወለፈንዲ ትውልድን የፈጠረ፤ በአጉል ነፃነት ስም ግብረ-ሰዶማዊነትን እንደጥሩ እሴት ከመቀበልም አልፎ ምስራቁን ዓለም ለመበከል በፊልምና ሙዚቃ የሚታክት፣ መሰይጠንን ከመሰልጠን ያልለየ፤ አይ ፈረንጅ!"

መኪናቸው ዋናውን የቦሌ አስፓልት ትታ ወደ ኮሮኮንች መንገድ ታጠፈች:: ፐ/ር እሴ በሃሳብ ማዕበል መዋዠቁን ቀጥለውበታል፤

"አይ ፈረንጅ! የጥቂት መሰሪ ኢሉሚናቲዎች ሴራ ሰለባ ሆኖ ሰርቆም ይሁን ለፍቶ በሰበሰበው ሃብት ምድራዊ ጉልበቱን ያደራጀ ፈላጭ ቆራጭ፤

የዓለምን ሃብት በሞኖፖል ተቆጣጥሮ በቅንጦት የሚኖር፣ የራሱ ያልሆነው ሃብት እየቆረቆረው በምቹ አልጋ ላይ የሰላም መኝታ አጥቶ የእንቅልፍ ኪኒን የሚቅም፣ አንዳችም ምድራዊ ፍላጎቱ ሳይጓደል፣ የረሳት ነፍሱ እየታዘበችው ራሱን የሚያጠፋ፤ አልያም እውነተኛ ደስታን ከሌለችበት ስፍራ እየፈለገ የገንዘብ ሱስ፣ የወሲብ ሱስ፣ የምግብና መጠጥ ሱስ፣ የልብስና ጫማ ሱስ፣ የብልጭልጭ ህይወትና አደንዛዥ እፅ ሱስ የደቆሰው፣

በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከራሱ አልፎ አማራጭ ለሌለው ታዳጊ ልጁ እነዚህን አጥፊ ሱሶችን በገፍ ያወረሰ፣ ሰርክ የሰበከ፣ ህሊናና አዕምሮን አሽቀንጥሮ የጣለ፣ ትርጉም አልባ፣ በስሜት የተሞላ የጭለማ ህይወትን ለብዙሃኑ ያዳረሰ:: ከራሱ አልፎ ፈሪሃ-እግዚአብሔርና ተቅዋ የሞላውን የአፍሪካና አረብ ሙስሊምና ክርስቲያን ህዝብ ወግና ባህል፣ ሞራልና ሰውነት ቁጥር በተለጠፈበት ወረቀት እየተመነ ከብራቸውን ያጣጣለ:: የብዙሃንን ንፁህ ደም አፍስሶ የያዘውን ምድር "ቅኝ ገዛሁኝ" ብሎ ጥቁሩን ህዝብ እንደ እንስሳ የነገደ:: የድፍረቱ ድፍረት ድሮም ፈጣሪ ያስገኛትን ሰፊ አህጉር "አሜሪካን አገኘናት" እያለ እንደ ጀብድ የሚያወራ፤ ‹ሬድ ኢንዲያኖች›ና ቀደምት ጥቁሮች በሰላም የሚኖሩበት ድረስ ሄዶ በጅምላ እየጨፈጨፈ የተቀራመተውን ምድር ካላንዳች ሃፍረት የኔ ብሎ በታሪክ የሚያስተምር የፈረያን ፈጣጣ፤ ... "እስኪ አሁን ሰው ይኖሩበት የነበረን አህጉር ‹ለመጀመሪያ ጊዜ አገኘሁኝ› ብሎ ማወጅ ምን የሚሉት ዘበት ነው?!" አሉና ፐ/ር በራሳቸው ሃሳብ ሳይታወቃቸው ፈገግ አሉ::

"እርግጥ ነው ያስቃል፤ ፈረንጅ እፍረት አልባ ነው!" ብለው ፈገግታቸውን ቋጩና ሃሳባቸውን ቀጠሉ፤ "አሜሪካ የሚባል ሀገርም ወረረ እንጂ ፈፅሞ አላገኘም:: ለዚህም እውነቱን ቢናገር ኖሮ "ድሮ መኖሩን ያላወቅነውን ህዝብና ሀገር በመሳሪያ ጉልበት ወረርንና መሬቱን ዘረፍን" ማለት ነበር የሚገባው፤ እሱ ግን ይህም ሳይበቃው እንደገዛ ንብረቱ እያፈሰ የወሰደውን የአፍሪካ ወርቅና የከበሩ እንቁዎች በራሱ ባንክ ቤት አከማችቶ፣ እንደግል ሃብቱ እያስቆጠረ በዓለም ላይ የሃብት ቁንጮ ሲባል የሚታበይ፣ የወርቁ እውነተኛ ባለቤት ለሆኑት አፍሪካውያን በአራጣ እያበደረ ደግ እንደሰራ ሁሉ የሚመፃደቅ:: ከወርቅና እንቁ እጅግ የሚልቁትን እልፍ አእላፍ ብራናዎች፣ የጥበብ መዛግብት ብሎም ጥንታዊ ቅርሶችን በመርከብ ጭኖ

ወስዶ በራሱ ሙዚየም ካለይሉኝታ ማስጎብኘቱ ሳያንስ አከሱምን የሚያክል ትልቅ ሃውልት ካለርህራሄ ከስሩ ጎምዶ ወስዶ የከተማው ዋና አደባባይ ላይ የሚያቆም፣ እቁሞም መልስ ሲባል መከራከር የሚቃጣ የሌባ አይነ-ደረቅ፡፡

አይ ፈረንጅ! … ነገሩ ሁሉ የሚያስገርም ጉድ፤ የሚመራው መንግስት ድሮ የሰራው ግፍ እንኳን አልበቃ ብሎት ሰበብ እየፈጠረ፣ ራሱ ያስለጠናቸውን አረመኔ ሰዎች የሃገር መሪ አድርጎ እየሾመ፣ ከዚያም ህዝቡ ቢቃኝ ሲልም ህጻን፣ ሴት፣ አዛውንት ሳይል በቦንብ ያለ ልዩነት እየገደለ፤ ኢራቅ፣ አፍጋኒስታን፣ ሊቢያ፣ ሶሪያንና የመንን በዲሞክራሲ ስም የወረረ፣ በጦሩ ከሰማይ የእሳት ዝናብ እያወረደ ንፁሃንን ደም የሚያፈስ፤ እንባ የሚያስነባ አረመኔያዊ ስራ የሚሰራ፣ የሰው ልጅ ለቅሶና ስቃይ ደንታም ሳይሰጠው አሁንም በግልፅ የንዳጅ ስርቆቱን ያጧጧፈ ዘራፊ…"

ፐ/ር እሴ ጭንቀታቸውን ለመርሳት የገቡበት የሃሳብ ውቅያኖስ ይባሱኑ ታላቅ የሆነ ሃዘንና ቁጭት ሲፈጥርባቸው ይታወቃቸዋል፡፡ ዞር ብለው ፍሬድሪካን፣ የሚወዷትን ‹ፈረንጅ› አስተዋሏት፡፡ የመያዛቸው ጉዳይ ምንም ደንታ ሳይሰጣት እንቅልፏን እየለጠጠች ነበር፡፡ ዝም ብለው ሲያስተውሏት ተፈጥሮባቸው የነበረው ንዴት ቀስ በቀስ በርህራሄና ፍቅር ሲሸረሸር ይታወቃቸዋል፡፡ "አይ ፈረንጅ!" አሉ ፐ/ር እሴ፤ በለሆሳስ "በጥቂቶች እርኩስ ሴራ ላይ በተመሰረተ አስተሳሰብ ሰለባ የሆናችሁ ምስኪኖች፤ የምታደርጉትን የማታውቁ ትላልቅ ጨቅላዎች፣ በጥቂት መሰሪ ጓጉንቸሮች ስራ እየተወቀሳችሁ ለውጥ ለማምጣት የከበዳችሁ፣ ጦርነት ስትላኩ ምክንያቱን እንኳን ሳትጠይቁ ‹እሺ› እያላችሁ እየሄዳችሁ ትርጉም ለሌለው ውጊያ ደማችሁን የምታፈሱ፣ ያላችሁበትን የጥፋት መንገድ ሲነገራችሁ የማትሰሙ አስቸጋሪ ልጆች… እውነተኛው እውቀት ገና ከለጋነት የተሰወረባችሁ ዘናጭ፣ ነጭና ቀይ፣ ምስኪን ከርታታዎች…"

መኪናቸው ለ20 ደቂቃዎች ያህል በኮብል ስቶኑ ላይ ከተጓዘ በኋላ ከአንድ ሰዋራ ስፍራ ላይ ከተገነባ ቢጫ ፎቅ ሲደርስ ፍሬን ቆንጥጦ ቆመ፡፡ ፐ/ር እሴ ፍሬድሪካን ቀሰቀሷት፡፡ ሦስቱ ሰዎች ከፓትሮሉ ዱብ ዱብ ብለው ወረዱና ሁለቱ ወደፎቁ መግቢያ ሲያመሩ ሌላኛው ደግሞ ለእነፐ/ር እሴ በሩን ከፈተላቸው፡፡ ተከታትለው ወደፎቁ ዘለቁ፡፡ ፐ/ር እሴ ሊያስከስስና ሊያሳስር የሚችል ምንም አይነት ወንጀል እንዳልሰሩ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ቢሆኑም እየሆነ ባለው ነገር ግን በመጠኑም ቢሆን መፍራታቸው ግን አልቀረም፡፡

*** ፆ – ፆ ***

ፅዮን ከቤቷ በር ደጃፍ በርጩማ ላይ ቁጭ ብላ ከአዋቂው የሰማችውን የድግምት ጉዳይ እያብሰለሰለች ሳለ ከሰውዬው ንግግር ጋር አብሮ የሚሄድ አንድ የልጅነት ክስተት ድንገት ትውስ አላት፡፡

«ያኔ በየዋህነት ዘመኗ ነው፣ የፋሲካ ሰሞን ነበር፡፡ ከእነጩኒ ጋር ቃጤ ቃጤ እየተጫወተች ሳለ የሁሉም ጣት ላይ የተሰካ እርሷ ላይ ግን የሌለ ነገር ትመለከታለች፡፡ በግሏ ለመስራት ሞከራ ሞከራ ባይሳካለት፣ ከጓደኞቿ ማነሷ ቢያስከፋት እየተነጫነጩች ኢትኤል ጋር ሄደች፡፡

በስሜት ተውጦ ብይ ሲጫወት ነበር ያገኘችው፡፡ የያዛትን ብይ ከጉርጓ ለመክተት እያለመ ሳለ ከጎኑ መጥታ ስትቀመጥ ብይ ማንከባለሉን ትቶ ተመለከታት…

"ቃጤ ቃጤ አለቀ እንዴ?"

"አስጠላኝ ባክህ… ደግሞ ይቺ ጩኒ ዝም ብላ ታፋፍራለች!" እንደማለቃቀስ ቃጣት፤

እሷን ሲደብራት እሱም አንዳች መጥፎ ስሜት ይሰማዋል። "ጆላቲ ልግዛልሽ?" አላት፤ ጥዋት ቀይሮት ከሰዓት በአቧራ አፈርድሜ ካበላው ሱሪው ውስጥ ምናልባት ከተበላሁኝ ብሎ ለክፉ ቀን ብይ መግዣ የደበቃትን 10 ሳንቲም ጎልጉሎ እያወጣ። ኢትኤል ለወትሮው በኪሱ ብር ጠፍቶ ባያውቅም ለብይ መጫወቻ ግን ያለውም ስለሚወስድበት ይህቺን 10 ሳንቲም ቀርቅሮ ደብቆ ነበር ያተረፋት፡፡ ትንሽ ብትመስልም ያኔ ሳንቲሟም ሃያል ናት፤ ለእሱ የተበላውን ማስመለሻ ሁለት ብይ፣ ለፅዮን ደግሞ የ‹ጆሊጁስ› በረዶ ገዝታ ታላቅ ደስታን የመፍጠር ብቃት ነበራት።

ፅዮን ግን ትንሽ አሰብ አደረገችና "አልፈልግም!" አለች፤ በጆላቲ አልደለልም በሚመስል ለዛ! ኢትኤልም በጆላቲ መጨከኗን ሲያውቅ የእውነትም እንደከፋት ገባው፤ የሷ መከፋት ደግሞ እሱንም ምቾት ይነሳዋል… መፍትሄ ያስፈልጋል፡፡

"እሺ ነይ ብይ እንጫወት…" ብሎ ብይ አስጨበጣትና "አንቺ በአንድ ጉርጓ ብቻ ተጫወቺ እኔ ግን በሁለት ጉርጓ…" … ከማለቱ፣ እሷ ጉርጓ ቀርቶ ወሬ የማስጨረስ ትዕግስት ስላልነበራት የሰጣትን ብይ ወርወር አድርጋ ጀርባዋን ሰጠችው… ብዩን ተፍ ተፍ ብሎ ከወደቀበት አገኘና ወደእሷ ተመለሰ፡፡

"እሺ ምን ላድርግልሽ?" ጠየቃት… ዝም አለች፤ ዝም ስትል ይባስ ከፋው፤ ምን ሊያደርግላት እንደሚችል ግራ ገብቶታል!

"የጩኒን ጣት አየኸው?"… አለችው ጣቶቿን እያጣጠፈች፤

አይኑን ቃጤ ቃጤ ወደሚጫወቱት ሴቶች ሰደደው፤ የጩኒ ጣት ላይ ‹ሔድና-ሞል›ን የሚያኸል ተደራራቢ አረንጓዴ የዘንባባ ቀለበት ተሰክቷል።

"ቀለበቱን ነው?" አላት፤

"አዎ… አንዴ ብቻ አስደርጊኝ ብያት እምቢ አለችኝ…" ስትል የኩርፊያዋ ምክንያት በደንብ ገባው።

"አይዞሽ" ብሏት ተነሳና ዘንባባ ፍለጋ ከነፈ።

….ከሰዓታት ፍለጋና የእልህ ‹ኮንስትራክሽን› በኋላ ‹ቡርጅ-ዱባይ›ን የሚያስንቅ የዘንባባ ቀለበት ሰርቶላት አሁንም ሲከንፍ ወደ መጫወቻ ሜዳው ሄደ።

የልፋቱን ዋጋ ሰጥቷት ስትስቅ ለማየት ጓግቷል። ከስፍራው እንደደረሰ ግን በድንጋጤ ክው ብሎ ነበር የቀረው… ፅዮን አየችውና እየሳቀች ወደሱ መጣች…

የፊቱ መለዋወጥ ግራ ገባት መሰል፤

"ምነው ኢታ ምን ሆነኻል?" አለችው፡፡

"ቀ…… ቀለበቱን ከየት አገኘሽ?"

"ዋሴ ነው የሰራልኝ… አያምርም?"

"ያ… ያምራል…" አለ ኢትኤል፤ ከአንገት በላይ፡፡

እሷ የዋሴን የዘንባባ ቀለበት አይኑ ላይ ስትደቅንና እሱ ደግሞ የሰራላት የዘንባባ ቀለበት ከእጁ ላይ ሽርተት ብሎ ሲወድቅ አንድ ሆነ፤

ትንሿ ፅዮንም ከመሬት የወደቀውን የኢትኤል ስሪት አየችና ጎንበስ ብላ አነሳችው፡፡

"ምንተ ነው ኢ.ታ?" አንዴ እሱን አንዴ ቀለበቱን እያየች ጠየቀችው፤ እሱም ዝም ብሎ አንዴ እሷን አንዴ ከጣቷ የጠለቀው የዋሴን ቀለበት እያየ ፍዝዝ ብሎ ቀረ። በልጅነት ልቡ ትልቅ ሚስጥር የተጋለጠበት ስለመሰለው ትቷት ወደቤቱ ሮጠ።

ትንሿ ፅዮን ነገሩ ሳይገባት ብዙ ስትጫወት ቆየች። የኋላ ኋላ ግን የዘንባባውን ቀለበት ለእሷ ሰርቶ መምጣቱና ስለተቀደመ መናደዱ ገባት። የዋሴን ቀለበት አውልቃ ጣለችና የኢትኤልን ቀለበት አጠለቀች። ልታሳየው ጓጉታ እየበረረች ወደ ኢትኤል ቤት ሄደች።

ወትሮ እንደደህንነት ቢሮ በር ሁልጊዜ የሚዘጋው የእነኢትኤል ትልቅ ግቢ ካለልማዱ ገርበብ ተደርጎ ተከፍቷል። ፅዮን ለኢትኤል ቀለበቱን እንዳደረገች ከማሳየቱ እኩል በፍፁም አይታው የማታውቀውን የነኢትኤልን ቤት የማየት ሌላ ጉጉት ተፈጠረባት። በቅጡ የቆርቆሮ አጥር የሌለው ቤት ውስጥ ያደገችው ፅዮን የተለያዩ ቀለሞች ባሏቸው ጠርሙሶች ካሸበረቀው የጡብ ግድግዳ አጥር ሰተት ብላ ወደውስጥ ገባች።የግቢው ማራኪ ውበት አፏን አስከፍቷት ለጥቂት ሰከንዶች ቆማ ቀረች። ከሰፊው ግቢ ከወደግራ በኩል ከተደረደሩት ሰርቪሶች መካከል በአንዱ ክፍል ውስጥ የኢትኤልን ድምፅ የሚመስል ድምፅ ስትሰማ ከአድናቆቷ ብንን አለች።

"ኢ… ኢትኤል…" ብላ እየተጣራች ወደ ክፍሉ ተጠጋች። ውስጧ ግን ከአሁን አሁን አቶ ሳዖል ወይም ወ/ሮ እመቤት አዩኝ በሚል ፍርሃት ተወጥሯል። እየቀረበች ስትመጣ በድጋሚ ከክፍሉ አንዳች ድምፅ ተሰማት፤ አሁን ላይ የሰማችው ድምፅ ግን ከኢትኤል ይልቅ የሌላ የባዕድ ድምፅ ነበር የሚመስለው። ማረጋገጥ ግን ነበረባት፤ ወደበሩ ስትጠጋ ወለሉ ላይ ቁጤማ እንደተንዘነዘ አስተዋለች። በሩን ገርበብ አድርጋ ስትገባ አንድ መጥፎ ጠረን አፍንጫዋን ጠረቀሳት። የመስኮቱን መጋረጃ አልፎ በሚገባው ጭላንጭል ብርሃን ኢትኤልን በክፍሉ ውስጥ ፈለገችው፤ አላገኘችውም። ግን በትልቅ ቁም-ሳጥን ከተከለለው መደብ ላይ አንድ የሚንቀሳቀስ አካል አስተዋለች። ተጠምልሎ የተኛ ሰውም መሰላት። ከመደቡ ስርም ትልቅ የብረት መዘፍዘፊያ፤ ከጎኑም ግዙፍ ጀበናና እጅግ ትላልቅ ሲኒዎች ተደርድረዋል።

"ኢትኤል?" እያለች ወደ መደቡ ስትጠጋ፤ አንድ ረጅም፣ ጥምልል ነገር ሽረር ብሎ ከመደቡ ላይ ተሰየመ። ፅዮን በድንጋጤ ጮኸች፤ ወደ ኋላዋ ፈንጠር ብላም ምንነቱን ለማየት ሞከረች፤ አዎ አንድ ጥቁር ዘንዶ ከመደቡ ላይ ሆኖ እያፈጠጠባት ነበር። በልጅ ጭንቅላቷ ሮጦ ማምለጥ እንዳለባት ብታስብም በጣም ስለደነገጠች ሙሉ ሰውነቷ ተሳሰረ፤ አንድ እርምጃ

እንኳን አቅቷት ቆማ ቀረች:: ዘንዶው ከመደቡ በዝግታ ወረደ:: ከፉኛ የፈራችው ፅዮን አይኖቿን ጨፍና ድጋሚ ልትጮኽ ስትል አንድ ነገር ማጅራቷን ይዞ ወደኋላዋ ጉተታት፤ "ቢቃ ተበላው!" አለች በልቧ::

ቀጥሎ ግን "ተው ኮብራ ተመለስ!" የሚል ትዕዛዝ ሰማች:: ይህንን ድምፅ በእርግጥ በድንጋጤና ፍርሃት ውስጥ ሆናም ቢሆን ትለየዋለች::

"ምን እየሰራሽ ነው እዚህ?" አላት ኢትኤል እንደ መቆጣት እያለ::

"እ… አንተን ፈልጌ መጥቼ ነዋ::" መለሰችለት፤ በፍርሃት እንደተዋጠች፤

በልጅ ለዛ… "እና በር ላይ ሆነሽ ብትጠሪኝ ኮ እመጣ ነበር:: ዛሬ ‹ኮብራ› በጣም ብዙ ምግብ በልቶ ስለጠገበ ነው እንጂ አልቆልሽ ነበር!" አላት፤ ይዟት ወጥቶ የኮብራን ከፍል በር እየዘጋ::

"አላወቅሁም… እኔ እኮ ቀለበቱን አድርጌ ላሳይ…" ብላ ፅዮን አረፍተ-ነገሯን ሳትጨርስ የወ/ሮ እመቤት ጩኸት ተተካ "እናንተ ልጆች እሱ በር ጋር ምንድነው የምትሰሩት?" ብለው ከዋናው ቤት ደረጃ እየወረዱ ሲጠጉ ፅዮን መሆኗን አወቁ:: "እንዴ! እንዴ እኔ ጠፋሁኝ! አትሂድ እያልኩህ መሄድህ ሳያንስ ጭራሽ ቤቴ ድረስ ይዘሃት መጣህልኝ የኔ ጀግና!" እያሉ ወደእነርሱ ሲንደረደሩ ኢትኤል ወደ ፅዮን ዞረና፤ "አሁን ቶሎ ብለሽ አምልጪ… ያየሽውን ነገር ደግሞ ለማንም እንዳትናገሪ… ከተናገርሽ ግን እኔ ነኝ የምገረፈው" አላት፤ ፅዮን በመስማማት ራሷን ነቀነቀችለትና ፈር.. ብላ ከግቢው ወጣች:: ያን ቀን ያየችውንም የእነኢትኤል ቤት ሚስጥር እሱ እንዳይገረፍ ብላ እስካሁን ለማንም ተንፍሳው አታውቅም:: እሱ ከሚገረፍባት የሆዷን በሆዷ ይዛ ለእናቷ እንኳን አልነገረቻትም ነበር::››

ፅዮን ከልጅነት ትውስታዋ ስትመለስ ኢትኤል ይናፍቃት ጀመር:: እርግጥም በስልክ እንኳን ካወሩ መቆየታቸው እውን ነው:: ስልኳን አውጥታ ወደ ስልኩ ደወለች:: ደጋግማ ብትደውልም በቅጡ እንኳን ሳይጠራ ዘጋባት:: ለማመን ቢከብዳትም ውስጧ የፈራውን ለራሷ አንሾካሾከች "ብሎክ አደረገኝ እንዴ?"… ሃይለኛ ራስ ምታት ውጥር አድርጎ ሲይዛት ደቂቃ አልፈጀበትም ነበር::

*** ቶ – ቶ ***

ኢትኤልና ቢታንያ ከተዋወቁ ከሁለት ቀናት በኋላ በጅማ ከተማ አለ ከሚባል ሆቴል ውስጥ ለእራት ታድመዋል:: ኢትኤልን ብቻ ሳይሆን በሆቴሉ ውስጥ ከሌላ ሴት ጋር ያሉ ወንዶችን ጭምር ያስደመመና በተደጋጋሚ አይኖቻቸውን ወደሷ እንዲልኩ ያስገደደ ገላጣ የእራት ቀሚስ ለብሳ የመጣችው ቢታንያ የቦታው ንግስት ሆናለች:: ጥቁሩ ገላጣ ቀሚስ ከዳሌዋ አልፎ ያልወረደ ሲሆን ቀይ ጥርት ያሉ እግሮቿን ከላይ እስከታች ያስጎበኛል:: ከበስተጀርባዋ በሰውነቷ ልክ ይወጣና ወገቧ ጋር ሲደርስ ጨርቁ ገላዋን ወደሚያጋልጥ ወንፊትነት ይቀየራል:: በፊትለፊት በኩልም ቢሆን የቀሚሱ ወንፊትነት ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚያስችል ሁኔታ የውስጥ ገላዋን ያሳያል:: በአጠቃላይ ከውድ መስታወቷ ፊት ቆማ የፈጀችው ሰዓት በተግባርም የኢትኤልን ብቻ ሳይሆን የብዙ ወንዶችን ልብም የሚያነሆልል ሆኖላታል::

"ቆይ ያቺ ፅዮን ያልካት ልጅ የምን ዲፓርትመንት ተማሪ ነች?" አለች ምግብ አዘው እየጠበቁ፤

"የሜድስን ናት::"

"የኛ ዶርሟ ፅዮን እንዳትሆን ብቻ?!" አለች ቢታንያ በአግራሞት፣

"እንዴ ታውቂያታለሽ እንዴ?"

"አዎ በደንብ ነዋ... ግን ገርሞኛል!"

"ምኑ?"

"አይ ማለቴ አንተ በጣም ‹ኩል› ልጅ ነህ! እንዴት ከእሷ አይነት ስገጤ ፋራ ጋር ጓደኛ እንደሆንክ ገርሞኝ ነው::" አለችው፤

"ለምን ፋራ አልሻት?" ኢትኤል የእድሜ ልክ ጓደኛው ‹ፋራ› መባሏ ቢያስከፋውም ስሜቱን ለራሱ ለማስቀረት እየታገለ ነበር::

"የሷን ፋራነት ካልተረዳህማ አንተም ስገጤ ፋራ ነህ ማለት ነው::" አለች ቢታንያ እየሳቀች::

ኢትኤል ከዚህ በኋላ መልስ ቢመልስላት እንዳትጣለው ስለሰጋ ዝምታን መረጠ:: ለራሱ ግን ቃልም ሳይተነፍስ ስለ ፅዮን ማብሰልሰል ያዘ:: ያዘዙት የሸከላ ጥብስ ቀርቦ የፈላው ዘይትና ቅባት ቸፍ..ቸፍ..ቸፍ.. እያለ ፍንጥርጣሪው እጆቹን ቢያቃጥለውም ስለፅዮን ማሰቡን ግን አላቆመም:: እርግጥ ፅዮን ተሸቀርቅራ የምትወጣ ዘናጭ ላትሆን ትችላለች፤ ተኳኩላ ወጥታም አይን ውስጥ የምትገባ ሴት ላትሆን ትችላለች፤ ንግግርም የማታበዛ ዝምተኛ ልትሆን ትችላለች ግን ፋራ አይደለችም:: ትህትናዋና አስተዋይነቷ በእሱ ብቻ ሳይሆን በብዙዎች ዘንድ የሚደነቅላት፤ በዚያ ላይ አንድም ቀን ስትዋሽ ታይታ የማታውቅ፤ ያላትን በሙሉ ከመስጠት ወደኋላ የማትል ደግ

ሴት ናት:: ‹ይህ ባህሪዋ ፋራ የሚያስብላት ከሆነ አራድነት ምን ዋጋ አለው?› አለና ኢትኤል በዚሁ ጥያቄ እንደተዋጠ ቢታንያን አስተዋላት:: ከነመፈጠሩም ረስታው ገል ጥብሷን በልዩ ደስታ እየተመገበች ነበር:: ትንሽ ታዘባት:: እሷ ጋር ያለ ፅዮን ጋር የሌለ ምን ነገር ኖሮ ይሆን ፅዮንን ፋራ ያለቻት ብሎ በቅጡ አስተዋላት:: ቆንጆነቷን ባይከድም ፊቷ ላይ የደፋችው ሜካፕ በትክክል መልኳን እንዲያይ አልፈቀደለትም:: የአይኖቿ ኩዳንና ሽፋሽፍቶች ላይ የነሰነሰችው ግራጫ ቀለምና ብልጭልጭ ነጠብጣብ አይኖቿን እንዳትከፍት ሸክም እየሆነባት ውብ ብሌኖቿ እንደልብ እንዳይታዩ አግዶባታል፤ እዋባለሁኝ ብላ ተፈጥሯዊ ውበቷን የደበቀች ሴት መሰለችው::

"ብላ እንጂ ምን ታፈጣለህ?" አለችው ድንገት፤

"እየበላሁኝ ነው::" አለና አንድ ጉርሻ ጠቅልሎ ወዳ'ፉ ሰደደ፤

"ቢታን?" አላት፤ አላምጦ እንደዋጠ፤

"ወዬ.. ማሬ!"

"እስኪ ስላንቺ በደንብ ንገሪኝ?"

"ቂቂቂ... እኮ ምን ልንገርህ?"ሳቋ ከጠረጴዛዋ አልፎ ስለተሰማ ብዙዎች ዞሩ፤

"ቢታንያን ግለጪያት እስኪ....?"

"እ... ቢታንያ ማለት ነፃ፣ መጨናነቅ የማትወድ፣ ሳቅና ጨዋታ ብቻ የምትፈልግ፤ እና በተረፈ እስካለሁኝ ድረስ ዘና ብዬ ወጣትነቴን ማሳለፍ እንዳለብኝ የማምን ሴት ነኝ:: እ... አይበቃም?" አለች ፈገግ እያለች::

"አይ አሪፍ ነው!" አላት በቀዘቀዘ ስሜት፤

ቀጥላም... "ብታይ ዛሬ የ‹ሳምሰንግ ኤድጅ› አዲስ ሞዴል ስልክ አይቼ እንዴት እንደሚያምር ‹አህ ማይ ጋድ›!" አለች በግነት፣

"እውነት ያምራል?" አለና ወደ ምግቡ ተመለሰ፤

"ያምራል ብቻ!.. ያ ስልክ ቢኖረኝ ሌላ ምንም አልፈልግም::"

"ያን ያህል የሚጋነን ነው?"

"እንዴ ምን ማለትህ ነው? ያን የመሰለ ስልክ ከመያዝ በላይ ሌላ ምን ትፈልጋለህ?"

"ካልሽስ ይሁንልሽ እኔ ምን እላለሁኝ" አላት በቸልተኝነት፤

"ያንተን ባላውቅም እኔ አዲስ ሰው ስተዋወቅ በመጀመሪያ የምታዘበው ልብሱንና ጫማውን ሲሆን ቀጥሎ የማየው የስልኩን ‹ሞዴል› ነው!" አለች ረገጥ አድርጋ፤ ኢትኤል ወድያው የለበሰችው ልብስ ላይ አይኑን ተከለ:: በስሱ ቀሚስ ከተሸፈነው ይልቅ ያልተሸፈነው የሰውነት ክፍሏ ያመዝናል:: ከስር እንደዶሮ ማንቁርት የረዘመ ‹ቋ› ‹ቋ› ጫማ አጥልቃለች:: ያያት ብቻ

ሳይሆን ስትራመድ የሰማት እንኳን እሷኑ እንዲመኝ ያለመች ይመስላል:: በአጠቃላይ ‹ብራሷ ውበትና ቁሳቁስ ለየት ብላ ለመታየት የምትለፋ አይነት ሴት› መሆኗን በቀላሉ ታዝቧል::

"ግጥም ማንበብስ ትወጂያለሽ... ያዝናናሻል?" አላት፤

"ኧረ ምን ነካህ ኢትኤልዬ? በዚህ ዘመን ቁጭ ብዬ የማንም ፈላስፋ ያሰካካውን ግጥም ቤት መታ አልመታ እያልኩኝ ላንብብ እንዴ?... ይልቅ ንገረኝ እስኪ አንተን ምን ያዝናናሃል?"

"አይ ሌላ ጊዜ እነግርሻለሁኝ::"

እራት በልተው ጨርሰው ትልቁን ወይን እየተጎነጩ ለግማሽ ሰዓት ያህል እንደቆዩ ሁለቱም ሞቅ አላቸው:: ቢታንያም ከስር እግሮቿን እየሰደደች ወንድነቱን ትፈታተነው ጀመር:: ኢትኤል በደቂቃዎች በፊት ስለሷ ያሰበው አሉታዊ ነገር በስሜት ወላፈን ሲተንን ታወቀው:: ተያይዘው ከሆቴሉ ፊትለፊት ከሚገኝ ጭፈራ ቤት እስኪገቡ ድረስ በአንድ እጇ ሲጃራዋን እያቦነነች በአንድ እጇ ደግሞ እሱን ማሻሸቷን ያላቆመችው ቢታንያ ገብተው መጨፈር እንደጀመሩ ላዩ ላይ ተለጥፋ መውረግረግ ጀመረች:: በየመሃሉም የሲጃራ ጭስ በአፉ ሙሉ ትነፋበታለች:: ኢትኤል በበኩሉ ቤት ሲቀይሩ ንፋስ ስለመታው ስካሩ በርዶ የቅድሙን ሃሳብ ማብሰልሰል ይዟል:: የሲጃራዋን ጭስ እያራገበ ከጎኗ ቢቆምም በሃሳብ ግን ልክ እንደጭሱ በንፋሱ እየተገፋ ከእሷ ብዙ ርቆ ሄዶ ነበር::

ካለአንዳች መልዕክትና ጥልቀት ቂጥ ለማወዛወዝ ብቻ የሚገፋፉ የአፍሪካ፣ ላቲንና አሜሪካ ዘፈኖችን ሲከፍት የነበረው ዲጄ፤ ቢታንያን እንደእብድ ያስፈነጫትን የሪሃና ዘፈን ከከፈተ በኋላ ብዙዎችን ለጎጃም እንቅጥቅጥ ከወንበራቸው ያስነሳ፣ ‹ማር እስከጧፍ› የሚለውን የቴዲ አፍሮ ሙዚቃ ከፈተ፤ ቢታንያ ስትቀመጥ ኢትኤልና ብዙሃን ተነስተው መጨፈር ጀመሩ::

"♫ *ብራናዬ አንቺ የልጅነቴ ጓዴ... ተረሳሽ ወይ የእሳት ዙሪያው ተረት ባንዴ፤*

*ብራናዬ አንቺ የልጅነቴ ቀለም እኔ እንዳንቺ ያጠናሁት ፊደል የለም::"*

ሲል ኢትኤል ካለምንም ቅድመ ሁኔታ የፅዮንን ስልክ ቁጥር አወጣና እየደወለ ከ‹ክለቡ› ወጣ:: ቢታንያ ልትይዘው ብትሞክርም አልተሳካላትም::

*** ዖ – ዖ ***

***"የወርቅ ቀለበት በእርያ አፍንጫ እንደሆን ፥ ከጥበብ የተለየች ቆንጆ ሴትም እንዲሁ ናት::" (ምሳ፤ 11:22)***

*** ቶ - ቶ ***

ፅዮን የስልኳ ጥሪ ከእንቅልፏ ቀሰቀሳት:: ጥዋት ስትደውል ብሎክ ያደረጋት ሰው አሁን ሲደውል ስልኩን ማንሳት አልፈለገችም:: አንደኛው ጥሪ ዘግቶ ሁለተኛው ጥሪ ሲጀምር ‹ብሎክ ሳያደርገኝ ኔትወርኩ ስላልሰራ ቢሆንስ?› ብላ ራሷን መጠየቅ ጀመረች:: ሁለቴ ጠርቶ ዘግቶ ለሦስተኛ ጊዜ መጥራት ሲጀምር ግን በጭካኔ መቀጠሉ አላስቻላትም፤ ስልኩን አነሳችው::

"ሄሎ! ሄሎ!"... "ፂያ ደህና ነሽ?" አለ ኢትኤል ሃፍረት በተሞላበት ድምፅ፤

"ደህና ነኝ... ምንድነው ከኋላህ የምሰማው ድምፅ፤ እየጠጣህ ነው እንዴ?"

"ኧረ አይደለም! ዶርም ልጆች ዘፈን ከፍተው ነው::" ብሎ ዋሻት፤ እሷን መዋሸት ባይፈልግም መጠጥ ሲጠጣ ምን ያህል እንደሚከፋት በሚገባ ያውቃል:: "የት ጠፍተሽ ነው ግን?... ግቢም አላይሽም?"

"አይ ትንሽ ችግር አጋጥሞኝ ነው!"

"ምን?!... የምን ችግር ፂያ?... ለምን አልነገርሽኝም?"

"ልነግርህማ ብዙ ሞክሬ ነበር፤ የሆነ ቀን በሌሊት ደውዬልህ ያላነሳህ ቀን ትዝ ካለህ?" አለችው ደከም ባለ ድምጽ፤

"አዎ ያን ቀን ተኝቼ ነበር::" ብሎ አሁንም ለ2ኛ ጊዜ ዋሻት ኢትኤል፤ ከቢታንያ ጋር እየተሳሳምኩኝ ነበር ብሎ መመለስ ከባድ ቢሆንበት፤

"ያን ቀን እንኳን እሺ ይሁን... ቢያንስ ግን መልሰህ ትደውላለህ ብዬ ጠብቄ ነበር፤" አለች ፅዮን፤ ትዝብቷ ከቃልም በላይ በልቧ ቀርቷል::

"ይቅርታ ፂያ..." አለ በሀፍረት ለዛ፤ መልስ ትሰጠኛለች ብሎ ቢጠብቅም ዝም አለች:: "እሺ አሁንም አትነግሪኝም ያጋጠመሽ ችግር ምን እንደሆነ?"

"እነግርሃለሁኝ ኢታ..... አባቴ እኮ ሞተ..." ብላ ማልቀስ ጀመረች፤

"ምን?..." አለ ኢትኤል በድንጋጤ፤ "እ... እንዴት?... መቼ?"

"አምስት ቀን ሆኖታል አሁን?" አለችው በኃይል እየተነፈሰች::

"አሁን የት ነሽ አንቺ?"

"ቤት ነኝ::"...አለች:: "የት አዲስ አበባ?" መልሶ ጠየቃት፤

"አዎ"...ኢትኤል ምን ብሎ ሊያናግራት እንደሚችል ግራ ተጋባ::

"ቆይ ግን በጣም አሟቸው ነበር እንዴ?"

"አዎ" አሁንም ዝምታ ተተካ፤ "ግን ኢትኤል..." አለች ፅዮን፤ እንዳዲስ እያለቀሰች፤ "ለምን ደበቅከኝ?"......... "ምኑን ነው የደበቅኩሽ ፂያ?"

"እናትና አባትህ የኔ አባት ላይ ድግምት አሰርተው እንደነበር?"

"ምን?" አለ ኢትኤል፤ ከስካሩ ጋር ተደምሮ የምታወራው ነገር በፍጹም ትርጉም አልሰጥህ እያለው፤

"እምን ለምን አልነገርከኝም?… ቢገባህስ አባትና እናቴ ደጋግመው ሲነግሩኝ የማልቀበለው፤ ያኔ በልጅነቴ ዘንዶውን ከቤታችሁ አይቼ እንኳን እንዳችም ጥርጣሬ አድሮብኝ የማያውቀው አንተን ስለማምንህ ነበር እኮ ኢታ፡፡"

"ምን እያወራሽ ነው ፂያ?" አለ ኢትኤል፤ በእውኑ ይሁን በቅዠት ያልገባውን የሰልከ ንግግር ለማመሳከር ስልኩን እየተመለከተ፤

"እያልኩህ ያለሁትማ…" አለች ፅዮን በረጅም አየር እየማገች፤ "እያልኩህ ያለሁትማ ኢትኤል… እኔ አፈቅርሃለሁኝ፤ ከልጅነት እስከ እውቀት እንዳንተ የወደድኩት ሰው በምድር ላይ አይገኝም፡፡ የማከብረውን ጓደኝነታችንን ላለማጣት ብዬ የሆዴን በሆዴ ይዤ ፍቅርህን ለአመታት ታቅፌያለሁኝ፡፡ አንተ ግን የአባቴን ህመም መንስኤና መፍትሔ እንኳን ሳትነግረኝ ከኔ መደበቅን መርጠሃል፤" አለች ድጋሚ ሳግ እየተናነቃት፤

"ትሰሚኛለሽ ፅዮን!?" አለ ኢትኤል፤ ፅዮን እየነገረችው ያለው የአዳዲስ እውነታዎች ጋጋታ ናላውን እየፈታው "የእውነት ስለምን እያወራሽ እንደሆነ ምንም አልገባኝም?!" ብሎ ጮኸ፤

"እያልኩህ ያለሁትማ አባትህና እናትህ በእኔ አባት ጋሽ ጀንበሬ ላይ ጠንቋይ ቤት ሄደው ድግምት አሰርተዋል፡፡ እንዲታመም አድርገውም ገድለውታል፡፡ አንተም ደግሞ ይህንን እውነታ ልብህ እያወቀው ደብቀኸኛል ነው፡፡" አለችው፤ … ኢትኤል ተበሳጨ፤ "እኮ የእኔ እናትና አባት ናቸው ጠንቋይ ቤት ሄደው ድግምት ያሰሩት?" አለ ኢትኤል ስካሩን የሚያንር ቁጣን እየተቆጣ፡፡ መልሷን ለመስማት እንኳን የሚያስችል እርጋታ ስላልነበረው ጆሮዋ ላይ ጠረቀመባት፡፡… ፅዮን በበኩሏ ራሷን መቆጣጠር አቅቷት ስልኳን አሽቀንጥራ ወርውራ ከግድግዳው ጋር አጋጨችው… ስክሪኑም ተሰባበረ፡፡ በእዚሁ እልህ ውስጥ ሆና ስቅስቅ ብላ እያለቀሰች የሌሊቱ ሁለት ሦስተኛ ተጋምሶ ሊነጋጋ አካባቢ ነበር እንቅልፍ የጣላት፡፡ ዳሩ ምን ዋጋ አለው "ወይ ጉዴ … ወይ ጉዴ… አውይ ጉዴ!" የሚል የእናቷ ቀውጢ ድምፅ በጊዜ ነበር የቀሰቀሳት፡፡ … እናቷ ከበራፍ ላይ ቆመው… "ውይ … ውይ … ውይ መጥኔ!… እነዚህ ሟርተኛ ጎረቤቶች እኔን ከነሙሉ ቤተሰቤ ማጥፋት ነው እንዴ እቅዳቸው?" እያሉ ሲጮኹ ፅዮን ወደ ውጭ ወጣች፤ "ምነው እናቴ… ምነው ምን ተፈጠረ?''… "ምኑን ልንገርሽ ልጄ፤ ኢታዬም እንዴ ምን የሚያህል የተገነዘ አይጥ ደጃፌ ላይ ጥለው መተታቸውን ሲያስቀጥሉ፡… ኢታዬም ወይ?…"

*** ቶ - ቶ ***

ኢትኤል ስልክ ሊደውል በወጣበት ወደ ሃያ ደቂቃ ገደማ ቆይቷል፡፡ ቢታንያ ብቻዋን ቆማ እየጨፈረች ስለነበር ብዙ ጠጪዎች አይኖቻቸውን ጥለውባት ነበር፡፡ ከእነርሱም አንዱ የውስኪ ብርጭቆውን እንደያዘ ወደእሷ ተጠጋ፡፡

"መደነስ እንችላለን ቢታ?" አላት፤ ወደ ጆሮዋ ተጠግቶ፣ በጣም እየጮኸ፤

"እ… እሺ ግን አንድ ሙዚቃ ብቻ ነው፡፡" አለችው እሷም ዞራ፤ እጁን ያዛትና ወደዳንስ ወለሉ ሳብ አድርጎ አስገባት፡፡ በሰዉ ፍላጎት ተደግሞ የተከፈተው የቴዲ አፍሮ ዘፈን ወደ ማብቂያው ነበርና እንደነገሩ እስከስታ ቢጤ መቱ፡፡ የሱ ሙዚቃ ሲያልቅ ለመቀመጫና ዳሌ ውዝዋዜ የሚመች የላቲን ዘፈን ተከፈተ፡፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ተራርቀው ደነሱና ቀስ በቀስ እላዩ ላይ ተለጥፋ መተሻሸት ጀመሩ፡፡ ከውጭ በስልኩ ተናዶ የተመለሰው ኢትኤል የቀድሞው ቦታ ላይ ቆሞ እያያት ነበር፡፡ ንዴቱ ላይ ንዴት እየታከለበት፤ ተኪላ መለኪያዎችንም አከታትሎ እየጋተ ስለነበር በሞቅታ እየተንደረደረ ሄዶ ቢታንያን ከሚያስጨፍራት ሰው ላይ ምንጭቅ አድርጎ ለያት፡፡ እጇን ይዞ እየጎተተም ወደ ጓሮ ወሰዳት፡፡ ካለምንም ትንፋሽም ከንፈሯን ይስማት ጀመር፡፡ ቢታንያም የአፀፋውን እጅና እግሮቿን መላ አከላቱ ላይ ጠምጥማ ከንፈሩን ምጥጥ አደረገችው፡፡ የሁለቱም ሰውነት እንደ ፍም እሳት ጋለ፤ በዚሁ የስሜት እሳተ ጎሞራ እየተተኮሱ በሞገደኛ ደመ-ነፍስ እየተመሩ ቤርግ ያዙ፤ ምን እንደሆኑ በውል ሳያውቁት ሌሊቱ ነጋ፡፡ ኢትኤል ጥዋት ከእንቅልፉ የቀሰቀሰው የዮሴፍ የስልክ ጥሪ ነበር፡፡ ባላለቀ እንቅልፍ ውስጥ እየተጨናበሰ ስልኩን አነሳው፤ "ሄሎ ኢታ?" አለ ዮሴፍ የተሸበረ በሚመስል ድምፅ፤

"አቤት… አቤት…" አለ ኢትኤል ራሱን እያነቃቃ፤

"ስማ የት ነው ያለከው?!… ሁሉም ተማሪ መጥቷል አንተ ብቻ ነው የሌለኸው!" ኢትኤል ስልክ ማናገሩን አቁሞ ሰዓቱን ተመለከተ፤ ለሁለት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ይላል፡፡

"ምንድነው የምታወራው ገና አንድ ሰዓት ከአርባ አምስት እኮ ነው፡፡"

"ወይኔ አንተ ጭራሽ አልሰማኸም እንዴ?" አለ ዮሴፍ፤

"ምንን?"

"ዶ/ር እሳቱ ሁለት ሰዓት ላይ ኑ… ማለቱን ነዋ!"

ኢትኤል ከአልጋው ላይ እንደ ካራቴ ፊልም ‹አክተር› ፍንጥር ቀጥ ብሎ ተነሳ፡፡ ሱሪና ሸሚዙን በፍጥነት ለብሶ ዚፑን ሳይዘጋ፣ ቁልፉን ሳይቆልፍ የመኝታ ቤቱን በር ብርግድ አድርጎ ወጣ፡፡ ከሆቴሉ በችኮላ ወጥቶ ወደሆስፒታል የሚወስደውን ባጃጅ ተሳፈረ፡፡ ሙሉ ሃሳቡ ያለው ዶርሙ በምን ፍጥነት ደርሶ ነጭ ካባውን ለብሶ ‹ዋርድ› መድረሱ ላይ ነበር፡፡ ሆስፒታሉ በር ጋር ደርሶ ከባጃጁ ወርዶ ሊሄድ ሲል "ብራዘር ሂሳብ አልሰጠሽኝም፡፡" አለው የባጃጁ ሹፌር በእርጋታ፤

"ወይኔ በጣም ሶሪ!" ብሎ ኢትኤል ኪሶቹ ውስጥ ገባ፡፡ ከሞባይሉ በቀር አንዳችም ሳንቲምም ሆነ የብር ኖታ ግን አላገኘም፡፡ በድንጋጤ ከው እንዳለ አንዴ መሬቱን አንዴ የባጃጁን ሹፌር እያየ የሌለውን ብር ፍለጋ ኪሶቹን እስኪቀደዱ ድረስ በረበራቸው፤ ማታ ተራግፎ ያደረ ባዶ ሱሪ ብር አይወልድ ነገር ጨነቀው፡፡

የባጃጁ ሾፌርም መጨነቁን አይቶ፤ "አብሽር በቃ አትጨናነቂ፣ ሌላ ቀን ሲኖርሽ ትከፍያለሽ፡፡" ብሎት ባጃጁን አዙሮ ሄደ፡፡ ኢትኤል ግን ኪሶቹን መፈተሹን ወድያውኑ አላቆመም ነበር፡፡

እየከነፈ ዶርሙ ደርሶ፣ ነጭ ጋውኑን ለብሶ ላቡ እስኪንቸረፈፍ እየሮጠ ዋርድ ሲደርስ 2 ሰዓት ከሃያ ደቂቃ ሆኖ ነበር፡፡ ግን ይሄ ሁሉ ልፋቱ ጥቅም አልባ ነበር፡፡ ዶ/ር እሳቱ ለጥቂት ቀድሞት ደርሶ ተማሪዎች ጋር ‹ራውንድ› ጀምሮ ነበር የጠበቀው፡፡ በተቻለው መጠን እንዳያየውና አሁን መምጣቱን እንዳያውቅበት ተደብቆ ተማሪዎቹን ተቀላቀለና ከዮሴፍ ጀርባ ቆመ፡፡ ዶ/ር እሳቱ ፊርዶበት የመጀመሪያው አልጋ ባለቤት የሆነውን አብርሃም እየነተረከው ነበር፡፡

"እኮ ለምንድነው ፀሐይ ላይ እንዲያወጡ ያልነገርካቸው? ለስሙ አሁን የአስራ ሦስት ወር የፀሐይ ፀጋ ምናምን አላት የምትባል ሃገር ውስጥ ቁጭ ብለን፤ የፀሐይ ብርሃን የቤታችን በራፍ ድረስ እየመጣ እኛ ግን ህፃናትን ከቤት አውጥቶ ፀሐይ ማሞቅ እንዳለብን ባለማወቃችን የልጆች አጥንት መጣመም የለበትም፡፡ አሁን ያንተ ልጅ ብራኬት ሆኖ ቢወለድ ምን ይመስልሃል?" አለው አብርሃም ላይ አፍጥጦ፡፡

"አይ ዶ/ር ለእናትየው እኮ ‹አድቫይስ› አድርጊያታለሁኝ አከስቱ ነች ዛሬ ያላወጣችው…" ብሎ አብርሃም ሊያስረዳ ሲሞክር፤ ዶ/ር አበራ በጣም በቁጣ መነፅሩን መንጭቆ አወለቀና በከፉ አይን እየገረመመው፤

"አትመልስልኝ!" ብሎ አንባረቀበት፤ አብርሃም ሽምቅቅ ብሎ ወደመሬት አጎነበሰ፡፡ "መሳሳቱ ሳያንስ ስህተቱን ከዶ የሚከራከር ተማሪ በጣም ነው የሚያናድደኝ!" አለና ተማሪዎቹን በሙሉ እየገላመጣቸው... "ኢትኤል?" አለ አይኑን እሱ ላይ ተከሎ፤ "አቤት" አለ ኢትኤል ከበስተጀርባ፤ ልቡ ደረቱን ለንጥቃ ልትወጣ እስኪመስለው ድረስ ፍርሃት እየወረረው፡፡ "ና ወደፊት!... ምን ስትሰራ ነው አርፍደህ የመጣኸው?" አለው በለበጣ፤ ቀጥሎም ኢትኤል ከጎን ኪሱ ላይ ያንጠለጠለውን የስም መለያ ባጅ ነቀለበት፡፡

በእሱ ቤት ተደብቆ እንደገባ ሲያስብ የነበረው ኢትኤል እንደተነቃበት ሲያውቅ ከመደንገጥ በቀር መልስ አልነበረውም፡፡

"ምነው ዝምተኛ መሰልክ እሳ?... ማታ ማታ በየጭፈራ ቤቱ ስትጮኸ ምነው ዝምተኝነትህ ወዴት ጥለኸው ነበር፡፡ አሁን ከዚህ <ራውንድ› ለቀህ ሂድልኝ፤ እኔ እዚህ የምመጣው የማንንም ውርጋጥ ለማስተማር አይደለም!" አለና የኢትኤልን የስም መለያ ባጅ መሬት ላይ ጥሎ ረገጠው፡፡ ኢትኤል እንባና እልህ እየተናነቀው እዚያው ቆሞ ቀረ፡፡

"ውጣ እኮ ነው ያልኩህ ምን ቆመህ ታየኛለህ?" ብሎ ድጋሚ አንባረቀበት፤ ኢትኤል ግን ንቅንቅ አላለም፡፡ አብርሃም ወደ ኢትኤል ዞሮ ተመለከተው፡፡ እጁን ለቡጢ ጨብጦ በእልህ ሲቃ ውስጥ እንዳለ በቀላሉ ተረዳ፡፡ ቀስ ብሎ አቀፈውና እየገፋ ይዞት ወደውጭ ወጣ፡፡

"እዎ እንደዚህ ከቢጤህ ጋር ተያይዘህ ውጣ፤ አንተኛውንም ቢሆን ቀድሜ ማባረር ነበረብኝ... ደደቦች!" አለና መነፅሩን መልሶ አደረገ፡፡

ኢትኤል በአብርሃም ክንድ ተደግፎ ወደ ዶርም ሲሄድ የትናንት ማታ አንድ ክስተት በጭላንጭል እየታወሰው ነበር፡፡

"እዎ ቢታንያን ሲያስጨፍር የነበረው ሰው፤ እርግጥም መነፅር አድርጎ ነበር፤ ነጥቄ ስወስድበት..." ... አለ እያጉተመተመ፡፡

"ምንድነው የምትለው ኢታ?" አለ አብርሃም ግራ እየተጋባ፤

"እዎ ራሱ ነበር አብርሽ!... ትዝ አለኝ!"

"ማነው?"

"እሳቱ ነበር ቢታንያን ሲያስጨፍራት የነበረው... ከእሱ ላይ ነው ነጥቄ የወሰድኳት... አዎ ራሱ እሳቱ ነው!" አለ እየተርበተበተ፤ አብርሃም ምንም መልስ ስለሌለው በዝምታ ኢትኤልን ጥብቅ አድርጎ ያዘው፡፡ በብዙ ስሜት የተዋጡት ሁለቱ ጓደኛሞች ወደ ዶርማቸው አቅጣጫ የሚወስደውን መንገድ እንደያዙ በዝግታ ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡

*** ፬ – ፬ ***

ቶላ በጓደኞቹ መባረር በጣም አዝኗል፡፡ የዶ/ር አበራን ቂም ያዥነት ስለሚያውቅ በተለይ ኢትኤልን ፈተና ላይ አግኝቶት እንዳይጥለውም ሰግቷል፡፡ በሌላ በኩል ዶ/ር አበራ እነኢትኤልን ካባረረ በኋላ የተቀሩትን ተማሪዎች እየሰደባቸው ያለው ስድብ «ወይኔ በተባረርኩኝ ኖሮ!» የሚያስብል ሆኖበታል፡፡ «በልቡ የእኔ አልጋ ላይ ባልደረሰ» እያለ መመኘቱንም አልተወም፡፡ ፈጣሪም የልቡን ጭንቀት ሰምቶ ይመስል ልክ የእሱ አልጋ ጋር ሲደርሱ የዶ/ር አበራ ስልክ ጠራ፡፡

“ሄሎ!” አለ ዶ/ር አበራ የስልኩን መስታወት ዳበስ አድርጎ እያነሳ፡፡ "እዎ አስታውሼሻለሁኝ… እምም መቼ አሁን? … እሺ በቃ ከ10 ደቂቃ በኋላ እደርሳለሁኝ፤”… ስልኩ ተዘጋ፤

“ለነገሩ እንደእናንተ አይነት ተማሪዎችን ከማስተማር ትቶ መሄድ ይሻላል!” አለና ወደ በሩ ዞሮ፤ ለመውጣት ራመድ ሲል ሁሉም ጥግ ጥጉን ያዘና ሰፊ መንገድ ከፈተለት፡፡ የእሱን እግር ተከትለውም ሁሉም ተራ በተራ ከዋርዱ ወጡ፡፡

ቶላ እንደወጣ ቀጥታ ወደ ካፌ አመራና ምሳውን በላ ወይም እንደ ተማሪዎች አባባል ካፌ ሰቀለ፡፡ ከዚያ መልስ ወደ ዶርም ለመመለስ አቅዶ የነበረ ቢሆንም የተጫጫነው ድካም ዶርም ከሄደ ወደ እንቅልፍ እንደሚቀየር መገመት አላዳገተውም፡፡ ከግቢው ፊትለፊት አንድ የጀበና ቡና ጠጥቶ እግረ መንገዱንም ያለቀበትን ስክሪፕቶ ተክቶ፣ ትንሽ ነቃ ብሎ ቢመለስ የተሻለ እንደሚሆን አሰበና ወደ ውጭ አመራ፡፡

ሆስፒታሉ ውስጥ የተኙ ታካሚዎችን ለመጠየቅ በመጡ ሰዎች የተጨናነቀውን የሆስፒታል በር ተጋፍቶ ካለፈ በኋላ ከአስፓልቱ ግራና ቀኝ ከተደረደሩት የ‹ኮንቴይነር› አርከበ ሱቆች መካከል ወደ አንዱ አመራ፡፡ ወጣት ቀጫጫ ባለሱቅ፤ ታክሲ የሚያስቆም ተርዚና በጉንጩ እንደወጠረ ከመደርደሪያው ጀርባ ብቅ አለ፡፡

“አካም አልቴ?” አለ ቶላ፤

"አልሃምዱሊላህ!" አለ ባለሱቁ፤

"ስኪሪፕቶ ጂራ?"

"ጂራ… ብሪ ሸን" አለና ባለሱቁ አንድ የኬንያ ቢክ ሲሰጠው ቶላም የ5ብር ኖታ በምትኩ ከፈለ:: ወደ ቡና መጠጫው ሊያመራ እንደዞረ አንድ ሽማግሌ ከፊት ለፊቱ ድቅን ብለው መንገዱን ዘጉበት፤

"ቶላ… ቶላ… ቶላ…" አሉት ማራኪ ፈገግታ ፊታቸው ላይ እየተነበበ፤

"እ.. አቤት፤" አለ ቶላ፤ ህይወቱን በሙሉ አይቷቸው በማያውቅ አንድ ሰው ስሙ ሦስቴ መጠራቱ እንቆቅልሽ እየሆነበት፤

"ምነው ልጄ ፈራኸኝ እንዴ?" አሉ ይበልጡኑ ፈገግ እያሉ፤ ቶላ መልስ ሳይሰጣቸው በዝምታ ተመለከታቸው:: ምናልባትም በፊት የሚያውቃቸውና አሁን የረሳቸው አባት ከሆኑ ብሎ በደንብ አስተዋላቸው::

የእርግብ ላባ የመሰለ ሽበታቸው ከደመና የተሰራ አክሊል ይመስል ልዩ ግርማ ሞገስን ችሯቸዋል:: ግንባራቸው ላይ ያሰሩት፣ ትንሽዬ የአክሱም ሃውልትን መስሎ የቆመው የኦሮሞ አባ-ገዳዎች መለያ ቅርፅ፣ የያዙት ጫፉ ቢረሌ የሚመስል፣ ዙሪያውን ቀለበት የታሰረበት ከታችም 2 እግሮች ያሉት ዘንግና በጥቁር፣ ነጭና ቀይ ዘርፍ ያጌጠ ጋቢያቸው የአባ-ገዳ አባትነታቸውን በደንብ ይመሰክራሉ:: የቀይ-ዳማ ፊታቸው ልዩ የሆነ አባታዊ ብርሃን ይተፋል:: አይኖቻቸውም የሰከነ የጥበብ ማንነታቸውን ያንፀባርቃሉ::

ቶላ እኚህን ባለ ግርማ ሞገስ አባ-ገዳ ከዚህ በፊት እንደማያውቃቸው አረጋግጧል::… "ይቅርታ አላወቅኩትም አባቴ…" አለ ቶላ በሃፍረት አንገቱን እየደፋ፤

"ምንም ችግር የለውም አሁን ታውቀኛለሃ ልጄ፣ ታውቀኛለህ ማለት ደግሞ ስሜን፣ ስራዬን፣ መኖሪያዬን ማወቅ እንዳልሆነ ግን እወቅ:: የኔ ልጅ፣ ሁሉን ቻይ በሆነው ፈጣሪ ፍቃድ በስምም ከመፈቀድ በላይ እኛ ብዙ ነን:: እኔ የገዳ አባት ነኝ:: አንተን ዛሬ የማበስርህ ደስታ እና የምነግርህ ማስጠንቀቂያ ስላለኝም መጥቻለሁኝ:: እናማ… " አሉት::

ቶላም "አባቴ የሚነግሩኝ ነገር ምንም እየገባኝ አይደለም" አላቸው ጣልቃ ገባና፤

"እየህ ልጄ ሁሉም ሰው የሚኖረው በገባው ልክ ነው:: የሁሉም ሰው ጭንቀት ይለያያልና፤ ሁሉም ሰው የሚረዳህም በሚያውቀው ልክ ነው:: አዎ! ሁሉም ሰው በገባው ልክ ይኖራል::

በደንብ የገባው ህይወትን ምታምር ትርጉም በተሞላች ቅጂዋ ይረዳታል:: በተቃራኒው ግን ቋንጣ ዘርተው ፍየል የሚያጭዱ የሚመስላቸው ግብዞች አሉ:: ዛፍ በጊዜ ብዛት ወንበር እንደማይሆን ሁሉ ካለትክክለኛው መንገድም ስኬት አይገኝም:: አስታውስ ከኖርካቸው ቀናትና ሰዓቶች ሁሉ በእድሜም በእውቀትም ትልቅ ሆነህ የምትገኝበት የአሁኑ ሰዓት ነው:: ትናንትን አታገኛትም፣ በትዝታህ ማህደር ብትኖር እንጂ… ነገም ያንተ አይደለችም፣ በተስፋህ መስፋት ብታቅዳት እንጂ… ዛሬ ግን ያንተ ናት!!" … ቶላ ከአፋቸው የሚወጣውን የህይወት ትምህርት አፉን ከፍቶ እያዳመጠ ነበር::

"ቶላ…" ብለው ጠሩት በአባታዊ ለዛ፤

"አቤት፤" አላቸው::

"ለመሆኑ የስምህን ትክክለኛ ትርጉም ታውቃለህ? ይህቺ ያሰርካት የአዳችን፣ የአድባር ዛፍስ ትርጉሟን ታውቀው ይሆን?… አይመስለኝም!… ስለዚህም ጉዞህን እወቅ! እጣ ፈንታህን አንተ ቅርፅ ታስይዛታለህና::" አሉት፤

ቶላ ከኪሱ ውስጥ ስልኩ ሲጠራ ታወቀው:: ነገር ግን የአባ-ገዳውን ንግግር ላለማቋረጥ ሲል ስልኩን ሳያነሳው ዘገየ፤ ስልኩ በድጋሚ ሲጥራ አውጥቶ ሲመለከት ‹ቢሊሱማ› ይላል:: "ይቅርታ አባት አንዴ ስልኩን ላንሳው?" ብሎ ዞር አለና ስልኩን አነሳ::

"ስልኩን አታነሳም እንዴ?" አለ ቢሊሱማ ከሌላኛው የስልክ ጫፍ፤

"እና በምንድነው አሁን ምታዋራኝ?" ሁለቱም ሳቁ፤

"የት ነህ?"

"ግቢ በር ጋር ነኝ፤ ቡና ልጠጣ ነው::"

"መጣሁኝ ጠብቀኝ" … አለ ቢሊሱማ፤

"እሺ፤" ብሎ ስልኩን ዘግቶ ሲመለስ አባገዳው ከቦታቸው አልነበሩም:: አስፓልቱም ላይ ወጥቶ ላይና ታች ቢያማትርም በቅርብ ርቀት ላይ ቆመው ከሚሰብኩ አንድ ባህታዊ በስተቀር አባ-ገዳውን አባት ሊያገኝ አልቻለም:: "በዚህች ቅፅበት ወዴት ተሰወሩ?" ብሎ ጥያቄ እንደሆነበት ስልኩን ወደ ኪሱ መለሰ::

ቢሊሱማ ቶላ ጋር ለመድረስ ጊዜ አልፈጀበትም:: ወትሮም ብዙዎች የመስከሩለት ቀልጣፋ ወጣት ሐኪም ነው:: ሲራመድ ፈጣን፣ ሲያወራ ፈጣን፣ ሲበላ ፈጣን... ባጠቃላይ የሚያደርገውን ነገር በቶሎ መጨረስ የሚወድ ሰው ነው:: ይህ ባህሪው በእርግጥም ፍጥነትን በሚሻው የህክምና የመጨረሻ ዓመት «ኢንተርን-ሺፕ» ስራው ላይ እጅጉኑ ረድቶታል::

"ቡና ልጠጣ ነው አላልከም እንዴ ምንድነው እዚህ ፈዘህ የቆምከው?"
"አይ አንድ የሚገርሙ አባ ገዳ አሁን ከመምጣትህ በፊት እያነጋገሩኝ... ብቻ ከመቅፅበት የት እንደገቡ አጣኋቸው..."
"ምነው ቶላ ይሄ የእሳቱ ራውንድ ‹ሃይፖግላይሲምያ›* ውስጥ አስገብቶህ መቀባዠር ጀመርክ መሰለኝ?" አለ ቢሊሱማ እየሳቀ፤ (*የስኳር መጠን በደም ውስጥ ማነስ)
"በእናቴ እምልልሃለሁኝ እውነቴን ነው፤ ‹ሃይፖ› ውስጥ ገብቼም እየቃዠብኩኝ አይደለም በቅርቡ ነው ካፌ ምሳ የበላሁት::" ቶላ ኮስተር ብሎ መለሰለት፤
"ለማንኛውም እቱ ጋር ቡናዋ አሪፍ ነው፣ እዚያ አብረን እንጠጣለን::" አለና ይዞት በልዩ የጀበና ቡና ማዕዛ ወደተሞላች ዳስ ወሰደው::

"ለምንድነው የባለፈው ስብሰባ ላይ ያልተገኘሽው?" አለው ገና እንደተቀመጡ፤

"አዎ ምን ላድርግ ብለህ ነው ፈተና ስለደረሰ በጣም ብዙ ‹ከቨር› ማድረግ ያለብኝ ፖርሽኖች ስለነበሩ ነው... በዚያ ላይ አዲስ የሚወሰን ነገር ካለ ካንተ እሰማለሁኝ ብዬ ነው::"

"ራስህ ብትገኝ ግን ጥሩ ነበር፤ ለማንኛውም ዛሬ ዋርድ እንዴት ነበር?"
"ባከህ አዛ ነበር፤ ብዙ ልጆች ተባረዋል::"
"አንተስ... ለነገሩ እንደዚያ እያነበብክ ብትባረር ነዋ የሚገርመኝ!" አለ ቢሊሱማ ፈገግ እያለ፤
"ባከህ ለዚያ አይደለም... የኔ አልጋ ላይ ስላልተደረሰ ነው የተረፍኩት፤"

"ዋናው መትረፍህ ነው:: ሰውዬው ካጠመደ የሚለቅ አይደለም:: የኛ ጊዜ ራሱ የፈተናቸውን ብዙ ተማሪዎችን ጥሏል::"

"አዎ እኔም ሰምቼያለሁኝ በናትህ አብርሃምና ኢትኤል ጉዳቸው ነው፤ በዚያ ላይ እኮ የቃል ፈተናችን አንድ ሳምንት ነው የቀረው::" አለ፤

"የእውነትህን ነው?... ከዚያ እረፍት ትወጣላችሁ ማለት ነው?"

"አዎ እንወጣለን፤ ማዘርን እስከማያት ጓጉቻለሁኝ፤" አለ ቶላ፤ ቢሊሱማ በቀላሉ ነበር መናፈቁን ቶላ ፊት ላይ ያስተዋለው::

"አትጨነቅ፤ ብቻ ጤና ትሁንልህ እንጂ መገናኘታችሁማ መቼ ይቀራል፤" አለ ቢሊሱማ አይኖቹን ቡዝዝ አድርጎ፤

"አዎ ልክ ነህ::" ብሎ ቶላ ለእራፊ ያህል ዝም ካለ በኋላ አከሎም "የእውነት ግን ኢትኤልና አብርሃምን ዶ/ር እሳቱ ከጣላቸውና አንድ አመት ሙሉ ካስደገማቸው በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው::" አለ::

"ባከህ ለራስህ እዘን" ተቆጣ ቢሊሱማ፤ የያዘውን ቡና በቅጡ ፉት ሳይል እያስቀመጠ... "እነርሱ፣ በተለይ ኢትኤል የሃብታም ልጅ እንደሆነ ቦንቱ ነግራኛለች:: ቢወድቅ ቀርቶ ቢባረር እንኳን ብዙ ሺህ ብር ከፍሎ በግል የሚያስተምረው ቤተሰብ አለው:: አንተ ግን ቢያንስ ለድሃዋ እናትህ ተምረህ ድረስላት::" አለ ቢሊሱማ በስሜታዊነት፤

ቶላ መልስ ሳይሰጠው ቡናውን ማጣጣሙን ቀጠለ:: ሃሳቡ ደግሞ በከፊል ቅድም አናግረውት የሄዱት አባ-ገዳ ጋር ነበር:: ያወሩለት ቃላቶች እንደገደል ማሚቱ አሁንም በውስጡ ያስተጋባሉ:: የጠየቁት ጥያቄዎችም እንደቃጭል ጆሮው ላይ ያቃጭላሉ::

*"ለመሆኑ የስምህን ትክክለኛ ትርጉም ታውቃለህ? ይህቺ ያሰርካት የአዳችን፣ የአድባር ዛፍስ ትርጉሟን ታውቀው ይሆን? ጉዞህን እወቅ! እጣ ፈንታህን አንተ ቅርፅ ታስይዛታለህና::"*

"ሄይ! ለመሆኑ የምነግርኸን እያዳመጥከኝ ነው?" አለ ቢሊሱማ በንዴት፤
"ኧረ አዎ!" አለ ቶላ ከሃሳቡ ድንገት እየባነነ፤
"ለማንኛውም ከፈተናህ መልስ ሐሙስ ማታ ታላቅ ተቃውሞ ስላለ ተዘጋጅ!" አለውና 5 ብር አስቀምጦ ተነስቶ ወጣ፤ ቶላ ከኋላ ቢጠራውም እንዳልሰማ ሆኖ ሄደ:: ቶላም ተናዶበት እንደሄደ ስላወቀ ቅያሜ አልያዘበትም::

*** የ – የ ***

ቶላ አባ-ገዳውን ፍሊጋ ሲወጣ ያያቸው ባህታዊ ከሰሞኑ የብዙ የጅማ ኗሪዎችን ቀልብ የሳቡ አባት ናቸው:: ከየት እንደመጡና ማን እንደሆኑ የሚያውቅ አንድም ሰው ግን አልተገኘም:: በአቧራ ምክንያት ከቢጫነት ወደ ቡኒነት የተቀየረ የመነኩሴ ቀሚስ ለብሰዋል፣ ካደረጉት ቢጫ ቆብ ስር የተገመዱት የጸጉራቸው ጉንጉኖቻቸው እየፈለቁ ወርደው አንገታቸው ላይ ግዙፍ መስቀሉን ካሰሩበት ቢጫ የዶቃ መቁጠሪያ ዙሪያ ያበቃሉ፡ ከጅማ ሆስፒታል በር ትይዩ ቆመው መስበክ ከጀመሩ ቀናቶች ተቆጥረዋል::....

*"የዘንድሮ ሰው እህሉን ለድሃ ከሚያካፍል ነቀዝ አስቢበላበት ድረስ ደብቆ ማስቀመጥን ይመርጣል::" አሉ፣ በከፍተኛ ድምፅ፣ መሬት መሬቱን እያዩ ቀጠሉ፣*

*"አብዛኛዎቻችሁ አሁን እዚህ የተደረደራችሁ ሰዎች ቤታችሁ ባለው ሶፋ ላይ ድሃ ሰው አስቀምጣችሁ የማታውቁ ናችሁ:: አዎ! አንተ በገዛኸው ሶፋ ላይ ድሃ ተቀምጦበት አያውቅም:: «ሶፋዬ ይቆሸሽብኛል» ብለህ ከበረንዳ ትሸኛለህ:: አሁንስ ቢሆን በልብሴ መቆሸሽ ለምን ትገረማላችሁ? ይህ ጨርት በሁለት ብር ሳሙና መፅዳት ይችላል:: ልብ ግን ያለንሰሃ መፅዳት አይችልም!!!" አሉ፣ ሁሉን ሰውም በአርምሞ እየተመለከቱ፣*

*"ሁልህም ትንሳኤ... ትንሳኤ... ትላለህ ጎረቤትህን ጠርተህ ታበላለህ፣ በምላሹ ደግሞ ጎረቤትህ አንተን ጠርቶ ያበላህል ለድሀ የምትሰጠውም ትርፍራፊህን ነው:: ስህተታችን አይን አውጥቶ ደሃ ሲሞት ማዘጋጃ-ቤት፣ ሀብታም ሲሞት ደብረ-ሊባኖስ እንቀብራለን፣ የሃብታም ብር የአንዳንዶቻችንን የሃይማኖት አባቶች ልብ እየገዛው ለሃብታም እናጎበድዳለን:: እኔ አንተ ፊት የቆምኩት ግን ድሪቶ እንድትገዛልኝ፣ ለአንገቴ ወርቅ፣ ለእግሬ ጫማ ወይም ቀሚሴን እንድትቀይርልኝ አይደለም::*

*የለም...የለም... በእግዚአብሔር ስም መነገድ ታላቅ ኃጢያት ነው:: ወዳጆቼ! ሰማያት እንደ ወረቀት ይጠቀለሉ፣ መሬትም በፍርሃት ትንቀጥቀጥ:: በዘመናት የእግዚአብሔር ቁጣ በካዱት ላይ ታላቅ ነበር::" አሉ ወደ መሬት ባንድ እግራቸው እየተንበረከኩ፣ ቀኝ እጃቸውንም ሽቅብ እየሰበቁ፣.... "ዛሬም ግን ስራችን ያው ነው፣ ለታይታና ለወሬ እንጂ ትክክለኛ ሃይማኖታችንን ረስተናታል:: በዚህ ዘመን አንተ ገንዘብ ሰላለህ ሚስትህ እያለቀሰች 80ሺህ ብር ከፍለህ እየሩሳሌም ትሄዳለህ:: አንተ ገንዘብ ሰላለህ የቀጠርካት ሰራተኛ «ተቸገርኩኝ» ብላ እያለቀሰች 3000 ብር ከፍለህ አክሱም ፅዮን ትሄዳለህ::*

አሁን ግን እውነቱን እነግርኃለሁ፣ ቅዱስ ስፍራዎች ቢኖሩም እግዚአብሔር ግን የእየሩሳሌም ብቻ አምላክ አይደለም፣ ወይም የአክሱም ፅዮን ብቻ አምላክ አይደለም፡፡…እ/ር የዓለም ሁሉ አምላክ ነው፤ እ/ር የልብህ አምላክ ነው፤ እ/ር በቤትህ ውስጥ አለ፤ እ/ር በዚህ አለ፣ ባለኸበትም አለ፤ እ/ር በምትራመድበትና በምትተነፍስበት እስትንፋስ ሁሉ አለ፤ የቅድስቲቱን ቤተ ክርስቲያን ገዳማት በስጋዊ ሽታ ለማወድ ከመትመመህ በፊት ቅዱስ ቃሉን አክብርና በልብህ ውስጥ ቤተ-ክርስቲያኒቱን አንፅ፡፡ እ/ርን ማወቅ ማለት ላገባሃት ሚስት ጥሩ መሆን ነው፡፡ እ/ርን ማወቅ ማለት ‹ያለኝ ይበቃኛል› ማለት ነው፡፡ እ/ርን ማወቅ ማለት በማንም ላይ ኃጥያት አለመስራት ነው፡፡ እ/ርን ማወቅ ማለት የራስን ስሜት መወሰን ነው!" ብለው ከእንብርክካቸው ተነሱ፤

"አዎ እውነቱን ልንገራችሁ ህዝቤ እውቀትን በማጣቱ ጠፍቷል፡ እምነትን መቀለጃ አድርጎታል፡፡ ፈረንጅ ባንተ ሃገር ፀበል እየተጠመቀ ከኤች አይ ቪ እየዳነ ነው፡፡ እመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይሻል እንዲል ቅዱስ ቃሉ አንተም የምትጠመቅ በጥርጣሬ ውስጥ ሆነህ ነው፡፡… እውነቱን ልንገርህ! በግፍ በሰበሰብከው ብር 3 ወርና 3 ዓመት በየደብሩ ከምትዞር ለ3 ደቂቃ እ/ርን በንጹህ ልብ ማሰብ የበለጠ ዋጋ ይኖረዋል፡፡ ከቤትህ ሆነህ ጸበሉን በእምነት ብትጠጣውም ያድንህማል፡፡ …ድስ ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ከ40 ዓመት በላይ ሆኖታል፤ የታለ አንተ የዳንከው? እምነት የለማ!…ፀበል ስትሄድ "ልሞክር" ብለህ ነው፤ ገዳምም ስትሄድ "ልሞክር" ብለህ ነው፤

…አዎ አሁንም ተመለስ፤ ከዘላለማዊው መንግስት ይልቅ አንተን የምታሳስብህ ይህቺ ከንቱ ጠፊ ዓለም ናት፡፡ ስላለህ አትኖርም፣ ስለሌለህ አትሞትም… ከእነዚህ ድንጋዮች ስር በህይወት እንዲኖሩ የፈቀደላቸው ጉንዳኖች አሉ፡፡" ድጋሚ በርከክ ብለው ከመሬት ድንጋይ እየፈነቀሉ… "እነዚህን ጉንዳኖች እንዲኖሩ የፈቀደ አምላክ እኔና አንተን አባትና እናት እንደሌለው ህጻን አልተወንም፡፡ ይልቅስ የመጨረሻው ቀን ደርሷልና በንስሃ ነፍስህን አጠባት፡፡ "ተመልሼ እመጣለሁኝ" እንዳለን እርሱን ለመቀበል እንዘጋጅ፡፡ ሳይነግረን ሳያሳውቀን ድንገት ከእኛ ጋር ይቆማልና፡፡ ከሰው ልጆች፣ በፃድቃንም ዘንድ ቢሆን የሚመጣበት ትክክለኛ ሰዓትና ቀን አይታወቅም፡፡ ግና መምጫው ቀን ሲደርስ የሚከሰቱትን የምፅዓት ቀን ምልክቶች ቀድሞ በቃሉ ትንቢትን ነግሮናልና እንዘጋጃለን፡፡ አነሆ የሰው ልጅ ሆይ ስማ፤ ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ላይ የእሱን መምጣትና የዓለምን መጨረሻ ምልክት እንደ ነገረን፤ ማንም እንዳያስተን መጠንቀቅ አለብን፡፡ እንዳትረሱ ጌታ እንዲህ

*ይላልና፤… "ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ:: ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፤ አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው:: ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግስትም በመንግስት ላይ ይነሣልና፥ ርሃብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል፤ እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው:: በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጧችኋል ይገድሉአችሁማል፤ ስለስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ:: በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ፤ እርስ በእርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ፤ እርስ በእርሳቸውም ይጣላሉ፤ ብዙ ሐሰተኞች ነብያትም ይነሳሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ ከዓመፃም የተነሳ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች:: እስከ መጨረሻው የሚፀና ግን እርሱ ይድናል::"*

*እናም አስተውሉ የጦር ሃይሎች ከመቼውም ጊዜ በላይ የተደራጁበት ዘመን ላይ ደርሰናል:: የምድርና የአየር መዋጊያ መሳሪያዎችን ሃገራት በገፍ የታጠቁበት ዘመን ላይ ነው ያለነው:: የ1ኛውና የ2ኛው እያሉ በመቁጠር ሊያሳምሩት ቢሞክሩም የዓለም ጦርነቶችም ሚሊዮኖችን ደመከልብ አድርገው አልፈዋል:: በምድር ላይ ታላላቅ ድርቅና ርሃቦች ተከስተዋል:: አሁን እንኳን የሰው ልጅ በእውቀት ጫፍ ደርሻለሁኝ እያለ ዘልዓለማዊውን አምላክ ለመገዳደር በሚቃጣበት ወቅት ከአምስት ሰው አንዱ እየተራበ ነው:: «የብዙ ሰዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል» እንዳለውም የፍቅር ዋጋዋም በብር ተተክቷል:: ቸነፈር ንፋስና ማዕበሉ፣ ሰደድ እሳቱ፣ አየር መዛባቱ፣ መሬት መንቀጥቀጡ ህዝብን እያስጨነቀ ነው:: ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 12 ላይ በዚያ ዘመን ዕውቀት ይበዛል እንዳለው፤ የሰው ልጅ በዓለማዊ ትምህርት በየቀኑ ቢኮፈስም የእግዚአብሔርን ቅጣት ማንም አያቆመውም:: በቴክኖሎጂው ለጊዜው ተደሳስተ እንጂ ጥፋቱን ግን ማቆም አልተቻለውም:: የሚያሳዝነው ትንቢቱ ይፈፀም ዘንድም ወሲባዊ ቀውስ ነግሶ ወንዶቹ "ሴት ነኝ" እያሉ፤ 200.000.000 ግብረ-ሰዶማውያን ምድራችን ላይ በነፃነት ሲቦርቁ የምናይበት ዘመን ላይ መድረሳችን ነው:: ስለዚህ ጆሮ ያለህ በሙሉ ስማኝ፤ የጭንቅ ጅማሬ አሁን ነውና፣ ወንድም ቀበቶህን ሴቱም መቀነትህን አጥብቅ፤ በንስሐ ነፍስህን አድስ፤ ትዕዛዛቱንም አክብር!!…"*

ብዙ የአካባቢው መንገደኛ፤ ቆሻሻ ልብስ ከለበሰው ከዚህ ሰው የሚወጡ እንቁ እንቁ ቃላቶች ሰበውት ለማዳመጥ ከቦ ቆሟል:: ግና ከቆሙት ውስጥ ጥቂቱ ነበር የት/ቱን አስኳል እየተረዳ የነበረው:: ከዚያ ጥቂት መካከልም ከፊሉ "እኚህ ሰው እውን ባህታዊ ከሆኑ ስለዓለማዊ ኑሮ እንዴት ይህን ሁሉ ሊያውቁ ቻሉ?" ብሎ የሰማውን እውቀት ከእምነቱ መርህ ለማካተት አልተቻለውም ነበር::የሚሰማ ካለ ግን እውነት ተናጋሪ ሁሌም አይጠፋም::

*** ፶ - ፶ ***

ፕ/ር እሴና ፍሬድሪካ ከሦስቱ የደህንነት ሰዎች ጋር ተከታትለው ወደ ውስጥ ሲዘልቁ በበርካታ ኮምፒዩተሮችና የሳተላይት መቀበያ መሳሪያዎች የተሞላ አልፍኝ ነበር የተቀበላቸው:: ሰዓቱ መሸትሸት ቢልም በየጠረጴዛው ላይ የተቀመጡትና ኮምፒዩተር ላይ በትላልቅ የጆሮ ማዳመጫዎች መልዕክት የሚልኩና የሚቀበሉ ኦፕሬተሮች፣ የተጠረጠሩ ግለሰቦችን ንግግር የሚቀዱ ጠላፊዎች፣ ፀሐፊዎችና መርማሪዎች ጨምሮ ፎቁ ውስጥ የሚሯሯጡት ሰዎች ብዛት እነፕ/ር እሴን አስገርሟቸዋል:: ሰዎቹ ፍሬድሪካን በሩ ላይ ከተቀመጠው ሶፋ ላይ እንድትቀመጥ አዘዟትና ፕ/ር እሴን አንድ ነጠል ብሎ እንደ ትልቅ ሳጥን ከቆመ፣ በአራቱም አቅጣጫ ምንም አይነት ከፍተት ከሌለው አሸግ ክፍል አስገቧቸው::

ፕ/ር እሴ ከክፍሉ መሃል ላይ የተቀመጠው ከብ ጠረጴዛ ፊት ወንበር ስበው ተቀመጡ:: ከእርሳቸው ትይዩም አንድ ወንበር ተቀምጧል:: በተረፈ ሌላ ምንም እቃ የሌለበት ኦና ክፍል ነው:: በግራ በኩል ግድግዳው ላይ ተሰንጎ የሚገኘው ሰፊ መስታወት የእርሳቸውን ምስል አንፀባርቆ ቢያሳያቸውም ከውጭ ያለውን ሰውም ወደ ውስጥ የሚያሳይ መሆኑን በቀላሉ መገመት ችለዋል::

ለደቂቃዎች ብቻቸውን ክፍሉ ውስጥ ቁጭ ካሉ በኋላ ከሦስቱ ሰዎች በእድሜ ታላቅ የሚመስለው፣ በቁመትም አጠር ብሎ ተከለ-ሰውነቱ ግን ፈርጠምጠም ያለው ግለሰብ የክፍሉን በር ከፍቶ ገባና ከፊታቸው ያለውን ወንበር ስቦ ተቀመጠ:: አይን አይናቸውን እያየም ከኪሱ መቅረፀ-ድምፁን አውጥቶ ጠረጴዛ ላይ አኖረው::

"ቡና ወይ ሻይ ይፈልጋሉ?" አላቸው፤

"አይ አያስፈልገኝም፣ አመሰግናለሁኝ::"

"እሺ እንደዚያ ከሆነ መጀመር እንችላለን፣" አለና መቅረፀ-ድምፁን ጠቅ አድርጎ አበራው:: "እሺ ፕ/ር እሴ እኔ መርማሪ አክሎግ እባላለሁኝ፤ በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሽብር ክትትል ደህንነት ቢሮ መርማሪ ነኝ:: ፍቃደኛ ከሆኑ አንዳንድ ጥያቄዎችን ልጠይቆት ፈልጌ ነበር?"

"እዚህ ድረስ ካመጣችሁኝ በኋላ ፍቃደኝነቴን ብትጠይቁኝ ምን ዋጋ አለው? ይልቅ የምትጠይቁኝን ነገር ቶሎ ቶሎ ጠይቁኝና በጊዜ ልቀቁኝ፤ በጣም ለአስፈላጊ ጉዳይ ነበር አመጣጤ፤" አሉት::

"ብዙም ጊዜ አንፈጅብትም ፕ/ር፤ ለመጨረሻ ጊዜ ከኢትዮጵያ የወጡት መቼ እንደሆነ ሊነግሩኝ ይችላሉ?" አለ መርማሪ አከሎግ፤

"‹አልምስት›... ከሁለት ዓመታት በፊት ነበር::"

"በእነዚህ ሁለት አመታት ውስጥ የት የት ሃገራት ሄደዋል?"

"እምም... መጀመሪያ የሄድኩት ያው እስራኤል ነው:: ለጥቂት ወራት ካስተማርኩኝ በኋላ ወደ ግብፅ ለጥናት ሄጄ 2 ሳምንት አካባቢ ቆይቻለሁኝ:: ከዚያም ለሁለት ወራት ያህል ሩሲያ ነበርኩኝ"

"ለምን ነበር ሩሲያ የሄዱት?" ጠየቀ መርማሪ አከሎግ፤ በትናንሽ ሰርሳሪ አይኖቹ እየመረመራቸው፤

"ሩሲያ የሄድኩት በአክሱም ከማደርገው ጥናቴ ጋር በተያያዘ ነው::" አሉና ፕ/ር እሴ በረጅሙ ተንፍሰው ንግግራቸውን ቀጠሉ፤ "በአክሱም አካባቢ የሚገኙ ጥንታዊ የገዳማት ስዕሎች ጋር የሚመሳሰሉ የእመቤታችን ማርያምና የእየሱስ ክርስቶስ ጥንታዊ ስዕሎች በሩሲያ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያኖች ውስጥም እንደሚገኙ መረጃ ስለነበረኝ ይህንኑ ለማጣራት ነበር አካሄዴ..."

"እና እዚያ ያገኙት ነገር ምንድነው?"

"እዚያ ያገኘሁትማ ከጠበቅኩትም በላይ ነበር:: ‹ዘ አርት ኦፍ ሩሲያ› ከሚል አንድ ዘጋቢ ቪድዮ ላይ ባገኘሁት መረጃ መሰረት የሩሲያ ስልጣኔና የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የተጀመረው ከአንድ ከምስራቅ አፍሪካ በመርከብ ተሳፍሮ በመጣ ጥበበኛ ሰው ነበር:: ከዚህም ጋር ተያይዞ በቅርቡ ከግብፅ የፒራሚድ ‹አርኪዮሎጂካል ሳይቶች› ከተገኙ ስዕሎች ጋር የሚመሳሰሉ ስዕሎችን ስላየውም ነበር ለማጣራት ሩሲያ ድረስ ያቀናሁት:: እዚያ ሄጄም በጎበኘኋቸው በኪነ-ህንፃ ጥበብ በተራቀቁ ጥንታዊ ቤተ-ክርስቲያኖቻቸው ውስጥ ያገኘኋቸው ስዕሎች፣ መጽሐፍቶችና ቅርያች እውነታውን አረጋግጠውልኛል::"

"ምንድነው እውነታው?" አለ መርማሪ አከሎግ፤

"ጌታ እየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም የሃበሻ መልክ እንደነበራቸውና ብሎም ለብዙ አመታት ኢትዮጵያ ውስጥ መኖራቸው ነው:: ይህንን

በኢትዮጵያ፣ በግብፅና በእስራኤል ያሉ ስዕሎችና ብራናዎች ብቻ ሳይሆኑ በሩሲያ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙም መረጃዎች ያረጋግጣሉ::"

"እውነት ከሆነ የምርም የሚገርም ነው! የሆነው ሆኖ..." አለ አከሎግ ወደ መጠይቁ ዋና ምክንያት እየተመለሰ፤ "ፐ/ር አንዷለምን ያውቋቸዋል?"

"አዎን አውቃቸዋለሁኝ::" መለሱ ፐ/ር እሴ፤

"እሺ ጥሩ፤ ራሺያ በነበሩበት ወቅት አግኝተዋቸው ነበር?"

"አዎን"

"ለምን ጉዳይ ነበር ያገኟቸው?"

"የድሮ ወዳጄ ከመሆናቸውም በላይ ከእኔ በተሻለ ሩሲያን ስለሚያውቋት ላማከራቸው አስቤ ነው ያገኘኋቸው::"

"ሌላ ምንም የተነጋገራችሁት ነገር የለም?"

"የለም!"

"ፐ/ር አንዷለም በኢትዮጵያ መንግስት ደረጃ የሚፈለጉ የጸረ ሰላም ፖለቲከኛ እንደሆኑ ያውቃሉ?"

"ኧረ በፍፁም!" አሉ ፐ/ር እሴ እንደመደንገጥ እያሉ፤ "ከዚህ በፊት የተቃዋሚ ፓርቲ አባል እንደነበር ባውቅም በወንጀለኝነት እንደሚፈለግ አላውቅም ነበር::"

"እሺ አምኖታለሁኝ::" አለ መርማሪ አከሎግ የግራና ቀኝ እጅ ጣቶቹን አጠላልፎ በሰራው ድልድይ አገጩን እየደገፈ:: "ግን ምንም አይነት ለየት ያለ ነገር አላወራችሁም... አልያም ወደ ኢትዮጵያ አድርሱልኝ ያሉት ዕቃ ወይም መልዕክት የለም?"

"ኧረ በፍጹም!" አሉ ፐ/ር እሴ::

"እሺ በበኩሌ ጥያቄዎቼን ጨርሺያለሁኝ ግን በእርስዎ በኩል ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባ መልዕክት እንዳለ ስለተነገረን ለማረጋገጥ ያህል የእርሶንና የፍሬድሪካን እቃዎች በጥንቃቄ መፈተሽ አለብን!" ብሏቸው ተነስቶ ወጣ:: የፐ/ር እሴና የፍሬድሪካ ሻንጣዎች ብትንትን ተደርገው አንድ ባንድ መፈተሹ ሁለት ሰዓት ገደማ ነበር የፈጀው:: ደብዳቤ፣ መሳሪያ ወይም ለየት ያሉ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች እንደመርፌ ተፈለጉ፤ ምንም ግን አልተገኘም:: የስልኮችና ላፕቶፖቻቸው የማለፊያ ቃሎቻቸውን እንዲሰጡ ከተደረገ በኋላ ማጣራቱና ምርመራው እስኪያበቃ የዛሬን ሌሊት እዚሁ እንደሚያሳልፉና

ለፍሬድሪካም የእንግዳ ማረፊያ ክፍል እንደተዘጋጀላት ተነገራቸው፡፡ T/C እሲ "እሜን" ብለው ከመቀበል ውጪ ምንም አማራጭ አልነበራቸውም፡፡

_ በማግስቱ ጥዋት ደገፍ ብለው ካሸለቡበት ጠረጴዛ ላይ አከሎግ ነቅነቅ ነቅነቅ አድርጎ ሲቀሰቅሳቸው ሳያነቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ጠረጴዛ ላይ መተኛታቸውን አስበው ፈገግ አሉ፡፡

"ልዩ ፈገግታ ተላብሰዋል ፕሮፌሰር! በነፃ ሊለቀቁ እንደሆነ ቀድመው አውቀዋል ማለት ነው፡፡" አለ አከሎግ ፊታቸው ላይ ያስተዋለው የማለዳ ፈገግታ አስገርሞት፡፡

"ወንጀል የሌለበት ሰው እኮ አካሉ ቢታሰርም ህሊናው ነፃ ስለሆነ ፈገግታው ቀርቶ ለቅሶውም ይማርካል፡፡" አሉት ፈገግታቸው ሳይለያቸው፡፡ እርጋታቸው እንቆቅልሽ እንደሆነበት ማታ በኢንፎርሜሽን ባለሙያዎች ሲበረበሩ ያደሩትን ስልከና ላፕቶፓቸውን አስረከባቸው፡፡

*** ቶ – ቶ ***

እነኢትኤል ከተባረሩ ሁለት ቀናት በኋላ የህፃናት ህክምና ክፍል የዓመቱ የመጨረሻው ራውንድ ፕሮግራም ነበር፡፡ በዶ/ር እሳቱ ካሁን በኋላ እንዳትመጡ ተብለው የተባረሩት ኢትኤልና አብርሃም የዛሬ ተረኛው አስተማሪያቸው ዶ/ር ሳሙኤል እንደሆነ ካረጋገጡ በኋላ ነበር ዙሩን የተቀላቀሉት፡፡

ዶ/ር ሳሙኤል የወትሮ እርጋታው ሳይለየው ከተለመደው በተቃራኒ ከመጨረሻው አልጋ ነበር ዙሩን የጀመረው፡፡ አልጋው ስሙ በአልፋ-ቤቲካል ቅደም ተከተል መሰረት በዜድ ስለሚጀምር ሁሌም የመጨረሻ ተመዳቢ የሆነው የዘይኔ አልጋ ነበር፡፡ በምግብ እጥረት ተጎድቶ ቅጭጭ ያለምስኪን የ3 ዓመት ህጻን ልጅ አልጋው ላይ ተቀምጧል፤ አይኑን ቁልጭ ቁልጭ እያደረገ የከበቡትን ተማሪዎች በየተራ ያያል፤ ፈገግታ የሚባል ነገር ግን አይታይበትም፡፡ የተራቡ ህጻናት የየዋህነት ሳቅ ጨዋታቸውን ተነፍገዋል፤ ያስራባቸውን ማህበረሰብ በጥራጣሬ አይን እያዩ ይነጫነጫሉ፤ ያለቅሳሉ፡፡ ዶ/ር ሳሙኤልም ይህን ህጻን ለመመርመር ጠጋ ሲል ልጁ ከፉኛ እያለቀሰ ከእናቱ እቅፍ ተወሸቀ፡፡ ጎስቃላ እናቱ ከቅስሟ ጋር ተሰብሮ ያልተቃናውን አንገቷን እንደደፋች አቀፈችው፤ ለእናት ህጻን ልጇን መመገብ

ካለመቻል የተነሳ አይኗ እያየ ገላው ሲመናመንና ሲታመም እንደ መመልከት ያለ ምንስ ሽንፈት ይኖራል?!... ዶ/ር ሳሙኤል ለመመርመር ያደረገው ሙከራ በልጁ አሻፈረኝ ባይነት ስላልተሳካ... "የማን ‹ቤድ› ነው?" አለ ወደ ተማሪው እየዞረ፤... ዘይኔ ወደፊት ቀረበና የልጁን የጤና ታሪክና የምርመራ ውጤቶች በዝርዝር አነበነበ:: ዶ/ር ሳሙኤል በጥሞና ሲያዳምጠው ከቆየ በኋላ እንደጨረሰ ሲያረጋግጥ... *"So you are thinking this is a primary malnutrition, and then what do you think is the cause for it?* (ይህን ልጅ ያከሳው የምግብ እጥረቱን እንደሆነ ነግረኸናል... ግን የምግብ እጥረቱ ምክንያትስ ምን ይመስልሃል?)" ብሎ ጠየቀው፤

"*The mother told me her husband is a farmer who gets 500 birr per month and the family doesn't get enough amount of proteinous foods like meat, egg and milk.* (እናቱ እንደነገረችኝ ባሏ በወር 500 ብር የሚያገኝ አርሶ አደር ስለሆነ በፕሮቲን የበለፀጉ እንደስጋ፣ እንቁላልና ወተት ያሉ ምግቦችን ቤተሰቧ አያገኝም::")

"Did they grow fruits in their farmland? (የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬዎችንስ ይተክላሉ?)"

"*They only told me that they grow and sale maize, I don't know about the fruit and vegtables...* (በቆሎ እንደሚሸጡ ነግረውኛል ግን አትክልትና ፍራፍሬ እንዳላቸው አላጣራሁም::)" አለ ዘይኔ በግልፅነት፤ ዶ/ር ሳሙኤል አንገትና ቅንድቡን ከፍ ዝቅ እያደረገ ከሰማው በኋላ ታካሚውን ልጅ ወዳቀፈችው እናት ዞረ፤ እናትዬው ለልጁ በብርጭቆ የታሸገ ብርቱካናማ ጁስ እያጠጣችው ነበር:: ተቀበላትና ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ጣለው::

ተመልሶም "ለልጁ ከሚሰጠው ህክምና ጋር ይሄን አንፈቅድም እሺ፤ ሌላም ጊዜ የታሸገ ጁስ ትገዢለታለሽ እንዴ?" አላት እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል እያደረገ፤

"አዎ፤ አንዳንዴ ምግብ እንቢ ሲለኝ ገዝቼ አጠጣዋለሁኝ፤" አለች እናት... አንገቷን ደፍታ የአልጋ ልብሱን እያሻሸች፤

"ሁሌም የሚገርመኝ ነገር እኮ ነው!" አለ ዶ/ር ሳሙኤል የህጻኑን እናት በፈገግታ እያየት... "ብር የለንም እንላለን የማይጠቅም የውጭ ስኳርና ኬሚካል ለልጆቻችን እንገዛለን... እስኪ የዚህ ጁስ ዋጋ ስንት ነው?".......

"20 ብር::" አለች፤ ከኪሱ የዳፍውን ጁስ ሂሳብ 20 ብር አውጥቶ ሰጣትና ሌላ ጥያቄ አስከተለ፤

"አንድ ማንጎ እናንተ አካባቢ ስንት ብር ይሸጣል?"

"ጊዜው ከሆነ 1 ብር፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ 3 ወይ 4 ብር ይገኛል" አለች::

"ታድያ በ2 ብር እንኳን ብናስበው በ20 ብር ምን የመሰሉ አስር ትኩስ ማንጎዎችን ገዝተሽ በንፅህና አዘጋጅተሽ ብትሰጭው አይሻልም? ደግሞስ ባላችሁ መሬት ላይ ቆፈር ቆፈር አድርጋችሁ የአቮካዶ ዛፍን ብትተክሉ የጅማ አፈር ለም ነው ልጅሽ እንዲህ ባልሆነ ነበር:: እንዲህ ስልሽ ደግሞ ይህ ችግር ያንቺ ብቻ ሆኖ እየወቀስኩሽ እንዳይመስልሽ፤ አብዛኞቻችን ልጆቻችንን የጠቀምን እየመሰለን ለስላሳ መጠጦችንና የታሸጉ ጁሶችን እናጠጣቸዋለን:: ገና በለጋነታቸው ኩላሊቶቻቸውንም በአርቴፊሻል ቀለምና ኬሚካል እንዋጋዋለን:: የለስላሳ መጠጦች 20% ፀረ-አረም ኬሚካል እንዳላቸው፤ በጊዜ ሂደት አጥንትን እንደሚያሳሱ... አንዳንዶቹማ ሲፈሉ እንዳስፓልት መስሪያ ‹ሬንጅ› አይነት ኬሚካል እንደሚቀየሩ ማንም አይነግረንም:: ይጣፍጣል እያልን ታሽጎ በፀሃይና ሙቀት የዳከረ ነገር እያጠጣናቸው፤ የእድሜ ልክ ህመም እንተክልባቸዋለን::

...በጣም የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ የታሸጉ ምግብና መጠጦቹ በእኛ ሀገር የተመረቱ እንኳን አለመሆናቸው ነው:: ለምለም አፈር፤ ለሌላም የተረፈ ውሃና የማያቋርጥ የፀሐይ ብርሃን እያለን የማንጎና በርቱካን ጁስ ከበረሃዎቹ የአረብ ሃገራት ይላከልናል:: ስንዴና ገብስ የሚያፈስ ገበሬ፤ የሸንኮራ አገዳ ጫካ እያለን ብስኩትና ቸኮሌት እናስልካለን:: ኦቾሎኒና አትክልቱን ሳናጣ፤ በጋማና የቀንድ ከብት ሃብታችን ‹ከአፍሪካ አንደኛ› እየተባልን የላሞቻችንን ወተት መጠቀም አቅቶን ሌላው ቀርቶ ልጆቻችን ሲራቡ የምናከምበትን ፎርሙላ ወተትና ‹ፕላምፒነት› ቀምሞ ማዘጋጀት እያቃተን የውጭ እርዳታ እንጠብቃለን::" አለና በረጅሙ ተነፈሰ፤ ሁሌም ቢሆን አንድ ነጥብ ለማስተማር ይጀምርና በስሜታዊነት ብዙ መናገሩ የተለመደ ባህሪው ነው::

*"Anyways let's return to our patient, so any additional cause you identified? (ለማንኛውም ወደ ታካሚያችን ሁኔታ እንመለስና እስኪ ሌላ ያገኘሽው የአጥረቱ ምክንያት ካለ ንገሪኝ?)" አለ ወደ ዘይኔና ወደ እንግሊዘኛ ቋንቋው እየተመለሰ፤ "Plus the baby has four older siblings who share his daily meal together with him. (በዚያ*

*ላይ ይህ ህጻን ጋር አብረው ምግቡን የሚጋሩት አራት ታላላቅ ወንድምና እህቶች አሉት፡፡)" አለ ዘይኔ በእርጋታ፤*

*"So what do you think we should do about that? (ለዚህ ችግር ታድያ ምን ማድረግ ያለብን ይመስልሃል?"*

*"We should tell her to give him his meal alone. (ለልጁ ለብቻው ምግብ እንድትሰጠው ማድረግ፡፡)"*

*"Yeah, If that is possible, but what about the future plan. (ያን ማድረግ ከቻለች ጥሩ ነው ግን ለወደፊት እቅዷስ?)" ብሎ ቢጠይቀውም ዘይኔ መልስ ስላልነበረው ዝም ቢል ዶ/ር ሳሙኤል ፍንጭ ሰጠው፤ "Won`t you advice her about family planning? (ስለቤተሰብ ምጣኔስ ምክር አያሻትም?)"*

*"ያስፈልጋል... እመክራታለሁኝ፡፡" አለ ዘይኔ፤*

*"ምን ብለኸ?... በነገራችን ላይ ማነው ዘይኔ ነው አይደል ስምህ፤ ባልሳሳት ሙስሊም ነኸ አይደል?" አለ ዶ/ር ሳሙኤል፤*

"እዎ!" አለ ዘይኔ በለዘብታ፤

"አይዞህ አትፍራ፤ በበኩሌ ሃይማኖቱ ምንም ይሁን ምን ሃይማኖተኛ ሰው ግን እወዳለሁኝ፡፡ አንዳንድ ተማርን ያሉ አላዋቂዎች «ሁሉም ነገር በአጋጣሚ ነው የሚፈጠረው» ብለው ሃይማኖት ስህተት መሆኑን ሊያሳምኑን ቢጥሩም እኔ ግን አልቀበላቸውም፡፡ ዝንጀሮና ጦጣ አያቶች እንዳሉን ቢነግሩን አላምንም፡፡ የሚገርመው እኮ ከእነርሱ መሃልም ታላቅ የሚባሉት ሳይቀሩ የአምላክን ህልውና ተቀብለው፤ የሃይማኖት አስፈላጊነትም መስክረው ነው ያለፉት፤ ልክ ታላቁ ሳይንቲስት አልበርት አንስታይን "ሳይንስ ያለሃይማኖት እውር ነው!" እንዳለው ማለት ነው፡፡ ለማንኛውም ሃይማኖትህን የጠየኩህ በወሊድ መቆጣጠሪያ መንገዶች ዙሪያ ያለህን አመለካከት ለማወቅ ነው፡፡ ያው አንዳንድ ሃይማኖቶች የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን እንደማይደግፉ የታወቀ ነው፡፡ ለማንኛውም ይህቺ እናት ያሉትን ልጆቿን መመገብ ሳትችል ሌላ ልጅ እንድትወልድ አንመክራትም፡፡ እንግዲህ በሃይማኖቱ በኩል ያለውን ነገር አባቶች በደንብ ማብራሪያ ሊሰጡበት ይችላሉ፤ በእኛ በጤና ባለሙያዎች ዘንድ ግን አላስፈላጊ እርግዝና ተብሎ ዕንስ ከሚጨናገፍ ብሎም ልጅ ተወልዶ በምግብ እጥረት ከሚሰቃይ የቤተሰብ ምጣኔን ተግባራዊ ማድረግ የተሻለ አማራጭ እንደሆነ እናምናለን፡፡" አላና ሃሳቡን ቋጨ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ምግብ እጥረት ያለበት ልጅ ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተጓዳኝ የጤና እክሎችና

የሚደረግላቸውን ህክምና በዝርዝር ካስረዳቸው በኋላ ወደ ቀጣዩ እልጋ ተሸጋገረ:: ይሄ የዮሴፍ አልጋ ግን ለጊዜው ታካሚ የሌለበት ባዶ ስለነበር እሱ ተዘለለና ወደ ቀጣዩ አመሩ፤ የዮሴፍ ፊት ላይ ልዩ ፈገግታ ተስተዋለ:: ቀጣዩ እልጋ ላይ አንድ በዘረ-መል መዛባት ምክንያት የፊንጢጣው ቀዳዳ የተዘጋ (Imperforated Anus) ታካሚ ጨቅላ ተኝቷል፤ የቀዶ ህክምናውን ሰዓት እየተጠባበቀ ነበር:: የአልጋው ባለቤትም ከባቹ ሲቃዮች መካከል የሚመደበው ወጋየሁ ነበር:: እንከን የሌለበት የሚመስል ታሪከና የምርምራ ግኝቱን ለሁሉም አቀረበ:: ስለበሽታው መንስኤና ተያይዘው የሚመጡ ሌሎች ችግሮችን በዶ/ር ሳሙኤል ጥያቄ መሰረት አብጠልጥሎ አስረዳ:: ዶ/ር ሳሙኤል የወጋየሁን እውቀት ለማረጋገጥ ሌላ ጥያቄ መጠየቅ አላስኘውም ነበር:: የሆነ ነገር ትዝ እንዳለው ሁሉ ፈገግ ብሎ ወደተቀሩት ተማሪዎች ዞረ::

"አንድ ቀልድ ልንገራችሁማ፤" አለና ተመቻችቶ ቆሞ ማውራት ጀመረ፤ "ከእለታት አንድ ቀን የሰውነት አካል ክፍሎች በሙሉ እርስ በእርሳቸው ፉክክር ጀመሩ፤ ለሰው ልጅ መኖር እጅግ አስፈካጊ የሆንኩት "እኔ ነኝ"… "እኔ ነኝ"… እያሉ ተጨቃጨቁ:: በቅድሚያ ለሁሉም የመከራከሪያ ነጥቡን ያቀረበው አንጎል ሲሆን "እኔ ከሌለሁኝ የሰው ልጅ የማሰብ ሃይሉን ያጣል፤ እናንተንም በሙሉ የሚያስተናብር አይኖርም፣ እኔ ቀን ከሌት ሳልል ልብ እንዲመታ፣ ሳንባ እንዲተነፍስ፣ ጨጓራ እንዲፈጭ ባላዝዝ የሰው ልጅ ለደቂቃም መኖር አይችልም፤" ብሎ ጠንካራ የመከራከሪያ ነጥቡን አቀረበ::

— ከዚያም እድሉ የተሰጠው ልብ ወደአንጎል ዞሮ "አንተ የፈለግከውን መልዕክት፣ የፈለግከውን ሃሳብ ብታመነጭ እኔ ለደቂቃዎች ደም በሃይል እየረጨሁኝ ላንተ ማድረሴን ባቆም ቅድሚያ የምትሞተው አንተ ነህ:: እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል እኔ የምልከለትን ደም ካላገኘ ሟች ነው:: የሰው ልጅም ካለእኔ የመኖሩ ነገር ቅዠት ነው" ብሎ ተናግሮ ሲቀመጥ፤ "እንደዚያማ አትበል አያ ልብ… አንተ የምትረጨው ቀይ ፈሳሽ የኔን ኦክስጅን ካልተሸከም ጥቅም አልባ እንደሆነ ረሳህ እንዴ?" አለ ሳንባ በግርምት ወደልብ ዞሮ "ለማይክሮ ሰከንድ ሳላርፍ የተቃጠለውን አየር እያወጣው ንጹሁን አየር ባላስገባ ኖሮ ሁልሽም ታፍነሽ ትሞቺ ነበር!" አለ::

ዶ/ር ሳሙኤል ሁሉም ተማሪዎች ተመስጠው እየሰሙት እንደሆነ ካረጋገጠ በኋላ ትረካውን ቀጠለ— "እናማ ሌሎችም እንደጨጓራ፣ ኩላሊት፣ ጉበት… ጉሮሮ፣ አይን፣ እጅ፣ እግር ወዘተ ያሉ የሰውነት አካሎች በየተራ እየተነሱ ለሰው ልጅ ህልውና ያላቸውን አስተዋፅኦ ዘረዘሩና በስተመጨረሻ የፊንጢጣ ተራ ደረሰ:: እርሱም እንደ ሌሎቹ አካላት

ያለውን ጠቀሜታ መናገር ሲጀምር ሁሉም የሰውነት አካላት ከት ብለው ይስቁበት ጀመር:: "አንተ ደግሞ የእኛን ትራፊ ከማራገፍ ውጪ ምን ጥቅም አለህና?" ብለውም ተሳለቁበት:: ከርከሩም የፊንጢጣን ሃሳብ ሳያስተናግድ አበቃ:: በመናቁ ከፋኛ የተበሳጨው ፊንጢጣም "ቆይ ማንነቴን አሳያችዋለሁኝ!" አለና የታችኛውን በር ጥርቅም አድርጎ ዘጋ::

ታድያ እነዚህ አካላቶች የተከራከሩበት የሰው ልጅ በጥዋት "ሃገር ሰላም!" ብሎ ከእንቅልፉ ተነስቶ ቁርሱን በልቶ ከቤቱ ወጣላችሁ:: ሁሉም የሰውነት አካላቶቹ ተግባራቸውን ሲፈፅሙ ቆዩ:: ጨጓራም ከጥርስ የተረከበውን ምግብ ፈጭቶ ለትንሹ አንጀት አስረከበ፤ እርሱም ጠቃሚ የሆኑትን እየመጠጠ ወደ ደም ላከና የተረፈውን ለትልቁ አንጀት አስረከበ:: ትልቁ አንጀትም ስራውን ጨርሶ ወደታች ሊልክ ሲል በሩ ጥርቅም ተደርጎ ተዘግቶ አገኘው:: ሽንት ቤት ለመጠቀም የሄደው ሰውዬም ታግሎ ታግሎ እዳሪውን ማውጣት አቃተው:: ሃኪም ቤት ቢሄድም ምንም ችግር እንደሌለበት ይነገረዋል:: ከአንድ ቀን በኋላ ሆዱ ውስጥ ታላቅ ጭንቀት በመፈጠሩ አንጎሉ ተወጠረ፣ ልቡ በፍጥነት ይመታ ጀመር፤ ሳንባም ጭንቅ ውስጥ ያለውን ሰው ትንፋሽ ለማድረስ ከአቅሙ በላይ ተሯሯጠ:: ጭንቁ የበዛባቸው የሰውነት አካላት ችግሩ የት እንደሆነ ሲያጣሩ ፊንጢጣ በሩን መዝጋቱን ተረዱ:: ሁሉም ተሰብስበው ፊንጢጣን ሊያናግሩ ወረዱ:: ያኔ እንዳልናቁት ሁሉ! ባይገርማችሁ" አለ ዶ/ር ሳሙኤል ተማሪዎቹን ፈገግ ብሎ እያየ… "ባይገርማችሁ እግሩ ላይ ወድቀው ይቅርታ ጠይቀውት ነው አሉ ከምጣቸው የገላገላቸው::"… ተማሪዎቹ እየተቀባበሉ ከት ብለው ሳቁ::

"ቀልዱስ ቀልድ ነው! ግን ሁሉም የሰውነት ክፍሎች ጠቃሚ እንደሆኑ በደንብ የሚገልጽ ታሪክ ስለሆነ ነው ያጫወትኳችሁ:: እኛ የሰው ልጆች የተገነባነው በልዩ መዋቅር ሆኖ ሳለ በነፃ ይህንን ሁሉ ሃብት የሰጠንን ፈጣሪ ከማመስገን ይልቅ በረባ ባልረባ ነገር ስናማርር ስለሚገርመኝ ነው:: አስገራሚውን አንጎላችንን እንኳን ብንመለከት አንዴ ወደሰውነታችን ክፍሎች የሚልከው መልዕክት በአለም ላይ ፈጣኑ የሚባለውን የፎርሙላ-1 መኪና ከሚሄደው ፍጥነት በላቀ ይጓዛል:: እኛ ብንተኛም ባንተኛም እርሱ ሳይተኛ ልባችንን፣ ሳንባችንና ሌሎችንም የሰውነት አካላቶቻችንን ያዛል፤ ከየትኛው ሰው ሰራሽ ኮምፒዩተር በላቀ ሃሳብን ያውጠነጥናል፣ ትውስታዎችን ያከማቻል፣ የፈጠራ ችሎታን ያዋቅራል:: ስራው ብዙና ውስብስብ ነው፤ የሰው ልጅ አካላትም በዋናነት የሚሰሩት ለአንጎላችን ግሉኮስና ኦክስጅንን ለማድረስ ነው::

የሚገርመው ግሉኮስና ደም ያነሰው ሰው «ፌንት» አደረገ ተብሎ የሚወድቀው ከልቡ የሚረጨው ደም የመሬት ስበት ተቃርኖ ሳይኖርበት ቀጥታ ወደ አንጎላችን መፍሰስ እንዲችል መሆኑንም ጥናቶች ጠቁመዋል:: ታዲያ ይህንን ኃይለኛና ውስብስቡን አንጎላችንን ትተን እንደ እጃችን ላይ ብቻ የሚገኙትን 20 ገደማ አጥንቶች ብናስተውልና እንዴት ተስተናብረው እንደሚተጣጠፉ፣ እቃ ሲይዙና ሲለቁ ያለውን መስተጋብር ብናውቅ እንገረማለን:: ከብዙ በአንዲት ጣፊያ ውስጥ ያሉት ሴሎች ውስጥ እጅግ ጥቂት የሚባሉት ‹ቤታ ሴሎች› የሚረጩት ኢንሱሊን የሁሉን የደም የስኳር መጠን መቆጣጠሩ ታላቅ ተዓምር እንደሆነ የሚገባን እነዚሁ ጥቂት ሴሎች ኢንሱሊን ማምረታቸውን አቁመው፤ ‹ስኳር በሽተኛ ናችሁ› ተብለን በቀን ሁለቴ በመርፌ ራሳችንን ኢንሱሊን መውጋት ስንጀምር መሆን የለበትም::

የመለስተኛ ትርንጎ መጠን ያላት ኩላሊት የምትሰራውን ስራ ታላቅ ዋጋ ሳንረዳው፤ በአልኮል፣ ሲጋራና አርቴፊሻል ምግቦች ከስራ ውጪ እናደርጋታለን:: ብዙ ብር የከፈልንበት ግዙፍ ቁም-ሳጥን የሚያክለው የኩላሊት-ማጠቢያ (ዲያሊስስ ማሽን) እንኳን በሚገባ ሊወጣው የማይችለው ስራ እንደሆነ ስንረዳ ከረፈደ ስህተታችን ሊገባንም አይገባም::"

በስሜታዊነት ሲያወራ የነበረው ዶ/ር ሳሙኤል ገና በሁለተኛው አልጋ ላይ ጊዜ መፍጀቱ ታወቀውና ሞባይሉን አወጥቶ ሰዓቱን ተመለከተ፤ ስድስት ሰዓት ከሩብ ይላል:: "በቃ አንድ ፔሸንት በፍጥነት እንይና ወደምሳ ትሄዳላችሁ::" አለና ወደቀጣዩ የቶላ አልጋ ተሻገረ፤

የቶላ አልጋ ላይ የተኛችው ነፍስ ሳታውቅ በወሊድ ጊዜ ኤች አይ ቪ ከእናቷ የተላለፈባት የ7 አመት ህፃን ነች:: ከዚህም ጋር ተያይዞ የሰውነቷ በሽታ የመቋቋም አቅም ደካማነት የተነሳ የሳንባ ምች በሽታ እጅጉን በርትቶባታል:: ካለማቋረጥ ታስላለች፤ መተንፈሱ እንኳን ካቅሟ በላይ ሆኖባት በኦክስጅን ሲሊንደር ድጋፍ ነበር የምትተነፍሰው:: ቶላ የልጅቱን የመድሐኒት አወሳሰድና የኑሮ ሁኔታ ጨምሮ ታሪኳን እያነበበ ነበር፤ ዶ/ር ሳሙኤል ግን በከፍተኛ የማዘንና ሰብዓዊነት ስሜት ተሞልቶ ልጅቱን እየተመለከታት ነበር:: ሳንባዋንና ልቧን ለመመርመር የጆሮ ማዳመጫውን አወጣ:: ልብሶቿን እያወለቀ ሳለ ከሬዝደንቶቹ አንዱ ጓንት ሲሰጠው እጁን ሲዘረጋ ሳይቀበለው ምርመራውን ቀጠለ::

*"The Mother already thinks it is her fault that her child got infected, checking her only child with gloves will make her think that we are discriminating her. And don't you forget*

*it was fear and lack of awareness that led to stigma and discrimination; this in turn has created vengeance that helped the virus to spread in the first place.* (እናቷ እኮ ልጇን ለዚህ ያበቃቻት እሷ እንደሆነች እያሰበች ራሷን የምትወቅስ ልትሆን ትችላለች:: በዚያ ላይ የሷን ልጅ ብቻ ለይተን በጓንት ስናከም የመገለል ስሜት ሊሰማት ይችላል:: በፍፁም መርሳት የሌለብን ነገር ደግሞ ከጅምሩም ቢሆን ይህ በሽታ እንዲሰራጭ ከፍተኛውን አስተዋፅኦ ያደረገው ከፍርሃትና አለማወቅ ተነስቶ የተፈጠረው ማግለልና መድሎ በቀልን በመውለዱ ነው::)" አለና ምርመራውን ጨርሶ ወደ ተማሪዎቹ ዞረ::

"You know its history right? How this disease (HIV) started? (ታሪኩን ታውቃለህ አይደል? ይህ በሽታ እንዴት እንደተከሰተ?") ቶላ ተጠየቀ፤

"Yeah, it was said to come from chimpanzees in West Africa. (አዎን፣ ምዕራብ አፍሪካ ውስጥ ከሚገኙ ቺምፓንዚ ወደ ሰዎች እንደተላለፈ ነው የሚነገረው::)" አለ ቶላ በእርግጠኝነት፤

*"Yeah, that is what they want you to believe. But we Africans have lived in the jungle with chimpanzees and other animals for millinias but we never had such kind of illness in our history. But I believe it was intentionally produced in the laboratory for depopulation purposes. And I say it is not a curse b/c it affects such innocent children who has nothing to do with sin. Ironically, they say it is a sexually transmitted disease initial consensus on the prevalence of the disease was not in those countries who have sexual intercourse in regular base and who doesn't put a taboo on it,* (አዎ ያ እነርሱ እንድናምን የሚፈልጉት እውነት ነው:: ነገር ግን እኛ አፍሪካውያን ስንት ሺህ ዘመናትን በጫካ ውስጥ ከቺምፓንዚና ሌሎች የዱር እራዊት ጋር ኖረናል፤ እንደዚህ መሰሉ ህመም ግን በታሪካችን ውስጥ አጋጥሞን አያውቅም:: በሌላ በኩል ደግሞ በሽታው የአምላክ እርግማንም እንዳልሆነ የሚያረጋግጥልኝ እንደዚህች አይነት ምንም ኃጢያት ያልሰራች ልጅን ሲያሰቃይ ነው:: የሚገርመው እኮ በሽታው የሚተላለፈው በግብረ-ስጋ ግንኙነት ነው ተብሎ በመጀመሪያ ቆጠራ ሲካሄድ ወሲብ እንደጉድ የሚፈፅሙት አውሮፓውያንና አሜሪካውያን እያሉ ከፍተኛ ተጠቂ ሆነው የተገኙት ግን በባሕልና

በሃይማኖት ታጥረው የሚኖሩት እንደ ህንድ፣ ቻይና፣ አፍሪካና አረቦች መሆኑ ነው)" አለ፣ ሲያወራ ከፍተኛ ቁጭት ይነበብበታል::

"This is your final week in Pediatrics right? (ይህ በህፃናት ህክምና ክፍል የምትቆዩበት የመጨረሻ ሳምንት ነው አይደል?)"

"Yes! (አዎ!)" አሉ አብዛኞቹ ተማሪዎች በአንድ ድምፅ፣

"እዎን የዛሬ እመት መገናኘት አለመገናኘታችንን የሚያውቀው ፈጣሪ ብቻ ነው:: ብዙ ምክር እንደማበዛባችሁም ይታወቀኛል:: በመጨረሻ ግን የምነግራችሁ፣" አለና ዶ/ር ሳሙኤል ለአፍታ በዝምታ ከቆየ በኋላ፣ "በመጨረሻ ግን የምነግራችሁ... የተሰጣችሁን የመማሪያ መፅሐፍት በአግባቡ ካነበባችሁ፣ ዋርድ ውስጥ የሚሰሩት ነገሮች ላይ ትኩረት አድርጋችሁ ከሰራችሁ በጥሩ ውጤት የምትመረቁ ሐኪሞች እንደምትሆኑ ጥርጥር እንደሌለው ነው:: ነገር ግን አደራ የምላችሁ በፈረንጅ የተፃፈላችሁን ከማንበብና ከመሸምደድ ባለፈ የሃገራችሁ ኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ አገናዝባችሁ፣ ሃገር ወለድ የሆኑ የህክምና ጥበቦችን አጥንታችሁ ወደ ተግባር መቀየር የምትችሉ ሃኪሞች እንድትሆኑ ነው::" አለና አልጋውን ደገፍ ብሎ ቆመ፣ የደከመው ይመስላል::

"ታዝባችሁ ከሆነ እዚህ ለስራ ልምድ የሚመጡ የኩባ፣ የፈረንሳይ፣ የጀርመን፣ ኮሪያና ሌሎች ሃገራት ዶክተሮች የህክምና ጥበብን የተማሩት በራሳቸው ቋንቋ ነው:: ይህ ደግሞ የህዝባቸውን የጤና እክሎች በሚገባ ለማወቅና ለመቆጣጠርም ይሁን ለማከም እንደሚያግዛቸው አይካድም:: ሙሉ በሙሉ መቀየር ባይሆንልን እንኳን ዋና ዋና የጤና ችግሮቻችንን መለየትና ማከም የምንችልበት በራሳችን ቋንቋ የተዘጋጀ ሃገር አቀፍ መመሪያ ሊኖረን ይገባል:: ወደድንም ጠላንም የጤና እክሎቻችንን ለማሸነፍ እንደ ሃገርም ሲሰፋም እንደ ጥቁር አፍሪካዊ የራሳችንን እውቀትና ችሎታ ማዳበር የግድ አስፈላጊ እንደሆነ ማወቅ አለብን::

ምዕራባውያን የእኛን የህዝብ ቁጥር ለመቀነስ እንዴ ኤች አይ ቪ፣ እንዴ ኢቦላ እያሉ ላብራቶሪ ውስጥ ገዳይ ቫይረሶችን ማምረታቸውና በተለያዩ መንገዶች መበተናቸውን አያቆሙም:: በቅርቡ በፈበረኩት የኢቦላ ቀውስ እንኳን መድሐኒቱ የለም ሲሉ ከርመው የእነርሱ ዶክተሮች በበሽታው ሲያዙ ግን የሚድኑበትን ህክምና እንዳገኙ አንረሳም:: በምድር ላይ ያለ በሽታ በሙሉ መድሐኒቱም በምድር አለ" ብሏልና የነዘይኔ ነብዩ ሙሐመድ፣ መድሐኒቱን እነርሱ እስኪያገኙልን አንጠብቅ::" አለ ዘይኔን በፈገግታ እያየ፣

'እውነቱን ነው የምላችሁ፤ ለእኛ ያለነው እኛው ነን፤ የራሳችንን ጥናት እናካሂድ፤ የጥንቱን ጥበባችንን ፈትሸን የራሳችን ቀለም ያለው ገንዘብና ጥቅምን ሳይሆን መተሳሰብና ተፈጥሮን የተንተራሰ ኢትዮጵያዊ የህክምና ስርዓት መፍጠር እንደምንችል አምነን እንንቀሳቀስ:: ሁላችሁም የቀጣዩ ትውልድ ተተኪ ሃኪሞች ይህ ሃላፊነት ሊሰማችሁ ይገባል:: ይህንን ሃላፊነት ተቀብላችኋል ብዬ አምናለሁኝ.. አይደለም እንዴ?" ብሎ ሲጠይቅ፤

"አዎ!" ብለው በስሜታዊነት ሁሉም ተማሪዎች ሲመልሱ መጮኻቸው እንኳን አልታወቃቸውም ነበር:: ዶ/ር ሳሙኤል በፈገግታ ተሞልቶ ሁሉንም ወደ ምሳ ሸኛቸው::

ኢትኤል፣ አብርሃም፣ ዘይኔ፣ ቶላ፣ ናዖድና ዮሴፍ ስለዶ/ር ሳሙኤል ለየት ያለ አመለካከት በመገረም እያወሩ ከሆስፒታሉ ወጡ:: ወደቤት፣ ወደቤተ-ክርስቲያንና መስጂድ ለመሄድ አብረው ወደታች ወረዱ:: በድንገት ግን አንድ አባት ከፊታቸው መንገዱን ዘግተው ቆሙ:: ያስቆሟቸው እኚያ ከሰሞኑ በጅሬን ሰፈር የጅማ ኑዋሪዎች ዘንድ መነጋገሪያ የሆኑት ባህታዊ አባት ነበሩ:: አምስቱ ጓደኛማቾች ደንግጠው ቆሙ:: "ስለምን ትደነግጣላችሁ?" አሉ ባህታዊው የደግ ሰው ደግነት፣ የየዋህ ሰው የህዋ-ነት፣ የገር ሰው ጌራ-ገርነት፣ የሚያንፀባርቅ ውብ ፈገግታ እየታየባቸው፤

"እግዚአብሔር ወደዚህ ትውልድ ፊቱን አዙሯልና:: አዎን! ከቃል ጠባቂዎች ሁሉ በላይ ቃል ጠባቂው አባት የቅድስት ምድሩን ህዝብ ያስባልና፤ የቅዱሳንን ጸሎት አይረሳምና:: መንገዱን የሳተን ትውልድ እሱ ወደ መንገዱ ይመልስ ዘንድ ይገለጣል:: ብቻውን ሆኖ ፈተናው ያስጨነቀውን ሁሉ እግዚአብሔር ያግዛል:: መንፈሱን ያፈሳል፤ በሁሉም ዘመን ለህዝቦቹ አስታዋሾችንም ይልካል::" አሉ፤... አብርሃም ሽቁጥቁጥ ብሎ አጎነበሰና መስቀላቸውን ተሳለመ::

"አብረሃም ልጄ ተባረክ፤ መርየም እንዴት ናት?" አሉት ትክ ብለው ፊቱን እየተመለከቱት፤ ልቡ ለሁለት ስንጥቅ አለች::

"አይዞህ አትደንግጥ የትኛውም ሃይማኖት የሚከተል ቤተሰብ ውስጥ ብትወለድም የእግዚአብሔር ውብ ፍጥረት መሆንህ አይፋቅም፤ ሰማይና ምድርን ከሚሞላው ምህረቱና ፍቅሩ አትገለልም::" አሉና ወደነኢትኤል ዞሩ፤ "ኢትኤል፣ ዘይኔ፣ ቶላና ናዖድ እናንተም ሁላችሁም የደጉ አምላካችን ስራዎች ናችሁ::" ሁሉም ስማቸው እንዴት እንደታወቀ ግራ እየገባቸው እርስበርሳቸው ተያዩ::

"አሁንም ስማችን ተጠራ ብላችሁ አትገረሙ፤ ይልቅስ በፈጠራችሁ አምላክ ጥበብ ተደነቁ፤ ካለመኖር ወደ መኖር መጣችሁ!! ከመወለዳችሁ በፊት ማንነታችሁንም የማታውቁ ምንም ነበራችሁ! እርሱ ግን ነፍስን ለገሳችሁ፣ አጥንትን አዋቅሮ ስጋ አለበሳችሁ:: በልጅነት የሚጠብቋችሁንም መልዓክት በግራና ቀኝ አኖረላችሁ:: እናንተ ግን በጉብዝና ዘመናችሁ ዝንጉና አላዋቂ ስትሆኑ የምዕራባውያንን የህይወት መንገድ ተከተላችሁ:: አሁንም እግዚአብሔር ለአባቶቻችሁ ለነ መልከፃዲቅ የዘላለም ከህነት ለግሷልና... ከነዮቶር ጋርም ቃል-ኪዳኑን ጠብቋልና በማይገመቱ፤ በማይመረመሩ መንገዶች በእኛ ህይወት ላይ ይሰራልና ወደ እናንተ በምህረት አይኑ ተመልከቷል:: ሁላችሁም በጥንቃቄ አድምጡኝ!" አሉ ኮስተር ብለው ሁሉንም ተራ በተራ እያዩ፤

"የሠራዊት ጌታ በእናንተ በኩል ለዚህ ትውልድ ያስተምራልና:: እንግዲህ ይህቺ ምድራዊ የአስኳላ ት/ት ፈተናችሁ ስታበቃ ሁላችሁም አንድ አይነት ህልም ታያላችሁ:: በእረፍት ጊዜያችሁም እነሆ ይህንን ህልም ካያችሁ ኋላ፤ 3 ቦታዎች ሄዳችሁ 3 ሰዎችን ታገኛላችሁ:: ይህም ታላቅ መገለጥን ይሆናልና::" አሏቸው፤... እነኢትኤል ግራ በመጋባት ውስጥ ተያዩ፤ "ሦስት ቦታዎች ያሉት የት የት ይሆኑ?" አለ አብርሃም ፈራ ተባ እያለ፤

"ሁሉም በጊዜው ይሆናልና በቅርቡ ታውቃላችሁ:: ከጅምሩ የነበራችሁን የእውነት ማንነት ግን አትርሱ፤ የልጅነት የዋህነት ውስጥ የነበራችሁን ደስታም አትዘንጉ፤ ጊዜ ባመጣው አብለጭላጭም የፅዮንን ምድር አትተኩ::" አሉ በተለይም ኢትኤልን እየተመለከቱ::

ካርድ ሊጋዛ ወደ ሱቅ ጎራ ብሎ የነበረውና ከኋላቸው ዘግይቶ የመጣው ዮሴፍ ተሰብስበው የቆሙት 5 የዶርም ጓደኞቹ ምን እያደረጉ እንደሆነ አልገባውም:: አምስቱም ባዶ አስፓልት ላይ የሆነ ሰው እያዩና እያዳመጡ ይመስል ፈዘው ቆመዋል፤... "እነዚህ ልጆች አበዱ እንዴ?" ብሎ ለራሱ ፈገግ አለና እየተንደረደረ ወደ እነርሱ ወረደ፤

"እናንተ ልጆች በቃ ለየላችሁ ማለት ነው?" እያለ እየጮኸ ሲጣራ ሁሉም ወደ ዮሴፍ ዞሩ፤ "ከማን ጋር ነው እያወራችሁ ያላችሁት?"

"ከእርሳቸው ጋር..." አለና ኢትኤል እጆቹን ባህታዊው ወደነበሩብት ቦታ ዘርግቶ ሲዞር በቦታው ማንም እንዳልነበር አየ:: ዮሴፍ ከት ብሎ ሳቀ፤ አምስቱም በድንጋጤና ጥያቄ ተሞልተው እርስ በርስ ተያዩ፤... "የት ገቡ?"... መልስ የለም...፤

*** ዩ - ዩ ***

ኢትኤል ከዮሴፍ ጋራ ወደቤት ለመሄድ ታክሲ ቢሳፈርም በመንገድ ላይ ሃሳቡን ቀየረ:: ከቀጣዩ ሳምንት ፈተና በኋላ ቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ለእረፍት መሄድን ስላቀደ ጅማ የምትገኘውን የእናቱን እህት ለመሰናበት ወሰነ:: በዚያ ላይ በቅርብ ቀን የአክስቱ ልጅ ከአውሮፓ እንደመጣች ተደውሎ ተነግሮታል፤ እሷንም መጠየቅ ነበረበት:: በተሳፈረው ታክሲ የጅማ መርካቶ ሰፈር ድረስ ሄዶ የመስመሩ መጨረሻ ላይ ወረደ::

ከመርካቶ በስተቀኝ ያለውን ዳገት ወጥቶ መንቲና ከሚገኘው የአክስቱ መኖሪያ ቅጥር ግቢ እንደደረሰ በሩን ደበደበ፤ ስለደከመው ቶሎ ገብቶ ማረፍ ፈልጎ ነበር:: የቤቱ ሰራተኛ ከፈተችለት:: አክስቱ የመጣው እሱ እንደሆነ ሲያውቁ ፊታቸው በደስታ እየፈካ መጥተው አቀፉት::

"ኢትኤል ልጄ በስንት ጊዜህ መጣኸልኝ፤" ብለውም እንደ ህጻን ልጅ ጉንጩን እያገላበጡ ሳሙት፤

"አዎ ትንሽ ት/ት ቢዚ አድርጎን እኮ…" አለ ኢትኤል በሃፍረት አንገት እየደፋ፤

"ችግር የለውም ዋናው አንተ ደህና መሆንህ… ውጤትህም ማማሩ ነው::" አለችና አቅፋ ወደ ውስጥ አስገባቸው፤ ልጇ ሰናይት ከውጭ ሃገር ድረስ ልጇን ይዛ መጥታለች:: መቼስ እህትህም አይደለች እስኪ በቅጡ ተዋወቁና ተጨዋወቱ::" አሉት ቤት እንደገቡ:: ሰናይት ከቡኒ ሶፋ ላይ ተቀምጣ የተኛውን ልጇን በስስት እያየች ነበር የጠበቀችው:: ተነስታ ሰላም ከተባባሉ በኋላ ከኢትኤል ጋር ስለትምህርት እና የውጭ ኑሮዋን ስለመሳሰሉ ጉዳዮች በወፍ በረር ተጨዋወቱ:: ከዚያም ምሳ ቀርቦ ከተመገቡ በኋላ የሠራተኛዋን ጉድጉድ ያባባሰውን ቡና መጠባበቅ ጀመሩ:: ኢትኤል ተሰናብቶ ለመውጣት እያሰበ ሳለ በሩ ተንኳኳና አንዲት ሴት ፔርሙዝ ይዛ ገባች::

"ሰላም ህሊናዬ… ግቢ … ግቢ…" አሏት የሰናይት እናት በተለመደው እናታዊ ፈገግታቸው፤

"እንዴት ናችሁ?… ሰላም ናችሁ ሰኒዬ?… ትንሽ ሙቅ ነገር እኮ ይገቴልሽ መጥቼ፤" አለችና ፔርሙዙን አጠገቧ አስቀምጣ እሷ ደግሞ ቀጣዩ ሶፋ ላይ ተቀመጠች::

ኩባያ መጣና ሙቁ ተቀዳ:: "እፍ… እፍፍ…… እፍፍፍ…"… ህሊና ለአራስ መጠገኛ ብላ ያመጣችው የአጃ ሙቅ የአራሲቱን ሰናይት እስትንፋስ አሟጦ ሊጨርስ ምንም አልቀረውም፤ ሞቅታው አለቅህ ብሎታል:: አራሷ ሰናይት

ትንፋሿን በጥቁር ከናፍሮቿ በሰራችው ከብ ቅርጽ በኩል በፍጥነት እያሾለከች የኩባያ ሙቋን ለማብረድ ትሞክራለች፣ መለስ ብላ ደግሞ ከጎኗ ወደተጋደመው ጨቅላ ህፃን በስስት ዓይን ታማትራለች:: ኢ.ትኤል እንደከብር እንግዳ እንገቱን ግራና ቀኝ እያዞረ ሁሉንም ይከታተላል:: በሰማው መሰረት የአክስቱ ልጅ ሰናይት ከፈረንሳይ ሀገር ድረስ በሀገሯ ደንብና ወግ መሰረት ለመታረስ እናቷ ቤት ከመጣችበት ቀን ጀምሮ ጎረቤትና አብሮ አደጓ ህሊና ሙቅ አዘጋጅታ ስታመጣላት ዛሬ ሦስተኛዋ እንደሆነ አውቋል::

"ወይኔ ሰኒዬ ልጅሽ እንዴት ያምራል፣ ልክ ፎቶ ላይ ያየሁት ፈረንሳዊ አባቱ አንቶኒን ነው የሚመስለው::" አለች ህሊና በአድናቆት፤

"ነው ብለሽ ነው?" መለሰች ሰኒ የገዛ ልጇን እንደ አዲስ ሰው እየተመለከተችው፤

"በትክክል በአንቶኒ ነው የወጣው፤ እንዴ! ቁልጭ እኮ እሱን ነው የሚመስለው ፤በደንብ እይው እስኪ?"... ሰኒ በደንብ ህፃኑ ላይ አፈጠጠች ፤

"አይኑ፣ የአፍንጫው ሰልካካነት፣ የፀጉሩ ሉጫነት ... " ህሊና የቻለችውን ያህል መመሳሰሎችን ዘረዘረች፤

"በይ በይ አንቺ ትንሽ ቆይተሽ ቁመናውና አረማመዱ ልትይኝ ነው፣ የፈለገ ቢሆን በዚህ እድሜው መልኩን መለየት ትንሽ እሚከብድ አይመስልሽም?" ጠየቀች ሰናይት፣ ህሊና ባሏን እንደዚህ ማደናነቋ አፍንጫዋን እያሾለው፤

"ካንቺ ስላልወጣ ቀንተሽ ነው አይደል ሰኒዬ? እንደውም ከቆንጆዬው አንቶኒ በመውጣቱ እድለኛ ነሽ"

"እና አንቺም ለምን አትወልጂለትም..." አጉረመረመች ሰናይት፤

"ምን አልሽኝ ሰኒዬ?"

"አይ እኔ ብዙም መመሳሰሉ አልታየኝም ህሊናዬ::" መለሰችላት፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሙቁ ፉት እያለችለት፤

"ኸረ ተይ፣ ሌላው ቢቀር ቅላቱ እንኳን አይታይሽም፣ እንዳንቺ ጥቁር ሆኖ ቢወለድ ምን ያህል እንደሚቆጭሽ አስበሽዋል?" አለች ህሊና ፈገግ ብላ ወደኢ.ትኤል እየዞረች፤ ደስ ይበላት ብሎ ፈገግ አለላት::

"ምን ለማለት ፈልገሽ ነው?" አለች ሰናይት፤ ስሜታዊነቷን ሲያይ ገና በቅጡ ያልበረደውን ሙቅ ህሊና ፊት ላይ የምትከልሰውም መሰለው ነበር፤ "ቆይ ልጇ እንደ እኔ ቢጠቁር ምን ከፋት አለው?"

"መቼስ ሰኒዬ ህፃን ልጅ ቀይ ሲሆን የበለጠ እንደሚያምር የሚጠፋሽ አይመስለኝም::"

"ማነው ያለው?!" ሰናይት በንዴት እየጋለች ነው፤

"እህህ… ሁሉም ሰው ነዋ!" አለች ህሊና፤ በሰናይት ስሜት መለዋወጥ ደንገጥ ብላ፤ "አይደል እንዴ ወንድሜ… ተሳሳትኩኝ?" አሁንም ማረጋገጫ ፍለጋ ወደ ኢትኤል እየዞረች፤ ኢትኤል በበኩሉ የአከስቱን ልጅ ንዴት ላለማባባስ አንድም የድጋፍ ቃል አልተነፈሰም::

ሰናይት ራሷን እንደምንም ተቆጣጥራ ሙቋን አንዴ ፉት አለች:: ኢትኤል ሁለቱ ሴቶች የሚከራከሩበትን እውነታ በዝምታ ማስላሰል ጀመረ፤ ጥቁርነትን መልከጥፉነት ያደረገው ማነው? ቀይነትንስ ውበት አድርጎ የሾመው ማነው? የአፍንጫ መሰልከክና የፀጉር ሉጫነትስ የውበት መለኪያ እንዲሆኑ ማነው የወሰነው? የምዕራባውያን ተፅዕኖ ወይስ የኛ ድክመት? ለነገሩ ከልጅነታችንም ጥቁር ኔግሮነት ከማስጠላትና ከጨለምተኝነት ጋር ሲያያዝልን አድገናል፤ በራሱ ሃሳብ ራሱ ተወጥሮ ታሰረ:: ወደ ጨቅላው ልጅ አማተረ፤ ለሽ ብሎ ተኝቷል፡ አይኑን ከሱ ሲያነሳ ህጻኑ ከተኛበት አልጋ በላይ የልጅ ልጇን እንዲጠብቅላት አከስቱ፡ የሰናይት እናት የለጠፈችው ሰምዐታዊ መንፈሳዊ ስዕል ከአይኑ ገባ፤ በስዕሉ ላይ ቅዱስነት በመልከ መልካም ፈረንጅ ወጣት፤ እርኩስነት ደግሞ በፉንጋ ጥቁር መላጣ ሰው ተወክሏል፤ ቀይ ከላይ አሸናፊ፤ ጥቁር ከታች ተረጋጭ ሆኖ ቀርቧል::

‹እውነት የገድሉ ታሪክ እንዲህ ነው ወ[illegible] ገድሉን ወደ ስዕል የቀየረው ፈረንጅ ስለሆነ ነው?› ብሎ በጥርጣሬ ራ[illegible] ጠየቀ፡ ድሮ በልጅነቱ ፅዮንን ተከትሎ ቤተ-ክርስቲያን ሲሄድ ቅዱስ-ሚካኤልን የሚያሳዩ ብዙ ዘመን ያስቆጠሩ የሚመስሉ ቅዱሳን ስዕሎችን ተመልክቷል:: ቅድስና የሚነበብበት ጠይም መልዓክ፤ ፍትሃዊነትን በሚያሳይ መልከ በአውሬ መልከ በተሳለ ዲያቢሎስ ላይ በአሸናፊነት ቆሞ የሚያሳዩ ቅዱሳን ስዕሎችን በደንብ ያስታውሳል:: ኢትኤል ባያምነውም መፅሐፍ-ቅዱስን ማንበብ ግን ይወዳል:: ጥቁርነትን ከፀለምተኝነት የሚያገናኝ ጥቅስም እስከዛሬ አግኝቶ አያውቅም፤ መልሶ ደግሞ ‹እግዜር ራሱ ብርሀንን እንጂ ጨለማን ፈጥሮ መልካምነቱን አልመሰከረም› ብሎ መጠራጠሩን መልሶ ተጠራጠረው፤ ‹አምላክ ነው ያሳነሰን ማለት ነው?› ብሎ ተስፋ ወደ መቁረጡ እያመዘነ፤ የፍጥረትን ጅማሬ በምናቡ ሲያመላልስ ድንገት ጅምሩ ታወሰው፤ ‹ግን እኮ› አለ፤ ከራሱ ጥያቄና መልስ አዙሪት ነቅቶ እየወጣ::

"ግን እኮ ከብርሀን መፈጠር ቀድሞ የነበረው የእግዜር መገኛ ጨለማ ነበር፤ ነጩ ብርሀን ዘግይቶ የመጣ ነው:: አይንን ሲጨፍኑ ባለው ጭለማ ስክነትና ጥልቅ ፀጥታ ውስጥ መሆን ታላቅ ሰላምን እንደሚቸር ከዚህ በፊት አንድ መፅሐፍ ላይ ማንበቡም ትዝ ይለዋል:: "እውነትም ጥቁርነት መታደል

ነው ለካ!" አለ በስሜት፣ ጮኾ መናገሩ ግን አልታወቀውም ነበር።… "ኢትኤል ምን አልህ?" አለች የአከስቱ ልጅ ሰናይት፣ ጓደኛዋ ህሊናም ዞራ እያየችው ነበር።

"አይ ስለጥቁርነት ትንሽ ተመራመርኩና ጥቁርነት ፀለምተኝነት እንዳልሆነ ለራሴ ስነግረው ነው የሰማችሁኝ፤" አላቸው በስሱ እየሳቀ፤

"እንዴ ታድያ ምን ጥያቄ አለው። ባሌ አንቶኒ እንኳን ፈረንጅ ሆኖ በጥቁርነት በተለይ ደግሞ በኢትዮጵያዊነት እንዴት እንደሚደነቅ ብታውቅ እኮ… እኔንም ይገርመኛል።" አለች የአከስቱ ልጅ ሰናይት፤

"የምርሽን ነው?…" አለች ህሊና በመገረም፤ "እኔ ፈረንጆች እኛን የሚያውቁን በርሃብና ችግር ብቻ ይመስለኝ ነበር።" ብላም አከለች።

"እውነትም ግን እኔም ገርሞኛል፤ ምን ይሆን ኢትዮጵያዊነትን እንዲያደንቅ ያደረገው ምክንያት፤ ወይስ ያንቺን ውብት እያየ ነው ሰኒዬ?" አለ ኢትኤል ቀበል አድርጎ፤ ሦስቱም ሳቁ።

"አይ የኔም ውበት እንዳለ ሆኖ… " አለች ሰናይት መሳቋን ሳታቋርጥ፤ "በሚገርማችሁ ሁኔታ ይሄ የራስ-ተፈሪያኒዝም የሚባለው እንቅስቃሴ ፈረንሳይን ጨምሮ በብዙ የአውሮፓ ሀገሮች በጣም ተስፋፍቷል። በዚያ ላይ ስለኢትዮጵያዊነት ያላቸው እውቀት ኢትዮጵያዊ ነኝ የምለውን እኔን ራሱ ያስደነግጠኛል። በኢትዮጵያና አፍሪካ የኦሪጅናሊቲና መንፈሳዊነት መነሻ ምድርነት አበክረው ያምናሉ።" አለች ሰናይት፤

"አዎ እኔም በቅርቡ አንድ ጀርመን ላይ የተዘጋጀ የሬጌ ኮንሰርት አይቼ የሰዉ ብዛት፣ ባለድሬድ ፀጉሩ ፈረንጅ መዓት እጅግ ነበር ያስገረመኝ።" አለ ኢትኤል በቅርቡ ከኢንተርኔት አውርዶ የተመለከተውን የሬጌ ሙዚቃ ኮንሰርት እያስታወሰ፤

"ምንድነው የምታወሩት? ይሄ የማይመስል ወሬ ሊያሳምነኝ አይችልም!" አለች ህሊና ሁለቱንም በሽሙጥ እያየች፤ "አንድ ተራ የኢትዮጵያን ንጉስ አምላክ አድርገው ስለተቀበሉ ሰዎች የምራችሁን እያወራችሁ እንዳይሆን ብቻ…" ብላም አሽካካች።

"ምን እያወሩ ነው አንቺዬ?" አሉ የኢትኤል አክስት፤ የኢትኤልና ህሊና የቡና ሲኒዎች አጠገብ የዳቦ-ቆሎ አቅርበው ከጎናቸው እየተቀመጡ፤

"አይ ስለራስ-ተፈሪያኖች እየነገርኳቸው ነበር፡፡ ያው የተሳሳቱት ነገር ሊኖር ይችላል ማሚ… ግን እውነቱን ለመናገር እንቶኒ አንድ ቀን ትልቅ የሬጌ ኮንሰርት ላይ ወስዶኝ ያየሁት ነገር እጅግ ነው ልቤን የነካው፡፡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አውሮፓውያን ስለማያውቋት ሃገሬ የቃል-ኪዳን ምድር እያሉ ባንድነት ሲዘምሩ፤ አረንጓዴ ቢጫና ቀዩ አርማችን በባዕድ ምድር ላይ ካላንዳች ጦርነት በፍቅርና ዜማ ብቻ ከፍ ብሎ ሲውለበለብ ማየት ለየት ያለስሜት ፈጥሮብኝ ነበር፡፡ ኢትዮጵያዊነት በችግር በሚጠቀስበት ዘመን የኢትዮጵያ ባንዲራ እጅግ ከፍ ብሎ ሲውለበለብ ማየት በእርግጥም ውስጤን በሃሴት ሞልቶታል፡፡ ሴቶቹ እኮ ለመጥቆር ካላቸው ፍላጎት ቆዳቸውን ‹ታን› ሲያደርጉ፤ ወንዶቹ ለስላሳ ፀጉራቸውን እንደኛ ከርዳዳ ፀጉር ድሬድ ለማድረግ የሚያዩትን መከራም ብታዩ እኮ እንዴት እንደሚያሳዝኑ…! እውነት ግን ብናስተውል ኖሮ ጥቁርነትን ከፉንጋነት መቁጠራችን ፍፁም ስህተት እንደሆነ ይገባን ነበር፡፡" አለች ሰናይት ልጇን በስስት እያየች፤

"አይ ሰኒዬ ‹ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ› ሲባል አልሰማሽም ማለት ነው፡ ለነገሩ ባትሰሚም አያስገርምም ከፈረንሳዊ ባል ተረትና ምሳሌ መጠበቅ ዘበት ነው፡፡" አሽሙሯ ጣል ያደረገችው ህሊና በድጋሚ ሳቀች፤

"ጥቁርነት አያስጠላም ማለት እኮ ቀይነት ያስጠላል ማለት አይደለም፡ ይለያያሉ ለማለት እንጂ፤ ውበት ደግሞ እንደተመልካቹ ነው!" ሰናይት በፍጥነት አፀፋውን መለሰች፡ ትንሽ ተናዳለች፤

"ይሁንልሽ እስኪ፡ ለማንኛውም ቻው፤ ቤተ ወጥ ጥጄ ነው የመጣሁት" ህሊና ተነሳች፤… "ምነው ልጄ ትንሽ አትጫወቺም?"

"አይ ልሂድ ማዘር፤" ብላ ወጣች፤ የኢትኤል አከስትም ተከትለዋት ወደውጭ ወጡ፡፡ ኢትኤል ሰናይትን እያስተዋላት ነበር፤ በዝምታ ተውጣ ሙቋን ደጋግማ ትነካካለች፤ የእጇ ሙቁ ግን አሁን የእጇ ቅዝቅዙ ሆኖ ጭስ እንኳን ማምረቱን አቁሟል፡፡ ውስጧ ግን በንዴት እየፈላ እንደነበር ፊቷ ላይ ያዳመነው የስሜታዊነት ጉም ይመሰክራል፡፡ ብዙም ሳይቆዩ ከእንቅልፉ የነቃው ክልስ ልጇ "እሪሪ…" ብሎ አለቀስ፡ የተረፈውን ሙቅ ደፋችና ልጇን አቅፋ እያባበለች ወደመኝታ ቤቷ ገባች፡፡

ኢትኤል የአከስቱ ልጅና የህሊና ክርክር ብዙ ጥያቄዎችን ፈጥሮበት አልፏል፡፡ ጠይም ነኝ ብሎ ስለሚያስብ መጥቆር የፉንጋነት መገለጫ መሆኑ ይህን ያህል የሚያሳስበው ነገር አልነበረም፡፡ ክልስ ልጅም ጥቁር ሆነ ተብሎ ፉንጋ መባሉ ግን ገርሞታል፡፡ ምንአልባትም የነጭ አረመኔያዊ ጌትነት እና የጥቁር የተናቀ ባርነት ባልነበኛት፤ በእልፍ ውድ ልጆቿ ደምና አጥንት ታፍራ

ተከብሯ በኖረች ድንግል ሀገር» ኢትዮጵያ ተወልዶ ባያድግ ደግሞ ጥቁርነት ከፉንጋንት ብቻ ሳይሆን ከባርነት ጋርም ያለው ከፉ ገፅ በገባው ነበር፡፡

"ኢትኤል ቡናህን ጠጣ እንጂ ልጄ... ጥለንህ ጠፋን አይደል?" አሉት ከውጭ አከስቴ እየገቡ፤

"ኧረ ችግር የለውም አከስቴ..." አለ እንደመቅለስለስ እያለ፤

"ባይገርምህ የጠፋው ወንድሜ ያንተ አንተ ኤልካኖ ፀጉሩን ሳይቆረጥ ረጅም ሹሩቤ አድርጎ የሚሰራ... ይሄ ሰኒዬ አሁን ያለችው... ‹ራስታ› ነው ‹ላስታ› የምትለት አይነት ነበር፡፡ የጭንቅላቱ ነገር ልከ እንዳንተ ልዩ ነበር፡፡ የታሪከና የመፅሐፍ-ቅዱስ እውቀቱ በብዙዎች የሚደነቅ ነበር፡፡ በት/ቱም ስንት ዩንበርስቲ በጣጥሶ ወይ ዶከተር ወይ ኢንጅነር ይሆናል ብለን ስንጠብቅ እርሱ ግን ጸጉሩን አንዠርግጎ ከሃገር ሃገር ሲዋትት አንድ ቀን ሳያርፍ በዚያው ወጥቶ ቀረ፡፡"... አሉ በቁጭት ነጠላቸውን እየቋጩ፤

"የት እንደሄደ አይታወቅም?" አለ ኢትኤል፤

"በጭራሽ... ያልፈለግንበት ቦታ አለ ማለት ይከብደኛል፡፡ በቅርቡ እንኳን ሰሜን አከሱም አካባቢ ታይቷል የሚል ዜና ሰምተን ታናሽ ወንድሙ በግሉ ሄዶ ቢያስፈልገውም ሊያገኘው አልቻለም፡፡" አሉና በረጅሙ ተንፍሰው፤ "መቼስ እግዛሔር በፈቀደ ቀን መገኘቱ አይቀርም፡፡ እኔ ግን ሁሌም አንተን ሳይ እርሱን ነው የማስታውሰው፤ ስምህንም እኮ እሱ ነው ያወጣልህ... በዚያ ላይ መልካችሁ ራሱ ይመሳሰላል፡፡"

"እውነትሽን ነው አከስቴ?... እኔ እኮ በልጅነቴ ካለኝ ደብዛዛ ትዝታ ባሻገር ፎቶውንም አይቼ አላውቅም፤" አለ ኢትኤል፤

"እንዴት እናትህ እስካሁን አላሳየችህም?... ቆየኝ እንዲያውም አሁን አልበሙን አምጥቼ አሳይሃለሁኝ" ብለውት ተነሱና መኝታ ቤት ገቡ፡፡ አልበሙን አመጡናም ገለጥ... ገለጥ... አድርገው አንድ ጎልማሳ ፎቶ ጋር ሲደርሱ አይናቸው እንባ እስኪያቀር ድረስ ተመለከቱት፤ ከዚያም ፎቶውን እንዲያየው ለኢትኤል አሳለፉለት፡፡ ኢትኤልም አልበሙን ተቀብሎ በልጅነት ልቡ በጭላንጭል የሚያስታውሰውን የአጎቱን ፎቶ ተመለከተ፡፡ አይኑን አላመነውም፤ የሠራ አካላቱ በሙሉ በድንጋጤ ተሞላ፡፡ ወድያውኑ አከስቱን ይቅርታ ጠይቆ ሰናይትን እንኳን ቻዎ ሳይል በችኮላ ከቤቱ ወጣ፡፡ በፍጥነት ከጅማ መርካቶ ወደ ሆስፒታል የሚሄድ ታከሲ ተሳፈረ፡፡ ያየውን ነገር ለማመሳከር ጓጓቷል፡፡

*** ፉ – ፉ ***

# ምዕራፍ ፮ - ሣህ … ራህ … ውሃ… !

… (ቁራኒ - ወሎ፤)

ከአስፓልት ይልቅ ጥርጊያ ኮሮኮንች መንገዶች፤ ከረጃጅም ፎቆች ይልቅ የተመዘዙ፣ የተንሰራፉ፣ በርካታ ቅርንጫፎችን ያቀፉ ዋርካና ባህር ዛፎች፤ ከመኪኖች ይልቅ ወጠምሻ ፈረሶች፤ በሰውና በእንስሳት ሀይል የሚገፉ ጋሪዎች የሚበዙባት የገጠር ወረዳ ነች:: ኗሪዋም ቢሆን በየለቱ ከተፈጥሮ ጋር እያበረና እየታገለ፣ ተመሳሳይ የሚባል የድግግሞሽ ህይወትን ዓመት ከዓመት የሚያሳልፍ ነው፤ አዲስና መጤ፣ ቢድዓ ነገር አይወድም::

በመንደሩ ውስጥ ለአቅመ-አደም ደርሰው በወጉ ትዳር ከመሰረቱ አባ-ወራዎች መካከል አከረም አንዱ ነው:: አከረም በአባቶቹ ታሪክ ምክንያት በመንደሩ የሚከበር አባወራ ነው:: በዚህ ማህብረሰብ ዘንድ መከበሪያ ከሆኑ ነገሮች መካከል የጦርነት ላይ ጀግንነት አንዱና ዋነኛው ነው:: የአከረም አባት ሃጂ መሐመድና አያቱ ሼህ ዳውድ የሰፈሩ አድባር የነበሩ፤ ባለፉት ነገስታት ዘመን የጠላት ወራሪ በመጣ ጊዜ የእናት ሀገር ጥሪን በወኔ ተቀብለው እየዘመቱ ጀብድ የሰሩ ጀግኖች ነበሩ:: ይህም ከራሳቸው አልፎ ለአከረም ጥሩ ስም አኑረው እንዲያልፉ አድርጓቸዋል:: አከረምም ቢሆን እስካሁን ሃገር አቀፍ ጦርነት ላይ ተሳትፎ ባያውቅም የበቃ ፈረስ ጋላቢና አዳኝ መሆኑን ብዙ ጊዜ አስመስክሯል::

አከረም በስራው ዘርፍም ቢሆን ጎበዝ ገበሬና ለአንድ አባወራ በቂ የሚባሉ ከብቶች ባለፀጋ ነው:: ገና በአፍላ እድሜው ካገባት ባለቤቱ ወርቅነሽ አንድ ወንድና ሦስት ሴት ልጆችን ማፍራት ችሏል:: ሀሰን የቤቱ አንጋፋ ልጅ ሲሆን ገና ከለጋነቱ እርሻና ጉልጓሎን ስላስተማረው አሁን በደንብ የሚያግዘው ታዳጊ ጎረምሳ ሆኗል:: የመጨረሻ ልጁ የሆነችው የአምስት ዓመት እንቦሳዋ ራህማ ገና ዘላ ያጠገበች ሚጢጢ ነች:: ቦጨቅ ቦጨቅ ያለች አረንጓዴ ቀሚሷን እያውለበለበች ካላንዳች ጭንቀት፣ ስፈው የሰፈሩ ሜዳ ላይ ስትቦርቅ ነው የምትውለው...

በዚህ በነአከረም መንደር ሌላ እንግዳ ሰው ቀርቶ የመንደሩ ነባር ኗሪ እንኳን በደንብ የማያውቋቸው አንድ ሼህ ከድር የሚባሉ ሽማግሌ ሰውም አሉ:: መንደርተኛው በዓመት ውስጥ የሚያያቸው በጣት ለሚቆጠሩ ጊዜያት ነው:: በረጃጅም ዛፎች በታጠረው ጫካ ተከበው፣ ዱር ቤቴ ብለው፣ ከሰው መንጋ ተገንጥለው ይኖራሉ::... የአካባቢው ሰው ስለርሳቸው ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡ አፈ-ታሪኮችን ሲሰማ አድጓል:: አያት ለአባት ፣ አባት ደግሞ ለልጅ እያስተላለፈ በልጅነት እንደሚነገሩት የአባባ ገብረ-ሃና ተረቶች ሁሉ የሰፈሩ አዛውንቶች የሼህ ከድርን ታሪክና ገድሎች ለልጅ ልጆቻቸው ስላስተላለፉ ስለ ማንነታቸው በጥቂቱም ቢሆን የማያውቅ ሰው አልነበረም:: እርሳቸውም ቢሆኑ የታሪኮቹን እውነትነት አሁንም ለማረጋገጥ ይመስል፣ እንደ መስቀል ወፍ ብቅ እያሉ አስገራሚ ነገሮችን እያደረጉ ከሰው አይን መሰወራቸውም አልቀረም:: ...ጊዜው ከአንድ ዓመት በፊት ነበር፣ ወቅቱ የበልግ ወራት ነው፣ አዝመራው እጅግ ሰምሯል፣ አካባቢው በአረንጓዴ የተፈጥሮ እፅዋት አጅብ ብሏል፣ ትንሿ የአከረም ልጅ ራህማ ጢባ-ጢቤ መስሪያ ሰፋፊ ቅጠል ፍለጋ ከጨፌ ትገባለች፣ ገና በፍለጋዋ እንደተሰማራች በአረንጓዴ ሳር ከተጋረደው ረግረጋማ ስፍራ የተኛ እባብ ትረግጣለች:: ተስፈንጥሮ እግሯን ይነድፋታል:: የእባቡ መርዝ አደገኛ ከሚባሉት ነበርና ራህማ ወዲያውኑ ራሷን ስታ መድከም ትጀምራለች:: የልጅቱ እግር ላይ የነበረው የመነደፍ ምልክት ጊዜ ሳይሰጥ እየሰፋና እየጠለቀ ሄዶ የሚዘገንን ቁስል ይሆናል፣ እሷም ድክምክም ትላለች::

አባቷ አከረም ከቤቱ ጣሪያ ጋር ተያይዞ ከተሰራው ደጃፉ ላይ በባለ 3 እግር ዱካው ላይ አረፍ ብሎ ተቀምጦ ነበር:: ከራህማ ጋር ሲጫወቱ የነበሩ ልጆች እየበረሩ መጥተው በእባብ መነደፏን የነገሩት:: በድንጋጤ ዘሎ ከወንበሩ ተነሳና በብርሃን ፍጥነት ወደ ቦታው ከነፈ:: ከስፍራው ደርሶም ወደ ጨፌው ከመዝለቁ ልጁ ተዝለፍልፋ መሬቱ ላይ መዘርጋቷን ተመለከተ፣ ህይወቷ ከፍተኛ የሆነ አደጋ ላይ መውደቁ ታወቀው::

በድንጋጤ የስሜት ማዕበል ውስጥ እየዋለለ ፈጠን ብሎ ይዟት ወደ ፈረሱ አመራ፤ ኮርቻው ላይ አሳረፋት፤ ከኋላም አቅፎ እየጋለበ በቅርብ ወደሚገኘው ጤና ጣብያ ገሰገሰ:: የፈረሱ አቅም የሚፈቅደውን ያህል እየነደለው፤ በፍጥነት እየጋለበ ቢሄድም የራህማ ጤና ግን ከፈረሱ ኮቴዎች እየቀደመ ማሽቆልቆሉን ተያይዞታል:: ስሟን እየጠራ ድምፁን ቢያሰማት፤ ቢዳብሳት፤ ምላሽ ከማግኘት ፈንታ ያለ ልክ አቅሟ እየደከመበት ሲመጣ ፍርሃት ገባው፤ ሆዱን ባር ባር አለው::

ድንጋጤና ስጋት እየተማቱበት ፈረሱን አቆመና ራህማን አቅፎ አወረዳት:: ከመንገዱ ጎን ከሚገኝ ዋርካ ስርም አሳረፋት:: ራህማ ከእጁ ላይ ዝልፍልፍ ብላ ብትወድቅ፤ ቆፍጣና ልቡ በሀዘን ቋፍ ተጠምቆ ተልፈሰፈሰ:: መሬቱ ላይ ድፍት ብሎ በምሬት ካነባ በኋላ ወደ ሰማይ አንጋጦ... "የአላህ! ያረቢ! እባከህን ይህቺን ነፍስ ያላወቀች አንድ ፍሬ ልጅ ታደግልኝ:: ያ ኢላሂ! ይህ ፈተና ከኔ እንዲያልፍ እጠይቅሃለሁኝ:: ለብቻዬ አትተውኝ! የባሪያህን ጭንቀት አትመለከትምን?" ሲል በምሬት ጮኸ፡ ወድያው ግን ከየት እንደመጣ ያልለየው አንድ ድምፅ፤

“ተው ያሸባብ፤ በሺህ መሰላል የማትወጣው ሃጢያት ውስጥ ራስህን አትከተት፤ አትሳሳት! የኛ አል-ረህማን እንኳን ራህማን ማንንም አይተውም!" ሲል መለሰለት:: አከረም ደንገጥ ብሎ ድምፁ ከወዴት እንደመጣ ለማወቅ አካባቢውን በተደጋጋሚ ቢቃኝ አንዳች ውል የሚል ነገር ማየት ተሳነው:: ነገር ግን ጀርባውን አጥንቶ ወደ ልጁ ዞር ሲል ከልጁ አጠገብ አንድ ትልቅ ሽማግሌ ሰው ቆመው ተመለከተ:: ነጭ ጀለብያ ለብሰዋል፤ አናታቸው ላይ ቀይና ነጭ ኢማማ ጠምጥመዋል፤ በቀኝ እጃቸው የ ‹Y› ቅርፁን ባላ፡ የቆሌ ከዘራ ተደግፈዋል፤ በግራ እጃቸው የሚቆጥሩትን ሙስብሃና ቅዱስ ቁርዓን ይዘዋል::... "ልጅህ ራህማ ምን ሆና ነው?" አሉት በመርማሪ አይን አተኩረው እያዩት፤

"ስሟን እንዴት አወቁ?" አለ አከረም ግራ እየተጋባ፤

“ኢብሸር ወንድሜ! እኛ ያ በኒ አደሞች (የአዳም ልጆች) የማያስጨንቅ ነገር እያስጨነቀን እድሜያችንን ማሳጠራችን ያሳዝናል፡ ይልቅ አሁን የልጅህ ነፍስ ከሆነ የሚያስጨንቅህ የሆነውን ነገር ንገረኝ::" አሉት፡ ንግግራቸው የስሜታዊ ሰው ቢምስልም ፊታቸው ላይ የሚነበበው ግን የሚያረጋጋ ስከነትና ደስ የሚል ፈገግታ ብቻ ነበር::

"እ...እባብ....... እባብ ነድፏት ነው::" አለ አከረም ድጋሚ እየተርበተበተ፤

እርሳቸውም ሙስብሃቸውን ከአንገታቸው አጥልቀው በርከከ አሉና የራህማን እግር አነሱ:: ትንሽ ካስተዋሉ በኋላ በሹከሹከታ ድምፅ ዱአ አደረጉበት፣ ኋላም የተነደፈችበትን ቦታ ጭምቅ አድርገው መግል መሳይ ነገር ከእግሯ እንዲወጣ አደረጉ:: ከዚያም ብድግ አሉና ከዛፉ አስር እርምጃ ያህል ርቆ የሚገኝ ቁጥቋጦ ውስጥ አንዲት ቅጠል ነጥለው አወጡ፣ ምራቃቸውን እንትፍ ብለው በመዳፎቻቸው መሀል ከፈተጉት በኋላ የራህማ ቁስል ላይ አደረጉት፣ አከረም አይኑ እያየ የራህማ እግር ወደ ቀድሞው ጤናማ ገፅታው ተመለሰ፣ መገረሙን ያስተዋሉት ሼህ ከድር ፈገግ አሉና፤..
"እንግዲህ ምን እንላለን? ነፋስ ከየት እንደመጣ ወዴት እንደሚያመራ ባናውቅም፣ መልኩን ማየት ቢሳነንም በነፋስ ሀይል እና ግፊት ውዲህና ውዲያ የሚያንገዋልሉትን፣ እሚውለበለቡትን ቅጠሎች ማስተዋል ግን ከቶ አይሳነንምና፣ የጀሊሉ ፈጣሪ ስራም በዚህ ይመሰላል::" ... ወድያውም ራህማ ነቃችና "ጋሼዋ" ብላ አባቷ ላይ ተጠመጠመች:: አከረም በክንዱ ደገፍ አድርጎ ካነሳት ኋላ እስከትረጋጋ ድረስ ጉያው ስር እቅፍ አደረጋት::

"አልሃምዱሊላህ፤ እርሶንም አመሰግናለሁኝ ያ ወልዩላህ፤ እንግዲህ ከምስጋና ውጪ ምን እንደምከፍሎት አላውቅም::" አለ አከረም እንዳጎነበሰ::

"አትደነቅ አንተ ሰው፤ ኸይርን የማድረግ ነገር ልብህ ‹ሃይ› ካለስ ይህ ዛሬ ያየኸውን ነገር ሄደህ ከባለቤትህ በቀር ለሰፈሩ ኑዋሪዎች እንዳትናገር:: ነገር ግን እኔን ማግኘት የሚፈልጉ ወጣቶች ወደ መንደሩ በመጡ ጊዜ አንተ ወደ እኔ ምራቸው፤" አሉት::

"እሺ ግን ማንነቶን እኮ አልነገሩኝም?... እኔስ ያሉበትን ሳላውቅ እንዴት ነው ወደ እርሶ የምመራቸው?" ጠየቀ አከረም እንዳጎነበሰ፤

"ሼህ ከድር በላቸው፤ እንዲህም ይሆናል፣ እነርሱ በመጡ ቀን ማግስት ማለዳ ከደጃፍህ ካለው ዛፍ የተቀመጠች ግመልም ወደ እኔ ትመራችኋለች፤" መለሱለት፤ ከዚያም ዝምታ ተተካ...

አከረም አላመነም፤ በግርምትና ግርታ ተሞልቶ የእኚህን ባለብዙ ታሪክ ሰው ፊት ለማየት ቀና አለ:: እርሳቸው ግን በቦታው አልነበሩም:: ያን ቀን ቤቱ ተመልሶ የተከሰተውን ነገር ለሚስቱ ነገራትና ለሌላ ሰው ግን እንዳትናገር አስጠነቀቃት:: ወጣቶች ሲመጡ ላክ ያሉት ነገር ግን ትርጉም ስላልገባው ዝምታን መረጠ:: መልዕክታቸው ላይገባው ይችላል፤ የማይክደው እውነታ ግን ያንን እለት ታላቁን የወሎ ወልይ ሼህ ከድር በአካል ማግኘቱ ነው::

*** ፶ - ፶ ***

የእኒያ ከሆስፒታል ሲወጡ አስቀመው ያዋሯቸው ባህታዊ ነገር በነኢትኤል ላይ ትልቅ ጥያቄ ፈጥሯል:: እንቆቅልሹን ያጠበቀባቸው ደግሞ በአካባቢው ለብዙ ቀናት ሲያስተምሩ የነበሩት ባህታዊ ለእነርሱ መልዕክታቸውን ካስተላለፉ በኋላ ዳግም ላይታዩ መጥፋታቸው ነው::

አብርሃም ከሌሎቹ ተማሪዎች ለየት ባለ ባህታዊው ስለመርየም መጠየቃቸው ትልቅ ጥያቄን ፈጥሮበታል:: አንዴ በጥሩ አንዴ በመጥፎ መንገድ እየተረጎመው ከራሱ ጋር መሟገት ስራው ሆኗል:: መርየም ስትናፍቀው ክስተቱን በጊዜያዊነት ይረሳውና ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ባህታዊው ሰው ወደ ምናቡ ገብተው ያስጨንቁታል::

ዛሬም ከመርየም ጋር ተቀጣጥሮ ቁጭ ባለበት በየመሃሉ ስለ ባህታዊው እያሰበ ነበር:: ብዙም ሳታረፍድ የደረሰችው መርየም ሳያያት ከኋላው መጥታ ጉንጩን ሳመችው፤ ፈገግ ብሎ በቀኝ እጁ ግራ ጉንጯን ከቀኝ ጉንጩ አጣብቆ አቀፋት፤ ተነፋፍቀው ነበር… አንዴ ደግማ ጉንጩን ሳመችውና ከጎኑ ወንበር ስባ ተቀመጠች::

"ደህና ነሽ ሜሩዬ?…" አላት ከሃሳቡ እየነቃ፤

"ደህና ነኝ አልሃምዱሊላህ፤… ግን ምን ሆነኸ ነው እንዲህ የተከዝከው? ከሩቅ ጀምሬ እያየሁህ ነበር፤" አለች ሂጃቧን እያስተካከለች፤

"ያው ናፍቀሽኝ ይሆናላ::"

"መናፈቅማ እኔም ናፍቀኸኛል ወላሂ… ግን ተው አትዋሸኝ… የቅድሙ ትካዜ የናፍቆት ብቻ አይመስለኝም!"

"አንቺን ልዋሽሽ አልችልም… አንድ ነገር እያሳሰበኝ ነበር፤" አለ ጠረጴዛውን በጣቱ እየደበደበ፤…

"ምን አብርሽ?"

"ከሰሞኑ አንድ ባህታዊ እኔና ጓደኞቼን አጋጥመውን ነበር::" አላት፤

"ባህታዊ ማለት እንደ መነኩሴ ናቸው?"

"እዎ እና አምስት ሆነን ነበር ያገኘናቸውና በሚገርምሽ ሁኔታ ግን እኔን ለየት ባለ መልኩ ‹መርየም እንዴት ናት?› ብለው ጠየቁኝ!"

"ወላሂ በል?" አለች መርየም በግርምት፤

"ወላሂ…" መለሰ አብርሃም እየሳቀ፤ መርየምም ፈገግ አለችና አከላም

"የምር ግን ስሜን ከየት አውቀውት ነው?"

"አላውቅም… እኔን ግን ከዚያ በላይ ያስጨነቀኝ ንግግራቸው ከኋላ ሌላ መልዕክት ይኖረው ይሆን ብዬ ነው::"

"ምን አይነት መልዕክት?" ጠየቀችው፤

"ማ… ማለቴ…" ለመመለስ አቅማማ፤

"ንገረኝ አብርሽ አትፍራ፤"

"ማ… ማለቴ እኔ ክርስቲያን ነኝ አንቺ ደግሞ ሙስሊም እና ይሄ ነገር ሃጥያት እንደሆነ በቅኔ ተናግረውኝ የሄዱም እየመሰለኝ ትንሽ እየተጨነቅኩኝ ነው::" አላት አቀርቅሮ፤

መርየም በዝምታ ቆየችና አይን አይኑን በስስት እያየች ማውራት ጀመረች::… "አትጨነቅ አብርሽዬ፤ እርግጠኛ ነኝ እርሳቸው ስለእኔ የጠየቁህ በ‹ኔጌቲቭ› ቢሆን ኖሮ ስለስራህ ይኮንኑህ እና ይቆጡህ ነበር:: እርሳቸው ግን ‹መርየም ደህና ናት ወይ?› ብለው እንደጠየቁህ ነው የነገርከኝ:: ላታምነኝ ትችላለህ ግን ሰሞኑን እኔ ራሱ እንዲህ ያሉ ሃሳቦች ውስጤን ውጥር አድርገው ይዘውት ነበር:: እናም ቁርዓን ስቀራ ነበር… እና…" ቃላቶቿን አላስጨረሳትም፤

"እንዴ እንዲያውም አስታወስሽኝ፤ ሱረቱል-መርየምን በትርጉም አነባለሁኝ ብለሽኝ አልነበር?" አለ አብርሃም፤

"ውይ አንተ ደግሞ ምን አስቸኮለኽ? እኔም እኮ ስለዚያው ልነግርህ ነበር::" አለችና ቀጠለች… "እናም እንዳነበብኩት መርየም ወይም ድንግል ማርያም ማለት ብቸኛዋ በቁርዓን የተጠቀሰች፤ በጣም ፃዲቅና የተለየች ሴት ናት:: ቀጥሎም መልዓኩ ጅብሪል ወይም ገብርኤል በድንግልናዋ ፀንሳ በድንግልና እንደምትወልድ ያበስራታል::" አለችው፤

"ልክ እንደኛ ማለት ነው፤ እኔ ግን የምልሽ ለምንድነው እናንተ ሙስሊሞች ለመልዓክትና ነብያት ከእኛ ለየት ያለ ስም የምታወጡት?…

ማለቴ ገብርኤልን ጅብሪል፣ ሰለሞንን ሱለይማን ወዘተ የምትሉት?" አለ አብርሃም ፈገግ እያለ፤

"እንዴ ሌላ ስምማ አውጥተን እኮ አይደለም:: ያው እንደምታውቀው ለነብዩ መሐመድ ‹ሰለል-ዓለይሂ ወሰለም› (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የወረደላቸው ቅዱስ-ቁርዓን በአረብኛ ቋንቋ ነው:: በአረብኛ ቋንቋ ውስጥ ደግሞ በአማርኛ ውስጥ ያሉት የኀምስና የሳብዕ እናባቢዎች ስለሌሉ ነው፣ ማለት ‹ሄና ሆ፣ ሴና ሶ፣ ሜና ሞ...› ምናምን የሉም:: ስለእዚህ እናንተ ኤሎሄ ስትሉ እኛ ‹ኤ›ን ወደ ‹አ›፣ ‹ሎ› ወደ ‹ላ›፣ ‹ሄ› ደግሞ ወደ ‹ሀ› ቀይረን አላህ እንላለን:: በተመሳሳይ መንገድም እናንተ ሰለሞን ስትሉ እኛ ‹ሱ› ለይ ‹ማ›ን እንላለን፣ ገብርኤል ስትሉ የገ ፊደላትም በአረብኛ ስለሌሉ ወደ ‹ጂም› ቀይረን ጅብሪል እንላለን... ሙሴ ስትሉ ሙሳ እንላለን:: እንጂ የምንጠራቸው ነብያትም ሆኑ መልዓከት የተለዩ ሆነው ወይም ስማቸው ተቀይሮ አይደለም::" አለችው፤

"የእውነት ሜሩ ‹ታንክ ዩ›፤ ባይገርምሽ የዶርማችን ልጅ ዘይኔ ሲያወራ ሁሌም ግራ የሚያጋባኝን ነገር ነው መልስ የሰጠሽኝ፣ እንደዚያ ከሆነ እኮ አንድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ገብርኤል ወይም ሚካኤል ብሎ በአማርኛ መጥራት ይችላል ማለት ነው አይደል?" አለ አብርሃም በጥያቄ መልክ መርየምን እያየት፤

"አዎ ምንም ችግር የለውም:: እንዲያውም እነዚህን መልዓከት ማወቅና ማመን እስልምና ግዴታ አድርጓል::" አለች መርየም፣

"ለምን ግን ይህ እውቀት ከእኛ ክርስቲያኖችም ይሁን ሙስሊሞች ተደብቆ እርስ በርስ በፍቅር መኖር እንዳንችል እንደተደረገ አይገባኝም::... ለማንኛውም እስኪ ሌላ ስለጌታችን መድሐኒታችን ክርስቶስ የምታምኑትን ንገሪኝ እስኪ?" አላት ከቡን የመስታወት ጠረጴዛ ደገፍ ብሎ እያያት::

"እና እሷ ‹ወንድ ያልነካኝ ድንግል ሆኜ እንዴት አረግዛለሁኝ? › ብላ ስትጠይቅ፤ መልዓኩም የአላህ ወይም ኤሎሄ ቃል ይሁን ካለው እንደሚሆን ይነግራታል:: እርሱም መሲሒ እንደሚሆን፣ ሌሎች ምዕራፎችም ላይ ደግሞ በመንፈስ-ቅዱስም እንደሚታገዝ*፣ በዚያም ላይ ብዙ ህግጋትን

ሊያፀና የተወሰኑትንም ሊቀይር እንደወረደ ይናገራል:: በዚያ ላይ ሳይሞት በህያውነት እንዳረገና ደጃል ወይም 666ን ሰይጣንን ገድሎ ምድርን በፍትህና በእምነት መንገድ ሊመራ ተመልሶ እንደሚመጣ ይናገራል:: ("5:110)" አለችና ወደኋላዋ ወንበሯን ደገፍ ብላ ተቀመጠች:: ብዙ ስላወራች ደከሟት ነበር:: በልቧ አብርሃም እነዚህን እውነታዎች ሲያውቅ ወደ እስልምና ሃይማኖት ሊመጣ ይችላል የሚል ምኞት አድሮባታል:: እሱ ሙስሊም ሆነ ማለት ካለችግር ቤተሰብ ፈቅዶ መጋባት ይችላሉ፤ ጭንቀቷም በሙሉ ይፈታል ማለት ነው::

"እውነት ደስ ይላል፤ ቋንቋችንም አንድ ቢሆንማ ሃይማኖታችንም እጅግ ነበር የሚመሳሰለው፤" አለና አከሎም "ቆይ እኔና አንቺ ሁሌም ስለሃይማኖት ብቻ ነው እንዴ የምናወራው? ኧረ ወሬ እንቀይር::" አላት ፈገግ ብሎ::

መርየምም በራሷ የሞኝ ሃሳብ ራሷን እየታዘበች ወደ ሌላ ጭውውት ገባች:: ብዙ እየሳቁ ሲያወሩ ሳያስቡት ሰዓቱ ገስግሶ ኖሮ የመለያያ ሰዓታቸው ደረሰ::

ትኩስ ፍቅር ላይ ያለችው መርየም ከአብርሃም ጋር መለያየት ሞት ነው ሚሆንባት:: ሲጀመርም ከብዙ ቀናት ናፍቆት በኋላ የሙስሊም ጓደኞቿ ሐዩኝ አላዩኝ እያለች በድብቅ ስለምታገኘው መለያየቱ በጣም ይከብዳታል:: የመሄጃያቸው ሰዓት ሲደርስ አብራው ሆና ነው ማዘን የምትጀምረው፤ ገና አብረው ቁጭ ብለው በፍቅራቸው ግለት ውስጥ ያለውን እስትንፋስ በቅጡ ሳያወጉት፤ እንደሚለያዩ እያሰበች ትተክዛለች።

ናፍቆቱ በአብርሃምም ዘንድ አለ:: ግን ከራሱ ይልቅ የእሷ ሃዘን ይበረታበታል:: ልብ ብሎ ሲያያት፤ ታሳዝነዋለች!... የሆነ... ከሆዱ ውስጥ ትልቅ የፍቅር ቪላ ቤት ገንብቶ ዋጥ ቢያደርጋትና በሄደበት ሁሉ እንደ እርጉዝ ሴት ተሸክሟት ቢዞር ይመኛል። የአይኑ ናፍቆት በበረታ ቁጥር አምጦ እየወለዳት አይኗን በስስት ቢያያት ... የአይኑ ናፍቆት በረድ ሲልለትም ደግሞ ወደ መኖሪያዋ ዋጥ የሚያደርጋት የሆነች... ኪኒኒ ነገር... ሚጢቆ... ሚጢጢዩ ህፃን ብትሆንለትም ይመኛል።

ምኞት አይከለከል ሰፊ ነው፤ እውነታ እንጂ ካለው ውጪ የሌለበት የተገደበ፤ ምንም አቅም ስለሌለው... አይችለው እዳ ሆኖበት... ባይዋጥለትም...እንዲቷን፣ ቆንጆዬዋን፣ የፍቅር ቀንዲሉ መርየምን በልቡ ብቻ ይዞ በአካል ይለያታል:: .

..የዘንድሮ ኑሮ ከዛሬው ሙቀት ወጥተው ተጨማሪ ማገዶ ካልከተቱባት በቀር ነገን በብርድ ልታቆረፍደን እንደምትችል ምድጃ ናትና ለኑሮ ውጣ ውረዱ፤ ከት/ት ቀጥሎ ለሚጠብቃቸው ፈተናቸው ማጥናት ስላለባቸው ሁለቱ ይለያያሉ፤ ሁለቱንም ይከፋቸዋል… የሷ ግን በጣም ይለያል… እቅፍ አድርጓት… ውሽቅ ብላበት… ከመደሰት ይልቅ ትጨነቃለች! ምናልባትም ለሃዘኗ ናፍቆቷን ያገዘው ሌላ ምክንያት ሊኖራት ይችላል፡፡

… አብርሃም ጊዜው ገስግሶ የሚለያዩባትን ደቂቃ እያሰበች ፊቷ እንደነሐሴ ሰማይ ነሓሳማ ቀለም ለብሶ ከፍት ሲላት አያት።… "ማር ልትሄድብኝ ነው?"… አለች መርየም በለሆሳስ፤

"የኔ እናት አለሁኝ… " ቢላትም… አጥብቆ ቢያቅፋትም አትረጋጋም፡፡

"ቢሆንም መሄድህ አይቀርም እኮ አብርሽዬ…" እያለች ትቆዝማለች… አብርሃም የሚላትን ነገር ያጣል፡፡

እርግጥ ነው ልቡ ያውቀዋል… መሄዳቸው አይቀርም… መለያየታቸው አይቀርም… ግና ዳግም መገናኘታቸውም አይቀርም፤

የናፍቆትና ፍቅር ድግግሞሹ የሚጣፍጥ ስቃይ ነውና… እንደመራብና መጥገብ! 1000,000 ጊዜ እየሞቱ… ዳግም 1000,000 ጊዜ እንደመነሳት… ይቀጥላል…

***

*We are no other than a moving row*
*Of Magic Shadow-shapes that come and go,*
*Round with the Sun-illumined Lantern held*
*In Midnight by the Master of the Show;*

✍ *(Omar Kayam)*

*** ዶ – ዶ ***

ፕ/ር እሴና ፍሬድሪካ ጥዋት ከደህንነቱ ቢሮ እንደወጡ ላዳ ታክሲ ተሳፍረው ቀጥታ ያመሩት ወደ ግዮን ሆቴል ነበር፡፡ ከረጅም ጉዞ በኋላ በተቀበላቸው ያልተጠበቀ ነገር ምክንያት በቅጡ እንቅልፍ አላገኙም ነበር፡፡ እንግዳ ተቀባዩ ሴት ክፍላቸውን እንዳሳየቻቸው ሻወር ለመውሰድ እንኳን አቅም አጥተው አልጋቸው ላይ ተዘርረው ነበር የተኙት፡፡ ለስምንት ሰዓታት ያህል ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ውስጥ ከቆዩ በኋላ ነበር እንዳዲስ ታድሰው፣ ‹ሪፍሬሽ› አድርገውም የተነሱት፡፡ በጋራ ሻወር ወሰዱ፤ ልብስ ቀያይረውም ምሳ አዘዙና ከፍላቸው ድረስ አስመጥተው ተመገቡ፡፡ በእንቅልፍና መብሉ አቅማቸው መለስ ሲል የታወቃቸው ፕ/ር እሴ የሚወዷትን ከተማ ውበት ለማየት ወጣ አሉ፡፡

ፕ/ር እሴ ኢትዮጵያ ደርሰው ከተመለሱ በኋላ ባለፉት ጥቂት አመታት ውስጥ አዲስ አበባ ላይ የተወሰኑ ለውጦች እንደተደረጉ አስተውለዋል፡፡ ባቡሮች ሸከተፍ ሸከተፍ እያሉ በራሪ፣ ተሳቢና ሰርጓጅ ዘንዶዎች መስለው ይምዘዘጋሉ፤ ማራኪ ማራኪ ረጃጅም ህንፃዎች በየቦታው በቅለዋል፤ እጅግ ግዙፎቹ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ባንክ ቤቶች ዋና ቢሮ ሆነው የተሰሩት ናቸው፡፡ በአስፓልቱም መለስተኛ ቪላ ማስገንባት የሚያስችል ዋጋ የወጣባቸውን መኪኖች ጨምሮ የተሽከርካሪው ቁጥር በመጠኑ መጨመሩን አስተዋሉ፡፡

*"So what is your next plan? Are we leaving to Axum tomorrow or...? (አሁን ታድያ ቀጣይ እቅድህ ምንድነው?... ማለቴ ወደ አክሱም ነገ ነው የምንሄደው ወይስ...?)" ጠየቀች ፍሬድሪካ እየተጓዙ ሳለ፤*

*"Not actually. (አይ አንሄድም፤)"*

*"Why? (ለምን?)"*

*"I have to see a colleague in Addis Ababa University and then we will probably leave next week. (አንድ የማገኘው አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሚሰራ ወዳጄ አለ፡፡ እሱን ካገኘሁት በኋላ ቀጣይ ሳምንት ላይ እንሄዳለን፡፡)"*

*"... Or you can give me the key and I will go and fix things by myself till you arrive there (ወይ ደግሞ የሚስጥሩን ቁልፍ ስጠኝና እኔ ቀድሜህ ሄጄ ነገሮችን አስተካክዬ እስክትመጣ እዚያው ልጠብቅህ፡፡)*

"No (አይሆንም)" አሉ ፕ/ር ቆፍጠን ብለው፤

"Why? (ለምን?)" ፍሬድሪካ ግራ የተጋባች ትመስላለች፤

"We should go together. (አብረን ነው አክሱም መሄድ ያለብን፡፡)"

"Don't you believe me? (ምነው አታምኚኝም እንዴ?)" አለች እንደ መቆጣት እያለች፤

"*Off-course I believe you, still we must go together.* (በደንብ ነው እንጂ የማምንሽ ቢሆንም ግን አብረን መሄድ ነው ያለብን፤)

ፍሬድሪካ እንዳኮረፈ ሰው እየተነጫነጨች ከእርሳቸው ቀደም ብላ መራመድ ጀመረች:: ብሔራዊ አካባቢ ሲደርሱ ፈጠን ፈጠን ብለው ተራመዱና እጇን ያዟት:: ኩስትር እንዳለች ዞር ብላ አየቻቸው፤

"I am sorry fredi... I will make it up to you. (ይቅርታ ፍሬዲ፣ ደግሞ ላስቀየምኩሽ እክስሻለሁኝ::" አሏት በመለማመጥ አይኖቿን እያዩ፤

"*How?* (እንዴት ነው የምትክሰኝ?)" አለች ወደሳቸው ዞራ እየቆመች፤

"Why don't we sit for a drink and I will tell you... (ለምን ካንድ ካፌ ነገር ተቀምጠን አላወራሽም?)" አሉና፤ እጇን ይዘው ወደ አንድ ከጡብና ፕላስቲክ የተሰራ ከሚመስል ካፌ ገቡ::

"*Listen to me my dear, I promise I will give you the secret soon but first I do really have to talk to my friend... it is very important that I do so!* (ስሚኝ የኔ ውድ፤ የሚስጥሩን መፍቻ ቁልፍ በቅርቡ እንደምሰጥሽ ላረጋግጥልሽ እወዳለሁኝ፤ ግን ከዚያ በፊት የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ወዳጄን ማግኘቴ እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ተረጂኝ::)" አሏት በአፅንኦት፤ ባይዋጥላትም ተቀበለችው:: እዚያው አብረው ቁጭ ባሉበትም የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የታሪክ ክፍል ምሁር የሆኑት ፕ/ር ዳግማዊ ጋር ደውለው ለረጅም ሰዓት አወሩ... ስልኩን ሲዘጉት፤ "So what did he say? (እና ምን አለኸ?)" አለች ፍሬድሪካ፣ በፅሞና የስልክ ንግግራቸውን ስትከታተል ቆይታ፤

"We will see him the day after tomorrow. (ከነገ ወዲያ እናገኛቸዋለን::)" መለሱላት፤ እሷ ግን ሃሳቧ ሁሉ ያለው እከሱም ያለው ድብቅ ሃብት ጋር ነው... መታገስ የምትችል አትመስልም::

*** ፉ – ፉ ***

*"ጥል ክርክርን ታስነሳለች፤ ፍቅር ግን ኃጢያትን ሁሉ ትከድናለች፡፡" (ምሳ፤ 10፡12)*

*** ቶ – ቶ ***

የፈተናቸው ቀን ዋዜማ እንደመሆኑ ሁሉም በታላቅ ጭንቀት ተውጠዋል፡፡ በተለይ ኢትኤል "የነገው ፈተና ላይ ዶ/ር እሳቱ ያገኙኝ ይሆን ወይ?" እያለ ተጨንቋል፡፡ ከዚህ በፊት ያነበበውን ነገር መከለስ እንኳን ከብዶት ይወዛገባል፡፡

አብርሃም ዝም ብሎ ያስተውለዋል፡፡ በበኩሉ የመርየም ናፍቆት እና የዚያ ባህታዊ እንቆቅልሽ ትዝ እያለው ንባቡ እየተረበሸበት ነው፡፡ ለነገሩ ነገ ፈተና ሆኖ አለማንበብ አስፈርቶት እንጂ በዚህ ሁኔታ የሚያነበው ት/ት ለነገ ፈተናው አንዳችም እንደማይጠቅመው ልቡ ያውቀዋል፡፡ ናዖድ ለነገ ፈተና የሚለብሰውን ነጭ ሸሚዝና የጨርቅ ሱሪ እያጠበ ነበር፡፡ ዘይኔ በበኩሉ ከባድ ራስ ምታት አሞት ከአልጋው ተጋድሟል፡፡ ከሰው ፊት ቆሞ የመናገር ፍርሃት ያለበት ዘይኔ ከድሮ ጀምሮ የቃል ፈተና ዋዜማ ቀን የራስ ምታት ሰላሙን ይነሳዋል፡፡ አንብቦ ያላዳረሰው ክፍል የበዛበት ዮሴፍ ‹ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ›ን እያስመሰከረ ነው፡፡

"ኢታ ምነው ሰላም አይደለህም እንዴ?" አለ አብርሃም ወደ ኢትኤል በጥያቄ አይን እየተመለከተ፤

"ኧረ ደህና ነኝ... ብቻ ነገ ፈታኝ ሆኖ ዶ/ር እሳቱ እንዳይደርሰኝ ልቤ ሰግቷል፤" አለ ኢትኤል አንገቱን እንደደፋ፤

"ባክህ አትፍራ እግዚአብሔር ያለው ነው የሚሆነው!" አለ አብርሃም በአበረታች መንፈስ፤

"አዎ ወላሂ አትፍራ! እኔም ዱዓ አደርግልሃለሁኝ፡፡" አለ ዘይኔ ቀበል አድርጎ፤
"ቲሽ ያንተ ዱዓማ ቢቀርብን ነው የሚሻለው!" አለ ዮሴፍ በሹፈት፤
"ዘይኑ ተወው... ጆሲን አትስማው... ‹ታንክ ዩ› ግን..." አለ ኢትኤል ለጥቆ፤
"በነገራችን ላይ ስለ ፀሎት ስታወሩ የዚያ ያስቆሙን አባት ነገር አልገረማችሁም?" አለ ናዖድ፣ አረፋውን ከመዘፍዘፊያ ወደ መዘፍዘፊያ እያገለባበጠ፤

"ባህታዊውን ሰው ማለትህ ነው አይደል?… አዎ እኔም ዝም ብዬ ሳስባቸው ነበር፡፡" አለ አብርሃም ቀበል አድርጎ፤

"አዎ ወላሂ… ግን አብርሃም… ምን አይነት ሰዎች ናቸው ባህታዊዎች በአላህ?" አለ ዘይኔ የማወቅ ጉጉት እየተነበበበት፤

"በእርግጥ ያው አስመሳዮቹም እንዳሉ ሆነው እወነተኛ ባህታዊዎች ግን ስለእግዚአብሔር ህግጋትና ወንጌል ብለው ዓለምን የናቁ መናኞች ናቸው፡፡ ሃብት ንብረታቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እርግፍ አድርገው ከዱር በረሃው የሚኖሩ የእምነት ሰዎች ናቸው፡፡ እንደዚህ አይነት ሰዎችን ለመረዳት ራስህን በእነርሱ ቦታ ላይ አድርገህ ማሰብ ይጠበቅብሃል፡፡ እኛ ሆዳችንን የሚሞላ ነገር በልተን፣ ከምቹ ሞቃታማ አልጋችን ውስጥ ገብተን እንተኛለን፡፡ ቤተ-ክርስቲያን ወይም እንደ ዘይኔ ከሆነ ደግሞ መስጅድ ማለዳ ተነስተን ለመሄድ እንቅልፍ ጥሎን እንቀራለን፡፡ እንደነዚህ አይነት ሰዎች ግን በፆመኛ ሆድ አልያም የረባ ነገር ባልቀመሱበት ሆዳቸው፣ ምቹ አልጋ ላይ ሳይሆን ከሚቆረቁር ጠፈር፣ አልያም ከሳር ጉዝጓዝ፣ ወይም ከዛፍ ጥላ ስር በቀን ውስጥ ለጥቂት ሰዓታት ጋደም ብለው ሌሊቱን በሙሉ ሲፀልዩና ሲቀድሱ ያድራሉ፡፡ በሳምንት አንድ ወይ ሁለት ቀን ሳይሆን የእለት ተእለት ስራቸው አምልኮና ምስጋና፣ ዝማሬና ልመና የሆነ፡፡ ለዝና፣ ለጥቅም አልያም ለይስሙላ ሳይሆን ለእውነት ሲሉ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ብርቱዎች ናቸው፡፡" ብሎ የቃላት ዳንቴሉን የጨረሰው አብርሃም በረጅሙ ተነፈሰ፤ ሁሉም የዶርሙ አባላት ገርሟቸው እየሰሙት ነበር፡፡

"በእየሱስ ስም፤ ኧረ አብርሽ! እንደዚህ ሲሪየስ ሆነህ ስታወራ አይቼህ አላውቅም፤… ጌታን፡፡" አለ ናዖድ እየተገረመ፤

"እኔም ወላሂ ገርሞኛል፤ ወይ ደግሞ ሁሌም በሃይማኖት ጉዳይ ስለምንከራከር ከልባችን ስለማናዳምጥህ ይሆናል፡፡"

"እውነትም ለዚያ ይሆናል ዘይኔ፡፡" አለ አብርሃም በሃሳቡ እየተስማማ "ከመከራከር የልብ መድረቅ እንጂ ምንም ቅድስና አይገኝም፡፡ ባይገርምህ ከመርየም ጋር ስለእስልምና አውርቼ ስንት ነገሮች እንዳወቅኩኝ ብነግርህ አታምነኝም፡፡" አለ አብርሃም፤

"እስኪ ስለምን እንዳወቅክ ንገረኝ?" አለ ዘይኔ ፈገግ ብሎ፣

"ብዙ ነገር ነው የነገረችኝ ብቻ ግን እስልምና እና ክርስትና እጅግ የተቆራኙ ሃይማኖቶች እንደሆኑ ተረድቻለሁኝ:: በዓለም ላይ ለክርስትና ከየትኛውም ሃይማኖት በላይ የሚቀርበው እስልምና እንደሆነ አውቂያለሁኝ:: ድሮ የእስራኤልና ፍልስጤምን ፀብ በዜና ምናምን ሳይ ለእስራኤል ነበር ደግፌ የምመለከተው:: በግፍ የህፃናትና ሴቶችን ደም እያፈሰሰች እያየሁኝ እንኳን አይሁዶችን መቃወም አይሆንልኝም፡ ‹‹እስራኤል›› ስለተባለች ብቻ የክርስቲያን መንግስትም ትመስለኝ ነበር:: ነገር ግን አመራር ላይ ያሉትን ጨምሮ አብዛኛው እስራኤላዊ አይሁዳዊ ሲሆን እየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መምጣቱን የማይቀበሉ ብሎም ድንግል ማርያም ከጋብቻ ውጪ የወለደችው ነው እያሉ ጌታችን መድሐኒታችን እየሱስ ክርስቶስን በአጠያፊ ስም የሚጠሩ መሆናቸውን በቅርቡ ነው ያወቅኹት::" አለ ዘይኔን በአንክሮ እያየው፤

ኢትኤል የሚሰማው ነገር ማርኮታል፤ "ዛሬ የምታወሩት ነገር ደስ ይላል:: እንደኔ እንደኔ ሃይማኖቶች በሙሉ ‹‹በበጎ ነገር በርቱ ከከፉ ስራ ራቁ›› ብለው እንደሚያስተምሩ አምናለሁኝ:: ያው በግሌ ስለ አምላክ መኖር ጥርጣሬ ቢኖርብኝም የእውነት የምነግራችሁ የእናንተ ህይወት ግን ያስቀናኛል::" አለ በመሃል ጣልቃ ገብቶ፤

"ምንድነው ነገ ፈተና ሆኖ እናንተ ስለሃይማኖት የምታወሩት?" አለ ዮሴፍ በፌዝ ቃና፤

"ባይሆን አንተ ጌታን የምትቀበልበት ቀን ነው የሚናፍቀኝ?" አለ ናዖድ በአጸፋው ወደ ዮሴፍ ዞሮ፤ ልብስ አጠባውን ጨርሶ ከአልጋው እየተቀመጠ፤

"አቦ አትጨቅጭቀኝ ለራሴ መርቅኚያለሁኝ፤ ላጥናበት!... <<እግዚአብሔርን እናውቃለን››፣ <<ሼኪ ነኝ››፣ ‹‹ጌታን ተቀብለናል›› ጺሪሪም ጺሪሪም የሚሉት የት ደረሱና ነው እኔን ተቀበል የምትለኝ? ለስሙ ‹ኢትዮጵያ የሃይማኖተኛ ሀገር ነች፤› ይባላል ግን ርሃብተኛ፣ ችግረኛና በሽተኛ የሞላባት ሃገር ናት፤ እግዚአብሔር እውነት ካለ ለምን አይረዳትም? ደግሞስ አማኝ ተብዬው አይደል እንዴ ዘረኛ፣ ሐሜተኛ፣ ምቀኛ፣ መሰሪና ተንኮለኛ::" አለ ዮሴፍ በምሬት፤

ክርክር ውስጥ ለመግባት የፈለገ ስለሌለ መልስ የሰጠው አልነበረም:: ሁሉም ተራ በተራ ወደ ንባባቸው ተመለሱ:: ኢትኤልም ነገ ዶ/ር እሳቱ ሊፈትነኝ ይችላል የሚለው ፍርሃት ጋር እየታገለ የቻለውን ያህል አጠና:: ጭንቀቱ አላስተኛ ብሎት ትንሽ ቢያታግለውም 8 ሰዓት በላይ አልቆየም:: ሌሊት 9:00 ሰዓት ላይ ሁሉም የዶርሙ አባላት ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወስጥ ነበሩ፤...

*** ቶ – ቶ ***

*"አባይ የምድር ዓለም ሲሳይ*
*የቅድመ ጠቢባን አዋይ፥*
*አባይ የጥቁር ዘር ብስራት*
*የኢትዮጵያ ደም የኩሽ እናት፥*
*የዓለም ሥልጣኔ ምስማክ*
*ከጣና በር እስከ ካርናክ*
*በጡትሽ እቅፍ እንዲላክ*
*ለ‹ራሀ› ለፀሐዩ ግማድ ፥ ለ‹ጣሀ› ለከዋከብት እምላክ*
*ከጥንቱ ፍጡራን ጮራ ፥ የመነጨሽ ከኩሽ አብራክ::"*

( ሓ ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን)

*** ቶ – ቶ ***

…3500 ዓመታት በፊት፤

ከኢትዮጵያ ማህፀን፣ ከግዙፍ ተራሮቿ የፈለቀው የግዮን ወንዝ በግርማ ሞገስ ረጅሙን ጉዞውን ‹ሀ› ብሎ ይጀምራል:: በኃለ ሃይል የሚገፋው ቀዝቃዛ ውሃ ብዙ ሺህ ኪ.ሜ ፈሶ የኩሽ ምድርን ያቋርጣል:: ንጉስ አከናሁስ ረጅሙን ጠመዝማዛ የውሃ መስመር እያዩ ተመስጠዋል፤ እርግጥም ማለቂያ ያለው አይመስልም:: ለረጅም ጊዜ ያዩትና ያደነቁት የጥቁር ግብፅ የስልጣኔው ማማ ቢሆንም ዛሬ ግን ሁሉንም እንዳዲስ ነበር የሚያዩት፤ የንግስናቸው የመጨረሻ ቀን ነበርና::

ከታላቅ ተራራ፤ ኢትኤል፣ ቶላ፣ አብርሃም፣ ዘይኔ፣ ናዖድና አንድ ሌላ ሰው ጎን ለጎን ቆመዋል:: ንጉስ አከናሆስ ጠይም ፊት ያላቸው፤ በእንቁ ያቆጠቆጡ አልባሳት ለብሰው፣ በወርቅ የተለበጠ ጫማ ያጠለቁ፣ ሾጣጣ የሚባል አክሊል የደፉ ባለነጭ ፂምና ሹሩቤ ንጉስ ናቸው:: አብረቅራቂ የ ‹ቶ› ምልክትን በእጃቸው እንዳንጠለጠሉ፤ በ2 ግዙፍ ከቡር ዘቦቹ ታጅበው ወደነርሱ ሲመጡ ግርማቸው ቢከብዳቸው እነኢትኤል ጎንበስ አሉ::

*"ተነሱ! ተነሱ!" አሉ ከፊት ለፊታቸው እየቆሙ፤*

*"ቀና በሉና የዛዮንን ወንዝ ተመልከቱት እስኪ?" አሉ ወደ አባይ ዞረው፤*

*"የዛዮን ወንዝ ምንድነው?" አሉ እነኢትኤል በአንድ ድምፅ፤*

"እ! እናንተ የምትጠሩት አባይ ብላችሁ ነውና፣ ምንጩ ግን ከላይ... ከላይ ከዛዮን ነው፣ ከዛይ ከሳባይ ሰማይ መውጫ ወ-ፀሐይ፣ ከላይ ከ‹ሃይ› ከበላይ... ከአባይ፣ ከላይ ከግዮን፣ ከላይ ከ‹ላዮን›፣ ከላይ ከራማ ከተማ፣ ከደብረ-ፅዮን ተራራ ነው ምንጩ፤ ግና በእናንተ ዘመን አላዋቂዎች ዘንድ የንጉስ ዛዮን ርስት የሆነው ግዮን ‹‹አባይ› የተባለው ሃገሩን ከዶ ስለሚሄድ ነው›› የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ታራምዳላችሁ:: ዳሩ ግን ግዮን ሃገሩን አልካደም... ግዮን ሐገሬ ብሎ የሚያውቃት ይህ የምታዩትን ሰፊ የኩሽ ምድር ነበር:: ከጣና ሐይቅና ከታንጋኒካ ጀምሮ በእናንተ ዘመን ሜድትራኒያን ብላችሁ በቀየራችሁት የኤርትራ ባህር አልፎ መካከለኛው ምስራቅ ድረስ ያለውን ሰፊ ግዛት ነበርና! አባይስ የተባለው አብይ ወይም ዋና የኤደን ወንዝ ስለነበርም ነው:: ከዋናው፣ ጠና ካለው የጣና ሀይቅ ተንፈላሶ የሚፈስ ዋና-ተኛ ዋና ወንዝ፣ አባይ!... እዩት እስኪ አያምርም፤" አሉ ንጉስ አከናሆስ በአፅንኦት፤

"ያምራል ጃንሆይ፤" ሁሉም በአንድ ድምፅ መለሱ፤

"ውሃን አይነት ልፍስፍስና በራሱ መቆም የማይችል ነገር እንዴት ያንን ሁሉ ሜዳ አረሰርሶ፣ ድንጋይ አርጥቦ፣ በረሃ አጠጥቶ ሲጓዝ አለመድከሙን ላስተዋለው ተዓምር ነው:: እርግጥም እንደዚህ የምታዩትን የመሰለ ውበት ያለው ወንዝ መሰረቱ አንድ ነውና ስሙኝ ::" አሏቸው በአስገምጋሚ ድምፅ፤

"እንሰማለን ያስተምሩን፤" አሉም በአንድነት፤

*** ቶ – ቶ ***

*"የሰው አፍ ቃል የጠለቀ ውሃ ነው ፥ የጥበብም ምንጭ ፈሳሽ ወንዝ ነው::" (ምሳ፤ 18፡4)*

*** ቶ – ቶ ***

"የፍጥረት በሙሉ ዋና ግብዓትና ህልውና፣ ከ4ቱ 3 እጅ ውሃ ነው:: ውሃ እናንተ ሃይድሮጅንና ኦክስጅን ብላችሁ በተማራችኋቸው ሁለት ዋና ዋና ንጥረ-ነገሮች የተገነባ ውህድ ነው:: ውህድ ማለት ደግሞ የቁስ-አካል መደባለቅ ብቻ ሳይሆን ጥልቅና ረቂቅ መስተጋብር ነው:: እናም ይህ የሁለቱ ንጥረ-ነገሮች በአሳታዊ ፖዘቲቭና ኔጌቲቭ አከናፋት የመፋቀር ሃይል ይጣፋና፣ ከሌላም የማይፈልጉ ሁለት ንዑሶች ማለትም ወደ ‹O› ና ‹O› ፣ ከዚያም ወደ ድምር (**ወ**) ይቀየራሉ፤ የፍጠረት በሙሉ ጅማሮ ‹ሀ› ሆነውም፤ በአንድነት የፈጠሩት ማንነት ‹**ውሀ**› ተብሎ ይጠራል::

ስለዚህም የእነዚህ ሁለት ንጥረ-ነገሮች መፋቀር የምታዩትን ረጅም ወንዝ ጉዞ ያስቀጥላል፤ ማራኪ፣ ‹ፏ› የሚያረግ ሐሴትን የሚሰጡ ፏፏቴዎችን ያንዠረግጋል፣ የዝናብን ጠብታ አጣብቆ ይዞ ከሰማይ እስከ ምድር ያጓጉዛል፤... ያለበለዚያማ የዝናብ ጠብታ አየር ላይ በንፋስ ተበታትኖ እንደሚጠፋ አመድ በሆነ ነበር:: ታድያ ይህ ነው የውሃ ሚስጥር ፣የህያውነት የህይወት ምንጭ ያደረገው፣ ያህዋ ፍጥረት! ተዋህዶው ነው አንድነት::"

"አንድነትና ውህደት ይህ ከሆነ ተቃራኒውስ ምንድነው?" ... በጋራ ጠየቁ

"ማወቅ ትፈልጋላችሁን?"

"አዎ!" ብለው በአንድ ድምፅ ከመመለሳቸው፤ ከፊታቸው ከየት መጡ ያልተባሉ እልፍ አዕላፍ ከወገብ በላይ ራቁታቸውን ያሉ፣ በአብዛኛው ቀይና ነጭ የቆዳ ቀለም ያላቸው የጉልበት ሰራተኞች ፈሰሱ:: ግማሾቹ በረጅም ሰልፍ በሰርጥ በሰርጥ ተሰድረው፤ ወፋፍራም ገመድ ይዘው ግዙፍ አለቶችን ይጎትታሉ:: የተወሰኑት ደግሞ ረጃጅም አለንጋዎችን እንደያዙ ከፈረሶች ላይ ተሰይመው ይከታተሏቸዋል:: የደከመና የለገመን ሾጥ እያደረጉ ይቀጣሉ:: ሌሎች ባሮችም የንጉስና ንግስቲቱን እንዲሁም መሳፍንትና የቤተ-ጣዖታት አገልጋይ ካህናትን በትከሻቸው በተሸከሙት ዙፋን ላይ ተጠግርረው ይጓዛሉ:: እነርሱ ልክ እንደ አራት የመኪና ጎማ ሆነው የተሸከሙት የጋሪ ወንበር ላይ የተቀመጡት ሹማምንት ደግሞ በምቾት ወይን እየጠጡና ፍራፍሬዎችን እያጣጣሙ ይንፈላሰሳሉ::

እዚህ ግድም ያለው የግዮን ወንዝም ይህን ትዕይንት ታዝቦታል፣ በገፁም አንፀባርቆታል:: በባርነት አቅማቸው እስኪሟጠጥ በሚሰሩ ሰዎች ላብ ወዘና ቀለሙ ጠቁሯል፣ በረጃጅም አለንጋዎች ግርፊያ የባሪያዎቹ ጀርባቸው ላይ እንደወጣ ጠባሳ ውበቱ ተጨማዷል:: ከማዕበሉ የሚነሳ ሞገድ በስፍራው ያለውን የግፍና ለመኖር የሚደረግን ትግል ያዘለ አየር ያናፍሳል::

"የእነዚህ ምስኪን ሰራተኞች ላብ ከቁብም የማይገባ ሲሆን፣ ዋጋ የማያገኙበት ልፋታቸውም እንደ ከንቱ ይቆጠራል:: ፒራሚዶችን በሰው ልጆች አቅም መገንባት የቀልድ ስራ እንዳይመስላችሁ::" አሉ ንጉስ አከናሁስ እጆቻቸውን ወደባሪያዎቹ ዘርግተው፤ ሁሉም በመስማማት አንገታቸውን ነቀነቁ፤

"ይህን አንድ ፒራሚድ ለመጨረስ ብዙ አስርተ ዓመታትን ፈጅቷል፤ ብዙ ሺዎችም ለዚህ ዓላማ ሲሉ ተሰውተዋል፤ እስካሁንም ግን አልተጨረሰም::" አሉ ንጉሱ በትካዜ፤

"ይቅርታ ያድርጉልኝ ጃንሆይ፣ አንድ ፒራሚድ ለመስራት ይህን ያህል ከባድ ከሆነ እነዚያ ሁሉ ታላላቅ ፒራሚዶች እንዴት ተገነቡ?" አለ ኢትኤል ራቅ

ብለው ወደሚገኙ ከእነዚህኛው ፒራሚድ በውበትም በግዝፈትም ወደ ሚበልጡ ፒራሚዶች በጣቱ እየጠቆመ፤...ካለምንም የጊዜ ልዩነት አምስቱም ራሳቸውን በግዙፍ ፈረሶች ላይ ተቀምጠው ከአንድ የሚገነባ ታላቅ ፒራሚድ ስር አገኙት። ወዲያውም ሰማይ ተከፈተ፤ ንፋሳት የተሸከሟቸው አለቶች፣ ከበላይ ትላልቅ የፒራሚድ መስሪያ ድንጋዮች ሲወርዱ አዩ፤ መንኮራኩሮችም የሚመስሉ አካላት ካላንዳች ችግር ሲንሳፈፉ፣ እየወረዱም እየተሰካኩ ፒራምዱ ሲገነባ ተመለከቱ።

ያኔ ለኩሽ ምድር ዘመኑ የፅድቅና ዕውቀት ጊዜ ነበር። ለምለም፣ ወርቅማና ደም መሳይ ቀለሞች ጎልተው ከወጡበት የቀስተ-ደመና ሰፊፍ ስር ፀጋ፣ እምነትና ፅናት የሚዘንብበት ማለፊያ ወቅት ነበር። ከቀስተ-ደመናው ዙሪያ ደግሞ አሁን መጤዎቹ ‹ሲ.አይ.ኤ›ና ‹ሞሳድ› እንደ አርማ የሚጠቀሙበት ንስር አሞራ ክንፎቹን ዘርግቶ ይበራል። መነሻ ምሳሌው ግን ባለአክናፋት መልዓክትን ሰማይ ወለድ ፀጋ አመልካች ሲሆን፤ የዣ-ንስር ዐሞራ፣ ከምድር ብዙ ጫማ ርቀት ከደመና ከፍ ብሎ እየበረረ መሬት ላይ ያሉትን ጥቃቅን የምድር ህይወት ነገሮች እየነጠለ አጥርቶ፣ አንጥሮ... አነጣጥሮ ማየት ይችላል። ‹ዣ›ን-አሞራ የተባለውም ፊደሉ ‹ዣ› ራሱ ሁለት ክንፎቹን ዘርግቶ አንድ እግሩን እንደዘረጋ ንስር ይመስላል። እንደዚሁም የያኔ ነገስታት በአምላክ ፍቃድ አግኝተው፣ ተቀብተው በመንፈሳዊ አክናፋት ታላቅ ዙፋን ላይ ቢቀመጡም ታች ድረስ እየወረዱ ‹በፍትህ እጃቸው› የተራ ተብዬውን ህዝብ ብሶት ያዳምጡና መቀጣት ያለበትንም እየነጠሉ ይፈርዱበት፣ ‹ዧ› ብሎ የሚፈስ በረከት ከላይ ተቀብለው ያፈሱ እንደነበር ያሳያል።

"ያኔማ! እነዚህ ግዙፍ ድንጋዮች በአምላክ ፍቃድ ከንፋሳት ይጓዙ ነበር፤" አሉ ንጉሱ፤ ሁሉንም በሃዘን አይን እያዩ፤ "ያኔማ! እኛም አምላክን አላስቀየምንም፤ በራሳችንም አልታበይንም ነበር። እያችሁ ልጆቼ እኛ የሰው ልጆች ትንሽ ሃይልን አምላክ በቸረን ቁጥር በራሳችን መኩራራት እንጀምራለን። በገነባናቸው ረጃጅም የፒራሚድ ሃውልቶቻችን እየተመካን ያስገነባንን አምላክ ግን እንረሳለን። አይነ ልቦናችን ተዘግቶብን የፒራሚዱ ጫፍ ላይ ደርሰን ፕሮ ለመሆን እንኳትናለን። ነገር ግን ህይወትና እውነት አንድ ከበላይ ደርሰን የምንቆምበት ጫፍ ያለው ፒራሚድ አይደለም። ህይወት በተስፋ እየኖሩ በየቀኑ የሚፈቷት እንቆቅልሽ እንጂ ተፅፋ ያለቀች ድርሰትም አይደለችም። በምንሄድበት ጉዞ በሙሉ አመስጋኝና ተብቃቂ ካልሆንን በስተቀር በስጋ የማይገኝ የከፍታ ጫፍን ስናሳድድ ለዘላለም እናሽልባለን። ተኝተን ራሳችንን የማናውቅ ደካሞች ሆነን ሳለ ንጉስ ነን እያልን የተቀመጥንበት የዙፋን ወንበር ጊዚያው ቁስ እንደሆነ እንረሳለን።"

አሉ ንጉስ አክናሁስ፣ ሁሉንም አንድ ባንድ እየተመለከቱ፤ "የሰማነው በቅጡ እንዲገባን ትንሽ ቢብራራልን ጃን..ሆይ?" አሉ ሁሉም በአንድ ድምጽ፤

"ይኻውላችሁ... ይህ አሁን ያላችሁበት ትዕይንት ህልም እንዳይመስላችሁ:: ፈጣሪ በገለጠልን የጊዜ ቀመር አደራደር፡ የስነ-አዕምሮና ደቂቀ መሰውረ ጥበብ ተጠቅመን ወደፊት ለሚመጣው ትውልድ ያስቀመጥነው የትውስታ ጥቅል ቢሆን እንጂ:: ምክንያቱም በዚህ አካሄዳችን ከቀጠልን ከአምላካችን ቁጣ የተነሳ ከጠፊዎቹ እንደምንሆን አውቀነዋል:: በተለይ አሁን እኔ ከወረድኩኝ በኋላ የሚመጡት ተተኪ መሪዎቻችን በራስ ወዳድነትና በራስ ገነንነት መዘፈቅ ስናስተውልና የቀደምት አባታችንን ካህን ሄኖክ ትንቢት ስንመረምር የኛ ስልጣኔ ከጠፊዎቹ እንደሆነ አውቀነዋል:: ይህም የሆነበት ምክንያት የስልጣኔያችን መሰረት የነበረውን አምላክ ከደን፡ ውህደታችንን ‹ፉ› ተዋህዶ ዘንግተን፤ የአንድነትና የፍቅርን ኪዳን አፍርሰን በስሜታዊነትና በጉልበት መግዛት ስለጀመርን ነው:: ፒራሚዶቻችን የሀይል ምንጭና የመንፈሳዊነት ተመስጥኦ ማዕከል ከመሆን ይልቅ ስንሞት መቀበሪያና የጉራችን ማሚያ የድንጋይ ቤቶች ሆኑ:: አምላክ በለገሰን ጥበብና ስልጣን የገዛናቸው ህዝቦች በፀጋዎቻችን እጅጉኑ ተደንቀው እኛን እንደ አማልክቶቻቸው ቆጥረው በሰገዱልን ጊዜ ኩራት በልባችን ተዘራች፡ ያቺ ኩራትም ከትውልድ ትውልድ አልፋ ልጆቻችንን ፈረዖንነት ተጠናወታቸው:: አገዛዛችንም ከሰላምና ፍትህ ባሪያዎቻችንን ወደ መበደልና ግፍ ተቀየረ:: በአንድ አምላክ ስር ሁሉንም ዜጎች በህብረት ያላቀፈ አገዛዝ ደግሞ መውደቁ አይቀርም::" አሉና ለሰላሳ ሰኮንዶች ያህል ፒራሚዱን ሸቅብ በጥሞና ሲያዩ ቆዩ፤ በየትኛውም አቅጣጫ ፀሐይ ብትወጣበት ጥላ እንዳይኖረው ተደርጎ በልኬት የተሰራ እፁብ ድንቅ የኪነ-ህንፃ ጥበብ ፈሶበታል::...መልዕክታቸውን ቀጠሉ ንጉስ አክናሁስ...

. "የፒራሚድ አንዱ ባንዱ ላይ የመደራረብ አገዛዝ ስርዓት እንደማይሰራ እወቁት:: ምክንያቱም ገና ከጅምሩም የፍጥረት ስርዓቱ ሉል መሳይ እንጂ ፒራሚድ አልነበረም:: ምድር የተፈጠረችው እንደ እንቁላል አይነት ክብ ሆና ነበር:: የሉል ቅርጽ በዚህች እልፍ ህዋ ውስጥ እጅግ የተረጋጋ ቅርጽ ሆኖ እናገኘዋለን:: ለዚህም ይመስላል በ‹ራህ› ፍጥረት ውስጥ... ዐለማትን መገኛ ጋላክሲ፣ የብርሃንና ሙቀታችን ምንጭ ፀሐይንና ሌሎችን ከዋክብትን፡ የሰውነታችን ትናንሾቹ የህይወት ክፍሎቹ ሴሎችን፡ ነፍስ የሌላቸው የቁስ-አካላቶችን የገነባው ትንሹ ብሎኬት አቶምም የሉል ቅርፅ ያለው፡ ከእርሱ የሚያንሱትና ያኔ የኩሽ ምድርም ስልጣኔ ስንጠቀም እንደንጉሳችን ኤሌክትራ ኤሌክትሮ ብለን የጠራነው የሃይል ፍሰት መለያ ጎቶንም የሉል ቅርፅ ነው::

ምክንያቱም ሁሉም ፍጥረታትና ሃይላት ከአንዱ ወደ አንዱ መንከባለል፣ መተላለፍ፣ መጋራት እና መሽከርከር እንዲቻላቸው ነበር፡፡ እንጂ በተቃራኒው በመቋጠር፣ በመቀማትና በማጋበስ የተገነባ የ3 ማዕዘኖች ጥርቅም ፒራሚድን ተፈጥሮ አታውቀውም፡፡ አንበሳ ሚዳቆን አባሮ ይበላል፣ አንበሳው ሞቶ በስብሶ ቅጠላቅጠል ጋር ተዋህዶ ሲበቅል ደግሞ ሌላ ሚዳቆ ትበላዋለች፣ አሽከርከሪቱ ይኸው ነው... ቀጣይ ነው..."

"እናማ ልጆቼ!" አሉ ፊታቸው ላይ ጭንቀትና ሃዘን እየተነበበ፤ "እናማ ልጆቼ ብዙሃኑን ከስር ተሸካሚ ጥቂቱን ከላይ ተጠቃሚ አድርገን የገነባነው ፒራሚድ መቃብራችን መሆኑን አትጠራጠሩ፡፡ የተሻለች ኢትዮጵያን ከፈለጋችሁም ሁሉን ያካተተች፣ በአንድ እግዚአብሔር ስር የተዋሃደች ሀገርን መመስረት ይገባችኋል፡፡ የሃይማኖት፣ ብሔርና ፖለቲካዊ ቁርሻችሁን ትታችሁ ወደ ተከባበረ አንድነት መምጣት አለባችሁ፡፡ ይሕ እናንተ ያላችሁበት ዘመን ዳግም ይህን ጥበብ የሚጠይቅ ዘመን ነውና፡፡ የምድር አውታራት ላይ ሳጥናኤላዊ ፒራሚዶች እየተገነቡ እንደሆነ እወቁ፤ ከ‹**ራ**› ተራራ የቅዱስ ንዑዳንን ሰማያዊ ግብረ-ሃይል አሰልፉ፤ ለማይቀርላችሁ ውጊያ ንቁና ተዘጋጁ፡፡ እንግዲህ እናንተ ስድስታችሁም ብዙሃኑን ስለምትወክሉ ተመርጣችኋል፡፡ ለተቀረው የዘመናችሁ ትውልድ መልእክቱን እንድታስተላልፉ በተስፋ እንልካችኋለን፣ ሰባተኛዋ ጋርም ትገናኛላችሁ፡፡

በሉ ሂዱና ሦስት ሰዎችን አግኙ፤ ከመጀመሪያው ሰው 3 ታሪኮችን ትሰማላችሁ፤ ሁለተኛው ሰው 3 ገለፃዎችን ይነግራችኋል፤ ሦስተኛው ሰው ዘንድ ስትሄዱ ደግሞ 3 ማረጋገጫዎችን ይሰጣችኋል፡፡ እንግዲህ የመጀመሪያው የምትሄዱበት ሰው ጋር **ትዕግስትን** ታጥቃችሁ ሂዱ፤ ሁለተኛው ሰው ጋር **ማስተዋል**ን ይዛችሁ ተጓዙ፤ ሦስተኛው ሰው ጋር ደግሞ በ**ፍቅር** ድረሱ፤ ጥበቡንም ለትውልድ አስተጋቡ፡፡" አሉና መሬቱን በያዙት በትር አንዴ መቱት፤ ቀጠሉም "በቅድሚያ በእኛ የኩሽ ቋንቋ ‹**ወል**› ወይም አንድነት ብለን ወደሰይምናት ወደ ወሎ ታቀናላችሁ፡፡ ቁራኒ ከሚባል ቦታ አከረም የተባለ ሰው ጋርም ታርፋላችሁ፡፡ እርሱም ሼህ ከድርን እንዲያገናኛችሁ ጠይቁት... ስታገኟቸውም ሦስት ታሪኮችን ትሰማላችሁ፡፡"፤ ብለው ንጉስ አክናሁስ ጀርባቸውን ሰጥተዋቸው ጉዞ ጀመሩ፡፡

"እንዴ ጃንሆይ የተቀሩት ሁለቱ ሰዎችስ የት እናገኛቸዋለን?" ሁሉም ጠየቁ፤

"ለሁሉም ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ አለው፡፡" አሉ ንጉስ አክናሁስ ሳይዞሩ፤

ወድያውም ከየት መጣ ያልተባለ ሃይለኛ የአሸዋ ቧይት ንፋስ እነኢትኤልን ከበባቸው፤ ሽቅብ አጎናቸው... ስድስቱም እየጮኹ ከእንቅልፋቸው ነቁ፡፡

…ሁሉም ከው ብለው ነበር ከእንቅልፋቸው የተነሱት፣ ከሌሊቱ 9 ሰዓት ከሩብ ላይ:: እንቆቅልሽ፣ ግርምት፣ ድንጋጤና ግራ መጋባት የተምታታባቸው አምስት ፊቶች እርስ በእርስ ተያዩ::

ቃላት ባይለዋወጡም ሁሉም ስለቀሰቀሳቸው ህልም ግን ሳያወሩ ተግባብተዋል:: "በስመ አብ ወ ወልድ ወ መንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ!" አለ አብርሃም እያማተበ፤

"በእየሱስ ስም ምን አይነት ህልም ነው?" ናዖድም ተቀበለው፤

"ኢና ሊላሂ ወኢና ኢላሂ ራጂኡን… በህይወቴ እንዲህ የእውነት የሚመስል ህልም አይቼ አላውቅም ወላሂ!" አለ ዘይኔም በጥያቄ አይን ሁሉንም እየተመለከተ፤…"በጣም የሚገርምህ አሁን ተነስቼ እንኳን ህልም መሆኑን ማመን ከብዶኛል::" አለ ቶላ ቀበል አድርጎ፤

"እኮ ሁላችሁም የፒራሚዱ ንጉስ ያለበትን ተመሳሳይ ህልም አይተናል ነው የምትሉኝ?" አለ ኢትኤል በመደነቅ ሁሉንም እየተመለከተ፣

"አዎ".. "አዎ".. "አዎ".. አሉ ሁሉም በመቀባበል፣ ቀጥሎም ስላዩት ህልም አንድ ባንድ እያወሩ በተመሳሳይነቱ እጅግ ተገረሙ::

"እኔ የምለው በህልማችን ውስጥ የነበሩት ንጉስ ስድስታችሁ ተመርጣችኋል ነበር ያሉት፤ እኛ ደግሞ አምስት ነን ስለዚህ ስድስተኛው ማነው?" አለ ዘይኔ በጥያቄ አይን እያያቸው፤ ሁሉም እንቅልፉን ወደለጠጠው የዶርሙ ስድስተኛ አባል ዮሴፍ ዞሩ:: ቶላ ወደ አልጋው ሄደ፣ "ጆሲ… ጆሲ… ተነስ!" እያለም ነቀነቀው፤ ዮሴፍ እያሊቃቀሰ ተነሳ::

"ጆሲ ህልም አይተሃል… ንገረን?" እያሉ ሁሉም ተፈራረቁበት፣ ጆሲ ሰዓቱን ተመለከተ፤ ውድቅት 10:00 ሰዓት ነው፤… "እናንተ ያማችኋል እንዴ? የምናባታችሁ ህልም ነው?.. አቦ! ነገ ተፈታኝ ነኝ ልተኛበት አትረብሹኝ::" አለና ራሱን በብርድ ልብስ ጥቅልል አድርጎ ተኛ:: እነኢትኤል ስድስተኛው ሰው እሱ እንዳልሆነ አውቀዋል… ማን ሊሆን እንደሚችል ግን ማንም አላወቀም:: ነገ ተፈታኝ ናቸውና ለ2 ሰዓትም ብትሆን ለመተኛት ወደ አልጋቸው ተመለሱ:: ልክ የዶርሙ መብራት እንዳጠፋ ናዖድ መሳቅ ጀመረ፤

"ናዖዴ ምንድነው ያሳቀኽ?" አለ አብርሃም፤ በሹክሹክታ፤

"አይ በህልማችን ያንን የጣ አሞራ ሳስብ ምን እንደመጣልኝ ታውቃለህ?"

"ንገረኝና ልተኛ"….. "ያ አንተ ራሱ የምትወደው፣ ‹‹እንደ ንስር ወደላይ! ወደላይ! ወደላይ፣ እንደ ንስር ወደላይ! ወደላይ!›› የሚለው የአውታሩ መዝሙር::"… ሁለቱም ስቀው ወደ እንቅልፋቸው ተመለሱ::

*** ዩ – ዩ ***

ዛሬ የፈተና ቀን ነው! ... ኢትኤል ነጭ ሸሚዙን እስከ ማንቁርቱ ቆለፈ፤ ከዚያም በላዩ ያጠለቀውን ሰማያዊ ከረቫት ማስተካከል ያዘ፡፡ ተፈትኖ ሲወጣ የነበረው አብርሃም አየውና ወደሱ መጣ፡፡ በየምድባቸው የስም ተራ መሰረት አብርሃም አንደኛ ተፈታኝ ሲሆን ኢትኤል ደግሞ ሰስተኛ ተፈታኝ ነበር፡፡

"ከረቫትህ ተዛንፏል ቆይ ላስተካክልልህ..." አለና የኢትኤልን ከረቫት ላላ ጠበቅ እያደረገ አስተካከለው፡፡

"እንዴት ነበር ‹‹ኤግዛም›› (ፈተና)?" አለ ኢትኤል፤ የጓደኛውን ውጤት ለማወቅ እየጓጓ፤

"በጣም አሪፍ ነበር ይመስገነው..."

"ማን ጋር ነው የተፈተንከው?"

"ዶክተር ትህትና ጋር ነበር፡፡"

"አይ አሪፍ ሰው ደርሶሃል፡፡"

"አዎ ብዙም አላስጨነቀችኝም... አንተ ግን ፈርተሃል አይደል ኢታ?" አለው ከረቫቱን አስተካክሎ እንደጨረሰ፤

"እንዴት አልፈራ ... ፈታኜ እሳቱ ቢሆንስ?" አለ ኢትኤል፤

"አትፍራ እግዚአብሔር ያውቃል፤ ደግሞ ጥዋት ቤተ-ክርስቲያን ስሄድ ላንተም ለእኔም ነው የፀለይኩት... እሱ ይረዳሃል" አለውና ተሰናብቶት ሄደ፡፡

ኢትኤል በጭንቀት ውስጥ እንዳለ አንድ ሬዝደንት ወደሱ መጣ፡፡

"ኢትኤል አንተ ነህ?"

"አዎ" መለሰ ኢትኤል፤

የቃል ፈተናውን የሚፈተንባት አንድ ታካሚ ሊመርጥለት እንደሆነ ነግሮት ይዞት ሄደ፡፡ በመንገዳው ላይ ሳሉ ፈራተባ እያለ፤ "ፈታኜን ማወቅ እችላለሁኝ?" ብሎ ሬዝደንቱን ጠየቀው፡፡ ሬዝደንቱም እርምጃውን እንደቀጠለ አንድ ወረቀት ገልጦ ተመለከተና፤ ፊቱንም ሳያዞር፤ "ዶክተር አበራ ነው፤" ብሎ መለሰለት፡፡ ኢትኤል በድንጋጤ ልቡ ቀጥ አለች፡፡ ‹‹የፈሩት ይደርሳል የናቁት ይወርሳል›› የተባለው በእርሱ በርግጥም ተከሰተ፡፡

እንደመሚ እየተራመደ ለፈተናው የተመደበባት ታካሚ ጋር ደረሰ፡፡ ሰላምታ ከሰጣት በኋላ ከጎኗ ወንበር ስቦ ተቀመጠ፡፡ ኢትኤል የታካሚዋን ታሪክ እየጠየቀ በዶሴው ላይ ሲያሰፍር፣ አካላቶቿን እየመረመረ ሲመዘግብ ውስጡ ግን በፍርሃትና በተስፋ መቁረጥ እየደለዘ ነበር፡፡ የተሰጠው ጊዜ ሲያልቅ ወደ መፈተኛው ክፍል መሄድ ነበረበትና የቅድሙ ሬዝደንት መጥቶ ሲጠራው ተነስቶ ወጣ ፡፡ ሬዝደንቱም አስከትሎ ወስዶት ከመፈተኛው ክፍሉ ፊት ለፊት

ቁም አለው:: ስሙ እስኪጠራ ጠብቆ እንዲገባ ነግሮትም ሄደ:: ኢትኤል የክፍሉ በር ላይ መንቆራጠጥ ጀመረ፤ ከራሱ ጋር በሃሳብ እየተሰናሰነ…

"ቆይ አሁን ዶክተር እሳቱ አግኝቶ ቢጥለኝ ምንድነው የማደርገው?… መቼስ አዲስ አበባ ሄጄ የግል እማራለሁኝ እንጂ አንድ አመት ሙሉ ቤት ቁጭማ አልልም!… ግን ደግሞ ጓደኞቼስ?… እነአብርሃምስ?… እንዴ መርሳቴ… ፅዮንስ?… ወይ ጉዴ! አዎ ፅዮንስ?!" ብሎ ራሱን ሲጠይቅ ድንገት መንቆራጠጡን ትቶ ቀጥ ብሎ ቆመ:: ‹‹አዎ ፅዮንስ?›› ሲጀምርም ጅማ ዩኒቨርስቲ ሞልቶ የመጣው እሷኑ ብሎ ነው::ከልጅነቱ ጀምሮ ፅዮን ከማንነቱ የማይነጥላት የእሱነቱ አካል ነች:: እርግጥም ካለእሷ ህይወቱ ትርጉም አልባ ሩጫ ናት:: የኢትኤል ሩጫም ቢሆን ውበት የሚኖረው አባርሽ ላይ ሲሮጥና ፅዮንን ሲያስፈታ ነው:: ካለ'ሷ ያለው ታሪኩም ቤት እንደሚያፈራርስ ግጥም ለዛ የለውም:: ቤት የሚያፈርስ ግጥምም ቢሆን ለሷ ሲያነብላት እያበረታታች የፈረሰውን እንዲጠግነው የምታደርገው ሴት ፅዮን ብቻ ናት::

"አዎ በፍፁም አይሆንም፤" አለ ነፍሱን በርብሮ ለአደጋ ጊዜ የተቀመጠችውን ጥንካሬውን እያወጣ:: "አዎ በፍፁም መውደቅ የለብኝም! ፅዮንን ትቼ አልሄድም::" አለና ፈተናውን እንዴት ማለፍ እንዳለበት ማውጠንጠን ጀመረ:: በእርግጥም ከእሱ የሚጠበቀውን በሙሉ አድርጓል ማለት ባይቻልም ከእሳቱ ማስፈራሪያ ጋር እየታገለ የቻለውን ያህል አጥንቷል:: ቢታንያን አግኝቶ ለተወሰኑ ቀናት ከጥናት መዘናጋቱ ግን እሙን ነው:: ቢሆንም በምርቃናም ይሁን በቡና መነቃቃት እየታገዘ ብዙ ሌሊቶችን በንባብ አሳልፏል:: ትልቅ ውጤት ባያስጠውም ለማለፍ የሚሆን እውቀት ግን አለው::

ችግሩ ግን ማለፍና መውደቁ ከእሱ እውቀት በላይ በሆነች እድል ክር ላይ መንጠልጠሏ ነው:: የፈለገውን ያህል እውቀት ቢኖረው እሳቱ ከፈተነው ከወዳቂዎቹ እንደሚሆን አያጠራጥርም:: ከእሱ አቅም በላይ የሆነውን ነገር በምን ሊፈታው እንደሚችል አሰበ:: በዚህች ደቂቃ ሊረዳው የሚችል ሌላ ማንንም አካል የለም:: እሱና የእሱ ችግር ተፋጠዋል… ፍርሃቱ ቀስ በቀስ ሲመለስ ይታወቀዋል:: ለፅዩን ደውሎ ጭንቀቱን ሊያጋራት አስቦ ቢሞክርም ስልኳ ይጠራል እንጂ አይነሳም ነበር:: ከዚህ ከአቅሙ በላይ በሆነ ፈተና ፊት ብቻውን እንደሆነ ሲሰማው እጅግ ተጨነቀ፤ ወዲያው ግን ውስጡ በአንዳች ሃይል ሲሞላ ተሰማው:: ከህሊና የነጠረች ጥሪ፥ ዘማም ዜማ ያለው አፅናኝ መልዕክት፤ የእኚያ ባህታዊ ሰው ንግግር በአዕምሮው ውስጥ ያስተጋባ ጀመር::

***"እግዚአብሔር ወደዚህ ትውልድ ፊቱን አዙሯልና፡፡ አዎን! ከቃል ጠባቂዎች ሁሉ በላይ ቃል ጠባቂው አባት የቅድስት ምድሩን ህዝብ ያስባልና፡፡ መንገዱን የሳተን ትውልድ እሱ ወደ መንገዱ ይመልስ ዘንድ ይገለጣል፡፡ ብቻውን ሆኖ ፈተናው ያስጨነቀውንም ሁሉ እግዚአብሔር ያግዛል፡፡ መንፈሱን ያፈሳል፤ በሁሉም ዘመን ለህዝቦቹ አስታዋሾችን ይልካል፡፡"***

"አዎ! ‹ፈተናው ያስጨነቀውን ሁሉ እግዚአብሔር ያስባል፡፡› አውቃለው ብቻዬን አይደለሁም፡፡" አለ ኢትኤል ከተመስጦው እየነቃ፤ ከአይኑ እንባ ግጥም ብሎ ሞልቷል፡፡ "አዎ እስካሁን ስፈልገው እሱም ሲጠራኝ የነበረው አንድ አምላክ ሁሌም ከጎኔ ነው፡፡" አለና አይኑን ጨፍኖ መፀለይ ጀመረ፡፡

*"በሰማያት ያለህ ፈጣሪዬ ሆይ፤ ምልክቶችን ስትልክ፤ በማነባቸው መፅሐፍቶች፣ በጓደኞቼ ምክሮች፣ በምሰማውና በማየው ሁሉ ጥያቄዎችን ስትፈጥርብኝ ለመቀበል የከበደኝ አስቸጋሪ ሰው እንደሆንኩኝ አውቃለሁኝ፡፡ አሁን ግን በዚህ ፈተና ፍርሃት ውስጥ ሆኜ አንተን ተቀብያለሁኝ፤ እርዳታህንም እሻለሁኝ፡፡ አብርሃም እንደሚለው አንተ እግዚአብሔር ፍቅር ነህና፣ ዘይኔም እንደነገረኝ እጅግ በጣም ርህሩህና አዛኝ ነህና እርዳታህን እሻለሁኝ፤ ለጭንቁ ድረስ፡፡ የዓለማት አምላክ እግዚአብሔር ሆይ የሚረዳኝ የለምና ከእኔ አትራቅ፡፡ አሜን!"* ብሎ አይኑን ሲገልጥ ሬዝደንቱ ከፊቱ ቆሞ እያየው ነበር፡፡

"ምንድነው ጀለሴ ያጠናኸውን እየሸመደድክ ነው እንዴ?" አለው፤ ኢትኤል አይኑን ጨፍኖ በለሆሳስ የሚለውን ነገር መስማት ያልቻለው ሬዝደንት፤

"አይ ትንሽ ፈርቼ ስለነበር እየፀለይኩኝ ነው፡፡" አለ ኢትኤል ፈገግ እያለ፤

"እንግዲያውስ ፀሎትህን ሰምቶሃል፡፡" አለ ብላቴናው ሬዝደንትም ፈገግ ብሎ፤

"እንዴት?" አለ ኢትኤል በመገረም፤

"ካንተ በፊት ዶ/ር አበራ ጋር የተፈተኑት ሁለቱም ልጆች እያለቀሱ ነበር የወጡት፡፡ አንተን ልጠራህ ስሄድ ግን ዶ/ር አበራ ትንሽ አሞት ወጥቶ ነበር፡፡ አሁን ደውሎ መምጣት እንደማይችልና እሱ ጋር የተመደቡትን ተማሪዎች ሌላ ሰው እንዲፈትናቸው ነግሮኛል፡፡ ለዚህ ነው ፀሎትህን ሰምቶሃል ያልኩህ፡፡" አለው፤

"ማነው የሚፈትነኝ አሁን?" ጠየቀ ኢትኤል በጉጉት፤

"ዶ/ር ሳሙኤል ነው!" አለ ወጣቱ ሬዝደንት ዞሮ እያየው፤..."እኬ!" አለ ኢትኤል የተሰማውን ታላቅ እፎይታና ደስታ ለመቆጣጠር እየታገለ፤

*ከ30 ደቂቃዎች በኋላ ታላቅ ፈገግታ ፊቱ ላይ የሚነበብበት አንድ የህክምና ተማሪ ከዶ/ር ሳሙኤል ቢሮ ሲወጣ ተስተውሏል፡፡*

*** ቶ – ቶ ***

♫ ♪ *"ነቅቻለው… ተርፌያለው… ራሴን ላድን ቆርጬያለሁ፣*

*ሴቱ ላይ - ብርሃኑን ላይ… አይኔ ላይፈዝ - ጨለማው ላይ፣*
*ልፈልገው ከዋለበት - ፍፁም ፍቅር ከምላበት*
*ራሱ ላይ - ጎዳናው ላይ - ፍቅርን ላገኝ - ፊት ለፊት ላይ፣*
*መንገዴን ለየ… አይኔ ብርሃን አየ*
*…በቃ በቃ ድሮ… የጨለማው ኑሮ፡፡"*

…በሬጌ ምት ያሸበረቀ ማራኪ ድምፁን እና ለየት ያለ ጥልቅ መልዕክት ያላቸውን ግጥሞቹን ለአድናቂዎቹ በቅምሻ ብቻ ሰጥቶ ሳይጠገብ በሞት የተለየው አርቲስት እዮብ መኮንን ሙዚቃ ከታክሲው ስፒከሮች ይተምማል፡፡ በተሳፋሪ ብዛትና የፀሐይቱ ሙቀት የተጨናነቀውን ታክሲ ፈታ የሚያደርግ እርግብግቢትንም ይረጫል፡፡ ከሁሉም ተሳፋሪዎች በተለየ ግን ከሙዚቃው ጋር ድምፁን ከፍ አድርጎ የሚያንጎራጉር አንድ ወጣት ነበር፡፡

ኢትኤል ከሆስፒታሉ ሲወጣ ይዞት የወጣው ፈገግታ እስካሁን ፊቱ ላይ ይነበባል፡፡ ከእዮብ ጋር አብሮ ያዜማል፡፡ እውነትም ዛሬ የነቃበትና ብርሃንን ያየበት ቀን ስለሆነ ዘፈኑ ተገጣጥሞለታል፡፡ ስልኩ ከኪሱ ውስጥ ጮኸ፤ ቢታንያ ነበረች የደወለችው፤ አነሳው…

"አንተ ግን በጣም የኮራህ አይመስልህም?" አለችው፤ እንደተናደደች ድምጿ ያሳብቃል፡፡

"ኧረ አለሁኝ…" አላት እየተቅለሰለሰ፤

"እኔ ልዘጋህ ጫፍ ላይ ደርሼያለሁኝ፤" አለች፤ ማስፈራሪያ መሆኑ ነው፡፡

"ይቅርታ ፈተና ስለነበረኝ እኮ ‹ቢዚ› ሆኜ ነው!"

"የምን ፈተና?… ፈተና ነበረህ እንዴ ዛሬ?… ብቻ ‹ዋት ኤቨር› ግን እንድታረቅህ የምትፈልግ ከሆነ አሪፍ ምሳ ጋብዘኝ፤" አለች በቁንጠኛ አነጋገር፤

ኢትኤል ግን ጥያቄዋን ሳይመልስላት ቆየ፤ ምን ሊላት እንደሚፈልግ አያውቅም፡፡ እውነቱ ግን ውስጡ ቢታንያን እንኳንስ ሊያገኛት በሞባይል ሊያወራት ራሱ አልፈለገም፤ ልቡ እየፈለገ ያለው ፅዮንን ብቻ ነበር፡፡ ምንም የጥፋተኝነት ስሜት ሳይሰማው ስልኩን ጆሮዋ ላይ ዘጋባት፡፡ ደጋግማ ስልኩን

አስጮኸቻት:: በንዴት ብው ብላ ኢየበደች እንደሆነ ገምቷል:: እሱ ግን ከዛሬ ጀምሮ ይህ ግንኙነት መቆም እንዳለበት ወስኗል፣ የሷን ስልክ ብሎክ አድርጎ እንዲህ የሚል አጭር የፅሁፍ መልዕክት ላከላት::

*"ቢታንያ አንቺን በማወቄ ደስ ቢለኝ እንጂ አልከፋም፣ ትንሽም ቢሆን ላሳለፍናቸው ጊዜዎች አመሰግንሻለሁኝ:: ግን ይቅርታ ከዚህ በኋላ ላገኝሽ አልችልም:: ግንኙነታችንም እዚህ ላይ ማቆም አለበት:: ቀኑ ሲደርስ ላንቺ የሚሆን የራስሽ ሰው እንደምታገኚ አልጠራጠርም፣ ምን አልባት አለባበሱንና የምግቢሉን ምርጫ አይተሽ ካልሸሸሽው ማለቴ ነው:: እኔ ግን ልቤን የተቆጣጠረች አንድ ፉራ ሴት አለች፣ ፅጮን ትባላለች:: ላንቺ ግን በህይወትሽ መልካሙን ሁሉ እንዲገጥምሽ እመኝልሻለሁኝ:: ቻዎ::"*

...

ኢትኤል ከሚኒባሱ ሲወርድ ከጀግና እፎት ተመዞ ጠላቱ ላይ እንዳየለ ሰይፍ የሚዋጋው ስለታማ ፀሐይ ስር ነበር ራሱን ያገኘው::

ከአንዲት ከመንገዱ ዳር ከተቀመጠች ሴት በስተቀር ሁሉም ሰው አካላትን ወደ ትነት ለመቀየር ትንሽ ከቀረው ፀሐይ ለማምለጥ ቆጪ አደባባይ ላይ ወዲህ ወዲያ ይሯሯጣል:: ለአፍታ የማትሮጠዋን ሴት ትክ ብሎ አያት:: ከአስፈሪ ገፅታዋ ታጅባ ወበቁን ከቁብም ሳትቆጥረው፤ ከጠራራዋ ፀሐይ ጋር ተፋቅራ ተቀምጣለች:: ኢትኤልን በጎሪጥ እየቸውና ከመቅፅበት ዘላ ቆመች...

"ቦኸ!... ምን አባህ ታፈጥብኛለህ?" እንደ መብረቅ አስገመገመችበት፤ ሊሸሽ ቢያስብም ወንድነቱ ግን ተናንቆ አስቀረው::

"አሁን ከኔ ከባዶዋ ውዳቂ ምን አገኝ ብለህ ነው የምታፈጥብኝ?፤ ወይስ አሳዘኜኸ ነው?... ቂቂቂቂ... አንተም ወደድኩሽ ልትለኝ እንዳይሆን በ'ናትህ" አሽካካች... ተስፋ በራቀው የደስታ መሳይ የስቃይ ድምፅ፤

ወድያውም ጨኸቷን ገታ አድርጋ ከራሷ ጋር ለሆሳሳዊ ውይይት ያዘች፤

"ቆይ ግን ለምንድነው ሁሉም እንደዚህ የሚያፈጡብኝ...ፈጣጣ ሁላ፤ ቆይ እኔ ለየት ያለ ነገር አለብኝ እንዴ ሆ! ሆ! ሆይ!... ከሚያፈጡ አይረዱኝም... ለወሬና ወቀሳ ነው እንጂ ... ፈጣጦች ቢያፈጡ፣ ምንስ ቢሰጠጡ ፣ ምንም አያመጡ........ ቂቂቂቂ!"

... አጭር ግጥም ገጠመች፤ ኢትኤል ግራ ምታጋባ ሴት ሆናበት የፀሐይዋንም ግለት ረስቷት ቆሞ ያያታል:: አውቆ አበድ የሚሏት አይነት ሳትሆን አትቀርም ብሎም ገመቷል::

በሳቅ እየተትረመረመች ከቦታዋ ተመልሳ ቁጭ አለች:: መቀመጫዋ አፈር ነካ እንጂ ምንም አይነት የማረፍ ምልክት ግን አይታይባትም:: ከእሳት አጠገብ የተቀመጠ በረዶ እንዴት ያርፋል:: እውነትም ውስጧ አላረፈ ኖሮ

ተስፈንጥራ ተነስታ ከፊት ለፊቷ ከቆሙት ታክሲዎች መሀከል ወደ አንዱ ማስታወት ተጠግታ ራሷን ማስተዋል ጀመረች:: ኢትኤልም እዚያው በቆመበት ሆኖ ገፅታዋን አስተዋለው::

በመንገላታት ብዛት ቢደበዝዝም አረንጓዴ ቢጫና ቀይ እንደነበረ የሚያስታውቅ መቀነት ቢጤ ወገቧ ላይ ሸብ አድርጋለች:: ከልብስነት ተራ የወጡ ቆሻሻ ሹራቦችን ደራርባ የለበሰች ቢሆንም ሲበዛ መቀጨጯን ግን መደበቅ አላስቻላትም:: ከልብሶቿ እጅታዎች በርትፈው የወጡ የእጅና እግር ጣቶቿ በእድፍ ተሸፍነዋል:: ፊቷ የሸፈነው ቆዳ ያኔ በኢልኒኖ ተቃጥለው እንደጠወለጉ ምስኪን የኢትዮጵያ ዛፎች ከስም ብሷል:: በየአቅጣጫው ባለፈው እንዳጋጠመው ላቦሮው ልጅ ያለቅጥ የተንጨበረረው ፀጉሯም ቢሆን ከሚሊኒየም በኋላ ቅባትና ማበጠሪያ እንዳላየ ያሳብቃል:: ከሚሊኒየም ጀምሮ ውዱ ኑሮ ለሚሊየነሮች እንጂ ለድሆች ስላልሆነ ግምቱ ተጨባጭ መሰረት ያለው ይመስላል::

ሴቲቷ ለግማሽ ደቂቃ ያህል ራሷን ስትመለከት ቆይታ ድንገት… "ቆንጆ ነኝ! ቆንጆ ነኝ!… " ብላ ዘለለች፤

"እሱም ሁሌ ቆንጆ ነሽ ነበር የሚለኝ…"አለች ደግሞ መልሳ ዝላዩን እየተወች፣

"እኔም አምኜው ነበር… ማመኔ ግን ሞኝ ያስብለኛል እንዴ?… እንዴ ሞኝማ አይደለሁም::"… ራሷ ጠይቃ ራሷ መለሰ ከአስፓልቱ ጥጋ ጥግ የተጣሉ ፌስታሎችና ቅራቅንቦዎችን መለቃቀም ያዘ:: ቀጥላም የሰበሰበችውን ቆሻሻ በትከሻዋ ተሸክማ ወደቦታዋ ተመልሳ ገና ቁጭ ከማለቷ የለቃቀመችውን ግሳንግስ በሙሉ ወደ መሬት በተነችው፤ ከበስተግራዋ የቆመ ሰው ያለ ይመስልም ወደ ግራዋ ዞራ አይኖቿን እያጉረጠረጠች በጉልበቷ ተንበረከከች:: ቀጥላም ፊቷን በሁለት እጆቿ እየቧጠጠች መጮኸ ጀመረች፤

"ዘ… ር… ኡ… ዘሩ!… እባክህን ከፊቴ ዞር በል:: ውሸታም! ውሸታም ነህ! ድጋሚ ላይህ አልፈልግም:: ያንን ሁሉ ጊዜ "እወድሻለሁኝ" የምትለው ለካ ዋሾ ኖረሀል:: ትዝ ይልሃል ያኔ ስላሜን እንዳረገዝኩኝ የነገርኩህ 'ለት?…"

ወድያው ንግግሯን አቆመችና ጭንቀት በተሞላበት ድምፅ ተንተባተበች፤

"ል… ልእእ… ልጄ… ልጄ… ልጄስ… የት አለች?… … ልጄ የታለች?!"

ከ'ንብርከኳ ተነስታ የመኖሯ ብቸኛ ምክንያት የሆነችው ልጇን ፈለገቻት…

"ማማዬ… ማማ… የኔ ህይወት ስላሜ…" ስሟን እንደ ዳዊት ደጋገመችው፤

አንድ እንደ ሸንበቆ ቀጥና ልትሰበር ምንም ያህል ያልቀራት ልጅ ከአስፓልቱ የወዲያኛው ጎን ብቅ አለች:: የሴቲቷ ፊት በደስታ ፈካ፤ ልጅቷም ለሚርመሰመሱት መኪኖች ደንታም ሳትሰጥ በባዶ እግሯ ፊር ብላ መጥታ

ከእናቷ ጉያ ውስጥ ውሽቅ አለች፡፡ ‹ምንም ብትቆሽሽ እናት ሁሌም እናት ናት› አለ ኢትኤል በልቡ፤

"ሰላምዬ ማማዬ፤" አለቻት ልጇን ጭምቅ አድርጋ እያቀፈቻት፤

"አቤት እማ!"

"አባትሽን ታውቂዋለሽ?"

"ኧረ እማ! ስለአባቴ 'ኮ በደንብ ነግረሽኝ አታውቂም፤" መለሰች ልጂት፤

"ለነገሩ አንቺ እንዴት ታውቂዋለሽ እኔ ራሱ አላውቀውም፤ ... ቆይ! ቆይ! ግን አውቀዋለው እንጂ፤ አባቴ ከመሞቱ በፊት ነበር እኮ ከዘርዬ ጋር ያስተዋወቀኝ፡፡ እንዴ... እንዲያውም አሁን አንቺ ከመምጣትሽ በፊት እዚሁ ነበር፡፡ ለምንድነው ግን አንቺን የማይወድሽ ሰላምዬ? እኔን'ኮ ሁሌም እወድሻለው፤ እ... አፈቅርሻለሁኝ ይለኝ ነበር፤ አንቺ እስከትመጪ ድረስ፡፡ አዎ፤ እኔ የማውቀው ዘሩ አንቺን ሳረግዝ ሞቷል፤ አንቺን የእውነት ዘመዱን ትቶ ወደቤተሰቡ ወግኖ ሸሽቷል፤ ካንዲት የብሔሬ ተወላጅ ነች ካላት ጋር ተጋብቶ ይኖራል፡፡ እሷም እኔን ለማጥፋት ጠንቋይ ቤት ተመላልሳለች፤ ዘንዶ እየቀለበች፤ በሙተቶቿ ህይወቴን በጥብጣ ከነልጄ በረንዳ ጥላኛለች፡፡ ወይኔ ልጅት! እሱን ብዬ ነበር እኔስ መዋተቴ..." ኢትኤል ሴትዮዋ ልጇን ስታይ ተፈጥሮባት የነበረው ደስታ ቀስ በቀስ በሀዘን ሲሸረሸር ተመለከተ፤

"ሰላምዬ እኔ ቆንጆ አይደለሁም እንዴ?" ጠየቀች ልጇን፤

"ሌሎች የፈለጉትን ቢሉሽም አትስሚ፣ አትደማመጪ እሺ እማ... አንቺ ብዙ ውበትን የተቸርሽ ቆንጆ ነሽ፤" ብላት ስታበቃ ሰላም ለእመሉ ያህል ከእናቷ ጎን ለደቂቃዎች ከተቀመጠች በኋላ ተነስታ አስፓልቱን ተሻግራ ሄደች፤

ባለ ኢትዮጵያ መቀነቷ እናት ግን በፀሐዩ ንዳድ ስር እዚያው ስፍራዋ ላይ ኩርምት ብላ ቁጭ እንዳለች አለች፡፡ የሚሰማት ባይኖርም በየመሀሉ ወደ አላፊ አግዳሚው ቃላትን ትወረውራለች... በተስፋ ታጥራ እየጠበቀች... ምን አልባት የሚሰማ ካለ እያለች፡፡ በድግምትና ክፋት፣ በዘረኛ አባወራ የተጎሳቆለን የእናት ሃገር ጥሪ የሚሰማ ካለ እያለች ነበር፡፡ ከዚያም አንድ ገብስማ ላባ ያላት ዶሮ መጣችና ከሴትዮዋ ጎን ኩሷን መጣል ጀመረች፡፡ ኢትኤል ይህ ገርሞት ሲዞር በተመሳሳይ ጊዜ አንድ በማርሴዲስ የጀርባ ወንበር የተቀመጠ ድንቡሎ ልጅ አፐል እየገመጠ ሲፍለቀለቅ ተመለከተ፡፡

ይሕቺን ምስኪን ግን ከዚህ በላይ ቆሞ ሊታዘባት አልቻለም፤ ወደ ራሱ የኑሮ ዱብ ዱብ መመለስ ነበረበትና ሀሩሩ ላይ ትቷት ወደተከራየው ክፍል አቀና፡፡ በውስጡ ግን *"ሰሚ አልባ ወገኖቹ"* የሚል ግጥም ተረግዞ ነበር፤ ቤቱ

እንደደረሰም ከአልጋው ላይ ተጋደመና የሚወዳትን የግጥም ደብተሩን አውጥቶ እንዲህም ሲል ወለደው፤

*✍ ከሰው ተራ ወጥተው - ሳሉ ማይቆጠሩ*

*እልፍ አሉ ወገኖች ወገን የተራቡ፥*
*የኑሮ ቁስለኞች ኖረው የማይኖሩ፤*
*በሰሚ አልባ ጩኸት*
*ዝንት ዓለም ሚጣሩ፡፡*

ኋላም ያቺ ከምስኪኗ ሴት አጠገብ መጥታ ኩሷን የጣለችው ዶሮ ታወሰችው፤ አንዲት ሌላ ግጥምም በውስጡ ተፀነሰች፤ እንዲህም ተገላገላት…

*✍ የዓለም ትርጉም ማለት? አንድም ናት ሁለት*

*ስታድል ማትለይ ማትከፍል በስህተት*
*እልፍ ያላት ስለእውነት…*
*እኛ ባንፈጠር ስርዓቷን ባንበክል*
*ምስኪኑን ከቆሼ ከገንዳ ባንጥል*
*ከደላው አድልተን ባናስ ምጥ አፐል*
*ከልኩ አትረፍርፈን እንቁላል ባንጥል*
*ለሌለው ሰስተን የኩስ ኳስ ሳንሸልም፤*
*አብረን ብንበርካት አብስለን በቅመም*
*አሳረ-ሁለት ብልት ዶሮ ናት የኛ ዓለም፡፡*

አዎ ይህቺ ዓለም እኛ የሰው ልጆች ከተጨካከንባት እርሷም ጨካኝ ትሆናለች፡፡ የዚህችም ሴትዮ ህይወት እንዲህ መሆን ጀርባ ተጠያቂ ሰዎች እንዳሉም ከንግግሯ መረዳት ችሏል፡፡ ሰዋሰው ከጎደለው ንግግሯ ለመረዳት እንደቻለው የልጇ አባት ትቷት እንደሄደና የብሔሩ አባል የሆነች ሌላ ሴት እንዳገባ እሷም ደግሞ በጥንቆላና ድግምት የዚህችን ሴት ህይወት እንዳበላሸች ተረድቷል፡፡

"ቆይ ግን ይህ ድግምት የሚባል ነገር የእውነት ቢሆንስ?… ጠንቋይ ቤት እየሄዱ የሚያስደግሙት ነገር የእውነት ሰዎችን እየጎዳ ቢሆንስ?" ብሎ ራሱን ጠየቀ፤ ቀጥሎም ፅዮን የነገረችው ነገር ትዝ አለው፡፡ "የእውነትስ እኛ ቤት ያለው ዘንዶ ለምን ይሆን ቡና እየተፈላ እጣን የሚጫጫስለት?፤ እናትና አባቴስ ለምን ይሆን በየጊዜው ዶሮና ፍየል ይዘው እዚያ አዋቂ ተብዬ ቤት ይሄዱ የነበረው? አዋቂ ተብዬው ጠንቋይ ቢሆንስ? ፅዮን የነገረችኝ በሙሉ

የእውነት ቢሆንስ?" ለማመን አሻፈረኝ ቢልም ውስጡ ግን እየሞገተው ነበር:: እናትና አባቱን እንዲህ መወንጀል ቢከብደውም አንድም ቀን ቤተ-ክርስቲያን ሲሄዱ አይቷቸው እንደማያውቅና ከእሱ ከልጃቸው በቀር ለሌላ ለማንም በጎ ነገር ሲያደርጉ አይቷቸው እንደማያውቅ ልብ ያለው አሁን ነበር:: ብዙ ጊዜ እሱ ባለበትም አነጋሽ ጀምበሬን ለማጥቃት ይመሳጠሩ እንደነበር ትውስታዎቹ ግልጥልጥ አሉለት::

ፅዮንን እንደዚያ አመናጭቆ ስልክ ጆሮዋ ላይ የዘጋባት እውነትን ስለተናገረች መሆኑን ሲያስበው ፀፀት ውስጡን ሞላው:: አሁን ደውሎ ይቅርታ ሊላት ፈልጎ ደጋግሞ ቢሞክርላትም ስልኳ አልተነሳም ነበር:: የእሷን ስልክ ሞከሮ እንደዘጋ ድንገት ስልኩ ይጠራ ጀምር:: እሷ መስላው በደስታ ስልኩን ሲያየው <DAD> ይላል፤ አባቱ ሳሪል ነበር የደወሉት፤ አነሳው::

"ሄሎ ልጅ ኢትኤል... እንዴት ነበር ፈተናው መቼስ ለመምጣት አሰብክ?"

"ጥሩ ነበር... እግዚአብሔር ይመስገን::" መለሰ ኢትኤል፤

‹‹እግዚአብሔር›› የሚለው ቃል ከልጁ አፍ መውጣቱን በሰሙ ግዜ... "ምን?..." ብለው ጮኹና በዝምታ ተዋጡ፤ እንደ ደነገጡ ያሳብቅባቸዋል፤... አከለውም፤ "ዛሬ ደግሞ ያለወትሮህ እግዚአብሔር ይመስገን ምናምን ከየት ነው ያመጣኸው?" አሉ በስሱ እየሳቁ፤

"እሱ ስለረዳኝ ነዋ::" መለሰ ኢትኤል ቆፍጠን ብሎ፤

"ባክህ ይሄ የሞኞች አባባል ነው:: ያላየነው ያልዳሰስነው አምላክ ማንንም ሲረዳ አይተነው አናውቅም:: አንተ ደግሞ ስላጠናህ እንጂ የምታልፈው በሌላ ሃይል እርዳታ አይደለም:: ከሰራህ ከለፋህ ታገኛለህ አራት ነጥብ::" አሉ አቶ ሳሪል አራቱን ነጥቦች በድምፃቸው እያደመቁ::

"ታዲያ ለዚያ ነበራ አንተና እናቴ ተያይዛችሁ ያ ጠንቋይ ቤት እየሄዳችሁ የምትለማመኑት?!" አለ ኢትኤል እልህ እየተናነቀው፤

"ምን አልክ አንተ የተረገምክ... ይህቺን ይወዳል ሰውዬው፤ አባትህ መሆኔን ረሳህ እንዴ?"... የወረደባቸው ዱብዳ የቀላል አልነበረም::

"አልረሳሁም፤ ግን ሁሉንም ነገር አውቄዋለሁኝ:: ሀብታችሁን በሙሉ የሰበሰባችሁት በድግምት ሴራ እንደሆነ፤ የሰውም እንባ እንደሆነ፤ የፅዮንን አባት ጋሽ ጀምበሬንም የገደላችሁት እናንተ እንደሆናችሁ ደርሼበታለሁኝ::" አለ ኢትኤል ቅዝቅዝ ብሎ፤

"ምን አይነት የድፍረት ወሬ ነው የምታወራው? ከመቸ ጀምሮስ ነው እንዲህ የናቅከኝ... ወይስ ፅዮን የሚሏት የዚያ የከይሲ ልጅ ምናምን

እስነካችሁ?... ድሮም ቢሆን ከሷ ጋር ጭራ መቁላትህን አልወደድኩትም ነበር::" ንግግራቸው እየጋለ መጣ፤ "ደግሞስ አንተ ገና ለገና ጎረመስኩኝ ብለህ የእኛን የወላጆችህን ስራ የመቆጣጠር ስልጣን የለህም:: እኔና እናትህ የፈለግነውን የማድረግ መብት አለን::... አዎ ጠንቋይ ቤት ሄደናል የምታመጣውን አምጣ፤ አዎ! ያንን ሽማግሌ በሙተት ደፍተነዋል፤" ሳአል ቱግ ብለው ሲናገሩ ከእርሳቸው ድምጽ ጀርባ ግን "ምንድነው ሳያሌ... ምንድነው ጉዱ?..." የሚሉ የተጨነቁት የእናቱ ወ/ሮ እመቤትን ድምፅ ኢትኤል እየሰማ ነበር:: አባቱም የአቅሙን ከወረደበት በኋላ "እንቺ ይሄን ከንቱ ልጅሽን አናጋሪው::" ብለው ስልኩን ለእናቱ ሰጧት::

"ሄሎ ኢትኤሌ... ልጄ... ምን ሆንኽብኝ ነው?" አሉ ወ/ሮ እመቤት፤ እንባዎች በመንታ በመንታ እየሆኑ በጉንጮቻቸው ላይ እየወረዱ መሆኑን ማየት ባይቻለውም እያለቀሱ መሆኑን ግን ከድምፃቸው መረዳት ችሏል:: እሱም ሳይታወቀው አይኖቹ በእንባ ሲሞሉ ታወቀው::

"ለምን ግን እማ?... ለምን ክፉ ነገር በምስኪን ሰዎች ላይ ማድረግ አስፈለገ?"

"ልጄ እኔ ክፉ ሴት አልነበርኩም:: ግን ችግር ክፉ ነው:: ሁሉንም አባትህ የነገረህን ነገር ያደረግንበት ምክንያት አለን::" አሉ ወ/ሮ እመቤት በለቅሶ እየተነፋረቁ፤ "እመነኝ ልጄ ችግር ክፉ ነው:: ትዝ ይለኛል አንተን እርጉዝ ሆኜ የሚላስ የሚቀመስ በቤት ውስጥ ሳይኖር የተራብኩበት ጊዜ ነበር:: ከኔ መራብ በላይ አንተን ምንም በሌለበት አና ቤት ውስጥ ልወልድ መሆኔን ሳስብ ደግሞ ይበልጥ ይጨንቀኝ ነበር:: የዚያን ሰሞን ነበር አባትህን ይዞኝ አንድ ጠንቋይ ቤት የወሰደኝ::" አሉና በዝምታና ስርቅታ ለተወሰኑ ሰኮንዶች ቆዩ:: "ልብ ብለህ አድምጠኝ ልጄ... እኔ ካንድ አብራኬ፣ ካንተ ምንም አልደብቅህም!" ብለውም ቀጠሉ::

"ለክፉ ቀን የቋጠርናትን በሙሉ ከገበርነውና እግሩ ላይ ወድቀን ከሰገድን በኋላ ጠንቋዩ ሃብታም ሊያደርገን ቃል ገባልን:: ነገር ግን የሃብታችን መሰረት የሚሆነው መሬታችን እንደሆነም ገለጸልን:: ያኔ ደግሞ በመሬት ይገባኛል ከጎረቤታችን ጋሽ ጆንበሬ ጋር ፍርድ ቤት እየተካሰስን ነበር:: ይህንን ነገር ለጠንቋዩ ስንነገረው ሃብታም እንዳንሆን ያሰረብን፣ ወደፊት ሃብታም ብንሆን እንኳን መጥፊያችን በዚሁ ጎረቤታችን ጋሽ ጆንበሬ በኩል እንደሚመጣና ቀድመን ካላጠፋናቸው እንደሚያጠፉን ነገሩን:: አመንነውና መተቱን አሰራን፤ ጋሽ ጆንበሬም ታመሙና ለይገባኛል ከርከሩ የሚያበቃ ጤናም ሆነ ገንዘብ ስላጡ መሬቱ ለእኛ ተፈረደልን::

ጠንቋዩም በፍርድ ቤት የተፈረደልን መሬት ላይ የጥቁር ዶሮ ደም እንድንረጭበት ነገረን:: ከዚያም ሌሊት ሌሊት እየተነሳን ቦታውን እንድንቆፍር አዘዘን:: አንድ 5 ቀናት ያህል ሌሊት ሌሊት እየተነሳን ቦታውን ስንቆፍር ቆየንና በስድስተኛው ቀን ሌሊት ላይ እየቆፈርን ሳለ አንድ ትልቅ የብረት ሳጥን ተቀብሮ አገኘን:: ሳጥኑንም ስንከፍተው አንድ ጥቁር ዘንዶ በወርቅ ክምር ላይ ቁጭ ብሎ ነበር ያገኘነው:: በጣም ተደናግጠን ሳጥኑን ከድነን አስቀመጥነውና በማግስቱ ጠንቋዩ ጋር ሄደን የሆነውን ነገርነው:: እርሱም ዘንዶውና ወርቁ የእርሱ ስጦታዎች እንደሆኑ ነግሮን ‹‹ኮብራ›› ብለን የጠራነውን ዘንዶ በግና ፍየል እንድንቀልበው ወርቁንም መንዝረን ሃብታችንን እንድናሰፋበት አዘዘን:: እንግዲህ የምታየው ሃብታችን ሁሉ ምንጩ ይሄ ነው እኛም በየጊዜው እየሄድን አስራቱን ለጠንቋዩ እንከፍላለን::" አሉና በረጅሙ ተነፈሱ፤ ኢትኤል በበኩሉ ይህ ሁሉ አስፈሪ እውነታ ከእሱ ተደብቆ መቆየቱ እየገረመው፤ በሌላ በኩል ደግሞ «ምነው ባልተነገረኝ» እስኪሚል ድረስ ውስጡ እየተረበሸ ነበር ያዳመጣት፤ ታሪኩን ጨርሳ ዝም ስትልም መልስ ስላልነበረው እሱም ዝም ብሎ ነበር የቀረው፤

"እና ግን ልጄ ይሄን ታሪክ የነገርኩህ ባደረግነው ነገር እኛ ወላጆችህን እንደማትጠላን ስለማምን ነው:: እንደሚገርምህ ባውቅም ይህ እኛ ብቻ ሳንሆን ከምትገምተው በላይ ብዙ ሰዎች ሃብትን ለማካበት የሚጠቀሙበት መንገድ ነው:: ደግሞም መርሳት የሌለብህ ሁሉንም ነገር ያደረግነው ላንተ የተሻለ የድሎት ህይወትን ለመፍጠር አስበን እንጂ ድግምት የምንሰራ መጥፎ ሰዎች ሆነን አልነበረም::" አሉ ወ/ሮ እመቤት::

"እንደዚያ ከሆነ አትጨነቁ ከዚህ በኋላ የእናንተን ገንዘብም ሆነ ምንም አይነት እርዳታ አልፈልግም::" አለ ኢትኤል፤ ሊወርድ የደረሰ እንባውን እየጠረገ፤... "እንደዚያ አትበል ኢትኤሌ፤ አሁን ፈተና ጨርሰሃል... አዲስ አባ ናልኝ፤ ለቤትህ ብቃልኝና በደንብ እናወራለን::" አሉት፤

"አይ አዲስ አባ አልመጣም::"

"ለምን?"

"ወሎ ልሄድ ነው::"

"እኮ ለምንድ... " ... የስልኩ ጥሪ ተቋረጠ:: የአባቱ የሞባይል ካርድ እንዳለቀ ገምቷል፤ ነገር ግን መልሶ ለመደወል ቅንጣት ፍላጎት አልነበረውም:: እንዲያውም ስልኩን ሙሉ ለሙሉ አጠፋው:: ከዚህ በኋላ ከእናት አባቱ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በፍፁም እንደድሮ እንደማይሆን ልቡ አውቆታል::

***Emancipate yourself from mental slavery none but ourselves can free our minds, Have no fear for Atomic energy cause none of them can stop the time. (Redemption Song, Bob Marley)***

*** ፆ – ፆ ***

የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲው ፕ/ር ዳግማዊ ቀጠሮ አክባሪ ሰው ናቸው:: ፕ/ር እሴና ፍሬድሪካ ያረፉበት ግዮን ሆቴል ድረስ <ቪ-8> መኪናቸውን እያሽከረከሩ ቀድመው ደርሰው ነበር:: ከበር እየጠበቋቸው እንደሆነም በስልካቸው ምልክት አደረጉላቸው:: ለመዘገጃጀት ጥቂት ተጨማሪ ደቂቃዎች የፈጀባቸው ፕ/ር እሴና ፍሬድሪካ በችኮላ ወጥተው መጡ፤ እርሳቸው ጋቢና ገብተው ሲቀመጡ እሷ ደግሞ የኋለኛ ወንበር ላይ ተቀመጠች:: … "እንዴ ታላቁ የታሪክ ሊቅ ፕ/ር እሴ፤" አለ ፕ/ር ዳግማዊ ሞቅ ያለሰላምታ እየሰጣቸው፤

"ምን ታላቁ ትለኛለህ ባክህ፤"

"Hello there, I am Professor Dagmawi, an old friend of this guy. (ሰላም ብያለሁኝ፤ ፕ/ር ዳግማዊ ነኝ፤… የዚህ ሰው የረጅም ጊዜ ወዳጅ ነኝ::)" አሉ ፕ/ር ዳግማዊ ፈገግ ብለው ዞረው ፍሬድሪካን እየጨበጧት፤

"Nice to meet you, I am Doctor Fredricka. (ዶ/ር ፍሬድሪካ እባላለሁኝ፤ ስላገኘሁ ደስ ብሎኛል፤)" ብላ አፀፋውን መለሰች፤

"እንዴት ነው አማርኛ ትባንናለች እንዴ?" አሉ ፕ/ር ዳግማዊ በወጣትነታቸው ጊዜ የሚጠቀሙትን የአራዳ ቋንቋ እየተጠቀሙ፤

"አይ አትባንንም::" አሉ ፕ/ር እሴ የራሳቸው ንግግር እያሳቃቸው፤

"እንደዛ ከሆነማ በነፃነት በቋንቋችን ትንሽ ቦጨቅ ቦጨቅ አድርግልኛ?… ከየት አገኘሃት ይህቺን ቀንበጥ ልበል ወይስ … ነጭ ጥጥ ፀጉር ያላት የወጣት እማሆይ፤"

"እማሆይስ ወደህ…ያቺን የደቡብ አፍሪካ ሌክቸረር፣ ትልቋን ሴትዮ አፍቅረኽ በዳዴ ኬፕ-ታውን ድረስ የተጓዝከውን ረሳህ እንዴ ጃል?" አሉ ፕ/ር እሴ፤

"<አ ማይ ሚስ ኡቡንቱ!> እንዴት እወዳት እንደነበር እኮ!… የኔ ጥቁር አዝሙድ ፊት… ሃሃሃ…" አሉና በእፍታ ትዝታ ውስጥ ሳቁ፤ ከዚያም ወደ ፕ/ር እሴ ዞረው፤ "ኖ! ኖ! ኖ! አሁን የኔን ለዘመናት ያመነዠግነውን ወሬ ተውና ያንተን አዲስ የፍቅር ታሪክ አጫውተኝ::" አሉት፤

ፕ/ር እሴ ከፍሬድሪካ ጋር ከተገናኙበት ቀን ጀምሮ እስካሁን ያለውን ታሪካቸውን በአጭሩ አጫወቱት፡፡

"ወንድሜ አንተ ነህ እድሜህን እየኖርካት ያለኸው... እኛ ነን እንጂ እዚህ ሃገር እናገልግል ብለን ግልገል በግ... ሞኝ የሸከላ ገል ሆነን የቀረነው፡፡" አሉ ፕ/ር ዳግማዊ በቃላት እየተጫወቱ፤

"ምን ባከህ ሁሉም ነገር አይተህ እንደምትተረጉመው እንዳይመስልህ!" መለሱ ፕ/ር እሴ በመስኮቱ ወደ ውጭ እያማተሩ፡፡ ቀለል አድርጎ አሪፍ መልዕክት ያላቸውን ዘፈኖች የሚያዜመው አብዱ ኪያር ሙዚቃ ከመኪናው ስፒከር አልፎ ይሰማል፤

♫ *"ያልገቡበት የለም... ያልገቡበት የለም... ያልገቡበት የለም*
*ሙቀትና ብርዱን ችለው በዚህች ዓለም*
*ይህቺ ቀን ታልፋለች እያሉ በማለም፤*
*ስትጣሪ ያልመጡት ጠልተውሽ አይደለም*
*እናቱን ሚጠላ ካንቺ አልተፈጠረም፡፡"*

መኪናው የአቡነ-ጴጥሮስን ሃውልት ሁለት ሦስተኛ አክብባ ወደ ፒያሳ መንገድ ያለውን አስፓልት ይዛለች፡፡ ፕ/ር እሴ በወጣትነታቸው እንደ እሳት ሲነዱ ጥሩ ምድጃ የሆነቻቸውን ፒያሳ ተመለከቷት፡፡ ልባቸው በተለያዩ ስሜቶች ተሞላ፤ ስለሚወዷት ልዩ ስሜት ትሰጣቸዋለች፤ ድሮም አሁንም፤ ለነባሩም ለእንግዳውም፣ ለሃብታሙም ለድሃውም፣ ለቆንጆውም ለፉንጋውም፣ ለነቃውም ለተኛውም ሳቅና ጨዋታን በገፍ የምትገብር ሰፈር ናትና፡፡ ፕ/ር እሴ የአዲስ አበባን አሮጌ ቆርቆሮዎች ሲያዩ የብረት ቀለም ቀብተው ቢያስዉባቸው፣ የባቡሩ ሃዲድ ግንቦች ላይ ኢትዮጵያዊ ስዕሎችን አስለው አደባባዮቹን የታሪክ መስካሪ ሙዚየሞች ቢያደርጓቸው ተመኙ፡፡

ፕ/ር ዳግማዊ፤ "ካስቴሊ ደውዬ ለምሳ ቦታ አስዝያለሁኝ፤ እዚያ እንብላና ወደ 6 ኪሎ እንሄዳለን፡፡" ብለው መኪናቸውን ቦታ አስይዘው አቆሙ፡፡ ለሦስት ወርደውም ካስቴሊ ምግብ ቤት ዘለቁ፡፡ ምሳው ታዞ ቁጭ እንዳሉ፤

"እኔ የምልህ እንዴት ነው የሃገሪቱ ሁኔታ?" አሉ ፕ/ር እሴ ዝምታውን ለመስበር፤

"የሃገሪቷ ሁኔታማ የህዝቧ ሁኔታ ነው፡፡ የህዝቧ ሁኔታ ደግሞ ያው እንደምታውቀው ትራማይሌ ነው፡፡ ድሮና ዘንድሮ ለውጥ የለም... ያኔ በኛ ዘመን ነጭ አብዮት፣ ቀይ አብዮት እያልን ከመሰደድና መገደል ውጪ ምንም አላተረፍንም፡፡ ማርክሲስት ሌኒኒስት እያልን እ/ርን ከደን «ስራ ነው» እምላከ በማለታችን ቅጣቱ ወርዶብን ሊሆን ይችላል፡፡ አሁን ደግሞ ሰዉ

ኑሮ እንደ መኮረኒ ጎብጦበት ከተመቸው ያልተመቸው ስለሚያመዝን ሃገሪቱም አኩርፋለች ማለት ይቻላል:: ያው መንግስትም አላዳምጥም ከማለት አልፎ ማውራት አትችልም እያለ ስለሆነ ሰዉ ተለጉሟል:: የከተማው ሰው እውቀትና ምላስ ይዞ ከፖሊስ በትር ጋር መጋፈጥ የሰለቸው ይመስል ትኩረቱን ወደ ቢዝነሱ አድርጓል:: ሃሳቡን ለመግለፅ የወጣ ተቃዋሚ ጥይት ሲተኮስበት፣ ምን የሚያክል ዱላ ሲደልቀው ምን ያድርግ ታድያ?!" አሉና በምጸት ፈገግታ ፕ/ር እሴን ተመለከቱና ቀጠሉ፣

"ፌደራልና መከላከያ ለእሱ ጥበቃ መቆሙ ቀርቶ በእሱ ላይ በከስከስ ሲቆምበት ምን ያድርግ:: የፀጥታ ሃይሉ ከኢትዮጵያ ሳይሆን ከሌላ ባዕድ ሃገር የመጣ እስኪመስል ድረስ የገዛ ህዝቡን አስቀይሞታል:: ልዩ መለዮ የለበሰ ሰው መንገድ ላይ ሲያጋጥመው ‹‹ለእኔ ሰላም ነው የቆመው›› ብሎ ከሚመካበት ይልቅ ውስጡ በፍርሃትና ጭንቀት የሚሞላው ህዝብ ቁጥር ያመዝናል::"

"በጣም ያሳዝናል፤" አሉ ፕ/ር እሴ፤ በቦሌ አየር ማረፊያ ያጋጠማቸውን ችግር ለፕ/ር ዳግማዊ ሊነግሯቸው ከጅለውም ነበር:: ግን ላለፈ ነገር ጓደኛቸው ላይ ጭንቀት ከመፍጠር ውጪ ምንም ጥቅም እንደማይኖረው ተገንዝበው ተዉት እና "ምንድነው ትላለህ ታዲያ መፍትሔው?" አሉ፤

"በበኩሌ እትዬ አስካለች ትል እንደነበረው አጤ ኃይለ ስላሴ ኢትዮጵያን ረግመዋታል ብዬ ተቀብያለሁኝ" አሉ ፕ/ር ዳግማዊ፤

"እንዴት?" አሉ ፕ/ር እሴ እየሳቁ፤

"እትዬ አስካለማ የሚሉት ‹ውለታዬን በሚበላና ክብሬን በሚያዋርድ ሁኔታ ከስልጣን አወረዳችሁኝ› ብለው የተቆጡት አጼ ኃይለ ስላሴ እርሳቸው የገዙበትን ያህል ዓመታትን ኢትዮጵያና ህዝቦቿ በሰላም ማጣትና እርስበእርስ ግጭት እንድትታመስ ተራግመዋል ነው:: እኔም ይሄን እውነት ነው ብዬ ተቀብዬ የእርግማኑን ማለቂያ ቀን እጠብቅ ነበር፤" አሉ ፕ/ር ዳግማዊ ችምችም ያሉ ጥርሶቻቸውን ለፕ/ር እሴና ፍሬድሪካ እያስጎበኙ::

"ወይ አንተ፤ ብለህ ብለህ የሰፈር አሮጊት ወሬ ማመን ጀመርክ!" አሉና ፕ/ር እሴ ከት ብለው ሳቁ፤ "ምን ላድርግ ብለህ ነው፤ አሁን ግን እግዚአብሔር ከረዳቸው ከአንድ ለማ መገርሳ ከሚባሉ ሰው ጋር የመጡ ሰዎች ተስፋን አሰንቀውኛል::" አሉና አከለውም፤ "የሆነው ሆኖ ግን ለምንድነው እኝህ በችኮላ አዳራሽ አዘጋጅልኝ፣ አንድ ስልጠና ለተማሪዎች መስጠት እፈልጋለሁኝ ብለህ ነፍሴን ያወጣኸው?" ብለው ጠየቋቸው፤

"አንድ ማስተማር የፈለግሁት ነገር ስላለ ነው::" አሉ ፕ/ር እሴ በደፈናው፤

መኪናቸው በአፍንጮ በር በኩል ሹልክ ብላ አለፈች:: ከዚያ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ 5ኛ በር በኩል 6 ኪሎ ካምፓስ ገቡ::

… በቅርብ ዓመታት ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረው የማንዴላ አዳራሽ በተማሪዎች ተሞልቷል:: ብዙዎቹ የT/C እሴን ስራዎች መስማት የፈለጉ የታሪክ ተማሪዎች ሲሆኑ ከሌሎች ዲፓርትመንቶችም የመጡ አሉ:: በኋላ በር በኩል ወደ ውስጥ ሊዘልቁ ሲሉ ፍሬድሪካ ከንዳቸውን ያዝ አድርጋ እየሆነ ያለው ነገር በሙሉ እንቆቅልሽ እንደሆነባት ነገረቻቸው:: T/C እሴም ዝግጅቱ ያላሰቡት ‹ሰርፐራይዝ› እንደሆነ ነግራዋት ወደ መድረኩ ወጡ:: ንግግራቸውንም እንዲህ ሲሉ ጀመሩ…

"ልጆቼ ማሰብ ያስከፍላል እንዴ?…" ታዳሚዎቹን ተራ በተራ እያዩ፣ ተማሪዎቹ በማጉረምረምና በመሳቅ ማሰብ እንደማያስከፍል መሰከሩ፤

"አዎ አውቃለሁኝ! ዛሬ ከታሪክ ጋር የተያያዘ ስልጠና ጠብቃችሁ እንደመጣችሁ:: ግና ዛሬ የማስተምራችሁ ስለ ‹‹ማሰብ›› ነው:: ሰበካም በሉት ት/ት ብቻ አንዳች ነገር ጨብጣችሁበት እንደምትሄዱ እገምታለሁኝ::

ታላቁ ፈላስፋ ቡድሃ "ሰው ማለት የሚያስበው ነገር ነው!" ይለናል:: አሁን እዚህ አዳራሽ ያላችሁ ሰዎች በሙሉ በአንድ ወቅት የእናትና አባቶቻችሁ ሃሳቦች ብቻ ነበራችሁ:: ይህ አሁን የተሰበሰብንበት አዳራሽ ራሱ በመጀመሪያ ሃሳብ ብቻ ነበር:: የምታነቡት መፅሐፍ፣ የምትሰሙት ሙዚቃ፣ የምታዩት ፊልም በሙሉ የአንድ ሰው ሃሳብ ነበር:: ስለዚህ ዛሬ እናስብ እላችኋለው! ለተሻለ ህይወት! …ማሰብ የሰው ልጆችን ከእንስሳት ያላቀ ብቻ ሰዎችን ከሰዎች፣ ማህብረሰብን ከማህብረሰብ ያለያየ ትልቁ እውነታ ነውና። ከሺህ አንበሶች ፈርጣማ ጉልበት የአንድ የሰው ልጅ ጥልቅ አስተሳሰብ እንደሚበልጥም እወቁ:: ዓለም አሁን ያለችበትን ደረጃ ላይ የደረሰችውም በሰው ልጆች እሳቤ ጣልቃ ገብነት ነው::

የኛ ሃገር ሰው "ሃሳብ አታብዛ!" እያለ ይመክርሃል! እንደ እኔ ግን ሃሳብ አታብዛ የሚለው ‹‹ሃሳብ›› ማለት መጨነቅ ስለሚመስለውና ልዩነታቸውን ስለማይረዳ ነው እላችኋለው:: ሃሳብ ወይም "Imaginative Thinking" ማለት መጨነቅ ሳይሆን ነገሮችን ሰፋ አድርጎ ተመልክቶ፣ በጥሞና አሰላስሎ ነፃ ፍቃድ ባለው አዕምሮ መፍትሔ መፈለግ ማለት ነው:: ማሰብ ማለትም ከመጨነቅና ከማዘን ወጥቶ ወደ ማስተዋልና ወደ ባለራዕይነት የመሄጃያ መንገድ ነው:: እንደሰው ልጅነታችንም የነፃነታችን ጥግ የሚገለፀው የፈለግነውን ነገር በፈለግነው ጊዜና ቦታ፤ በራሳችን ፍቃድ ማሰብ በመቻላችን ነው።

"በእርግጥ ነፃነታችን በተግባርና ቃላት ሊገለፅ ይችላል፤" አሉ ፐ/ር ከንፍቸው የተቀመጠላቸውን የኮዳ ውሃ ከፍተው እየተጎነጩ፤

"በእርግጥ ነፃነታችን በተግባርና ቃላት ሊገለፅ ይችላል፤ ነገር ግን ቃላትና ተግባርም ቅድሚያ ሐሳብ ሆነው እንደሚፀነሱ መዘንጋት የለበትም።… አንዳንድ አንገላቸውን ዘግተው በምላሳቸው ብቻ የሚያወሩ፤ ከተናገሩ በኋላም ምንድነው ያልኩት ብለው የሚያስቡ እንደ ትራምፕ አይነት ግለሰቦች ቢኖሩም ማለቴ ነው።" ብለው ሳቁ፤ የተወሰኑ ተማሪዎችም አጀቧቸው፡፡

"የዛሬውን መልዕክቴን ቀለል ለማድረግ ያኽል… ሐሳብ ሁሉን ማንነታችንን ይቀርፃል ከሚለው መሰረታዊ አስተሳሰብ ልጀምር። ከፉ ሐሳብ ከፉ ቃልና ተግባር ይወልዳል… መልካም ሐሳብም እንደዚያው፤ …ሴባ ጥዋት ተነስቶ የመስረቁን ሐሳብ ሳይተልምና ሳያምንበት ለስርቆት አይሰማራም። አንድ ሚሊዮን ብር ያለው ሰው ገንዘቡን እንዴት መጠቀምና ወደ ፍሬያማና ትርፋማ ቢዝነስ መለወጥ እንዳለበት በአስተውሎት ማሰብ ካልቻለ በኪሱ ያለው ገንዘብ ተበትኖ የሚያልቅ ወረቀት እንጂ አንጡራ ሀብቱ አይሆንም። ሁሉንም እውነታ ሐሳብ ይወልደዋልና፤

… ተመስጦ ማሰብና ነገሮችን ማገናዘብ ደግሞ ለደስተኝነትና ስኬታማነት ቁልፍ ነው። ዛሬ ላይ ስከን ብለን የመንገዳችንን አቅጣጫ ካልተመለከትን፤ መስመራችንን ከተሻለው የህይወት አቅጣጫ ጋር ካላስተናበርን ከደነበረ በሬ በምንም አንሻልም። የነገን ኑሮውን እረፍ ብሎ ሳያስብ የሚጓዝ ሰው ኮምፓስ የጠፋበት መርከበኛ አልያም ከአዲስ አበባ ጎንደር በጅማ በኩል እንደሚጓዝ ሹፌር ወይም በደመና ተጋርዶ የመሄጃያ አቅጣጫውን ሳያውቅ በህልም አለም አውሮፕላኑን እንደሚያበር ፓይለት ይመስላል፡፡" ከፊታቸው የተሰየመውን የኮዳ ውሃ ድጋሚ ተጎነጩትና ቀጠሉ፤

"በግሌ ሃይማኖታዊ ድርሳናትን ለመመርመር ባደረግኩት ጥረት ማሰብ አንዱ የመንፈሳዊነት መገለጫም እንደሆነ አረጋግጫለሁ። ይህንን ደግሞ ከኔ በላይ መነኮሳት አባቶቻችንና የሙስሊሞች ወልዮቻችን በሚገባ ያውቁታል! … እ/ርም በመፅሐፍ-ቅዱስ የፍጥረትን ሚስጥራት ደጋግመን በልቦናችን እንድናስብና እንድናስተውል ያዘናል፤ ለምሳሌ በመጽሐፈ-ነገስት ቀዳማዊ ምዕራፍ ስምንት፤ ቁጥር 18 ላይ ‹‹እግዚአብሔር ዳዊትን በስሜ ቤት ትሰራ ዘንድ በልብህ አስበሃልና ይህን በልብህ ማሰብህ መልካም አድርገሃል›› ይለዋል፡፡ ወደ ሙስሊሞቹም ስንሄድ ቁጭ ብሎ ማሰብና ተፈጥሮን ማስተንተን የአምልኮ (ኢባዳ) አካል ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን የልብህ እሳቦት ወይም ኒያ ልክ ፈጣሪ እንደሚሰጠንም ይመሰክራል።… መቼስ ይሄ ሰው

ሰባኪ ነው ፕሮፌሰር ብላችሁ ግራ እንደሚገባችሁ አውቃለሁኝ::" አሉና ፈገግ አሉ፤

"ዞር ዞር አንድ ማወቅ ያለብን ነገር ቅድም እንዳብራራሁት ማሰብ ማለት መጨነቅ አለመሆኑን ነው። እንዲያውም ታላቁ የማሰብ ደረጃ የሚገኘው በፀሎት አልያም በእርጋታ በተሞላ ተመስጦ (Meditation) ውስጥ ነው። ይህም በምሲጋናና የተፈጥሮን ጥልቅ ሚስጥራት ባገናዘበ ምናበ ሐሳብ ማለት ነው።

... ሌላው ልብ ልንለው የሚገባ ነገር ደግሞ ማስብና ማስተዋል የት/ት ደረጃ የማይወስነው ለሁሉም የተሰጠ ፀጋ መሆኑን ነው። ለዚህም ነው፤ በህይወታችን ውስጥ "ተምሪያለሁኝ... አውቂያለው..." ከሚል የኔ ቢጤ ፕሮፌሰር ተብዬ የተሻለ ማስተዋልና ማንነት ያለው ማንበብና መፃፍ የማይችል አርሶ አደር ልናገኝ የምንችለው።

... እውቀት ማለት ፊደል መቁጠር ብቻ የሚመስላቸው ሰዎች ብዙ በተማሩ ቁጥር ስለ ህይወት ማሰብያና ማሰላሰያ ጊዜ እያጡ ከሰው ተራ ይወጣሉ፤ ሲከፋም መፅሐፍ እንደተጫነበት ሮቦት እየሆኑ፤ ለራሳቸውም ለሌሎችም ከደስታና ሰላም ይልቅ ሐዘንና መከራን ያበዛሉ፤ እናንተም ወደፊት በእዚህ አካዳሚካል ዘርፍ ማደጋችሁ አይቀርምና አደራ የምላችሁ ስትመረቁ ማሰብ፣ ማስተዋልና ከህይወታችሁ ጋርም ማዛመድን እንዳትረሱ ነው::

... እውነቱን ለመናገር ማሰብና ማስተዋል በእርግጥ በእውቀት ሊደገፍ ይችላል። እውቀት ግን በርካታ ጥሩና መጥፎ፤ አጥባቢና አስፊ እንድምታዎች እንዳሉት ልብ ማለት ያስፈልጋል:: "ሁሉንም እዩ የሚበጃችሁን ያዙ" እንዲል ቃሉ የምንቀጥፈው የእውቀት ተክል አሜኬላ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን:: የምናነበውን ነገር፣ የሰማነውንም ነገር ይሁን ያደግንበትን እውቀት ከራሳችን ማንነት ጋር ከማዋሃዳችን በፊት በህሊና ዳኛ ፊት ልናቆመው ይገባል::

... የሚያሳዝነው ነገር ይህ እናንተ ወጣት የሆናችሁበት ዘመን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የሰው ልጅ በነፃነት፣ የማሰብ ሀይል ፈተና ውስጥ የወደቀበት ወቅት መሆኑ ነው። ሰይጣን አምላኪዎች የሰው ልጅን አዕምሮ በተለያዩ ዘዴዎች 'ቢዚ' በማድረግ በቁጥጥር ስር አውለውታል።

... የእነርሱ ስውር እጅ ያለባቸው መዝናኛ ፕሮግራሞች፣ በየዕለቱ እንደ አሸን ይፈላሉ፤ ፊልሙ ባብዛኛው በቆነጃጅትና ብርቅርቆች ታጅቦ ልብን ያሸፍታል፤ ዘፋኞች ወጣቱን ከወሲብና ብር  በስተቀር ምንም እንዳያሳስበው ሳያሰልሱ ይሰብካሉ:: ቁም ነገር ማውራትና ማስተዋልን እንደ ፋራነትና ሞኝነት እንዲቆጠር ያስተምሩታል፤ ህዝቡ ከመረጃ እንዲርቅና ለእውቀት ቀርቶ ለፀሎቱ እንኳን ጊዜ እንዳያጣ አድርገው በተከታታይ ፊልሞች ጊዜውን

ይፈጁታል፡፡ በየጊዜው ሱስ የሚያሲዙ የሞባይል ጌሞችን እየፈበረኩ አይኑ እስኪደክም ድረስ ሞባይል ጎርጓሪ ወጣት እንዲበዛ ይለፋሉ፡፡

ከዚህ የተረፈውን ወጣት ከልክ ባለፈ ሁኔታ፤ ከፍቅር ይልቅ ወደ ፀብ እስኪገፋ ድረስ በእግር ኳስ ጨዋታ እንዲዝናና ሳይሆን እንዲወጠር ያደርጉታል፡፡ በከተማው የሚገኙ ሃገር በቀል ቡድኖችን ከማወቅና ከመደገፍ ይልቅ የአውሮፓ ቡድኖችና ተጫዋቾች እንዲያደንቅ ሚዲያውን በእነርሱ ዘገባ ያጥለቀልቁታል፡፡ የአውሮፓ ተጫዋቾችን የጫማ ቁጥራቸውን እስከ ማጥናት ድረስ ብሎም የኳሱን ዓለም ቢዝነስ የመዘዋወሪያና የደመወዝ መጠን እየሸመደደ ጭንቅላቱን በማይጠቅመው እውቀት እንዲሞላ ያበረታቱታል፡፡ ወጣቱ ኳስ ተጫውቶ ጤናውን ከመጠበቅና መንፈሱን ከማደስ ይልቅ ከ«ዲ ኤስ ቲቪ» ፊት ተቀምጦ እንዲውል ይከርቡታል፡፡ በቁማር ሱስ በሚለከፉ እንደ ፑልና ከረንቡላ አይነት ጨዋታዎች ወጥረው ይዘው ቀኑን ሙሉ ያውሉታል።… ካለአንዳች አላማ ተራ ህይወት ኖሮ፡ ተራ ሞት እንዲሞት እንደ ኮንክሪት ይሞሉታል።" አሉና በአብዛኛው ወጣት የሆነውን ታዳሚያቸውን ተመለከቱት፡፡

"እንግዲህ የተናገርኳቸው ነገሮች ብዙዎቻችሁን የሚነካ እንደሆነ አምናለሁኝ፤ ነገር ግን እንዳይሰማችሁ ብዬ እውነታውን ሳልናገር ብቀር ይጸጽተኛል፡፡ ትዕግስቱ ኖሯችሁ ይህንን ንግግሬን እስከዚህ ድረስ በጥሞና እያዳመጣችሁኝ ስለሆነ ደግሞ አመሰግናችኋለሁኝ፡፡ አንዳንዶቻችሁ ደግሞ በልባችሁ <<ይህ ፕሮፌሰር ተብዬ ምንድነው የሚፈላስፈው?>> ልትሉኝም ትችሉ ይሆናል። ጓዶች! ይሄ የማሰብ ጥበብ ፍልስፍና አይደለም፤ ለምሳሌ «ሰር አይዛክ ኒውተን» ከብዙ አመታት በፊት *<<Energy is neither created nor destroyed but transformed from one form to another>> (ሃይል አይፈጠርም ወይም አይጠፋም ነገር ግን ከአንድ አይነት ወደ ሌላ አይነት ሃይል ይቀየራል)* ብሎ ነበር፡፡ በፊዚክሱ የቅርብ ግኝት መሰረት ደግሞ ልክ እንደ ኤሌክትሮ ማግኔቲክ ሃይሎችና ሜካኒካል ኢነርጂዎች ሁሉ እያንዳንዷ የምናስባት ነገር ኢነርጂ እንደሆነች ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ በየስኮንዱ የምንለቃት የአዕምሯችን ሃሳብ ካለገደብ በዩንቨርስ ውስጥ ትጓዛለች ማለት ነው፡፡ አንድን ሃሳብ በተደጋጋሚ ማሰብ ደግሞ የመከሰት እድሉን ከፍ የሚያደርግ ሃይልን ይለግሰዋል፡፡ ለዚህም ይመስላል አባቶቻችን "የፈሩት ይደርሳል" የሚሉት፤ ምክንያቱም አንድ የምንፈራው ነገር ካለ ሌት ተቀን ስለዚያ ነገር ስለምናስብና የማንፈልገው ነገር እውን እንዲሆን በተዘዋዋሪ ስለምናግዘው ማለት ነው፡፡

የሚያሳዝነው ግን የዘመኑ ወጣት ማሰቢያና ማስተዋያ ጊዜውን እንዲያጣ ፈረንጆቹ ብዙ ሌት ተቀን መልፋታቸው ነው:: ከምታስቡት በላይም ስኬታማ ሆነዋል። … እኛ ኢትዮጵያውን ግን ገና ብዙ ስራዎች ይጠብቅብናል:: ለሚጠበቁብን የለውጥ መንገዶች ደግሞ መጀመሪያ መለወጥ ያለበት አስተሳሰባችን ነው:: የምቀኝነት፣ ተንኮል፣ ጥቅም ወዳድነት፣ ስንፍናና በሌሎች ልፋት የመበልፀግ ግብዝነት፣ ዘረኝነትና ሌሎችን የመናቅ ኩፍሰኝነት ሁሉ የሚጀምሩት ከጠባብ አስተሳሰብ ነውና መጀመሪያ መስራት ያለብን አስተሳሰባችን ላይ ነው:: አዕምሯችንን ከእነዚህ መሰል አፍራሽ አስተሳሰቦች አፅድተን ለበጎ ፍፃሜ የሚያነሳሱ በሆኑ በፍቅር፣ በአንድነት፣ በሰላምና ደስታ ላይ የተመሰረቱ ገንቢ አስተሳሰቦች እንሙላው:: ለተረዳችሁኝ በሙሉ አደራ የምላችሁ ከዚህች ደቂቃ ጀምሮ ስለአስተሳሰብና ተመስጥኦ ጓደኞቻችሁን ና ቤተሰቦቻችሁን በማሳወቅ በስውር ከተጣለብን የአዕምሮ እሥር-ቤት ራሳችሁንም ሌሎችንም ነፃ እንድታወጡ ነው።

… የዋጋ ውድነት በወጠራት ሀገር ማሰብም ተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይጣልበት በፊት ቶሎ ቶሎ እናስብ!"… አሉና ተማሪው ላይ ሳቅ ከጫሩ በኋላ ከመድረኩ ወረዱ፤

ሁሉም በአዳራሹ የነበሩ ተማሪዎች እየሳቁ አዳራሹን በጭብጨባ ሞሉት፤ ፐ/ር ዳግማዊም ባልጠበቁት ንግግር ተገርመው አብረው እያጨበጨቡ ነበር::

*** ቶ – ቶ ***

…

የቃል ፈተናው ለኢትኤል ዶርም 6 አባላት ጥሩ የሚባል ሆኖ ነበር ያለፈው::

ኢትኤል በእረፍቱ ወደ ወሎ ለመሄድ መወሰኑን ሲነግራቸው አብርሃምና ቶላ ወዲያውኑ ነበር አብረውት ለመሄድ የወሰኑት:: ትንሽ አቅማምተው የነበሩት ዘይኔና ናያድም ለመስማማት አንድ ቀን ብቻ ነበር የፈጀባቸው:: የዚያ አስገራሚ ህልም ነገር የሁሉም ጭንቅላት ውስጥ ጥያቄ ፈጥሮ ስለነበር እንቆቅልሹን የመፍታት ውስጣዊ ፍላጎት በርትቶባቸዋል:: ስድስተኛው የዶርማቸው አባል የሆነው ዮሴፍ እነርሱ ያዩትን ህልም ለማየት አልታደለም:: ነገር ግን የዶርሙ ልጆች በሙሉ እንደሚሄዱ ሲሰማ መነጠል ስላልፈለገ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ‹የወሎ ሴቶች ቁንጅና ልዩ ነው!› ሲባል ስለሚሰማ በዚሁ አጋጣሚ ለማየት በዚያውም እድሉን ሊሞክር አብሮ ለመሄድ ወሰነ:: ለእነርሱ የእንቆቅልሽ መፍቻ ጉዟቸው ሲሆን ለእሱ ደግሞ እንደ «ቫኬሽን» ያለ መፍታቻ ነበር::

እናም ነገ በሌሊት መንገድ እንደሚጀምሩ ተስማሙ:: አብርሃም ደግሞ ከመሄዱ በፊት መርየም ጋር አንድ የመጨረሻ ምሽት ማሳለፍ እንዳለበት ያውቃል:: የሞባይል ስልኩን አወጣና የመርየምን ስም መርጦ ሊደውልላት ሲል ስልኩ እጁ ላይ እንዳለ ቀድሞ መጥራት ጀመረ፤ የደወለችው መርየም መሆኗ ደግሞ እየገረመው አረንጓዴውን ተጭኖ አነሳው፤

“ሄሎ ሜሩዬ እንዴት ነሽልኝ?… አይገርምም ልደውልልሽ ስል…”

“ተቀደምሃል የኔ ቀርፋፋ፤” አለችና በስሱ ሳቀች፤ “እኔ ደህና ነኝ አልሃምዱሊላህ ካንተ ሃሳብና ናፍቆት በስተቀር… ደህና ነህ ግን?… ጠፋህብኝ እኮ!”

“ደህና ነኝ ሜሩዬ… አንድ የሚገርም ነገር ልነግርሽ ነበር” አላት በጉጉት፤

“አንተ ሲገርም በአላህ እኔም እኮ የሆነ ነገር ልነግርህ ነበር!” አለች መርየም፡ “እውነት?… እሺ ቀድመሽ ያንቺን ንገሪኝና እኔ እነግርሻለሁኝ::”

“እሺ… ካርዴ እስኪዘጋ ላውራህ፤” አለችው

“ችግር የለውም እኔም በቅርብ ካርድ ስለሞላሁኝ ከዘጋብሽ እደውልልሻለሁኝ፤” አላት::

“እሺ… ትናንት የሚገርም፣ የእውነት የሚመስል ህልም አይቼ… አንተ እኔና ሌሎች ያንተ አራት ጓደኞች ይመስሉኛል ከትልቅ ተራራ ላይ ቆመን…” …አብርሃም አፉን ከፍቶ ቀረ::

*** ዩ – ዩ ***

አብርሃም ህልሙ ላይ የነበረችው 6ኛዋ ሰው መርየም መሆኗን ካረጋገጠ በኋላ በአካል ተገናኙና እራት እየተመገቡ አብረው ወሎ እንዲሄዱ ጠየቃት:: እርሷም ቤተሰቦቿን የማሳመኛ መንገድ ፈልጋ አብረው እንደሚሄዱ ተስማምተው አሪፍ የፍቅር ወጎችን አውግተው ተለያዩ:: አብርሃም ዶርሙ ሲደርስ እነኢትኤል ስለነገው ጉዟቸው ሲጨዋወቱ ነበር የደረሰው:: ከቶላ በስተቀር ሁሉም ነበሩ::

“እኔ እኮ የፈራሁት ወሎ ከደረስን በኋላ ይህን አከረም የተባለውን ሰው ባናገኘውስ ብዬ ነው?” አለ ዘይኔ፤

“ማድረግ ያለብን እኮ ወሎ እንደደረስን ቁራኒ የሚባለውን አካባቢ አጠያይቀን እንሄድና እዚያው አካባቢ በርካሽ መኝታ መከራየት ነው:: ከዚያም ወደየቤታችን መመለሻ ብር ያህል እስኪቀረን አንድ ሁለት ቀን

አዚያው እናርፋለን:: በእነዚህ ቀናት እየዞርን አጠያይቀን አከረም የሚባል ሰው ካላገኘን ወደየቤታችን እንመለሳለን ማለት ነው:: ቀላል አይደል?" አለ ለመሄድ ከሁሉም በላይ የቋመጠው ኢትኤል፤

"እኔ እንጃ ብቻ..." አለ ናዖድ በመጠራጠር፤

"በናታችሁ ከዚህ በኋላ ወደኋላ መመለስ የለም:: አስቡት እስኪ ይሄ ያየነው ህልም ወደ «ሪያሊቲ» ቢቀየር ምን ያህል <<ኤክሳይቲንግ» (አስደናቂ) ነገር እንደሚሆን አስባችሁታል:: ስለዚህ ናዖድ በጌታ ይገፀሃለሁኝ፣ ዘይኔም በአላህ ይሁንብህ በሙሉልብ አምነንበት ነገ ጉዟችንን እንጀምር::"አላቸው፤

"እዎ እኔም እቀበለዋለሁኝ፤ እንኳን እናንተ ሴቷ መርየምም ከእኛ ጋር አብራ ወሎ ለመሄድ ተስማምታለች::" አለ አብርሃም ቀበል አድርጎ፤

"የምርህን ነው?... እንዴት?" አለ ኢትኤል በመገረም፤

"ህልማችን ውስጥ የነበረችው ስድስተኛዋ ሰው እሷ ነበረች፤ እሷም ህልሙን አይታለች::" አለ አብርሃም ፊቱ እየፈካ፤ ይህ እውነታ ከቃላትም በላይ ነበርና ሁሉም በዝምታ አዩት:: ናዖድና ዘይኔም ካለምንም ማቅማማት ለመሄድ ተስማሙና እቃቸውን ማስተካከል ጀመሩ:: የዶርሙ ስድስተኛ አባል የነበረው ቶላ ግን እስከ 5 ሰዓት ድረስ አልመጣም ነበር:: ካለወትሮው ማምሸቱ ሁሉንም ገርሟቸዋል:: ወዲያውም በግቢው ውስጥ የብዙ ተማሪዎች ጩኸት፣ ቀጥሎም ተኩስና የአምቡላንስ ሳይረን ድምፅ መስማት ጀመሩ:: የተማሪዎች ተቃውሞ መነሳቱን ገምተዋል:: ቶላ ጋር ቢደውሉለትም ስልኩ ዝግ ነበር፤ ያንን ሌሊትም ዶርሙ ሳይመጣ አደረ:: በማግስቱ ማለዳ 11 ሰዓት ላይ በሞሉት ማንቂያ ደውል ተነስተው፤ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ለመጀመር ተዘገጃጅተው እንደጨረሱ ኢትኤል ቶላ ጋር ስልክ ደወለ፤ ጠራለት::

"ሄሎ ኢታ?" አለ ቶላ፤ ድምፁ ደከም ብሏል፤

"ሄሎ ቶሊ እንዴት ነህ? ምነው ድምፅህ ደከሙብኝ?"

"አይ ደህና ነኝ፤ ከእንቅልፌ ስለቀሰቀስከኝ ነው ድምፄ የተቀየረብህ፤" አለ ቶላ ለድምጹ ሃይል ለመስጠት እየሞከረ...

"እሺ ግን በሰላም ነው ማታ ዶርም ያልመጣኸው?... በዚያ ላይ ረብሻ ነበር! አስጨነቅከን እኮ?!" አለ ኢትኤል፤

"አይ ጓደኛዬ ቢሊሱማ ጋር አድሬ ነው:: ሶሪ ስላስጨነኳችሁ::" አለ ቶላ፤

"እሺ ግን አሁን እኮ በተባባልነው መሰረት ወደ ወሎ ጉዞ ልንጀምር እየተነሳን ነው:: አትመጣም እንዴ?" አለ ኢትኤል፤

"ውይ… እኔ እንኳን አልችልም:: በቃ እናንተ ሂዱና እኔ ሰሞኑን እመጣለሁኝ::"

"ብትኖር ደስ ይለኝ ነበር ግን ካልክ ይሁን ምን አደርጋለሁኝ… ደግሞ ሁሉም <<ቻዎ» በልልኝ እያሉኝ ነው::" አለ ኢትኤል፤ ውስጡን የሆነ ነገር ቅር እያለው፤

"እሺ ሁሉንም ተሰናበትልኝ፤ መልካም መንገድ ይሁንላችሁ… በቅርቡ እንደማያችሁ ተስፋ አደርጋለሁኝ በልልኝ::" አለ ቶላ፤

"እሺ ቶሊ… ቻዎ::" ብሎ በቅሬታ ውስጥ ስልኩን ዘጋ::

ኢትኤል፣ አብርሃም፣ ዘይኔ፣ ናዖድና ዮሴፍ መለስተኛ የጀርባ ቦርሳዎቻቸውን እንዳነገቱ ዶርማቸውን ቆልፈው ወጡ:: በፌደራል የተሞላውን ግቢ አቋርጠ እቃ ማስፈተሻ ዋናው በር ጋር ሲደርሱ ቀድማቸው ደርሳ ስትጠብቃቸው ከነበረች መርየም ጋር ተገናኙ:: ሁሉም ቦርሳዎቻቸውን አስፈትሸው ከጅማ ዩንቨርስቲ ቅጥር ግቢ ወጡ:: ረጅሙን ጉዟቸውን ባንዲት እርምጃም ጀመሩ፣ ከዚያም ባንዲት ታከሲ መናኸሪያ ደረሱ፣ የጅማ አባጅፋርን ለምለም ከተማ ለቀው ጉዞ ጀመሩ:: በእውቀትም በአካልም ግዙፍ በነበሩት ንጉስ አባ-ጅፋር የተሰየሙትን በጅማና አዲስ አበባ መካከል ያሉትን ከተሞች ሰርቦ - አሰንዳቦ (ሀሰን-ዳቦ) - ደነባ - ሰኮሩ - የም (ደቡብ ከልል) - ናትሪ ላይ ዮሴፍ ጫት የገዛበት - ከዚያም አ[illegible]ልቲ (ኦሮሚያ ክልል) - አልፈው ግቤ ድልድይ ደረሱ:: እዚያም ለፍተሻ ወረዱ:: ከተደረደሩት ብዙ የፍራፍሬ አይነቶች የሚያማምሩ ብርቱካኖችን ሸመቱ:: ግዢውን የፈፀመው ኢትኤል ሊገዛ በወረደበት የታዘበው ነገር ቢኖር ተጓዦች እየጣሉት ወንዙን በከፍተኛ ደረጃ የበከለውን የፕላስቲክ ኮዳ ወይም ሃይላንዶች ክምር ነበር::

ፍተሻው አብቅቶ ወደመኪናቸው ተመልሰው ገቡና የደቡብ ክልሏን ወልቂጤ አልፈው እንደገና የኦሮሚያ ክልል ወደሆኑት ወሊሶና ቱሉ-ቦሎ ሲገቡ የኢትዮጵያ ህዝብ በክልል የማይገደብ ምን ያህል ድብልቅልቁ የወጣ እንደሆነ ታዝበዋል:: ጉዟቸው ግን ገና ብዙ ነገር የሚያሳያቸው እንደሆነ አላወቁም፤ በአስፓልት ብቻ ሳይሆን በጥበብና መንፈሳዊ መንገዶችም ጭምር ብዙ ርቀት ሊጓዙ ታጥቀው መነሳታቸውን ልብ አላሉትም:: … ገና የጉዞ ሞራላቸው ስላልተዳከመ ያን ቀን አዲስ አበባ እንደገቡ ማረፍም ሳያስፈልጋቸው ነበር ወደ ወሎ በአዳሪ መኪና የገሰገሱት::

*** ፉ – ፉ ***

## ምዕራፍ - ፺ … ወሎየው ወልይ

*መናውን ፈሰርነው አንተ ሳትናገር፥*
*ድቤውም ዋሸንቱም መሰንቆው ጭራ ኣይቀር*
*ጢጅና ጉማሬ ጫት ሰንቅም እንደምር፤*
*ጀባ ብለንሃል በዟሂር መነጸር*
*ሐሲድ የሚመታ አንድ እንኩዋን ሹም ሳይቀር።*

*(✍ ሼህ ሁሴን ጅብሪል…)*

ሼህ ሁሴን መፅሐፍ ገላጭ አልነበሩም፡፡ በ1811 ዓ.ም ገደማ በወሎ ክፍለ ሃገር በወረሄመኖ አውራጃ፣ በባዙራ ምክትል በባሆች ቀበሌ፣ ልዩ ስሙ እምበለ ሴዳ ተብሎ በሚጠራ ቦታ ተወልደው በ1908 ዓ.ም በ97 ዓመታቸው አርፈዋል፡፡

አባታቸው በዘመኑ በቃሉ አውራጃ ታዋቂ ለነበሩት ለጉታው ሼህ ቡሽራ አድረው ለሰላሣ ዓመታት በመዋሪድነት አገልግለዋል:: ጌታው ሼህ ሁሴን መፍረድ የጀመሩት ገና በሰባት ዓመታቸው እንደሆነና የሚናገሩትም መሬት ጠብ እንደማይል ተጽፏል፡፡ ‹በእ/ር ስም አሐዱ› ወይም "ቢስሚላሂ" ብለው ፍርድ የጀመሩት በአጼ ዮሐንስና በመምሬ ግርማ በተባሉ ቄስ ነው ይባላል።

በተለይ ወደፊት የሚሆነውንና የሚመጣውን ከነመፍትሔው መናገራቸውና መተንበያቸው ታዋቂነትን ቸራቸው፡፡ የሚናገሩትም በግጥም ነበር። ከዚያ ነገሥታቱም፣ መሳፍንቱም፣ ትንሹም ትልቁም እሳቸውን መጀን ማለት ያዘ። ትንቢታዊ ግጥሞቻቸውን ከአረኛ እስከ ቃዲ ያውቀዋል፣ይለዋል:: ሼህ ሁሴን የነቢዩ መሐመድ ተከታይ ነበሩ፤ እንደ ዓባይ ጠንቋይ መጽሐፍ ኣይገልጡም፣ ጠጠር ኣይጥሉም:: ግን ሱረት (ሐቀኑር) ያሸታሉ፣ ሶላታቸውን በስርዓት ያቆማሉ፤ ጫት ይቅማሉ፤ ብርዝ ይጠጣሉ፣ ፍርድም ሲፈርዱ ማለት የሚታያቸውን ሲናገሩ ብርዝ በፎሌ (በሸክና) ይዘው ነበር ይባላል:: አሁንም ግን እንደርሳቸው ያሉ ወልዮች በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚገኙ ልብ ማለት አለብን፡፡

*** ቶ – ቶ ***

አከረም የዝሁር (የምሳ ሰዓት) ሰላቱን ሰግዶ እንዳሰላመተ ራህማ እየሮጠች በሩን በርግዳ ገባች፡፡..."ጋሽዬ... ጋሽዬ..." አለች በልጅ ለዛ፤

"ምነው ራህሚ?" አላት አከረም፤ እቅፍ አድርጎ ጉንጮቿን እየሳማት፡፡

"አንተን የሚፈልጉ እንግዶች ይገቴ መጥተዋል፣" አለች፡፡

"የምን እንግዶች?" አለ አከረም ወደ በሩ ጠጋ ብሎ እየተመለከተ፤ ወድያውም አምስት ለግላጋ ወንድ ወጣቶች አንዲት ሂጃብ ከጠቀለለች ብርቱካን መሳይ ልጅ ጋር ወደእሱ ቤት ሲመጡ ተመለከተ፡፡..."ወርቄ?" አለ፡ ማድቤት ወደነበረችው ባለቤቱ እየተጣራ፤

"እወይ ውዴ" አለች ከውስጥ ሆና፤

"ነያ ወጣ በይ እስኪ አንቺዬዋ፣ ከከተሜ ግድም የአላህ እንግዶች ሳይመጡብን አልቀረም፡፡ ወጣ በይና ምሳም ቤት ያፈራውን አዘጋጂ፡ ቡናም አፍይላቸው ቆሎም አቅርበሽ ኻድሚያቸው፡፡" አላት፤

ባለቤቱ ወርቅነሽ ከማድቤት ስትወጣና እነኢትኤልም የቤቱ ደጃፍ ጋር ሲደርሱ አንድ ሆነ፤"ደህና ዋልሽ?" አለ ኢትኤል ከአንገቱ ጎንበስ ቢጤ እያለ፤... "ክብሩ ይስፋ ለመድሐኒዓለም!" አለች፤

"ይቅርታ እዚህ አካባቢ የአከረምን ቤት ማግኘት እንችል ይሆን?"

"ጌ! ልጆች የአከረምስ ቤት ይኸው አይደል፤ እኔ ደግሞ ባለቤቱ ነኝ፤ ምነው በደህና ነው?" አለች፤ ወድያው እንግዶቹ ልጆች በከፍተኛ ደስታ ተውጠው ተቃቀፉ፡፡ ንግግራቸውን ሰምቶ የወጣው አከረምና ወርቅነሽ ግራ ተጋብተው ይመለከቷቸዋል፡፡

"አፉ በሉን... እናንተን ስንፈልግ በጣም ደከሞን ተስፋ ልንቆርጥ ስንል ስላገኘናችሁ ነው በጣም ደስ ያለን፡፡" አለ ዘይኔ ግራ መጋባታቸውን ሲያይ፤

"እሺ ልጆቼ፤ በሉ አርሂቡ ወደ ውስጥ ግቡ፤ ከመንገደኛም አይደል የመጣችሁት ይደክማችኋል፡፡" አለችና ወደ ውስጥ አስገባቻቸው፤ ሁሉም አንድ አንድ በርጩማ ይዘው ቁጢጥ አሉ፡፡

"እና ምን እግር ጣላችሁ የኛ መንደር?" አለ አከረም ቡናው ተጠጥቶ ካበቃ በኋላ ቆሎ እየተቆረጠመ፤

"የማይታመን ነገር ሊመስል ይችላል፡፡... እዚህ የመጣነው ግን አንተን በህልማችን ስላየንህ ነው፡፡" አለ ኢትኤል፤ አከረምና ወርቅነሽ ለቅፅበት ተያዩና በሳቅ ፈረሱ፤

"ተዉ ልጆቼ በእመቤቴ፤ ዘንድሮ ደግሞ እንዲህ አይነት ቀልድ ጀመራችሁ እንዴ?" አለች ወርቅነሽ፤ "ወላሂ ያስቃል" አለ አከረም ቀበል አድርጎ… "እኔ ደግሞ ምን ኹኜ ነው ህልም ላይ የምታይ?"

"እርግጥ ነው እኛ እንኳን አንተን በህልም አላየንህም…"

"ዲየግ! እንዲያ በሏ ዛዲያ…"

"ነገር ግን በህልማችን ያየነው አንድ ሰው፤ ያንተን ስምና የምትኖርበትን ቦታ ስም ነግሮን አንድ ሼህ ከድር የተባሉ አባት ጋር እንደሚያገናኙን ቃሉን ሰጥቶን ነው::" ብሎ ኢትኤል ሲናገር አከረም በድንጋጤ ክው ብሎ ቀረ::

"ማን አላችሁኝ የማገናኛችሁን ሰው ስማቸውን?" አለ በአመከሮ፤

"ሼህ ከድር፤" መለሰ ዘይኔ፤

"የአላህ ያለ…" አለ አከረም በአድናቆት፤ "ምነው አከረሜ?" አለች ወርቅነሽ በሁናቴው ግራ ተጋብታ… "ማናቸው ሼህ ከድር?"

"ልጃችን በመርዝ የተነደፈች ጊዜ ዱዓ አድርገው ያዳኑልን የአላህ ወልይ እኮ ናቸው:: የሚገርመው ደግሞ እርሳቸውን የሚፈልጉ እንግዶች እኔ ጋር እንደሚመጡ ነግረውኝ ነበር::" አላት በግርምት፤ እነኢትኤል ፊታቸው ፈገግታ እያጥለቀለቀው እርስ በርሳቸው ተያዩ:: እውነትም ጉዟቸው የቃል-ኪዳን ጉዞ፤ ታማኝ መሰረት ያለው መገለጥ ኖሯል::

"እና እንዴት ነው የምትወስዳቸው ታዲያ?"

"ግ… ግመሏ…" አከረም ተንተባተበ፤

"የምን ግመል?" ሁሉም በጉጉት ጠየቁት፤

"ዛሬን እዚህ አድራችሁ እስኪነጋ መጠበቅ አለባችሁ::" አለ አከረም፤ ሼሁ የነገሩትን እያስታወሰ፤ እነኢትኤል ፍራሽና ጉዝጓዝ ተደርድሮላቸው እንዲተኙ፤ መርየም ደግሞ ከራህማ ጋር እንድትተኛ ተወሰነ:: ዮሴፍና ናዖድ ግን ቤርግ ተመልሰን እናድራለን ብለው ወጡ:: ኢትኤል ዮሴፍ ቢራ ለመቃማመስ እንደሚሄድ ገምቷል፤ ናዖድ ደግሞ መኝታው ካልተመቸው እንቅልፍ እንደማይወስደው ጠንቅቆ ያውቃል::

መርየም የማታ ሰላቷን እነአከረምን ተከትላ ከሰገደች በኋላ ለአብርሃም ምልክት ሰጥታው ወደ ውጭ ወጣች:: ትንሽ ቆይቶ ተከትሏት ወጣ::

"የኔ ፍቅር ደህና ነህ በአላህ?" አለች ገና ከመውጣቱ ጥብቅ አድርጋ እያቀፈችው::

"ደህና ነኝ ሜሩዬ… አልደከመሽም አይደል?" አላት በስስት እያያት፤

"ትቀልዳለህ እንዴ?… እንደዛሬም ተነቃቅቼ አላውቅም:: ይሄን ሁሉ አጃኢብ የሚያሰኝ ነገር ሲከሰት እያየሁኝ የምን ድካም ነው የምታወራው?"

"አይ እንደዛ ከሆነ ደስ ይላል፤ እኔ ደግሞ መንገዱ ያደከመሽ መስሎኝ ትንሽ ጨንቆኝ ነበር::"

"ሌላ ያስገረመኝ ነገር ምን እንደሆነ ታውቃለህ?… የአከረምና ወርቅነሽ ፍቅር፤ አንገቷ ላይ ያሰረችውን ትልቅ ግማደ መስቀል እያየሁኝ እንኳን ክርስቲያን መሆኗን መቀበል እስኪከብደኝ፤ እርሱንም እንደዚያ ቁርዓን አሳምሮ እየቀራ ሲሰግድ እያየሁት ሙስሊም መሆኑን እስከጠራጠር ድረስ ነበር የሃይማኖታቸው መዋሃድ ያስገረመኝ::" አለች፤

"ማርያምን እኔም ግርም ነበር ያለኝ::" አለ አብርሃም፤

"እነርሱን ሳይ ምን እንዳሰብኩኝ ታውቃለህ?…" አለችው በሃፍረት ቢጤ እየሳቀች፤ "እኔና አንተም ልክ እንደእነርሱ አብረን የምንኖርበትን ጊዜ፤"

"እውይ የኔ ማር!" ብሎ ጥብቅ አድርጎ አቀፋት::

አብርሃምና መርየም ተቃቅፈው እንደቆሙ ኢትኤል በሩን ከፍቶ ወጣ::

"ሰሪ አብርሽ አቋረጥኳችሁ… ለፅዮን እኮ ልደውልላት ብዬ ነው፤" አለ፤ በልቡ ግን ‹ምን አለ አሁን ፂያ ከጎኔ በኖረች› ብሎ ተመኝቷል፤ ባለመኖሯም አዝኗል::

"እንዴ ስልኳ ላንተ ይሰራልሃል?… እኔ እኮ ዛሬ ቀኑን ሙሉ ስሞክርላት ነበር፤ ስልኳ ይጠራል ግን አይነሳም::" አለች መርየም፤

"ምነው በጣም ፈልገሻት ነበር እንዴ?" ጠየቃት፤

"አዎ በእናትህ አንተም አልሰማህም እንዴ?" አለች መርየም ፊቷ በትካዜ እየተሞላ፤… "አልሰማሁም ምንድነው?" ኢትኤል ጠየቀ፤

"ዛሬ ለእኔም በንቱ ናት ደውላ የነገረችኝ!… ከሳምንት በላይ ዋርድ ስላልገባች ለ‹ኳሊ› ኤግዛም እንደማትቀመጥና አንድ አመት እንደምትደግም ስሟ ግቢ በር ላይ ተለጥፏል! ቶሎ እንድትመጣ ብዬ ብደውልላትም ስልክ አታነሳም:: አንድ የማውቃት የሰፈሯ ልጅ ጋር ብጠይቃትም ከእናቷ ጋር በር ቆልፈው እንደወጡ ለቀናት እንዳልተመለሱ ነገረችኝ:: ምን አልባት ካየችው ብዬ ቴክስት መሴጅ ፅፌ ልኬላታለሁኝ፤" አለችው፤

ኢትኤል በድንጋጤ እንደተሞላ ወደ ውስጥ ተመለሰ:: ሌሊቱን በሙሉ ስለፅዮን እያሰበ እንቅልፍ በአይኑ ሳይዞር ነበር ያደረው::

አከረምም በማግስቱ ዶሮ ሳይጮህ የ11:30 የማለዳ ሶላቱን ለመስገድ ሲነሳ ኢትኤልን ቁልጭ እንዳለ ነበር ያየው::

"ምነው መኝታው አልተመቸህም አይደል?" አለ በሀዘኔታ፤

"ኧረ በእውነት አይደለም:: ትንሽ የሆነች ነገር እያሰብኩኝ ነበር::" አለ ኢትኤል ድምፁ ሌሎቹን እንዳይረብሽ እየተጠነቀቀ፤

"ምነው ለኛ አይነገረንም እንዴ... የወሎ ሰው እኮ መለኛ ነው::" አለ አከረም እንደ ቀልድ፤ ኢትኤል በፅዮንና በእሱ መሃል ያለውን ረጅም ታሪክ አጠር አድርጎ አጫወተው::

"ወላሂ አብሽር የኔ ወንድም" አለ አከረም፤ "ይህች ልጅና አንተ ከልጅነት ጀምሮ ከፋት በሌለው ልባችሁ ተዋዳችሁ እንዲያደጋችሁ ነግረኸኛል:: እናንተን ያጣመራችሁ የዱኒያ ጥቅም ወይ ሌላ ተራ ነገር ሳይሆን ንፁህ ሙሃባ እንደሆነ እወቅ:: ፍቅር ደግሞ የአንዱ አምላካችን በረካ መገለጫ ነው:: እመነኝ ወንዲይሜ ፍቅርን የሰነቁ ሰዎች በጊዜና ቦታ ቢለያዩ እንኳ መገናኘታቸው የተቀደረ ነው:: እኔም ዱዓ አደርግልሃለሁኝ... አብሽር!" አለና ከተቀመጠበት ተነሳ፤ ኡዱ የማድረጊያ ኮዳውን ውሃ ሞላና ለመተጣጠብ ወደ ውጭ ወጣ:: ነገር ግን ወዲያውኑ ወደ ውስጥ ተመለሰ::

"ተነስ... ተነሱ... ሁሉንም ቀስቅሳቸው::" አለው ኢትኤልን በችኮላ፤

"ምነው ችግር አለ እንዴ?" አለ ኢትኤል ግራ በመጋባት፤

"ግመሏ!... ግመሏ እናንተን ቁጭ ብላ እየጠበቀች ነው::" ብሎ ጮኸ፤

ኢትኤል አብርሃም፣ ዘይኔና መርየምን ቀሰቀሰ:: ዮሴፍና ናዖድንም ደውሎ ጠራ:: 1 ሰዓት በኋላ ተሰባስበው እነአከረምን ለመስተንግዷቸው አመስግነው ቦርሳቸውን እንዳዘሉ ሲወጡ ወ/ሮ ወርቅነሽ ተከትላቸው ወጣች::

"ኧረገኘ አንድም ቀን ሳትደግሙ ልትሄዱ ነው?"

"አዎ እናታችን፤ ያው ጉዟችን ረጅም ስለሆነ ነው እንጂ እዚህ ብንቆይ በወደደን ነበር::" አለ ኢትኤል፤

"ካላችሁ ምን አደርጋለሁኝ:: እንኩ ቢያንስ ይህቺን አሹቅ ቆሎ ለመንገድ እንድትሆናችሁ ያዙ። ሥልቻዋ ውስጥም እርጎ ሞልቼያለሁኝ እንግዲያው እንደምትሆን አድርጋችሁ ተካፈሏት።" ብላ የቋጠረችውን ሰጠቻቸው፤ አመስግነው ተቀብለው ጉዞ ተጀመረ::

ከበራፍ ተቀምጣ የነበረችው ግመል እንደታዘዘች ሁሉ ብድግ ብላ ቆማ ወደ ሰሜን አቅጣጫ መጓዝ ጀመረች፤ እነ ኢትኤልም ተከተሏት፡፡ እየተጓዙ ሳለ፤ "አይ የኢትዮጵያ ህዝብ!" አለ ኢትኤል በሃሳቡ፤ "አይ የኢትዮጵያ ህዝብ! ከሌላው ህዝብ የሚለይ አንዳች ፀጋ አለው እኮ፡፡ ካለችው ጥቂት አብዝቶ የሚቸር፤ ችሮም የማይፀፀት፡፡ በባዶ ኪሱ ከትከት ብሎ የሚስቅ፤ ከራሱ አስቀድሞ በሞቴ እያለ ለሌላው የሚያጎርስ፤ ካነጠፋት እራፊ እንጀራ ላይ ሽሮዋን ፈሰስ አድርጎ በጥሩ ፈገግታ እንብላ የሚል የበረከት ህዝብ፤ የማያውቀው ሰው ሲያደናቅፈው "እኔን" ብሎ ራሱን የሚተካ፤ ተቸግረህ ብትከፋ ምንም ባይኖረው እንኳን "አይዞህ እ/ር አለ፤… አብሽር አላህ ያውቃል፤" እያለ የሚያፅናና ልዩ ህዝብ፡፡"

ንጋት አልፎ ለብዙ ሰዓታት ከተጓዙ በኋላ የማለዳው ብርድ በሀሩር ተተካ፡፡ ሙቀቱን ለመከላከል ግንባሮቻቸው ላይ ሽሚዝና ቲሸርቶቻቸውን ሸብ ያደረጉት እነኢትኤል የግመሉን እግር እየተከተሉ ጉዞውን ተያይዘውታል፡፡ ጫካ፣ ከዚያ ቁጥቋጦ፣ ከዚያም የገበሬ ማሳ፣ ከዚያም እልም ያለ ድንጋያማ ምድር… ሁሉም ይተካካል፡፡ ማታውን ሙሉ ፅዮንን ሲያስብ አድሮ የነበዘው አዕምሮው ላይ አሁን ራሱን ሰንጥቃ የምትገባው ፀሐይ ታከላበት ኢትኤልን ሃይለኛ የራስ ምታት ቀስፎ ያዘው፡፡… "‹ፓራስታሞል› ይዘሃል አብርሽ?" አለው ወደ አብርሃም ዞሮ፤

"‹ዳይክሎ› ነው የያዝኩት ልስጥህ?" … "ይሁን አዎ…"

"ወይ ጉድ ራስ ምታት ጀመረኽ አይደል?" አለ ዮሴፍ በሹፈት፤ "ገና ይሄ ፀሐይ የጭንቅላት ካንሰር ያስይዝሃል! ወይኔ እናቴ ምን ቀን ይሆን ስንቀለቀል የዚህ ግመል የመከተል ጉዞ አባል የሆንኩት?!"

"አንተ ወንድ አይደለህ እንዴ ኢታለቃቅስ፡፡" አለች መርየም፤ "እኔ ሴቷ እንኳን ደከመኝ አላልኩም፡፡"

መርየምና ዮሴፍ እየተከራከሩ ትንሽ እርምጃ እንደተራመዱ ግመሏ አንድ ጅረት ጋር ስትደርስ ቆጢጥ አለች፡፡

"ውይ አሁንማ ግመሏም ደከመች፡፡ በቃ እንመለስ!" አለ ዮሴፍ፤

"ይሄን ሁሉ መንገድ አቋርጠህ ከመጣህ በኋላ መመለሱ ለምን?" አለ አብርሃም፤ "ይልቅ እዚህ ጥላው ላይ ትንሽ እንረፍ፤" አለና ቦርሳውን አውርዶ የድንጋይ ጉቶ ላይ ተቀመጠ፤ ሌሎችም ተከተሉት፡፡ እፎይ ብለው ብዙም ሳይቆዩ አንድ ነጭ ጀለቢያ የለበሰ፤ ታዳጊ ወጣት እነርሱ ወደ ተቀመጡበት ቦታ ሲመጣ ተመለከቱት፤ ደርሶም እፊታቸው ቆመ፡፡

"ሰላም ለናንተ ይሁን፤" አላቸው፤

"ምን ሰላም አለ ይሄ ሙቀት እያለ፤" አለ ዮሴፍ፤

"ተወው እሱ ማለቃቀስ ስራው ነው፤ ሰላም ላንተም ይሁን::" አለ ኢትኤል ወደ ትንሹ ልጅ እጁን እየዘረጋ፤

"ሼህ ከድርን ፈልጋችሁ ነው አይደል የመጣችሁት::" አለ ትንሹ ልጅ፤

"አዎ... አዎ... እንዴት አውቀኽ ነው?" አለ ዘይኔ ከተቀመጠበት በአዲስ ሃይል እየተነሳ፤ ሌሎቹም ተከተሉት::

"እርሳቸው ናቸው የላኩኝ... ኑ ተከተሉኝ::" አለና ትንሹ ልጅ መልሳቸውንም ሳይጠብቅ ግመሏ ላይ ያለውን ገመድ ጎትቶ አስነሳትና ዞሮ መንገዱን ጀመረ:: ቦርሳዎቻቸውን በፍጥነት ተሸክመው ተከተሉት::

*** ቶ – ቶ ***

"ምንድነው ጉዱ እንደርስም እንዴ?" አለ ዮሴፍ ለ2 ሰዓታት ያህል ትንሹን ልጅ እየተከተሉ ከሄዱ በኋላ::

"አብሽር እየደረሳችሁ ነው::" አለ ትንሹ ልጅ፤ ፊቱ ላይ አንዳችም ድካም አይታይበትም::

"አንተ የሼህ ከድር ልጅ ነህ?"፤ ጠያቂው ናዖድ ነበር::

"አይ አይደለሁም:: እኔ በእርሳቸው መድረሳ ውስጥ ሂፍዝ የማጠና ደረሳ ነኝ::" አለ ትንሹ ልጅ፤

"ኧረ እባካችሁ በአማርኛ እንነጋገር፤" አለ ዮሴፍ እየሳቀ፤

"እኔ እነግርሃለሁኝ... መድረሳ ማለት እንደ ቄስ ት/ቤት ሆኖ ቁርዓንና እስላማዊ አስተምሮቶች የሚሰጥበት ቦታ ሲሆን ሂፍዝ ደግሞ ሙሉ ቁርዓንን በቃል የመያዝ ረጅም አመት የሚፈጅ ሸምደዳ ነው:: ደረሳ ማለት ደግሞ ተማሪ ነው::" አለና ዘይኔ አብራራላቸው፤

"እና እዚህ እልም ያለ ምድረ-በዳ ውስጥ ታዳጊዎች የሚማሩበት የሙስሊም ት/ቤት አለ ነው የምትለኝ?" አለ ኢትኤል በጥያቄ መልክ ወደ ልጁ እየዞረ::

"አዎ 10 ነን አልሃምዱሊላህ፤ እኔ ግን ከሁሉም በእድሜ ትንሹ ስለሆንኩኝ ለመላላክ ይመርጡኛል::"

"ቆይ እንዴት አውቃችሁት ነው እዚህ ድረስ ለመማር የምትመጡት በአላህ?" ጠየቀች መርየም፤

"እኛ አይደለንም አውቀን የምንመጣው፤ በአላህ ፍቃድ ገና ከህፃንነታችን ጀምሮ ለመድረሳው እንድንሆን የተመረጥን መሆኑን የሚያውቁት ራሳቸው ሼህ ከድር ናቸው:: እራሳቸውም ናቸው ቤተሰባችን ድረስ ሄደው

ወላጆቻችንን በማስማማት ይዘውን የሚመጡት:: ትልቅ የአላህ ወልይ ስለሆኑ ማንም እርሳቸውን እንቢ አይልም::"

"እና ግን ቤተሰቦቻችሁን አታገኙም ማለት ነው?" መልሳ ጠየቀችው፤

"በሁለት አመት አንዴ እንድንሄድ ይፈቀድልናል ግን ስለዚህ ስፍራ እንድንነግራቸው አይፈቀድልንም::" አለ፤

"እሺ ግን ምግብ ምናምንስ ከየት ታገኛላችሁ?" አለው ኢትኤል፤

"በቀን ውስጥ ሁለቴ ብቻ ነው የምንመገበው፤ በሳምንት ውስጥ ደግሞ ከረመዳን ወር ውጪ ሰኞና ሐሙስን እንፆማለን:: በመድረሳችን የጓሮ አታክልትና ፍራፍሬ እናሳድጋለን፤ ስንዴም እንዘራለን፣ 3 ግመሎችና 5 ላሞችም አሉን:: አልሃምዱሊላህ፤ የእርሳቸው በረካ ለጉድ ስለሆን አጥረት አያጋጥምም:: ድንገት ቢያጋጥም እንኳን ሁለት ደረሳዎች ሆነን ማዶ ካሉት ገበሬዎች ተርቲብ እንሰበስባለን::"

"ይገርማል፤ ምን አይነት ነው ግን መድረሳቹ… ማለቴ ትልቅ ቤት ወይስ?" ብሎ ዘይኔ ጥያቄውን ሳይጨርስ ልጁ ቀበል አድርጎ፤ "ምን አስቸኮለኽ ወንድሜ? ይኸው ደርሰናል የለ እኮ! ራስህ ታየዋለህ" አለው፤ ቆሞም ግመሏን ካንድ መሬት ተምሶ ከተሰካ ጣውላ ቢጤ ላይ ሸጥ አድርጎ አሰራት::

መሽትሽት እያለ ነበር:: በዚያ ላይ ሁሉም ደክሟቸዋል፣ ርቧቸዋል፣ ውሃ ጠምቷቸዋል:: ሁሉም ልጁ መድረሳ ያለው መዳረሻ ደርሰው ጀርባቸውን እስኪያሳርፉ ጓግተው ነበር:: ነገር ግን ትንሹ ልጅ እያደረገ ያለው ነገር እንቆቅልሽ ነበር የሆነባቸው፤ አውላላ ሜዳ ላይ ቆሞ "ደርሰናል" ሲል እያፌዘ መሆኑንም ተጠራጥረዋል:: ከፊትለፊታቸው ከቆመው ግዙፍ አለት በስተቀር ባዶ ስፍራ ነበር:: "ኧረ ፈላው ሙድ እየያዘብን ነው መሰለኝ?" አለ ዮሴፍ፤

ትንሹ ልጅ ግን፤ "ኑ ተከተሉኝ!" አለና ከአለቱ ስር ባለች ጠባብ ኩርባ ዞረ፤ ተከተሉት:: በአለቱ ጀርባ በኩል ትልቅ ከብ ድንጋይን ተመለከቱ:: ከስሩ ወለሉ ላይም እንደመንሸራተቻ የሚመስል ረጅም ሸንቁር አለ:: ትንሹ ልጅም ከሸንቁሩ ስር አንዲት ትንሽዬ አሎሎ ሲገፋ ትልቁ ከብ ድንጋይም ከብልል አለ:: በቀኙ በኩል ሁለት ሰው ጎን ለጎን ሊያስገባ የሚችል ከፍተት ተፈጠር:: ከውስጥ እንደሙዚቃ ያለ ድምጽም መሰማት ጀመሩ::

"ኑ ግቡ!" ብሏቸው ወደ ውስጥ ዘለቀ፤ እነኢትኤል በአድናቆት ፈዘው ከቆሙበት ለመንቃት ሰኮንዶች አስፈልገዋቸው ነበር:: ወደ ቀልባቸው እንደተመለሱ ተከታትለው ወደ ውስጥ ገቡ::

*** ዶ – ዶ ***

♫ *"መርሃባ ነቢ መርሃባ... አሰላማሊይኩም፥*

*መርሃባ ነቢ መርሃባ... አሰላማለይኩም፥*
*በሐረር በጓጉ በንጉስ በሃና*
*ጌትዬዋ ሲሮ ለጉድ ዘለቀና*
*ምድሬ ላይ ዘነበ - የሃድራው ደመና*
*እንደ አባይ ጎረፈ - ረጋ እንደጣና::" ...*

የሼህ ከድር ጥዑም መንዙማ በአንድ ወጣት ደረሳ ድቤ ድብ... ድብ... ድብታ እና በሌሎቹ ጭብጨባ ታጅቦ ሃድራውን አደማምቆታል:: ከላይ ከዋሻው መካከል ላይ ባለ ምሶሶ ላይ የተሰቀለው ማሾ ከ60 ሻማ አንፖል ያልተናነሰ ብርሃንን ይፈነጥቃል::

ሼህ ከድር ልክ እነኢትኤልን እንዳዩ እግራቸውን አነፋረው ከተቀመጡበት ተነሱና ወደ እነርሱ መጡ:: ሁሉንም ወንዶች እያቀፉ ሰላም አሏቸው፤ መርየምን ደግሞ ግንባሯን ሳም አደረጓት::

"አርሂቡ ውድ ልጆቼ... እናንተ ለእኔ እንደዚህ ትውልድ አምባሳደሮቼ ናችሁና በክብር ነው የምቀበላችሁ::" አሉ፤ በደስታ እንደተሞሉ::

"ተፈደሉ... እስኪ ቁጭ በሉ... ና ማነህ ጃዕፈር እስኪ ወተት ቅዳላቸው፤ ሙልሙል ካለም አቅርብላቸው::" ብለው አዘዙ፤

ከቀርከሃ በተሰሩ ኩባያዎች ትኩስ ወተት ተሰጣቸው፤ ሙልሙልም ተቆራርሶ በሰፌድ ቀረበላቸው:: ልክ በልተው እንዳበቁ አንዱ ልጅ የማታ ኢሻ ሰላት አዛን አለና መርየምና ዘይኔን ጨምሮ በሼህ ከድር መሪነት አሰገዷቸው::

ሰላቱ እንዳበቃ ቁጭ ብለው ሙስበሃቸውን ሲቆጥሩ የነበሩት ሼህ ከድር፤ "እስኪ ሁላችሁም ወዲህ ሰብሰብ በሉ፤" አሉ የማሾው መስቀያ ምሶሶ ስር ደገፍ ብለው እየተቀመጡ:: ደረሳዎቹና እነኢትኤልም ከበዋቸው ተቀመጡ:: "እነዚህ ልጆች ከጅማ አባ-ጅፋር ድረስ ለኢልም (እውቀት) ብለው የመጡ ናቸው፤ መሄጂያቸውም ገና ሩቅ ስለሆነ ኢንሻላህ ሦስት እውነተኛ ታሪኮችን በተቻለኝ ፍጥነት እነግራችሁና እሸኛቸዋለሁኝ፤ በጥሞና አድምጡኝ::" አሉና በተቀመጡበት ተመቻቹ::

"ውድ እንግዶቼ እነዚህ ታሪኮች በቁርዓንና ሃዲስ ላይ ብቻ ሳይሆን በወንድሞቻችን ክርስቲያኖች ቅዱስ መፅሀፍትና የታሪክ መዛግብት ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን እንዲያውቁ እፈልጋለሁኝ:: "አይ አሻፈረኝ አንተ ሽማግሌ ነህ! ታሪክ ትረሳለህ፤" ካላችሁኝም ሄዳችሁ ብታጣቅሱ ‹‹ያ ሼባ ልክ ነበር ለካ›› እንደምትሉ አልጠራጠርም::" አሉና ስቀው አሳቋቸው፤

"… እስኪ ትረካዬን ለመጀመር ያኸል አብረን በምናብ ዘመንን ወደኋላ እንቅዘፍ። 1500 ድፍን ዓመታትን ወደኋላ ተጉዘን፤ ከለተና ሰልስተ ሺህ ኪሎ ሜትሮችን ወደ ሰሜን ብንጓዝ ራሳችንን የጥንቱ የአረ-ቢያ ቁረይሽ ምድር ላይ እናገኘዋለን። በእጃቸው ከጭቃና አሸዋ ቀርፀው ያበጇቸውን አሻንጉሊት ጣዖቶች የሚያመልኩ፣ ኢ-አማኞች በሞሉት ምድር ውስጥም እንዋትታለን። እንደበረሀው ሀሩር ጭንቅላታቸው የደረቀ፣ ሴት ልጆቻቸውን ከነህይወታቸው የሚቀብሩ ባለህገ-አራዊት ሰዎች መሀል እንባዝናለን። የእየሱስ ክርስቶስን አስተምህሮ አልቀበልም ያሉ፣ የሙሴን ህግ ማፈኛ ያደረጉ ከህዲዎች በሀብታቸው ኩራት ትናጋ ተወጥረው፤ በሀጢያት ያጨማለቋትን የአብርሀም ልጅ የእስማዔል የተስፋ ምድር መካን የአሁኗ ሳውዲ አረቢያን እናስባት። አብርሀም ጣዖታትን አፈራርሶ የፈጣሪን መካነ ማደሪያ የገነባባት መካ እውነትን የካዱ ሰዎች ወረዋት የጣዖታት መፈንጫ ሆና ነበር። ካዕባ ውስጥም ብዙ ጣዖታት ተሰግስገውበት ነበር፡፡

በወቅቱ የነበረውን የስህተት መንገድ የተመለከቱ ክርስቲያንና አይሁድ መምህራን ሁኔታውን ለመቀየር ብዙ ደክመዋል። ግና ይህ ነው የሚባል ለውጥ ማስገኘት ሳይችሉ ቀሩ። ለዚህ ዝቅጠት መድሃኒት ይልከላቸው ዘንድም ከአላህ (ኤሎሄ) ተዕምርን ጠብቀው ከመቀመጥ በቀር የነበራቸው አማራጭ አልነበረም።

….በዚህ ተስፋ አስቆራጭ ወቅት ውስጥ ነበር ከአብርሃምና ከኢትዮጵያዊቷ የሣራ ባሪያ አጋር ልጅ ከእስማኤል ዘር ከሆነው ከበኒ ሐሺም ጎሣ ሙሐመድ የተባለ ጨቅላ ልጅ ወደዚህች ምድር የተቀላቀለው። ለጨለመው የአረቢያ ምድርም ሰላምን ያበሰረው። ገና በጨቅላነቱ እናቱን አሚናን ያጣው ይህ ህፃን ጡት አጥብታ እንደ ሁለተኛ እናት ተንከባክባ ያሳደገችው ኡሙ አይመን የተባለች ኢትዮጵያዊት ባሪያ ነበረች፡፡ ታድያ በወጣትነቱ ምግባረ ምስጉን የነበረ ሙሐመድ በ40 ዓመቱ፤ "ፈጣሪ አንድ ነው!" የሚል ‹የተውሂድ›፣ ወይም የእኛ ክርስቲያኖች እንደሚሉት የ‹ተዋህዶ› አስተምህሮት ይዞ ሲመጣ የቅርብ ዘመዶቹ እንኳን ሳይቀሩ 'አበደ' ነበር ያሉት። 365 ጣዖታት መሥዋዕት እየቀረበላቸው በሚመለኩበት ዘመን ፈጣሪ አንድ ነው ማለት የፌዝ ፌዝ ነበርና።

…. ይህንን ለወቅቱ ኗሪዎች ግራ የሆነ መልዕክት ይዞ ሲነሳ ግን ከጎኑ ሊቆሙ የፈቀዱት ህሊናቸው የበራ ጥቂት የቅርብ ወዳጆቻቸው ብቻ ነበሩ፡፡ ይልቁንም ነብዩ መሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) እና ተከታዮቻቸው ከጣዖት አምላኪዎች ከፍተኛ የሆነ ፈተና ነበር የገጠማቸው። ተሰደቡ፣ ተዘረፉ፣ ተሸማቀጡ፣ ተደበደቡ … በስተመጨረሻም ተሰደዱ። እርሳቸው በመጀመሪያ ጧይፍ ወደ

ምትባል ሃገር ጥገኝነትን ለማግኘት ቢ.ስደዱም እዚያም የድንጋይ ውርጅብኝና ዘለፋ ነበር የተቀበላቸው:: በዚህ የጭንቅ ጊዜም አንድ ጥሩ ክርስቲያን እንደረዳቸው ተዘግቧል። ቀጥሎ እርሳቸው ወደ መዲና ከተማ ሲጓዙ ሌሎች በርካታ ተከታዮቻቸውን ደግሞ የፈጣሪና የፅድቅ ሀገር ወደ ነበረችው ወደኖይቷ ቅድስት ምድር ኢትዮጵያ ላኳቸው። ነብያችን ከዚያ በፊት የኢትዮጵያን ምድር አይተዋት ባያውቁም ውስጣቸው ግን ቅድስነቷንና የነብያት መጠጊያነቷ ነግሯቸው ነበርና!

**"ኢትዮጵያ የእውነት ሀገር** ናት:: በውስጧም ሰውን የማይበድል እርሱም ዘንድ አንድም የማይበደል ንጉስ አለና ወደዚያ ብትሄዱ መልካም ነው::" ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ቃል በቃል እንደዚህ ነበር ያሉት:: ልብ በሉ ልጆች ኢትዮጵያ የእውነት ወይም የሃቅ ሀገር ነች ነው ያሉት ረሱላችን (ሰ.ዐ.ወ):: ሃቀኝነት ደግሞ አላህ ሱብሃነ ወታዕላ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የእምነት መገለጫ እንደሆነ ነግሮናል:: "ወተዋሰው ቢል ሃቂ ወተዋሰው ቢ' ሰብሪ" ብሎ በእውነተኝነትና ትዕግስት ውስጥ የሚዘወትሩ ሰዎችን የእምነትና በጎነት ደረጃ ጋር አስተካክሎ ኪሳራ ውስጥ እንደማይገቡ ይነግረናል::

አንዳንድ ፈትዋ ሰጪዎች ይህ ቃል የሚወክለው የያኔይቱን እንጂ ያሁኗን ኢትዮጵያ አይደለም ብለው ሲሞግቱ ሳይ ይገርመኛል:: አወለን ሃዲሱ ላይ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) የአሁኖቹ ወይም የወደፊቶቹ ሳይሆን በደፈናው ‹ኢትዮጵያ› ነው ያሉት፤ በሌላ ሃዲሳቸው ላይ ደግሞ ሙስሊሞች "ኢትዮጵያውያኖች መጥተው ካልወጓችሁ አትንኳቸው፤" ብለው ማዘዛቸው ለሃበሻ ምድር ያላቸውን በጊዜ ያልተገደበ ክብር ያሳያል::

አለይኩሊ ያህል ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አምነዋቸው የወንድማቸውን ልጅ ጃፈርና ሌሎች 16 የመጀመሪያ ሙስሊሞችን ቀይ ባህርን ተሻግረው ኢትዮጵያ እንዲሄዱ ላኳቸው:: ያኔ የነበሩትም የኢትዮጵያ ንጉስ - ነጋሲ ግርማ-አስፈሪ ሲሆኑ፤ የክርስትና ተዋህዶ አማኝ ነበሩ:: እጅግ ፍትሐዊና አስተዋይ መሪም ነበር:: ጥሩ ክርስቲያን ምሳሌ ከመሆኑ ብዛት ‹‹አጥልቋል በአንተ የተውሂድ ገመድ›› እያሉ መንዙማ ይገጥሙለት ነበር የድሮ ወልዮቻችን::" አሉና ፊታቸው ላይ ልዩ ፈገግታ እየታየ እነኢትኤልን አንድ በአንድ ተመለከቷቸው፤ ሁሉም በተመስጦ እያዳመጧቸው ነበር::

"እኒህም ያኔ የነበሩ የሃበሻ ንጉስ እርግጥም ነብያችንን ያላሳፈሩ ታላቅ ሰው ነበሩ:: እሙ ሰላማና ሌሎችም በዘገቡት ሐዲስ መሰረት ወደ ሃበሻ የተላኩት ስደተኛ ሶሃባዎች የትልቅ እንግዳ አቀባበል ነበር የተደረገላቸው:: ንጉሱ ባለ ወርቀ-ዘቦውን የቤተ-መንግስታቸውን መጋረጃ አስወርደው አሳጥበው፤ ቀይ

ምንጣፍ አስነጥፈው ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም በወርቅ ያቆጠቆጠ አክሊል ደፍተው የንግስና ካባቸውን ደርበው፣ እንዲሁም ኢትዮጵያውያን የክርስትና ካህናቶቻቸውን በክህነት ልብሳቸው እንዲገኙ አዘው ነበር የጠበቋቸው:: መጠጊያ ፍለጋ ከመጡት 17ቱ የመጀመሪያ ሙስሊሞች መካከል አንዷ የነበረች ኡሙ ሰላማ (ረ.0) እንደተናገረችው፤ ንጉስ ግርማ-አስፈሪ እና የተዋህዶ ካህናቶቹ ከሚያምር አለባበሳቸውና መለኮተ-ፀባያታቸው ጋር በተርታ ቆመው ሲቀበሏቸው ‹ግርማ-ሞገሳቸው ያስፈራ ነበር› ብላለች::" አሉና ሼህ ከድር ዙሪያቸውን ቃኘት ቃኘት አደረጉ፤ "ማነህ ልጅ አቡበከር፣ እስኪ ሱረቱል ማኢዳህ (የማእድ ምዕራፍ) ቁጥር 82ና 83ን ቅራልን" አሉት፤ ሙሉ ቁርዓንን በቃሉ የሸመደደው ሃፊዙ አቡበከር በሚያምረው ድምፁ አንቀፆቹን ቀራቸው::

"አሁን አቡበከር የቀራላችሁ አንቀፅ በአማርኛ ሲተረጎም እንዲህ ይነበባል ‹በእርግጥም! ከአይሁዳውያን፣ ከከፉ ከሃዲዎች እና ከሰዎች መካከል ሃያላን ተብለው የሚጠሩትም ለአማኞች ወይም ሙስሊሞች በጠላትነት ይነሳሉ፣ በተቃራኒው ደግሞ እነዚያ "እኛ ክርስቲያኖች ነን::" የሚሉት ግን ለአማኞች ወይም ሙስሊሞች የቅርብ ወዳጆች ሆነው ታገኛቸዋለህ! ይህም የሆነው ጥሩ ቀሳውስትና የማይኮሩ ወይም ዓለምን የናቁ መነኮሳት በእነርሱ ዘንድ ስላሉ ነው::" እንደ ማለት ነው:: ከዚህ የሃዲስ ሳይሆን የፈጣሪ የአላህ የራሱ ቃል ከሆነው አንቀፅ እንደምንረዳው የክርስቲያኖችና ሙስሊሞችን ህብረት ጥልቅ መሆኑንና፤ አላህ የተዋህዶ ክርስቲያኖች ካህናትና መነኮሳትን በግልፅ እንዳወደሳቸው ነው::

"የአላህ!" አሉ ሼህ ከድር በግነት… "የአላህ! ባንተ መሞገስ ምን ያህል መታደል ነው!… ብቻ ወደ ታሪኩ ስንመለስ ከዚህ ከተረጎምኩላችሁ አንቀፅ ስር ያለው አንቀፅ በፍቺ ደረጃ ወደ አማርኛ ሲተረጎም፤

‹‹እነዚያ ለነብያችን ያወረድነውን ሰሚዎች የሆኑት የኢትዮጵያ ካህናቶች ቁርዓኑ በተነበበላቸው ጊዜ እውነትን ስላስተዋሉ አይኖቻቸው በእንባ ይሞላል፤ ‹እኛንም ከአማኝ ምስክሮች መካከል ፃፈን› ይላሉ::›› እንደ ማለት ይሆናል::

ይህ ቁርዓንም የወረደው ንጉስ ግርማ-አስፈሪ ሶሃቦችን የተቀበሏቸው ጊዜ የተከሰተውን ሁኔታ ለማመልከት ነው:: ባይገርማችሁ ጣዖት አምላኪ የነበሩት የአረብ ቁረይሾች ያባረሯቸው ሙስሊሞች በኢትዮጵያ ምድር መጠጊያ መጠየቃቸውን በሰሙ ጊዜ እየከነፉ ነበር ወደዚህ የመጡት:: ሲመጡም ንጉስ ግርማ-አስፈሪን መደለያ የሚሆን እጅግ ብዙ ወርቅና

ሌሎችም ስጦታዎች ይዘው ነበር:: ሃሳባቸውም ስጦታቸውን ለንጉሱ አቅርበው በምትኩ ስደተኞቹን ሙስሊሞች አስረው ለመውሰድ ነበር:: ታዲያ ያ ፍትሃዊ ንጉሳችን ካመጡት የመደለያ ስጦታ አንዲቷንም ሳይነካ ነበር ለውሳኔ የሰበሰባቸው:: ንጉስ ነጃሺ ሙስናን አልቀበልም ያሉ የመጀመሪያው መሪ ይሆኑ እንዴ?" አሉ ሼህ ከድር እየሳቁ፤ ሁሉም አጀቧቸው::

"ታዲያ በፍርዱ ቀን ቁረይሾች ‹‹እነዚህ ሰዎች ጣዖቶቻችንን ከደዋልና እንድናስራቸው ይሰጡን›› ብለው ከጠየቁ በኋላ ለሙስሊሞቹ ደግሞ እንዲናገሩ እድል ተሰጣቸው:: የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የወንድም ልጅ የሆነው ጃዕፈርም ወደፊት ቀረበና ለንጉሱ ነብዩ ሙሐመድ ከመነሳታቸው በፊት ይኖሩበት የነበረውን የጨለማ ህይወት አስረዳ:: አሁን ግን ተውሂድና ስነምግባርን የሚያስተምር አንድ ነብይ እንደተላከላቸውና ቁርዓን የሚባል ቅዱስ መፅሐፍ እንደወረደላቸው ተናገረ:: ንጉሱም ድንግል ማርያምን እጅግ የሚወዱና የሚያከብሩ ሰው ስለነበሩ ስለእሷ ታሪክ በቁርዓን ውስጥ እንዳለ ጠየቁት:: እሱም መኖሩን ነግሯቸው ቁርዓኑን ከፍቶ ሱረቱል መርየምን ቀራላቸው:: ማርያም በምጧ ጊዜ ያጋጠማትን ስቃይ የሚተርከ አያ ሲያነብላቸው ንጉሱን ጨምሮ ሁሉም ካህናት ነበሩ በእንባ የተራጩት:: ወዲያውም ነበር ለሶሃቦቹ ምግብና ማረፊያ እንዲሰጣቸው ያዘዙት::

እንግዲህ በዚህ መሰል አስገራሚ ታሪክ ወደ ኢትዮጵያ የገባችው እስልምና ሃይማኖት ነው በፍቅርና ሰላማዊ መንገድ ተስፋፍታ እዚህ የደረሰችው:: ይህንን ካወቅን የሙስሊሞችንና ክርስቲያኖችን ወንድማማችነትን የሚቃወም ሙስሊምም ሆነ ክርስቲያን በስህተት መንገድ ውስጥ እንደሆነ መረዳት አለብን:: አሁን ላይ በዓለም ዙሪያ እያየን ያለነው ነገር ግን በጣም አስፈሪ ነው:: በምዕራባዊ ካፊሮችና ጥቅም ወዳዶች ምክንያት የእስልምናና ክርስትና ገፅታዎች እየተበላሹ፤ በመሃላቸው ያለውም ውብ ታሪክ እንዲደፈርስ እየተደረገ ነው::

በቅዱስ-ቁርዓን ውስጥ "ላ ኢቅራ ፊ ዲን!" (2:256) ብሎ በሃይማኖት ማንንም ማስገደድ እንደሌለ አምላካችን አላህ በግልፅ ቢነግረንም፤ "ለሰው ልጅ ያላዘነ እኔ አላዝንለትም፤" ብሎ በቅዱስ ቃሉ ቢያስጠነቅቀንም እንጀራ ፍለጋ ከሃገራቸው የወጡ ምስኪን ሰዎችን በሃይማኖት ስም እስከ ማረድ ድረስ አረመኔያዊ ተግባሮች በአደባባይ ሲፈፀሙ እያየን ነው:: ራሳቸውን የክርስቲያን ሃገራት ነን ብለው የሚጠሩ ምዕራባውያን አስልጥነው የመሰረቷቸው እነዚህ ሙስሊም ተብዬ ተቋማት ብዙ የእስልምናን ስም የሚያጠፉ ስራዎች ይሰራሉ::

እውነቱን ቢያውቁትስ ሙስሊም ማለት የሰላም ህዝብ እንጂ አሸባሪ አይደለም:: ሃገራት ለእነርሱ ህግጋት እንገዛም ባሉ ቁጥር የሰው ሃገር

የሚወሩት እነርሱ፣ ሆቴል ወይ ጭፈራ ቤት ሳይሆን ሙሉ ከተማና ሙሉ ሃገር የሚያሸብሩት እነርሱ:: በአስራና መቶዎች የሚቆጠሩ ሳይሆን በቦንቦችና ሮኬቶች መቶ ሺዎችን የሚፈጁት እነርሱ ናቸው::

ዳሩ ሚድያው በእጃቸው ነውና ዓለም የሚያምነውም እነርሱኑ ነው:: በየሳምንቱ በግፍ የሚፈሰው በሺዎች የሚቆጠሩ የሶሪያ፣ የሊቢያና የየመን ህፃናት ደም ዘበት ይመስል አውሮፓ ወይ አሜሪካ 10 ሰው ከሞተ ግን ዜናው ይራገባል። ሁሉም ተንታኝ ለጥቃቱ እስልምናን ለመውቀስ ይሯሯጣል። ምክንያቱም ጦርነቱም ሆነ እርስ በርስ መጠፋፋቱ የሀይማኖት ስምን ሽከፎ ተካሂዷልና ነው።

የትክክለኛው የክርስትናና እስልምና አስተምህሮ እንዲሁም የአብሮነት ታሪካቸው እንዲረሳ ሸይጣን ብዙ ብዙ ስራ ሰርቷልና! አሁን ላይ ሁለቱ ሃይማኖቶች ጥላቻ ሆኗል መቋጫቸው፣ ደም መፋሰስ ሆኗል ግብራቸው።"

"... ያም ሆኖ ግን አልሃምዱሊላህ" አሉ ሼህ ከድር ፊታቸው ላይ ተፈጥሮ የነበረው ጭጋግ እየተገፈፈ፣ "አዎ አሁንም ቢሆን አልሃምዱሊላህ፣ ከቅድስት ምድራችን የፍቅር ብርሀን አሁንም አልጠፋም! እንደኔ እምነት መካ የምትገኝባት የሳዑዲ አረቢያ ሃገር እንኳን ጥጋብ ወጥሯት ምስኪኖቹን የመኒዎች በቦንብ በምትደበድብበት በዚህ አስቀያሚ ዘመን ትክክለኛውን የእስልምናና የክርስትና መንገድ እየተከተልን ያለነው እኛ ኢትዮጵያውያን ነን ብል አጋንኜ እንዳይመስላችሁ።"... ብለው ካጣጠፏቸው እግሮቻቸው መካከል አንዱን ዘረጉና ቀጠሉ፣

"ምንም እንኳን የሀይማኖታቸው እውቀት ያልገባቸው ጥቂት 'እኔ ብቻ አውቃለሁኝ' ባይ ሰዎች ፀብና መለያየትን ለመፍጠር ቢሞክሩም የኢትዮጵያ ሙስሊምና ክርስቲያን ህብረተሰብ ትዕዛዛቱን ከሌሎቹ በተሻለ እየተከተለ መሆኑ እሙን ነው። በዚህ ዘመን ያሉ ወጣት ሙስሊሞች ግን እንደአባት አያቶቻቸው ኢትዮጵያዊነቱን ያልቀቀ ውብ እስልምና እየተከተሉ ነው ለማለት ግን አልደፍርም:: በርካቶቹ የዚህች የአሜሪካኖች አሻንጉሊት በሆነች ሳውዲ አረቢያ ግዞቶች ናቸው:: ኢትዮጵያዊ የሆነውን የጥንት ገናና እስልምና መርሳታቸው ሳያንስ አንዲት ኪታብ ባነበቡ ማግስት የኪታብ ቤተ-መፅሐፍት የሆኑ ኡለማ አባቶቻቸውን ሲያንቋሽሹ ይስተዋላሉ::

እንደነገርኳችሁ ኢትዮጵያ እንደ ሃገር እስልምናን እጆቿን ዘርግታ የተቀበለችው ከመካ ና መዲና ራሱ ቀድማ ነው:: በዚህ ረጅም እድሜዋ ደግሞ እልፍ የሃይማኖቱ ሊቅና ወልዮችን አፍርታለች፣ የራሷ ወዝ ያለው እስላማዊ ባህል አዳብራለች:: ይህቺ ኢትዮጵያ የሚሏት ቀላል የሁብ ምድርም እንዳትመስላችሁ!

ሙፍቲ ዳውድ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት በርካታ መፅሐፎችን በ17 ግመሎች አስጭነው ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ በመግባት ወሎ ውስጥ የለኮሱትን የጥበብ ችቦ ተረክበው ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላለፉ ብርቅዬዎች መብቀያ፣ መለኮታዊ መሰላልን እስከጫፍ የወጧት፣ የነሼህ ሙሐመድ ሻፊ አገር፣ የነሼህ ወረባቦ፣ የነሼህ አባድር፣ የፈቂህ ዙበይር አገር፣ የነ ጀማሉዲን (አኒዬ)፣ የነሼህ ቃጥባሬ (ጉራጌ) ፣ የነሼህ አህመድ አለም (የዳናው)፣ የነ ሐጅ ቡሽራ (የገታው)፣ የነ አብርሄት፣ የነ ሸረፈዲን ኢብራሂም (የቦረናው) ፣ የእነ አባ ጅፋር (ጅማ)፣ ሙሂብ አልከሲዬ(የስልጢ)፣ የነ ሸህ የህያ ዩሱፍ (የወረሂምኑው) ሃገር ኢትዮጵያ የነ ጦልሃ ጃዕፈር አገር፣ የነ ጌትዬ አገር . . . እንዳሁኑ ዘመን የሃይማኖት ፍንዳታ ወጣቶች ‹ዲኔ› ‹ዲኔ› ማለት ብቻ ሳይሆን ሃቂቃውን የዲን መሰረትም ጠንቅቀው ያወቁ፤ የአረብ የቋንቋ ሊቆችን ትክሻ ለትከሻ መጋፋት የሚያስችል አቅም የነበራቸው የነህው (grammer syntax) ሊቅ የነ ሸህ ሾንኬ፣ የነሸህ ሰይድ ሷዲቅ፣ የነ ታጁዲን፣ የነ ሸህ ወሌ፣ የወሎው ሼህ ሁሴን ጅብሪል ሀገር ናት፤ ኢትዮጵያ!" ፤ ሲናገሩ በስሜት ተሞልተው ነበር::

..."እርግጥ ነው በታሪካችም አንዳንድ ፅንፈኛ ክርስቲያን ንጉሶችና በአክራሪ አሚሮች መካከል ጦርነቶች ተካሂደው የነበረ ቢሆንም ለሃቂቃ በቆሙ የሃይማኖት አባቶች ብርታት አንድነታችን ሳይፈርስ ቀጥሏል:: እነዚህ ታላቅ ኡለማዎችም ሆኑ አሁንም ያሉ ተተኪዎቻቸው የእስልምና ሃይማኖትን ትክክለኛ ጥበብ ስለሚያውቁ የሌላውን ሃይማኖት አይነኩም:: አንድ እውነተኛ የኢትዮጵያ ሙስሊም እንኳን ክርስቲያን ወንድሙን ለመጉዳት ማሠብ ይቅርና ለማስቀየም እንኳን ቢዳረግ ምህረት ከጠረገው የነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) መንገድ እንደራቀ ያውቃልና ነው። ክርስቲያኑም እንደዚያው አብሮ መኖርና ፍቅርን ከእየሱስ ክርስቶስ (ዐ.ሰ) በሚገባ ተምሯልና ለደም መቃባት አይነሳም። ፈጣሪ የባረካት ምድር ላይ ነንና በፍቅር እንኖራለን:: ለስሙ በሸሪያ ነው የምመራው በምትል፤ መኳንንቶቿ አሚሮች ውስኪና ቆነጃጅት በገፍ ከሚገቡላት፤ ብሎም ጎረቤቷ ያሉትን ንጹህ የመናውያን ለጥቅም ስትል በጦር ጀት እየደበደበች፤ ሰው እየገደለች ለሮቦት ግን ስንትና ስንት ብር አፍስሳ አሥርታ ለብረት የሰው ዜግነት ከሰጠችው ያሁኗ ሳኡዲ የሚጠነክር እንጂ የሚያንስ የዲን ትግበራ የለንም። ማህበራዊ አኗኗራችን ከኛ አልፎ በጦርነትና ሽብር ለምትናወጠው ዓለም ምሳሌ ሊሆን የሚችል እንደሆነ እሙን ነው።" አሉና ሼህ ከድር ከተቀመጡበት ብድግ ብለው ከዋሻው ግድግዳ በአንደኛው ጎን ከተደረደሩት ኪታቦች መካከል አንድ ኪታብ መፈለግ ጀመሩ::

ኢትኤል ከአብርሃምና ዘይኔ መሃል ነበር የተቀመጠው:: በተለይ ዘይኔ እጅግ ተመስጦ የሼኩን ወግ ሲከታተል እንደነበር አስተውሏል:: በበኩሉ ስለነብዩ ሙሐመድ እና ስለኢትዮጵያዊ እስልምና ይህን ያህል እውቀት አልነበረውም:: ከዘይኔ ንግግሮች በስተቀር የሚያስታውሰው አንድ የፌስቡክ ፅሁፍ ነበረ:: ከጥቂት አመታት በፊት ሙስሊም ያልሆነ ሚካኤል ሃርት የተባለ የታሪክ ተመራማሪ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ትልቅ ተፅእኖ ፈጣሪ የነበሩ ሰዎችን አወዳድረው ነበር:: ከፍተኛ ጥናት ካደረጉ በኋላም በሰው ልጆች አኗኗር ውስጥ ታላቅ ተፅዕኖ የፈጠሩና የብዙ ማህብረሰቦች ህይወት ውስጥ ምሳሌ ከሆኑ 100 ሰዎች ውስጥ አንደኛው ነብዩ ሙሐመድ መሆናቸውን እንዳረጋገጡ ሙስሊም የፌስቡክ ጓደኞቹ ሼር ያደረጉትን አይቶ ገርሞት ነበር:: አሁን ከዚያም የበለጡ አስገራሚ ታሪኮችን እየሰማ ነው:: የሌሎቹን ባያውቅም እሱ ግን እንዲህ ብሏል… "የነብዩ ሙሐመድን ነብይነት በሃይማኖቱ ምክንያት መቀበል ያቃተው አንድ ሰው ታላቅ ተፅዕኖ ፈጣሪና ጥሩ አርዓያነታቸውን ግን መካድ አይችልም::" …ሼህ ከድር የፈለጉትን ኪታብ አግኝተው እያራገፉ መጡና ከቀድሞ ቦታቸው ተቀመጡ::

"እና እንዳልኳችሁ ልጆቼ ከሃበሻው ቢላል ውጪ ሌላ ሰው አዛን ሲል የሚከፋቸው ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የአህለል ኪታቦችን ማለትም የክርስቲያኖችን መፅሐፍት አምነን እንድንቀበል ብቻ ሳይሆን በደንብ እንድንመረምራቸው አዘውናል:: ከእነዚህም ዋናዎቹ ኢንጅል ወይም ወንጌል፣ ተውራት/ቶራህ ወይም ኦሪት እና ዘቡር ወይም መዝሙር ሲሆኑ በተጨማሪም ሌሎች ቅዱሳተ-መፅሐፍትም እንዳሉ ጠቁመውናል::

አንዳንድ ኡስታዞች ‹‹እነዚህ አሁን ያሉት መፅሐፍት የሰው እጅ ገብቶባቸዋልና አንቀበልም» ይላሉ:: ነገር ግን ቁርዓንና ሃዲሶች ጋር የማይጋጩና እጅግ ታላቅ መለኮታዊ ጥበቦችና ታሪኮችን ያዘሉ መዛግብቶች በቅጡ ሳይመረምሩ እጅ ገብቶባቸዋል በሚል ጭፍን ምክንያት ማጣጣል ከአንድ ሙስሊም የማይጠበቅና እጅግ የሚያሳዝን ተግባር ነው:: እንኳንስ እነዚህን መሰል ቁርዓንም እንድናነባቸው ያዘዘንን መፅሐፍት ይቅርና ማነኛውም እውቀት በእስልምና ዘንድ ያለውን ዋጋ ያልተረዱ ሰዎች ናቸው እንዲህ የሚሉት:: የመጀመሪያው የቁርዓን ቃል እኮ በገብርኤል በኩል ሲወርድ ‹‹ኢቅራ›› ወይም ‹‹አንብብ›› ብሎ ዝም ነው ያለው እንጂ ቁርዓን ወይም ሃዲስ ወይም ባይሎጂ ወይም ሂሳብ ብቻ አንብብ አይደለም ያለው:: ይህም ማለትም የእውቀት መንገድ ሰፊና ጠረፍ አልባ እንደሆነ አመላካች ነው:: ለእዚህም ነው ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) "እውቀትን ፍለጋ እስከቻይና ድረስም ቢሆን ሂዱ›› ያሉት፣ ለዚህም ነው አል-አሊም ጌታችን "ኑን

ወልቀለሚ ወማ የስጡፉን፤" ብሎ በብዕርና በቀለም (በፅሑፍ) ምሎ የሚናገረው:: እናም ዛሬ በእነዚህ አህለል ኪታቦች መፅሐፎች ያሉ ሶስት ታሪኮች በእስልምናችን ከምንመራበት ቁርዓንና ሃዲስ ጋር እያመሳከርኩኝ እነግራችኋለሁኝ::" አሉና አንዲት ኪታብ ገለፁ::

"የመጀመሪያው ታሪክ የሚሆነው በከርስቲያኖችም በሙስሊሞችም ዘንድ እንደሚታመነው በመጨረሻው ዘመን፣ በቂያማ መዳረሻ ላይ ይመጣሉ ተብለው የተተነበያላቸው ጉግ ማንጉግ ወይም በአረብኛው ጁጅ ማጁጅ ተብለው የሚታወቁ ፍጥረታት አሉ:: እጅግ በርካታ ቁጥር ስፍር የሌላቸውና አለምን እንደ አንበጣ የሚወሩ ፍጥረታት እንደሆኑ ትንቢቶች ተከትበዋል:: ታዲያ እነዚህ ፍጥረታት ከበፊትም የነበሩና በአካባቢያቸው ያሉ የሰው ልጆችን ሲያስቸግሩ የነበሩ ፍጥረታት እንደሆኑ ታሪክ ይነግረናል::"

"ታዲያ አሁን የት ነው ያሉት?" አለ ዮሴፍ እያቋረጣቸው፤

"ሶብር (ታገስ) ልጅ ዮሴፍ ልነግራችሁ ነው፤ አላህ በቅዱስ-ቁርዓኑ ሱረቱል-ካፍ ወይም የዋሻው ምዕራፍ ላይ ለነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላቸዋል፤

*"ስለ «ዙልቀርነይን»ም ይጠይቁሃል፤ "ለእናንተ ታሪኩን አነብላችኋለው" በላቸው:: (83) (ንገራቸው) እኛ በምድር ላይ አደላደልነው፤ የነገርንም ሁሉ መፍትሔ ሰጠነው:: (84) መንገድንም ወደ ምዕራብ ተከተለ:: (85) ወደ ፀሐይ መግቢያም በደረሰ ጊዜ ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ አያት፣ በዚያም ሕዝቦችን አገኘ፤ እኛም፤ "ዙልቀርነይን ሆይ! እነዚህን ህዝቦች ትቀጣቸዋለህ ወይስ ለእነርሱ መልካም ነገር ትሰራለህ?" አልነው:: (86) (እርሱም) "በደለኛ የሆነን ሰው እንቀጣዋለን፤ ወደፊትም ወደ ጌታው ሲመለስ ብርቱ ቅጣት ይጠብቀዋል፤" አለ:: (87) "ያመነና መልካም ሥራ የሰራ ሰው ግን እርሱ መልካም ነገር ያገኛል፤ በእርጋታም እናዘዋለን፤" አለ:: (88) ከዚያም መንገዱን ቀጠለ:: (89) ወደ ፀሐይ መውጫ በደረሰም ጊዜ ለነሱ ከፀሐይ በታች መጠለያን ባላደረግንላቸው ሕዝቦች ላይ ስትወጣ አገኛት:: (90) እነሆ እንዲህም ሆኗል፤ በሆነውም ሁሉ በእርግጥ አናውቃለን:: (91) ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ መንገድን ቀጠለ:: (92) በሁለት ጋራዎች መካከል በደረሰ ጊዜም ንግግርን በጣም በጥቂቱ የሚያውቁ ህዝቦችን አገኘ:: (93) እነርሱም "ዙልቀርነይን ሆይ! ጉግ ማንጉጎች በመሬታችን ላይ ጥፋትን የሚያስፋፉ አበላሺዎች ናቸውና በእኛና በእነርሱ መካከል ግንብን ታደርግልን ዘንድ እንጠይቅሃለን፤ ለእዚህም የስራህን ዋጋ እንከፍላለን፤" አሉት:: (94) (እርሱም) "እኔ ጌታዬ የሰጠኝ ሀብትና ስልጣን ከሁሉም በላጭ ነው፤ እናንተም ታግዙኛላችሁ ጠንካራ ግንብን እንገናባለን" አላቸው:: (95) "ታላላቅ የብረት ዘንጎችን ስጡኝ፤" አለ፤ በሁለቱ ተራራዎች መካከልም ሙሌትን ከሞላ በኋላ "ወላፈኑን በቀንዱ ንፉበት" አላቸው፤ እንደ እሳትም ፍም ከሆነ በኋላ "የቀለጠውን ነሐስ አምጡ" አለና በላዩ ላይ አፈሰሰበት:: (96) (ያንን ግንብም) ጉግ ማንጉጎች ወጥተው ሊዘሉትም ሆነ ቆፍረውት ሊያልፉት አልቻሉም:: (97) (ሲጨርስም)*

*"ይህ ግንብ ከጌታዬ ዘንድ ችሮታ ነው፤ የጌታዬ ቀጠሮ በመጣ ቀን ግን እንዲፈርስ ይፈቅዳል (ጉግ ማንጉጎችም ይወጣሉ)፤ የእርሱም ቀጠሮ የተረጋገጠ ነው፤" አላቸው:: (98) በዚያም በሚወጡበት ቀን አንዱ በአንዱ ላይ እየተተረማመሱ ይመጣሉ፤ በመለከቱም በተነፋ ጊዜ ዳግም እንሰበስባቸዋለን::"*

እንግዲህ ይህ ታሪክ የሚገኝበት የቁርዓን ምዕራፍ እያንዳንዱ ሙስሊም በየሳምንቱ ጁምዓ ቀን እንዲያነበው ብለው ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ያዘዙት ምዕራፍ ነው:: በቁርዓኑ መሰረትም ይህ ዙልቀርኒን የተባለ ሰው ትልቅ ሃይልና የሁሉን ነገር መፍትሔ የተሰጠው ሲሆን በስሩ ያለው ሰፊ ግዛት ላይ በምዕራቡ ጥግ ፀሐይ እየጠለቀ በተመሳሳይ ሰዓት ደግሞ በሌላኛው ምስራቃዊ ግዛቱ ፀሐይ እንደሚወጣ እንረዳለን:: ይህም አሁን ባለው ካርታ መሰረት በምዕራብ ከ‹ማያ› ሜክሲኮ እስከ ምስራቅ ቻይና ቤይጂንግ በሰሜንም እስከ ሩሲያ ያለውን የሚወክል ሆኖ አንዱ በእሱ ግዛት ስር ያለ ሃገር ሲነጋ በተመሳሳይ ሰዓት ሌላኛው ሃገር ደግሞ ይመሻል ማለት ነው:: ታድያ ከዚህ አስገራሚ ታሪክ ጋር ተያይዞ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) እንደተናገሩት ይህ ጉግ ማንጉጎችን በግንብ ዘግቶ ያካለላቸው ታላቅ ሰው የፅድቅ ንጉስ ሲሆን ግዛቱ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ የተዘረጋ እንደነበር አትተዋል:: ከዚህም በተጨማሪ እጅግ ጉልበት ያለውና ጥበበኛ ሰውም እንደነበር ተናግረዋል:: ታዲያ ይሄንን የቁርዓንና ሃዲስ ታሪክ አንብበው የእሱን ማንነት የገመቱ ብዙ ነበሩ:: ነገር ግን በተለይ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች በሚቀበሉት አንድ ጥንታዊ መፅሐፈ ያሻር የተሰኘ መፅሐፍ ላይ አንድ እንዲህ የሚል ታሪክ አለ::

አንድ ስሙ እሴ የተሰኘ የኢትዮጵያ ካህንና ንጉስ ነበር:: ይህ ንጉስ በምድር ላይ ከኖሩት ነገስታት ሁሉ የላቀ እንደነበር መጽሐፉ ሲነገርን፤ እሴ እጅግ ሃያል የሰው ልጅ ወይም ዲበ-ሰው ሲሆን የተወለደው ከ3700 ዓመታት በፊት እንደነበር ይተረካል:: ነብይና ካህን ከመሆኑም ባሻገር መንግስትነት በፍትሐዊነት እንዲሆን ከማንም ቀድሞ አቅዶ የፍትሐ-ብሔርን ህግጋት አርቅቆ አውጇል፤ ሰንደቅ አላማ የሃገራት መለያ እንዲሆን ወስኖ ለኢትዮጵያም የቀደምት አባቱን የኖህን የተስፋ ቃል-ኪዳን ቀስተ-ደመና ቀለሞች አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ አድርጎ አስቅሏል:: በተጨማሪም የዘረመል እውቀት፣ የእፅዋት ተመራማሪና የማእድናት አዋቂ እንደነበርም ተዘግቧል:: በተለያዩ ድንጋዮች ላይ ተመራምሮ ስለድንጋዮች ባህሪና ተግባር መጽሐፍ ፅፏል:: ንፁህ ውሃ መጠጣትም እድሜ ያረዝማል በማለት የሚጠጣው ውሃ በተራሮች ከሚበቅሉ ልዩ ዛፎች ስር የሚፈልቅን ምንጭ ነበር:: በዚህ ጥበቡም በአምላክ ፍቃድ 500 ዓመታትን ገደማ ምድር ላይ እንደኖረ ተጠቅሷል:: አፍሪካንና መካከለኛውን ምስራቅና ከፊል አውሮፓን ሲያስገብር

ቆይቶ በክህነት ስሙ እስያኤል ተብሎ በጌታው ከተሰየመ በኋላ ደግሞ ዘመኑ ያፈራቸውን መሳሪያዎች በታጠቀ አንድ ሚሊዮን የኢትዮጵያ የጦር ሰራዊት ይዞ ዘምቶ የእስያን አህጉር በሙሉ በራሱ አገዛዝ ስር በማድረግ አካባቢውን በስመ-ክህነቱ ‹‹እስያ›› እንዳለው ተዘግቧል፡፡ በዚህም በእርሱ ግዛት ፀሐይ አትጠልቅም ነበር፡፡

ልብ በሉ እንግዲህ የእስልምናው ‹‹ዙል-ቀርነይን» እና በመፅሐፈ-ያሻሩ እስያኤል መካከል ያለውን ተመሳሳይነት፡፡ ሁለቱም እጅግ ብርቱ ሃያልና አዋቂዎች ቢሆኑም ሁለቱም ግን በጉልበታቸው የማይመኩ ካህንና ነብይ ነበሩ፡፡ ሁለቱም ታሪኮች ላይ ያሉት ሰዎች ግዛታቸው ፀሐይ የማትጠልቅበት ሰፊ ግዛት እንደነበር ተዘግቦልናል፡፡ የሚገርመው ደግሞ በቁርዓን ውስጥ በድንጋዮች ሙሌትና ነሐስ ማቅለጥ ስራ ታላቅ ግንብ እንደገነባ እናነብና በመፅሐፈ-ያሻረ ላይ ያለው እስያኤል ደግሞ በማዕድናት ጥናት የመጠቀ እውቀት እንደነበረው ብሎም ስለድንጋዮች ተመራምሮ መፅሐፍ እስከ ማዘጋጀት የደረሰ ታላቅ ንጉስ መሆኑን ይነግረናል፡፡ ታዲያ አንድ አስተዋይ ሰው የእነዚህን ሰዎች ታሪክ ሲሰማ አንድ አይነት ሰዎች ሊሆን ይችላሉ ብሎ መጠርጠሩ አይቀረም፡፡... አይደል እንዴ?" አሉና ሼህ ከድር በትረካቸው ተመስጠው የነበሩትን እነኢትኤልን አስደነገጧቸው፤ እነርሱም በአዎንታ አንገቶቻቸውን አንቀሳቀሱ፤

"ታድያ ያኔ ወጣት ሆኜ ይህ ጥያቄ ውስጤ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ግን እንዲሁ በቀላሉ ሳይሆን እርሳቸው እንዳሉት እውቀትን ፍለጋ እስከ ቻይና ድረስ ሄጄ ነው መልሴን ያገኘሁት፡፡ መጀመሪያ ያደረግኩት ነገር ቢኖር ይህ ታላቅ ንጉስና ነብይ ቢያንስ የምድርን ግማሽ የገዛ ስለሆነ እንዲህ አይነት ታላቅ ንጉስ በታሪክ ውስጥ መኖሩን ማጣራት ነበረ፡፡ ምላሼንም ያገኘሁት ከህንድ ሃገር ነበር፡፡ አሁን የምናውቃትን ህንድ ስርወ-መንግስት የመሰረታት አንድ ከምስራቅ የመጣ ጥቁር ንጉስ እንደሆነ ማመን ሊከብዳችሁ ይችላል፡፡ ግን እስያኤል የተሰኘው የኢትዮጵያ ንጉስ በስነ-መንግስትና በፍትሃ ብሔር ሊቅ እንደነበር ስናስታውስ ይህ ትርጉም ይሰጠናል፡፡ ነገር ግን አንድ ‹‹ራማያና» የተባለ የህንድ ቅዱስና ሃያል ሰው ብዙ ተዓምራትን እያደረገ ሙሉ ህንድን በጥበብና በሂንዲዩዝም አሃዳዊ ሃይማኖት እንደመራት ታሪክ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል፡፡ የዚህ ሰው ጠይም ኢትዮጵያዊ መልክ አሁንም በሂንዱ ቤተ-መቅደሶች ተሰቅሎ ይገኛል፡፡ ከዚህም በላይ ‹‹ራህማይ›› የሚባል አክሱምን የሰራ የኢትዮጵያ ንጉስ እንዳለ በኢትዮጵያ የታሪክ መጽሐፍት ውስጥ በግልጽ ተፅፎ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል ‹‹India›› የሚለው ቃል በራሱ ትርጉሙ ‹‹ጥቁር›› ማለት ነው የሚሉት ራሳቸው ህንዶቹ ሲሆኑ ‹‹ህንደኬ››

የሚባሉት የኢትዮጵያ ንግስታትም ህንድን ለመግዛታችን ጠቋሚ ናቸው:: በኮምፒዩተራችሁ በሚገኙ ኢንካርታዎቻቹ ላይ ራማያና ብላችሁ ብትፈልጉና ከመዝሙሮቹ የመጀመሪያውን ብታዳምጡ ከው ነው የምትሉት፤ የምትሰሙት የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያናት ጥንታዊ ዝማሬ ይሁን የሩቅ ምስራቆቹን ህንዶች ዝማሬ ግራ ነው የምትጋቡት:: ይህም የሆነው በመጽሐፈ ያሻር መሰረት የእኛው ኢትዮጵያዊው ‹እስያኤል› ወይም ‹ራህማይ› ሙዚቃና ዝማሬ ወዳድ ንጉስና የዜማ ሰውም ስለነበር ነው:: በብዙ ህንድ በሚገኙ ቅርጾችና ስዕሎቹም ላይ ዋሽንት ይዞ መታየቱ ይህንን ያመለክታል፡ የያኔው የዜማ አቀናባሪ አባታችን ምቶች አሁንም በህንድ መዝሙሮችና ሙዚቃዎች ውስጥ ይንፀባረቃሉ:: ብዙ ኢትዮጵያውያን የህንድ ሙዚቃዎችን ሲሰሙ ልባቸው የሚሸፍተው ካለ ነገር እንዳይመስላችሁ::" አሉና ፈገግ ብለው ሁሉንም እያዩ ... "ከእናንተ ውስጥ የህንድ ሙዚቃዎችን የሚወድ የለም?" ብለው ጠየቁ፤ መርየም እንደ ማፈር ብላ ስቃ ፈቷን በከንዷ ሸፈነች፡

"አብሽር አትፍሪ፤ ስንት የሚያሳፍርና የሚያጸይፍ ዘረኝነትና ምቀኝነትን የመሰለ ባህሪ እያለ ይህንን በማድረግሽ አልታዘብሽም:: ነገር ግን ወደ ዋናው ነጥቤ ስመለስ ከእኛ ተሰውሮብን ታሪካችንን መዘገብ አቅቶን እንጂ ድንቅ ድንቅ ታሪኮች እንዳሉን ማወቅ አለብን እላችኋለሁኝ:: ይሄ ተረት ተረት ሳይሆን እውነተኛ ታሪክ ነው! ቅዱስ ራማ የሚባለው የሂንዱ ቅዱስ ጀግና የኢትዮጵያው እስያኤል ለመሆኑ ሌላው ማስረጃው ደግሞ ‹‹ታሚል›› ይባል የነበረ የጠፋ ግዛት ታሪክ ነው:: ታሚል ማለት ታሪክ አጥኚዎች እንደነበረ የሚያምኑት የአሁኖቹን ህንድ፣ ፓኪስታን፣ አፍጋኒስታን፣ ባንግላዴሽና መሰል ሃገሮችን ጠቅልሎ የሚይዝና የህንድ ውቅያኖስ ውስጥ የሰመጠ ቦታን ጨምር ሰፊና ታላቅ ግዛት ነበር:: ባይገርማችሁ የእዚህ የጠፋ ግዛት ቋንቋ የነበረው የታሚል ቋንቋ ፊደላት ከአማርኛ ፊደላት ጋር የጠበቀ ቁርኝት አላቸው:: ከእዚህ በተጨማሪም ትግራይ ውስጥ በሚገኝ ራማ በሚባል ስፍራ ድሮ ህንድን የገዛ ንጉስ እንደነበረ አፈ-ታሪኮች እስካሁንም ይነገራሉ::

ሌላው የዙል ቀርነይንን እስያኤልነት የሚያጠናክርልኝ ነገር የጉግ ማንጉጎች መገኛ የሚባለውን ቦታ ለማወቅ ሳነብ ነበር አስገራሚውን ግኝት የገጠመኝ:: የዚያን ጊዜ በነበሩ ብዙዎች እንደሚስማሙት ከሆነ ጉግ ማንጉጎች ተዘግቶባቸው ያሉበት ስፍራ ከእስያዋ ሀገር ሞንጎሊያ አካባቢ ነው:: ለዚህም መረጃ የሚሆነው አንድም ቅዱስ ቁርኣን ጉግ ማንጉጎች "ከበላያቸው ለፀሐይ ጥላ ያላደረግንላቸው ሰዎች" ካሉበት በስተሰሜን ነው ብሎ በሚጠቁመን መሰረት፡ «ጥላ» ማለት «ተራራ» ሲሆን በዓለም ላይ ደግሞ ከሁሉም ሃገራት ያነሰ ተራራዎች ያሏቸው የምስራቅ አውሮፓ ሃገሮች «ቤላሩስና ላቲቪያን የመሳሰሉ ሃገራት ሲሆኑ ሞንጎሊያ ዳግሞ ከእነዚህ ሀገራት

በስተስሜን ምስራቅ ነው የምትገኘው:: ሌላኛው ደግሞ የሞንግ ማንንግ ዘር እንዳለባቸው የሚመሰክሩ ቀደምት የሞንጎሊያ ኗሪዎችም መኖራቸው ነው::

ታዲያ እነዚህ ሞንጎላውያን ማዶ የነበሩና ያሉ ፍጡራን ጎግ ማንጎጎች ከሆኑ ቻይናውያን ከሞንጎላውያን ለመጠበቅ ብለው የሰሩት ታላቁ የቻይና ግንብ ከዙልቀርነይን ግንብ ጋር ይቀራረባል ማለት ነው:: ታሪኩን ይበልጥ የሚያጠናክርልን የአሁኒቷ ቻይናን የመሰረታት ዜንግ-ቂን የኖረበት ዘመን መፅሐፈ ያሻር እስያኤል ምድር ላይ ከኖረበት ዘመን ተመሳሳይ መሆኑ ነው:: የቻይና መጠሪያ ስም መነሻ ራሱ ብናይ ‹ቺን› ከሚለው የመጣ ሲሆን ይህም የተገኘው ‹ቂን› ከሚለው የዜንግ-ቂን ስም እንደሆነ ይነገራል:: እዚህ ላይ <<ዞል-ቀርነይን;; የሚለው ስም ከቻይናው ስርወ-መንግስት መስራች <<ዜንግ-ቂንን›› ጋር ያለውን መመሳሰል ልብ በሉ::" አሉና ፈገግ ብለው ቀጠሉ "ታዲያ ትልቁን ግኝቴን ያገኘሁት በቁርዓኑ ታሪክ መሰረት የዚህን ግንብ ገንቢ ማንነት ለማወቅ ባደረግኩት ጥናት ነበር:: ከሁሉም መላምቶች በላይ አውሮፓውያኑ ‹‹ይህንን ግንብ የሰራው የኛ ንጉስ ታላቁ አሌክሳንደር ነው›› ብለው የሚያስቀምጡት መረጃ አሳማኝ ሆኖ ስለተሰማኝ በክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ውስጥ ስለዚህ ሰው ሳጣራ ነበር አስገራሚውን መረጃ ያገኘሁት:: ይህም በኢትዮጵያ ያለው ፈረንጆቹ ‹‹አሌክሳንደር ዘ ግሬት›› ብለው የተረጎሙት ኦሪጅናሉ የግዕዝ መፅሐፍ <<ዘ ክልኤ አቅርንቲሁ›› የሚል ስያሜ እንዳለውና <<አቅርንቲሁ›› ማለትም በግዕዝና ትግርኛ መሰረት ባለሁለት ቀንድ እንደ ማለት ሲሆን፤ ይህም በቅዱስ ቁርዓን ላይ ባለው ታሪክ መሰረት ቀንድ እያስነፋቸው ግንቡን ከመስራቱ ጋር ተያይዞ ከተተረከው ታሪክ ጋር እጅጉን ይመሳሰላል:: የሚያሳዝነው ግን ይህንን ታላቅ ኢትዮጵያዊ ንጉስ ታሪክ አውሮፓውያኑ ከኛው ብራና ላይ ተርጉመው እነርሱን አሸንፎ ሲያስገብር የነበረ የኛን ንጉስ፤ የእነርሱ ንጉስ አስመስለው ሲኩራሩ እኛ ግን ይሄ ሁሉ መረጃ እያለን በዝምታ መቀመጣችን ነው::" አሉና በቁጭት እንደተሞሉ በረጅሙ ተነፈሱ፤... "እንግዲህ ዛሬ የምነግራችሁ የመጀመሪያ ታሪክ ይህ ነበር:: እውነታው ሲገለጽ የቅዱስ ቁርዓኑ ***ዞልቀርንይን፣ የቻይናው ዜንጉቂን፣ ንጉስ ዘክልኤ አቅርንቲሁ፣ የህንዱ ራህማያና የአክሱም ንጉስ ራህማይ፣ እስኩ-ሀንድ-ዳር የገዛ ታላቅ መሪ ወይም በስሙ-ከህነቱ እስያኤል*** ተብሎ እስያን ያስገበረው የኛው የመፅሐፈ ያሻሩ ኢትዮጵያዊ ንጉስ መሆኑን እንዳወቃችሁ አምናለሁኝ:: ነገ ደግሞ ሁለት ታሪኮችን አጫውታችኋለሁኝ፤ ለዛሬ ግን ይበቃል:: የሰማነውን እንድናስተውል ጀሊሉ ይርዳን... በሉ ደህና እደሩ፤" ብለው ከተቀመጡበት በትራቸውን ደገፍ ብለው ተነሱና ከዋሻው ወጡ::

# ምዕራፍ ፳ ........ ሳባውያንና ኑቢያት

*ከሁለት ቀን በፊት፤ ሐሙስ ምሽት 2፡00 ሰዓት፤*

እጬ ዶክተር ቢሊሱማ ራሱ ሲቀሰቅሰው በሰነበተው ተቃውሞ ላይ መገኘት አለመቻሉ እጅግ እያበሳጨው የማታ ታካሚዎችን ያስተናግዳል:: ካልጠፋ ቀን ዛሬ አዳሪ ዶክተር ሆኖ መመደቡ አውቀው ለነገር ያረጉበት እየመሰለውም ለብቻው ይብሰለሰላል:: ለሁለት ሰዓታት በዚያ ፍጥነቱ እየተሯሯጠ ሲሰራ ከቆየ በኋላ የጓደኞቹ ጨኸት ከሩቅ ተሰማው፤ ተቃውሞው ተጀመረ ማለት ነው:: ውስጡ ‹‹ሄደህ ተቀላቀላቸው፤ ተቀላቀላቸው›› የሚል ስሜት ይሟገተው ጀመር:: ከራሱ ጋር ለመሄድና ላለመሄድ እየታገለ ሳለ ድንገት የተኩስ ድምፆች መሰማት ጀመሩ:: እኩለ ሌሊት አካባቢ የተቃዋሚዎቹ ጨኸትም ወደ ዋይታና ሁካታ ተለወጠ:: ወንድሞቹን መርዳት አለብኝ ብሎ ተነስቶ ሊወጣ ሲል ሁለት ጎረምሶች አንድ በደም የተጨማላቀ ወጣት በክንዶቻቸው ተሸክመው እየከነፉ ሲመጡ ተመለከተ:: በተቃውሞው የተጎዳ ወጣት እንደሆነ ገምቷል:: ቶሎ ብሎ ብርቱ ታማሚ የሚተኛበትን ክፍል ከፈተላቸው:: ወጣቶቹ የተጎዳውን ልጅ አመጡና አልጋው ላይ አስተኙት፤ እሱ በህመም ውስጥ ሆኖ “ሃደኮ... ሃደኮ... (እናቴ... እናቴ...)” እያለ ያቃስታል፤

“ቢሊሱማ ሲያቹ... (ቶሎ በል፤)” አሉ ወጣቶቹ፤

“ማልታቴ (ምን ሆኖ ነው?)” አለ ቢሊሱማ፤ አደጋው የደረሰበትን የአካል ክፍል ለማወቅ በአይኑ እየቃኘ፤ የተመታው ልጅ ጀርባውን ሰጥቶ በግራ ጎኑ ቢተኛም ደሙ ቡልቅ ቡልቅ የሚለው ከቀኝ ትካሻው ላይ እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም ነበር::

"ረሳሳ! ...(ጥይት) ነው የመታው፤" አሉ ወጣቶቹ በድንጋጤ ውስጥ እንዳሉ፤

"እይዞህ...?" አለውና የእጅ ጓንቶቹን አጥልቆ የሚደማውን ቦታ በፋሻ ለመጫን ልጁን በጀርባው ገልበጥ ሲያደርገው ቢሊሱማ ከው ብሎ በቆመበት ቀረ:: አይኑን ላለማመን የቱንም ያህል ቢፈልግም የተመታው ልጅ ግን እርግጥም ራሱ ነው::

"ቶላ!" አለ በድንጋጤ፤ ሰማይና ምድሩ ሲገለባበጥበትም አልጋውን ደገፍ ብሎ አጎነበሰ:: ከመጀመሪያው አንድ ጓዱ በመጎዳቱ አዝኖ የነበረ ቢሆንም ተጎጂው ቶላ ይሆናል ብሎ ግን በፍፁም አላሰበም ነበር:: እንደምንም አቅሙን አሰባስቦ ተነሳና የጓደኛውን ህይወት ለማትረፍ መሯሯጥ ጀመረ:: ግሉኮስ ቀጥሎለት ደሙን ለማቆም በእሱ በኩል የሚጠበቅበትን ሁሉ እያደረገ ተረኛው አዳሪ ሬዝደንት ጋር ደወለ:: ሬዝደንቱም በፍጥነት መጥቶ ቶላን ከመረመረ በኋላ ወደ ‹ኦ አር› (ኦፕሬሽን ክፍል) ገብቶ ጥይቱ መውጣት እንዳለበት ተረዳ:: ነገር ግን ቶላ ብዙ ደም ስለፈሰሰው መጀመሪያ ደም ‹‹ትራንስፍዩዝ›› መደረግ እንዳለበት ለቢሊሱማ ነገረው:: ቢሊሱማም ጊዜ ሳይፈጅ የቶላን ደም ሳምፕል ቀዳና የእሱ ደም አይነት ጋር ተመሳሳይ የደም አይነት መኖሩን ለማወቅ ወደ ሆስፒታሉ የደም ባንክ ከነፈ:: በእያንዳንዱ እርምጃው ለቶላ የሚሆን ደም እንዲኖር እየተመኘ ነበር::

ለቶላ እንዲህ መሆን ጨካኙ ተኳሽ፣ የሱ አዛዥ ከፍ ሲልም አፋኝ መንግስት ተጠያቂ ነው:: ከዚያ ባለፈ ግን ቢሊሱማ በትንሹም ቢሆን ራሱን መውቀሱ አልቀረም፤ ምክንያቱም ከፈተና መልስ አንድ ቀን እንኳን ሳያርፍ ወደተቃውሞው እንዲሄድ የገፋፋው እሱ ነበር:: ቁጭቱን ያባሰበት ደግሞ ራሱ በጠራው ተቃውሞ ላይ እሱ ሳይገኝ ብቻውን ሄዶ መመታቱ ነው:: ቁጭትና ፀፀት እያንገበገበው ደም ባንኩ ጋር ደረሰና መስኮታቸውን አንኳኳ:: የላብራቶሪ ሰራተኞቹ ለሽ ብለው ተኝተው ነበር:: በሃይል ሲደበድብባቸው ተነሱና ከፈቱለት::

"ምን ሆነክ ነው ጃል?" አለው፤ መስኮቱን የከፈተለት ልጅ እግር ላብራቶሪስት፤

"በእናትህ አንድ ‹አክሲደንት› አለ፤ ቶሎ ይህንን ደም ‹ብለድ ግሩፕና ክሮስ ማች› ሰርተህ ደም ካለ እይልኝ፤" አለ ቢሊሱማ በችኮላ፤

"ውይ ያለው ሶስት ‹ቢ ፕላስ› ብቻ ነው፤ እስኪ ግን ፎርሙን ሞልተህ አምጥተሃል?" አለው ደም ያመጣበትን ብልቃጥ እየተቀበለው፤

"አ... አላመጣሁም፤" አለ ቢሊሱማ ወረቀቱን በመርሳቱ ከው እያለ፤

ላብራቶሪስቱ "ካለ ሪከዌስት ፎርምማ አንሰራም፤" ብሎ ብልቃጡን ሲመልስለት፤ የቢሊሱማ አይኖች ላይ እንባ ቸርፍፍ አለ:: ይህንን ያየው ላብራቶሪስት ምንም ተጨማሪ ጥያቄ ሳይጠይቀው ብልቃጡን ተቀበለው::

"በቃ አብሽር፤ እኔ ‹‹ብለድ ግሩፑን›› እየሰራሁኝ እጠብቅሃለሁኝ አንተ ፎርሙን ይዘህ ና!" አለው፤ ቢሊሱማ ላብራቶሪስቱን አመስግኖ ሲሄድ ጉንጩ ላይ የፈሰሰውን እንባ እየጠረገ ነበር:: ቶላ አንድ ነገር ቢሆን የቶላ እናት ምን ያህል ሃዘን ውስጥ እንደምትገባ ሲያስብ ነበር እንባ የቀደመው:: ፎርሙን ሞልቶ ሲመለስ ላብራቶሪስቱ ብለድ ግሩፕና ክሮስ ማቺን ሰርቶ ለቶላ የሚሆን ደም አዘጋጅቶ ነበር የጠበቀው::

"እድለኛ ነህ፤ የሱም ደም ቢ ፖላስ ነው… ማች አግኝቼልሃለሁኝ፤" አለው ፈገግ ብሎ፤ ቢሊሱማም ቅፅበታዊ ፈገግታ ብቻ አሳይቶት ደሙን ተቀበለና ለጓደኛው ለመድረስ በችኮላ ሄደ:: ከፍሪጅ የወጣው ደም እንዲሞቅ ከነጭ ጋውኑ ስር እቅፍ አደረገው:: ቶላ የተኛበት ክፍል ሲደርስ ቶላን ከቀድሞ ይበልጥ ተዳከሞ ነበር ያገኘው:: ያመጣው ደም ሞቅ ሲልለት ቶላ እጅ ላይ መርፌ ቀጥሎ 3 ሰዓት የሚፈጀውን የደም ሙሌት ጀመረ:: ከቶላ በኋላም ሌሎች 3 ተጎጂዎች መጥተው ስለነበር እነርሱን ለማከም እዚህ እዚያ ይዋከብ ገባ::

ከ2 ሰዓታት በኋላ የሌሎቹን ህክምና የጨረሰው ቢሊሱማ ወንበር ይዞ መጥቶ ደም እየተሰጠው ካለው ቶላ አጠገብ ተቀመጠ:: ሰዓቱ ሌሊት 9 ሰዓት ከሩብ ይል ነበር:: ቀኑን ሙሉ ሲሰራ ውሎ በዚያው አዳሪ የገባው ዶክተር ቢሊሱማ ድካምና እንቅልፍ ወጥረው ይዘውታል:: ቢያንስ ግን የቶላን የ3 ሰዓታት የደም ሙሌት መጨረስ እንዳለበት ያውቃል:: የቶላን ሁኔታ መርምሮ ደሙ ካለችግር እየሄደለት እንደሆነ አረጋገጠና ከወንበሩ ተቀመጠ:: የአልጋውን ጠርዝ ደገፍ ብሎም የቶላን ፊት እያየ በተስፋ መጠበቅ ያዘ፤ ነገር ግን እንዴት እንደሆነ በማያውቀው ሁኔታ እንቅልፍ ይዞት ሄደ::

***

ውድቅት 9 ሰዓት ከሩብ ላይ ነበር አንድ ሰው ቶላ የተኛበትን ክፍል በር ከፍተው የገቡት:: በቀስታ የቢሊሱማን ወንበር ዞረው አለፉና ከቶላ ፊትለፊት ቆሙ:: ራሱን የማያውቀውን ቶላ ትክ ብለው ተመለከቱትና ቀይ ብልቃጥ አውጥተው በቁስሉ ላይ ያለው ፋሻ ላይ አፈሰሱት:: ፋሻው ሲርስም የለበሱትን ረጅም ቡልኮ ሰብሰብ አድርገው አንድ የስላጣ ስፋት ያለው ቅጠል አወጡ:: ከዚያም የተለያዩ የጸሎት ቃላቶችን እያሉ ቅጠሉን ጭምቅ እያደረጉ የቶላ የቀኝ ትከሻ ቁስል ላይ ማንጠባጠብ ጀመሩ:: ከአፍታ በኋላ ቶላ መንቃት ጀመረ::

***

የወጣቶች የተቃውሞ ጩኸት ከዚያም የአስለቃሽ ጭስ ቃጠሎና የዐይን መለብለብ፣ ቀጥሎም የጥይት ድምፅ፣ የባሩድ ሽታና ዋይታ አሁንም እንዳዲስ ትዝ ይለዋል።

ፖሊሶቹ በመጀመሪያ ዋነኛ ተቃዋሚ ተማሪዎችን በአስለቃሽ ጭስ አዳክመው እንደ እባብ ከቀጠቀጧቸው በኋላ ኢላማቸውን በቅርብ ወዳገኙት ማንኛውም ተማሪ አደረጉት። ወንድ፣ ሴት፣ ያመፀ፣ ያላመፀ... ሁሉም ተማሪ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በዱላ ሲወገር ይታወሰዋል። ደብዳቢዎቹ እዚሁ ሀገር ተወልደው ያደጉ መሆናቸውን በሚያጠራጥር ሁኔታ እህትና ወንድሞቻቸው ላይ ጨከኑ፤ ሁኔታውን የታዘበውና እራሱን ወይም ልጁን በተደብዳቢዎቹ ቦታ አድርጎ ማሰብን እግዜር ለገለጠለት ሰው ልብ የሚያደማ ክስተት ነበር። የነገ ሀገር ተረካቢ ተማሪ እግር እግሩን በሰደፍ ሲቀለጠም፣ ወንዶች እንደ ሴት እያለቀሱ ሲለምኑ፣ ሴቶች ጫማዎቻቸውን እያወለቁ ከዱላው ለማምለጥ በፍርሀት ሲሮጡ፤ "እኔ እግዚአብሄርን ምንም የማውቀው ነገር የለም!" እያሉ በሀገራቸው ቋንቋ ቢለምኑም፣ የሀገራቸውን ፖሊስ ቢማፀኑም እንደባይተዋር የሚሰማቸው ሲያጡ በአይነ ህሊናው ታወሰው። ከዚያም ከጥቂት የተቃውሞው ጓደኞቹ ጋር የመጥረጊያና መወልወያ ዱላዎችን ሰባብረው ራሳቸውን ለመከላከል ሲይዙ፤ ከዚያም እንደአባቶቻቸው በትሮቻቸውን ይዘው "ሆ!" እያሉ ወደ ፖሊሶቹ ሲሄዱና ሲያስፈራሯቸው ቀጥሎ ግን ለየት ያለመለዮ የለበሱና ክላሻቸውን ያነገቡ የፀጥታ ሃይሎች ከፓትሮል ዱብ ዱብ ብለው ሲወርዱ፤ ከእነርሱም መሃል መሳሪያውን ደቅኖ ወደ እርሱ ሲመጣ፤ ቀልሃውን ስቦ ሲተኩሰው፤... በድንጋጤ ከተኛበት ድንገት ቁጭ ብሎ አይኖቹን ገለጠ። ከፊቱ አንድ መልካቸው አዲስ ያልሆነበት ሰው ቆመዋል። ሌባ ጣታቸውን ከንፈራቸው ላይ አድርገው ዝም እንዲል ነገሩትና ለጥ ብሎ ወደተኛው ቢሊሱማ ጠቆሙት፤ አትረብሸው እንደሆነ ገብቶታል።

"እማ ጋሪዳ'፤ (አሁን ደህና ነህ?)" አሉት ትከሻውን ይዘው ወደ አልጋው እያስተኙት።

"እንዳትረሳ ልጄ ያንተ መንገድ ገና ነው። ጥይትም ሆነ ዱላ ሊገድሉህ አይቻላቸውም፤ አንተ ደምና ስጋ ብቻ ሳትሆን ታላቅ ዓላማ ያለህ ማንነት ነህና። እንግዲህ አሁንም ደህና ሆነሃል እጣ ፈንታህን ተከትለህ ከወልዲያ በስተምዕራብ ማዶ ወዳለች አሮሞ ወደምትባል አካባቢ አቅና‹፤ ‹ኦቦ አራርሳን› ብለህም ጠይቅ ታገኘኛማለህ!" አሉት በእርጋታ፤

"ገሩ… (ግን)…" ግን ብሎ ሊያወራ ሲል አሁንም ጣታቸውን ከንፈራቸው ላይ አድርገው "እሽሽ… ማረፍ አለብህ፤" አሉት፤ ተመልሶ ተኛ:: እርሳቸውም ብልቃጣቸውን መልሰው ከከረጢታቸው መልሰው ከተቱ:: ቀስ ብለውም ቢሊሱማ ያለበትን ወንበር ዞረው አለፉና በሩን ከፍተው ወጡ::

"ቢሊ?… ቢሊ?… ቢሊሱማ?" አለ ቶላ ከቅድሙ በርተት ባለ ድምፅ፤

ቢሊሱማ ተነሳና ጓደኛው እንደነቃ ሲያይ እጅግ በጣም ተደስቶ አልጋው ላይ ተፈናጦ አቀፈው::

"እንዴት ሊሆን ቻለ?… ብዙ ደም እኮ ፈሶህ ነበረ!" አለና ቀኝ ትከሻው ላይ ያለውን ፋሻ ከፈት ሲያደርግ በአድናቆት ደንዝዞ ቀረ:: ከቶላ ትከሻ ላይ የነበረው በጥይት የተመታበት ቁስል የቆየ ጠባሳ ይመስል ሙሉ ለሙሉ ደርቆ ነበር:: …"ለሳምንት ነበር እንዴ የተኛሁት?" አለው እየሳቀ፡

"ሁሉንም እነግርሃለሁኝ ቁጭ በል፤" አለው ቶላ::

ቢሊሱማም እየሰጠው የነበረው ደም ስላበቃ ዘጋለትና ከጎኑ ተቀመጠ:: ቶላም ስለአባ-ገዳው መምጣትና እሱን ስለማከማቸው አጫወተው:: ቢሊሱማም በሰማው ሁሉ በጣም ከተገረመ በኋላ በእርግጥም ይሄ ተዓምር እንደሆነና አባ-ገዳው እንዳሉት ‹‹ኦሮሞ›› የሚባለው አካባቢ መሄድ እንዳለበት ሲመክረው ቶላም መሄድ ፈልጎ እንደነበር ግን ገንዘብ እንዳሌለው አጫወተው:: ቢሊሱማም የዚህ ወር ደሞዝ ወጥቶለት ነበርና ብር እሱ እንደሚሰጠው ተስማሙ:: በዚህ ሰዓት ነበር ኢትኤል ለቶላ <<ልንሄድ ነው›› ብሎ የደወለለት::

*** ⚲ – ⚲ ***

ፕ/ር እሴ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲውን ስልጠና ጨርሰው ሲወጡ ፍሬድሪካ መጨቃጨቋን አላቆመችም ነበር::

"*I think you have forgotten why you brought me here in the first place! (ከመጀመሪያውም የመጣንበትን ምክንያት የዘነጋኸው እየመሰለኝ ነው!)*"

"*What do you mean? (ምን ለማለት ፈልገሽ ነው?)*" ጠየቃት፡

"*We were supposed to go to Axum and solve the secret… instead you are giving useless lectures. (አክሱም ለመሄድና ሚስጥሩን ለመፍታት ነበር እኮ አመጣጣችን፤ አንተ ግን በተቃራኒው በየቦታው እየዞርክ ጥቅም የሌላቸውን ንግግሮች ታደርጋለህ!)*"

"*I didn't forget why we are here but these guys took me by surprise and I had no option but to give that lecture, (የመጣንበትን አላማ ዘንግቼው አይደለም፤ ግን በድንገት ነው እንዳስተምር የጋበዙኝ እናም አማራጭ አልነበረኝም::) አሏት፤*"

*"But it seems as if you were prepared for it (ነገር ግን ንግግሮቹን በደንብ የተዘጋጀኸባቸው ነው የሚመስሉት)" አሊቻቸው በሽሙጥ ዘይቤ፤*

"Not actually! (እንዲያ እንኳን አይደለም)" ብለው ፕ/ር እሴ ንግግራቸውን ሳይጨርሱ ፕ/ር ዳግማዊ እያጨበጨቡ ወደ እነርሱ መጡ::

"ፕ! ማለፊያ ንግግር ነበር!" አሉና አከለውም "ኑ በሉ! ወደ ሆቴላችሁ ልሸኛችሁ::" ብለው ወደ መኪናው ሲወስዷቸው፤

"Actually…" አሉ ፕ/ር እሴ የፕ/ር ዳግማዊን እጅ ያዝ እያደረጉት:: "የመኪና አከራዮች ጋር ብትወስደኝ እመርጣለሁኝ፤"

"ካልክ ምን ገዶኝ፤ እዚሁ አካባቢ የመኪና አከራይ ድርጅት ስላለ ወደዚያ ልወስዳችሁ፤" አሉና መሪውን አዙረው ቁልቁል መንዳት ጀመሩ፤

"እኔ የምልህ ያ የኔ ተማሪ የነበረው፤ አጭር መለጥ ያለ ልጅ? እንዲያውም የግቢው ሰቃይ ተብሎ የተሸለመው አያሌውን አወቅከው?" አሉ ፕ/ር እሴ ወደ ፕ/ር ዳግማዊ እየዞሩ፤

"አዎዋ በሚገባ እንጂ… አያዬን የሚረሳ አለ እንዴ?… ከእሱ ጋር እኮ በፌስቡክ በደንብ እናወራለን::"

"አዎ ከእኔም ጋር እንደዋወል ነበረ:: በሶሻል ሳይንስ ፒ.ኤች.ዲውን ጀርመን እንደጨረሰና ወልዲያ ዩንቨርሲቲ እየሰራ እንደሆነ ነግሮኝ ነበር:: አሁንም እዚያው ነው ያለው እንዴ?" ጠየቁ ፕ/ር እሴ፤

"አዎ እዚያው ነው ያለው፤ እንዴ አሁንማ ትልቅ ሰው ሆኖ ብታየው አታውቀውም፤ ገርጀፍጀፍ ብሏል:: ባልሳሳት በወልዲያ ዩኒቨርስቲ የሶሻልና ቢዝነስ ሳይንስ ክፍል ፕሬዝዳንት ነው::"

"እስኪ ስልኩን አፈላልግልኝ…"

"እሺ ግን ለምን ፈልገኸው ነው?"

"መሄድ ስላለብኝ ነው::"

"ወዴት?" አሉ ፕ/ር ዳግማዊ በጥያቄ አይን ፕ/ር እሴን እያዩ፤.."ወልዲያ፤" አሉ ፕሮፌሰሩ፤ በደፈናው::

*** ቶ – ቶ ***

*ወሎና ገራዶ ባቲና አምባሰል*
*እህል እየበሉ ሰው ወዶ መብሰልሰል፤*

*** ዮ – ዮ ***

እነኢትኤል አብዛኛውን የሌሊት ክፍል አልተኙም፡፡ ከዋሻው ውስጥ በተነጠፉ ሰሌኖች ላይ ተደርበው የተነጠፉት ሰፋፊ የፋርስ ምንጣፎች ላይ ነበር አስመራ ድርድር ሰርተው በተርታ የተኙት፡፡ ለመርየም ከዋሻው የወዲያኛ ጥግ ላይ ለብቻዋ ቦታ ተሰጣትና በምንጣፉ ላይ የተወሰኑ አንሶላዎች ተደራርበው ተነጠፉላት፤ ከወንዶቹ መለያ የሚሆንም ሽራ ተወጥሮ ተከለለላት፡፡ በአጠቃላይ ግን ሁሉም ያ ልስላሴና ሙቀት ለለመደው ገላቸው የሚመች መኝታ አልነበረም፡፡ የተወሰኑት ደረሳዎች ሌሊቱንም ሳይተኙ በለሆሳስ ቁርዓን ሲቀሩና ዱዓ ሲያደርጉ ነበር ሌሊቱን የገፉት፡፡ ዮሴፍ ሞባይሉን አብርቶ ቻርጁ እስኪዘጋበት ድረስ ‹ቻት› እያደረገበት ነበር፡፡ ኢትኤልም በአንድ በኩል የመኝታው መቆርቆር በሌላ በኩል የፅዮን ሃሳብ እያንገላታው እንቅልፍ አልወሰደውም ነበር፡፡ በተኛበት ሲገላበጥ ዘይኔ ሳይተኛ አይኖቹን ጣራው ላይ እንዳፈጠጠ አገኘው፡፡… "ዘይንሻ ምነው?… እንቅልፍ እንቢ አለሽ እንዴ?" አለው ኢትኤል ድምፁን ዝቅ አድርጎ፤

"አዎ ወላሂ፤ ይሄ ቦታ፣ እኚህ ሼህ በውስጤ ብዙ ጥያቄዎች ፈጥረውብኛል፡፡ እስኪ እያቸው እነዚህን ልጆች፤ ጠግበው ባይበሉም፣ ዘንጠው ባይለብሱም፣ መኝታው ባይመቻቸውም ልዩ ደስታና የመንፈስ ሰላም ይነበብባቸውል፡፡ ለምን እንደሆነ ታውቃለህ?…" አለው ዘይኔ ወደ ኢትኤል እየዞረ፡፡ ኢትኤልም «እኔ ምን አውቃለሁኝ» አይነት ፊት አሳየው፡፡ "እንዲህ ደስተኛ የሆኑት ህይወትን በዚህች አጭር እድሜ ባላት ዓለማዊ ኑሮ ስላልተመኗት ነው፡፡ የቀጣዩን ዓለም ሃጅርና ሽልማት እያሰቡ በመንፈሳዊ መብራት ቀኑንም ማታውንም በብርሃን ስለሚያሳልፉ ነው ፊታቸው በደስታ የፈካው፡፡" አለና ዘይኔ ለደቂቃዎች ዝም ብሎ ቆየ፤ ከዚያም "ትንሽ ውጪ ወጥቼ አየር ወስጄ ልምጣ፤" ብሎት ሌሎችን ላለመቀስቀስ በዝግታ ተነስቶ ሄደና ካልተኙት ደረሳዎች አንዱን የድንጋዩን በር ከፍቶለት ወጣ፡፡

ዘይኔ ከዋሻው ሲወጣ በከዋክብት ያጌጠ ውብ ሌሊት ነበር የተቀበለው፤ ጨረቃዋም ከፀሐይ የተዋሰችውን ብርሃን ፍንትው ብላ አንፀባርቃ ሌሊቱን ሌሊት ለማለት በሚከብድ ሁኔታ ደመቅመቅ አድርገውታል፡፡ ነፍስን ከሚያድስው ነፋሻማ አየር እየተነፈሰ ትንሽ እንደተራመደ ከሩቅ ባለ ጉቶ ላይ የተቀመጠ ሰው ተመለከተና ወደዚያው አቅጣጫ አቀና፤ አጠገቡ ሲደርስም ሼህ ከድር በቦታው ላይ ተቀምጠው አገኛቸው፡፡ እግሮቻቸውን አነፋረው በተለምዶ መጅሊስ እንደሚባለው አይነት አድርገው ተቀምጠዋል፤ ከፊታቸው በኮባ የተጠቀለለ ጫት ተቀምጧል፡፡

"ጫት መቃም ሃላል ነው እንዴ?" አላቸው ከጎናቸው እየተቀመጠ፤

"የሌላውን ባላውቅም ለእኔ ግን ሃላልም ሃራምም የምናደርገው እኛው ነን ብዬ አምናለሁኝ:: እንደናንተ ትውልድ ጫትን የእንቶ ፈንቶ ማዕድ ሳናደርገው፣ ሺሻ በምትሉት ጣዖትና ሲጋራ በምትሉት የጤና ጠንቅ ሳናጅበው፤ ለተመስጦና ንባብ ያማረ ምርቃናችንን በኸምር ሳንሰብረው በክብር ነበር የምንቅመው። " አሉትና ፈገግ ብለው አዩት::

"ልክ ዮሴፍና ኢትኤል እየቃሙ እንደሚያነቡት ማለት ነው?" አለ ዘይኔ፤

"አዎ ብዙ ኡለማዎችም ሌት ተቀን ከኢባዳቸው ጎን ለጎን ኢልምን ለማወቅ ይቅሙ ነበር፤ ሌሊቱን በሙሉ በነሻጣ ዱዓ ሲያደርጉ፣ ተፈጥሮን በተመስጦ ሲያስተነትኑ በኢባዳ ያነጉ ነበር... ለማንኛውም ወደዚህ ከመጣህ አይቀር እስኪ ሰማዩን ቀና ብለህ ተመልከት::" አሉት... ዘይኔ ቀና አለ፤ እርሳቸው ቀጠሉ "እኛ የሰው ልጆች እንደ ጨረቃ ነን:: ውብ ጨረቃ ብርሃንን ከፀሐይ ተቀብላ እንደምታንፀባርቅ ሁሉ እኛም እውቀትና ጥበብን ከእውቀት ባለቤት ከሆነው አምላካችን ቀስመን እናስተጋባለን:: ከእኛ ውስጥ ታላቅ ተቅዋ ያለውና በእምነት ኖሮ፤ በእውቀቱ የመጠቀ ሰው እንደደማቅ ኮከብ መስሎ ለሌሎች ሊያበራ ይችላል::" አሉትና ወደላይ ቀና ብለው ሰማዩን እያማተሩ፤

"በደንብ ቀና ብለህ እየው እስኪ አያምርም?" አሉት፤

"...በጣም ያምራል!" አለ፤ ዘይኔም እንደእርሳቸው ቀና ብሎ ሰማዩን እየተመለከተ:: ቀጠሉ... "ከምድር ቀርቶ ከፀሐይም በግዝፈትም ይሁን በሙቀት በብዙ ሺህ እጥፍ የሚበልጡ ኮከቦች እንዲህ እንደትናንሽ የዴኮሬሽን መብራቶች በአና ሰማይ ላይ፣ ካለ ገመድ፣ ካለ ምሰሶ ድጋፍ በአምላክ ሃይል ተንሳፈው ሲንቆጠቆጡ እንዴትስ ላያምሩ?... የዚህ ዘመን ልጆች ለአፍታ እንኳን ቀና ብላችሁ ሰማይን ሳታዩ ታረጃላችሁ:: የሰማይን ሰላም፣ የደመናን ፈትል፣ የወጋገን ፍካት፣ የጀንበርን ቅላት፣ የጨረቃን ግርማ፣ የከዋክብትን ፀዳል ያቀፈን የአማላክ የጥበብ ሸራ አንድም ቀን በአስተውሎ ሳታዩ፣ አንድም ቀን ሳታደንቁ፣ መንፈሳችሁን ሳታድሱ ታረጃላችሁ:: ማጎንበሱም በትህትናና መተናነስ ቢሆን እኮ ጥሩ ነበር፤ የሚያሳዝነው እናንተ የምታጎነብሱት ብር ለመቁጠር ብቻ መሆኑ ነው:: አብዛኛዎቻችሁ አጎንብሳችሁ ስትሰሩ፣ አጎንብሳችሁ ስታጠኑ፣ አጎንብሳችሁ ስልክና ኮምፒዩተሮቻችሁን ስትነካኩ የምትውሉት ጥበብና ፀጋን ሽታችሁ ሳይሆን ያንኑ ብር የመቁጠር፤ ዘመኑ የጣለባችሁን ግዴታ ለመወጣት ነው:: ከቀናት በአንዱ ግን ቀና ብላችሁ የሰማይን ስፋት ብታስተውሉ የእናንተ እጅ ላይ ያለው ብር እናንተን ያገለግል ዘንድ የተመረተ ስዕልና ቁጥር ያለው ጠባብ ወረቀት እንጂ የህይወት ትርጉም እንዳልሆነ ይገባችሁ ነበር::" ብለው በሽረፍታ ዘይኔን አዩት፤

"ልጄ ሆይ እንዳትረሳ፣ ብር እና ሃብት በእድሜህ ሂደት እየመጣ ሊሄድ ይችላል፣ አንተ ግን አንተ ነህ፣ ሰማይና ምድር ያንተ ሃብት ቢከመርም ደንታ የላቸውም፣ ፀሐይና ጨረቃም ጉዟቸውን ይቀጥላሉ:: እመነኝ በብርህ ኢቃን ልትሸምት ትችላለህ፣ የነፍስ እርካታን ግን አትሸምትም፣ በብርህ ጥሩ ምግብ ልትበላ ትችላለህ አፈር የማይበላውን ስጋ ግን መገንባት አትችልም፣ በብርህ ውብ ልብስ ልትገዛ ትችላለህ ግርማ ሞገስን ግን መግዛት አትችልም፣ በብርህ ወሲብንና አብሮ መሆንን ልታተርፍ ትችላለህ ፍቅርንና የጠለቀ ግንኙነትን ግን አትገዛም:: በእጅህ ያለው ብር ከላይ ያልኩህን ነገሮች ሊሰጥህ የሚችለው በጎነት ከተጨመረበት ብቻ ነው፣ በጎነት ደግሞ ከየዋህነትና ከእምነት ይወለዳል:: በጎ መሆንም ከሃብታሙ ይልቅ ለድሃው ይቀለዋል:: ሃብታሙ ጎንበስ ብሎ ብር ሲቆጥር ድሃው ወደሰማይ ቀና ብሎ ጥበብ ተመልክቷልና::" ብለው ወደ ዘይኔ ዞሩና፣ "በል ሂድ ልጄ በወሬ አደረቅሁ አይደል፣ ትንሽ እረፍ በልና ለሱቢህ ሶላት እንቀሰቅስሃለን::"

"እሺ፣" አላቸውና ተመልሶ ወደ ዋሻው ገባ:: ሌሊቱን በሙሉ አብሯቸው ሆኖ ቢያዳምጣቸው ግን ደስ ባለው ነበር::

*** ፉ – ፉ ***

በማግስቱ ማላዳ ሱቢህ ሶላት 11:30 ላይ ከተሰገደ በኋላ ለ30 ደቂቃ ያህል የቁርዓን መቅራት በደህና ተካሄደና ሼህ ከድር የተኙትም ተቀስቅሰው እንዲሰበሰቡ አዘዙ:: ለሶላት የተነሱት መርየምና ዘይኔ፣ ናዖድ፣ ኢትኤል እና አብርሃምን ቀሰቀሷቸው:: ሁሉም ብርዱ እያንቀጠቀጣቸው ተነስተው ሼህ ከድርን ከበቧቸው::

"ዛሬ የአላህ ፍቃድ ከሆነ፣ በመጀመሪያ የምነግራችሁ ትናንት ታሪኩን ያጫወትኳችሁ የእስያኤል ቅም አያት፣ የሙሴ አማት ስለሆኑት ኢትዮጵያዊ ወልይ ዮቶር-አብ ወይም አል-ኾዶር ነው::" ብለው ጀምሩ፣

"አሁንም ነብያችን ሙሐመድ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁንና ሁሌ ጁምዓ ቀን እንድናነበው ከመከሩን የቁርዓን ምዕራፍ ሱረቱል ካፍ፣ ከቁጥር 60 ጀምሮ እንደተፃፈው እና በሰሂህ ቡኻሪ ክፍል 6 ቁጥር 249 ተዘግቦ እንደሚገኘውና ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) በተናገሩት መሰረት፣ ከእለታት አንድ ቀን እስራኤሎችን ከግብጽ ባርነት ለማውጣት የተላከው ነብይ ሙሴ (ዐ.ሰ) ለተከታዮቹ እያስተማረ እያለ ከሚሰሙት ሰዎች መካከል አንዱ እጁን አወጣ:: እድሉ ሲሰጠውም "በምድር ላይ ካሉ ሰዎች በሙሉ በእውቀት የሚበልጠው ማነው?" ብሎ ጠየቀው::

"የሌላውን ባላውቅም ለእኔ ግን ሃላልም ሃራምም የምናደርገው እኛው ነን ብዬ አምናለሁኝ:: እንደናንተ ትውልድ ጫትን የእንቶ ፈንቶ ማዕድ ሳናደርገው፤ ሺሻ በምትሉት ጣያትና ሲጋራ በምትሉት የጤና ጠንቅ ሳናጅበው፤ ለተመስጦና ንባብ ያማረ ምርቃናችንን በኸምር ሳንሰብረው በክብር ነበር የምንቅመው። " አሉትና ፈገግ ብለው አዩት::

"ልክ ዮሴፍና ኢትኤል እየቃሙ እንደሚያነቡት ማለት ነው?" አለ ዘይኔ፤ "አዎ ብዙ ኡለማዎችም ሌት ተቀን ከኢባዳቸው ጎን ለጎን ኢልምን ለማወቅ ይቅሙ ነበር፤ ሌሊቱን በሙሉ በነሻጣ ዱዓ ሲያደርጉ፣ ተፈጥሮን በተመስጦ ሲያስተነትኑ በኢባዳ ያነጉ ነበር… ለማንኛውም ወደዚህ ከመጣህ አይቀር እስኪ ሰማዩን ቀና ብለህ ተመልከት::" አሉት… ዘይኔ ቀና አለ፤ እርሳቸው ቀጠሉ "እኛ የሰው ልጆች እንደ ጨረቃ ነን:: ውብ ጨረቃ ብርሃንን ከፀሐይ ተቀብላ እንደምታንፀባርቅ ሁሉ እኛም እውቀትና ጥበብን ከእውቀት ባለቤት ከሆነው አምላካችን ቀስመን እናስተጋባለን:: ከእኛ ውስጥ ታላቅ ተቅዋ ያለውና በእምነት ኖሮ፤ በእውቀቱ የመጠቀ ሰው እንደደማቅ ኮከብ መስሎ ለሌሎች ሊያበራ ይችላል::" አሉትና ወደላይ ቀና ብለው ሰማዩን እያማተሩ፤ "በደንብ ቀና ብለህ እየው እስኪ አያምርም?" አሉት፣

"…በጣም ያምራል!" አለ፤ ዘይኔም እንደእርሳቸው ቀና ብሎ ሰማዩን እየተመለከተ:: ቀጠሉ… "ከምድር ቀርቶ ከፀሐይም በግዝፈትም ይሁን በሙቀት በብዙ ሺህ እጥፍ የሚበልጡ ኮከቦች እንዲህ እንደትናንሽ የዴኮሬሽን መብራቶች በአና ሰማይ ላይ፣ ካለ ገመድ፣ ካለ ምሰሶ ድጋፍ በአምላክ ሃይል ተንሳፈው ሲንቆጠቆጡ እንዴትስ ላያምሩ?… የዚህ ዘመን ልጆች ለአፍታ እንኳን ቀና ብላችሁ ሰማይን ሳታዩ ታረጃላችሁ:: የሰማይን ሰላም፣ የደመናን ፈትል፣ የወጋገን ፍካት፣ የጀንበርን ቅላት፣ የጨረቃን ግርማ፣ የከዋክብትን ፀዳል ያቀፈን የአማላክ የጥበብ ሸራ አንድም ቀን በአስተውሎ ሳታዩ፣ አንድም ቀን ሳታደንቁ፣ መንፈሳችሁን ሳታድሱ ታረጃላችሁ:: ማጎንበሱም በትህትናና መተናነስ ቢሆን እኮ ጥሩ ነበር፤ የሚያሳዝነው እናንተ የምታጎነብሱት ብር ለመቁጠር ብቻ መሆኑ ነው:: አብዛኛዎቻችሁ አጎንብሳችሁ ስትሰሩ፣ አጎንብሳችሁ ስታጠኑ፣ አጎንብሳችሁ ስልክና ኮምፒዩተሮቻችሁን ስትነካኩ የምትውሉት ጥበብና ፀጋን ሽታችሁ ሳይሆን ያንኑ ብር የመቁጠር፤ ዘመኑ የጣለባችሁን ግዴታ ለመወጣት ነው:: ከቀናት በአንዱ ግን ቀና ብላችሁ የሰማይን ስፋት ብታስተውሉ የእናንተ እጅ ላይ ያለው ብር እናንተን ያገለግል ዘንድ የተመረተ ስዕልና ቁጥር ያለው ጠባብ ወረቀት እንጂ የህይወት ትርጉም እንዳልሆነ ይገባችሁ ነበር::" ብለው በሽረፍታ ዘይኔን አዩት፤

"ልጄ ሆይ እንዳትረሳ፤ ብር እና ሃብት በእድሜህ ሂደት እየመጣ ሊሄድ ይችላል፤ አንተ ግን አንተ ነህ፤ ሰማይና ምድር ያንተ ሃብት ቢከመርም ደንታ የላቸውም፤ ፀሐይና ጨረቃም ጉዟቸውን ይቀጥላሉ:: እመነኝ በብርህ አቃን ልትሸምት ትችላለህ፤ የነፍስ እርካታን ግን አትሸምትም፤ በብርህ ጥሩ ምግብ ልትበላ ትችላለህ አፈር የማይበላውን ስጋ ግን መገንባት አትችልም፤ በብርህ ውብ ልብስ ልትገዛ ትችላለህ ግርማ ሞገስን ግን መግዛት አትችልም፤ በብርህ ወሲብንና አብሮ መሆንን ልታተርፍ ትችላለህ ፍቅርንና የጠለቀ ግንኙነትን ግን አትገዛም:: በእጅህ ያለው ብር ከላይ ያልኩህን ነገሮች ሊሰጠህ የሚችለው በጎነት ከተጨመረበት ብቻ ነው፤ በጎነት ደግሞ ከየዋህነትና ከእምነት ይወለዳል:: በጎ መሆንም ከሃብታሙ ይልቅ ለድሃው ይቀለዋል:: ሃብታሙ ጎንበስ ብሎ ብር ሲቆጥር ድሃው ወደሰማይ ቀና ብሎ ጥበብ ተመልክቷልና::"

ብለው ወደ ዘይኔ ዞሩና፤ "በል ሂድ ልጄ በወሬ አደረቅሁ አይደል፤ ትንሽ አረፍ በልና ለሱቢህ ሶላት እንቀሰቅስሃለን::"

"እሺ፤" አላቸውና ተመልሶ ወደ ዋሻው ገባ:: ሌሊቱን በሙሉ አብሯቸው ሆኖ ቢያዳምጣቸው ግን ደስ ባለው ነበር::

*** ፆ – ፆ ***

በማግስቱ ማላዳ ሱቢህ ሶላት 11:30 ላይ ከተሰገደ በኋላ ለ30 ደቂቃ ያህል የቁርዓን መቅራት በደህና ተካሄደና ሼህ ከድር የተኙትም ተቀስቅሰው እንዲሰበሰቡ አዘዙ:: ለሶላት የተነሱት መርየምና ዘይኔ፣ ናዖድ፣ ኢትኤል እና አብርሃምን ቀሰቀሷቸው:: ሁሉም ብርዱ እያንቀጠቀጣቸው ተነስተው ሼህ ከድርን ከበቧቸው::

"ዛሬ የአላህ ፍቃድ ከሆነ፤ በመጀመሪያ የምነግራችሁ ትናንት ታሪኩን ያጫወትኳችሁ የእስያኤል ቅም አያት፤ የሙሴ አማት ስለሆኑት ኢትዮጵያዊ ወልይ ዮቶር-አብ ወይም አል-ኾዶር ነው::" ብለው ጀምሩ፤

"አሁንም ነብያችን ሙሐመድ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁንና ሁሌ ጁምዓ ቀን እንድናነበው ከመከሩን የቁርዓን ምዕራፍ ሱረቱል ካፍ፣ ከቁጥር 60 ጀምሮ እንደተፃፈው እና በሰሂህ ቡኻሪ ክፍል 6 ቁጥር 249 ተዘግበ እንደሚገኘውና ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) በተናገሩት መሰረት፤ ከእለታት አንድ ቀን እስራኤሎችን ከግብጽ ባርነት ለማውጣት የተላከው ነብይ ሙሴ (ዐ.ሰ) ለተከታዮቹ እያስተማረ እያለ ከሚሰሙት ሰዎች መካከል አንዱ እጁን አወጣ:: እድሉ ሲሰጠውም "በምድር ላይ ካሉ ሰዎች በሙሉ በእውቀት የሚበልጠው ማነው?" ብሎ ጠየቀው::

ገና በነብይነቱ ብዙ አመታትን ያልዘለቀው ነብይ ሙሴ ደረቱን ነፋ አድርጎ "እኔ ነኝ ከሁሉም በዓለም ላይ ካሉ ሰዎች የምበልጥ አዋቂ!" ብሎ መለሰ፤ ሙሴም ዘወትር እንደሚያደርገው ማስተማሩን እንደጨረሰ ራዕይ ይቀበል ዘንድ ለመፀለይ ወደ ኮረብታ ወጣ፡፡ እየፀለየ ሳለም የአምላክ ድምፅ ወደ እሱ መጣ፡ ‹‹እኔ አዋቂ ነኝ!›› ብሎ በመታበዩ ፈጣሪው ተቆጥቶ ነበር፡፡

የአምላክ ድምፅም፤ "ሂድ የሁለቱ ጅረቶች መገናኛ ከሆነው ቦታ፤ ካንተ የበለጠ አዋቂ የሆነን፤ የኔን አገልጋይ ባሪያ ታገኛለህ፤" አለው፤

ሙሴም "ጌታዬ ግን የጅረቱን መለያ እንዴት አገኘዋለሁኝ?" ብሎ ጠየቀ፡፡

አላህም "አንዲት አሳ ያዝና ሂድ፤" አለው፤ ከዚያም ሙሴ ዓሳውን በቅርጫት ለአገልጋይ ልጁ አስይዞ አዋቂ የተባውን ሰው ፍለጋ ጉዞ ጀመሩ፡፡ ለረጅም ጊዜ ይህ የእውቀት ባለቤት ሰው ያለበትን ቦታ ቢፈልጉም አላገኙትም ነበር፡፡ በጣም ደከማቸውናም ከአገልጋያቸው እያሱ ጋር ከአንድ ቋጥኝ ጎን አረፍ አሉ፡፡

"የጅረቶቹ መገናኛ ጋር እስከደርስ ድረስ መንገዴን አላቆምም፤ አመታትን ቢፈጅብኝም ተስፋ ግን አልቆርጥም!" አለው ሙሴ፤ አገልጋዩን እያሱን፤

ሂዱ ከተባሉበት ከጅረቱ ገባሮች መገናኛ ጋር ሲደርሱ ግን ቀኑ መሸትሸት ብሎ ነበር፡፡ በቦታው ካለ ቋጥኝ ላይ ጋደም ያለ እነርሱ ያላዩት አንድ ሽማግሌ ጥቁር ሰውም ነበር፡፡ አላህ የመራቸው ቦታ ላይ እንደደረሱ ያላወቁት ሙሴና እያሱ ግን አላስተዋሉም ነበርና ቋጥኙን ደገፍ ብለው እንቅልፍ ጣላቸው፡፡ እያሱም ቅርጫቱን መሸፈን ረሳ፤ ይዘውት የመጡት ዓሳም በሃይል እየተወራጨ ከቅርጫቱ ዘሎ ወጣና ትንግርት በሆነ መንገድ በዚግዛግ ቅርፅ በጅረቱ ላይ እየዋኘ ሄደ፤ አላህም ዓሳው የሄደበትን የፈፋውን መንገድ ውሃውን አቆመው፤ እንደ ሸለቆ አድርጎም አበጀው፡፡ ሙሴና እያሱም ከቋጥኙ ስር ሌሊቱን አሳለፉና በማግስቱ ጥዋት መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡ ያንን ቀንና ሌሊቱን በሙሉ በተሳሳተ መንገድ ተጓዙ፡፡ ቀጣዩን ሌሊት እንዳሰለፉ በጥዋት ሲነሱ ግን በጣም ርቧቸው ነበር፤

ምሳ ሰዓት አካባቢ ሙሴ(ዐ.ሰ) እያሱን፤..."እስካሁን ብዙ ተጉዘን ሰውነታችን ዝሏል ግን ቦታውን አላገኘነውም፡፡ በጣም ደክሞናል፣ ርቦናልም፤ ስለዚህ የያዝከውን ዓሳ አውጣና እንብላው፤" ብሎ አዘዘው፡፡

እያሱ ግን ፊራ ተባ እያለ ሽይጣን አዘናግቶት ዓሳው እንዳመለጠውና ትንግርት በሆነ መንገድ በውሃው ላይ እንደሄደ ነገረው፡፡ ሙሴ ይህንን ሲሰማ ወዲያውኑ ከተቀመጠበት ተነሳና፤

"ታዲያ ይሄ ነበር እኮ ስንፈልገው የነበረው ምልክታችን፤ በል ና አሁን የመጣንበትን መንገድ ተከትለን ወደ ቋጥኙ እንመለስ፡፡" አለውና

ፈለጎቻቸውን እየተከተሉ ተመለሱ:: ከአንድ ቀን በፊት ተደግፈውት ከተኙት ቋጥኝ ጋር ሲደርሱም እነሆ አንድ ጋቢ ያገለደመ ሰው ጋደም ብሎ ተኝቶ አገኙት::

"አንተ ነህ አዋቂው ሰው?" አለ ሙሴ ለማረጋገጥ ጓግቶ፤

አል-ኸዶርም በግርምት ዞር ብሎ ካስተዋለው በኋላ "እናንተ ሃገር እንደዚህ ነው እንዴ ሰው ሰላም የምትሉት?" አለው በቀልድ ለዛ፤

"እኔ እኮ ሙሴ ነኝ፤" አለ ሙሴ፤

"እንዴ አንተ ነህ እንዴ ለእስራኤል ልጆች የተላከው ነብይ?"

"አዎ እኔ ነኝ፤ ከምታውቀው እውቀትም ታስተምረኝ ዘንድ ነው ወዳንተ የመጣሁት አለው::"

"ሙሴ ሆይ፤ አምላክ ላንተ አሳውቆህ ለእኔ ያላሰወቀህ እውቀት እንዳለ ሁሉ፤ ለእኔ አሳውቆኝ ላንተ ያላሰወቀው ነገርም እርግጥ አለ:: ነገር ግን አንተ ከኔ ጥበብ ለመማር ትዕግስቱ ያለህ አይመስለኝም::" አለው::

"እንደፈጣሪ ፍቃድ ታጋሽ ለመሆን እሞክራለሁኝ፤ አንተንም የምታዘኝን ሁሉ እፈጽማለሁኝ፤ አስተምረኝ::" አለ ሙሴ ለማወቅ እየጓጓ፤

አል-ኸዶርም ከተቀመጠበት ተነሳ፤ "እሺ ካልክ አስተምርሃለሁኝ፤ ግን እኔ እስከምነግርህ ድረስ ምንም ጥያቄ መጠየቅ አይፈቀድልህም!" አለውናም አብረው ጉዞ ጀመሩ:: ከባህር ዳር እንደደረሱም በአካባቢው የነበሩ የጀልባ ባለቤቶች ካህኑን አል-ኸዶርን (ዮቶር-አብን)ን ስለሚያውቋቸው ካለምንም ክፍያ አሳፈሯቸው::"... አሉና ሼህ ከድር አንዱን ደረሳቸውን ወተት እንዲያመጣላቸው ነገሩት::

"ታሪኩን በሚገባ እየተከተላችሁ ነው አይድል ልጆች?" አሉ ሁሉንም ተራ በተራ እየተመለከቱ፤ "አዎ፤ ያ ኡስታዝ!" አሉ፤

ከመጣላቸው ወተት አንዴ ተጎነጩለትና ትረካቸውን ቀጠሉ፤ "እና ሙሴና አል-ኸዶር በጀልባው ተሳፍረው መጓዝ ጀመሩ:: እየተጓዙ ሳሉ አንዲት ድንቢጥ ወፍ መጣችና ከጀልባው ጠርዝ ላይ አረፈች፤ ጎንበስ ብላም ከባህሩ በመንቆሯ አንዴ ጠጣችለት::

አል-ኸዶርም ወደ ሙሴ ዞሩና "ከአምላካችን ዘንድ ካለው እውቀት አንፃር እኔና አንተ ዘንድ ያለን እውቀት ልክ ይህቺ ወፍ በማንቆሯ አንዴ የጠጣችውን ውሃ ይመስላል::" አሉት፤ ሙሴም በነገሩት እየተገረመ ጉዞው ቀጠለ:: በድንገት ግን ሙሴ ሲዞር፤ አል-ኸዶር አነስተኛ መጥረቢያ ይዞ ከጀልባው ርብራቦች መካከል አንዱን ጣውላ ሲነቅል አየው:: ከጠረፍ ሲደርሱም እነሙሴና አል-ኸዶርን ጨምሮ ሁሉም ተሳፋሪዎች ከጀልባው ወረዱ፤

ባለቤቶቹም ቢሆኑ ጀልባቸው ቀስበቀስ በውሃ እየተሞላ መሆኑን አላወቁም ነበር።

"እነዚህ ጥሩ ሰዎች በነጻ አሳፍረውን ሲያበቁ እንዴት ጀልባቸውን ታስምጥባቸዋለህ?" አለ ሙሴ አል-ኸዶርን በቁጣ እየተመለከተ፤

"እንግዲህ ቅድም የነገርኩህን መርሳት ጀምረሃል ማለት ነው። እኔ እስከነግርህ ድረስ ምንም አይነት ጥያቄ እንዳትጠይቅ ብዬህ አልነበረምን?..."

"እባክህን ያልከኝን በመርሳቴ ይቅርታ አድርግልኝ፤ ከዚህ በኋላ ለተቀረው መንገዳችን ግን ታጋሽ ለመሆን እጥራለሁኝ፤" አለ ሙሴ፤

"‹‹ትዕግስቱ ካለህ እንቀጥላለን፤›› አላቸው" ብለው ሼህ ከድር ትረካቸውን ሊቀጥሉ ሲሉ.. "እንኳንስ እሱ እኔም ትዕግስቴ አልቋል፤ ቶሎ ወደ ታሪኩ መጨረሻ ብትደርሱ ደስ ይለኛል።" አለ ዮሴፍ ንግግራቸውን እያቋረጠ፤

"ልጄ ትንሽ ትዕግስት ይኑርህ ታሪኩ ወደ መገባደጃው ነው።" አሉና ሼህ ከድር ታሪኩን መናገር ቀጠሉ... "ከዚያም ነብዩ ሙሴና አል-ኸዶር አንድ ላይ በባህሩ ዳርቻ ሲጓዙ ልጆች ተሰብስበው ሲጫወቱ ተመለከቱ። አል-ኸዶርም ከልጆቹ መኃል አንዱን ልጅ ነጥሎ ወሰደውና አንገቱን ቆርጦ ገደለው።" ሲሉ ዮሴፍ ዳግም ጣልቃ ገባና... "ጭራሽ ህጻን መግደል ያለበት ታሪክ ልሰማ ነው እንዴ እዚህ ድረስ የመጣሁት!" ብሎ ከመቀመጫው ዘሎ ተነስቶ ሄደ። ዘይኔና መርየም ታሪኩን ቀድመው ስለሚያውቁ አልተገረሙም ነበር። ኢትኤልና አብርሃም ግን ታሪኩ ባይዋጥላቸውም ቃል አልተነፈሱም። ከሰኮንዶች በኋላ ዮሴፍ ቦርሳውን ሸክፎ ከዋሻው ሲወጣ ተመለከቱት።

"እንዴ ጆሲ ወዴት እየሄድክ ነው?" አለ ናዖድ ግራ በመጋባት፤

"ኧረ ባክህ እኔ እዚህ ድረስ የመጣሁት ከእናንተ ጋር ፈታ እላለሁኝ ብዬ እንጂ የማይመስል ታሪክ ልሰማ አይደለም።" አለ ወደ ሼህ ከድር እያየ፤ እርሳቸው ግን መልስም ሳይሰጡት ሙስብሃቸውን እየቆጠሩ ነበር።

"እና ምን እያደረክ ነው?" አለው ኢትኤል፤

"ሳይመሽብኝ ከዚህ ልሂድና የአዲስ አባ መኪና ይገኝ ልመለስ ነው።" አለ ዮሴፍ በቁርጠኝነት፤

"እንዴ ቢጨርሱልህ ኖሮ እኮ ታሪኩን ትረዳው ነበር ወላሂ፤" አለ ዘይኔ ተነስቶ ወደሱ እየመጣ፤

"ፍቱኝ ቢቃ! እኔ ከዚህ በላይ ካለ ጥቅም የምሰቃይበት ምክንያት አይታየኝም። ሲጀምር ህልሙን ያየችሁት እናንተ በማያገባኝ እኔ ምን ቤት

ነኝና ነው፤ ይልቅ ከእኔ ጋር የሚሄድ ካለ ግን መምጣት ይችላል፡፡" አለ ሁሉንም አንድ በአንድ እያየ፤... የሚያጅበው ሰው ግን አላገኘም ነበር፡፡

"መንገዱንም እኮ አታውቀውም፡፡" አለች መርየም ሃሳብ እየያዛት፤

"ጃዕፈር ይህን ልጅ በሰላም ወደከተማ አድርሰኸው መኪና አሳፍረው፡፡ ልቡ ባልፈቀደበት ቦታ ማገንም እንዲሆን አይገባም፡፡" አሉና ሼህ ከድር ሃሳቧን ፈቱላት፤ ዮሴፍም ሁሉም ጓደኞቹ ጋር ከተሰነባበተ በኋላ ከጃዕፈር ጋር ወደ ወላጆቹ ለመሄድ ጉዞውን ጀመረ፡፡

ሁሉም ወደየቦታቸው እስኪመለሱ ድረስ ጠበቁና ሼህ ከድርም ትረካቸውን ቀጠሉ፤ "እናም ይገርማችኋል ሙሴ የአል-ኸዶርን ስራ ባየ ጊዜ እጅግ በጣም ተበሳጭቶ አል-ኸዶርን መውቀስ ጀመረ፡፡ ሰው መግደል ምን ያህል ታላቅ ሃጢያት እንደሆነ እየሰበከ ተናገራቸው፡፡ አል-ኸዶር ግን ቃላት ሳይተነፍሱ ከቆዩ በኋላ... "ሙሴ ሆይ! ከዚህ በላይ አብረን መዝለቅ የምንችል አይመስለኝም፤ ትዕግስቱ እንደማይኖርህ ከመጀመሪያም ነግሬህ ነበር፡፡" አሉት ትንሽ እየተቆጡ፤

ሙሴም ስህተቱ ሲገባው... "እሺ ይቅርታ ይደረግልኝ፤ ከዚህ በኋላ አንዲት ቃል ብተነፍስ ከመንገድህ አባረኝ፤" አለ ሙሴ በተማፅዕኖ፤

አል-ኸዶር - "እሺ ለመጨረሻ ጊዜ ይቅርታ አድርጌልሃለሁኝ፡፡" አሉና መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡ ከዚያም ትንሽ እንደተጓዙ አንዲት ከተማ ጋር ደረሱ፡፡ ደክሟቸውና ርቧቸው ስለነበርም በከተማይቱ ያሉትን ሰዎች ምግብና መጠለያ እንዲሰጧቸው ጠየቋቸው ሰዎቹ ግን ምንም አንሰጥም ብለው አባረሯቸው፡፡ ነገር ግን ከከተማው እየወጡ ሳለ አንድ ሊፈርስ ጫፍ ላይ የደረሰ ግንብ ተመለከቱ፡፡ አል-ኸዶርም ግንቦቹን በእጆቹ ይዞ ቆየና አፀናው፤ ወደ ቀድሞ ሁኔታውም ተመልሶ አዲስ ግንብ መሰለ፡፡

ሙሴም፤ "እንዲህ ተቸግረንና ተርበን አይተው ላባረሩን ሰዎች በጎ ነገር መስራት ምን ያደርጋል? ቢያንስ እኮ የስራህን ዋጋ ገንዘብ መቀበል ትችል ነበር፡፡" አለው፤

አል-ኸዶርም በሙሴ ተስፋ ቆረጠበት፤ "እንግዲህ የእኔና የአንተ የመለያያችን ቦታ ይሄው ነው፡፡ ስለሦስቱ ትዕግስት ስላጣህባቸው ነገሮች አሁን እነግርሃለሁኝ፡፡ የመጀመሪያው፤ የጀልባውን ጣውላ ፈንቅዬ ውሃ እንዲገባበትና እንዲሰምጥ ያደረግኩት በእዚያ አንድ አንባገነን መሪ ጀልባዎችን በሙሉ በጉልበቱ እየወረሰ ስለነበር ነው፡፡ እነዚህ ድሃ የጀልባይቱ ባለቤቶች ይህ ንጉስ ካለፈ በኋላ በከፊል የሰመጠው ጀልባቸውን አውጥተው እንዲጠቀሙም ነው፡፡

ሁለተኛ ላይ ስለገደልኩት ልጅ ማወቅ ከፈለግክ ደግሞ እናትና አባቶቹ እጅግ አመስጋኝና አማኝ ሰዎች ሲሆኑ ቤታቸውም በሰላም የተሞላ ነው:: ይህ ልጅ ግን እድጎ ከጎረመሰ ትዕቢቱ ሰማይ የሚነካ ለወላጆቹና ማህብረሰቡ ታላቅ መከራ የሚያመጣ መሆኑን አምላክ ስላሳየኝ ነው የገደልኩት::

ሦስተኛው ፈርሶ አግኝተነው ያደስኩት ግንብ ደግሞ የሁለት እናት አባታቸው የሞቱባቸው ህፃናት ርስት ነው:: አባታቸው ፃድቅ ሰው የነበረ ሲሆን ለልጆቹ ውርስ ብሎም ከዚያ ግንብ ስር ብዙ ወርቆች ቀብሮ አስቀምጦላቸዋል:: ስለዚህ ግንቡን ያደስኩላቸው ልጆቹ ለአቅመ አዳም ደርሰው ወርቁን እስኪያወጡት ድረስ ሌላ ሰው በቀላሉ እንዳያገኘውና እንዳያወጣባቸው ነው::" አለና አል-ኽዶር ሙሴን ትቶት ሄደ አላችኋለሁኝ::" አሉ ሼህ ከድር፤ ከዚያም ተራ በተራ ሁሉንም ተመለከቷቸው፤

"በጣም የሚገርም፣ የመታገስን ክብደት የሚያሳይ አስተማሪ ታሪክ ነው::" አለ ኢትኤል፤

"አዎ እኔም ገርሞኛል ግን እስካሁን ድረስ በእኛ መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው ከዮቶር-አብ ጋር ብዙም ግንኙነቱ ሊታየኝ አልቻለም፤" አለ አብርሃም::

"እኔም የሱን ሃሳብ እጋራለሁኝ፤ ደግሞም ስለኢትዮጵያዊነቱ ምን ማረጋገጫ አለ?"... ጠየቀ ናዖድ ቀበል አድርጎ::

"ወደዚያ ክፍል ገና ልመጣላችሁ ነበር:: ከዚህ ታሪክ እንግዲህ በግልፅ ማየት እንደሚቻለው አል-ኽዶር ከነብዩ ሙሴ እጅግ በእውቀትና ትዕግስት የበለጡ ካህን መሆናቸውን እንረዳለን:: ሙሴም ትዕግስት በማጣቱ ምክንያት ፈጣሪን እወቅ ብሎ የላከውን እውቀት አላገኘም:: ወደ መፅሐፍ ቅዱስ ገብተን ስናጠና ሙሴ ትዕግስቱን መቆጣጠር አቅቶት ግብፃዊ እንደገደለና ከዚያም እንዴት እንደሸሸ ከኦሪት ዘ-ጸአት ምዕራፍ ሁለት ከቁጥር 11 እስከ 22 እንዲህ ይነግረናል፤" አሉና ኪታባቸውን ገልጠው ማንበብ ጀመሩ::

"*11፤ በዚያም ወራት እንዲህ ሆነ፤ ሙሴ የጉብዝናው ወራት ላይ በደረሰ ጊዜ ወደወንድሞቹ ወጣ ፥ የሥራቸውንም መከራ ተመለከተ፤ የግብፅም ሰው የወንድሞቹን የዕብራውያንን ሰው ሲመታ አየ:: 12፤ ወዲህና ወዲያም ተመለከተ ፥ ማንንም አላየም ፥ ግብፃዊውንም ገደለው ፥ በአሸዋ ውስጥም ሸሸገው:: 13፤ በሁለተኛውም ቀን ወጣ፥ ሁለቱም የዕብራውያን ሰዎች ሲጣሉ አየ፤ በዳዩንም። ለምን ባልንጀራህን ትመታዋለህ? አለው። 14፤ ያም። በእኛ ላይ አንተን አለቃ ወይስ ዳኛ ማን አደረገህ? ወይስ ግብፃዊውን እንደ ገደልኸው ልትገድለኝ ትሻለህን? አለው። ሙሴም። በእውነት ይህ ነገር ታውቆአል ብሎ ፈራ። 15፤ ፈርዖንም ይህን*

ነገር በሰማ ጊዜ ሙሴን ሊገድለው ፈለገ። ሙሴ ግን ከፈርዖን ፊት ኰበለለ፥ በምድያምም ምድር ተቀመጠ፤ በውኃም ጕድጓድ አጠገብ ዐረፈ።

16፤ ለምድያምም ካህን ሰባት ሴቶች ልጆች ነበሩት፤ እነርሱም መጥተው ውኃ ቀዱ፥ የአባታቸውንም በጎች ሊያጠጡ የውኃውን ገንዳ ሞሉ። 17፤ እረኞችም መጥተው ገፉአቸው፤ ሙሴ ግን ተነሥቶ ረዳቸው፥ በጎቻቸውንም አጠጣላቸው። 18፤ ወደ አባታቸው ወደ ራጉኤልም በመጡ ጊዜ። ስለ ምን ዛሬ ፈጥናችሁ መጣችሁ? አላቸው። 19፤ እነርሱም። አንድ የግብፅ ሰው ከእረኞች እጅ አዳነን፥ ደግሞም ቀዳልን፥ በጎቻችንንም አጠጣ አሉ። 20፤ ልጆቹንም። እርሱ ወዴት ነው? ለምንስ ያንን ሰው ተዋችሁት? ጥሩት እንጀራም ይብላ አላቸው። 21፤ ሙሴም ከዚያ ሰው ጋር ሊቀመጥ ወደደ፤ ልጁንም ሲፓራን ለሙሴ ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠው። 22፤ ወንድ ልጅም ወለደች። በሌላ ምድር መጻተኛ ነኝ ሲል ስሙን ጌርሳም ብሎ ጠራው።" ...በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 3 ቁጥር 1 ጀምሮ እስከ 6 ደግሞ እንዲህ ይላል፤

"1፤ ሙሴም የዮቶርን የአማቱን የምድያምን ካህን በጎች ይጠብቅ ነበር፤ ወደ ምድረ በዳ ዳርቻም በጎቹን ነዳ፥ ወደ እግዚአብሔርም ተራራ ወደ ኮሬብ መጣ።

2፤ የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቍጥቋጦ መካከል ታየው፤ እነሆም ቍጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቍጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ።

3፤ ሙሴም። ልሂድና ቍጥቋጦው ስለ ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራእይ ልይ አለ።

4፤ እግዚአብሔር እርሱ ይመለከት ዘንድ እንደ መጣ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ከቍጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ። ሙሴ፥ ሙሴ ሆይ አለ።

5፤ እርሱም። እነሆኝ አለ። ወደዚህ አትቅረብ፤ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው።

6፤ ደግሞም። እኔ የአባትህ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ያይ ዘንድ ፈርቶአልና ፊቱን ሸፈነ።" ብሎ ይህቺን ጫማህን አውልቅ የተባለባትን ቅዱስ ስፍራ መገኛ ንጉስ የነበሩትን አል-ኸዶር (ዮቶር-አብ) ልጅ እንዳገባ ይነግረንና:: በኦሪት ዘኍልቍ 12:1 ላይ ደግሞ ይህቺ ሴት ኢትዮጵያዊ መሆኗን ቃል በቃል ይመሰክራል:: "ሙሴም ኢትዮጵያይቱን አግብቶአልና ባገባት በኢትዮጵያይቱ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ።"

ብለው ካነበቡ በኋላ ሼህ ከድር የኪታባቸውን ሌላ ገፅ ገለጡ፤ "ከእዚህ የቶራህ ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ታሪክ በቅዱስ ቁርዓን የ‹‹ዜናዎች ምዕራፍ 28፤ ቁጥር 15 እስከ 32›› ላይ እንዲህ ተከትቦልናል" ብለው ማንበብ ጀመሩ::

"(15) ከተማይቱንም ሰዎቿ በዝንጋቴ ጊዜ ላይ ሆነው ሳሉ ገባ:: በእርሷም ውስጥ የሚጋደሉ ሁለት ሰዎችን አገኘ:: አንዱ ከሱ ወገን (ከእስራኤል) ነው፤ ሌላው ግን ከጠላቱ ወገን (ከግብፆች) ነው:: ያ ከሱ ወገን የሆነው ሰውም (ለሱ አግዞ) ጠላቱ የሆነው ግብፃዊ ሰውን (እንዲመታለት) እርዳታ ጠየቀው:: ሙሳም (ግብጻዊውን) በቡጢ መታው፤ ገደለውም:: (የመታው ግብጻዊው እንደሞተ ባየ ጊዜ ደንግጦ) "ይህ የሰይጣን ሥራ ነው:: እርሱ ግልጽ አሳሳች ጠላቴ ነው" አለ:: (16) (ወደ አምላኩ ተመልሶም) «ጌታዬ ሆይ! እኔ ነፍሴን በደልኩኝ (ሰው ገደልኩኝ)፤ እባክህን ማረኝ አለ::» (ጌታም) ለእሱ ምሕረት አደረገለት፤ እርሱ መሓሪ አዛኝ ነውና:: (17) (ሙሴም) «ጌታዬ ሆይ! በእኔ ላይ (ይቅርታን) በመለገስህ ይሁንብኝ (ከስህተቴ እጸጸታለሁ)፤ ለአመጸኞችም (ከዚህ በኋላ) ፈጽሞ ረዳት አልሆንም አለ:: (18) በከተማይቱም ውስጥ (አምላኩን) ፈሪና (ምልከትን) የሚጠባበቅ ሆኖ አደረ:: በድንገትም ያ ትላንት እርዳታን የጠየቀው ሰው በጩኸት እርዳታን ይጠይቀዋል:: ሙሳ ለርሱ (ለሰውየው) «አንተ በእርግጥ ግልጽ ጠማማ ነህ፤» አለው::

(19) (ሙሳ) ያንን እርሱ ለሁለቱም ጠላት የሆነውን (ሌላ ግብጻዊ) ሰው በኃይል ሊይዘው በፈለገም ጊዜ (ግብጻዊው ሰውም) «ሙሳ ሆይ! በትላንትናው ቀን ነፍስን እንደ ገደልከ (ያንን ግብጻዊ መተህ ለሞት እንዳበቃህ እኔንም) ልትገድለኝ ትፈልጋለህን? አንተ በምድር ላይ ጨካኝ መሆን (በጉልበት ማሸነፍን) እንጅ ሌላ አትፈልግም:: ከመልካም ሠሪዎችም መሆንን አትፈልግም» አለው::

(20)(ከከተማይቱም ዳርቻ አንድ ሰው እየሮጠ (ወደሙሳ ) መጣ:: «ሙሳ ሆይ! ሹማምንቶቹ ሊገድሉህ ባንተ ይመካከራሉና (ከሃገር) ውጣ:: እኔ ላንተ ከመካሪዎች ነኝ» አለው:: (21) የፈራና የሚጠባበቅ ሆኖ (በጥንቃቄና በድብቅ) ከእርሷ (ከግብጽ ሐገር) ወጣ:: «ጌታዬ ሆይ! ከበደለኞቹ ሕዝቦች አድነኝ» አለ::(22) (እያመለጠ ሳለ) ወደ **መድየን** (ሀገር) አቅጣጫ ፊቱን ባዞረ ጊዜም «ጌታዬ ቀጥተኛውን መንገድ ሊመራኝ እከጅላለሁ» አለ::

(23) ወደ መድየን (ሃገርም) ውሃ በመጣ ጊዜ በእርሱ (በውሃው) ላይ ከሰዎች ጭፍሮችን (የከብት መንጋዎቻቸውን) የሚያጠጡ ሆነው አገኛቸው:: ከእነርሱ በታችም (ከውሃው መንጎቻቸው እንዳያጠጡ) ተከልክለው (የቆሙ) ሁለት ሴቶችን አገኘ:: (ሴቶቹንም) «ነገራችሁ (ችግራችሁ) ምንድን ነው?» (ለምን የከብት መንጋዎቻችሁን አታጠጡም) አላቸው:: (እነርሱም መልሰው) «(ወንዶቹ) እረኞቹ ሁሉ (መንጋዎቻቸውን ውሃ አጠጥተው ጨርሰው) እስከሚመልሱ አናጠጣም:: አባታችንም ትልቅ (አቅም የሌለው) ሽማግሌ ነው» አሉት::

(24) ለሁለቱም (የከብታቸውን መንጋ ተቀብሎ ውሃ) አጠጣላቸው፡፡ ከዚያም ወደ ጥላው ዘወር አለ፡፡ «ጌታዬ ሆይ! እኔ ከመልካም ነገር ወደኔ ለምታወርደው ፈላጊ ነኝ» አለ፡፡

(25) ከሁለቱ (የከብት መንጋቸውን ውሃ ካጠጣላቸው ሴቶች) አንደኛይቱ አይነ አፋር የሆነችው (እያፈረች) ወደሙሴ (ወደ ተጠለለበት ቦታ) መጣች፡፡ «አባቴ ለእኛ (የከብታችንን መንጋ) ያጠጣህልንን ዋጋ ሊሰጥህ ይጠራሃል» አለችው፡፡ ወደ እርሱ (ወደ አባታቸው ዮቶር-አብ) በመጣና (የሆነውን ሁሉ) ታሪኩን በእርሱ ላይ በተረከለትም ጊዜ «አትፍራ (አሁን) ከበደለኞቹ ሕዝቦች ድነሃል» አለው፡፡

(26) ከሁለቱ (ሴቶች) አንደኛይቱም «አባቴ ሆይ ቅጠረው፡፡ (እስካሁን) ከቀጠርከው ሰው ሁሉ በላጩ ብርቱው ታማኙ ነውና» አለችው፡፡

(27) (ዮቶር-አብም ሙሴን አለው) «ስምንትን ዓመታት ልታገለግለኝ እኔ ከእነዚህ ሁለት ሴቶቸ ልጆቼ አንዲቱን ልድርልህ እሻለሁኝ፡፡ (የምታገለግለኝን ዓመታት) ዐስር ብትሞላም ከአንተ (ምርጫ) ነው፡፡ አንተን ማስቸገርም አልሻም፡፡ አላህ የሻ እንደ ኾነ ከመልካሞቹ ሰዎች ኾኜ ታገኘኛለህ» አለው፡፡

(28) (ሙሳም ለዮቶር-አብ) «ይህ (ውለታ/ቃል-ኪዳን) በእኔና ባንተ መካከል (ረጊ/የጸና) ነው፡፡ ከሁለቱ ጊዜያቶች ማንኛውንም ብፈጽም በእኔ ላይ ወሰን ማለፍ የለም፡፡ አላህም በምንለነው ላይ ምስክር ነው» አለው፡፡

(29) (ከዚያም በመዳየን ምድር እያለ) ሙሳ ለቤተሰቦቹ (ለኢትዮጵያዊት ሚስቱና ልጁ) «እኔ እሳትን አየሁ፡፡ ከእርሷ (ሄጄ አጣርቼ) ወሬን አመጣላችኋለሁ፡፡ ወይም ትሞቁ ዘንድ ችቦ ለኩሼ አመጣላችኋለሁኝ» ባለ ጊዜ (የሆነውን አውሳላቸው)፡፡

(30) (ከእሳቷ ዘንድ) በመጣ ጊዜ እንዲህ አልነው፤ «በእሳቲቱ ያለው ሰውና በዙሪያዋ ያሉም ሁሉ ተባረኩ፡፡ የዐለማትም ጌታ አላህ ጥራት ይገባው፡፡ «ሙሳ ሆይ! እነሆ እኔ አሸናፊው ጥበበኛው አላህ ነኝ፡፡

(31) «በትርህንም ጣል» (ተባለ ጣለም)፡፡ እርሷ እንደ ትንሽ እባብ በፍጥነት ስትስለከለክ ባያትም ጊዜ፤(ፈራና) ወደ ኋላው ዞሮ ሸሸ፡፡ አልተመለሰምም፡፡ (አላህም) «ሙሳ ሆይ! አትፈራ፤ የእኔ መልክተኞች እኔ ዘንድ አይፈሩምና፡፡(አለው)

(32)«እጅህንም በአንገትጌህ (በእጅጌህ) ውስጥ አስገባ፡፡ ያለነውር (ያለ ለምጽ) ብርሃን ኾና ትወጣለችና፡፡ በዘጠኝ ተዓምራት ወደ ፈርዖንና ወደ ሕዝቦቹ (ኺድ)፡፡ እነርሱ አመጸኞች ሕዝቦች ናቸውና፡፡"(ተባለ)፡፡"

ሺህ ክድር ንባባቸውን አበቁና ቀና አሉ፡፡ ትንፋሽ ወሰዱናም ማብራሪያቸውን መስጠት ጀመሩ፤

"እንግዲህ አሁን በሰማችኋቸው የሁለቱ ቅዱስ መፅሐፍት ዘገባዎች መሰረት ሙሴ ትዕግስት አልባ ሆኖ ግብፃዊ እንደገደለና ሸሽቶም ወደመዳያን ምድር እንደመጣ እዚያም ሁለት ውሃ ሊቀዱ የመጡ ሴቶችን አግኝቶ እንደረዳቸው

ለዚህም የእርዳታው ሽልማት ዮቶር-አብ ቤቱ እንደጋበዘው ከዚያም ልጁን ሲጳራን እስከመዳር ድረስ እንዳቀረበው ይናገራል:: ታዲያ ሚስጥሩ ያለው ለእነዚህ ሁለት ሴቶች ውሃ ማጠጣቱ ለምን እንደትልቅ ነገር እንደተቆጠረለት ማወቁ ላይ ነው:: ላስረዳችሁ ነውና ከልብ አድምጡኝ"... አሉና በአፅንኦት መናገር ጀመሩ፤ ሼህ ከድር...

"በኦሪት- *ዘፀዓት ምዕራፍ 2 ቁጥር 18* ላይ አባታቸው ራጉኤል ልጆቹን <<ለምን ዛሬ ቶሎ መጣችሁ?» ብሎ ሲጠይቃቸው እናነባለን:: በዚያ ላይ ሴቶቹ ውሃ ከብቶቻቸውን እንዳያጠጡ የሚያግዷቸው ወንድ እረኞች በውሃው ገንዳ እንዳሉም ሁለቱም ትረካዎች ላይ እንብበናል:: ስለዚህ ከብቶቻቸውን ውሃ ማጠጣት ለእነዚህ ሴቶች ረጅም ጊዜን የሚፈጅና ትዕግስትንም የሚጠይቅ ተግባር እንደሆነ እንረዳለን:: ስለዚህ ቅድም እውቀትን ፍለጋ ወደ አል-ኸዶር ሄዶ ትዕግስት በማጣቱ ምክንያት ሳይማር የተመለሰው፤ ትዕግስትም በማጣቱ ግብፃዊ ገድሎ የሸሸው ሙሴ አሁን ግን ጉልቤ እረኞች ጋር ተጋፍቶ፣ በፀሐይ ሙቀት ስር በትዕግስት ያንን ሁሉ የከብት መንጋ ውሃ ማጠጣት ነበረበት:: ይህም ሙሴ ታጋሽ መሆኑን ለአምላኩ ለማሳየት እንደፈለገ ያሳየናል:: ይህንንም የሚደግፍልን ሙሴ በቁጥር 24 ላይ *ወደ ጥላው ዘወር ብሎ:: «ጌታዬ ሆይ!* ***እኔ ከመልካም ነገር*** *ወደኔ እንዳታወርድ ፈላጊ ነኝ»" ማለቱ ነው::*

በሌላ ጠሃ በምትሰኝ የቁርዓን ምዕራፍ ቁጥር 40 ላይ ደግሞ፤ አላህ (ሱ.ወ) ሙሴን እናቱ እንዳይገደልባት ፈርታ በግዮን ወንዝ ላይ በቅርጫት አድርጋ ልካው የፈረዖን ሚስት ካገኘችው በኋላ ያለው ታሪኩን እንዲህ ያወሳዋል፤ *«እንትህም በምትኼድና (ለእነፈረዖንም) የሚያሳድገውን ሰው ላመላከታችሁን በምትል ጊዜ (መወደድን ጣልኩብህ):: ወደ እናትህም ዓይንዋ እንዲረጋ (እርሷ) እንዳታዝንም መለስንህ (እናትህ ራሷ ያንተ ጡት አጥቢ ሆና ከፈረዖን ቤተ-መንግስት ገባች):: (አድገህም የግብጻዊን) ነፍስ ገደልክ:: (ሲያባሩህ) ከጭንቅም አዳንንህ::* ***ፈተናዎችንም ፈተንህ:: በመድየን ቤተሰቦችም ውስጥ (ብዙ) ዓመታትን ተቀመጥክ::*** *ከዚያም ሙሳ ሆይ! በተወሰነ ጊዜ ላይ መጣህ::"* ታዲያ በዚህ ጥቅስ መሰረትም መድየን ቤተሰቦቹ ጋር ለመቀላቀል አንድ ፈተናን ተፈትኖ እንዳለፈ ይነግረናል:: ይህንም ፈተና መጀመሪያ አል-ኸዶር ጋር እውቀትን ተማር ብሎ አላህ ልኮት ቢሄድም ትዕግስትን በማጣቱ ምክንያት ወድቆ ነበር:: ያኔ ወደ ግብፅ ተመልሶ እያስተማረ ሲቀጥል፤ በእዚህ ጊዜ ውስጥም ወደ ንግስና የወጣው አል-ኸዶር/ ዮቶር-አብ ተብለው 22 ዓመት ከነገሱ በኋላ የንግስና ዘመናቸውን ጨርሰው ወርደው፤ እድሜያቸው ነጉዶ ሽማግሌው ራጉኤል ተብለው የተቀመጡ አባት ነበሩ::

ትዕግስትን በማጣቱ ግብፃዊን የገደለው ሙሴ (ዐ.ሰ) ፊረዖን ሊገለው እያሳደደው ባለበት ወቅት ቀድሞ ወደ ማያውቀው ወደ መድያን ምድር ተሰደደ:: ያኔም ለብቻው በጭንቀትና ፍርሃት ውስጥ እያለ ትዕግስት አለማድረግ ያመጣበትን ችግር አይቶ ወደ አምላኩ ተፀፀተ:: ለዚህም መሐሪው አምላክ አዘነለትና ሁለተኛ እድል ላከለት፤ ሽምግሎ ከንግስናው ቢወርድም ጥበቡን ያላጣውን የዮቶር-አብን ልጆች አገኛቸው:: ይህን 2ኛ እድልም ሙሴ በሚገባ ተጠቅሞበት ሁለቱን ሴቶች አግዟቸው በትዕግስት የከብት መንጋቸውን ውሃ አጠጣላቸው:: በዚህ ስኬቱም ከዮቶር-አብ ጋር አብሮ የመኖርና ልጁን የማግባት ፀጋ ተሰጠው:: በዚህ ፈተናው የተማረው የትዕግስት ጥበብ ደግሞ ወደ ፊት የእስራኤል ልጆችን ከግብፅ ባርነት አውጥቶ ለሚጓዘው ከባድ የፈተና ጉዞ ላይ ታጋሽ እንዲሆን አድርጎታል:: ይህም ታላቅ እውነታ ነው:: ትዕግስት ለዘላለም የፀናች የጥበብ መግቢያ በር ናትና::" ብለው ሁሉንም በፈገግታ አስተዋሏቸው::

"ደስ የሚል ታሪክ ነው! አሁንም ግን የዮቶር ኢትዮጵያዊነት ላይ እርግጠኛ መሆን አልቻልኩም::" አለ ናዖድ፤

"ወደዚያው ልመጣልህ ነበር ልጅ ናዖድ፤ ልብ ብላችሁ አድምጡኝ፤ ቅድም እንደነገርኳችሁ መፅሐፍ-ቅዱስ የሲጳራን ኢትዮጵያዊነት በኦሪት ዘኍልቍ 12:1 መስክሯል፤ አሁን ደግሞ የሙሴ አማት ዮቶር-አብ ወይም አል-ኸዶር እንደሆነ ከተስማማን:: <<ኸድር» የሚለው ቃል ደግሞ በአረብኛው ትርጉሙ ጥበብና እውቀትን የተቸረ፤ ትክክለኛ የአምላክ አገልጋይ ማለት ሲሆን የሚገርመው ደግሞ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ይህ ሙሳን ያስተማረ ሰው ለምን «ኸድር» እንደተባለ ሲጠየቁ ˋኸድር ማለት <ደርቆ በነጣ (ፋርዋህ) ዛፍ ስር ቁጭ ሲል ካድራ (ሃድራ) ወይም አረንጓዴ (ልምላሜ) ስለሚያደርገው› መሆኑን ነግረውናል:: ይሕም ኢማም አህመድ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል::

ዮቶር ደግሞ የመዳያም ሰው እንደሆነ በግልፅ ተፅፏል:: ይህም መድያን ከሚባሉት የኦሮሞዎች ዘር መነሻ አባት ስም የተገኘ ነው:: መዳ ማለትም በኦሮምኛ ቋንቋ መሰረት ምንጭ (መነሻ) እንደማለት ነው:: በተጨማሪም በብዙ የጥንት ታሪክ ፀሐፊዎች እንደተገለፀው እነዚህ ህዝቦች በዛፍ ስር አምልኮ እንደሚፈፅሙ እና ሃይማኖታቸው ከተፈጥሮ ጋር እጅጉን የተቆራኘ እንደሆነ ይዘግባሉ:: ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከነገሩን ኸዶር ትርጉም ከዛፍ ስር የሚቀመጥ የልምላሜ ሰው ካሉት ጋር አጣምረን ካየነው እስካሁንም ድረስ በመደ-ወላቡ በኦዳ ዛፍ ስር የሚቀመጡትን የአባ-ገዳ ስርዓት ማሰባችን አይቀርም:: በተጨማሪም የዮቶር-አብ የሽምግልና ስም የሆነው «ራጉ-ኤል» በብዛት ከሚታወቀው መልዓኩ ‹ራጉኤል› የተለየ ስያሜ ሲሆን ይህ ስም

‹ራጉ› እና ‹ኤል› ከተባሉት ተዋቅሮ የተገኘ ነው፤ ‹ኤል› ማለት ያው አምላክ ማለት ሲሆን ‹ራጉ› የሚለው ቃል ደግሞ ‹ራጋ› ከሚለው የኦሮምኛ ቃል የተገኘ ነው፤ ‹ምስክር› እንደማለትም ነው፤ ይህም በአንድነት ‹የአምላክ ምስክር› የሚል ትርጉም የሚሰጥ ሲሆን በታሪኮቹ ውስጥ ዮቶር-አብ ለሙሴ የገለጠለት ምስክርነትም ይህንን ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል ሙሴ ይህ ኢትዮጵያዊ አማቱ ዮቶር-አብ ጋር ከ8 ላላነሱ አመታት ቆይቷል፡፡ ይህን እውነታ የሚያጠናክርልን ደግሞ በኦሪት ዘ-ፀዓት ምዕራፍ 18 ላይ በግልፅ እንደተዘገበው ዮቶር-አብ ስለህዝባዊ አስተዳደርና ፍርድ አሰጣጥ ለሙሴ ትምህርት መስጠቱ ነው፡፡ እንደተጻፈውም ‹በህዝቡ ውስጥ አዋቂዎችና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ምረጥና በአስተዳደሩ ያግዙህ አንተ በነብይነትህ ላይ አተኩር› ብሎ መክሮታል፡፡ ይህም ከሦንሸዋ ተመዝግበው ከጥንት የኢትዮጵያ አባቶች ሲወራረስ የመጣ ስልጣንን ለብዙ-በህዝቡ ዘንድ ታማኝ ለሆኑ ሰዎች በማከፋፈል የሚሰራ ከዲሞክራሲም የላቀ የመንግስት ስርዓት ሲሆን፤ ይህም ስርዓት በድሮ የአክሱማውያን መንግስት ስርዓት ውስጥ እንደነበርም በርካታ ጥንታዊ የታሪክ መፅሐፍት ዘግበዋል፡፡ አሁን በዚህ ዘመን እንኳን ያን መሰል አወቃቀር በአማራው የጎበዝ አለቆች፣ በኦሮሞ አባ - ገዳዎች፣ በጉራጌ የጆካዎች ወዘተ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ እንግዲህ እነዚህ ሁሉ አይንና ልቦና ያለው ሰው ሊያያቸው የሚችላቸው እውነታዎች ሙሴን ያስጠጋች፣ <ቅድስት ናትና ጫማህን አውልቅ› የተባለባት ምድር ኢትዮጵያ እንደሆነች በሚገባ ይረዳል፡፡ ከእውነታው ጋር አብሮ የማይሄደው የዘመኑ ዘገባ ደግሞ ሙሴ ቀይ ባህርን መከፈያ በትሩን ያገኘባትን <<የኮሬብ ተራራ» ከቀይ ባህር ማዶ ባለችው እስራኤል የምትገኝ ተራራ ናት የሚል አስተምሮ ነው፡፡ ሙሴና እስራኤላውያን በባርነት ፒራሚድ ለመስራት የዳከሩባት ምድር ግብፅ፤ ሙሴ ደግሞ ከግብፆች ሸሽቶ የተሰደደባት መደያም ያለችው በደቡብ፤ ሙሴ ደግሞ ተራራውን ያየው የመዳያሙን ኢትዮጵያዊ ዮቶር-አብ ከብቶች ሲያግድ፤ ታዲያ እንዴት ሆኖ ነው ኮሬብ ተራራ እስራኤል የሚገኘው ልጆቼ?" አሉና ሼህ ከድር በጥያቄ አይን ሁሉንም አዮቸው፡፡

"የሚደንቀው ነገር ደግሞ አላህ ጀሊሉም እንዲህ ብለው ሊዋሹ እንደሚችሉ ቀድሞ ያውቃልና አንድ ተዓምራዊ ቃል በቁርዓን ውስጥ አስቀምጧል፡፡" አሏቸው፤

"ምንድነው እሱ ቃል?" አሉ ሁሉም፤ የማወቅ ጉጉት እየተነበበባቸው፡፡

"ቅድም ባነብኩላችሁ የቁርዓን ምዕራፍ 28 ቁጥር 32 ላይ አንዲት ተዓምራዊ ቃል አስቀምጧል፡፡ ሙሴን ‹እጆችህን ከእጅጌዎችህ ከተህ አውጣቸው፤ ይበራሉ› ብሎ በሚያዝበት ቦታ ላይ አላህ በአረብኛው አንዲት

‹‹ብርሃን›› የምትል ቃል አውርዷል:: በአረብኛ መዝገበ ቃላት ውስጥ ግን ብርሃን የሚል ቃል የለም:: በአረብኛው እሳት ማለት ‹‹ናር›› ሲሆን ብርሃን ማለት ደግሞ ‹‹ዱሃ›› ነው:: እናም ይህቺ ‹‹ብርሃን›› የምትል በአረብኛ ፊደላት የወረደች የአማርኛ ቃል፣ **ምልከት**... ይህ የኮሬብ ተራራ በኢትዮጵያ እንደሚገኝ ለመጠቆም እንደወረደች እየተሰማኝ ሁሌም እገረምባታለሁኝ... ለማንኛውም ልጆቼ ሁለተኛው ታሪካችሁ ይሄንን ይመስል ነበር:: እንግዲህ ካህን የነበረው ዮቶር-አብ ወይም አል-ኸዶር የሙሴ አማት፣ አስተማሪና አለቃ እንደነበር ብሎም ይሕ ታላቅ ሰው በጫማ ለመርገጥ እንኳን የሚያሳሳ ቅድስትነቷ በተነገረላት የሁሉ መጠጊያ በሆነችው ሃገራችን እንደኖረ እንዳወቃችሁ አምናለሁኝ:: አሁንም ይህ ተረት ሳይሆን ታሪክ ነው::"

"እንኳን እነርሱ እኔም አስቸጋሪውም ለማመን እየዳዳኝ ነው::" አለ ዮሴፍ ከእነኢትኤል ጀርባ ፈንጠር ብሎ እንደቆመ:: ሁሉም በትረካው ተመስጠው ስለነበር መጥቶ ከእነርሱ ጀርባ እንደመቆመ ያዩት ሼህ ከድር ብቻ ናቸው:: ሁሉም ተነስተው አቀፉት::... "በሉ እንግዲህ የሰዓታት ናፍቆታችሁን ተወጡ! ከምሳ በኋላ ሦስተኛው ታሪክ አጫውታችኋለሁኝ::" ብለው፣ ባላ በትራቸውን ተደግፈው ተነሱና ወደ ዋሻው ገቡ::

ልክ እርሳቸው ወደ ዋሻው እንደገቡ የመርየም ስልክ አቃጨለች:: መርየም ደዋዮ ቢታንያ እንደሆነች ስታውቅ ከነኢትኤል ራቅ ብላ አነሳችው::..."ሄሎ"

"አንቺ አይጥ ምነው ዘጋሽኝ?" አለች ቢታንያ ከሌላኛው ጫፍ፤

"ትንሽ ስላልተመቸኝ ነው ቢታን?... እረፍት እንዴት ነው?"

"ምን እረፍት አለ ባክሽ ተይኝ እስኪ... እንዴት ነው ግን አሁንም አብሯችሁ አለ ኢትኤል?" አለቻት፤

"አለ ምን ይሆናል ብለሽ ነው... ህምም ባክሽ ግን እንደኔ ተስፋ ብትቆርጪ ነው የሚሻለው፤ ብታይ ወሬው ሁሉ ፅዮን ሆኗል፣" አለች መርየም ኢትኤል እንዳይሰማት እየተጠነቀቀች፤

"እርግጠኛ ነሽ ሜሩ... ለአንድ አመት እንደተቀጣች አውቆም ተስፋ አልቆረጠም?" አለች ቢታንያ በንዴት፣

"አዎ... እንዲያውም እስኪያገኛት ጓግቷል፣"

"ስለዚህ ልፋቴ ሁሉ መና ቀርቷል በይኛ" አለች ቢታንያ በቁጣ፣

"ምን አልሽ ቢታን?" አለች መርየም ጆሮዋን ማመን እየከበዳት::

"አይ ምንም..."

"የቧ መባረር ላይ እጄ አለበት እንዳትይኝ?"

"ቢኖርበትሳ ምን ታካብጂያለሽ?" አለች ቢታንያ፤
"እኮ ምን አርገሻል ንገሪኝ?" አለች መርየም በንዴት፤
"አልነግርሽም!... ብቻ እንድትባረር ማስደረጌን ካወቅሽ ይበቃሻል::" አለች ቢታንያ በስሜታዊነት፤
"ካሁን በኋላ ጓደኛዬ ብለሽ እንዳትጠሪኝ::" ብላ መርየም ስልኩን ጆሮዋ ላይ ዘጋችባት:: ቢታንያ ያደረገችው ነገር እጅግ አናዷታል:: እንዴት አድርጋ እንዳስባረረቻት ባታውቅም ቢታንያ ከአንዳንድ አስተማሪዎች ጋር ያላትን ለየት ያለ ግንኙነት ስለምታውቅ ይሄን ማድረግ እንደምትችል ታውቃለች::

*** ቶ – ቶ ***

ቆንጆ ነች፣ ማንንም ወንድ እጅ ማስከንዳት የምትችል ቆንጆ፤ ቢታንያ... በግቢው ወንድ ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን በሴቶችም ጭምር "ቆንጆ" እየተባለች የምትሞካሽ አይነት ተማሪ ናት:: ቆንጆ የሚያመርት ፋብሪካ ያለ ይመስል የዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ በውብ ተማሪዎች ቢሞላ እንኳን ከፋክክሩ ነጥራ መውጣት የቻለች... የተመሰከረላት "ቆንጆ" ነች!
እርግጥ ውበት እንደተመልካቹ ነው፤ ከፊቱ ስትመጣ የተመለከታት አብዛኛው ወንድ አንገቱን ጠምዝዞ እስከጀርባው ሲሸኛት ውሎ ላልተገባ የማጅራት ህመም መጋለጡ ግን የተለመደ ነው:: በቁምጣም ይሁን በተቀዳዱ ጂንስ ሱሪዎች ተነስታ ፌስቡክ ላይ በምትለጥፋቸው ፎቶዎች ከሁሉም የግቢው ሴቶች በልጣ በሺዎች የሚቆጠሩ ላይክና ኮሜንቶችን ታገኛለች:: ብዙ ብዙ የግቢው ተማሪና የከተማው ኗሪ አፍ አውጥቶ ስለውበቷ ሲመሰክር ተሰምቷል:: እሷም ሁሉንም ከመናቅ ውጪ ልቧን ለማንም ሰጥታ አታውቅም:: ተጋብዞ፣ ዘና ፈታ ብሎ ሹልክ ነው ‹ስታይሏ›:: አሁን ግን በህይወቷ ውስጥ አንድ ሰው ገብቶ ከዚህ በፊት ተሰምቷት የማያውቅ ልዩ ስሜት እንዲሰማት አድርጓል:: እሱም ግን በእሷ ዘንድ አንዲት እርባና በሌላት ሴት ተከቶ ትቷታል::
"በሌላ ከላስ ባላት ሴት ቢተወኝ እኮ ምንም አይመስለኝም ነበር!" አለች ከመስታወቷ ፊት ቁጭ ብላ እየተብከነከነች፤... "ለዚህች ለፋራ ፅዮን ተብዬ እኔን ቢታንያን ይተወኝ?... እኮ እኔን?" አለች በመስታወቷ ውስጥ ወደግራና ወደቀኝ እየዞረች ፊቷን እያየች:: ነገሩን የባሰ አቀጣጥሎ ያብሰለሰላት ደግሞ በአካል እንኳን ሳያገኛት በአንዲት የፅሑፍ መልዕክት መሰናበቷ ነበር:: "ምን ያህል ቢንቀኝ ነው ግን እንዲህ እንደተራ ሴት በ‹ቴክስት ብሬክ አፕ› የሚያደርገኝ?!" አለች በነገር ከንፈሯን እየመጠመጠች:: የሆነ ከዚህ በፊት ተሰምቷት የማያውቅ የእልህ ስሜት አንገቷን ሰንቅሮ ይዟታል:: "ቆይ

አፈቀርኳት የሚላት ያቺ እንከፍ ስትዘጋው መሄጃያ አጥቶ ይመጣት የለ! እንዲህ እንደተጫወተብኝማ አልቀራትም::" ስልኳን አነሳችና ወደ ፅዮን ስልክ ደወለች... መጥራት ጀመረ:: እጅግ የሚገርመው ለመርየምና ኢትኤል ያልተነሳ የፅዮን ስልክ ለቢታንያ ግን ተነሳ::

"ሄሎ ሰላም ነሽ አንቺ መናጢ?" በነገር ጀመረች ቢታንያ፤

"ይመስገነው፤ ደህና ነኝ፤" አለች ፅዮን በቀዘቀዘ ድምፅ፤

"ሲደወልልሽ ደግሞ ስልክ አታነሺም አሉ::"

"አዎ የስልኬ ስክሪን ተበላሽቶ ማንሳት አልቻልኩም ነበር::"

"ለዚያ ነዋ ለዓመት መባረርሽን ያልሰማሽው?"

"ምን?" አለች፤ ፅዮን በድንጋጤ፤

"እንዴ እንደ ጥሩ ነገር በግቢው ውስጥ በትልቁ ተለጥፎልሽ፤ አልሰማሁም እንዳትይኝ ብቻ?!...ቂቂቂቂ" ቢታንያ አሽካካች፤

"እን... እንዴት ላላውቅ እችላለሁኝ... እንዴ ቢያንስ ኢትኤል እንኳን አይነግረኝም?!" ፅዮን ተንተባተበች::

"እሱን ለቀቅ አድርጊው፤ ዛሬም አደዋወሌ እሱን አትጨቅጭቂው ልልሽ ነው:: ይሰማሻል ከዚህ በኋላ ኢትኤል የኔ ነው:: ይኻውልሽ ስልኬ ተባላሽ ብትይም እሱን እየደወልሽ መበጥበጥሽን ግን እንዳላቆምሽ ነግሮኛል:: ልጁን ለምንድነው የምትጨቀጭቂው? በቃ እርሺው ብዬሻለሁኝ እርሺው፤ ከእኔ ጋር የጦፈ ፍቅር ውስጥ ነው ያለው፤ ድንግል አድርገሽ እንዳስቀመጥሽው አላውቅም ነበር፤ ...ቂቂቂቂ" ድጋሚ ተስረቀረቀች:: ፅዮን መልስ አልሰጠቻትም፤ ስልኩ ተዘጋ... ቢታንያ አንጀቷ ቂቤ ሲጠጣ ይታወቃታል::

*** ዩ – ዩ ***

*‹‹እነዚያ ያመኑና እነዚያም አይሁዳውያን የኾኑ፣ ሳቢያኖችም፣ ክርስቲያኖችም (ከነርሱ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነና መልካምን ሥራ የሠራ ሰው በነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም:: እነርሱም ኢያዝኑም::›› (ሱራ ማኢዳህ-69)*

*** ዩ – ዩ ***

*እስኪ ቅድም የሄድከበትን ምክንያት ንገረን ዮሴፍ አሉት ሼህ ከድር፣ የመጨረሻውን ታሪካቸውን ሊናገሩ በተቀመጡበት::*

*ዮሴፍ አንገቱን እንደደፋ ለነኢትኤል ነግሯቸው የማያውቀውን ታሪክ መናገር ጀመረ... "እኔ እናቴ የሞተችብኝ ገና በልጅነቴ ነበር:: አባቴ ደግሞ የታሪክ አስተማሪና እጅግ ሲበዛ ወግ አጥባቂ ሰው ነበር:: ከልጅነቴ ጀምሮ ስለ ኢትዮጵያ ታላቅነትና ቅድስነት ሳያሰልስ ነግሮኛል:: ነገር ግን የሱ የታሪክ*

ጋጋታ የእሱን ግራሜ ከሬሽን ጃኬት ወደ ሌዘርነት ሲለውጠው አላየሁም:: ቅዱስ የምትባል ምድር ናት ብሎ ኢያስተማረኝ ያደግኩባት ኢትዮጵያም ችጋርና መከራን፣ ስደትና በሽታን፣ ርሃብና ጥማትን እንጂ ሌላ ምንም አልሰጠችኝም:: እርግጥ ከእነድህነቷም ቢሆን ኢትዮጵያን እወዳታለሁኝ.. የሆነ ጦርነት ቢነሳ ‹ሆ!› ብዬ ሄጄ እንደምዋጋም አምናለሁኝ:: በሃይማኖትም በኩል ለራሴ በክርስቶስ ከማመንና ድንግል ማርያምን ከመውደዴ ባለፈ የሃይማኖትና የታሪክ ዲስኩር አይመቸኝም:: ሲጀመር አሁን ራሱ እዚህ ለምን ተመልሼ እንደመጣሁኝ አላውቅም::" አለ ዮሴፍ፤

"ተመልሰህ የመጣኸውማ ቀጣዩን ታሪክ መስማት እንዳለብህ ፈጣሪ ስላቀደልህ ነው:: እስካሁን የኢትዮጵያን ታላቅነት የሚመሰክሩ ታሪኮችን ከነማጣቀሻው አስደግፌ አጫውቼያችኋለሁኝ:: እንግዲህ የአምላክ እንጂ የሰው ፍፁም የለምና የድሮ አባቶቻችን የሰሩትንም ስህተት ደግሞ በዚህኛው ታሪክ ላይ አጫውታችኋለሁኝ:: አሁን ያለንበት ነባራዊ ሁኔታ እንደእነርሱ ታላቅነትን ያለመላበሱ እውነታ ከእነዚህ ስህተቶቻቸው ጋር የተያያዘም ስለሆነ ት/ት ታገኙበታላችሁ ብዬ አምናለሁኝና እንደ አምላክ መሻት የመጨረሻውን ታሪክ እነግራችኋለሁኝ፤ እናንተም በትዕግስት አድምጡኝ!...

እንግዲህ የመጀመሪያው ታሪክ ላይ እንደምታስታውሱት እስያኤል ስለተባለና አፍሪካን ጨምሮ የአሁኖቹን እስያና ከፊል አውሮፓን ስለገዛ ታላቅ የኢትዮጵያ ንጉስና ካህን ነግሬያችሁ ነበር:: መፅሐፈ ያሻር እንደሚነግረን ይህ ሰው የአገዛዝ ስርዓትን በማርቀቅ ‹አንድ ሰው ከ10 ዓመት በላይ አንዲትን ሃገር መግዛት የለበትም› የሚል ህግ አውጥቶ እራሱ ባወጣው ህግም ራሱ ወርዶ ሌሎች ነገስታት እንዲመሩ እድል ሰጣቸው:: ይሄን ጊዜ በተፈራረቁ ነገስታት ሂደት ታዲያ የተዋህዶ እምነት ጎደፈች:: ይህም ስህተት በተለይ አሞን የተሰኘው ንጉስ እንደ አምላክ መታየት ከጀመረ በኋላ የከፋ ሆነ:: ታዲያ ታላቁ የኢትዮጵያውያን ንጉሶች ስህተት የተጀመረውም ያኔ ነው:: ለኢትዮጵያውን በሙሉ የመጀመሪያ አባት የሆነው ኤቶጵ ከዚያም እነዮቶር-አብና እሴ የነገሱበት ምድር ላይ የስህተት መንገድ የመረጡ ንጉሶች ተነሱ:: እነዚህም ወደ ጥፋት የገቡት አባቶቻቸው ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው አጅግ በርካታ የወርቅና እንቁ ሃብትና ታላቅ ግዛት ላይ በተንሰራፋው ምድራዊ ሃይል አጅጉን ስለተኩራሩና ‹‹የሃይል ሁሉ ምንጭ ፀሐይ ናት እኛም የእሷ ልጆች የምድርም አማልክቶች ነን›› በማለታቸው ነበር:: ለዚህም ፈርዖኖች እየተባሉ ሰው ይሰግድላቸውና ያመልካቸው ጀመር:: ይህም መከሰት የተጀመረው በእናቱ ኢትዮጵያዊ የሆነው ዳዊት በእስራኤል ውስጥ በኖረበት ዘመን ሲሆን በመጀመሪያ ግን በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ምዕራፍ 23 ተዘግቦ

*እንደሚገኘው በሰሜን ተራሮች ላይ የነበሩት አምራውያን (አማራውያን/ ከፍታ ላይ እንደሚገኙ አምራ የሚኖሩ) ዳዊትን በወጣትነቱ እንዳስጠጉት ይዘግባል፡፡ "(14፤) ዳዊትም በምድረ በዳ በአምባ ውስጥ ይኖር ነበር፥ ከዚፍ ምድረ በዳም ባለው በተራራማው አገር ተቀመጠ፤ ሳኦልም ሁልጊዜ ይፈልገው ነበር፥ እግዚአብሔር ግን በእጁ አሳልፎ አልሰጠውም። (15፤) ዳዊትም ሳኦል ነፍሱን ሊፈልግ እንደ ወጣ አየ፤ ዳዊትም በዚፍ ምድረ በዳ በጥሻው ውስጥ ይኖር ነበር። (16፤) የሳኦልም ልጅ ዮናታን ተነሥቶ ወደ ዳዊት ወደ ጥሻው ስጥ ሄደ፤ እጁንም በእግዚአብሔር አጸንቶ። (17፤) የአባቴ የሳኦል እጅ አታገኝህምና አትፍራ፤ አንተም በእስራኤል ላይ ንጉሥ ትሆናለህ፥ እኔም ከአንተ በታች ሁለተኛ እሆናለሁ፤ ይህን ደግሞ አባቴ ሳኦል ያውቃል አለው። (18፤) ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ቃል ኪዳን አደረጉ፤ ዳዊትም በጥሻው ውስጥ ተቀመጠ፥ ዮናታንም ወደ ቤቱ ሄደ።" ብሎ ይናገራል፡፡* ይህም ሳኦል ከሚገዛው ሰፊ የእስራኤል ግዛት ሸሽቶ ጥቅጥቅ ያሉ ደኖችና የማይደፈሩ ትላልቅ ተራራዎች ባሏት ኢትዮጵያ እንደተሸሸገ ይናገራል፡፡ ይህንም ምድር የመረጠበት ምክንያት አንድም የኢትዮጵያዊ እናቱ አዴል ሃገር (መፅ ሳሙ.ቀዳ ምዕ 1 ቁ 22) በመሆኑ ሁለትም የኢትዮጵያ ሰዎች ልክ እንደ እሱ ያሉ አማኞች በመሆናቸው ምክንያት እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡ ይህንንም የሚያጠናክርልን በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 26:6 ላይ ኢትዮጵያ ሌላ ግዛት የነበረችውን ንጉስና በኢትዮጵያ ነገስታት ታሪክ ውስጥ ስሙ የተጠቀሰውን ኢትዮጵያዊ ንጉስ አቢ ሜሌክን ጠቅሶ፤ *"ዳዊትም ኬጢያዊውን አቢሜሌክንና የጽሩያን ልጅ የኢዮአብን ወንድም አቢሳን። ወደ ሳኦል ወደ ሰፈሩ ከእኔ ጋር የሚወርድ ማን ነው? ብሎ ጠየቃቸው፤ አቢሳም። እኔ ከአንተ ጋር አወርዳለሁ አለ።" ብሎ ስለሚዘግብልን ነው" አሉና ኪታባቸውን ወደሌላ ገፅ ገለጡት፤*

*"እንግዲህ ይህን ታሪክ በቁርዓን ውስጥም ካየነው በሳባ ምዕራፍ ቁጥር 10..." ብለው ታሪካቸውን ሊቀጥሉ ሲሉ... "እንዴ?" አለ አብርሃም ጣልቃ ገብቶ፤ ከዚያም ወደ መርየም ዞሮ፤ "እንዴ በቁርዓን ውስጥ ብቸኛዋ በስሟ ምዕራፍ የተሰየመላት ሴት ድንግል ማርያም ናት አላልሽኝም ነበር?... ይኸው አሁን ደግሞ በንግስተ ሳባ ስም ሌላ ምዕራፍ አለ ቁርዓን ውስጥ፤..." አለ ግራ በመጋባት ስሜት፤*

*"ልጅ አብርሃም ተረጋጋ፤ እንዲያ አይደለም የታሪኩ አኸዋል፡፡ ባይገርምህ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)ንም ኢብኑ ጃሪር በዘገቡት ሃዲስ ላይ ስለ ሳባ ሲጠይቋቸው "ሴት ናት ወይስ ሃገር ነው?" ብለው ነበር የጠየቋቸው፡፡ እርሳቸው ግን ሴትም ሃገርም እንዳልሆነ ተናግረው የናህ ከዚያም የካም፥*

*የኩሽ የሆነ ወንድ ንጉስ እንደሆነ ሲናገሩ፡፡ ሳባ የእኛ አባት የሆነው ሔቶሮድጎም የሳባ የልጅ ልጅ ልጅ ነበር፡፡ ከዛሬን በፊት የኩሽን ምድር ስልጣኔ እንደመሰረተ የሚነገርለት ይህ ሰው በከህነቱ የታላቅነት ደረጃ ደርሶ ‹ሰብ› ምሉዕ ‹ሰው› ለመባል የበቃ ሲሆን ይህም የስሙ ትርጉም እስካሁን ባለው ቋንቋዎቻችንም ውስጥ ተወርሶ፤ ግለ***ሰብ***፣* **ሰብ**ዓዊ፣ ማህበረ**ሰብ**፣ ሀብረተ-**ሰብ** ወዘተ እንላለን፡፡ *ስለዚህ ልጅ አብርሃም ሆይ ‹ሳባ› ማለት የወንድ ስም ሲሆን በኩሽ ምድር ላይ የነገሰ የሳባውያን መስራች ንጉስ ነበር፡፡" አሉና ፈገግ ብለው አዩት፤ መልሱን ያገኘው አብርሃምም ተረጋግቶ ተቀመጠ፡፡ ትረካቸውን ቀጠሉ…*

*"አሁን ሳትበላችሁ አድምጡኝ፤ ቅ.ቁርዓን በሳባ ምዕራፍ ቁጥር 15 ጀምሮ እንዲህ ይላል «(15)ለሰበእ (ሰዎች) በመኖሪያቸው (ሃገራቸው ውስጥ) በእውነት አስደናቂ ምልክት ነበራቸው፡፡ ከግራና ከቀኝ ሁለት የአትክልት ስፍራዎች (ነበሯቸው)፡፡ «ከጌታችሁ ሲሳይ ብሉ፡፡ ለእርሱም አመስግኑ፡፡ (አገራችሁ) ውብ አገር ናት፡፡ (ጌታችሁ) መሓሪ ጌታም ነው» (ተባሉ)፡፡ (16)(እነርሱ ግን ከማመስገን) ዞሩ፡፡ በእነርሱም ላይ የግድቡን ጎርፍ ለቀቅንባቸው፡፡ በአትክልቶቻቸውም ሁለት አትክልቶች፣ ባለመርጋጋ ፍሬዎችን፣ ባለአሾህና ቁርቁራም ባለጥቂት ቅጠል ዛፎች(ቁልቋልና ግራር)ን ለወጥናቸው፡፡ (17)በመካዳቸው ይህንን መነዳናቸው፤ (እንዲህ ያለውን ቅጣት) በጣም ከሓዲን እንጂ ሌላውን እንቀጣለንን? (18)በእነርሱና በዚያች በውስጧ በረከትን ባደረግንባት አገር (በሻም) መካከልም ቅጥልጥል ከተሞችን አደረግን፡፡ በእርሷም ጉዞን ወሰንን፡፡ «ጸጥተኞች ኾናችሁ በሌሊቶችም በቀኖችም ተጓዙ፤» (አልን)፡፡ (19)«ጌታችን ሆይ! በጉዞዎቻችን መካከል አራርቅልን» አሉም፡፡ ነፍሶቻቸውንም በደሉ፡፡ (መገረሚያ) ወሬዎችም አድርገን አስቀረናቸው፡፡ መበታተንንም ሁሉ በታተንናቸው፡፡ በዚህ (ታሪክ) ውስጥ በጣም ታጋሽና አመስጋኝ ለሆነ ሰው ሁሉ መገሰጫዎች አሉበት፡፡ (20)ዲያቢሎስም በእነርሱ ላይ ምኞቱን (ያሰበውን) በእርግጥ ፈጸመ፤ ከአመኑትም (እምነት ካላቸው) የሆኑት ጭፍሮች በስተቀር (ሌሎቹ ሰዎች) ተከተሉት፡፡"* ይላል፤ ይህን ታሪክ በትክከል አስተውሎ ላየው እስከ የመን ድረስ ይገዛ የነበረ፣ መኳኳገ ፖርታል ፒራሚዶች እስከ ደቡብ አሜሪካና ታይላንድ ድረስ ሰርተው ከዓለም ጫፍ እስከጫፍ ይጓዙ የነበሩ ህዝቦችን ታሪክ ያሳያል፡፡ አሁን ሳህራ በረሃ የምንለው በሙሉ ለም አፈርና የስልጣኔ ማማ የደረሱ ጥቁር ነገስታት መናኸሪያ ነበር፡፡ የሚገርመው እነዚህ ሁለት ትላልቅ ግድቦችና የአትክልት መስኖ ቅሪቶች አሁን በየመን፣ አልጄሪያ፣ ሊቢያና ግብፅ አሸዋ ውስጧቸው በአርኪዮሎጂስቶች ተቆፍረው እየወጡ መሆኑ ሲሆን ይበልጥ የሚያስገርመው ደግሞ እነዚህ ትላልቅ የድንጋይ ቤቶች በሞሉት ቦታ ውስጥ እየተገኙ ያሉት የጥቁር ነገስታት ቅርፅ መሆኑ ነው፡፡

ባጠቃላይ አምላክን በመካድ የሰሩት በደል ትልቅ ዋጋን አስከፍሏቸዋል፡፡ ያው እስካሁንም መገረሚያ ታሪክ ብቻ ሆነው ቀርተዋል... የፒራሚድ ሰዎች፡፡ ባለራዕይው ናሆምም ነገሩን እንደትንቢት አድርጎ በመፅሐፍ ቅዱስ አስፍሮታል፡፡ትንቢተ ናሆም ምዕራፍ 3 ጀምሮም እንዲህ ይላል...

1፤ ለደም ከተማ ወዮላት! በሁለንተናዋ ሐሰትና ቅሚያ ምልቶባታል፤ ንጥቂያ ከእርስዋ አያልቅም። 2፤ የአለንጋ ድምፅ፥ የመንኰራኵርም ድምፅ፥ የፈረሶችም ኮቴ፥ የፈጣን ሰረገላም ጩኸት ተሰምቶአል፤ 3፤ ፈረሰኛው ይጋልባል፥ ሰይፍም ይንቦገቦጋል፥ ጦርም ይብለጨለጫል፤ የተገደሉትም ይበዛሉ፥ በድኖችም በከምር ይከመራሉ፥ ሬሳቸውም አይቈጠርም፤ በሬሳቸውም ይሰናከላሉ። 4፤ ስለ ተዋበችው ጋለሞታ ግልሙትና ብዛት ይህ ሆኖአል፤ እርስዋም በመተትዋ አጅግ በለጠች፥ አሕዛብንም በግልሙትናዋ፥ ወገኖችንም በመተትዋ ሸጠች። 5፤ እነሆ፥ በአንቺ ላይ ነኝ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፥ ልብስሽን በፊትሽ እገልጣለሁ፤ ኀፍረተ ሥጋሽንም ለአሕዛብ፥ ነውርሽንም ለመንግሥታት አሳያለሁ። 6፤ ርኵሰትንም በላይሽ እጥላለሁ፥ እንቅሻማለሁ፥ ማላገጫም አደርግሻለሁ። 7፤ የሚያይሽም ሁሉ ከአንቺ ሸሽቶ። ነነዌ ባድማ ሆናለች፤ የሚያለቅስላትስ ማን ነው? የሚያጽናናትንስ ከወዴት አፈልጋለሁ? **ይላል። 8፤ አንቺ በመስኖች መካከል ከተቀመጠችው፥ ውኃም በዙሪያዋ ከነበራት፥ ምሽግዋም ባሕር ከነበረ፥ ቅጥርዋም በባሕር ውስጥ ከነበረ ከኖእ አሞን ትበልጫለሽን? 9፤ ኢትዮጵያና ግብጽ የማይቈጠር ኃይልዋ ነበሩ፤ ፉጥና ልብያ ረዳቶችዋ ነበሩ። 10፤ እርስዋ ግን ተማርካ ፈለሰች፤** ሕፃናቶችዋ በመንገድ ሁሉ ራስ ላይ ተፈጠፈጡ፤ በከበርቴዎችዋም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ፥ ታላላቆችዋም ሁሉ በሰንሰለት ታሰሩ።"

በዚህ ትንቢት ላይ ጋለሞታይቱ ሃገር ነነዌ አመሳስሎ አሞናውያንን ጠቅሷል፤ ከዚህ ታሪክ ላይ እንድትረዱ የምፈልገው ግን የእኛ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንን የነበሩበት የአሞን (የአሙን) ጣዖትን የሚያመልኩት መንግስታት አላህን በማስቆጣታቸው ታላቅ በላ እንደወረደባቸው ነው፡፡ የእነዚህ ሳባውያን ኢትዮጵያውያን በመስኖች መሃል የተመሰረተች ታላቅ ስልጣኔ አሁን በህንድ ውቅያኖስ ውስጥ የሰመጠውን ታላቅ የታሚል ግዛት ጨምሮ ሰፊ ቦታን ያካልል ነበር፡፡ ፈጣሪያቸውን ባስቆጡ ጊዜ ግን ግድባቸው ፈርሶ በውሃ ተጥለቀለቁ፤ ከዚያም የግዮን ወንዝ ለብዙ ዓመታት ደረቀና የነበራቸው ታላቅ ስልጣኔ ከፊሉ ጠፋ ከፊሉም በቁልቋል ዛፍ የተሞላ የሳሃራ በረሃ ሆነ፤ ታላቅ ሰቃይና መከራም በህዝቡ ላይ ደረሰ፡፡

የእግዚአብሔር ቃል-ኪዳን ግን በከፊል ኢትዮጵያዊ ከሆነው ከዳዊት ጋር ቆሞ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት የተሰደደባት ታላቅ ሃገር ትቢያ ስትሆን ያየው ዳዊትም በመዝሙረ ዳዊት ምዕ.74 እንዲህ ብሎ በዝማሬ ተነቤየ፤

1፤ አቤቱ፥ ስለምን ለዘወትር ጣልኸኝ? በማሰማርያህ በጎች ላይስ ቍጣህን ስለ ምን ተቈጣህ? 2፤ አስቀድመህ የፈጠርሃትን ማኅበርህን፥ የተቤዠሃትንም የርስትህን በትር፥ በእርስዋ ያደርህባትን የጽዮንን ተራራ አስብ። 3፤ ጠላት በቅዱሳንህ ላይ እንደ ከፋ መጠን፥ ሁልጊዜም በትዕቢታቸው ላይ እጅህን አንሣ። 4፤ ጠላቶችህ በበዓል መካከል ተመኩ፤ የማያውቁትንም ምልክት ምልክታቸው አደረጉ። 5፤ እንደ ላይኛው መግቢያ ውስጥ በዱር እንዳሉም እንጨቶች፥ በመጥረቢያ በሮችዋን ሰበሩ። 6፤ እንዲሁ በመጥረቢያና በመዶሻ ሰበሩአት። 7፤ መቅደስህን በእሳት አቃጠሉ፤ የስምህንም ማደሪያ በምድር ውስጥ አረከሱ። 8፤ አንድ ሆነው በልባቸው በየሕዝባቸው። ኑ፥ የእግዚአብሔርን በዓሎች ከምድር እንሻር አሉ። 9፤ ምልክታችንን አናይም ከእንግዲህ ወዲህም ነቢይ የለም፤ እስከ መቼ እንዲኖር የሚያውቅ በኛ ዘንድ የለም። 10፤ አቤቱ፥ ጠላት እስከ መቼ ይሳደባል? ስምህን ጠላት ሁልጊዜ ያቃልላልን? 11፤ ቀኝህንም በብብትህ መካከል፥ እጅህንም ፈጽመህ ለምን ትመልሳለህ? 12፤ እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው፥ በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ። 13፤ አንተ ባሕርን በኃይልህ አጸናሃት፤ አንተ የእባቦችን ራስ በውኃ ውስጥ ሰበርህ። 14፤ አንተም የዘንዶውን ራሶች ቀጠቀጥህ፤ ለኢትዮጵያ ሰዎችም ምግባቸውን ሰጠሃቸው። 15፤ አንተ ምንጮቹንና ፈሳሾቹን ሰነጠቅህ፤ አንተ ሁልጊዜ የሚፈስሱትን ወንዞች አደረቅህ*። 16፤ ቀኑ የአንተ ነው ሌሊቱም የአንተ ነው፤ አንተ ፀሐዩንና ጨረቃውን አዘጋጀህ።" (*ግዮንን)

ቁጥር 16 ላይ ዳዊት በግልፅ ‹‹ፀሐይ አምላክ አይደለችም ተፈጣሪ ነች›› ብሎ በአምናውያን የፀሐይ አምላኪዎች ላይ የደረሰውን ጥፋት ምክንያት ይነግረናል፡፡"

አሉና ሼህ ከድር ሰማይ ላይ ወዳለችው ፀሐይ እየጠቆሙ፤ "ይህቺ ፀሐይ ከአምላኳ ትዕዛዝ አንዲትም ሳታፈነግጥ ለዘመናት እየወጣች የምትጠልቅ ስትሆን የሙቀትና ብርሃን ምሳሌዋ ልክ እንደ አንፖል ነው፡፡ አንፖሏ የኤሌክትሪክ ሃይል ካላገኘች እንደማትበራ ሁሉ የፀሐይም ሃይልና ጉልበት ምንጩ ደግሞ ፈጣሪ ብቻ ነው፡፡" ብለው እጃቸውን አወረዱ፤

"ወደ ሳባ ምዕራፍ ተመልሰን ከቁጥር 10 ጀምሮ ብናነብ" አሉና ሼህ ከድር ማንበብ ጀምሩ፤ "(10)ለዳውድም ከእኛ የኾነን ችሮታ በእርግጥ ሰጠነው፡፡ (አልንም)፡-«ተራራዎች ሆይ! ከእርሱ ጋር ውዳሴን መላልሱ(ዘምሩ)፡፡ በራሪዎችንም (አገራንለት)፡፡ ብረትንም ለእርሱ አለዘብንለት፡፡ (11)ሰፋፊዎችን ጥሩሮች ሥራ፡፡ በአሠራርዋም መጥኑ፡፡ መልካምንም ሥራ ሥሩ፡፡ እኔ የምትሠሩትን ነገር ሁሉ ተመልካች ነኝና" (አልነው)፡፡ (12)ለሱለይማንም ነፋስን የቀትር በፊት ጉዞዋ የወር መንገድ፤ የቀትር በኋላ ጉዞዋም የወር መንገድ (ወር የሚፈጅ ጉዞ በአንድ ቀትር

*እንዲጨርስ) ሲኾን ገራንለት:: የንሐስንም ምንጭ ለእርሱ አፈሰስንለት:: ከጋኔኖችም በጌታው ፈቃድ በፊቱ የሚሠሩን (የኢጋንንት ባሪያዎች አደረግንለት):: ከእርሱም ውስጥ ከትእዛዛችን ዝንፍ የሚል ከነዲድ እሳት ቅጣት እናቀምሰዋለን:: (13)ከምኩራቦች፡ ከምስሎችም እንደ ገንዳ ከኾኑ ገበታዎችም፤ ከተደላደሉ ታላላቅ ድስቶችም የሚሻውን ሁሉ ይሠሩለታል:: (አልናቸውም) «የዳውድ ቤተሰቦች ሆይ! አመስጋኞች ኾናችሁ (ለጌታችሁ) ሥሩ::» ከባሮቼ በጣም አመስጋኞቹም ጥቂቶች ናቸው:: (14)በእርሱም ላይ ሞትን በፈጸምንበት ጊዜ (ንጉሰ ሰለሞን ከሞተ በኋላም ያልሞተ መስሏቸው ኢጋንንቱ ሲታዘዙት) መሞቱን በትሩን የምትበላ ትል እንጂ ሌላ አላመለከታቸውም:: (ትሏ በትሩን በልታ ጨርሳው ከተደገፈበት ሲሰበርና) በወደቀ ጊዜም ጋኔኖች ሩቅን ምስጢር የሚያወቁ በኾኑ ኖሮ በአዋራጅ ስቃይ ውስጥ (መሞቱን ሳያውቁ እየሰሩ) የማይቆዩ እንደነበሩ ተረዱ::"* የሚል አሲደናቂ ፅሑፍ እናነባለን:: በዚህ አንቀፅ የዳዊትን ከሰሜን ተራሮች ጋር መዘመሩን አስታውሶ ጀምሮ ከዚያም ከነሐስ፣ ሰንፔርና ከሌሎች ውድ ማዕድናት ተቀይጦ እንደተሰራ የሚታወቀው አከሱም ሃውልት ከኢትዮጵያዊ ቤተሰቦቹ ጋር መስራት መጀመሩን፤ የእነዚህም ጥሩሮች ስራ በዳዊት ጊዜ ቢጀመርም በሰሎሞንም እንደቀጠሉ፤ አንድ ወር ሙሉ ሊፈጅ የሚችል መንገድን በአንዲት የቀትር ከሰዓት መሄድ የሚያስችሉ መንፈሳዊ መጓጓዣዎች እንደሆኑ ይጠቁመናል፤ ይህም <<አከሱማ» የተባለው በዚህ መጓጓዣ ከሌላ ቦታ የሚመጡም ሆነ የሚሄዱ ሰዎች አቀባበል ሲደረግላቸው <<አካም» ተብለው ‹‹እንኳን ደህና መጣችሁ» ስለሚባባሉ ነው::

ሌላ አስገራሚው ታሪክ ደግሞ አጋንንቶች የሰለሞን ባሪያ ሆነው ማገልገላቸውን የሚገልፅ ሲሆን ስራቸውን በሚገባ ካልሰሩ የእሳት ንዳድ የሆነ አለንጋ እየገረፈ ይቀጣቸውም ነበር:: ታዲያ ተዓምር የሆነው ታሪክ ያለው ቁጥር 14 ላይ ሲሆን ይህም የሚያትተው የሰለሞን ባሪያ ሆነው ሲሰሩ የነበሩት የሰውና የጋኔል ባሪያዎች መሞቱን ሳያውቁ አለቃቸው ጠቢቡ ሰሎሞን በትሩን ደገፍ እንዳለ ህይወቱ ማለፉ ነው:: እነርሱ ግን ለረጅም ጊዜያት መሞቱን ሳያውቁ የሚያያቸው መስሏቸው ታትረው ይሰሩ ነበር:: አንዲት እንጨት የምትበላ ትል በትሩን ውስጥ ለውስጥ በልታ እስከትጨርሰውና በትሯ የሰለሞንን አካል መሸከም አቅቷት እስከትሰበር፤ እርሱም ወደ መሬት እስኪወድቅ ድረስ መሞቱን አላወቁም ነበር:: ይህም ለእኛ የሚያስተላልፍልን ትልቅ መልዕክት ቢኖር አጋንንቶችም ሆኑ በአጋንንት እንሰራለን የሚሉ ጠንቅ-አዋዮች እንኳን ስለሌላው ወደፊት ቀርቶ ስለራሳቸው እንኳን እንደማያውቁ ነው::" አሉና ሁሉንም አንድ በአንድ ተመለከቷቸው፤ ተመስጠው እየተከታተሏቸው መሆኑን አረጋገጡና ቀጠሉ፤

"እናም ታሪኩን ስጀምር እንደነገርኳችሁ እነዚያ የጥፋት ስህተቶች በኢትዮጵያ ላይ የተከሰቱት ሃያሉና ጥበበኛው የኢትዮጲያ ንጉስ እስያኤል ወይም ዙልቀርኒን የስልጣን ገደብ ያስፈልጋል ብሎ ንግስናውን አሳልፎ ሰጥቶ ዓለምን እየዞረ ጀብድ እየሰራ በነበረበት ወቅት ነበር:: በሐገሩ ላይ የተከሰተውን በሰማ ጊዜም በሽምግልና እድሜው ትክክለኛውን ሃይማኖት ለማቅናት ተመልሶ መጣ:: ከኃርፍና ድርቅ የተረፈውን ስልጣኔያቸው እንዲያንሰራራ ደፋ ቀና ይሉ የነበሩ ኢትዮጵያውን በአዲስ መነሳሳት ሃገሪቱን ማሳደግ ጀመሩ:: ነገር ግን ይሄ ነገር ካልተዋጠላቸው መካከል አጋቦን የሚባል በወቅቱ የነበረ ንጉስና ሌሎችም የአምን ጣዖት አገልጋይ የነበሩ ካህናች ነበሩ:: ዝማሬና ግጥም በጣም ለሚወደው እስያኤል በመጀመሪያ ንግስናው ወቅት መንፈሳዊ መዝሙር ይዘምሩ ከነበሩት ዘማሪያን አዜባ የምትባለው አንዷ ስትሆን ሌላ ዘማሪ ከነበረ ጀንደረባ ጋር በፍቅር ትወድቅና ታረግዛለች፤ ትወልዳለችም:: ይህንን ለቤተ-መንግስትና ቤተ-ክህነቱ እጅግ አስነዋሪ የሆነ ድርጊት እንደተፈፀመ በሰማ ጊዜ እስያኤል እጅግ ተቆጥቶ ነበር:: ህግ ሲጣስ ሊመጣባቸው የሚችለውን የኃርፍና ውሃ መድረቅ ከባድ ቅጣት አሰበናም ለሁሉም መቀጣጫ ይሆኑ ዘንድ በሞት እንዲቀጡ ወሰነ::

ታድያ እስያኤል በስተርጅና ሲመለስ ነግሶ የነበረው ይህ አጋቦን የሚባል የአሙን አምላኪ ንጉስ በኋላ በመፅሐፈ ያሻር መሰረት እስያኤል ወላጆቿን ያስገደለባት ንግስተ ሳባ ተብላ ለምትነግሰው ሴት የእናቷ አባት ወይም አያቷ ነበር:: እሱም ነበር ከልጅነቷ ጀምሮ በድብቅ ያሳደጋት፤ ንግስተ ሳባም እናቷ ላይ እስያኤል ንጉስ ሳለ ያደረገባትንም በሙሉ ታውቅ ነበር፤ ደማቸውንም ለመበቀል ታቅድ ነበር:: እያደገች ስትመጣም ጥሩ ዜመኛና አገልጋይ ስለሆነች ተመልሰው የመጡት የሽማግሌው እስያኤል የቅርብ ሞግዚት ለመሆን ብዙ ጊዜ አልፈጀባትም:: ታዲያ አንድ ቀን ጥሩ አጋጣሚ ስታገኝ በተኛበት ገደለችው:: በአያቷ አጋቦን እጅም ተቀብታ ንግስተ-ሳባ ሆነች:: ነገር ግን ከእነዮቶርና እስያኤል በተለየ መንገድ ሄደች:: መጽሐፍ ቅዱስ ከመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ 10 ጀምሮ እንዲህ ይላል ‹‹1፤ የሳባም ንግሥት በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች። 2፤ በግመሎችም ላይ ሽቱና እጅግ ብዙ ወርቅ የከበረም ዕንቍ አስጭና ከታላቅ ጓዝ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ገባች፤ ወደ ሰሎሞንም በመጣች ጊዜ በልብዋ ያለውን ሁሉ አጫወተችው።

3፤ ሰሎሞንም የጠየቀችውን ሁሉ ፈታላት፤ ሊፈታላት ያልቻለውና ከንጉሡ የተሰወረ ነገር አልነበረም። 4፤ የሳባም ንግሥት የሰሎሞንን ጥበብ ሁሉ፥ ሠርቶትም የነበረውን ቤት፥ 5፤ የማዕዱንም መብል፥ የብላቴኖቹንም አቀማመጥ፥ የሎሌዎቹንም አሠራር አለባበሳቸውንም፥ ጠጅ አሳላፊዎቹንም፥ በእግዚአብሔርም ቤት

የሚያሳርገውን መሥዋዕት ባየች ጊዜ ነፍስ አልቀረላትም። 6፤ ንጉሡንም አለችው። ስለ ነገርህና ስለ ጥበብህ በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና እውነት ነው። 7፤ እኔም መጥቼ በዓይኔ እስካይ ድረስ የነገሩኝን አላመንሁም ነበር፤ እነሆም፥ እኩሌታውን አልነገሩኝም ነበር፤ ጥበብህና ሥራህ ከሰማሁት ዝና ይበልጣል። 8፤ በፊትህ ሁልጊዜ የሚቆሙ ጥበብህንም የሚሰሙ ሰዎችህና እነዚህ ባሪያዎችህ ምስጉኖች ናቸው። 9፤ አንተን የወደደ፥ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን፤ እግዚአብሔር እስራኤልን ለዘላለም ወድዶታልና ስለዚህ ጽድቅና ፍርድ ታደርግ ዘንድ ንጉሥ አድርጎ አስነሣህ። 10፤ ለንጉሡም መቶ ሀያ መክሊት ወርቅ እጅግም ብዙ ሽቱ የከበረም ዕንቍ ሰጠችው፤ የሳባ ንግሥት ለንጉሡ ለሰሎሞን እንደ ሰጠችው ያለ የሽቱ ብዛት ከዚያ ወዲያ አልመጣም ነበር። 11፤ ከኦፊርም ወርቅ ያመጡ የኪራም መርከቦች እጅግ ብዙ የሰንደል እንጨትና የከበረ ዕንቍ ከኦፊር አመጡ። 12፤ ንጉሡም ከሰንደሉ እንጨት ለእግዚአብሔር ቤትና ለንጉሡ ቤት መከታ፥ ለመዘምራኑም መሰንቆና በገና አደረገ፤ እስከ ዛሬም ድረስ እንደዚያ ያለ የሰንደል እንጨት ከቶ አልመጣም አልታየምም። 13፤ ንጉሡም ሰሎሞን፥ በገዛ እጁ ከሰጣት ሌላ፥ የወደደችውን ሁሉ ከእርሱም የለመነችውን ሁሉ ለሳባ ንግሥት ሰጣት፤ እርስዋም ተመልሳ ከባሪያዎችዋ ጋር ወደ ምድርዋ ሄደች።››

በዚህ ምዕራፍ መሰረት ንግሥት ሳባ ጠቢቡ ሰለሞንን ለመፈተን እስባ እንቆቅልሾችና እጅግ በርካታ ለስጦታ የሚሆን መደለያ ነገሮችን ይዛ እንደሄደች ይናገራል:: ብዙዎች ባይስማሙበትም በቁጥር 7 ላይ በተገለፀው መሰረት እ/ር ጥበብ የሰጠውን ንጉስ ተጠራጥሮ አለማመንና በስጦታና እንቆቅልሽ መፈተን የእማኝ ሴት ተግባር አይደለም:: ታላቁን የእግዚአብሔር ካህን ገድላ በአሞን ጣዖትና ፀሐይን አምላኪው አያቷ ኢጋቦን እርዳታ ወደ ንግስትነት የመጣቸው ንግስተ ሳባ ጠቢቡ ሰሎሞንን ካገኘች በኋላ አምላክን እንደተቀበለች ማስረጃዎቹ ግልፅ ናቸው::

በእኛ ቁርዓንም በነምል ወይም በጉንዳኒቱ ምዕራፍ ቁጥር 16 ጀምሮ የሰለሞንና ንግስተ ሳባን ታሪክ እንዲህ ይተርከዋል:: ``(16) ሱለይማንም ዳውድን ወረሰ::እሱም አለ «ሰዎች ሆይ! የበራሪን ንግግር (የወፍን ቋንቋ) ተማርኩኝ:: ከነገሩም ሁሉ (ሀብትና ጥበብ) ተሰጠን:: ይህ እርሱ በእርግጥ ግልጽ የኾነ ችሮታ ነው::» (17) ለሱለይማንም ሰራዊቶቹ ከጋኔን፣ ከሰውም፣ ከበራሪም የኾኑት ተሰበሰቡ:: እነሱም ይከመከማሉ:: (18) ከጉንዳንም ሸለቆ በደረሱ ጊዜ አንዲት ጉንዳን «እናንተ ጉንዳኖች ሆይ! ወደ መኖሪያዎቻችሁ ግቡ:: ሱለይማንና ሰራዊቱ እነርሱ ሳያውቁ እንዳይሰባብሩዋችሁ» አለቻቸው:: (19) (ሰለሞንም) በንግግርዋም እየሳቀ ጥርሱን ፈገግ አደረገ:: «ጌታዬ ሆይ! ያቺን በእኔና በወላጆቼ ላይ የለገስካትን ጸጋህን እንዳመሰግን የምትወደውንም በጎ ሥራ እንድሠራ ምራኝ::

*በችሮታህም በመልካሞቹ ባሮችህ ውስጥ አግባኝ» አለ፡፡" ሲል ድንገት መርየም ሳቀች፣*

*"ምነው ሳቅሽሳ መርየሞ?" አሏት ሼህ ከድር፤*

*"ኢዩ የጉንዳኗ ማስጠንቀቂያ አስቆኝ ነው፡፡ ማለት ወገኖቿ ተረግጠው እንዳይደፈጠጡባት ፈርታ ግቡ ስትል አስቤው ነው፡፡" አለች መርየም፤*

*"ተሳስተሻል!" አሏት ሼህ ከድር፤*

*"ምኑን?"*

*"እንዳይደፈጥጣቸው ሳይሆን እንዳይሰባብራቸው ነው የሚለው የጀሊሉ ቃል፤"*

*"አልገባኝም?" አለች መርየም ግራ እየተጋባች፤*

*"ይኸውልሽ ልጄ፤ የሰለሞን ሰራዊት ሲመጣ ጉንዳኖቹ ማውራታቸው ሊያስቅን ይችላል፡፡ ነገር ግን በቅርቡ ሳይንቲስቶች ባደረጉት ጥናት ጉንዳኖች የራሳቸው የሆነ መግባቢያ ቋንቋ እንዳላቸው አረጋግጠዋል፡፡ በሌላ በኩል ‹‹እንዳይሰባብረን» ነው የሚለው የቁርዓኑ ቃል ያልኩሽ አሁንም በተደረገ ሌላ የቅርብ ጊዜ ጥናት የጉንዳኖች አካል የተገነባው ሲልከን ከሚባል ማዕድን እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ይህም <ሲልከን» የተሰኘ ማዕድን ብርጭቆ እና መስታወት ለመስራት የምንጠቀምበት ነው፡፡ ቁርዓኑም ይህን ለማመልከት ጉንዳኗ ‹‹እንደ ብርጭቆ እንዳይሰባብሩን» እንዳለች ይነግረናል፡፡ ለማንኛውም ታሪኩን እንቀጥል ብለው አጎነበሱና ንባባቸውን ገፉበት፤*

*"20፤ በራሪዎቹንም ተመለከተ፤ (ሁድሁድ የሚባለውን ወፍ ሲያጣ) አለ፤ «ሁድሁድን ለምን አላየውም! በእውነቱ ከራቁት ነበርን፡፡ (21)(ቶሎ ካልተመለሰ) «ብርቱን ቅጣት በእርግጥ እቀጣዋለሁ ወይም ዐርደዋለሁ፤ ወይም ግልጽ በኾነ አስረጅ ይመጣኛል» (አለ) (22)(ወፉ) ዕሩቅ ያልኾነንም ጊዜ ቆዬ፡፡ አለም «ያላወቅከውን ነገር አወቅኩ፡፡ ከሰበእም እርግጠኛን ወሬ አመጣሁልህ፡፡ (23)«እኔ የምትገዛቸው የኾኑትን ሴት ከነገሩም ሁሉ የተሰጠችኝ አገኘሁ፡፡ ለእርሷም ታላቅ ዙፋን አልላት፡፡ (24) «እርስዋንም ሕዝቦችዋንም ከአላህ ሌላ ለፀሐይ ሲሰግዱ አገኘኋቸው፡፡ ሰይጣንም ለእነሱ ሥራዎቻቸውን ሸልሞላቸዋል፡፡ ከእውነተኛውም መንገድ አግዷቸዋል፡፡ ስለዚህ እነሱ (ወደ እውነት) አይምመሩም፡፡» (25) ለዚያ በሰማያትና በምድር የተደበቀውን ለሚያወጣው፤ የምትሸሽጉትንና የምትገልጹትንም ሁሉ ለሚያውቀው አላህ እንዳይሰግዱ (ሰይጣን አግዷቸዋል)፡፡ (26) አላህ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም፡፡ የታላቁ ዐርሽ (ዙፋን) ጌታ ነው፡፡ (27)(ሱለይማንም) አለ «እውነት እንደ ተናገርክ ወይም ከውሸታሞቹ እንደ ኾንክ ወደፊት እናያለን፡፡ (28)«ይህንን ደብዳቤዬን ይዘህ ኺድ፡፡ ወደእነርሱም ጣለው፡፡*

ከዚያም ከእነሱ ዘወር በል:: ምን እንደሚመልሱም ተመልከት::» (2)(የሳባ ንግስትም በደረሳት ጊዜ) አለች «እናንተ መማከርቶች ሆይ! እኔ ክብር ያለው ጽሑፍ ወደኔ ተጣለ::

(30) የተላከውም ከሰለሞን ነው፤ እርሱም እጅግ በጣም ሩኅሩኅና በጣም አዛኝ በኾነው አምላክ ስም ነው:: (31) «በእኔ ላይ አትኩሩ:: ታዛዦችም ኾናችሁ ወደኔ ኑ፤ (የሚል ነው):: (32) «(አለቻቸው) እናንተ መማከርቶች ሆይ! በነገሬ (የሚበጀውን) ንገሩኝ:: እስከምትገኙልኝ ድረስ ውሳኔ መስጠት አልችልምና» አለች:: (33) እነርሱም፤ «እኛ የኃይል ባለቤቶች የብርቱ ጦርም ባለቤቶች ነን:: ግን ትዕዛዙ ወደ አንቺ ነው:: ምን እንደምታዝም አስተውዪ፤» አሏት:: (34) (እርሷም) አለች «(መሰል) ንጉሦች ከተማችንን (በኃይል) ቢገቡባት ያበላሹዋታል:: የተከበሩ ሰዎችዋንም ወራዶች ያደርጋሉ:: እንደዚሁም (እነዚህ ከፉ) ይሠራሉ:: (35) «እኔም ወደእነርሱ (የመደለያ) ገጸ በረከትን እልከና መልከተኞቹ ምን አይነት መልዕክት ይዘው እንደሚመለሱ እጠብቃለሁኝ::» አለች:: (36) (መልከተኛውም) ሰለሞን ጋር መጣና መደለያ ስጦታና ገንዘቡን አቀረበ:: ሰለሞንም አለው «በገንዘብ ልትደልሉኝ ትሞክራላችሁን? ለእኔ አምላኬ የሰጠኝ እናንተ ከምትሰጡኝ እጅጉን የበለጠ ነው:: ይልቁንም እናንተ በገጸ በረከታችሁ ትደሰታላችሁ::» (37)«ወደእነርሱ (ወደመጣኸበት) ተመለስ:: እነርሱንም ከችሎታቸው በላይ በሆነ ሰራዊት እንመጣባቸዋለን:: ከግዛታቸው እነርሱ የተዋረዱ ኾነው እርግጥ እናወጣቸዋለን» (አለ)::

ከዚያም አማካሪዎቹን ሰበሰበና ንግስቲቱ በጣም የምትኮራበት ነገር ምን እንደሆነ ጠየቃቸው፤ እነርሱም የምትቀመጥበት በወርቅና እንቁ ያቆጠቆጠ ግዙፍ ዙፋን እንዳላት ነገሩት:: እርሱም አላቸው፤ 38«እናንተ መኳንንቶች ሆይ! እነዚህ ሳባውያን አማኞች ኾነው ሳይመጡ በፊት የንግስትዋን ዙፋን የሚያመጣልኝ ማንኛችሁ ነው?» ብሎ ጠየቃቸው:: 39 ከሚያዛቸው ጋኔሎች መካከል ኀይለኛው «ለችሎት ፍርድ ከተቀመጥክበት ከመነሳትህ በፊት እኔ ዙፋኗን አመጣልሃለሁኝ:: እኔም በእርሱ ላይ ብርቱ ታማኝ ነኝ» አለ:: (40) ያ እርሱ ዘንድ ከመጽሐፉ ዕውቀት ያለው ሰው (ከቶራህና ከቀደሙት የጥበብ መፅሃፍት የሚያውቅ) «ዓይንህን ጨፍነህ ከመከፈትግ በፊት በጥቅሻ ፍጥነት እኔ ዙፋኗን አመጣልሃለሁኝ» አለ፤ (እንደዚሁም አደረገ):: እርሱ ዘንድ ረግቶ ባየውም ጊዜ «ይህ ከጌታዬ ችሮታ ነው:: የማመሰግን ወይም የምክድ መኾኔን ሊሞክረኝ (ቸረልኝ):: ያመሰገነም ሰው የሚያመሰግነው ለራሱ ነው:: የካደም ሰው ጌታዬ ከእርሱ ተብቃቂ ቸር ነው(ስለካዱት አይጎድልበትም)» አለ::"

እንግዲህ እስካሁን ባየነው ትረካ እንደምንረዳው ንግስተ ሳባ የሰለሞንን የአንድ አምላክ እናምልከ ጥሪ ሳትቀበል በፀሐይ ማምለኩን ከመምረጧም

ባሻገር ጠቢቡ ሰለሞንን ለመደለል ብዙ ስጦታ በመልዕክተኛ ልካለት እርሱም ስጦታዋን ውድቅ አድርጎባታል፡፡ ከዚህም በኋላ የምትመካበትና የስልጣኗ መገለጫ የሆነው በወርቅና እንቁ የተሰራው ዙፋኗ እንደሆነ አውቋል፡፡ ከዚያ በመቀጠል በቁጥር 39 እና 40 ላይ የምናነበው እውነታ የሰው ልጆች ጥበባቸውን ከተጠቀሙ ምን ያህል ከአጋንንትና ጋኔሎች የበለጠ ሃይል እንዳላቸው አመላካች ነው፡፡ ምክንያቱም ዙፋኗን እንዲያመጡ ሰለሞን ሲያዛቸው ጋኔሉ ያለው ከተቀመጥከበት ሳትነሳ አመጣልሃለሁኝ ሲሆን ይህም የተወሰኑ ደቂቃዎች አንስቶ እስከ ሰዓታት የሚፈጅ ስራ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ነገር ግን በጎኑ የነበረ የሰው ልጅ ዙፋኗን በአይን ጥቅሻ ፍጥነት እንዳመጣለት እንረዳለን፡፡ ታዲያ ይህ ሰው በመፅሐፍት ብዙ እውቀት የነበረው እንደሆነ ስለሚጠቅስ የእነዮቶር-አብን ጥበብ ያጠና የኢትዮጵያ ሰው እንደሆነ ያጠራጥራል፡፡ ለማንኛውም ቀጣዩ ታሪክ ደግሞ ከመቅጽበት ዙፋኗ የተወሰደባት ኢትዮጵያዊቷ ንግስተ ሳባ ዙፋኗን ለማስመለስ ብሎም የዚህን ሃያል ጥበበኛ ንጉስ ሰለሞን የተባለ ሰው ሚስጥር ለመመርመር ወደእስራኤል አቀናች፡፡ ስትሄድም እጅግ በርካታ ስጦታዎችን ይዛና በተለይም ኢትዮጵያዊ ለመሆኗ ማሳያ የሆነውን አሁንም በሰሜን ትግራይ የሚመረተውን ከርቤና የሚያውድ ማዓዛ ያላቸውን እጣኖች ይዛ ተጓዘች፡፡ እዚህ ጋር ቁርዓንና መፅሐፍ ቅዱስን የሚያሰናስላቸው ታሪክ ደግሞ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንቆቅልሾችን መፍታቱንና ስርቶት የነበረውን ቤት እንዳሳያት ቢናገርም የእንቆቅልሾቹንና የቤቱን ምንነትና አፈታቱን በግልፅ አልጠቀሰም፡፡ አሁን ግን የማነብላችሁ አራት አንቀፆች ሁሉንም ሚስጥር የሚፈቱ ናቸው፡፡

*በሐዲስ እንደተዘገበው ከሆነ ሰለሞን የንግስተ ሳባን ዙፋኗን ፍለጋ መምጣት ባወቀ ጊዜ የእሷን ዙፋን ደበቀና ሌላ የእሷን ዙፋን የሚመስል ዙፋን በፍጥነት አሰርቶ ጠበቃት፡፡ ተካታዮቼን (41) «ዙፋንዋን ለእርሷ አሳስቱ፡፡ ታውቀው እንደኾነ ወይም ከእነዚያ ከማያውቁት ትኾን እንደሆነ፣ እናያለን፤» አላቸው፡፡ (42) ንግስተ ሳባም በመጣች ጊዜ፦ ተመሳስሎ የተሰራውን ዙፋን አሳይተዋት «ዙፋንሽ እንደዚህ ነውን?» ተባለች፡፡ ንግስተ ሳባም አይታና ዳብሳ «እርሱ ልክ እራሱ ነው መሰለኝ፤» አለች፡፡ (ሰለሞንም ይህ የውሸት ዙፋን እንደሆነ አሳያትና የምታየውንና የምትዳብሰውን ሳይሆን ከስሜት ህዋሳት በላይ የሆነውን ኤሎሂ እንድታምን ነገራት፤) እናም አላት «ከእርሷ ቀድመን ዕውቀት የተሰጠን አማኞች ነንና፤» (አለ)፡፡ (43) ከአንድ አምላክ ሌላ ትገዛው የነበረችውንም ፀሐይ እንዳታመልክ ከለከላት፡፡ እርሷ ከከሓዲዎች ሕዝቦች ነበረችና፡፡ ቀጥሎም በንፁህ መስታወት ወለልና ግድግዳውን ባስገነባው (44) ሕንጻውን ግቢ ተባለች፡፡ ባየቻውም ጊዜ ባሕር ነው ብላ ጠረጠረች፡፡ ከባቶችዋም ገለጠች (ልብሷንም አውልቃ ለመታጠብና ለመዋኘት ሞከረች)፡፡ «ሰለሞንም ከመስተዋት የተለሰለሰ*

ሕንጸ ነው» አላት፡፡ (በስተመጨረሻም) «ጌታዬ ሆይ! እኔ ነፍሴን በደልኩ (ባለማመንና እስየኤልን በመግደል)፡፡ ከሰለሞንም ጋር ሆኜ ለዓለማት ጌታ ለአሎሄ ታዘዝኩኝ» አለች፡፡"

ብሎ የእንቆቅልሾቹን ምንነት እና እንዴት እንደፈታላት ያሜውተናል፡፡ ይህም በሚታይና በሚሞቅ ፀሐይ ታምን የነበረችውን ንግስተ ሳባ በማይታይና ከስሜት ህዋሳት በሙሉ በላቀው ቅዱስ አምላክ እንድታምን ያስተማረበት መንገድ ነው፡፡ ታዲያ በዚህ ሁኔታ ከሰለሞን ጋር የተገናኘችው ንግስተ ሳባ ከእሱ ዘንድ ለመቆየት ወሰነች፡፡ በቆይታዋ ወቅትም በጥቁርነቷ ምክንያት ሌሎቹ የሰለሞን ሚስቶችና እቁባቶች በልዩ አይን ይመለከቷት ስለነበር፤ ቀድሞም ለእስያኤል ዘማሪ ሆና በዜማ ያደገችው ዜመኛዋ ንግስተ ሳባ በመኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ምዕራፍ 1 ቁጥር 5 እና 6 እንደተፃፈው እንዲህ ስትል አዜመች፤ ‹‹(5፤) እናንተ የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት ሆይ፥ እኔ ጥቁር ነኝ፤ ነገር ግን ውብ ነኝ፥ እንደ ቄዳር ድንኳኖች እንደ ሰሎሞንም መጋረጃዎች። (6፤) ፀሐይ መልኬን አከስሎታልና፤ ጥቁር ስለ ሆንሁ አትዩኝ፤ የእናቴ ልጆች ተጣሉኝ፥ የወይን ቦታዎችንም ጠባቂ አደረጉኝ፤ ነገር ግን የእኔን ወይን ቦታ አልጠበቅሁም።

ሰለሞን ግን በጣም ይወዳት ነበርና በሚስትነት አግብቷት ለተወሰኑ ጊዜያት አብራው እንድትቆይ አደረጋት፡፡ ልጅም አርግዛለት ቀዳማዊ ምኒልክን ወለደች፡፡ ልጁ ከበረታላት በኋላ የፀሐይ አምልኮን ለመቃወምና ወደሀገሯ ኢትዮጵያ መሄድ ነበረባት፡፡ በአንድ አምላክ ያምን የነበረው ቀደምት አባቷንም ለመዘከር ኢትያኤል ንግስት ሳባ ተብላ ነግሳ እንዳዲስ የኢትዮጵያን ክብር ለመመለስ አቅዳ ነበር የተጓዘችው፡፡... ሳባ በርሃ አቋርጣ ወደ ኢትዮጵያ በምትመለስበት ሰዓት ጠቢቡ ሰለሞን ህልም አለመ፡፡ ፀሐይ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ቦግ እልም ስትልና ኢትያኤልን የብርሃን አምድ በየደረሰችበት ሁሉ ሲከተላት፤ ባረፈችበት ስፍራ ሁሉ የብርሃን ድንኳን ሆኖ ሲያስጠልላትና ሲያደምቅላት ተመለከተ፡፡ ሕልሙንም ሲተረጉመው የመንግስቱ ዝናና ክብር ከሱ ተነጥሎ ወደ ኢትዮጵያ እንደ ሸሸ ተገነዘበ፡፡ የእስራኤል አለኝታና ክብር የነበረችውም ታቦተ-ጽዮን ከእስራኤል ላይ አፈትልካ እንዳመለጠችው ተረዳ፡፡ በመኃልይ በመኃልይ ድርሳኑም እንዲህ ሲል አንጎራጎረ፡፡ መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ምዕራፍ 3 ላይ... (6፡) መዓዛዋ እንደ ከርቤና እንደ ዕጣን የሆነችው፥ ከልዩ ከነጋዴ ቅመም ሁሉ የሆነችው፥ይህች ከምድረ በዳ እንደ ጢስ ምሰሶ የወጣችው ማን ናት? (7፤) እነሆ፥ የሰሎሞን አልጋ ናት፡ከእስራኤል ኃያላን ስድሳ ኃያላን በዙሪያው

ናቸው። (8፤) ሁሉም ሰይፍ የያዙ ሰልፈኞች ናቸው፤በሌሊት ከሚወድቀው ፍርሃት የተነሣሰው ሁሉ ሰይፉ በወገቡ አለ።"

እዚህ ላይ ‹‹ኃያላን›› በማለት የሚጠቅሳቸው ልጁ ምኒልክ ካደገ በኋላ አባቱ ዘንድ ከርሞ ከእየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ፅላቱን ይዞ ሲመለስ የሚያጅቡትን 40.000 ነገደ እስራኤላውያን ወታደሮች፣ ካህናትና ዘማሪያን ናቸው:: ‹‹የሰሎሞን አልጋ›› የሚለውም ፍቺ ከኢትያኤል ንግስተ ሳባ የተወለደው ልጅ የስርው መንግስት ዙፋኑን በኢትዮጵያ እንደሚመሰርት ይተነበያል::"

"ኢያዳመጣችሁኝ ነው አይደል ልጆች?" አሉ ሼህ ከድር፣

"አ…ዎ…" አሉ እነኢትኤል፣ ሁሉም ላይ የመድከምና የመሰልቸት ምልከት ይነበባል::

"አይዟችሁ፣ በአላህ ፍቃድ 3ቱንም ታሪኮችን ልናገባድድ ነው:: እንግዲህ የዚህ የሦስተኛውን ታሪክ መልዕክት በደንብ እንድትይዙት ዘንዳ ላስታውሳችሁ:: ይህ ታሪክ ከዚያ ከምድር ነገስታት ሁሉ ቁንጮ ከነበርንበት ለምን እንደወረድን አመላካች ሲሆን በሌላ በኩል እንደንግስተ ሳባ ኢትያኤል ከስህተታችን ተመልሰን በኢትዮጵያ አምላክ ካመንን ፈጣሪያችን ሊታረቀንና ጨምሮ ሊለግሰን ዝግጁ እንደሆነ ይጠቁማል:: እርግጥ ነው የንግስተ ሳባ ኢትያኤል ልጅ ቀዳማዊ ምኒሊክ ከእየሩሳሌም ይዟቸው በመጣውና አግዓዚ ወይም ነፃ አውጪ ብሎ በሰየማቸው የአባቱ ዘመዶች በኢትዮጵያ የነበረውን የፀሐይ አምልኮ ስርዓት መደምሰስና የአባቱን ሰለምናዊ ስርዓት ማንገሱ ጥሩ ተግባር ቢሆንም በስሜታዊነት ባቃጠላቸው ቤተ-ከህነቶችና ደብሮች ውስጥ እጅግ በርካታ የእነዮቶር-አብና እስያኤል መለኮታዊ ፀሁፎች፣ ቅርሶችና የጥበብ ውጤቶችን አብሮ በማጥፋቱ ታላቅ ስህተትን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አስቀምጧል:: በተመሳሳይም በኢትዮጵያ ምድር ላይ የተፈራረቁት ታላላቅ ነገስታት ከልማታቸው እኩል ጥፋታቸውም እየበረታ ኢትዮጵያን አሁን ላለችበት ደረጃ አድርሰዋታል:: በእርግጥ ከአፄ ቴዎድሮስ ዳግማዊ በኋላ የኢትዮጵያ አንድነት የወለደው ታላቅነቷ እየተመለሰ መስሎ እስከመጨረሻዊው ሰለምናዊ ንጉስ ቀዳማዊ ሐይለስላሴ ቢቀጥልም፣ ከጥንቱ የነዮቶር ስልጣኔያችን በተለየ መልኩ የፊውዳሊስት አገዛዝን በማራመዱ እኩል ተጠቃሚነትን አላረጋገጠም ነበር:: ይባስ ብሎም ደርግ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስትና ፸6 የሃገር አባቶችን በመረሸን አሳዛኝ አፈፃፀም እንዲኖረው ሆኗል:: ይህ የደርግ ስርዓት የፈጠረው ጨፍልቆ አንድ የማድረግ ስርዓትም በብሔር የመደራጀትን ነገር አስከትሎ ይኸው አሁን በዘርና ጎሣ የምንነቋቆርበት ዘመን ላይ ደርሰናል:: ነገር ግን ከቅርንጫፉ አልፎ የግንዱ ስር

ቢመረመር ሰራችን ተመዞ አንድ አባት በስመ ከሀንቱ ኤቶዮጵ የታባለው ኢትኤል ጋር ይወስደናል፡፡ በዘመናት ሂደትም ተዋደንና ተዋልደን ድብልቅልቅ ያሉ፣ እንደ ነብር ቆዳ የተዥጎረጎርን ቀይ፣ ጥቁር፣ የቀይ ዳማ፣ ጠይም ሃበሾች ተብለናል፡፡ እንኳንስ አባታችን አንድ ሆኖ ዘራችን ቢለያይ እንኳን እየሱስ ክርስቶስም የሚጠየፈው ነብዩ ሙሐመድም ደደብነት ነው ካሉት በዘር የመወገን ልማዳችን መላቀቅ አለብን፡፡ አሁን ደግሞ በዚህ አብይ ትውልድ ታላቅ መነቃቃትና የእውቀትና ፍቅር መብራትን እያየን ስለሆነ ለበጎ ራዕዩ እኛም በዱዓ ከጎናችሁ እንቆማለን፡፡" አሉና በትራቸውን ደገፍ ብለው ሲቆሙ ሁሉም ተከትለዋቸው ቆሙ፡፡

"እንግዲህ ልጆቼ ከእኔ ዘንድ ልትማሩ የሚገባውን እንዲህ ፈፀሚያለሁኝ፡፡ አላህ ካለ ሌላ ጊዜ ሌላ ትምህርት ላይ እንገናኛለን፡፡ ስራችንን ሁሉ ፈጣሪ እንዲወድልንና ሃገራችንን ሰላም እንዲያደርግልን አል-ራህማንን እንለምዋለን"

ሲሉ ሁሉም ደረሳዎች ተቀብለዋቸው ‹‹አሚን›› አሉ፡፡

"እንግዲህ እናንተንም ከዚህች ከቁራኒ በስተሰሜን ወደምትገኝ ኦሮሞ ወደ ምትባል ቦታ እመራችኋለሁኝ፡፡ በዚያም ስትደርሱ አቦ አራርሳ የሚባሉ አባትን ታገኛላችሁ፡፡. እርሳቸውም ሦስት አጫጭር መግለጫዎችን ይሰጧችኋል፡፡ እኔ እንግዲህ ሃላፊነቴን እዚህ ላይ ጨርሻለሁኝ!" አሉና ባላ ዱላቸውን ከፍ አድርገው አንዴ መሬቱን ደለቁትና ዞረው ወደ ማዶ ካለው ኮረብታ አቅጣጫ ተጓዙ፡፡

"በቃ ሸከፋችሁን እናውጣላችሁና ሂዱ፤ ከእዚህ እስከገራዶ እኔ አደርሳችሁና ከዚያ ወደ መርሳ ቀጥሎም ኦሮሞ ወደሚባለው አካባቢ በመኪና ትሄዳላችሁ፡፡" አለ ጃዕፈር ለደቂቃዎች ዝም ብለው ከተቀመጡ በኋላ፡፡ ሁሉም ተራ በተራ ተነሱና ወደዋሻው ገብተው ቦርሳዎቻቸውን ይዘው ወጡ፤ ዘይኔ ግን ከቦታው አልተነሳም ነበር፡፡

"ምነው ዘይኔ ተነስ እንሂድ እንጂ?" አለ ኢትኤል ወደ'ሱ መጥቶ፤

"እኔ አልሄድም ኢትኤል፡፡" አለ ዘይኔ እንዳጎነበሰ፤

"ምን ማለት ነው?" አለ ዮሴፍ ግራ እየተገባ፤

"ስለህይወት ትርጉምና ስለማንነቴ፣ ሃይማኖቴና ሃገሬ ያላወቅሁት ገና ብዙ ሚስጥር እንዳለ እየተሰማኝ ስለሆነ እዚህ ቆይቼ ከእነዚህ ልጆች ጋር፣ ከዚህ የአላህ ወልይ እግር ስር እውቀትን መማር እንዳለብኝ ወስኛለሁኝ፡፡" አለ ዘይኔ ቆፍጠን ብሎ፡፡ አብሯቸው እንዲሄድ ለማስማማት ቢሉት ቢሰሩት እሱ ግን ወይ ፍንክች አለ፡፡ ውሳኔውን ቀድሞ አፅንቶት ነበርና እንቢ አላቸው፡፡ አማራጭ እንደሌላቸው ሲያውቁ ሁሉም ተራ በተራ እያቀፉ ተሰናበቱት፡፡ የብዙ ዓመት ጓደኛቸውን በመለየታቸው እያዘኑ ከጃዕፈር ጋር ለጉዞ ተነሱ፡፡

*** ☥ – ☥ ***

*"በፋርስ ምንጣፉ ላይ በደረቱ የተኛው ፓናሶኒክ ቴፕ ምንኛ ታድሏል አልኩኝ - ለራሴ:: የሺህ ሊደም ደርቃ ጥዑም መንዙማ ለጥ ባለመሬት ላይ እንደሚወርድ የወንዝ ውሃ በእርጋታ ይፈስበታል፤ ያምማል፣ ይህ ወደነፍሲ የሚገማሸር ይህ እፁብ ዜማ ምን እያደረገኝ ነው፤ ተአምር በሚመስለው ተዓምርም በሚያከለው የነፍስ ዝማሬ ስጋዬም ነፍስ የሆነች ያህል ተሰማኝ! በረታሁ::*

*"ዓይን እንባ ነው እንጂ ደም አይደባልቅም፤*
*ጥርስ ወረተኛ ነው ወዳጁን አያውቅም*
*እኔስ ብዬ ነበር ተመልሶ አይስቅም::"*

(ፏስተቴ፣ በዶ/ር ዐብይ አህመድ፣ ምዕራፍ አንድ ገፅ 6")

*** ☥ – ☥ ***

"ውዱ ባለቤቴ አትበቀይልኝም ያለኝንማ እበቀልለታለሁኝ!!" አሉ ወ/ሮ ቤዛዊት ከልጃቸው ፅዮን ጋር ወደ ቡታጅራ መስመር የሙት መንፈስ ይጠራል ወደተባለው ደብተራ እየተጓዙ ሳለ:: ፅዮን ደግሞ በስልክ በሰማችው ነገር ውስጧ እርብሽብሽ ብሎ ፈዛለች:: ሐረ-ሸይጣን የሚባለው ሃይቅ ጋር እስከትደርስ ድረስ አንድም ቃል አልተነፈሰችም ነበር::

ይህ በስልጤ ዞን የሚገኝ ሀረ-ሸይጣን ሃይቅ በቀን ውስጥ ብዙ አይነት ቀለሞችን የሚቀይር ምትሃተኛ ሃይቅ ሲሆን የቀዬው ሰው በውስጡ ኤጋንንቶች አሉበት ብሎ ስለሚያምን ለዋናም ሆነ ለሌላ አገልግሎት ሃይቁን አይጠቀመውም:: አንዳንድ ቀናት ላይ ግን ቆሸሽ ያለ ጥቁር ቀሚስ ለብሰው ትልቅ መፅሐፍ የሚገልጡ ሽማግሌ ሰው ሲዋኙበት ይስተዋላሉ:: እኚህ ሰው ዛሬም ከቦታው ላይ ቆመው እነወ/ሮ ቤዛዊትን ከባለቤታቸው ሙት መንፈስ ለማገናኘት አቅደዋል:: ይህንም የሚያደርጉት ወ/ሮ ቤዛዊት ቤታቸው ውስጥ ያለውን አንዳችም እቃ ሳይቀር ሸጠው፣ ተለቅተው ተበድረው ያገኟትን 3000 ብር ስለሰጧቸው ነው:: ቅድሚያ ኤጋንንቶቹ ምንም ያህል እነርሱን ለማሳቅ ቢለፉ እነሱ ግን እንዳይስቁ ወ/ሮ ቤዛዊትንና ፅዮንን አስጠነቀቋቸው:: ድንገት ተሳስተው ከሳቁም ኤጋንንቶቹ አጠናግረው እንደሚያስቀሯቸው ነገሯቸውና ወደ አኑብንቧቸው ገቡ::

"ወ ዓውደ-ነገስት መስጥመ አጋንንት ወ ሙት መንፈስ ጸሎት በእንተ መሥጠመ ወአጋንንት ወሰይጣን ባሪያ ወሌጊዎን ጀን ወደባስ ደስከ ወጉዳሌ ዛር ወመጋኛ ወሾተላይ፤ ንዳድ ወመንሾ ምትሓት ወጽፍዓት፣ ጉስማት ወፍርቃቃት፤ ውጋት ወሰቅሰቃት:: ኤልከሻከሻ ወተልካሻ ቡዳ ወቂመኛ፣ ወመታዘል ወቡዳ ትከሻ፤ ወከከቡኒ አማድር ጨተታ ኩኩታኤል ጨትኩታኤል ሸተኩታኤል ትትኩታኤል ጀትኤል ዠትኩኤል ኩታታኤል ሊ ሊ ሊ፣ ሚ ሚ ሚ፣ ሯ ሯ ሯ፣ ሏ ሏ ሏ፣ ፏ ፏ ፏ፣ ሸ ሸ ሸ፡ ኸ ኸ ኸ፡ ጄ ጄ ጄ በኃይለ ዝንቱ አስማት አድኅነ ለእመትከ!!" እያሉ የተለያዩ ቃላትን ሲያንጸረጽሩ ከመቅፀበት የወ/ሮ ቤዛዊትና ፅዮን አይን እያየ ሐይቁ ወደደም ቀይነት ቀለም ተቀየረ::

ወዲያውም ደብተራው ድምፁን ከፍ አድርጎ መጣራት ጀመረ::

"በእናት አባቶቼ ላይ የሰፈራችሁ ጋኔሎች፣ በእኔም ላይ የነገሳችሁ አለቆቼ አሁንም እንደበፊቱ የእናንተን እርዳታ እሻለሁኝና ተገለጡልኝ:: ወአምተ ስባተ ለዲያቢሎ ኩሉ መናፍስቲን አዱ ወ ሰብአ ምስለ ሰለሞን ለባቢሎን ይስራኡ..." እያለም ማነብነቡን ቀጠለ:: ከአፍታ በኋላ ከወደሀይቁ መሃል ላይ ከብ ከብ የውሃ ቅርፆች ሲፈጠሩ ተስተዋለ:: ቀጥሎም የብዙ ሰዎችን ጫጫታ የመሰለ ድምፅ በአካባቢው መሰማት ጀመረ::

የመጀመሪያው አጋንንት ከውሃው ብቅ ሲል ፅዮን አይኖቿን ማመን ከብዷት በተደጋጋሚ አይኖቿን እየጨፈነች ከፈተቻቸው:: በተለምዶ ቆንጆ የምንለው ገፅታ ያለው ባለሉጫ ፀጉር፣ ቀይ፣ ሰውነቱ በሙሉ ወዝ በወዝ ሆኖ የሚያብለጨልጭ ዘንካታ ወጣት እርቃኑን ከውሃው ወጣ:: እሱን ተከትላ የወጣችው ደግሞ ውበቷ አይንን የሚያንጠባርር እርቃን ወጣት ሴት ነበረች:: ከዚያም ሌሎች ከኋላቸው ተከታትለው ወጡ:: ከእነርሱ በኋላ ግን በራሱ ላይ አብረቅራቂ ዘውድ የደፋ፤ ደረቱ ላይ የተወሰኑ ኒሻኖችን የደረደረ ጎልማሳ ንጉሳቸው ከሃይቁ ወጣ፤ ተከትለውትም ጎሽ ጎሽ የሚያካክሉ፣ እጆቻቸው እየጠበቡ... እየጠበቡ ሄደው ወደጎራዴነት የሚቀየሩ፤ ሁለት ግድንግድ ጠባቂዎቹ ወጡ::

ሁሉም በሰው ቅርጽ የተገለጡ አጋንንት እያሽካኩ፣ ፈሳቸውንም እያንዛረጡ በጨረፍታ ወ/ሮ ቤዛዊትንና ፅዮንን ያያሉ:: ወ/ሮ ቤዛዊት ሳያስቡት ሳቃቸው ቢመጣም እንደምንም ተቆጣጠሩት:: የችግርና ፈተና በትር የበዛባት ፅዮን ግን እንኳንስ ሳቋ ሊመጣ እየሆነ ያለውንም የምትከታተለው እንደሀልም ባለሁናቴ ውስጥ ነበር::

"አንተ ባሪያችን" አለ ወደ ሽማግሌው ደብተራ እየቀረበ፤ "ግብርህን ለማስገባት ትሰንፋለህ ለጥቅምህ ጊዜ ግን ትፈልገናለኸን?" አለ ዘውድ የደፋው ጋኔል፤

"ይቅርታዎን እከጅላለሁኝ የተከበሩ አለቃዬ፤ ከአሁን በኋላ ከበፊቱ በላቀ እንደማስገባም ቃሌን እሰጣለሁኝ!" አለ ደብተራው ሽብረክ ብሎ እጅ እየነሳ፤

"ዛሬ ደግሞ የባልና የአባታቸውን የሙት መንፈስ መገናኘት የሚፈልጉ እናትና ልጅ ይዘኸልኝ መጣህ::" አለ ወደ እነፅዮን ዞሮ፤

"አዎን አዎን ጌታዬ... እንዴት አወቁሳ?!" አለ ደብተራው በአድናቆት፤

ዘውድ የደፋው ጋኔል በኩራት "ከእኔ ከመቶ ጋኔሎች አለቃ ከሱቃኤል ምን የሚደበቅ ነገር ይኖርና!" አለና ወ/ሮ ቤዛዊትንና ፅዮንን ትክ ብሎ አያቸው::

"የጋሽ ጀንበሬ መንፈስ ማነጋገር የሚሻው ልጁን ብቻ ስለሆነ እናቲቱ ይጠብቁኛል::" አለና ሱቃኤል የፅዮንን እጆች አፈፍ አድርጎ ወደ ሐይቁ አቅጣጫ ወሰዳት:: ወ/ሮ ቤዛዊት ለመከተል ቢሞክሩም ደብተራው ከኋላ ይዞ አስቀራቸው:: ሐይቁ ዳርቻ እንደደረሱ ሱቃኤል ፅዮንን በሁለት እጆቹ ጭምቅ አድርጎ ይዞ...

"እኔ ሱቃኤል ነኝ፤ የሰው ልጆችን ስቃይ የማበዛ ጋኔል:: አንቺንም ወደእኔ እንድትመጪ በኑሮሽ፣ በጓደኛ፣ በትምህርትሽ ላይ መሰናክል እየፈጠርኩኝ ይኸው ዛሬ በእግዚአብሔር ተስፋ እንድትቆርጪ አድርጌሽ ወደ እኔ መጥተሻልና ነይ ልቀፍሽ..." ብሎ ጎተት አድርጎ አቀፋት:: ፅዮን በደም ስሯ ውስጥ አንዳች ነገር ሲሰርፅና ማንነቷን ቀስ በቀስ ሲቆጣጠረው ይታወቃት ነበር:: ከስርም ወደ ውሃው እየሰመጠች እንደሆነ በብዥታ ጠርጥራለች::

የልጃቸውን ወደ ሐይቁ መግባት ያዩት ወ/ሮ ቤዛዊት ከደብተራው እጅ ላይ ምንጭቅ አድርገው አምልጠው ወደሐይቁ ተንደረደሩ:: ነገር ግን ከሱቃኤል ጠባቂ ጎሽ መሳይ ሰዎች አንዱ የዛር ሰበቃ ለቀቀባቸውና ራሳቸውን ስተው ከመሬት ተዘረሩ:: ከሰዓታት በኋላ ሲነቁ ልጃቸውንም ይሁን ደብተራውን በቦታው አላገኙም ነበር::

*** ፶ – ፶ ***

# ምዕራፍ ፱ - ◚ ጥቁር- አከሱም ◚

## መዝሙረ ዳዊት - ምዕራፍ 2

"1፤ አህዛብ ለምን ያጉረመርማሉ? ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ?
2፤ የምድር ነገሥታት ተነሡ፥ አለቆችም በእግዚአብሔር መሢሕ ላይ እንዲህ ሲሉ ተማከሩ::
3፤ ማሰርያቸውን እንበጥስ፥ ገመዳቸውንም ከእኛ እንጣል::
4፤ በሰማይ የሚኖር እርሱ ይሥቃል፥ ጌታም ይሣለቅባቸዋል::
5፤ በዚያን ጊዜ በቁጣው ይናገራቸዋል፥ በመዓቱም ያውካቸዋል::
6፤ እኔ ግን በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ ንጉሴን ሾምሁኝ::
7፤ ትእዛዙን እናገራለሁ፤ እግዚአብሔር አለኝ:: አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁ::
8፤ ለምነኝ፥ አሕዛብን ለርስትህ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ::
9፤ በብረት በትር ትጠብቃቸዋለህ፥ እንደ ሸክላ ሠሪ ዕቃዎች ትቀጠቅጣቸዋለህ::
10፤ አሁንም እናንተ ነገሥታት፥ ልብ አድርጉ፤ እናንተ የምድር ፈራጆችም ተገሰፁ::
11፤ ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተገዙ፥ በረዓድም ደስ ይበላችሁ::
12፤ ተግሳጹን ተቀበሉ ጌታ እንዳይቆጣ እናንተም ከመንገድ እንዳትጠፉ፤ ቁጣው ፈጥና ትነድዳለችና:: በእርሱ የታመኑ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው::"

*** ቶ – ቶ ***

**"የወልይ ልጅ ወልይ፣ የጀግና ጀግና ነው**
**እኛ እንኳን ባንቀምሰው በሌላው አየነው፥**
**በልተው እየጠጡ ጅስማቸው ቀጭን ነው**
**ወትሮም ደጎና ኀበዝ አካለ ቀጭን ነው…**
**ተፈሪ የማይወፍር ሐሳብ በዝቶበት ነው::"**

(ሼኽ ሁሴን ጅብሪል)

*** ቶ – ቶ ***

"ንግስት ዘውዲቱ ለተፈሪ መኮንን መንገዱን ጠርጋለት እስከ አለተ-ሞቷ፣ እስከ 1923 ዓ.ም ድረስ በሰለሞናዊው ዙፋን ላይ ቆየችና ልክ እርሷ ስታርፍ ልዑል አሊጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን «ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ፣ በእግዚአብሔር የተመረጠ አሸናፊው የይሁዳ አንበሳ» ተብሎ ነገሰ:: 44 አመታትን ከገዛ በኋላ በ1967 ዓ.ም በህዝባዊ አብዮት ከስልጣን ተወግዶ የመጨረሻው የሰለሞን (የአግአዚ/ አርሞ) ሥርወ መንግስት ንጉሰ ነገስት ሆነ:: ኃይለ ስላሴ ባመዛኙ አሮሞ ነው:: እናቱ የሺህ እመቤት አሊ ጋምጮ በአባቷ በኩል የወረሂመኑ አሮሞ ናት:: በአዲስ ግኝት መሰረትም የሷም እናት ይብረሁልሽ በስልጤ-ጉራጌ እናቷ «ቂቶ» ትባል የነበረችው ወለተ-ጊዮርጊስ የወሎው አሮሞ ወልይ ሼህ ሁሴን ጅብሪል ልጅ ናት...::" ስለዚህም ሼህ ሁሴን ጅብሪል የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ቅድመ አያት ናቸው ማለት ነው::

*(የኦሮሞና አማራ እውነተኛ የዘር ምንጭ፣ በፕ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ፤ ክፍል-3፣ ገጽ 241)*

*** ☥ – ☥ ***

"ከአውሮፓ ስለሚጣልብን ማዕቀብ እኛ ቁብ አንሰጠውም! ወትሮም እኛ አውሮፓውያኖች አይደለንም:: ከእነርሱ ግዛትም አንድ ኢንች አንጠይቅም:: ስለዚህ ብሌር አንተም የራስህን ብሪቴን ጠብቅ፤ እኔም የራሴን ዚንባብዌ እጠብቃለሁኝ::

እኛ (አፍሪካውያን) ነፃ ሰዎች ነን:: ራሳችንን የቻልንም 54 ሀገሮች ስለሆንን ነፃነታችን እንፈልገዋለን... ሚስተር ባንኪሞን! እኛ ነፃ ሀገር ነን ብለን በየዓመቱ መስከረም ወር የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እየሄድን እንሰበሰባለን:: እዚያ ድረስ ለመሄድም ብዙ ገንዘብ እናጠፋለን:: ከአመት አመት ለጠቅላላው ኮሚቴ ንግግር አድርገን ወደ ቤት እንመለሳለን:: ግን በፀጥታው ምክር ቤት ያሉ ጉልቤ ጌቶች በቋሚ አባልነት እኛ ያለንን ስልጣን ያህል አይኖራችሁም ይሉናል:: እኛ ግን ዴጋግመን እንጠይቃለን!... እንጠይቃለን!... እንጠይቃለን!... የጸጥታው ምክር ቤት እንደገና ይዋቀር! ይሻሻል!... የጸጥታው ምክር ቤት ይለወጥ:: (ጭብጨባ)

እኔ ልነግርህ የምፈልገው ነገር አቶ ባንኪሞን.. አንተ በግልህ ጥሩ ሰው ነህ:: በእርግጥ ያንተ ሃላፊነት ባይሆንም ተዋጊያችን ልናደርግህ ግን እንሻለን:: ለማንነታችን፣ ለአፍሪካዊነታችን፣ ለሰብዕናችን እንታገላለን:: እኛ አፍሪካውያኖች ነን:: ግን እኛ እውነተኛ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባላት አይደለንም! የይምሰል አባላት ነን:: የይምሰል አባላት ሆነን ደግሞ መቀጠል አንፈልግም:: የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እንዲቀጥል ከተፈለገ ሁላችንም እኩል አባል መሆን አለብን:: እንደ እውነተኛ አባላት የሚደመጥና የሚከበር ድምፅ ሊኖረን ይገባል:: ከ54 የአፍሪካ ሃገራት ሁለት እንኳን ቋሚ አባላት እንዲኖሩ ለምን አይደረግም? **እኛም እንደነርሱ ሰዎች እንደሆንን ንገራቸው ሚስተር ባንኪሞን! መናፍስት እንዳልሆንን ንገራቸው! እኛም የዓለም አባል ነን፤ የዓለም አካል የሆነችው የአፍሪካ ልጆች ነን"...**

*( ሮበርት ሙጋቤ)*

***ቶ - ቶ***

*የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንትና የነፃነት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላ «A-Long Walk to Freedom>>በተሰኘው መፅሐፋቸው ላይ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘንድ ለጦር ስልጠና በመጡ ጊዜ የነበረውን ሁኔታ እንደሚከተለው ዘግበውታል፤*

*… (( "We then flew on to the conference in Addis Ababa on Ethiopians Airlines. As I was boarding the plane, I noticed that the pilot was black. I panicked – how can a black man fly a plane? A moment later, I felt angry with my self – I had fallen into the apartheid trap of believing that blacks were not as good as whites *** The conference was opened by Haile Selassie, The Emperor of Ethiopia and the Great* **Lion of Judah.** *In my speech at the conference, I spoke about the oppression of my people. I explained how all peaceful means of struggle had been closed to us and we had no choice but to form Umkhonto we Sizwe. *** … (P, 59)*

*After London, I left for the last leg of my trip – back to Addis Ababa. I had arranged to spend six months there getting military training.*

*I was taken to a suburb called Ko[illegible] where I met the man who was to train me. His name was Lieutenant Wondoni Befikadu, (Under the command of General Tadesse Biru) He was an experienced soldier who had fought underground against the Italians.*

*It was tough. We trained from 8 A.M to 1 P.M, broke for a shower and lunch. And trained again from 2 P.M to 4 P.M, After that we were given lectures on military science. I learned how to use an automatic rifle and pistol, and how to make small bombs and mines. What I enjoyed most were the "fatigue marches". We were given only bullets & a gun, and told to get to a certain place by a certain time.*

*The training course was supposed to last for six months, but after only eight weeks I got a telegram from the ANC. They told me it was time to come home. The armed struggle was taking off the commander of MK was needed.*

*I flew to Khartoum, and then on to Dares Salam (Yeselam Dar). There I met the first group of MK recruits who were on their way to Ethiopia for training. It was the first time that I was ever saluted by my own soldiers. It was a proud moment. ))*

*"መንፈሳዊነት ከሃይማኖት አይመጣም፡፡ መንፈሳዊነት የሚመጣው ከነፍሳችን ውስጥ ነው፡፡ ሃይማኖትንና መንፈሳዊነትን አንቀላቅል፡፡ ሃይማኖት ማለት መንፈሳዊነትን ለማጠናከር ለሰዎች የተፈጠረ ህግና ስርዓት ነው፡፡…*
*…መንፈሳዊነት ማለትም የርዕዮተ ዓለም አመለካከት አሊያም ስለአምላክ የሚያጠና የዕውቀት ዘርፍ አይደለም! መንፈሳዊነት ማለት ንፁህና በተፈጥሮ የሚቸረን የህይወት መንገድ ነው፡፡ መንፈሳዊነት በሰማየ ሰማያት ካለው የበላይ ሃይል፣ ጠፈር ጋር እንዲሁም እርስበርሳችን የሚያቆራኘን መረብ ነው!"*

*(ሞሐ አንበሳ ዘ እምነ ነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ!)*

*** ዮ - ዮ **

እነኢትኤል ዘይኔን ተሰናብተው በጃዕፈር አጃቢነት ከመንደሯ ወጡ። እስከ ገራዶ ድረስ አብሯቸው ከተጓዘ በኋላ ከገራዶ ወደ መርሳ የምትሄድ አንድ ሚኒባስ አሳፈራቸውና ተሰናበታቸው። ኢትኤል፣ ናዖድ፣ አብርሃምና መርየም የኋላ ወንበር ላይ ሲቀመጡ ዮሴፍ ደግሞ ከሦስተኛው ወንበር ጥግ መስታወቱን ተደግፎ ተቀመጠ። ከእሱ ጎን ባለው ባዶ ቦታ ላይ ደግሞ ፀጉሩን ያንዥረገገ አንድ ጎልማሳ ራስታ መጥቶ ተቀመጠ። ኢትኤልና ዮሴፍ ራስታውን ሰው አስተዋሉት። የተንዥረገገው ‹ድሬድ› ፀጉሩ ለማደግ ረጅም አመታትን የፈጀ እንደሆነ ያስታውቃል። የተፍተለተሉት ፂሞቹ እንደፀጉሮቹ መደረድ የፈለጉ ይመስላሉ። ፀጉርና ፂሞቹ ረዣዥም ቢሆኑም በጣም ንፁህ ናቸው። ራስታውም ፅድት ያለ የግርማዊ ጃንሆይ ምስል ያለበት ቲሸረትና ካኪ ቁምጣ ለብሷል። ልዩ መዓዛው ገና መኪናው ውስጥ ከመግባቱ ነበር የሁሉንም ተሳፋሪ አፍንጫ ያወደው። የሰውዬው ሁኔታ ለኢትኤል በልጅነቱ የሚያውቀውን አጎቱን ትውስታ ነበር ያመጣበት።

"ልክ እንዳንተ አይነት ራስታ አጎት ነበረኝ፤" አለው መኪናቸው ጉዞ ከመጀመሩ፤

"ዋው ይገርማል ወንድም… እንደኔ ቀሽት ሌላ ወንድ ያለ አይመስለኝም ነበር፤" አለ ራስታው፤ ሁሉም ገርሟቸው ሳቁ፤

"ላላ በሉ ስቀልድ ነው፤ የወንድ ልጅ ውበት ታጥቦ አይጠጣም። ዋናው ውበቱ ማንነቱን ማወቁና እሱነቱን አውቆ በራስ መተማመን መጓዙ ነው።" ሲል…

"አልገባኝም።" አለ ከአጠገቡ የተቀመጠው ዮሴፍ፤

"የወንድ ልጅ ዋናው ውበቱ በራስ መተማመኑ ነው። በራስ ለመተማመን ደግሞ ማንነትን ጠልቆ መፈተሽ በጣም ፒስ አለው።"

"እኮ ራስን ማወቅ ማለት ምንድነው?" አለ ዮሴፍ፤

"ይነገርሻል... እንድች ብለሽ እንዳታስቢ ማኗ..." አለና ራስታው ወደ ዮሴፍና ኢትኤል ዞሮ ቀጠለ።

"ያንተ ስም ማነው?"

"ዮሴፍ፤" ብሎ መለሰ፤

"እሺ ከስምህ ቀጥሎ ሁሌም ያንተ መገለጫ የሆነው ምንድነው?" ብሎ ጠየቀው፤

"ስራዬ!" አለ ዮሴፍ፤

"አይደለም!"

"የት/ት ደረጃው።" አለ ኢትኤል ከኋላ ጣልቃ ገብቶ፤

"አይደለም!" አለ ራስታው ሰው፤

"እና ንገረና ታዲያ?" አለ ዮሴፍ፤

"ከስምህ ቀጥሎ የምትጠራው የሁልጊዜም የማንነትህ አብነት አባትህ ነው። እናም ማንነትን ማወቅ የቤተሰብህን ብሎም የጥንት አባቶችህን ባህል፣ ወግና ታሪክ ማወቅ ነው። አንተ የሲዳማ ልጅ ከሆንክ ቢያንስ ‹‹ሲዳማ›› የሚለውን ቃል ትርጉም ማወቅ አለብህ። የሆነን ዘር ወግነህ ለፀብና ድጋፍ ከመሰለፍህ በፊት ብሔሬ ነው ስለምትለው ማህብረሰብ እሴት ጠለቅ ያለ እውቀት ማግኘት ይኖርብኻል። ያኔ የማንነትህ ክፍተቶችን የመሙያ አንድ ጥበብን ትቸራለህ። እኔም የምቆምበት መታያ መልኬ፣ የማልከደው ብዙ ብሔሮችን ያቀፈ እውነት ጥቁርነቴ ነው፤ ለዚህ የማንነቴን ትርጉም መብት መጠበቅ እና በውስጡ ያሉ ጥበቦችን ለማውጣት ደግሞ ሃላፊነት ወስጃለሁኝ፣ ይህም የህይወት ግቤ እንደሆነ አምናለሁኝ።"

"እኔ ግን ራስታዎች የጥቁር መብት ተከራካሪዎች አይመስሉኝም ነበር።" አለ ኢትኤል፤

"አሁንም የነገርኩህን ካስተዋልክ ለጥቁርነታችን ትልቅ ዋጋ እንደምንሰጥ ትረዳ ነበር ‹ማን›፤ እኛ ግን በሚገባ ጥቁርነታችንን እንወደዋለን፣ እናከብረዋለን። እርግጥ ብዙሃኑ የዘመኑ ወጣት በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት ጥቁር አፍሪካዊነቱን እንደመረገም ቆጥሮ ይጠላዋል።"

"ልክ እንደ እኔ አይነት ማለት ነው?" አለ ዮሴፍ እየሳቀ፤

"እይ እንዳንተ ሳይሆን እጅግ በሚገርም ሁኔታ ቆዳቸውን ብሊች እያደረጉ በሚካፕ ራሳቸውን ፈረንጅ ለማድረግ የሚጥሩ አንዳንድ ጥቁር አሜሪካውያንን ብታዩ ምን እያወራሁኝ እንደሆነ ይገባችሁ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች አፍሪካ ወለድ ጥቁርነታቸውን የሚጠሉት በቅጡ ስለራሳቸው አውቀው ማንነታቸውን በማይነቃነቅ መሰረት ላይ ስላላቆሙ ብሎም በምዕራባውያን ዘመን አመጣሽ ቴክኖሎጂና የታይታ ኑሮ ውስጥ ጥቁርነት፣ መልከ-ጥፉነት መሆኑን ስለሚሰበኩ ነው፡፡ ይህ የተሳሳተ አስተሳሰብም በእኛ ማህብረሰብ ዘንድም ጠልቆ እየገባ ነው፡፡

በተለይ በአዲስ አበባና በሌሎች ዋና ዋና ከተሞች እንደሚታየው ሁሉ ነገር ምዕራባዊ ሆኗል፡፡ ከካፌ ጀምሮ እስከ ህንፃ ድረስ የሚሰየመው በእነርሱ ቋንቋ ነው፡፡ የልጆችም ስም ሲወጣ የእንግሊዘኛ የስም ማውጫ ‹ግሎሳሪ› ማየት ከተጀመረ ከራረመ፡፡ ታዳጊዎቻችን የራሳቸውን ባህል ዘንግተው በመጤ ውርስ ባህል ‹‹ክሬዚ ዴይ›› እያሉ እብደትን ይለማመዳሉ፣ ‹‹ቤቢስ ዴይ›› እያሉ ሃላፊነት የማይሰማው የጎልማሳ ህፃናት ይሆናሉ፣ የአባቶቻችንን የመረዳዳት ባህል የሚያስተምራቸው ቢያጡ ጎረቤታቸው ያለ ወንድም እህታቸው ሳይበላ እያደረ እነሱ በመቶ ሺህ የሚቆጠር ብር አውጥተው ስዊት 16 ብለው ልደት ያከብራሉ፡፡ ‹‹ሃሎዊን ዴይ›› እያሉ ሴይጣናዊ አልባሳትን ለብሰው በባዕድ ማንነት ሲንከላወሱ ይታያሉ፡፡ ትንሽ አደግ ያሉት ወጣቶችም ‹‹ቫለንታይንስ ዴይ›› በአንድ ነጭ ሰው ስም እልፉን ፍቅር በአንዲት ቀን ሊገድቡት ቀይ ሽብር መስለው ይወጣሉ፤ በእንግሊዝና በስፔን ኳስ ተጫዋቾች የደሞዝ መጠንና የጫማ ቁጥር አዕምሯቸውን ሞልተውት ለህይወታቸው ጠቃሚ የሆኑ እውቀቶችና ጥበቦችን መጫኛ ቦታ ያጣሉ፤ ሺሻ እቃቸውን እንደጣዖት እየወለወሉ ውድ ሳንባና ልባቸውን ግን ያጠቁራሉ፡፡" አለ ራስታው ሁሉንም የሚኒባሷን ተሳፋሪዎች በመሰጠ ንግግር፤ ትንሽ እንደ ተጓዘ ሹፌሩ ከፍቶት ከነበረው ሬዲዮ አቦ ለማ መገርሳ የኦሮምያ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት በአንድ ወቅት ያደረጉት ንግግር እየተደመጠ ነበር፡፡ በመሐልም *"ኢትዮጵያዊነት ምክሬው ባላውቅም፤ ስሙ ባያምርም ሃሺሽ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው፡፡" አሉ አቦ ለማ፤ ሁሉም የታክሲው ተሳፋሪ ወደ ራስታው ሰው ዞረ፡፡*

*** ☥ - ☥ ***

"ግን እኮ ይቅርታ አድርግልኝና እናንተ ራስታዎችም እኮ ሺሻ ታጨሳላችሁ!" አለ ናዖድ፤

"ሃሃ... ‹‹ማን››፤ እኛ ሺሻ አናጨስም:: ሺሻ ማለት አረቦችና አውሮፓውያን ፋብሪካ ውስጥ ቀምመው በአፕልና ሌመን መሰል ቃናዎች ሽታቸው እንዲያውዱ አድርገው የሚያመርቷቸው ተገዝተውም የሺሻ እቃ በሚባል እንደጣዖት አንዴ ከሰል፣ አንዴ ገሰጢር፣ አንዴ መርፌ ስኩ፣ ውሃ ቅዱ ውሃ ድፉ እየተባለ ቀኑን ሙሉ ካላንዳች ስራ ቁጭ አድርጎ የሚያስውል ስራ አስፈቺ ነገር ነው:: ከዚያም በላይ ይህ ሺሻ የምትሉት ነገር ከሲጋራ እጅግ ብዙ እጥፍ ለሳንባ ካንሰርና ለልብ በሽታ የሚያጋልጥ ነው:: ጥሩ ጥሩ እየሸተቱ ስጋንና አዕምሮን አስሮ በዚህም ኑሮን የሚገድል ነገር ነው ሺሻ!"

"አዎ ልክ ነው፤ እኔም ባለፈው አንድ አርቲክል አንብቢያለሁኝ፣ ሺሻ በጣም ከፍተኛ የላንግ ካንሰርና የልብ ድካም በሽታን ያመጣል::" አለች መርየም በራስታው ንግግር ጣልቃ ገብታ::

"በትክክል እህቴ..." አለና ራስታው ቀጠለ "ሲጋራና ሺሻ ለእነዚህ ብቻ ሳይሆን ለእጅግ በርካታ በሽታዎችም ምክንያትም ነው:: በዓለም ላይ ብዙ ሚሊዮን ሰዎች በየዓመቱ እነዚህን ነገሮች በማጨሳቸው ለሞት ይዳረጋሉ::

እኛ ራስታዎች የምናጨሰው ግን ሃሺሽ ማሪዋና ወይም እፀ-ተመስጦ ሲሆን ይህም ዕፅ በተደረገበት ጥናት መሰረት ከቡና ያነሰ ሱስ የማስያዝ አቅምና ከአስፕሪን ያነሰ ‹ቶክሲሲቲ› ያለው ነው:: ይህ ቅጠል በውስጡ የያዘው <THC> የሚባል ንጥረ ነገር እንኳንስ በሽታ ሊያመጣ ይልቁንም ለስኳር፣ ለካንሰር፣ ለኤች አይ ቪ፣ ለማይግሬን እና ለግላውኮማ የሚታዘዝ መድሃኒትና የህመም ማስታገሻ እንዲሁም ጭንቀት ያለባቸውን ሰዎች የሚፈውስ ዕፅ እንደሆነ በወሬ ሳይሆን በሳይንስም የተረጋገጠ ነው:: ብዙ የህክምና ሊቃውንትም ሕጋዊ መድሐኒት እንዲሆን እየታገሉ ነው::

ባይገርማችሁ ይህ ተክል ቅጠሉ ለመድሃኒትነት እንደሚያገለግለው ሁሉ የግንዱ እንጨትም እንደ ገመድ፣ ዘይት፣ ሎሽን፣ የፀጉር ሻምፖና የመሳሰሉትን ምርቶችን ለመስራት የሚያገለግል ሲሆን ለኛ የተከለከለ እፅ ነው ያሉንን ተክል አውሮፓውያኑ ግን የብዙ ሚሊዮን ዶላር ካምፓኒዎችን አቋቁመው እንደሚሰሩ ማንም ሰው ጎግል አድርጎ ማረጋገጥ ይችላል:: እርግጥም አውሮፓዊ ካምፓኒዎች ማሪዋናን እያበቀሉና እያበላሉ ብዙ መገልገያዎችን በማምረት ትርፋማ ቢዝነስ ፈጥረዋል:: የሚያስደንቀው ደግሞ ከማሪዋና እንጨት የሚሰራ ጣውላ የእሳት ቃጠሎ በከፍተኛ ሁኔታ የመቋቋም አቅም አለው:: ለእኛ ግን አሁንም መጥፎ ተክል ነው ብለው ይሰብኩናል::"

"ለምን ይሆን እንደዚያ የሚያደርጉት?" አለ ንግግሩን ተመስጦ ሲያዳምጥ የነበረው ዮሴፍ፤

"እንደዚያ የሚያደርጉትማ ከእነርሱ ቢዝነስ ጋር አብሮ ስለማይሄድ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ቅጠል ከየትኛውም አህጉር በላይ የሚገኘው በኛይቱ አፍሪካ ውስጥ ነው፡፡ ዕፀ-ተመስጦና ዕፀ-መነቃቃት ከምናስበው በላይ ከእኛ ታሪክ ጋር የጠለቀ ቁርኝት አለው፡፡ ‹ማይቲካል ድራግ› ወይም የንጥቀት መድሃኒት እየተባለም ከመንፈሳዊነት ጋር ይያያዛል፡፡ ባይገርማችሁ በጥንት የኩሽ ነገስታት አስከሬኖች ላይ በተሰራው የአውቶፕሲ ምርመራ በሰውነታቸው የዕፀ-ተመስጦ ንጥረ ነገሮች ተገኝተዋል፡፡ ይህም ተክሉ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የአፍሪካ ሃብት እንደሆነ ይመሰክርልናል፡፡ እናም ይህ ተክል ለእኛ ያለውን ጥቅም አወቅን ማለት ለአውሮፓውያኑ ትልቅ ኪሳራ ነው፡፡ የማሪዋና ቢዝነሶቻቸውን ብቻ ሳይሆን የአልኮልና ሲጋራ ቢዝነሳቸውንም እጅግ ይዳከማል፡፡ ይህ ሁሉ ባይሆን እንኳን ሰክሮ የሚጣላና ቁም ነገር የማያስብ ትውልድ እንጂ መርቅና የሚያወሳስብና ጦዞ የእነርሱን ጭንቀት ረስቶ የሚስቅ ትውልድ እንዲፈጠር አይሹምና ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን የደስታ ምንጫችን ሊሆን የሚገባው ይህ መንገድ ነው ለማለት ሳይሆን ስለጠየቅከኝ ጥያቄህን ለመመለስ ያህል ነው፡፡ ማንኛውም በህይወታችን ላይ የሚገጥመን ነገር በራሱ ጥሩም መጥፎም አይደለም፡፡ ፈጣሪም ሁሉንም ነገር ለበጎ አስቦ ነው የፈጠረው፡፡ እኛ ግን በከፋትና በስሜት ግፊት ተመርተን ከፉ እናደርገዋለን፡፡ ለምሳሌ ምግብ ለሰው ልጆች በሙሉ የመኖር አንዱ አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ሁሉም ያውቀዋል፡፡ ነገር ግን ምግብ መብላትን የህይወታችን መመዘኛ አድርገን ሌት ተቀን የምናግበሰብስ ከሆነ እንደምዕራባውያኑ የምግብ ሱሰኞች ሆነን በውፍረት እንዋጥና ልባችንን አፍነን እናሽልባለን፡፡ እንዲሁ ሁሉ በማንኛውም ነገር ላይ ሙሉ ልቦናን መስጠት ታላቅ ጥፋት ነው፡፡ መብላትና መጠጣት፣ መጨስና ማድረግ ጨምሮ ማንኛውንም ነገር በህይወታችን ስናደርግ ለኛ የሚጠቅምና የሚጎዳውን አመዛዝነንና ከነገሩ እኛ ከፍ ብለን እንደ መገልገያ ነው ልናደርግ የሚገባው፡፡ ሌላ ምሳሌ ለመስጠት ያኸል አሁን ፈረንጆቹ ባመጡልን የኑሮ ዘይቤ መሰረት ፋሽን የሚባል ብሂል መጥቷል፡፡ እኛ ግን አንድን ልብስ ወይም ጫማ ልንገዛው የሚገባው ካለን ገንዘብ፣ ከጫማው ምቾትና ዘላቂነት አንፃር እንጂ ላዩ ላይ ከተለጠፈው ማርክ አንፃር አይደለም፡፡"

"እኔ ግን ለነጮች ጥልቅ የሆነ ጥላቻ እንዳለህ እየተረዳሁኝ ነው፤" አለ ኢትኤል፤ ራስታውን ትኩር ብሎ እያየው፤

"ባይገርምህ እኔ ሳልሆን እነርሱ ናቸው አንተንም እኔንም የሚጠሉን:: ምክንያቱም ጥቁሮች ነጮችን በጉልበት እንበልጣቸዋለን ለዚህም የቦክሱንና ሩጫውን አለም ማየቱ በቂ ነው፤ በመዝናኛውም አለም እንበልጣቸዋለን ለዚህም የሙዚቃውን ዓለም ኮከቦች ማስታወስ በቂ ነው፤ በስታይል እንበልጣቸዋለን፣ ድፍረት አይሁንብኝና ለአልጋ ላይ ጨዋታ እንኳን የነጮቹ ሴቶች የሚመርጡት እኛን ጥቁሮቹን ነው..." ሲል ሁሉም የሚኒባሱ ተሳፋሪዎች በሳቅ ፈረሱ::

"አዎ የምሬን እኮ ነው! በነገራችን ላይ እኛን ጥቁር እንድንሆን የሚያደርግን በቆዳችን ስር የሚገኝ ኬሚካል ‹‹ሜላኒን›› ይባላል:: በማሕፀን ውስጥ በሚጀምረው ሰው ልጅ ፅንስ አስተዳደግ ስነ-ፅንስ ወይም ‹‹ኢምብርዮሎጂ›› ይህን ኬሚካል የሚያመነጩት እጢዎች በኋላ አንጎል ከሚሆነው ክፍል ጋር አብረው የሚያድጉ ናቸው:: ለዚህም ነው በሜላኒን የጠቆረን ፀጉር ደርዶ ማሳደግ የቲሌቪዥንን አንቴና እንደመምዘዝ ነው የሚሉት:: ይህም የጥቁሮችና ሌሎች ነብያት ፀጉር ማሳደግ ከሜላኒን ጋር ግንኙነት ለመኖሩ አንድ ማሳያ ነው:: በዚያ ላይ በቆዳችን ስር ተሰራጭቶ ጥቁር የሚያደርገን ኬሚካል የፀሐይን አልትራ ቫዮሌት ጨረር በትነው ስን በርንን ወይም የቆዳ በፀሐይ መቃጠልን እና የቆዳ ካንሰርን እጅግ በጣም ይቀንሱልናል:: ለዚህም ነው ይህ ኬሚካል የሚያንሳቸው ፈረንጆች ውጭ በወጡ ቁጥር ሰን-ስክሪን የሚባል የፀሐይ አንፀባራቂ ክሬም እየተለቀለቁ የሚወጡት፣ ቆዳቸውን ፀሐይ እንዳይጠብሰው::

ሌላው ከዚህ ጋር በስያሜ የሚመሳሰለው **ሜላቶኒን** የሚባለው ንጥረ ነገር ሲሆን ይህ ደግሞ የሚመነጨው ፈረንጆቹ ‹ቴምፖራል› ወይም የቤተ-መቅደስ ክፍል ብለው በሰየሙት የአንጎል ክፍል ውስጥ በሚገኝ ሦስተኛው አይን በሚባለውና በግብፅ ሄሮግሪፎች ላይ ተስሎ ከሚገኘው ‹ፔናይል ግላንድ› ነው:: ይህም ሆርሞን ከጨለማ፣ እንቅልፍና ተመስጦ ጋር ተያይዞ በብዛት የሚመነጭ አስገራሚ ኬሚካል ነው:: 2ኛ ነገስት 8፡12፡13 ላይ ጠቢቡ ሰለሞንም "እግዚአብሔር በጨለማው ውስጥ እኖራለሁ ብሏል፤ እኔም ለዘላለም የምትኖርበት ማደሪያ ቤት በእውነት ሰራሁልህ፤" ብሏልና የዚህ የሜላኒንና የሜላቶኒን ነገር ታላቅ ሚስጥር ያለው ይመስላል::" አለና ራስታው ሰው ሁሉንም ተመለከታቸው፤ ሹፌሩ ሳይቀር ተመስጦ እያዳመጠው ነበር:: በተለይ እነዮሴፍ ከዚህ በፊት ልብ ያላሏቸውን የሳይንስ እውነታዎች እያጣቀሰ ሲያወራ ግራ ተጋብተው ነበር የሚያዳምጡት::

"ደስ ይላል ሃሳብህ... ነገር ግን..." አለ አብርሃም ሁሉም ራስታዎችን ለመቃወሙ ምክንያት የሆነውን ነገር ለመጠየቅ እየዳዳ፤

"አብሽር አትፍራ ጠይቀኝ፤" አለ ራስታው፤

"እይ እናንተ የምተውን ንጉስ ሃይለ ስላሴ አምላክ ነው ብላችሁ የምትቀበሉ ኢሉሚናቲዎች ናችሁ ሲባል ስለምሰማ ነው::" አለ አብርሃም፤

"ይሄ ጥያቄ ብዙ ጊዜ ይቀርብልኛል:: በመጀመሪያ ማወቅ ያለብህ ነገር ሁሉም ራስታ አንድ አይነት እንዳልሆነ ነው:: ከፊሉ ራስታ ሃይለስላሴን እንደ አምላክ፣ ከፊሉ ራስታ ለጥቁር ህዝብ የተገለጠ መሲህ፣ የተቀረነው ደግሞ የጥቁር ህዝብን ነፃ ለማውጣት በእግዚአብሔር የተቀቡ የይሁዳ አንበሳ ንጉስ-ነገስት እንደሆኑ ያምናል:: እንግዲህ ሁሉም ታሪክ የሚጀምረው አንድ ማርከስ ጋርቬይ የተባለ እ.አ.አ በ1887 ዓ.ም በጃማይካ የተወለደ፤ ምሁር፣ የጥቁር መብት ታጋይና ባለራዕይ ነበር:: አፍሪካውያን ባሪያዎች በአሜሪካና አውሮፓ በጥጥ ለቀማና በስፋፊ የሸንኮራ እርሻዎች ላይ የሚያዩት ስቃይ እጅግ ያሳዝነውና ለለውጥ ይነሳል:: ይህን ተግባርም በመፅሐፍ ቅዱስ በያዕቁብ መልዕክት ምዕ፤5:1-4 ሲያስቀምጠው "እነሆ እርሻችሁን ያጨዱት የሰራተኞች ደመወዝ በእናንተ ተቀምጦ ይጮሃል፤ የአጫጆችም ድምፅ ወደጌታ ፀባኦት ጆሮ ገብቶአል::" ይላል::

እንግዲህ ለዚህ ችግር ማርከስ ጋርቬይ እንደ አንድ መፍትሄ አድርጎ ያስቀመጠው፤ ከመነሻ አህጉራቸው አፍሪካ በጉልበት የተወሰዱትን ጥቁሮች በአሜሪካና ሌሎች ምዕራባዊ ሃገሮች እንዲደራጁ ማድረግና በኢኮኖሚ አቅምን ማጠናከር ነበር:: *UNIA (United Negro Improvement association)* ወይም የጥቁሮች የአንድነትና ኑሮን የማሻሻል ድርጅት አቋቁሞ ከሰራ በኋላ ‹‹Black Star Line›› የተሰኘ የመርከብ ንግድ ካምፓኒ አቋቁሞ የቻለውን ያህል ህዝብ ወደ አፍሪካ መመለስ ላይ እያለ ታስሮ ከ5 አመታት በላይ እስር ቤት አሳልፏል:: ምንም አፍሪካውያንን ነፃ የማውጣቱ ታላቅ አላማው ባይሳካለትም አሁን ዓለምን ላጥለቀለቀው የራስ-ተፈሪያዊነት እንቅስቃሴ መሰረት ጥሏል:: ይህም የሆነው ገና ተፈሪ መኮነን ወደ ስልጣን ሳይወጡ አንድ የአፍሪካ ንጉስ ነገስት ወደ ጃማይካ እንደሚመጡና ጥቁሩን ህዝብ ወደ ክብሩ እንደሚመልሱ ራዕይ በመናገሩ ነው:: ይህን ራዕይውንም የሚደግፍበት በዘፍ 49: ከቁጥር 9ና 10 ላይ ያለውን ‹‹(9) ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው:: ልጄ ሆይ ለአደን ወጣ፤ እንደ አንበሳም አሸመቀ፥ እንደ ሴት አንበሳም አደባ፤ ያስነሣውስ ዘንድ ማን ይችላል? (10) በትረ መንግስት ከይሁዳ አይጠፋም ፥ የገዢም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል ገዢ የሆነው እስኪመጣ ድረስ፤ የአህዛብ መታዘዝም ለእርሱ ይሆናል::" ቅዱስ ቃሎች ተጠቅሟል:: አንዳንድ ሰዎች ይህ ጥቅስ ለእየሱስ ክርስቶስ የተነገረ ትንቢት

ነው ቢሉም ቁጥር 10ን በደንብ ቢያጤኑት ይህ በትረ መንግስት ዋናው ገዢ እየሱስ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ የሚነግስ መሆኑን ይረዳል:: ታዲያ ይህን የማርከስ ጋርቬይ ትንቢት ተቀብለው ያመኑ ጃማይካዊ ራስታዎች፣ ተፈሪ መኮንን ሞሓ አንበሳ ዘምነገደ ይሁዳ/ ድል ነሺው የይሁዳ አንበሳ ተብለው ዙፋን ላይ ሲወጡ የተተነበየላቸው ንጉስ እርሳቸው እንደሆኑ አንዳችም አልተጠራጠሩም ነበር:: በዚያ ላይ ለስንት ዓመታት የጠፋ ዝናብ እርሳቸው መሬቱን እንደረገጡ ሲዘንብ የተተነበየላቸው ንጉስ እንደሆኑና ኢትዮጵያም የቃል-ኪዳኒቱ ምድር እንደሆነች ካለ አንዳች ጥርጣሬ ተቀበሉ::"

"ጃንሆይ ግን ይህን ያህል የሚያስከብር ስራ ሰርተዋል ብዬ አላምንም::" አለ አንድ ከፊታቸው የተቀመጠ ጎልማሳ ሰው::

"ይህም የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ አመለካከት ይመስለኛል::" አለና ራስታው ሰው ንግግሩን ቀጠለ፤ "ነገር ግን ኃይለ ስላሴ ምን እንደሰሩ ለማወቅ በመጀመሪያ አሜሪካና አውሮፓውያን በባርነት አገዛዝ ስር የሰረቱን ታላቅ ግፍ ማወቅ ግድ ይላል:: በትንቢተ ዕንባቆም ምዕራፍ 2 ቁጥር 12 ላይ "ከተማንም በደም ለሚሰራ፣ ከተማንም በኀጢያት ለሚመሰርት ወዮለት!" ብሎ እንደተተነበየው እነዚህም ካፒታሊስት ምዕራባውያን የአፍሪካውያን ሃገር ድረስ መጥተው የእልፎችን ደም ካፈሰሱ በኋላ ቅኝ ግዛት ብለው መቀመጣቸው ሳይንስ ከቡሩን የሰው ልጅ እንደ እንስሳ እያጋዙ፣ በአለንጋ እየገረፉ የጉልበት ስራዎችን ያሰሯቸው እንደነበር የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው:: ይህ አረመኒያዊ ስራቸውን ወደ ኢትዮጵያ ይዘው ቢመጡም አድዋ ላይ እነ ፊትአውራሪ ባልቻ አባ ነፍሶ እና ፊት አውራሪ ዲነግዴን የመሰሉ ጀግና ኢትዮጵያውያንን ያሰለፉት አፄ ምኒልክ ድል ነስተው ገተዋቸው ነፃነታችንን አስጠብቀዋል::

ይህችን ነፃ አገርም አባ ጠቅልል ተብለው የነገሱት ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ተረከበዋል:: እኚህም ከፍቅር ሃገር ሀረር ተወልደው፤ ያደጉ በሳል መሪ ነጻነትን ለሀገሬ ብቻ ሳይሆን ለመላው የጥቁር ህዝብ አስፈላጊ ነው ብለው ታላቅ የነፃነት ችቦን ለኮሱ:: የአፍሪካ ህብረትን በመመስረት ብዙ የአፍሪካ ሃገሮችን ከተጫነባቸው የባርነት ቀንበር ለማውጣት ሰሩ:: የደቡብ አፍሪካው ማንዴላና ተከታዮቹን ጨምሮ ብዙ አፍሪካውያንን በግልፅም ይሁን በድብቅ በመደገፍ ከሴይጣናዊ ጭቆና ነፃ አወጡ:: በጥንት ጊዜ ተግዘው ለሄዱት የኢትዮጵያ ልጆች ለሆኑት ጃማይካውያን (ጃማ-ሂካ የኦሮምኛ ቃል ሲሆን...የተሰወረ አይን ተፈታ/ተከፈተ ማለት ነው::) ሃገራቸው ድረስ ሄደው የተስፋ ጮራ ፈንጠቀውላቸዋል:: የተስፋይቱ ምድር ኢትዮጵያ መሆኗን ለሚያምኑ የተወሰኑ ጥቁሮች ደግሞ ሻሸመኔ ላይ መሬት ሰጥተው

እንዲሰፍሩና እንዲኖሩ አድርገዋል፡፡ ዓለም ለ2ኛው የዓለም ጦርነት ሲሰናዳ እንደ ሰላም መልዕክተኛ ሆነው ጄኔቭ ላይ ተገኝተው "ኢትዋኑ ከጦርነት የሚገኝ ትርፍ የለም!" ብለው ሊያስተምሩ ቢሞክሩም አውሮፓውያኑ ተሳልቀውባቸው ነበር፡፡ ሺዎችን አጉሮ በኬሚካል ሲያሰቃይ የነበረው ጨካኙ ናዚም ሆነ ሄሮሺማና ናጋሳኪ ላይ አቶሚክ ቦንብ ጥለው ሙቶ ሺዎችን እስከገደሉ እና አካል ጉዳተኛ እስካደረጉት አሜሪካውያን ድረስ የጦርነት ውጤቱ ሰቆቃና ስቃይ እንደሆነ ዓለም በምስክርነት አየ፡፡ ለዚህም ገና ከጅምሩ ሰላምን ሲሰብኩ የነበሩትን ጃንሆይን ዓለም አከበራቸው፤ በኒውዮርክ ታይምስ መፅሔትም የምዕተ አመቱ ምርጥ ሰው ብሎ ሸለማቸው፡፡ እንግዲህ አህዛብም ይታዘዙታል እንዲል ቃሉ የዓለም መንግስታትና ህዝቦች በሙሉ ለጃንሆይ የነበራቸው ክብር ያኔም ሆነ ዛሬ ድረስ የተለየ ነው፡፡"

አለና ራስታው ሰው ቁጭት ውስጥ እንደገባ ሁሉ ከንፈሮቹን እየበላ ቀጠለ፡፡ "እውነት ለመናገር ከብዙ ዘመናት በኋላ ኢትዮጵያን ወደ ቀደምት ክብሯ ለመመለስ የጣሩ ንጉስ ናቸው፡፡ የያኔ ኢትዮጵያውያን እንኳንስ በስደትና ድህነት ሊዋረዱ ቀርቶ ከምዕራባውያን ዜጎች የሚበልጥ ዋጋ ኖሯቸው ካለ ፓስፖርት በቀበሌ መታወቂያቸው ላይ ቪዛ እየተመታላቸው የትኛውም ሃገር መሄድ ይችሉ ነበር፡፡ እንግሊዛውያን ሲራቡ ስንዴ እስከመለገስ ደረጃ የደረሰች ሃገር ነበረችን፡፡"

"የራሱ ህዝብ ሲራብ ያልደረሰ ንጉስ ለመታየት ብሎ ውጭ ሃገር ስንዴ ቢልክ ምን ዋጋ አለው፡፡" አሉ አንድ ከገቢና የተቀመጡ ወ/ሮ፤

ራስታው መልስ ሳይሰጥ ሲያስብ ቆየና "በቅርቡ በስንክሳርና ማቆያ የሬዲዮ ፕሮግራም ላይ እዚሁ አካባቢ በጃንሆይ ጊዜ ተከስቶ ስለነበረው ድርቅ ያኔ የነበሩ ባለታሪኮችን እያጣቀሱ ማብራሪያ ሲሰጡ ነበር፡፡ አሁን የሞተን ሰው ስም እየጠራሁኝ መወንጀል ባልፈልግም የወሎና ትግራይ አውራጃ የነበሩ ገገርዎች ከአፄ ኃይለ ስላሴ ስልጣን ለመውረስ ከነበራቸው ፍላጎት ምክንያት በአውራጃቸው የነበረውን ድርቅና ርሃብ አፍነው በመያዝ ዜናው ለንጉሱ እንዳይደርስ አድርገው ነበር፡፡ የሚገርመው እኮ "ዋይ! ዋይ! ዋይ! ሲሉ፤ የርሃብን ጉንፋን ሲስሉ" የሚለውን ዘፈን የሰራበትን አጋጣሚ ከቡር ዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ሲገልፅ በወሎ ርሃብ እያለ በትንሽ ርቀት ላይ ባለች ከተማ ላይ ግን ዳቦ እጅግ በርካሽ ዋጋ ይሸጥ እንደነበር ተናግሯል፡፡ ይህም በዋና ከተማዋና በንጉሱ አካባቢ ያሉ ሰዎች ስለርሃቡ በቂ መረጃ እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

የአውራጃው ሹሞች አፍነው የያዙት የርሃብ አደጋ እየከፋ መጥቶ ከንጉሱ ጆሮ ዜናው ሲደርስ ጊዜ ሳይፈጁ ቦታው ድረስ በመሄድ ውሃ ሲያጠጡና የተራቡትን ሲመግቡ እንደ ነበር የፅሑፍና የፎቶ መረጃዎች አሉ:: ሌላው ደርግ ስልጣን ለመያዝ ብሎ የፈጠረውና በብዙሃን ዘንድ እንደ እውነት ተወስዶ የሚነገረው ሰው እየተራበ ለውሻቸው ልደት ኬክ አስደፍተው ከእንግሊዝ ሃገር አስልከዋል የሚል ፕሮፖጋንዳ ነው:: የጃንሆይ የግል ምግብ አዘጋጅ የነበሩት ሰው በሬዲዮ ቀርበው እንደ መሰከሩት ይህቺ ‹‹ሉሉ›› የተሰኘች ውሻ ሲጀመር ቆሪጥ ሳትሆን ከአንድ ጄነራል ለንጉሱ በስጦታ የቀረበች ነች:: ስሟ እንኳን የወጣላት ጃንሆይ በስጦታ በተሰጠቻቸው ጊዜ "ስሟ ማን ይባላል?" ብለው ሲጠይቁት ጄነራሉ በድንጋጤ የመጣለትን የሹፌራቸውን ስም ‹‹ሉሉ›› በማለቱ እንደሆነ አጫውተውናል::

የኛ ሰው ግን ማንበቡ ባይሳካለት እንኳን በቅጡ ትምህርትና ታሪክ አዘል የቲቪና የሬዲዮ ፕሮግራም ሳያዳምጥ፤ ተከታታይ ፊልም እያየ ውሎ በይስሙላ ብቻ የንጉስን ስም ያጠፋል:: ከበጎ ስራ ይልቅ ጥፋትን ፈልፍሎ ማውጣት የሚወድ ትውልድ መቼ ይሆን ከብር ለሚገባው ክብርን የሚቸር? ባጠቃላይ ይሕን ያህል ትልቅ ተፅዕኖ የፈጠሩ፤ እንደ ሙሴ ሁሉ በባርነት ቀንበር ውስጥ የነበሩትን የዓለም ጥቁሮች ከተጫነባቸው የባርነት ቀንበር ያላቀቁ ታላቅ መሪ እንዴት ከብራቸው ይጉደፍ:: ለእነ አፄ ሚኒሊክ፡ ለእነ አቡነ-ጴጥሮስ፣ የካቲት 12 ዓርበኞች መታሰቢያ፡ ለሴባስቶፖል ወዘተ ሃውልቶችን ያቆሙ ንጉስ እንዴት አንዲት ሃውልት በስማቸው ሳይቆምላቸው ይረሱ? ለት/ት ከሚሰጡት ትልቅ ቦታ የተነሳ የገዛ ቤተ-መንግስታቸውን ወደ ዩኒቨርስቲነት የለወጡ፣ ዞረው ያጠቋቸውን ኢትዮጵያውያን ውጭ ሃገር እየላኩ ምሁራን እንዲሆኑ ያስቻሉ:: የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና የኢትዮጵያ ቴሌኮም ድርጅትን ያቋቋሙ፤ ዘመናዊ ፍርድ-ቤትና የእስር ቤት አገልግሎት፣ የመጀመሪያው ህገ-መንግስትና ብሔራዊ መዝሙር ያስረቀቁ እና ሌላም ብዙ ብዙ ያደረጉ ንጉስ እንዴት ስም በማጥፋት ብቻ እናወሳቸዋለን?..." አለ ራስታው... በቁጭት እየተብከነከነ ነበር የሚያወራው:: ሹፌሩም የራስታው ጨዋታ ማርኮት የቴዲ አፍሮ ግርማዊነቶ የሚለውን ሙዚቃ ከዘፈኖቹ የስም ዝርዝር ፈልጎ ድምፁን ሞቅ አድርጎ ከፈተላቸው::

*♫ ♪ "ጁዳ አንበሳ አራት ኪሎ ቢከትምም ስድስት ኪሎ*

*ጥላ ሆኑን ትልቅ ዋርካ ለአንድነቷ ለአፍሪካ፡*

*አራዳ ታቦቱ በፒያሳ - ቀዳማዊ ንጉስ ጁዳ አንበሳ... ቀዳማዊ... ጁዳ አንበሳ፡*

*ግርማዊነቶ የህዝብ እንደራሴ - የአፍሪካ አባት ኃይለ ስላሴ፡"*

.... "ጃ ማን!!" ብሎ ሹፌሩን አመስግኖና ወደ ዮሴፍ ዞሮ "መፅሐፈ መክብብ ምዕራፍ 3 ቁ.4 ላይ ‹‹ለመዝፈንም ጊዜ አለው፡፡›› እንዲል ቃሉ፣ ሁሉም በጊዜውና በቦታው ሲሆን ያምራል፡፡ ይቺን ሙዚቃ እናዳምጥ አይደል?" አለ ራስታው የሚኒባሱን ተሳፋሪዎች በፈገግታ እየተመለከተ....

ሙዚቃው ሲያበቃ ራስታው ቀጠለ "... አዎ ይህ ወጣት አቀንቃኝ እኚህን ሰው በመዝፈንም በመልበስም በቻለው መንገድ ሁሉ ዘክሯቸዋል፡፡ የሌላው ዓለም ጥቁር ስለሳቸው ከኛ ይበልጥ ተመራምሮ ታሪክና ክብራቸውን አውቆ፣ በሬጌ ሙዚቃ ስማቸውን አናኝቶ፣ አንዳንዴም እስከ ማምለክ ድረስ ሲያደንቃቸው እንዴት እኛ ለማክበር እንኳን ተሳነን?" አለ ራስታው፤

"በል አንግዲህ ብለህ ብለህ ያንን አጭር ሰው አምልኩት እንዳትለን!" አሉ ገቢና ያሉት ወ/ሮ እየሳቁ፤

"ቅድም ስለእኔ ሳወራ የሰሙኝ አልመሰለኝም ግን እኔ ጃንሆይን አላመልካቸውም፡፡ በይሁዳው አንበሳ መንፈስ ተቀብተው ለጥቁሮች የተላኩ ንጉስ እንደ ነበሩ ግን አምናለሁኝ፡፡ የእርሳቸውን አምላክነት ማንኛውም የሃይማኖት እውቀት ያለው ሰው አይቀበልም፡፡ እርሳቸውም ቢሆኑ በተዋህዶ ህግና ስርዓት ተቀብተው የገዙ፣ ስዩመ እግዚአብሔር እያሉ በአምላካቸው ስም የሚገዙና ቅዱስ ቃሉን የሚያከብሩ ብልህ ንጉስ ነበሩ፡፡ ይህንን ለሌሎች ራስ-ተፈሪያኖች ማስተማር እንዳለብኝ አምናለሁኝ፡፡ በመጀመሪያ ግን ታላቅ ንጉስና የጥቁሮች አባት የሆኑ ሰው እንደነበሩ እኛ መቀበል አለብን፡፡"

"ራስታ ማለት ኢሉሚናቲ የሚሉት ጉድ እንደሆነ አንብቢያለሁኝ፤" አለ ከፊታቸው የተቀመጠው ጎልመሳ በእርግጠኝነት ስሜት፤

"ራስ-ተፈሪያዊነት ኢሉሚናቲነት አይደለም!" አለ ራስታው በግለት... ከዚያም በረጅሙ ተነፈሰና ቀጠለ፤ "እርግጥ ነው ማንም ሰው የመሰለውንና በእድሜው የቃረመውን እውቀት ተመርኩዞ ነው አስተያየት የሚሰጠው... አስተያየቱም መከበር አለበት። ቢሆንም ራስታዎችን በሙሉ '666' እያላችሁ የምትጠሩበትን የተሳሳተ እውቀት እንድትቀይሩ ከሰማችሁኝ ልንገራችሁ።

በመጀመሪያ የኢሉሚናቲ ግሩፖች አላማ ጠቅለል ተደርጎ ሲተረጎም 'ስሜትን መከተልና ጥቅምን ማግበስበስ' ሊባል ይችላል። ሰይጣን በተጠናወተው አደም ቫይሶፕስ የተመሰረተው ይህ ተቋም አላማው ከፈጣሪና ከህሊናቸው የራቁ ብር አምላኪ ሰዎችን በመፍጠር ለክርስቶስ ጠላት የሆነው የ666 መንግስት (ደጃል) መንገድ መጥረግ ነው፡፡ የሰውን ልጅ ከእምነት በማራቅ፣ እርስ በርስ በመከፋፈል፣ አዕምሮውን በወሲብ፣ አልኮልና ግልፍተኝነት (violence) በመሙላት በጊዜያዊ ደስታዎች ውስጥ የሚዋትት

ከንቱ ማድረግ ነው ግባቸው። በደመ-ነፍስ እንደ እንስሳ ኖሮ ፣ እውቀቱን ጉልበቱን ሁሉናተናውን ለነሱ ጥቅም እንዲገብር እስከ ዛሬ ድረስ ሳይታክቱ የሚንቀሳቀሱ ናቸው።

ለዚህም ከፉ አላማቸው ከሚጠቀሙት ስልቶች መካከል ፊልምና ሙዚቃ ተጠቃሽ ናቸው። … ለምሳሌ፡- የኢሉሚናቲ ምልምል ዘፋኞች ወጣቱን ትውልድ በእርቃን ገላቸውና የመዝፈን ተሰጦዋቸው በማጥመድ የህይወት ትርጉም ቁስ-አካላዊነት እንደሆነ ይሰብኩታል። ልብስ፣ ጫማ፣ ሞባይልና መኪና መለዋወጥና ቆንጆ ሆኖ ታይቶ መደነቅ… ብሎም በወሲብና በስካር አለም መከነፍን የህይወታቸው መርህ እንዲሆን ሳያሰልሱ በዘፈን ያስተምራሉ። ወንዶቹ ዘፋኞችም የሴት ዳሌ፣ ሽጉጥና ገንዘብ የኑሮ የመጨረሻ ስኬቶች እንደሆኑ አድርገው ህዝበ አዳምን በተለይ ደግሞ የዋሁን አፍሪቃና ሞኙን አረብ እንደ ላም ይነዱታል፡፡ ነገር ግን በዋናነት ፍቅር፣ ሰላምና አንድነትን የሚሰብኩ የሬጌ ሙዚቃዎች ተደማጭነት እንዳያገኙ ይለፋሉ፡፡ በየሰኮንዱ በዓለም አራት ኮርነሮች በአማካይ አንድ ሙዚቃው እንደ ሚደመጥለት መረጃዎች ያረጋገጡለትን የሬጌውን ንጉስ እስካሁን ድረስ የግራሚ ሽልማት ለመስጠት እጃቸውን ያሰረው ምን ይመስላችኋል? ብዙም ሰው የማይውቃቸው ለሴይጣን የሚጮኹ ሃርድ ሮክ የሙዚቃ ዘርፍ ዘፋኞች እንኳን በምድባቸው እየተሸለሙ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታላቅ ተደማጭነት ያለው የሬጌ የሙዚቃ እስካሁን ለምን የሽልማት ዘውግ ያልተሰጠው ይመስላችኋል? ምክንያቱም የሬጌ ሙዚቃ ኢሊሙናቲዎችን የሚጠዘጥዝ ዜማና ግጥም ስላለው ነው፡፡ ብዙም ባይሆኑም ወደሃገራችን ተመልሰንም እንደ ዘለቀ ገሰሰ፣ ቴዎድሮስ ካሳሁን እና እዮብ መኮነን ያሉ የሬጌ ዘፋኞችንና እንደ ቴዲ ማክና ኤልያስ መልካ ያሉ በሳል የሬጌ አቀናባሪዎችን ብናስተውል ከሚሰሩት የሙዚቃ ጥልቀትና መልዕክት አስተላላፊነት ባሻገር ለሌሎች ዘፋኝና አቀናባሪዎች አርዓያ ሊሆን የሚችል ስብዕናን የተላበሱ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ የሚሰብኩትም የፍቅርና አንድነትን መንፈስ እንጂ ጥላቻና ከፋትን አይደለም።" አለና ወደነኢትኤል ዞረ፣ ሁሉም ለመቀበል የሚከብደውን እውነት እየሰሙት ነበር፡፡

"ከነገርኳችሁ ሙዚቃዎችና ፊልሞች ሽያጭ ባሻገር የቶባኮ፣ ውስኪና ቮድካውን ገበያ፣ በአብዛኛው ኢሉሚናቲዎች የሚቆጣጠሯቸው ምዕራባዊ ካምፓኒዎች ያደሩታል፡፡ ልቅ የግብረ ስጋ ግንኙነቶችን የሚያሳዩ ፖርኖግራፊክ ፊልሞችን በኢንተርኔት እየበተኑ የወሲብ ንግዱን ያጧጡፋሉ፡፡ ምን ይሄ ብቻ የአፍሪካና አረብ ሀገር ህዝቦችን እርስበርስ አባልተው

ለሁለቱም ጎራ የጦር መሳሪያዎችን እየሸጡ በደም የተጨማለቀ ትርፋቸውን ይቆጥራሉ። ላለማርዘም ያህል ኢሉሚናቲ የሚባሉት የዓለም ጉልቤና ሴይጣናዊ አመራሮች ህዝቡን ከእምነት፣ ከእውቀት፣ ከንፁህ ፍቅርና አንድነት አርቀው መበዝበዝና መግዛት ነው አላማቸው።

እውነቱን ለመናገር የራስታ አራማጆች የኢሉሚናቲ ውጤቶች ሳይሆን እንዲያውም 4500 ዓመታት በፊት በግዮን ወንዝ ዙሪያ እንደ ነገሰው የኩሽ ዘር አሁንም የኩሽና ጥቁርን መንገድ ሽተው በዛዮን መንገድ ላይ እየተጓዙ የሚገኙ ወንድሞቻችን ናቸው:: የውበትና ጥበብ አባቶችን ገፅታ አስቦ ፀጉሩን እንዳንዠረገገው ቦብ ማርሌይ የኢትዮጵያን አፈር ናፋቂዎች፤ ወደ ቃል-ኪዳን ምድራቸው ኢትዮጵያ እንዳይደርሱ የሚጋረጥባቸውን የባቢሎን መሰናከል በፍቅር የሚያልፉ ተጓዦች:: በዚህም ለጥቁሮች ብቻ ሳይሆን ለብዙ ኢሉሚናቲዎች ለተቆጣጠሯቸው ምዕራባዊ ፈረንጆች ተስፋ እየሰጡ ብዙዎቹን እግዚአብሔር የለም ከሚል ጭለማና የኢሉሚናቲ ሴራ እያወጡ ወደራስታነት እየቀየሩ ያሉ ናቸው:: በዓለም አቀፍ ደረጃም አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ አርማችንን ከፍ አድርገው እያውለበለቡ ይገኛሉ::"

"እኔ ግን ለማመን ይከብደኛል ወላሂ፤ ማለት የእጅ ምልክታችሁ ራሱ አንድ አይነት እኮ ነው:: ደግሞ በዚያ ላይ ኃይለ ስላሴ እኮ ለሙስሊሞች ጥሩ አይደሉም::... ራስታዎችም ብትሆኑ የእስልምና ሃይማኖት ጋር አትስማሙም፤ ሲጀመር በቀለምና ዘር ለጥቁሮች ነው የቆምነው ምትሉ ከሆነ ሃይማኖታችሁ ከእኛ እስልምና ጋር ይጋጫል::" አለች መርየም::

"የኔ እህት መጀመሪያ ላስተካክልሽ፤ ራስ ተፈሪያኒዝም ሃይማኖት ሳይሆን ርዕዮተ ዓለም ነው:: እኛ ደግሞ ለጥቁር መብት እንታገላለን ማለት ዘረኛ ነን ማለት አይደለም:: ባይገርምሽ የመጀመሪያው የባሪያ ገዢዎችን በደል ተቃውሞ አሸንፎ የወጣ የጥቁር መብት አርዓያ ማን እንደሆነ ታውቂያለሽ?"

"አላውቅም::" አለች መርየም፤

"ቢላል አል ሃበሺ ይባላል::" አላት ፈገግ ብሎ፤ እሷም ሳቀች:: "እናም ለጥቁር መብት መታገል ዘረኛ አያስባልም:: ታላላቆቹ የጥቁር መብት ተሟጋቾቹ ማልኮም ኤክስና መሐመድ አሊ ሙስሊሞች መሆናቸውንም አትዘንጊ::

ሌላው ኃይለ ስላሴ ሙስሊሞችን አይወዱም ላልሽው ደግሞ ከየትኛውም የንጉሣዊ አገዛዝ በተሻለ ለሙስሊሞች መብት የሰጡ ንጉስ መሆናቸውን ልነግርሽ እወዳለሁ:: የመጀመሪያውን ቅዱስ ቁርዓን ወደ አማርኛ እንዲተረጎም ያደረጉት እርሳቸው መሆናቸውን ታውቂያለሽ? ታላቁን አንዋር መስጊድንና አዎሊያን ጨምሮ በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች የሚገኙ

በርካታ መስጂድና ደረሳዎችን መሰረት የጣሉ ንጉስ ማን ይመስሉሻል? እነ ቃጥባሬን፣ ሼህ ሆጀሌንና አልከሲዬን ጨምሮ ብዙ ሙሂቦችና ኡለማዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የበዙበት ዘመን የሆነውን የኃይለ ስላሴ አገዛዝ ሙስሊሞችን አይወድም ማለት በፍፁም የተሳሳተ አመለካከት ነው:: በእርግጥ በስራቸው የነበሩ አንድ ሃይማኖት አንድ ሃገር የሚሉ አክራሪ መሳፍንቶች ሙስሊሞችን ሊጨቁኑ ይችላሉ:: ነገር ግን የንጉስን ስብዕና በመሳፍንት ባህሪ መመዘን የሚገባ አይመስለኝም::

ጃንሆይ ይሰሩት የነበረውና አሁን ራስታዎች በእጀቻቸው በሚሰሩት የዳዊት ኮከብ ቅርፅ ዙሪያ ደግሞ ድሮም ብዙ አሉታዊ አስተያየቶች ያጋጥሙኛል። በዚህ የእጅ ምልክትና የኢሉሚናቲ ተብሎ በሚታወቀው የትሪያንግል ምልክት ዙሪያም እጅግ በርካታ ውዥንብሮች እንዳሉ ይገባኛል:: ነገር ግን ልብ ብሎ ለተከታተለው በግልፅ በፎቶዎችም ይሁን በቪድዮዎች ላይ ሊያየው ከሚችል እውነታ ስነሳ የጃንሆይና የርሳቸው ፍቅር ያሸነፋቸው ራስታዎች የሚያሳዩት አውራ ጣትን ከሌባ ጣት በማገጣጠም ቀስቱ ወደምድር የሚጠቁም የውሀ ጠብታ (water drop) ወይም የሻማ ላምባ (flame) የመሰለ ቅርፅ...

(✡)የዳዊት ኮከብ ቅርፅ ሲሆን፤ ይህም ባለ6 ጎን ኮከብ የሰው ልጅን የ‹☥›

ተዋህዶነት የሚወክል ብሎም የመሲሑ የእየሱስ ክርስቶስ መወለድን በሰማይ ላይ የጠቆመና ከዚያም አልፎ ሰብዓ ሰገሎችን (ኢትዮጵያዊ ካህናትን) ወደ መወለጃው ስፍራ የመራች ኮከብ ነች::

በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ይሕ የወንድና የሴትን ብልት የሚያሳይ ምልክት ነው የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ አለ:: ይህም አስተሳሰብ ሰይጣን ሆን ብሎ የሰው ልጆች አዕምሮ ውስጥ ያሰረፀው ነው:: ይህም የላሊበላ ቤተ-ክርስቲያኖች ውስጥ ይገኝ የነበረውን ምስል ናዚዎች ወስደው የጭካኔ ምስል እንዲሆን ካደረጉት ከስዋስቲካ ጋር ይመሳሰላል:: የክርስቶስን መገለጫዎች በመገልበጥ የሚታወቁት ሰይጣን አምላኪ የሆኑት ኢሉሚናቲ…

(free Manson's) በእጃቸው የሚያሳዩት ቀስቱ ወደ ሰማይ የሚጠቁም የሶስት ማዕዘን ቅርፅ ነው:: ባይገርማችሁ የቅርፆቹ ተቃራኒ መሆን የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም። የራስታዎችና ኢሉሚናቲዎች አስተሳሰብና እምነትም ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ ስለሆነ ነው። እርግጥ ይህ ኢሉሚናቲ የሚባል ነገር በዙሪያችን ተሰግስጎ ይገኛል:: ነገር ግን ራስታዎች ኢሉሚናቲ ሳይሆኑ ዓለም ላይ የእውነትና የፍቅር ብርሀን እንዳይጠፋ የጥልቁን 666 እየተዋጉ ያሉ 999 የዚማና ተስፋ ሰልፈኞች ናቸው። ትርጉሙ ፀጉር ማሳደግና ሴት ማባረር ብቻ የመሰላቸው ራስታ ተብዮ መወልወያ ራሶችን ሳይጨምር ትክክለኛ ራስታዎች

የቅድስት ምድራቸውን ባንዲራ ታጥቀው ለጥቁር ህዝብ እየታገሉ ያሉ የመንፈስ ወታደሮች ናቸው::" አለ ራስታው ፊቱ ላይ ፈገግታ እየተነበበት::

"በጣም ይገርማል!" አለ ዮሴፍ በራስታው ወሬ ከሁሉም በላይ ተመስጦ ስለነበር:: አስከትሎም... "ቆይ አሁን ይሄ ሁሉ ነገር ከሆነ፣ ማለትም የጥቁሮች መብት ረገጣና ባርነት ተከስቶ አሁን ነፃ ከሆኑ፣ የኢሉሚናቲዎች ጉዳይም አሁን እንዳልከው ሁላችንንም ውስጥ ተሰግስጎ ያለ ከሆነ የእናንተ ድርሻ አሁን ምንድነው?" ብሎ ጠየቀው ራስታውን፣

"እየውልህ ጆሲ፣ አሁንም ማወቅ ያለብህ ፈረንጆቹ እንዳልተኙልን ነው:: ያኔ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከማብቃቱ ገና ነበር ናዚ ውስጥ የነበሩ ጨካኝ ጨካኝ ሳይንቲስቶችን ‹‹ኦፕሬሽን ፔፐር ክሊፕ›› በተሰኘ ፕሮጀክት ወደ አሜሪካ አስመጥተው ለቀጣዩ የሰው ዘር ማጥፋት ዓላማቸው የተዘጋጁበት:: ፈገግታቸው ብቻ እንጂ ውስጣቸው አፍሪካውያን እንዳያድጉ እንደሚፈልጉ ግልፅ ነው:: በአፓርታይድ ሲያሰቃዩት የነበረው የደቡብ አፍሪካ ህዝብ ከስንት ትግልና ስቃይ በኋላ ነፃ ወጥቶ ኔልሰን ማንዴላም በቀል ይቅር ብሎ ለነጮቹ ይቅርታ ቢያደርግም እነርሱ ግን ከፋታቸው በዝቶ የዘመኑን ደቡብ አፍሪካዊ ወጣት በቫይረስ ከመበከል ወደኋላ አላሉም::

ሃገር ውስጥ የአገዛዝ ሁኔታዎች ጥሩም ይሁን መጥፎ የአፍሪካውያን መሪዎች ግን የአፍሪካን ሁለንተናዊ እድገት ለማረጋገጥ በተነሱ ቁጥር በምዕራባውያን ክፉ በትር መመታታቸው አልቀረም:: ኮ/ል መንግስቱ ሃ/ማርያም ‹‹ምዕራባውያን በእኛ ህይወት ውስጥ ገብተው የመወሰን መብት የላቸውም›› ብለው በፅኑ ያምኑ ስለነበር ምዕራባውያኑም ኮሎኔሉ ከስልጣን እንዲወርዱ የተቻላቸውን በሙሉ አድርገዋል:: ጦርም ልከው ያልወጉን አንድም የሶሻሊስቶች ራሺያ እገዛ ከጎናችን ስለነበር፤ ሁለትም ከወረሩን በኋላ የሚዘርፉት የነዳጅ ሃብት ስላልነበረን ይሆናል:: ከእሱ አገዛዝ መውደቅም በኋላ የቀድሞው ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ላይ ለ20 ዓመታት ሲገዙ ሃገራቸው ውስጥ የፈለጉትን ቢያደርጉም እንዳችም የተቃወማቸው የምዕራብ ሃገር መሪ አልነበረም:: ነገር ግን የምድር የሙቀት መጨመርና የአየር ንብረት ለውጥን መፍትሔ አፈላላጊ ሆነው ሲመረጡ ምዕራባውያኑ ጥርስ ነከሱባቸው:: በኮፐን ሃገን አሜሪካን ጨምሮ ሌሎችም የምዕራባውያን ሃገራት ለሙቀት መጠን መጨመርና ለምድር መበከል ምክንያት እንደመሆናቸው የቢሊዮን ዶላር የገንዘብ ካሳ ለአፍሪካውያን እንዲከፍሉ ለማድረግ በመሪነት ሲሰሩ እያለ መሞታቸው ሁላችንም የምናስታውሰው ሃቅ ነው::

ምጡቅ ጭንቅላት የነበረው ሳይንቲስት ቅጣው እጅጉ ለብዙ አመታት ለናሳ በታማኝነት ሲያገለግል ቆይቶ የትውልድና እድገት ሀገሩን ማዕድንና ነዳጅ ሃብት በሳተላይት አጥንቶ፣ በኢኮኖሚ ድሃ ሀገሩን ለመርዳት ወደ ኢትዮጵያ አሄዳለሁኝ ባለጊዜ ሚስጥራዊ በሆነ መንገድ እንዳስገደሉት ውስጣችን እያወቀው ዝም ብለን ተቀምጠናል፡፡ ለስንት ዘመናት በብቸኝነት ሊቢያን የገዙት ሞህመድ ጋዳፊ በጣሊያን ቅኝ ግዛት ፍርስርሷ የወጣውን ሃገራቸውን እንደ አዲስ ገንብተው ከዓለም ላይ ለኑሮ ምቹ ከሆኑ ሃገሮች ተርታ እንድትሰለፍ አድርገዋታል፡፡ ብዙ ከፉና ደግ ነገሮችን ሀገራቸው ውስጥ ሲከውኑ በቁራኛ ይከታተሉ የነበሩት ምዕራባውያን የሰብዓዊ መብት ጉዳይ አላሳሰባቸውም ነበር፡፡ ከጃንሆይ ጋር የሰሩት እና በፓን አፍሪካኒዝም ትልቅ እምነት የነበራቸው ጋዳፊ ግን ‹‹የአፍሪካን አንድነት ለማጠናከርና የንግድ ልውውጡን ለማፋጠን ብዙ ሺህ ቶን የሊቢያ ወርቅ ለአፍሪካው መገበያያ ብር ማምረቻ አዋጣለሁኝ፡፡ ከእንግዲህ በኋላ አፍሪካውያን ዶላርን ገለል አድርገው የራሳቸው የሆነ የብር ኖታ ይኖራቸዋል›› ብለው ሲነሱ ሊቢያ ላይ ጦርነት ለማወጅ ሳምንታት አልፈጀባቸውም ነበር፡፡ የጋዳፊዋ ሊቢያ ህዝቦቿ ተምረው ስራ እስኪያገኙ ደረስ ደምወዝ የምትቆርጥ፣ ኤሌክትሪክ፣ ትምህርትና የጤና አገልግሎቶች በነፃ ለዜጎቿ የምታቀርብና ለአዲስ ተጋቢ ጥንዶች የትዳር መያዣ ብላ 50000 ዶላር የምትለግስ ሃገር ነበረች፡፡ አሁን ግን ዴሞክራሲ እናመጣለን በሚሉት አሜሪካውያን የተያዘችው ሊቢያ የለቅሶና የችግር፣ የአይሲሲዎች መፈንጭያ ሆናለች፡፡

ነጮቹ የአፍሪካን ራስ-ገዝ እድገት ከሚያዩ ሞትን የሚመርጡ ይመስላሉ፡፡ አምጥተው እንደተከሉብን የእንቦጭ አረም አበባ ከላይ እያማረ ከስር የሀገር ደም የሚመጡ መሰሪዎችም በመሃላቸው አሉ፡፡ ብልጣብልጥና ተንኮለኝነት ከብልህነትና አዋቂነት ጋር አይምታታብን፡፡ ከላይ እየሳቁ ከስር ሃገር ለማጥፋት ወደኋላ የማይሉ ናቸው፡፡ የጃንሆይን ወዳጅ ፕሬዝዳንት ኬኔዲን በአደባባይ በአልሞ ተኳሽ ያስገደሉ ኢሉሚናቲዎች፣ ማይክል፣ ሉተርና ቱፓክም ላይ ይህን አፀያፊ ድርጊት ደግመውታል፡፡ ለተራ የእግር እንቅፋት ማስታገሻ ብለው ካንሰር የሚያመጣ መርፌ ለቦብ ማርሌን ወግተው ያስገደሉትም እነርሱ ናቸው፡፡

በተቃራኒው ግን የራስታዎች የህይወት መርሆ በአዎንታዊና መልካም መሰረቶች ላይ የፀና ነው። በነገራችን ላይ ራስ-ተፈሪያኒዝም በፍቅር፣ አንድነት፣ ተፈጥሮ አክባሪነት፣ ሙተዛዘን፣ የአፍሪቃ ነፃነትና የጥቁሮች መንቃት ወዘተ… ላይ የተመሰረተ የህይወት መንገድ እንጂ ሀይማኖታዊ ተቋም አይደለም። ህልማቸውም እንደኢሉሚናቲ ጥቂቶች ከላይ ሆነው ብዙሀኑ ከታች የሚሰቃይበት ፒራሚድ መስራት ሳይሆን ሁሉም የሰው ልጅ ተዋዶ

የሚኖሩባት የሰላም ምድር ማየት ነው። ጥንታዊ የኩሽ ነገድ ጥቋቁር ነገስታት አባቶቻችን አፍሪካን በታላቅነት እንደ ፒራሚድ፣ አክሱም ኑብያና ቲምቡክቱን የመሰሉ ስልጣኔዎችን በጥበብ አስተዳድረዋል፡፡ ነገር ግን ጥበብ ና ስልጣኔያቸውን በስርአት ባለማውረስ በተፈጠረው ከፍተት እየተዳከም በመጣው አገዛዝ ፣ መሰሪ የሆኑ ፈረንጆች እውቀታችንን ዘርፈው፣ ስልጣኔያችን ይበልጥ ተዳከሞ አሁን የ3ኛ ዓለም ያላደጉ ሃገራት ከተባሉት እንመደባልን፡፡ አስቀምጠን በስንፍናችን ያልገለጥነውን ብራናችንን እየገለጡ የሚያገኙትን እውቀት አዲስ ቴክኖሎጂ እያሉ ለኛ ይሸጡልናል፡፡ ነገር ግን ማዘንና መቆጨት አያዋጣንም፡፡ እርግጥ ነው ሃብታችንን ዘርፈው ወርቅ ቢያከማቹም እኛ ጋር ግን የማይሰረቅ እምነትና እውነት አሁንም አለ፡፡ የአክሱም ሃውልትን ቆርጠው ቢወስዱም የካሌብ ጥበብና የአክሱም ጽዮን መንፈሳዊ እምነታችንን ግን ሊወስዱ አይችሉም፤ ጻህም ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል፤ የሃብቶች ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር ነውና ከታመነው ክብራችንን ይመልሳል፡፡" አለና ለአፍታ ያህል ዝም ብሎ ቆየ፤

"እንግዲህ እኔና መሰሎቼም ዓላማችን ይህንን ነገር ለማሳካት እንጥራለን፤ በሰው ልጅ አዕምሮና እምነት ላይ አትኩረንም እንሰራለን፡፡"

"እሺ አሁን አንተ እዚህ ምን እየሰራህ ነው?" አለ ዮሴፍ፤

"ያው ሁላችንም ከ‹‹ብላክ ላይፍ ማተርስ›› ኦርጋናይዜሽንም ጋር በመተባበር ለጥቁሮች ህይወት መሻሻል የቻልነውን በሙሉ እናደርጋለን፡፡ እኔ ለምሳሌ በሃንጋሪ ያሉ ራስታዎች ጋር የማሪዋና ጥናት የማካሄድ የእፅዋት ተመራማሪ ስሆን እዚህ ክልል የመጣሁትም እስከ 2% የሚደርስ THC መጠን ያለው የዊድ ተክል በመርሳ አካባቢ እንደሚገኝ መረጃ ደርሶኝ ለማጣራት ነው፡፡ ይህን ፍሬ ካገኘሁም ብዙ በሄሮይንና ኮኬን አደገኛ ሱስ ለተጠመዱ አውሮፓውያን መፍትሔ አገኛለሁኝ ብዬ አምናለሁኝ፡፡ ተስፋ ለቆረጡ ኢ-አማኝ ሰዎች የተስፋ ብርሃን እንዳለ፤ ስሙን እንኳን ሰምተውት የማያውቁት አምላክ ለእነርሱ እንደሚያስብ ለማስተማርም ይረዳኛል፡፡"

"ኢ-አማኝ ሰዎች ነው ያልከኝ?" ጠየቀ ዮሴፍ፤.... "አዎ"

"ከዚህ ብዙ ይርቃል የእፅዋት ጥናቱን የምታደርግበት ቦታ?"

"ብዙም አይርቅም፡፡" መለሰ ራስታው፤

"አብረን ብንሄድ ደስ ይለኛል፡፡" አለ ዮሴፍ፤ እነ ኢትኤል ደንግጠው ዮሴፍን ተመለከቱት፡፡

"ምን ማለት ነው ካንተ ጋር እሄዳለሁኝ ማለት?" አለ ኢትኤል ገርሞት፤ ዮሴፍ ሁሉንም ተራ በተራ እያየ መለሰላቸው፡፡

"ጓደኞቼ እኔ ለእናንተ ጥሩ የምባል ጓደኛ እንዳልሆንኩኝ አውቃለሁኝ፤ ያን ሁሉ ጊዜ የሚያናዱ ጥያቄዎችን እየጠየቅኩኝ አዛ የማደርጋችሁ ለራሴ በውስጤ የሚፈጠሩብኝን መልስ አልባ ጥያቄዎች መመለስ ስላቃተኝ ነበር ብሶቴን እናንተ ላይ የምወጣው፤ ዛሬ ግን ማንም ሳይመለሱልኝ በውስጤ ተፈጥረው የቆዩ ጥያቄዎችን ይህ ራስታ ሰው መልሶልኛል:: እግዚአብሔር አልተጠራንም ብለው ላልቀሩትም ምልክትን እንደሚሰጥ አምኜያለሁኝ:: በዚያ ላይ እንደ እኔ መልስ አጥተው ላሉ ኢ-አማኞች ተስፋ ከመስጠት የተሻለ ተግባር ያለ አይመስለኝም::"

"እና ከዚህ ራስታ ጋር ለመሄድ ወስኜያለሁኝ ነው የምትለን?" አለ ናዖድ በግርምት፤

"አዎ ወስኜያለሁኝ፤... እሱ ፍቃደኛ ከሆነ፤" አለ ራስታውን እየተመለከተ::

ራስታው ዞር ብሎ ከጎኑ የተቀመጠውን ዮሴፍ አቀፍ አደረገውና "ብዙ ሰዎች የማይመለከታቸውን ነገር ሲከተሉ የሚመለከታቸውን ነገር ያጣሉ:: ስለ አውሮፓውያን አክተሮችና ሙዚቀኞች የመኪና አይነትና የቤት ውበት የሚያሳዩ ቪድዮዎችን ከኢንተርኔት እያወረዱ ላህጫቸውን እያዝረከረኩ ሲያዩ እየዋሉ ማትሪክና ኢንተራንስ ፈተና የሚወድቁ፤ ከዩንቨርሲቲ የሚጫሩ የዘመኑ ወጣቶች ያሳዝኑኛል:: አንተ ግን ይህን ህዝብ ለማከም እየተማረክ እስካለህና ተመልሰህም ትምህርትህን በሚገባ እስከተከታተልክ ድረስ እኔን የማትከተልበት ምክንያት አይታየኝም:: በዛዮን መንገድ ላይ ስንጓዝ የሚያጅቡንን ወንድሞቻችንንማ በደስታ ነው የምንቀበለው... ዋካንዳ!::" አለና ራስታውም አብሮት መሄድ እንደሚችል በፈገግታ አረጋገጠለት::

እነኢትኤል በራስታው ንግግር እንደ ተመሰጡ ከገራዶ መርሳ ያለው መንገድ ተገባዶ ኖሮ ሳያስቡት ነበር መርሳ የደረሱት:: መርሳ ላይ ሲወርዱ ዮሴፍ ከራስታው ጋር በመሄዱ ስለፀና ሁሉንም ተሰናብቶ ተለያቸው::

እነኢትኤል ደግሞ ከመርሳ ጎቢዬ ወደ ምትባው የገጠር መንደር የሚወስድ መኪና እየፈለጉ ሳለ አንድ ሰው ተመለከቱና ሁሉም ደንግጠው በቆሙበት ቀሩ::"እንዴ በጌታ ስም!... ቶላ ነው?" አለ ናዖድ በግርምት፤ ቶላ ከእነርሱ በትንሽ ርቀት ላይ ሆኖ፣ መሳፈሪያ መኪና ፍለጋ ቦርሳውን አንግቦ ወዲህ ወዲያ ያማትራል:: እነ ኢትኤል ፈጠን ፈጠን እያሉ ተራመዱና አጠገቡ ደረሱ:: ሲያያቸው በጣም በደስታ ተሞልቶ ሁሉንም እያቀፈ ሰላም አላቸው::

"ምን ትሰራለህ እዚህ?" አለ ኢትኤል::

"ታሪኩ ብዙ ነው ባክህ፤ አሁን ግን ጎቢዬ ወደ ምትባል ቦታ የሚሄድ መኪና እያፈላለግኩኝ ነበር::" አለ ቶላ ጓደኞቹን በማግኘቱ እየፈነደቀ፤

"ከጎቢዬስ ወደዬት ልትሄድ ነው?" አለ ኢትኤል መዳረሻቸው አንድ ሊሆን እንደሚችል እየጠረጠረ፡፡

"እዚያ ከደረስኩኝ በኋላማ ኦሮሞ ወደ ሚባል አካባቢ ለመሄድ ነው እቅዴ፡፡" አለ ቶላ፤

"እኛም እኮ ጉዟችን ወደዚያው ነው፡፡ በህልማችን በተጠቆምነው መሰረት ሼህ ከድር የሚባሉትን ሰው አግኝተናቸው ወደዚህ ስፍራ የመሩን እርሳቸው ናቸው፡፡" አለና ኢትኤል እስካሁን የተከሰተውን በሙሉ ባጭሩ ለቶላ ነገረው፡፡ ቶላም ስለደረሰበት አደጋና ስለ አባ-ገዳው እሱን መንከባከብ ነገራቸው፡፡ የሆነውን በሰሙ ጊዜም እጅግ ተደመሙ፡፡

አብረው ለተወሰኑ ጊዜያት መሳፈሪያ ከፈለጉ በኋላ አንዲት ወደ ጎቢዬ የምትሄድ መኪና አገኙና ተሳፈሩ፡፡ ከረጅም ጉዞ በኋላ ጎቢዬ ሲደርሱም የአካባቢውን ሰዎች ኦሮሞ የሚባለው አካባቢ እንዴት መሄድ እንደሚችሉ ጠየቋቸው ፡፡ ከጎቢዬ በስተምስራቅ በ3 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ያለ ቀዬ እንደሆነ ነግረዋቸው፤ነገር ግን መኪና እንደማያገኙና ብር መክፈል ከቻሉ ግን ባለጋሪዎች ሊያደርሷቸው እንደሚችሉ ጠቆሟቸው፡፡ ሁለት በዘርፍና በማርገጫ ያጌጡ ጋሪዎችንም ተከራዩና ተጫኑ፡፡ ቼ በል ጋሜ በሚል ሹፌር፤ ለመገልበጥ ብዙም በማያሰጋ ተፈጥሯዊ መጓጓዣ ጉዞ ወደ መንደረ "ኦሮሞ" ተጀመረ፡፡

*** ♀ - ♀ ***

# ምዕራፍ ፲ - ቆሮ ቃሮ ገዳ ፉኖ

*** ☥ - ☥ ***

"አብራምም ድንኳኑን ነቀለ መጥቶም በኬብሮን ባለው በመምሬ **የኢድባር ዛፍ** ተቀመጠ፤ በዚያም ለእግዚአብሔር መሠውያን ሠራ።"
(መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ፣ ምዕራፍ ፲፤16)

*** ☥ - ☥ ***

"የእግዚአብሔርም መልአክ መጥቶ በዖፍራ ባለችው ለአቢዔዝራዊው ለኢዮአስ በነበረችው **በኢድባሩ ዛፍ** በታች ተቀመጠ፤ ልጁም ጌዴዎን ከምድያማውያን ለመሸሸግ በወይን መጥመቂያው ውስጥ ስንዴ ይወቃ ነበር።" (መጽሐፈ መሳፍንት 6:11)

*** ☥ - ☥ ***

"♫ኢያንደንቆ ኑጊ ጄማ ዳሁ
ኢሚማን ኮ ጡሪ ሲቲ ሃ ታሁ፤
አንቦ ጉባ - ያ ባለ ጎዳሬ፣ ያ ባለ ጎዳሬ፣
ወሊጋራ ያ ባለጎዳሬ፥
አርሲ ጉባ - ያ ባለ ጎዳሬ፣ ያ ባለ ጎዳሬ፥
ሶሎሎራን - ያ ባለ ጎዳሬ፥
ሱመ አብዲን ኮ - ያ ባለ ጎፈሬ፤
ኤስ ጂርታ ያ ባለጎፈሬ? … ያ ባለጎፈሬ፥ ያ ባለጎፈሬ፥
ሱመ አብዲን ኮ ያ - ያ **ቆሮ** ኮ
ኢሳ ጂርታ - ያ ጃጀቤኮ - ያ ጃጀቤኮ፤
ጋሪዋን የሚሾፍራት ወጣት ባሊጋሪ በሚያምር ድምፁ የሃጫሉ ሁንዴሳን ሙዚቃ ያስረቀርቀዋል፡፡ በዚህ ውብ ድምፅ ዜማ ታጅበው ለ20 ደቂቃ ያህል ከተጓዙ በኋላ አርሞ የሚባለው አካባቢ ደረሱ፡፡

*ኪጋሪው ወርደው በአካባቢው ያገኙትን ሰው «የአቦ አራርሳ ቤት የት ነው? » ኢየሉ ቢጠይቁም የሚነግራቸው ሰው ግን አላገኙም:: በኋላ ግን አንዲት ሻይ ቤት ደጃፍ ላይ የተቀመጡ አዛውንት የሚሉትን ሰው እንደሚያውቁ ነገሯቸው::*

*"እከሲ! እናንተ አቦ አራርሳ የምትሉት ሰው በጎል ማሳነቱ ዶ/ር ጉዲና ይባል የነበረ የኦሮሞ ታሪክ ተመራማሪ ሲሆን አሁን ግን በሽምግልናው የገዳ ስርአትን መርጦ ከዚህች መንደር ማዶ የሚኖር ሰው ነው::" አሉ:: ለነኢትኤል ከበረንዳው ስር በረድፍ ቆመው እያዳመጧቸው ነበር:: አዛውንቱ አከለውም፣ "ይህ የገዳ ስርዓትን አጅግ የሚወድ ሰው «አሁን ያለሁበት ማህበረሰብ አርቴፊሻሉ የምዕራባውያን ተፅዕኖ አጥቅቶታልና አብሬ መኖር አልችልም» ብሎ ከዛፉ ስር ዳስ ቀልሶ መኖር ከጀመረ ብዙ ዓመታትን አስቆጥሯል:: ቤተሰቦቹም ቢመክሩት ቢለምኑት ወደ ቤቱ አልመለስም ብሎ በአቋሙ ስለፀና ተስፋ ቆርጠው ትተውታል:: በማይታወቅ ጥበብ አንበሶችን እንደ ሚያረባም ይነገራል:: «የአንበሶች አለቃ» የሚል የቅጥል ስምም የሰፈሩ ሰው አውጥቶለታል::" አሉ፣ በትዝታ ተውጠው መሬት መሬቱን እያዩ፣*

*"የአንበሶች አለቃ ነው የሚባለው አሉን?" ብሎ ጠየቀ ቶላ ነገሩ እያስገረመው፣*

"*አዎ! ብዙ አንበሶችን እንደሚያሳድግ መንደሩ በሙሉ ያውቃል::* ከሰሞኑ እንኳን የዚሁ አካባቢ ኑዋሪ የሆነች ልጃገረድን 2 ጎረምሶች ሊደፍሯት ሲሉ አንድ የእርሳቸው አንበሳ እንዳስጣላትና በኋላም የመንደሩ ሰዎች እስኪደርሱላት ድረስ መጠበቁን ሰምተናል::"

"የሚገርም ነው!...ግን የት ልናገኛቸው እንችላለን?"አለ ቶላ አንገቱን ነቅንቆ፣

"ይሄ ነው የሚባል መገኛ አድራሻ እንኳን የላቸውም፣ ከዚያች ከተራራው ባሻገር ካለችው የአድባር ዛፍ ስር አልፎ አልፎ ይቀመጣሉ፣ እድላችሁን ብትሞክሩ ደግ ነው::" አሏቸው አዛውንቱ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ካለ ትልቅ ዋርካ ዛፍ ጣታቸውን እየጠቆሙ::

እነ ኢትኤል አዛውንቱ በነገሯቸው መሰረት የትልቁን ዛፍ አቅጣጫ ተከትለው ሄዱ:: ከቦታው ሲደርሱም እድለኛ ሆነው ኖሮ አቦ አራርሳ በቦታው ነበሩ:: ቅርንጫፎቹን እንደ ንስር ክንፍ ባሰፋው ዋርካ ስር ቁጭ ብለው ነበር ያገኟቸው::

አቦ አራርሳ ከጃኖ የሚመሳሰል ልብስ ለብሰዋል፣ እንደ ኦሮሞዎች ባህል ትንሽዬ አክሱም የመሰለ ቅርፅ ከግንባራቸው ላይ አሹለው አስረዋል:: ከወደ ግንባራቸው ትንሽ ገባ ያለው፣ የገብስ አውድማ የመሰለ አፍሯቸው የአንበሳ ጎፈሬ ይመስላል:: ፊታቸውን ያካበበው ፂም ወደ በረዶ ንጣት የሚያደላ ሃጫ

ነው፡፡ በእጃቸው ላይ ከጫፉ ላይ ወፈር ብሎ የቢረሌ ቅርፅ ያለው እንደ አባ-በራ ‹‹ቢራ››፤ እንደ ጸደይ ጸዳል ፍካትን የሚወክል፤ ከስር ሁለት እግር ያለው ዱላ ተደግፈዋል፡፡

እነኢትኤል አጠገባቸው ሲደርሱ ካገነበሱበት ቀና አሉ፤ ቶላ እየሳቀ ሄዶ አቀፋቸው፡፡ እሱን አቅፈው ሰላም ካሉት በኋላ "አካም ያ ቄሮ፤ ቶላና ጓደኞቹ፡፡" ብለው ተነስተው ሁሉንም በየተራ አቀፏቸው፤ ለጥቀውም…

"እስኪ ከእናንተ ግጥም ማንበብ የሚወድ ማነው?" አሉ፤

"እኔ"፤ አለ ኢትኤል… አቦ አራርሳም ከተደገፉት ዛፍ ግንድ ስር ያለውን ሳጥን ከፈቱ፤ ከውስጡም አንድ መፅሐፍ መዘው አወጡና ለኢትኤል ሰጡት፡፡ ኢትኤልም የመፅሐፉ ሽፋን ላይ ያለውን የፃህፊውን ስም አየና ፈገግ አለ፡፡ በጣም የሚወዳቸውና የሚያደንቃቸው ገጣሚ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ስም በደማቁ ተፅፎበታል፡፡ አጥፈው የሰጡትን ገፅ ገለጠና ማንበብ ጀመረ፤

*✍ ርቱእ ጀምዓ - ብፁዕ ጀምዓ … ለካ አንተ ነህ*

*አባ ገዳ ኢልመ ገልማ - ያዳ አሮሞ ሻማ*\
*ዋቃ ገዷኒ - ነማ አሊኒ*\
*ሱማ አከሱማ - የተሰኘው እንደ አክሱማ*\
*የተባልከው ፍፁም ጀምዓ - ለካ አንተ ነህ፤*\
*አገኦ…ጋ - ጂገሎ…ጋ - አባ ሰርዳ - አባ ገዳ*\
*አባ ፈርድ ነበልባሉ - ቅድመ አሪት ባህሉ*\
*ያኢ ቢያ አባ ቃሉ - ቃሉ የማይቀለበስ ቃሉ… ለካ አንተ ነህ፤*\
*ሴራት አርካ - አገ ገዳ - የኢድባር ዋርካ!*\
*ያዴ እናቴ - ያዴ እሴቴ - ያዴ አቴቴ - ያዴ ሰቴቴ*\
*የአቴህ ሆራ የኩሽ ነዶ - አባ ቦኩ አከ ሚዶ*\
*በአናትህ ከለቻ - የምትጠልቅ አንተ ብቻ*\
*የካን ኢድ ኢዶ ምድር - ተነባቢ የአሰር ሚስጥር*\
*አባ ወሮ አባ ወራ - አባ ባሮ አባ በራ - አባ ካሮ አባ ካራ፡*\
*የጅቡቲም ጀበ ጂሾ - የመቀ ዲሾም መቀዲሾ፡*\
*የነሙቴሳም ካምባላ እንደብራሾ ካምፓላ*\
*መን-ደላ አከ ማንደላ - መቁደላ አከ መቅደላ - የፉላኒ ካኖ ደላ፡*\
*የምትሰኝ የምታሰኝ…*\
*የነና ቤት አባ ወራ - የላሊቤት ላሊ በራ - የከረዩ አባ ከራ*

*በጎፈሬህ ስሪት ላባ አዶ አዶዬ ውብ ቀዘባ*
*አዳ የከለቻ ተሸላሚ*
*የአዱ ግንባር ተቀዳሚ*
*የአዲስ ዘመን መፀው ኢደይ*
*አዳ አዱኛን እልል እሰይ የምታሰኝ የምትሰኝ… አዱ አዱኛ*
*አባ ቢሌ የአካ ኪሌ… የአባ ቢሌ - ለካ አንተ ነህ!*

*ገዳ ገዳም - የዓለም ሰላም!*
*ገዳ ቢሊሱማ ሳቃ - ፈከ ጉራቻ አከ ዋቃ*
*የፀሐፍት ኣምላኩ አኒ - ያለበሰህ ድርብ ካኒ!*
*የጥቁር ፈረያን ልሳን - የአዴ አዳ ጸሐይ ብርሃን*
*የአዱሊስ አዱኛ ኪዳን*
*አባ ገዳ - አባ በዓል*
*የቅድመ አከሱማይት ቃል - የአስርቱ በሮች መሰላል*
*የማለዳ ንጋት ፀዳል - የአኑስ አሪሳ ተምሳል - ለካ አንተ ነህ!*
*አገ ኢ…ጋ - ጂገ ሎ…ጋ፥*
*ያ ኢ ቢያ! አባ ቃሉ - ቃሉ የማይቀለበስ ቃሉ፤*
*ርቱዕ ጀምዓ - የተባልከው አገሱማ እንደ አከሱማ!*
*ያደ ኦሮማ ሻማ - አባ ገዳ ኢልመ ገልማ - ለካ አንተ ነህ።*
*…………………………………………………… (1964 ዓ.ም፤ ድሬ ሊበን)*

…ተመስጠው ሲያዳምጡ የነበሩት አቦ አራርሳ ግጥሙ እንዳለቀ መፅሐፉን ተቀበሉትና ወደቦታው መለሱት።

"ይህን ግጥም ስሰማው ለእኔ ከአቦ አራርሳ ኢልመ ገልማ ኣባ-ገዳ የተፃፈ ይመስለኛል።" አሉና ሳቁ፤ አከውም፤ "በሉ አንድ አንድ ጡብ ያዙና ቁጭ በሉ።…

እና እንዴት ነህ ቶላ በደንብ ተሻለህ?"

"አዎን፤ ገለታ ዋቃ ደህና ነኝ…" ቶላ ፈገግ ብሎ መለሰ።

"እንግዲህ ቶላ፣ የቢሊሱማው ነጻነት ወዳጅ ደህና ከሆነ እኔም ቶሎ ላጫውታችሁና ልሸኛችሁ። በነገራችን ላይ ሼህ ከድር እንዴት ናቸው?… አርጅተዋል መቼስ አሁን አይደል?"

"ደህና ናቸው፤ ብዙም አርጅተው ደከመዋል የሚባል ሁኔታ ውስጥ አይደሉም።" አለ ኢትኤል፤ ሁሉም እንደተቀመጡ።

"ያን የመሰለ የግመል ወተት እየጠጣ ምን ይሆናል እሱማ!" አሉና ፈገግ አሉ፣ አቦ አራርሳ:: "ለማንኛውም ዛሬ ከእኔ የምታገኙት 3 አጫጭር ገለፃዎችን ነው:: ከጥንቱ የሱባ ቋንቋ የተወለደው የኦሮሞኛ ቋንቋ ተናጋሪ ብሆንም ሁላችሁም እንዲገባችሁ ወንድሙ በሆነው የአማርኛ ቋንቋ መግለጫዎቼን እሰጣችኋለሁኝ:: እንግዲህ የመጀመሪያው ገለፃ ማን ነበርን? የሚለውን ጥያቄ የሚያብራራ ሲሆን ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ሁለተኛው ገለፃዬ ለምን ከከፍታችን ዝቅ አልን? ወደ ሚለው ምክንያት ይወስደናል:: እነዚህን ከጨረስን በኋላ ደግሞ በመጨረሻ ወደ ፊቱ እንመለስ! ወደሚለው የመፍትሔ ሃሳብ እንሄዳለን ማለት ነው::" አሉና ገለፃዎቹን ለመጀመር ራሳቸውን አመቻቹ::

"ለመሆኑ ቶላ ባለፈው የጠየኩህን የስምህን ትክክለኛ ትርጉም አወቅኽ? ይህቺ ያሰርካት የአዳችን፣ የአድባር ዛፍ ትርጉምስ?" አሉት ትክ ብለው እየተመለከቱት፤ ቶላ አላወኩም በሚል ሃፍረት ተሞልቶ አንገቱን ወደ መሬት ደፋ::

"ግድ የለም አትጨነቅ ልጄ በዋቃ ፍቃድ ማስተዋሉ ካለህ የሁለቱንም መልስ ዛሬ ታገኛለህ::... እሺ እንግዲህ በመጀመሪያ ‹‹ማን ነበርን?›› የሚለውን ገለፃ ልንገራችሁ:: እኛ ለሄኖክ መጀመሪያ ከወረደለት የሱባ ቋንቋ ሱባውያን ከተባልንበት ጀምሮ እስከ ኖኅ ልጅ ኩሽ ልጆች ዛዮናውያን፣ ግዮናውያን፣ ሳባውያን፣ መዳውያን፣ አቢሲኒያውያን፣ ቴስባውያን፣ አምናውያን፣ አምራውያን፣ ከሁሉም በላይ የምንወደውን ‹‹ኢትዮጵያዊያን›› የሚል የከብር ስም አምላካችን ሲሰጠንም መልከ ብዙ፣ ባለ ቱባ ባህል፣ ባለ ብዙ ታላላቅ ስሞች ባለቤት የሆንን ህዝቦች ነን::

"ይህም ታሪካችን በዚህች አሁን ባለንባት ኢትዮጵያዊ አባቶች እንደተደረጉ ብዙ ተጨባጭ የቅርስና የብራና ማስረጃዎች በብዙ ሙዚየሞችና ገዳማት ተቀምጠው ይገኛሉ:: እኔ ደግሞ በስነ-ቃልና በቋንቋ የወረስነውን ማስረጃ እነግራችኋለሁኝ::

ከጅምሩ በኖኅ ጊዜ ዓለም በሙሉ በውሃ ከጠፋች በኋላ፣ ምድርን በሞላው ውሃ ላይ ስትዋትት የነበረችው መርከብ ያረፈችበት ደረቅ መሬት የኢትዮጵያ ሰሜን ተራሮች ናቸው ስንል ይስቁብናል:: እኔ ግን ከስሜ ጀምሬ እውነታውን እመሰክራለሁኝ:: ምክንያቱም ‹‹አራርሳ›› ማለት በኦሮምኛ ቋንቋችን ይቅርታ አደረገ ወይም ምህረት አወረደ ማለት ሲሆን፣ መፅሐፍ ቅዱስም የኖኅ መርከብ ያረፈበትና የእግዚአብሔርን ይቅርታና ምህረት በቀስተ-ደመና ያየበት ቦታን **አራራት ተራራ** ይለዋል:: ይህም አራራት ተራራ... **ራህ ራራ**... የፈጣሪ

**መራራት... አራርሳ ተራራ** እንደ ማለት ነው:: **ራህ** ደግሞ የእግዚአብሔር ስም ሲሆን የሕዝነትና ከጭለማ የመውጣት ብርሃን መጠሪያን ይወክላል:: ራራ፣ ራህማ፣ ራማ... ‹‹**ራዛ**›› እንደሚባለው አንበጣ በል አሞራ ፍርሃትን የሚኖድል የፍላፃ **ጣዛ**፣ ራአይ ማለትም **ራህን እይ**፣ ከራህ መገለጥም ተመልከተ፣ **ራሲ**... ራህ-ስር ማለትም የራህ እንደራሴ ሆኖ መዋሃድ፣ **ራማ** ማለትም የ**ራህ-ማ** ሲሆን ፤ ‹‹**ማ**›› የምትለው ፊደል በሳባውያን ቋንቋ በልብ ቅርፅ (♡) የምትወከል የፍቅር መገለጫ ናት:: ልጅ እንደተወለደ ‹‹እ**ማማ**›› ብሎ አፍ እንደሚፈታው ሁሉ፣ የምንወደውን **ማ**ፍቀር፣ **ማ**ድነቅ፣ **መ**ውደድ፣ **መ**ናፈቅ፣ ልብ ቅርፅ ሳባ መሆን የራህን ‹‹**መ**›› **መ**ረዳት፣ **መ**ውደድ፣ **መ**ናፈቅ፣ **ማ**ፍቀር፣ **ማ**በር፣ **መ**ራራት እና ወዘተ ይገልጻል:: "ራሄሎ ደዊያችንን ይፈውሳል!" እንዲል ባላገሩ: **ራህ - ሄሎ**፤ ራህንም እንደማመስገን ነበር::" እሉና ሁሉንም ተራ በተራ ተመለከቷቸው፤ ግራ ተጋብተው ይመለከቷቸዋል::

"እሺ! የገባው ገብቶታልና ወደ ሁለተኛው ማን ነበርን? ገለፃ አልፋለሁኝ:: እኔም የቀደምት ሃይማኖት ምንጭ እንደሆንን ደግሜ እመሰክራለሁኝ:: መዳውያን እንደ **መዳ - ወላቡ** በኦሮምኛችን ‹‹መዳ›› ምንጭ፣ ‹‹ወላቡ›› ም ነፃነት ማለት ነውና፤ እግዚአብሔር ሰውን ከሃጢያት ነፃ አውጪ መንገድ የሚያመነጭብን እንደነበረን አሳውቃችኋለሁኝ:: የጥንቱ የገዳ ስርዓታችን እንደንጉስ ዳዊት አማካሪ ባለራዕይው **ጋድ** ያለ የ**ገዳ** አስራት ነው:: **ገድ** የቀናላቸው፤ መልካም መንፈሳዊ ዕ-**ድል** ያላቸው ገዳ-ማት፣ **ጉዳም - ጉዳ** ታላቅ ሰላም፤ ምዕራባውያንም ወርሰው በእንግሊዘኛው ቋንቋ ‹‹**ጉድ**›› የመልካም ነገር መገለጫ ብቻ ሳይሆን ‹‹**ጋድ**›› እያሉ የአምላክ መጠሪያ እስከ ማድረግ የደረሱበት እውነታ ነውና::

እነሆ! ከአዳ ሰፊ የ‹‹**ዣ**›› **ዋ** - ርካ ፤ እንደ ‹‹**ዣንጥላ**›› በተዘረጉ ቅርንጫፎች፤ የ‹‹**ዣ**››**ን**›› -ጥላ ስር፤ የአድባር ዛፍ ስር የሚደረግ የአምልኮ ተግባር፣ አንዱን የበላይ አምላክ በዛፏ ቅርፅ በተፃፈችው ፤**ዋ-** ላይ ‹‹ቃ››ን ጨምረን ‹‹**ዋቃ**›› ብለን ስንጠራው እሱም ጥበብና ዕድቅን ላከልን:: ብዙ **ነቢያት** ማለትም **ኑ-ቢያት** ፤ ባለ ራዕይዎችና ካህናት ከውስጣችን አወጣ:: ሰሎሞን በመጽሐፈ-ነገስት ቀዳማዊ ‹‹እግዚአብሔር፤ ‹‹በጨለማው ውስጥ እኖራለሁኝ›› ብሏል:: ***(8:12)*** ብሎ ሳይጽፍ በፊት እኛ ‹‹**ዋቄ ገራ ጉራቻ**›› ብለን ዋቃ በገለጠልን ጥበብ መሰረት እግዚአብሔር በጥቁሩ ጭለማ እንደሚገኝ እናምን ነበር:: የፈጣሪያችን ማንነት ከብርሃን ብቻ ሳይሆን

በጭለማ ውስጥ የሚገለጥ ሚስጥርም እንደሆነም ተረድተን ነበር:: ይህም በመጻሐፎቻችሁ በነጭ ወረቀት ላይ ያለ **ጥቁር ፅሑፍ** እንደሚደምቅ ሁሉ የጥቁርነትን የጠለቀ ትርጉም ይወከላል::" አሉና ከኋላቸው የተሰየመውን ግዙፍ ዛፍ እስከጫፍ ድረስ ሽቅብ አዩት፤ ከነ ሙሉ ግርማ ሞገሱ ልጆቹን እንዳቀፈች እናት ሁሉንም አካበ ቁልቁል ያያቸዋል::

"ይህን ዛፍ ከችግኝነት መሬት አንስቶ አሳድጎ ታላቅ አድባር ያደረገ ፈጣሪ የቀላል ጥበበኛ እንዳይመስላችሁ!" አሉና እነኢትኤልን ተመለከቷቸው:: "እናንተማ የአውሮፓውያን ሳይንስ ስላነበባችሁ እኛ ያልተማርን አባቶቻችሁ እውቀት አልባ እንመስላችኋለን:: ነገር ግን ለኛም የጥበብ ሁሉ ምንጭ የሆነው አምላክ ብዙን እውቀት ይገልፅልናል:: የእናንተ ሳይንቲስቶች አቶምና መጠነ ቁስ የሚባለው ነገር በሙሉ ተደምሮ በጠፈር ውስጥ የሚይዘው ቦታ ከ5 ፐርሰንት እንደማይበልጥና ቀሪው 95 ፐርሰንት ምንነቱን ባላወቁት ዳርክ ማተር እና ዳርክ ኢነርጂ ተይዞ እንደሚገኝ ያወቁት በቅርብ ነበር:: በቀጣይነት እየሰፋ ያለው ጠፈርም መስፋፋቱ ወደመበተን እንዳይቀየር አጣብቆ የሚይዘው አንድ ስውር ሃይል እንዳለ ማስተዋል እንኳን የቻሉት በቅርቡ ነው:: እኛ ግን አምላካችን በገለጠልን ጥበብ መሰረት **‹‹ዋቄ ገራ ጉራቻ››** ብለን የእግዚአብሔር ሃይል ከብርሃኑ ይልቅ በስውሩ ጭለማ ውስጥ እንደሚገኝ መስክረናል:: ከሚታየው የላቀ ያልተገለጠ በምንምነት ያለ መንፈስ ዓለምን እንዳቆማት እናምናለን:: ‹‹ኡርጂ ጉሬሳ›› እያልን የከዋክብትን መሞትና ወደብላክ ሆልነት መቀየር ከዚያም ዳግም መነሳት ገልጠናል:: ይህም ስለሃይማኖታችን ቀደምትነትና እውነተኝነት የነገርኳችሁን፣ ‹‹ማን ነበርን››? 2ኛ ገለፃ መዝጊያ ሃሳብ ይሆናል::" አሉና አቦ አራርሳ በትራቸውን እያወዛወዙ ለደቂቃዎች በሃሳብ ተውጠው ቆዩ::

"‹‹ማን ነበርን›› ጥያቄያችን ቋንቋዊ መልስ ማሳረጊያ የማደርገው ሦስተኛ ገለፃዬ ከቦታዎችና መጠሪያዎች ጋር ያለውን መመሳሰል በማሳየት ነው:: የጥንት ግሪካዊ የታሪክ ዘጋቢዎች እንደፃፉትና በካርታዎችም ላይ ተስሎ እንደሚገኘው እስከ ቅርብ የሙቶ ከፈለ ዘመናት ድረስ መላው የአፍሪካ አህጉር ኢትዮጵያ ይባል እንደነበር ማስረጃ ሆነው ተቀምጧል:: የእነዚህ የኤቶጵ ልጅ በሆነው በመደባይ የኦሮሞ ብሔር አባት እና የሱ ልጆች በሆኑ ታላላቅ ነገስታት አፍሪካን ብቻ ሳይሆን እስያና አረብ ሃገራትን በሙሉ አካለን ገዝተናል:: ታሪክን ለማጥፋት ቢጥሩም ይዳፈናል እንጂ አይጠፋምና በተለያየ መንገድ ይገለፃል::

ያኔ ቀደምት አባቶቻችን ሲቆረቁሯቸው ባወጡላቸው ስም አሁንም የሚጠሩ ሃገሮች መኖራቸው ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው:: ለምሳሌ፣ በኦሮምኛ ቋንቋ

‹‹**ቢያ**›› ማለት ‹‹**ሃገር**›› ማለት ሲሆን፤ አሁን ያሉት ሊ-ቢያ (በስተምዕራብ ያለች ሃገር)፣ ዛም-ቢያ የወዛሞች/የቅባት ሀገር፣ ኑ-ቢያ (የኛ ሀገር) ፣ ናሚ-ቢያ (የስርዓት ወይም የሰው ሃገር) ፣ አረ-ቢያ እና ሌሎችም መጥቀስ ይቻላል:: እንዲሁም ኬንያም - ኬኛ - የኛ ማለት እንደሆነ ሁሉ ማሊ፣ ታንዛኒያ ካም-ፓላ፣ ሴና-ጋል፣ ፖርት ኦፍ ጋል- ‹ፖርቱጋል› እያልን ብዙ ሃገራትን መጥቀስ እንችላለን:: ሌሎችም የቋንቋ መወራረሶችን ለመጥቀስ ያህል የእኛን አባት ‹‹**ኤቶዮጵ**›› የክብርና ጥበብ ከፍታ ለመግለፅ ፈረንጆቹ ‹‹**ቶፕ**›› ይላሉ፣ ግሪኮቹ የእኛን ንጉስ ‹‹ዛዮን›› እንደ አምላካ ‹‹ዚየስ›› ብለው ያመልኩታል:: ‹‹ዮ**ቶር**››ን ደግሞ ‹‹**ቶር**›› እያሉ በአፈ-ታሪኮቻቸው ውስጥ እንደ ሌላ አማልክት ያገዝፉታል:: እንግሊዘኛም የዙፋን ‹‹**ትሮን**››፣ የፋኖ ችቦ ‹‹ቶርችና››፣ የጥበብ መግቢያ በር ‹‹**ዶር**›› አድርገው እስካሁንም ቃላቱን ይጠቀሙበታል:: እኛ ‹‹አካም›› ስንል እነሱ ‹‹ዌልካም›› ይላሉ እኛ ‹‹ፈያ›› ስንል እነሱ ‹‹ፋይን›› ይላሉ... ሚስጥሩ ቢጠና ዝርዝሩ እጅግ ብዙ ነው::

ሌላው የገዳና የኦሮሞ መለያ አርማ የሆነው ቀይ ነጭና ጥቁር ባንዲራ ነው:: እነዚህ ቀለማት የሚያሳዩት ለአባታችን ኖኅ የታየውን የምህረት ቃል ኪዳን ቀስተ ደመና ወርሶ ኤቶዮጵ በእናት ኢትዮጵያ ባውለበለባት በአረንጓዴ ልምላሜና ተፈጥሯዊነት፣ በቢጫ ወርቃማ ተስፋና እምነት እንዲሁም በአባቶች ቀይ ደም መስዋዕትነት ምድር ውስጥ በሰላም እየኖርን ራሳችንን በመንፈስና ስጋዊ ህይወት ማላቅን ይወክላል:: ይህም ቅድም እንደነገርኳችሁ በጥቁር ዋቃ የሚሰጥን ጥልቅ ጥበብ እንደ እሳት **ቀይ** በሆነና እስከ ደም መገበር ሊያደርስ የሚያስችል መስዋዕትነትን በመክፈል ወደዚህች ምድር ላይ የሰላም፣ የስልጣኔና የኑሮ ነጭ ብርሃን መፈንጠቅን ያመለክታል:: እነዚህም ብርሃኖች ከዚህች አሁን ካለንባት አሮሞ ከምትባል ስፍራና ከቦረናና ቦረንቱ በመነሳት በዕድቅና በጥበብ የመሩትን ኑባውያንና መዳውያንን ዮቶራዊ ሃይሎች ይወክላል:: አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ባንዲራችንን ከ20 በማያንሱ የአፍሪካ ሀገራት ባንዲራ ሆነው ከማየታችን ባሻገር ይህንን የገዳ ቀይ፣ ነጭና ጥቁር ባንዲራ አባቶቻችን በገዢቸው፤ በአሁኒቷ ኢትዮጵያ አቅራቢያ ባሉ ሃገራት ማለትም በግብፅ፣ በሱዳን፣ በማላዊና በአንጎላ ባንዲራዎች ላይ ተመሳሳይ ቀለማትን እናገኛለን::

ኦሮምኛ ጨፋሪዎች የአንበሳ ጎፈሬ አድርገው ጃዲሜ የሚሉት፣ አርበኞቻችን የአንበሳ ቆዳ የሚለብሱት የድሮ ጥቁር አንበሳ ገዳይ ጀግና ነገስቶቻችንን ጎፈሬና አፍሮ በማሰብ ሲሆን፤ አፍሮዎቹ የሰሜን ምስራቅ ወንድሞቻችንም አፋሮች ተብለዋል:: እነዚህ አፋሮች በቀይ ባህርና በኤርትራ ባህር ዙሪያ በነበራቸው የመርከብ ላይ ንግድ ታላቅ ተደራሽነት ነበራቸው::

ጠቅላላዋ አፍሪካ እስከ ቅርብ መቶ አመታት ድረስ ኢትዮጵያ ትባል የነበረች ቢሆንም አውሮፓውያኑ ቀኝ ገዢዎች የአህጉሪቷን ስም አፍሪካ ያሉት በነዚህ አፋር ወንድሞቻችን ስም በመመስረት ነው:: ከኛው ታሪክ የወጣ ስም ግን አልሰጧትም:: የሚያሳዝነው ግን የእነዚህ ታሪኮች ባለቤትነታችን መዳፈኑ ሳያንስ ከኢትዮጵያዊነት ጋር የጠለቀ መሰረት ያለውን የማህፀኗን ፍሬ ኦሮሞ ህዝብን ከሌላ ሀገር ተሰዶ መጥቶ የተስፋፋ ብሔር አድርገው የሚናገሩ ከንቱዎች መኖራቸው ነው:: ግን አንርሳ፤ እውነትን መደበቅ እንጂ ማጥፋት አይቻለንም::" አሉ ኮስተር ብለው::

የመጀመሪያውን ገለፃ እንደጨረሱ አንድ አንበሣ ጎምለል ጎምለል እያለ ከዛፉ ጀርባ ብቅ አለ:: እነኢትኤል ደንግጠው ከተቀመጡበት ብድግ አሉ፤ አንበሳው ግን በዝግታ መጥቶ ከአቦ አራርሳ እግር ስር ተቀመጠ::

"ቁጭ በሉ... አትፍሩ..." አሉ አቦ አራርሳ የአንበሳውን ጎፈሬ ዳበስ ዳበስ እያደረጉ:: እነ ኢትኤል ልባቸው በከፍተኛ ፍጥነት እየደለቀ ለመሮጥ እያኮበኮቡ ነበር::

"አትረበሹ ይህ አንበሣ ‹ና ንከሰኝ› ብትሉት እንኳን አይነክሳችሁም:: ይልቅ በፍርሃት እየተረበሻችሁ አትረብሹት፤ ቁጭ በሉ!!" አሏቸው ቆጣ ብለው:: ከመርየም በስተቀር ሁሉም በፍርሃት እንደተዋጡ ተመልሰው ቁጭ አሉ:: መርየም ግን ከአብርሃም ጀርባ ተደግፋ ቆመች::

"ቶላ ና እስኪ ወደዚህ?" አሉት አቦ አራርሳ፤

ቶላ ፈራ ተባ እያለ ወደ እርሳቸውና ከእግራቸው ስር ወደ ተጋደመው አንበሣ ተጠጋ:: አቦ አራርሳ መፍራቱን ሲያዩ "ና ቶላ! አትፍራ! ጎፈሬውን ዳብሰው::" አሉት:: ቶላ ግን በፍርሃት ተውጦ እጆቹን ማንቀሳቀስ አልቻለም:: እርሳቸው ቀጠሉ፤

"ቶላ ማንነትህ ውስጥ ያለውን የአንበሣ መንፈስ ጠልቀህ ካወጣህ አንበሣን አትፈራም:: የድሮ አባቶችህ ለምን የአንበሣ ጎፈሬ እንደሚያደርጉ፣ አርበኞች ለምን የአንበሣ ቆዳ እንደሚለብሱ፤ አሁንም ያሉ የኦሮሞ ፈረስ ጋላቢ አባቶች ለምን የፈረሳቸው ኮርቻ ልብስ ላይ የአንበሳ ቅርፆችን እንደሚያኖሩ ማወቅ አለብህ:: ካልነኩት የማይነካ፣ የሚበቃውን ያህል ካገኘ ለነገ ብሎ ሙት እንስሳ የማያሳድር ግርማ ሞገስ ያለው አንበሳ ህዝብ ነበርንና ነው::" አሉና ትክ ብለው ቶላን ተመለከቱት፤ ወዳያው ከተደገፉት ዛፍ ስር የነበረውን ሳጥንም ከፈቱና ሌላ ገዘፍ ያለ መፅሐፍ አወጡ:: መጽሐፉንም ለቶላ ሰጡት:: ቶላ መጽሐፉን ተመለከተው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ነበረ:: "ከፈትና መጽሐፈ መሳፍንት ምዕራፍ 10 ቁጥር 1 እና 2ን አንብብልን!" አሉት:: ቶላም ማንበብ ጀመረ፤

"(1፤) ከአቤሜሌከም በኋላ ከይሳኮር ነገድ የሆነ የዱዲ ልጅ፣ የፎሖ ልጅ ‹‹ቶላ›› እስራኤልን ለማዳን ተነሣ፤ በተራራማውም በኤፍሬም አገር ባለችው በሳምር ተቀምጦ ነበር።" ብሎ ቁጥር አንድን ካነበበ በኋላ ስሙን በማየት ደንግጦ በድጋሚ ለማረጋገጥ አነበበው:: እርግጥም ቶላ የሚለው ስሙ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀሱን አያውቅም ነበር:: ራሱን አረጋጋና ስለቶላ በደንብ አውቅ ይሆናል ብሎ ጥቅሱን ማንበቡን ቀጠለ:: ከስር ያለውን ጥቅስ አነበበ::

"ነገር ግን ቁጥር 2 ላይ "በእስራኤልም ላይ (ቶላ) ለሀያ ሦስት ዓመት ፈረደ፤ ሞተም፥ በሳምርም ተቀበረ።" ይልና የሱን ታሪክ ዘግቶ በቁጥር 3 ወደሌላ ታሪክ ያልፋል:: በጥያቄ እንደተሞላ መጽሐፍ ቅዱሱን ዘግቶ ለአቦ አራርሳ መለሰላቸው::

"አዎ አውቃለሁኝ፤ ውስጥህ የተፈጠረውን ጥያቄ የሚያጠፋ መልስ እንዳላገኘህ:: ግን እመነኝ የ‹‹ቶላ›› ማንነት እንደአንበሳ ጥልቅ ነው:: እነሆ በኦሮምኛው ቋንቋ ቶላ ማለትም ነፃ አውጪና ሃገርን ከጥፋት አዳኝ ንጉስን ይገልፃል:: በእኛ ዘንድ ባሉ መዛግብትም በተለይ በወርቅና እንቁ ማንጠር የረቀቀ እውቀት የነበረው ሰው እንደ ነበረ ተዘግቧል:: መጽሐፉም እኔ ዘንድ ይገኛል:: እንግዲህ ይህ ማንነታችንን አለማወቃችን ወደ ሁለተኛው ገለፃ የሚያስፈልገው ‹‹ለምንስ ዝቅ አልን?›› ወደሚለው ጥያቄያችን ይወስደናል::" አሉና ከተኛው አንበሣ ጎፈሬ ላይ እጃቸውን አንስተው በሁለት እጃቸው በትሩን ይዘው ንግግራቸውን ጀመሩ:: .

"እንደነገርኳችሁ የገዳ ስርዓታችን፤ ይህቺ የአድባር ዛፋችን በእ/ር ዘንድ በተቸረን ስርዓትና ወግ የምንመራባት የጥበብ መንገድ ነበረች:: ነገር ግን ሰይጣን ሁሌም ቢሆን የእግዚአብሔርን ህዝብ ከመፈተን ወደኋላ ብሎ አያውቅም:: በግልፅ ከሚፈጥረው ፈተና በላቀ ደግሞ በመሰሪነት የሚያስቀምጥልንን ስውር ወጥመድ ለማለፍ ይበልጥ የሚከብድ ነው:: ይህንን ወጥመዱን ቀድመን ለማየት አይነ ልቦናችንን ከፍተን በንቃት ካልተጠባበቅነው ደግሞ ያስተናል::
እናም ቅድም ከነገርኳችሁ ታላቅነት ዝቅ እንድንል ካደረጉ ዋና ዋና የአባቶቻችን ስህተቶች መካከል 3ቱን እገልፅላችኋለሁኝ::

1ኛ፤ ጥንት የነበሩ መዳውያን አባቶች በገዳ ስርዓት ሲገዙና በአድባር ዛፍ ስር አምልኮ ሲፈፅሙ፣ በውሃ ዙሪያ ኢሬቻንም ሲያካሂዱ አንዱን የዓለማት አምላክ እግዚአብሔርን አስበው ነበር:: **ገዳ** ማለት ስርወ ቃሉ **ካ-አዳ** ነው፤ ‹‹ካእ›› ማለት እግዚአብሔር ማለት፤ ‹‹አዳ›› ደግሞ ስርዓትና ወግ ነው::

የዛፉ ፈጣሪ፣ የውሃው አፍሳሽና ሁሉን አድራጊ እንድ ‹‹ዋ-ቃ›› ወይም ‹‹ዋ-ካ›› እንደሆነ ያምኑ ነበር:: ነገር ግን የእነርሱ ልጆችና የልጅ ልጆቹ እውቀትን እያጡ፣ በሰይጣን ውስወሳ ተሸውደው ፈጣሪን ሳይሆን ፍጡሩን መለማመን ያዙ:: ቀስ በቀስም የዛፉን ፈጣሪ ከማምለክ ዛፉን ወደ ማምለክ ከፉ ልማድ ተቀየሩ:: እነዚህ ወደ ስህተት የገቡ አባቶቻችን ባለማወቅ ዛፉን ቂቤ ያጠጡትና በሬና በግ እያረዱም ደም ይቀቡት፣ ይሰግዱለትና ይለማመኑት ጀመር::

2ኛ፤ ጥንት አባ-ገዳዎቻችንን እና ንጉሶቻችንን ስንሾም የነበረንን ስርዓት አበላሽተን በጉልበትና በብልጠት የሚነግሱ፤ ከዚያም ከኛ እውቀትን በቃረሙ ምዕራባውያን ስርዓት የሚገዙ መሪዎች መጡ:: ብዙ የታሪክ ሰዎች ባደነቁት የፍትህ እና መንግስታዊ ስርዓታችን መሰረት ጥበብና ስነ-ምግባር ያለው የሃገር ሽማግሌ የሰፈሩ ተወካይ ይሆናሉ፤ ከዚያም እነዚህን መሰል የየሰፈሩ የተከበሩ አባወራዎች እየተገናኙ ከእነርሱ መካከል በስነ-ምግባር፣ እውቀትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለውን ነበር ሀገር እንዲመራ የሚያነግሱት:: ታዲያ ይሄ ውብ የፍቅርና የሰላም አመራራችን እንደዋዛ ተረሳ:: በዚህ ዘመን በባእዳን አስተምሮ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ስርአት ዘረጋን በብሔርም መደራጀት ላይ በማተኮር ብዙ ስህተት ተሰራ::

3ኛ፤ የብርሃን ከለቻ የሆነውን ግንባራችን ላይ የምናስረውን የጥበብ መገለጫ የወንድ ብልት ቅርፅ ተምሳሌት ነው ማለታችን ሳያንስ፣ ሲሄዱና ሲመጡ ‹‹አክሱማ›› እየተባባሉ በመንፈስ ምጥቀት የሚጓጓዙበት የነበረውን ‹‹አክሱም›› በወንድ ብልት አምሳል የተሰራ ሀውልት ነው ብለን ካድን:: አሁን እንኳን በቴክኖሎጂ ማቆም ያቃተንን ትልቅ የጥበብ ውጤት አራከስን:: እናንተን በደፈናው ይህ የአክሱም ሰንፔር ነሐስ ታላቅ መጓጓዣ እንደነበረ ብነግራችሁ ለማመን እንደሚከብዳችሁ አውቃለሁኝ:: በሩም የተዘጋ ተራ ድንጋይ ሊመስላችሁ ይችላል:: በሩ ግን የሚከፈተው በእጅ ሳይሆን በንቃተ ህሊናና በጥልቅ መንፈሳዊነት ነው::" አሉና ደግመው መፅሐፍ ቅዱሱን አንስተው ለአብርሃም የእጅ ምልከት በማሳየት ጠሩትና ሰጡት፣ "እስኪ ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ አንድ ከቁጥር 12 ጀምረህ እስከ 19 አንብብልን፤" አሉት፤ አብርሃምም በታዘዘው መሰረት መፅሐፍ ቅዱሱን በጥንቃቄ ተቀብሏቸው ማንበብ ጀመረ…

*12፤ እያንዳንዱም ወደ ፊት ቀጥ ብሎ ይሄድ ነበር፤ መንፈስም ወደሚሄድበት ሁሉ ይሄዱ ነበር፥ ሲሄዱም አይገላመጡም ነበር። 13፤ በእንስሶቹ መካከል እንደሚነድድ የእሳት ፍም ያለ ምስያ ነበረ፤ በእንስሶች መካከል ወዲህና ወዲያ የሚሄድ እንደ ፋና*

*ያለ ምስያ ነበረ፤ ለእሳቱም ፀዳል ነበረው፥ ከእሳቱም መብረቅ ይወጣ ነበር። (14፤ ) እንስሶቹም እንደ መብረቅ ምስያ ይሮጡና ይመለሱ ነበር። (15፤) እንስሶችንም ስመለከት፥ እነሆ፥ በአራቱ እንስሶች አጠገብ በምድር ላይ አንድ አንድ መንኰራኵር አየሁ። (16፤) የመንኰራኵሩም መልክ እንደ ቢረሌ ነበረ፤ አራቱም አንድ አምሳያ ነበሩ፤ ሥራቸውም በመንኰራኵር ውስጥ እንዳለ መንኰራኵር ነበረ። (17፤) በአራቱ ጐድናቸው ይሄዱ ነበር፤ ሲሄዱም አይገላመጡም ነበር። (18፤) ቁመታቸውም የረዘመና የሚያስፈራ ነበረ፤ የአራቱም ክበብ ዙሪያው በዓይን ተሞልቶ ነበር። (19፤) እንስሶቹም በሄዱ ጊዜ መንኰራኵሮቹ በአጠገባቸው ሄዱ። እንስሶቹም ከምድር ከፍ ከፍ ባሉ ጊዜ መንኰራኵሮቹ ከፍ ከፍ አሉ።"* ... ብሎ ጨረሰ፡፡

"እንግዲህ ይህ ጥቅስ የሰንፔር ከፍ ተደርገው የተሰሩ አክሱሞችን እንደሚወክሉ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ እንደመንኮራኩርም ይመስላቸዋል፡፡" አሉ አቦ አራርሳ፤

"ግን አራቱ እንስሳዎች ማናቸው?" አለ ኢትኤል የተፈጠረበትን ጥያቄ እየገለጠ፤

"እሱን ባህታዊው አጎትህ ይነግሩሃል፡፡"

"ማ... ማን አሉኝ? የት ነው እርሳቸውንስ የማገኘው?" አለ ኢትኤል በጉጉት ተሞልቶ፤

"ሼህ ከድር በቅጡ ስለ ትዕግስት ያስተማሯችሁ መስሎኝ ነበር፤ ለማንኛውም ሁሉም በጊዜው ይደርሳል፡፡ ግን የጥቅሱን አክሱምነት የሚያጠናክር፤ መጓጓዣነቱን የሚያሳይና ኢትዮጵያ ውስጥ ይገኝ እንደነበር የሚጠቁም ሌላ ጥቅስ አንብብላቸው አብርሃም፡፡ ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 3 ከቁጥር 10 እስከ 15 ጮክ ብለህ አንብብለን" አሉት፤ ጀመረ... "(10፤) እርሱም። የሰው ልጅ ሆይ፥ የነገርሁህን ቃሌን ሁሉ በልብህ ተቀበል በጆሮህም ስማ። (11፤) ተነሥተህም ወደ ተማረኩ ወደ ወገንህ ልጆች ሂድ፤ እነርሱም ቢሰሙ ወይም ባይሰሙ። ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ብለህ ንገራቸው አለኝ።(12፤) መንፈስም አነሣኝ፥ በኋላዬም። የእግዚአብሔር ክብር ከቦታው ይባረክ የሚል የጽኑ ንውጥውጥታ ድምፅ ሰማሁ። ( 13፤) የአራቱም እንስሳ ክንፎች እርስ በርሳቸው ሲማቱ፥ በአጠገባቸውም የመንኰራኵሮችን ድምፅ፥ የጽኑውንም ንውጥውጥታ ድምፅ ሰማሁ። (14፤) መንፈስ አንሥቶ አስወገደኝ፥ እኔም በምሬትና በመንፈሴ ሙቀት ሄድሁ፥ የእግዚአብሔርም እጅ በላዬ በርትታ ነበር። (15፤) በቴልአቢብም ወዳሉ በኮቦርም ወንዝ አጠገብ ወደ ተቀመጡ ምርኮኞች መጣሁ፥ በተቀመጡበትም

ቦታ ተቀመጥሁ፤ በዚያም ሰባት ቀን በድንጋጤ በመካከላቸው ተቀመጥሁ።" ብሎ ለሁሉም እንዲሰማ ከፍ አድርጎ አነበበና አብርሃም መጽሐፍ ቅዱሱን መልሶ ተቀመጠ፡፡

"በዚህ ጥቅስ ላይ በደንብ እንዳያችሁት ትንቢቱን የሚናገረው ሕዝቅኤል ከአከሱም ወደ ሃገሩ ቴል አቢብ በመንፈስ ተመንጥቆ ሲሄድ ያሳያል፡፡ ታዲያ ይህንን የመሰለ ታላቅ ንውጥውጥታ ይፈጠርበት የነበረን የጥበብ ምሳሌ ከወንድ ብልት ቅርፅ ነው የተሰራው ማለታችን ቅጥፈት ነው፤ የትኛውስ የወንድ ብልት ነው መስኮትና በር ያለው?!... የሚገርመው እኮ በጊዜ ሂደት የእኛ አላዋቂነት ይበልጥ በርትቶ፤ ሃውልቱን የወንድ ብልት ቅርፅ ነው ከማለት አልፈን የሃውልቱን ፈጣሪ ማስተዋል ተሳነን፤ ዛፉን እንጂ የዛፉን አብቃይ ረሳን፤ የሚወዳቸው የነበረ አምላካቸውም በስራቸው ተቆጣ፣ ቅጣትም አወረደና ዓለምን የገዛንበት ታላቅ ስልጣኔያችንን በአንድ ሌሊት አጠፋው፡፡" አሉና አቦ አራርሳ በሃዘን ስሜት ወደ መሬት አጎነበሱ፡፡

*"ነገር ግን እግዚአብሔር ህዝቡን ቢቆጣም አይጨከንበትምና አሁን ደግሞ **‹‹ወደፊቱ እንመለስ››** የሚለውን ሦስተኛ ገለፃ ልስጣችሁ፣ መፍትሔውንም ስለምገልፅላችሁ አድምጡኝ፡፡ እንደ ወተት የሚጣፍጥ ራዕይ የሚናገረውን የአናኒን ስም ከጠቀሱት ጥቂት ጥቅሶች መካከል ህምምም... እስኪ ልጅ አብርሃም ከመጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ ከቁጥር 5 ጀምሮ አንብብልን፡፡"*
*አብርሃም ከማውጫው ላይ ምዕራፉንና ቁጥሩን አውጥቶ ንባቡን ቀጠለ፡፡*

"(5፤) ባኦስም በሰማ ጊዜ ራማን መሥራት ተወ፥ ሥራውንም አቋረጠ። (6፣) ንጉሡም አሳ የይሁዳን ሰዎች ሁሉ ሰበሰበ፤ ባኦስ ይሠራበት የነበረውን የራማን ድንጋይና እንጨት አስወገዱ፥ እርሱም ጌባንና ምጽጳን ሠራበት። (7፣) በዚያን ጊዜም **ባለ** ራእዩ አናኒ ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ አሳ መጥቶ እንዲህ አለው። በሶሪያ ንጉሥ ታምነሃልና፥ በአምላክህም በእግዚአብሔር አልታመንህምና ስለዚህ የሶሪያ ንጉሥ ጭፍራ ከእጅህ አምልጦአል። (8፤) ኢትዮጵያውያንና የልብያ ሰዎች እጅግ ብዙ ሰረገሎችና ፈረሰኞች የነበሩአቸው እጅግ ታላቅ ጭፍራ አልነበሩምን? በእግዚአብሔር ስለ ታመንህ በእጅህ አሳልፎ ሰጣቸው፥ (9፤) እግዚአብሔርም ልቡ በእርሱ ዘንድ ፍፁም የሆነውን ያፀና ዘንድ ዓይኖቹ በምድር ሁሉ ይመለከታሉ፡፡ አሁንም ንጉስ አሳ ስንፍናን አድርገሃል፡፡ ስለዚህም ከዚህ በኋላ ጦርነት ይወርስሃል፡፡"

"ይህ ጥቅስ ከላይ ሲያዩት ኢትዮጵያን በአሉታዊ መንገድ የሚያነሳ ቢመስልም በባለራዕዩ አናኒ አፍ ግን አንድ ታላቅ መልዕክት ተላልፏል፡፡ ይህም ማንኛውም ህዝብና ንጉስ ለፈጣሪው ከታመነና በጎ ከሰራ እ/ር

እንደሚያልቀው፣ በተቃራኒው ደግሞ ካፈነገጠ እንደሚቀጣው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር አሸናፊ ያደረገው ህዝብም ታዛዥ የማይሆን ከሆነ እንደሚያጠፋው ይመሰክራል:: እናም በኛ ላይ ገዝፈው የሚታዩ መንግስታት ከእ/ር መንግስት አፈንግጠው ከወጡ ምርኳቸው ለእኛ እንደሆነ ማወቅ አለብን::

ለዚህም ነው የዚህ ዘመን ወጣቶች ለለውጥ የተመረጣችሁት:: ተስፋና እምነታችን እዚህ ትውልድ ላይ ታላቅ ነውና:: ይህ የቁሮና ቃሮ ትንታግ ትውልድ ከግምት በላይ ሆኖ ኢትዮጵያን ወደቀድሞ ክብሯ እንደሚመልሳት እናምናለን:: ልጆቼ መፍትሔው አንድነት፣ እምነትና ተግባር ነው::" አሉና ሁሉንም አንድ በአንድ ከተመለከቱ በኋላ ቆላን እያዩ ንግግራቸውን ቀጠሉ::

"ቄሮ ቆላ የአንተና የሌሎች እልፍ ኢትዮጵያውያን መሰዋዕትነት ለከንቱ እንዳልሆነ እወቅ! እንደጥንታዊ አባቶቻችሁ ብቻ ሳይሆን በቅርብ ዘመናት እንደተነሱት የጦር ጀግኖች ብ/ጄነራል ታደሰ ብሩ፣ መብረቁ ጄነራል ጃገማ ኬሎ፣ የጣሊያን የእግር እሳት ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ያለ ኢትዮጵያዊ ወኔ ታጥቃችሁ ተነስታችኋልና:: እመኑኝ ብላቴናው ቴዲ አፍሮ "ንቃ በመንፈስ ለአንድነት ካሳ ተነሳ!" ብሎ እንደዘፈነው ቶዌድሮስ በኢትዮጵያ ይነግሳል::ከሙስሊም አባት ይወለዳል የተባለው የትንቢት ቃሉ ይፈፃማል:: በዚህ የፍቅር፣ ይቅር ባይነትና አንድነት አገዛዝ ውስጥ ማንነታችንም ዳግም ይነግሳል:: አሁንም እምነትና ጥበቡን ካገኘን እንደአከሱም ጊዜ ከአይን ጥቅሻ ፍጥነት መጓዝ የማንችልበት ምንም ምክንያት የለም።

ዋናው ለስኬትና ፍቅር መጠበቅ ያለብን ደግሞ የአንድነታችን መሰረት የሆኑ ባህሎቻችንን ነው:: ምክንያቱም አንድነት ማለት መንፈሳዊነት ማለት ነው::

አሁን ተቀምጠን የምናወራባት ቦታ ‹‹**ወሎ**›› ራሷ ትርጉሟ አንድነት እንደማለት ነው:: ‹‹**ወል**›› የሚለው ቃል ምንጩ የጥንት አባቶቻችን የኩሼቲክ ቃል ሲሆን unity ከወል-አጋ (ታላቅ አንድነት)፣ ወል-ቂጤ (አንድነት በእኩልነት)፣ ወል-ይታ (የእውነት አንድነት) ፣ ወል-መራ (የአንድነት መረብ) ፣ ወል-ዲያ (በገጠር ያለ አንድነት) ፣ ወል - ቃይት (የፀና አንድነት) ፣ ወል-ኢሶ (የአንድነት አድራሻ) እና ሌሎችም ብዙ ሀገሮችን መጥቀስ ይቻላል:: ይህም ‹‹ወል›› የሚል ታላቅ ቃል ልክ ‹‹ውል›› ተፈራርሞ በጋብቻ እንደመኖር ያለ፤ ሁሉንም የማቀፍ የአንድነትና የህብረት አመልካች ቃል ነው:: ለዚህም አንድነት ፍቅር ‹‹ወልይ›› ‹‹ሁሉ››ንም መያዝ (Wholeness ፣ Wellness) ‹‹ዌልነስ›› እና ‹‹ሆልነስ›› ደግሞ የመንፈሳዊነት (Holyness) <<ሆሊነስ>> መግለጫ እንደሆነ እንወቅ::

እናም ይህንን ታላቅ አንድነታችንን አስሮ የያዘው እፁብ ድንቅ ባህላችንን እንንከባከበው:: ምክንያቱም የገዳ ስርዓት ክብር ካጣ የኢትዮጵያም አንድነትና ክብር አደጋ ውስጥ እንዳለ እንወቅ:: የአማራ ነበዝ አለቆች ሲሰንፉ አማራ ብቻ ሳትሆን ኢትዮጵያም እንደደከመች እንረዳ:: የትግሬዎች አባይቲ አዲዎች አንድነትን ማስከበር ካልቻሉ ችግር እንደሚከሰት እንገንዘብ:: የጉራጌዎች እጅን ደገፍ ብሎ የተቀመጠ አሳቢ ሰው የምትመስል ዛፍ ስር ያለን ‹‹የጆካ›› ስርዓት፣ የሲዳማ ‹‹አፊኒ›› ስርዓት፣ የሃዲያ ‹‹ሴራ›› ስርአት እና የመሳሰሉት ውብ ውብ ባህሎቻችን በጥልቅ መመርመር፣ እንደ አይኖቻችን ብሌኖች መጠበቅና የሚገባቸውን ክብር ማግኘት አለባቸው:: *የእኛ ንጉሥ እስያኤል ሌሎች ሃገራትን ሲያስገብሩ የመሰረቱት ሂንዲዩዝም ሃይማኖት ያፈራቸው እነ ዳሌ ላማ፣ ጉሩጂ፣ ስሪ ስሪዎች ዓለም አቀፍ ተደማጭነትን አግኝተው:: የእኛዎቹ ቀደምት አባቶች፣ ለፍቅርና ለሰላም የቆሙ የእኛ መራጌታዎች፣ አባ ገዳዎች፣ የጆካዎችና ሼኾች በሀገር አቀፍ ደረጃ እንኳን ተቀባይነት ማጣታቸው ያሳዝናል::*

...እናም ቄሮዎች፣ቃሮ ፋኖዎችና ዘርማ፣ ይህንን ሙስና፣ ዘረኝነትና መከፋፈል የተጠናወተው አገዛዝ ለመገርሰስ ታላቅ ስራ ሰርታችኋል:: *ሁሉም መንግስት ልማትም ጥፋትም ይሰራል፤ በፍርዱ ሁሉ ፍጹም ደግሞ እግዚአብሔር ብቻ ቢሆንም የአንዳንድ መንግስታት ከፋት [illegible]ግጠንም ያልፋልና የከፈላችሁት መስዋዕትነት ዋጋው ትልቅ ነው:: አሁ[illegible]ም ድሮ የነበረበት የፅድቅናና የተሰሚነት ደረጃ ላይ እንዳልሆንን በማወቅ ለተሻለች ሃገር ተግታችሁ ስሩ::*

*ልጆቼ ስለባህልና ቱፊታችሁ እንዲሁም ስለ ሃይማኖታችሁና ታሪካችሁ ለማወቅ የታሪክ ተመራማሪ፣ ዲያቆን፣ ቀራፊ ወይም ደረሳ መሆን አይጠበቅባችሁም:: እንግዲህ ዛሬ ከእኔ የሰማችሁትን የጥበብ ቃላት በልባችሁ ያኑርላችሁ:: ከእኔም ዘንድ መጥታችሁ ከስሬ ቁጭ ብላችሁ እውቀትን ስለመስማታችሁ ዋቄ ፈታ ያከብርልኝ::" አሉና በዱላቸው መሬቱን ሁለቴ መቱ... "አሁን ደግሞ የጉዟችሁ የመጨረሻ መዳረሻ ወደሆነው ወደ ራማ ገዳም እልካችኋለሁኝ:: እዚያም ባህታዊው አባ ኤልካናን ታገኛላችሁ::"*

*አሉና ከጎን ኪሳቸው አንዲት የተጠቀለለች ወረቀት አውጥተው ለኢትኤል ሰጡት "በቅድሚያ ግን ወደ ወልዲያ ዩንቨርሲቲ ትሄዱና አንድ ፕ/ር አሌ ለሚባሉ ሰው ይህንን እጅግ ጠቃሚ መረጃ የየዘ ደብዳቤ ትሰጡልኛላችሁ:: አደራ ደብዳቤውን ለእርሳቸው ብቻ ማንም ሳየይ ነው መስጠት ያለባችሁ:: በሉ እንግዲህ ሂዱ፤ የተቀረው ጉዟችሁ ይቅናችሁ፣ ከእኔ ዘንድ የነበራችሁ ቆይታ ግን በእዚሁ ያበቃል::" አሉና ከሳጥናቸው መሃከል አንድ በሰም የታሸገ ጥቅልል አውጥተው ሰጧቸው::*

ኢትኤል ጥቅልሉን መልአከት በሃላፊነት ተቀብሎ ሁሉም ተነስተው ጉዞ ሊጀምሩ ሲሉ ቶላ ከተቀመጠበት ሳይነሳ ቀረ::

"ቶላ እንሂድ እንጂ ተነሳ፤" አለ ኢትኤል ዞሮ እያየው፤

"እሱ አይሄድም" አሉ አባ አራርሳ ሁሉንም በአርምሞ እያዩ፤ "አዎ አልሄድም ኢትኤል፤" አለና ቶላም ተቀበላቸው፡ "እዚሁ ከአርሳቸው ጋር ቁጭ ብዬ ስለራሴ ብዙ ማወቅ ያለብኝ ነገር እንዳለ ተረድቻለሁ::" አላቸው::

ኢትኤል፣ አብርሃም፣ መርየምና ናዖድ ቶላንና አባ አራርሳን ተሳንብተው ጉዞ ጀመሩ:: ከአርሳቸው ተለይተው እንደሄዱ ቅድም ያመጣቸው ባለጋሪ ከአካባቢው በቅርበት አገኙትና አሮሞ ተብሎ ወደሚጠራው መንደር ድረስ ሄዱ:: በእጃቸው የነበረው ብር ወደ ማለቁ ቢቃረብም የአባ ገዳውን ትዕዛዝ ለማክበር ወደ ወልዲያ የሚሄድ መኪና ተሳፈሩ:: መኪናቸው ከኦሮሞ መንደር አሮጌ በምትባል የገጠር ከተማ አልፋ ወልዲያ እስከትደረስ ድረስ ኢትኤል የሎሬቱን ግጥምና ከአባው ገዳው የሰማውን የእውቀት ትምህርት እያውጠነጠነ በሚወዳት የግጥም ደብተሩ ላይ አንዲት ግጥም ከተበ:: ርዕሱንም ኩ-ኣዳ አለው...

✍ ኩ-ኣዳ

ያ... ኢዬ አቴቴ
ያ... አደይ እቴቴ - የእናቶች ኩራት
ያ... ኣዳ' ባህሉ - የኑሮ ስርዓት፤
ያ... ገዳ' ድባብ - የሁሉም አባት።
የአምላክ መ̄መሪያ! ቅድሙ-አሪት ህጉ፥
ከበላይ - እንደ 'ጃ' ... ያህዋ
እንደ 'ዣ'-ሀግ... 'ካ'-ኣዳ
ገለታ ለዋቃ!
የሀድያ ዋኣ!
በስዋሂሊ ዋካ!
ምስጋና ይድረሰው ለዓለማቱ ጌታ፤
<ጋደ> ቢሉት ፈረንጆች ገዳምም ሳይገቡ
ገድ እንዲቀናቸው ተውሰው ሊገቡ፤
ጥንት ነው የሰጠው መርጦ ለአባ-ገዳ
የኢድባር ዋርካ ስር - ቅርንጫፉ ሰፊ - መሰብሰቢያ ኣዳ'፡፡

***

*ጥንቆላም አይደለም- የባዕድ አምልኮ*
*የነዮቶር ፍትህ ቶራህ ቀደም ቶኮ*
*የሰማይ ስርአት ነው የአርያም ተልዕኮ፤*
*ካ'ሉ አይለወጡም… ቃ'ሉ አይታጠፍም*
*ያፀናውም ኪዳን ፈፅሞ አይፈርስም፤*
*ለኤቶጵ ልጆች - ኢጆሌ ኦሮሚያ፥*
*ግዙፍ ዣን አምራ - ያ ማራው ተራራ*
*ወንድማማች ህዝቦች - ኦሊቲን ኢትዮጵያ!*

***

*በፅድቅ ተገዝው ታሪክ እንደሰሩ፥*
*ላ'ፎ… ደግ ሰዎች ነቅተው ይነሳሉ*
*እንደጥንቱ ቱፊት፥*
*በፍቅራቸው ሰላም- ዳግም ይገናሉ።*

*** ☥ – ☥ ***

ወልዲያ ዩንቨርሲቲ ገና የወጣትነት እድሜ ውስጥ እየገባ ያለ በቅርብ ጊዜ የተመሰረተ የት/ት ተቋም ነው:: ከአስር ዓመታት በፊት መስረተ ድንጋዩ ተጥሎ ቢመሰረትም በጥቂት ዓመታት ውስጥ እምርታ ማሳየት የቻለ ተቋም ነው:: በተለይ የህብረተሰቡን ሁነኛ ችግሮች ለመፍታት በባህሪይ፣ ባህልን በጠበቀ አኗኗርና አረንጓዴ ስልጣኔ በተሰኘው መርሃ ግብር አመርቂ ውጤቶች በማስገኘቱ ተመስጋኝ ሆኗል:: እነኢትኤል የጅማ ዩንቨርሲቲ መታወቂያዎቻቸውን በሩ ላይ ለሚገኙ ጥበቃዎች አስይዘው፣ እየተፈተሹ ገቡ::

ፐ/ር እሴ የሚባሉ ሰው እንዴት እንደሚያገኙ ማንን መጠየቅ እንዳለባቸው እየተወዛገቡ ሳለ ድንገት አንድ ትልቅ ባነር ከናዖድ አይን ገባ::
አንድ ፂማም ሽምገል ያሉ ሰው ፎቶና ከጎናቸውም በደማቁ
«በፐ/ር እሴ ዳግማዊ የሚሰጥ፤ **‹‹ወደራሳችን እንመለስ››** በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሴሚናር ሁላችሁም እንድትታደሙ ተጋብዛችኋል:: ሴሚናሩ የካቲት 21/ 2010 ዓ.ም ከሰዓት 8:00 ጀምሮ በዋናው ግቢ አዳራሽ ይሰጣል» ይላል፤
እነኢትኤል ጥቅልሉ የተላከላቸው፣ የሚፈልጓቸው ሰው እርሳቸው እንደሆኑ ለማወቅ ብዙ ማሰብ አልተጠበቀባቸውም:: ናዖድ ሰዓቱን ተመለከተ፣ 8:35 ይላል::
"ሴሚናሩ ተጀምሯል ማለት ነው::" አለ ወደ አብርሃም ዞሮ፤

"አዎ ቶሎ ከሄድን እንደርስበታለን፡፡" አለ አብርሃም፤ በቅርብ ያገኟቸውን ተማሪዎች አዳራሹ የት እንደሚገኝ ጠይቀው በተጠቆሙት መሰረት በፍጥነት ወደ አዳራሹ ሄዱ፡፡ ደርሰው ወደ ውስጥ ሲገቡም በወልዲያ ዩንቨርሲቲ ተማሪዎች በተሞላው አዳራሽ ውስጥ ፕ/ር እሴ ንግግራቸውን እያደረጉ ነበር፡፡

"... እናም እንዳልኳችሁ፤ መልካም አስተዳደር የሚመነጨው ከመልካም ስነ-ምግባር ነው፡፡ መልካም ስነ-ምግባር ደግሞ ከልጅነት ጀምሮ በማንነታችን ውስጥ የሚቀረፅ ነገር ነው፡፡ በተለይ አሁን ላይ ያለው የኛ ማህብረሰብ ግን ይህንን የስነ-ምግባር ነገር ችላ ያለው ይመስላል፡፡ አንድ ልጅ አካዳሚክ እውቀቱ ላይ ጎበዝ ከሆነ በቂ ማንነት እንዳለው ይታሰባል፡፡ ነገር ግን የአካዳሚክ እውቀት መስጫ መንገድ ሆኖ የተከሸነውን የት/ት ካሪኩለም ብናይ በሁሉም አቅጣጫ ሙሉ ሰው የመሆን መንገድን የማይጠርግ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ካሪኩለማችን የልጆችን ዝንባሌና ተስጥኦ ከቁብ የማይቆጥር ከመሆኑ ባሻገር በኑሯችን ውስጥ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የህይወት ትምህርቶችን ከግምት ያላስገባ ነው፡፡ ብዙዎቻችን ስለትክክለኛ የኢትዮጵያዊነት ታሪክና ትርጉም፣ ስለ አንድነትና ፍቅር፣ ስለመተማመንና አብሮ መኖር፣ ስለ ግብረ ገብ፣ ስለ ሰብዓዊነት እና መረዳዳት፣ ስለዋና ዋና ቋንቋዎቻችን፣ ስለሃገራችን ነባራዊ ሁኔታና ከእኛ ስለሚጠበቀው ፋይዳ፣ ከሰው ጋር የመግባባት ጥበብ፣ በኑሮ ተብቃቂና ደስተኛ የመሆን ጥበብ ወዘተረፈ ያሉ በእለት ተእለት ኑሯችን ላይ ፋይዳ ያላቸውን እውቀቶች ሳንማር እስከ ፕሮፌሰርነት እርከን እንደርሳለን፡፡ እኔን ጨምሮ..." ብለው በስሱ ሳቁና ንግግራቸውን ቀጠሉ...

"ልብ እንድትሉ የምፈልገው ነገር ግን በህፃናት አዕምሮና አስተዳደግ ላይ መስራት ለአንዲት ሃገር መሚዓ እድል ታላቅ ሚና እንዳለው ነው፡፡ በሃገራችን ጥሩ አስተሣሰቦችን በመትከል ሊጠቀስ የሚችለው የስነ-አዕምሮ ሐኪሙና ደራሲው ምህረት ደበበ እንዳለው "የህፃናት አንጎል ልክ ታሽጎ እንደሚምጣ አዲስ ኮምፒዩተር ነው።" የገዛነው ኮምፒዩተር የምንጭንበትን ነገር ተቀብሎ "ሴቭ" አድርጎ "ፕሮሰስ" እንደሚያደርገው ሁሉ የእኛም ህፃናት በአካባቢያቸው የሚያዩትን፣ የሚሰሙትንና የሚማሩትን ነገር ለቀም አድርገው ከአዕምሮ ማህደራቸው ያስቀምጣሉ፡፡

የፈረንጅ ተከታታይ ፊልም ላይ የጥቁርን የበታችነት ብቻ እያየ፤ አላስፈላጊ የባልቴት ወሬዎችን እየሰማ፤ ወሲብ ቀስቃሽ የቆነጃጂት ድርጊቶችን፤ ስካርንና ሲጋራ ማጨስን ብቻ እየቃረመ ያደገ ልጅ ታላቅ ፈጠራን የሚያገኝ ሳይንቲስት አልያም በህክምናው ዓለም አንቱ የሚባል ሐኪም ይሆናል ብሎ ማሰብ ዘበት

ነው፡፡ በእውቀትና ምግባር ሳይኮተኮቱ በመዝናናት አባዜ ውስጥ ብቻ የሚያድጉ ልጆች የሞሉት ትውልድ የዘቀጠ ማንነት ያለው ህዝብ እንዲኖራቸው ምዕራባዊ ሃገራት ላይ እየተፈጠረ ያለው ቅጥ ያጣ ትውልድ ምስክር ነው፡፡ ለዚህም የጦርነት ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ የጽድቅና ጥበብ ታሪካችንም በካሪኩለሙ ይታቀፍ፡፡ በየደቂቃው አዲስ ነገር በሚመረትበት፣ በየሲኮንዱ እቃዎች ማሻሻያ እየተደረገባቸው በሞዴልና በውበት በሚያሸበርቁበት ዘመን በቁሳ ቁስ ደስታን አገኛለሁኝ ብሎ የሚያስብ ትውልድ መፍጠር እውነትም ዝቅጠት ነው፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ እነዚህ የማብረቅረቅና ከሌሎች ልቆ የመታየት አባዜዎች ዘመናዊ ጣዖቶች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ጣዖት እንደ አምላክ ለዘላለም ዘላቂ አይደለምና፡፡ ዛሬ ተጨብጭቦለት የገዛኸው አዲስ ሞባይል ዓመትም ሳይሞላው ተራ ተብሎ ይናቃል፡፡ ስለዚህ ደስታህን በአልፎ ሂያጅ ቅራቅንቦ ላይ አትትከል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ቁስ-አካል ወይም በራሱ እርኩስ ነው ማለት አይደለም፡፡ ምንም አይነት በዓለም ላይ የሚገኝ ነገር በራሱ ክፉም ሆነ ደግ ሊሆን አይችልም፡፡ የኛ አጠቃቀም፣ ጊዜውና ቦታው ነው ይህንን የሚወስነው፡፡

ለምሳሌ ወሲብን ብንወስድ በሁለት በሚተማመኑ፣ ለይሉኝታ ሳይሆን በእውነተኛ መፈቃቀር ላይ ተመስርተው ለተጣመሩ፣ የቤተሰቦቻቸውን በጎ ፍቃድ አግኝተውም ጎጆ ለመሰረቱ ጥንዶች የፍቅራቸው አካላዊ መገለጫ ሲሆን አንዲትን የ10 ዓመት ልጅ ልጃገረድ እጆች ጠፍንጎ አስሮ በጉልበት ለሚፈፅመው ደግሞ የሃጥያቶች ሃጥያት ነው፡፡ ነብዩም "ሰርግ ላይ ሙዚቀኛ ላኩ፤" እንዳሉትና ቃና ዘ ገሊላ ላይ ጌታ እየሱስ ውሃውን ወደ ወይን ቀይሮ ደስታቸውን እንዳስቀጠለው በሰርግ ቀን መዝፈንና መዝናናት ክፋት ላይኖረው ይችላል፡፡ ቤተ-መቅደስ ውስጥ አልያም ቤተ-መፅሐፍት ውስጥ ገብቶ የሰርግ ሙዚቃ መክፈት ግን እርግጥም ህግን ማፍረስ ነው፡፡

እውነተኛው ደስታ ከልፋትን መድከም በኋላ የሚገኝ የዚህም የቀጣዩም ዓለም ሽልማት እንጂ በብር የሚሸምቱት ቅራቅንቦ አይደለም፡፡ በደም ከተጨማለቀ ስቃይ መሃል ቆንጅዬ ጨቅላ ልጅ እንደሚወጣው ሁሉ ከፈተና በኋላም ታላቅ ሽልማት አለና፡፡ ለዚህም ልፋትና እውነተኛ ደስታን የሚቀዳጅ ጉዞ ቆርጠን መነሳት አለብን፡፡"... አሉና አጎንብሰው የሚያነቡትን ወረቀት እያዩ ለብዙ ሰኮንዶች ቆዩ...

"እናም ወደራሳችን እንመለስ እላችኋለሁኝ፡፡ በቴሌቪዥን ሂፕኖታይዝድ የሆኑ አዕምሮቻችንን በጥሩ እውቀትና በተመስጦ እናዕዳ፣ የልጆቻችንንም ንጹህ ጓዳ አንበክል፡፡ አባቶቻችን ከእሳትና ከሰይፍ ጋር ተጋድለው፣ አጥንትና ደማቸውን ገብረው ነፃ ሃገር አውርሰውናል፡፡ አሁን ግን ጦርነቱ የጋሻና የጦር

ሳይሆን ከዚያም የሚብሰው ስውር የአዕምሮና የመንፈስ ውጊያ ነው:: መርሳት የሌለብን የማይታይ ጠላት ከሚታየው እንደሚበረታ ነው::

ደስ የሚያሰኘው ነገር ደግሞ ለማይታየው ጠላታችን የማይታዩ መሳሪያዎች መኖራቸው ነው:: ለዚህም ለውጡን ከሶስቱ ዋና ዋና መሳሪያዎቻችን ከአስተሳሰባችን፣ ከባህሪያችንና መንፈሳዊነታችን ይጀምራል:: እነዚህ መሳሪያዎቻችን በዓለም መብራት ሲታይ ከንግግርና ተግባራችን ጋርም መዋሃድ አለበት::

ለልጆቻችን የምናወጣውን ስም ትርጉም ምን እንደሆነ እንኳን የማናውቅ ስንቶቻችን ነን:: ለምሳሌ ልጃችንን ‹‹ኤልያስ›› ብለን እንሰይምና "‹ኤልያስ› ማለት ምን ማለት ነው?" ተብለን ስንጠየቅ "በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ ነብይ ስም ነው!" ብለን እንመልሳለን:: ‹‹ኤልያስ›› የሚለው ስም ትርጉም ግን መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ ስም አይደለም:: ‹ኤል› ማለት ‹አምላክ› ማለት ሲሆን ‹ያ› ደግሞ ‹ያ›ህዋ ወይም ለዘላለም ህያው የሆነን አምላክ አመላካች ነው:: ስለዚህ ኤልያስ ማለት ‹‹አምላኬ ህያዉ ‹ያህ› ነው::›› ማለት ይሆናል::

ሲቀጥል ትርጉሙን ከማወቅ ባሻገር፤ የፈረንጅ ስሞችን እያመጣን ሞኒካ፡ ቬሮኒካ ከምንል በራሳችን ውብ ቋንቋ ውስጥ ያሉትን ስሞች እንጠቀም:: ዮዲት፣ ሳሌም፣ ሳባን የመሰሉ ውብ የአማርኛ ስሞች፣ ጊፍቲ፣ ሴና፣ ሲፈንን የመሰሉ ምርጥ የኦሮምኛ ስሞች፣ ኢዛናና ፍዮሪናን የመሰሉ ውብ የትግርኛ ስሞች፤ ቲና፣ ሜሩና ሂኒን አይነት የጉራጌ ስሞችንና ሌላም እጅግ በርካታ ምርጥ ምርጥ ሀገራዊ ስሞች እያሉን ለምን ወደ ባህር ማዶ እናማትራለን?" አሉ አዳራሹ ውስጥ ያሉትን በሙሉ በጥያቄ እየመለከቱ::

"በባዕድ ቃላት ሰይመን ከምናረዝማቸው ፎቆቻችን እኩል የእኛም አስተሳሰብና እውቀት ኢትዮጵያዊነቱን ሳይለቅ አብሮ ማደግ አለበት፤ ካለበለዚያ የፎቆች ቾምቾም ጠዓም እንደሌላቸው ሽንኮራዎች ቾምቾም ይመስላል:: የምንሰራውን የማናውቅ፣ በራስ መተማመን የሌለን ከርፋፋ ከሆንን ግን የሰጠናትን የምታበቅል ግሩም ምድር ይዘን የቲማቲም ድልህ ታሽጎ በበረሃ ከተሞሉት የአረብ ሃገራት ይላከልናል:: የቀርካ ኩባዮቻችንን፤ ባህላዊ መጠጫዎቻችን ንቀን፣ ለአንድ ሺህ አመት መሬት ውስጥ ቢቀበሩ እንኳን የማይበሰብሱ ይህን ለም አካባቢያችንን በካይ በሆኑ የፕላስቲክ ኩዳዎች ውሃ እንጠጣለን:: ለዚህም አብነት ያህል የጎረቤታችንን ኬንያን ተሞክሮ ማየት እንችላለን:: አንዲት የማንበቢያ ቤተ-መፅሐፍት ሳንገነባ፤ 10 ፑል እና ከረንቡላ ቤቶች ደርድረን ከብ ድንጋይ ከማጋጨት ባሸገር ቁም ነገር የሌለን ባዶዎች እንሆናለን። ኳስ ማየቱንስ ይይ ግን ወጣቱ ከማድሪድና

ባርሴሎና በላይ የቡናና ሳንጂዬ(ቅ/ግዮርጊስ) ጉዳይ ካላሳሰበው፣ የሮናልዶ ግራ እጅ ትንሿ ጣቱ ጥቁር የጥፍር ቀለም ተቀብታለች እያልን አንቶ ፈንቶ የምናወራ ከሆነ ግን እኛም የትንሿ ጣቱ ጥፍሮች ዋጋ ነው ያለን:: ገና ለገና ውስኪና ቮድካ አገኘው ብሎ ጠላ፡ብርዝና ጠጁን የሚንቅ፣ ዘመን አመጣሹን እየተመገበ አንባሻ፣ ድፎና ሙልሙሉን የሚያንቋሽሽ፣ ለራሱ ባህል ቅንጣት ታክል ክብር የሌለው ትውልድ ምንም ፋይዳ የለውም::

ግዕዝኛ፡ኦሮምኛ፡ትግርኛ ወዘተ... ያሉ ቋንቋዎችን ሳንለምድ ለፈረንሳይኛና ቻይንኛ የምንጓጓ ከሆነ ኢትዮጵያዊነታችን መስማትና መናገር የተሳነው ኢትዮጵያዊነት ይሆናል።

ፈረንጆቹ ግዕዝኛን በማስተርስና ‹‹ፒ ኤች ዲ›› ደረጃ እያስተማሩ የኛን የጥበብ መፅሐፍት ሲመራመሩ እኛ ፈረንሳይኛ ተምረን ሴት የምናማልል ከሆነ ጅላጅሎች ነን። በቀን ውስጥ 5 ሰዓት የማትሞላ ጊዜ ቢሯችን ውስጥ ተጎልተን በፌስቡክ ቻት ስናደርግ ውለን ማታ ከስራ መልስ ፈታ ለማለት ብለን ቺርስ እያልን የባንኮኒ ወንበር የምናሞቅ ከሆነ እኛ የሃገር ማነቆዎች ነን:: ሰፈራችን ውስጥ የተከመረው ቆሻሻ ተባብረን እንደማንሳት እንዳይሸተን አፍንጫችንን ይዘን የምናልፍ ከሆነ፤ የሰፈራችን የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጭቃ ሞልቶት ተባብረን ከማስተካከል ይልቅ የግቢያችንን ደጃፍ ብቻ ሊሾ የምናስለስን ከጭቃው መንገድ እንዳለፍን በሊስትሮ ጫማችንን አስውበን የምንጓዝ ከሆነ ደረታችንን ነፍተን ኢትዮጵያዊ ነን የምንልበት ሞራል ሊኖረን አይገባም::" አሉና የእጅ ሰዓታቸውን አየት አድርገው ቀጠሉ፤

"ስለዚህ እንንቃ፣ ወደራሳችን እንመለስ፤ የተዘረፉትን መፅሐፍት እናስመልስና በጥልቀት እንመርምር:: መርምረንም መደነቅ ብቻ ሳይሆን እኛም የራሳችንን ታሪክ ለመፃፍ እልህ ይያዘን:: ሴቶቻችንም አርቴፊሻል የሆነን ውብት ለማግኘት በመኳተን ጊዜ ማጥፋት ይቅርባችሁ:: ወንዶችም እንደ ገመሬ ዝንጀሮ ፓንትና ቂጣችንን ሳናስጎበኝ ሱሪያችንን በቅጡ ታጥቀን እንነሳ:: ቁጭ ብሎ እንደ ባልቴት ወሬ ከማፍላት ለለውጥ እንትጋ፣ ቁጭ ስንል አንባቢ፣ ተመሳጭና ፀሀፊ እንሁን ስንቆምም ደከመን ለፍተን ተጨባጭ ለውጦች የምናመጣ ሃያሎች እንሁን:: ታዳጊዎቻችንም ቡጭቅጫቂ ልብሶችና ብጭቅጫቂ ሃሳቦችችሁን ቀጣጥላችሁ ምሉዕ አድርጓቸው::

በዋናነት ሃገራችንን ከተቀባይነት ወደ ሰጪነት እናሳድጋት:: አስመጪና አከፋፋዮች አምራችና ላኪዎች ለመሆን ግባችንን እናስምር:: ምርጥ ምርጡን እቃ ኤክስፖርት ስታንዳርድ ብለን ለእነሱ እየላክን ለራሳችን ግን የማይረባውን ምርት መጠቃማችን ይብቃ:: ምን የመሰለ የአዞ ቆዳ በአንድ ሺህ ብር ልከን የላስቲክ ጫማ 2000 የምንገዛበት የሞኝነት ንግድ ይሻሻል::

‹‹ሜድ ኢን ኢትዮጵያ›› የሚለው መለያ ከቲሸርትና ሹራቦች ላይ ገንጥለን እስከ መሸጥ ድረስ የጠላነውን የሃገራችንን ምርት እንወደደው፤ በአልፍ አይነት ፋሽን ሊዘጋጁ የሚችሉ የባህል ልብሶቻችንን ለብሰን በውበት እንድመቅ:: እንደ መርቲ የታሸገ ቲማቲም ይብዛልን፣ እንደ አምቦ ውሃ ሃገር በቀል ለጤና ተስማሚ ለስላሳዎች ይመረቱ:: እንደ ቢሾፍቱ ያሉ መኪናዎች ይብዙ፣ በቃና ቲቪ ምትክ ኢትዮጵያዊ ቻናሎች እንይበት፤ ፊልሞቻችን ‹‹ሳቁና ውጡ›› ከሚል ገንዘብ መሰብሰቢያ ሃሳብ ወጥተው የጠለቁ የኢትዮጵያ ታሪኮችን ለዓለም ለማዳረስ ይሰሩ፤ ፍቅር እስከ መቃብርና ኦሮማይን መሰል ታላላቅ ድርሰቶቻችንን እና በእውነተኛ ኢትዮጵያዊ ወኔ ወጥተን ጀብዱ የሰራንባቸውን ጦርነቶች ወደ ፊልምነት የመቀየር ታላቅ ራእይ ይዘው ይነሱ፤ ዘፋኞቻችን ‹‹ከሆሆታና ዳሌዋ›› መጥቀው በሃገር በቀል ዜማዎች ብሎም እንደ ወጣቶቹ ሮፍናንና ሳሚ በሬጌና በመሳሰሉት በማዋሃድ ዓለም አቀፍ ተደማጭነት የሚያገኙበት ጥራት ያለው ስራ ይስሩ… በአጠቃላይ ሁሉም በየተሰማራበት ሁሉ ለሃገሩና ለወገኑ እድገትና ለውጥ ተግቶ ይስራ፤ ወደራሳችንም ተመልሰን ኢትዮጵያዊ ስልጣኔን እንስልጥን:: …ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናችኋለሁኝ::" ብለው ከመድረኩ ሲወርዱ አዳራሹ በሙሉ በጭብጨባ ተሞላ፤

ፕ/ር እሴ ከመድረኩ ሲወርዱ መድረኩን ያመቻቸላቸውና ከጅምሩም አቀባበል ያደረገላቸው ዶ/ር አያሌው ወደ እርሳቸው መጣ::

"አዎ ትክክል ብለዋል ፕ/ር… ወደ ራሳችን እንመለስ!… የሚገርመው ደግሞ እኛም በዚህ ዩኒቨርሲቲ ይህንን ንድፈ ሃሳብ በካሪኩለማችን ውስጥ አስገብተን በመሞከር ላይ ሳለን እርሶ መምጣቶት ነው::" አላቸው፤

"አመሰግናለሁኝ ዶ/ር አያሌው፤ እውነትም ደግሞ እየሰራችሁት ያላችሁት ነገር ለሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች አርዓያ ሊሆን የሚችል ነው::"

እነኢትኤል እንደምንም በተማሪዎቹ መካከል እየተሽሎከሎኩ ወደ መድረኩ ተጠጉ:: ፕ/ር እሴና ዶ/ር አያሌው አጠገብ እንደ ደረሱም "ሰላም ዋሉ ፕ/ር እሴ?" አለ ናዖድ እንደ ነገሩ ጎንበስ እያለ፤

"ሰላም ነኝ እ/ር ይመስገን፤" አሉ ፕ/ር፤ አድናቆታቸውን ለመግለፅ የመጡ ተማሪዎች መስለዋቸው ነበር::

"ይቅርታ አድርጉልንና ለብቻዎ ብናናግርዎ?" አለ ኢትኤል እየተቅለሰለሰ፤

ፕ/ር እሴ ትንሽ አሰብ አደረጉና፤ "እሺ ግን ጥቂት ደቂቃዎች ነው የምሰጣችሁ ወደ አክሱም ጉዞ መጀመር አለብኝ::" አሉ፤ ከጎናቸው ወደ ቆመችው ፍሬዲካ ዞረውም "Excuse me, I will be back in a minute

(ይቅርታ፤ ከአንድ ደቂቃ በኋላ እመለሳለሁኝ) አሏትና እነ ኢትኤልን ከአዳራሹ ጥግ ይዘዋቸው ሄዱ::

"እርስዎ ጋር የላኩን አንድ አቦ አራርሳ የሚባሉ አባ-ገዳ አባት ናቸው:: ይህንን ለእርስዎ ለብቻዎ እንድንሰጦት አዘውናል::" አለና ኢትኤል በርሳውን ከፍቶ በሰም የታሸገውን ጥቅልል ሰጣቸው:: ፐ/ር እሴ ጥቅልሉን ተቀብለው በቀስታ ዘረጉትና ማንበብ ጀመሩ::

ፐ/ር እሴ ደብዳቤውን ለ3 ደቂቃ ያህል ፊታቸው ላይ የተለያዩ የመገረም ምልክቶች እየተነበቡ ፊደላቱን ሲያነቡ ከቆዩ በኋላ ደብዳቤውን በጥንቃቄ ጠቀለሉት፤ ፊታቸውን ታላቅ የእፎይታና የደስታ ድባብ ሞልቶታል:: ከዚያም ከሳምሶናይታቸው ብዙ የመቶ ብር ኖቶች አወጡና 10.000 የኢትዮጵያ ብሮችን ቆጥረው ለኢትኤል ሰጡት:: ኢትኤል፣ አብርሃም፣ መርየምና ናዖድ እየሆነ ያለው ነገር ግራ ገብቷቸው እርስ በርስ ተያዩ:: በእርግጥ ወደ አዲስ አበባ ልመለስ ቢሉ እንኳን በቂ የሚባል ብር ባይዙም ከፐ/ሩ ለመቀበል ግን አቅማሙ፤… "ኧረ ፐ/ር እሴ ይሄ ሁሉ ብር ምን ይሰራልናል::"

"ያዙት ግድ የለም፤ ለእናንተ ሳይሆን አባ ገዳው በደብዳቤው ባዘዙኝ መሰረት ለራሴና ለሃገሬ ስል ነው የምሰጣችሁ… እና ሁላችሁም ከጅማ ዩንቨርሲቲ ነው ለዚህ ጉዞ የመጣችሁት?" አሉ ፐ/ር እሴ ፈገግ ብለው:: ኢትኤል መከራከሩ ለውጥ እንደማያመጣ ስለገባው ብሩን ተቀብሎ ከኪሱ ከተተ::… "አዎ ሁላችንም ከጅማ ዩንቨርሲቲ የህክምና ክፍል ነው የመጣነው፤" አለ፤… "አራታችሁም?"

"አዎ! በእርግጥ ሰባት ነበርን ግን ሦስቱ መንገድ ላይ የየራሳቸውን እውነት እያገኙ ተለይተውናል::" አለ፤

"ወዴት?… ወደ ቤተሰባቸው ተመልሰው ነው?" አሉ ፐ/ር እሴ፣

"ኧረ እኛ ቤተሰብም ሳያውቅ ነው ለዚህ ጉዞ የተነሳነው!" መለሰ ናዖድ:: በህልም መገለጥ ተነስቶ እዚህ የደረሰ ታሪካቸውን እጠር አድርጎ አጫወታቸው:: ኢትኤል በወጋቸው መሃል ፈንጠር ብላ ቆማ ጥርጣሬ በተሞሉ መርማሪ ዓይኖች የምታያቸውን ሴት ፈረንጅ አስተውሏል:: በኋላም ስልኳን አውጥታ ደውላ እጇን እያወራጨች ስትነጋገር አስተውሏታል:: ልክ ናዖድ ተርኮ ሊያጠናቅቅ ሲል ጥቁር ሙሉ ልብስና ፀሐይ መነፅር ያደረጉ ሁለት ሰዎች መጥተው ከእሷ ጋር ሲያወሩም ተመለከተ:: ወዲያውም ሁለቱ ሰዎች ፐ/ር እሴና እነኢትኤል ወዳሉበት ራመድ ራመድ እያሉ መጡ:: "እንዴ ኢንስፔክተር አክሎግ፣ ምን እግር ጣለኽ?" አሉት ዞረው በግርምት እያዩት፣

"አንድ የአሸባሪዎች መልዕክት እያስተላለፉ እንደሆነ መረጃ ደርሶን ነው የመጣነው፤ ለመሆኑ እነዚህ ወጣቶች እነማን ናቸው?" አለ አክሎግ እነኢትኤልን በአንክሮ እየተመለከተ፤

"አይ ዝም ብለው ዛሬ ስለሰጠሁት ት/ት ሊያናግሩኝ የመጡ ተማሪዎች ናቸው::" አሉ ፕ/ር እሴ፤ ውስጣቸው የተፈጠረውን ፍርሃት ላለማሳበቅ እየጣሩ ነበር::

"እስኪ መታወቂያ ይዛችኋል?" አለ ከአክሎግ ጋር አብሮ የመጣው ፖሊስ፤

"የጅማ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ነን፤ ለጠባቂዎቹ መታወቂያዎችንን አስይዘን፤ አስፈቅደን ነው የገባነው::" አሉ:: እነአክሎግ ግን አላመኗቸውም ነበር::...ፍሬድሪካ ፈንጠር ብላ ቆማ እየሆነ ያለውን ትከታተላለች::

"የጅማ ካምፓስ ተማሪዎች ወልዲያ ድረስ ምን ሊሰሩ ነው የመጡት?" አለ አክሎግ ጥርጣሬውን እየናረ::

"አይ ላስረዳህ እችላለሁኝ" ብሎ ኢትኤል ሊናገር ሲል ከአክሎግ ጋር የነበረው ፖሊስ "እሱን ጣቢያ ስትደርስ ትናገራለህ?" አለና ገፍተር ሲያደርገው ከኋላው የነበረ ጣውላ አደናቀፈውና በጀርባው ወደቀ:: ወዲያውም አብርሃም "ምንም ያላደረግን ልጆችን ስለምንድነው ጣቢያ የምትወስዱን!" ብሎ አክሎግ ላይ ጮኸበት::

ከአክሎግ ጋር የነበረው ፖሊስ ትዕግስቱ አልቋል:: "ኧረረረ እነዚህ አደገኛ ቦዘኔዎች ናቸው ጃል፤ ሊደበድቡን እኮ ነው:: በሉ! በሉ! ሌሎች ፖሊሶችም ጠርተን በዱላ ከምትገቡ አሁን በስርዓቱ ተከተሉኝና ወደ ጣቢያ እንሂድ" አለ በቁጣ::

ፕ/ር እሴ "አይሆንም ምንም የማያውቁ ልጆች ማሰር አትችሉም::" አሉ፤

"ምንም የማያውቁ መሆናቸውን አጣርተን የምናረጋግጠው ይሆናል ፕ/ር፤ እርስዎ ከእኔ ጋር ይመጡና ምርመራ እንዳርግቦታለን:: የእነርሱም ነገር እስኪጣራ ዛሬ ወልዲያ ማረሚያ ቤት ያድራሉ::" አላቸው:: አማራጭ የሌላቸው እነኢትኤል ፖሊሱን ተከትለው ወጡ:: ፕ/ር እሴና ፍሬድሪካም ከመርማሪ አክሎግ መኪና ውስጥ ገቡና ወልዲያ ወደሚገኘው የደህንነት ቅርንጫፍ ቢሮ ሄዱ::

*** ፍ – ፍ ***

ወልዲያ የእስረኞች ማቆያ ጠባብ ክፍል፤ ኢትኤል ከአንዱ የክፍሉ ጥግ ቆጭ ብሎ በፍርሃትና ጥርጣሬ ይንቀጠቀጣል:: በክረምት ብርድ ውስጥ ግድግዳ ተለጥፋ እንደተኛች ድመት ኩርምት ብሏል:: ለሃያ ሰው መኝታ

ሊሆን የሚችለው ቤት መቶ በሚጠጉ ታሳሪዎች ታጭቋል:: መርየም ከሴቶች ጋር የታሰረችበትን ክፍል፤ አፍቃሪዋ አብርሃም በሚያሳዝን ቁዘማ ውስጥ ሆኖ ይመለከተዋል:: ናዖድ በተቻለው መጠን ለመረጋጋት እየሞከረ ቢሆንም ቤተሰቡ እስር ቤት መግባቱን ቢሰማ ምን ሊለው እንደሚችል እያሰበ በጭንቀት ተውጧል:: ህልማቸውን ማመናቸው፤ ሃገር አቋርጠው መምጣታቸው እና እውነትን መፈለጋቸው ልክ አይደለም ብለው እስኪጠራጠሩ ድረስ ፈርተዋል፤ ትምህርታቸው፣ ተስፋቸው፣ የቤተሰቦቻቸው ልፋት… ሁሉም ጥያቄ ውስጥ ገብቷል:: የእስር ቤቱ ሁኔታ አርግጥም ተስፋ አስቆራጭ ነበር:: በተለይ ፀሐይ ጠልቃ አንድ ጥግ የተሰቀለችው ስልሳ ሻማ አንፖል ሰፊውን ማጎሪያ ብርሃን ማዳረስ ስላቃታት ጭለማ ሲውጣቸው ተስፋቸውም አብሮ ደበዘዘ::

"አብሽር ብዙ አትጨነቁ፤ የመጣውን በፀጋ መቀበል ነው::" አላቸው አንድ ከጎናቸው የተቀመጠ ጎልማሳ ሰው:: "ለመሆኑ በምንድነው የገባችሁት?…"

"መቼስ ያው የፈረደበት ፀረ-ሰላም ሃይል ተብለው ነዋ የሚሆነው!" አለ በቅርብ የሚገኝ ታሳሪ፤

"አይ ሲታዩ እንኳን ገና ይመስላሉ፤ ለነገሩ አሁን የአራት ዓመት ልጅም አሸባሪ ተብሎ መታሰር ጀምሯል::" አለና ሁሉንም አሳቃቸው፡

"አይ እንደዛ እንኳን አይደለም::" አለ ናዖድ፤ አንገቱን እንደደፋ፡

"አይ የዘንድሮ ልጆች ያቺን ሃሺሽ ይዛችሁ ተይዛችሁ ነው አይደል?" አሉ አንድ ሽምገል ያሉ ታሳሪ፤

"ኧረ እንደዚያም አይደለም ፋዘር" አለ አብርሃምም አንገቱን ደፍቶ፡

"ሆ እንግዲህ ምትነግሩን ከሆነ ንገሩን፤" አለ አንዱ ከወዲያ ቆሞ ሸንቱን በጀሪካን የሚሸና ግብዲያ ታሳሪ፤

ኢትኤል ታሪካቸውን በእርጋታ ለሁሉም ተረከላቸው:: በእስር ቤቱ የነበሩ ታሳሪዎች የተረት አባት ከበው ተረት እንደሚያዳምጡ ህፃናት ተመስጠው በጉጉት ነበር ያዳመጡት:: አንዳንዶቹማ የወልዩን ሼህ ከድርና አባ ገዳውን ታሪክ ሲሰሙ እንባ በአይናቸው እየሞላ ነበር:: ከሌላው ቀን በተለየ የደስታ ስሜት ውስጥ ሆነውም እዚያችው በተጣበቁበት እንቅልፍ ተራ በተራ ከእስር ነፃ አወጣቸው:: አብርሃምና ናዖድም ቁጢጥ ባሉበት እንቅልፍ ጣላቸው:: ኢትኤልና መጀመሪያ ላይ ለምን እንደታሰሩ የጠየቃቸው ጎልማሳ ሰው ብቻ ነበር ያልተኙት:: ከብዙ ማንኮራፋቶች መካከል እያንሾካሾኩ ያወራሉ…

"እውነት ግን በጣም የሚገርም ታሪክ ነው የነገርከን!" አለ ጎልማሳው፤

"ታሪኩ እንኳን ለሰሚው ለእኛም የማይታመን ነው:: የሆነው ሆኖ ግን አንተስ ለምን ይሆን የታሰርከው?" አለና ኢትኤል በተራው ጠየቀው፡

"የኔማ ተው ለሰሚም አይነገር፡፡… ከጠየቅከኝ ዘንዳ ልንገርህ እንጂ፣" አለና ታሪኩን ጀመረ፣ "እኔ እንግዲህ እመቤቴ ማርያም በምታውቀው አንድም ሰው ላይ ከፋትን አድርጌ የማላውቅ ሰው ነበርሁኝ፡፡ ከገጠር መንደሬ እንገቴን ደፍቼ አጥንቼ፣ የዩንቨርሲቲ መግቢያ ውጤት አምጥቼ በአካውንቲንግ ሙያ ዲግሪዬን ያዝኩኝ፡፡ ከብዙ የስራ ማፈላለግ ልፋቴ በኋላም በአንድ አነስተኛ ድርጅት አካውንታንት ሆኜ ተቀጠርሁኝ፡፡ ከድርጅቱ ሰራተኞች ጋር የምንጥለው እቁብ ነበር፣ አንድ ጊዜ ዳጎስ ያለ ብር ሆኖም ወጣልኝ፡፡ ለ6 ዓመታት ያህል በስራዬ ከማገኛት ብር ቆጥቤ ያጠራቀምኩት ብር ጨምሬበትም አንድ ባጃጅ ገዛው፡፡ ሰው ምን ይለኛል ሳልል ቀን ቀን ስራ እየዋልኩኝ ማታ ማታ እስከ 6 እና 7 ሰዓት በባጃጄ የኮንትራት ተሳፋሪዎችን እያጓጓዝኩኝ ለዓመት ያህል ሰራሁኝ፡፡ በዚህ ወቅትም ታናሽ ወንድሜን ከገጠር አስመጥቼ መንጃ ፍቃድ እንዲያወጣ አደረግሁት፡፡ በቀጣዩ አመትም የሰራሁበትን ብር አጠራቅሜ፣ ባጃጄንም ጥሩ በሚባል ዋጋ ሸጬ፣ ከቅርብ የስራ ጓደኞቼም የተወሰነ ብር ተበድሬ አሟላሁኝና ሚኒባስ ታክሲ ገዛሁኝ፡፡ ወንድሜ በሚንባሷ ታክሲ እየሰራ እኔ ደግሞ ደሞዜን እያጠራቀምኩኝ ትንሽ ከቆየሁኝ በኋላ ህጋዊ የሂሳብ አማካሪነት ፍቃድ አውጥቼ የራሴን አነስተኛ ድርጅት አቋቋምኩኝ፡፡ ይህም ድርጅት በእመቤቴ በረከት ከጠበቅኩት በላይ አትራፊ እየሆነ መጥቶ ሌላ ታክሲ ጭማሪ እንደገዛ ሆንኩኝ፡፡ በዓመቱም ቆንጆ የሚባል መኖሪያ ቤት አስገነባሁኝ፡፡" አለና በረጅሙ ተንፍሶ ቀጠለ፣

"እናም በዚህ መልኩ ሃብት እያካበትኩኝ በመጠኑም ቢሆን ገንዘብ ያለው ሰው መባል ጀመርኩኝ፡፡ ያኔ ነበር ቃልኪዳንን የተዋወቅኳት፡፡ መጀመሪያ ስትቀርበኝ አይን አፋርና ስለፍቅር ምንም የማታውቅ ምስኪን ሆና ነበር፡፡ ቆንጆ ነች፣… በዚያ ላይ እናቴ "አግባ! አግባ! አግባ!" እያለች ትጨቀጭቀኝ ስለነበር እድሌን ልሞክር ብዬ ቀረብኳት፡፡ አብሮነታችንን ሹፌሩ ታናሽ ወንድሜ አልወደደውም፣ እሱ ቀድሞውንም ቀልቡ ጠልቷት ነበር፡፡ እኔ ግን አልሰማሁትም! በህይወቴ መጨነቅን ትቼ ደስተኛ የሆንኩባቸውን ጊዜያት አብረን ካሳለፍን በኋላ ልንጋባ ተስማማን፡፡ የዛሬ 6 ወር ገደማም ቅልጥ ያለ ድግስ ደግሼ አገባኋት፡፡ ቤቴ ቤትሽ፣ ሐብቴ ሐብትሽ ብዬ ሁሉንም ሰጠኋት፡፡ ቀድሞውንም አቀራረቧ ለይስሙላ ኖሮ የሷ ክህደት ግን ለመገለፅ ጊዜ አልፈጀበትም ነበር፡፡ ከመኖሪያ ቤታችን አካባቢ ካለ አንድ ጎረምሳ ጋር በተደጋጋሚ እንደምትገናኝ ሰዎች ሲነግሩኝ አላምንም ብዬ ብቆይም አንድ ቀን ወንድሜ በሌላ ሰበብ ወስዶኝ በአይኔ በብረቱ ከሌላ ወንድ ጋር ስትማግጥ አየኋት፡፡" አለ… በደብዛዛዋ የማጎሪያ አንፖል የጎልማሳው አይኖች በእንባ ሲሞሉ ኢትኤል አስተዋለ፡፡

"እምኗያት ነበር… አወዳት ነበር… ግን ከዳችኝ:: ታዲያ ማታ ቤት ስትመለስ እንድንነጋገር እንደምፈልግ ነገርኳት:: ዛሬ ያረገችውን በሙሉ እንዳየሁና በድብቅ የምትሰራውን እንደማውቅ ስነግራት መልሷ ምን ሊሆን ይችላል ብዬ ፈርቼ ነበር:: እሷ ግን ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ እየሳቀች መፋታት እንደምንችል ነገረችኝ:: ‹ይዘህ አነቃት… አነቃት…› አለኝ:: ከተቀመጥኩበት ሶፋ ብድግ ብዬ ወደሷ ከመጠጋቴ ሰፈሩን በእሪታና በጩኸት ሞላችው:: ወዲያውም ጎረቤቶቻችን መጡ:: ሊያረጋጓት ቢሞከሩም እሷ ግን ፖሊስ ካልተጠራ ሞቼ እገኛለሁኝ አለች:: ይህቺ መሰሪ ግን ሁሉንም ቀድማ አቅዳው ኖሮ ፖሊሶቹ ደጃችንን እንደረገጡ ‹‹ኡ!… ኡ!… ኡ!… ተደፈርኩኝ፤›› እያለች እንዳዲስ መጮኽ ጀመረች:: ፖሊሶቹም ካለምንም ምስክር እና ካለምንም ቅድመ ሁኔታ አስረው ወኅኒ ቤት ወረወሩኝ:: ይኸው እስካሁንም አንዳች ፍርድ ሳላገኝ ለሦስት ወራት ያህል እዚሁ ታጉሪያለሁኝ:: ወንድሜ እንደነገረኝ እሷ የፍቺ ወረቀቷን ጨርሳ ግማሽ ሃብቴን ለመውሰድ ተቃርባለች:: እኔ እንግዲህ በዋስ ከመውጣት ጀምሮ እስከ 17 ዓመታት ፅኑ እስራት የሚዳርግ ክስ ከፊቴ ተደቅኖብኝ አለሁት:: ይሕ በጩኸትና በማስመሰል ከሚያሳምኑ ሰዎች ጎን የቆመ የፍትህ ስነ-ስርዓት ስንትና ስንት እኔን መሰል ባሎችንና አባወራዎችን እያዋረደና ህይወታቸውን እያበላሸ እንደሆነ ለማወቅ ከእስር ቤት የተሻለ የምስክነት ስፍራ ያለ አይመስለኝም:: እ… ማን ነበር ያልከኝ ስምህን…?" አለው፡ ….

"ኢትኤል"፤ መለሰ ኢትኤል::

"ልጅ ኢትኤል የኔ ፈንታ እንዳይደርስህ ከልቤ እመኝልሃለሁኝ:: አሁን እንቅልፍ አይኔን ሊያስከድነኝ ከጫፍ ስለደረሰ ልተኛ… በል ደህና እደር::" አለውና ከጎኑ ካሉት ታሳሪዎች የተረፈችውን ቦታ አብቃቅቶ ጎኑን አሳረፈ::

ባለታሪኩ ጎልማሳው ሰው ሲተኛ ኢትኤል ከሰፊው ማጎሪያ ያልተኛ ብቸኛው ሰው ሆነ:: ጭንቀትና ፍርሃት ከሞላው የሃሳቡ ማህደር እየዋኘ ሊተኛ አልቻለም:: ለነገሩ ሊተኛም ቢፈልግ የሚያስተኛ ሁኔታ ውስጥ አልነበረም:: ከዚያ ሁሉ ታሳሪ የሚወጣ የተቃጠለ አየር አፍንጫን ይሰነፍጣል:: ለነኢትኤል የሌላቸው ነፃነት ያላቸው አይጦች ከኮርኒሱ ላይ ይጨፍራሉ፤ ቁንጫዎች ፍንጥር ፍንጥር እያሉ ይፈነጥዛሉ፡ ትኋኖች ከቆዳው ላይ ይርመሰመሳሉ፤ በየሰኮንዱ ያሳክኩታል:: ሙቀትና ፍትጊያው የአዕምሮን ሰላም ይነሳል:: ኢትኤል በዚሁ ስቃይ ውስጥ ሆኖ እስረኞችን አሰባቸው:: እያንዳንዱ ሃሳቡን በነፃነት የመግለፅ ሰብዓዊ መብቱን ተጠቅሞ መንግስትን የተቃወመ በሙሉ ‹‹አሸባሪ›› በሚል ተልካሻ ምክንያት የሚታቀቱ እንደዚህ አይነት ማጎሪያ ውስጥ እንደሆነ ሲያስበው ዘገነነው:: በዚህ ላይ ደግሞ

ግርፊያና ማሰቃየቱ ሲጨመረ ያለውን ሃዘናቸውን ማሰብ ከህሊናም በላይ ነው:: እሱም እንዲችው ሲሰቃይ 11 ሰዓት ሞላ:: ከአቅሙ በላይ የሆነው አካሉ ማረፍ ነበረበትና እንቅልፍ ሸለብ አደረገው::

"ከጅማ የመጣችሁ ተማሪዎች!... ከጅማ የመጣችሁ ተማሪዎች?...ትፈለጋላችሁ!" የሚል ጥሪ ማለዳ 12:30 ላይ ሲቀሰቅሳቸው ኢትኤል ከእንቅልፍ የነቃ ሳይሆን አይኑን ጨፍኖ የገለጠ ነው የመሰለው:: "ተነሱ... ተነሱ...! እየተጠራችሁ ነው::" አለ ማታ ታሪኩን ያጫወተው ጎልማሳ፤

ኢትኤል፣ አብርሃምና ናዖድ የተደረደሩትን እስረኞች እንዳይረግጡ በጥንቃቄ እየተራመዱ ወደበሩ መጡ:: ከበሩ ላይ አንድ የመቶ አለቃ ቆሟል::

"በሉ እቃ ካላችሁ ያዙና ውጡ... በነፃ ይለቀቁ ተብሏል::" ሲላቸው በታላቅ ደስታ ፈንጥዘው ተቃቀፉ:: ልብሶቻቸውን ሊያመጡ ተመልሰው ሲገቡ ማታ ታሪካቸውን የሰሙ ብዙ እስረኞች የደስታቸው ተካፋይ ስለሆኑ ተራ በተራ አቀፏቸው:: ኢትኤል ማታ ከተኛበት ቦታ ሲደርስ ብዙ ሲያወጋው ያመሸው ጎልማሳ በፈገግታ ተሞልቶ "ልትወጡ ነው አይደል ወንድሜ!... ደስ ይላል!" አለና ተነስቶ አቀፈው:: "እዚህ ቤት አንዲትም ቀን ደግሞ ማደር ትልቅ ቅጣት ነው:: እስኪ ለእኛም የነፃነታችን ቀን ይቃረብልን ዘንድ እኚያን እናገኛችኋለን ያላችሁትን ባህታዊው ኤልካናን አፀልዩልን::" አለው::

"የምናገኛቸው ከሆነ እንዲፀልዩላችሁ እነግርላችኋለሁኝ::" አለ ኢትኤል:: ኢትኤል፣ አብርሃምና ናዖድ ሁሉንም ተሰናብተው፤ ልብስና ብራቸውን ከፖሊስ ጣቢያው ተቀብለው ሲወጡ መርየምና ፕ/ር እሴ ውጭ ላይ ቆመው እየጠበቋቸው ነበር:: አብርሃም እየሮጠ ሄዶ መርየም ላይ ተጠመጠመባት፤ ለረጅም ሰዓትም ተቃቅፈው ቆዩ::

የማታ ታሳሪዎች ሻወር ወስደው ልብሳቸውንም ቀያይረው እስኪመለሱ ፕ/ር እሴ፣ ፍሬድሪካና ዶ/ር አያሌው እየተጨዋወቱ ጠበቋቸው:: ጨራርሰው መጡናም አጠገባቸው ተቀመጡ:: "ፕሮፌሰር መቼም ዋስ ሆነው ስላስወጡን አመሰግኖታለሁኝ::" አለ ኢትኤል፤

"ዋስ ሆኜ አይደለም ያስወጣኋችሁ::" አሉ ፕ/ር እሴ፤

"እና እንዴት ነው የወጣነው?" አለ ናዖድ በመገረም፤

"አክሎግ ነው ቶሎ እንድትለቀቁ ያዘዘው::"

"ለምን ይሆን?" አለ ኢትኤል፤ "እርግጠኛ አይደለሁም ግን ለእኔ እንድትሰጡኝ ያመጣችሁትን ደብዳቤ ተቀብሎኝ ለረጅም ጊዜ ካነበበው በኋላ ‹አሁኑኑ ተፈታችሁ መሄድ አለባችሁ› ነው ያለኝ::"

"ወደየት ነው መሄድ ያለብን ፐ/ር?" አለ ኢትኤል፤ "እኔ ከወልዲያ ወደ አክሱም ከዚያም ወደ አደዋዋ ራማ መንደር፣ እናንተ ደግሞ ከወልዲያ ወደ ቆቤ ከዚያም ወደ ራማ ተራራ፤ ኪዳነ ምህረት ገዳም።" አላቸው ፐ/ር እሴ አዲስ መነቃቃት እየተነበበባቸው።

"ወይኔ ወላሂ በጣም ደክሞናል እኮ ፕሮፌሰር! ማታ እኮ ሳንተኛ ነው ያደርነው፤" አለች መርየም ወገቧን በእጇቿ እየደገፈች፤ አብርሃም እቅፍ አድርጎ ደገፋት።

"አይዞሽ የኔ ልጅ... አውቃለሁኝ ከኔም የበለጠ አድካሚ መንገድ እንደመጣችሁ። አሁን ግን ወደ መንገዱ መቋቻ ተዳርሳችኋል። እኔም የኔን ጉዞ ባስቀጥልም፤ በፀሎት አስባችኋለሁኝ፤ ዳገቱ ላይ አትድከሙ... ከተራራው ጫፍ ላይ ያለውን ቸቦ አንስተን፣ ከፍ አድርገን ለህዝባችን ብርሃኑን እናዳርሳለን።" ብለው፤ የሁሉንም ስልክ ተቀብለው በስልካቸው ከመዘገቡ በኋላ ተሰናብተዋቸው ሄዱ።

ኢትኤል በጉዟቸው ውስጥ ያገኟቸውን የእነርሱ ቢጤ ተጓዥ በአይኑ ሸኛቸው። ትናንት ቆማ ስትከታተላቸው የነበረችውና በኋላም ደህንነቶቹ ሊመጡ ሲሉ ስልክ ደውላ ስታነጋግር የነበረችው ፈረንጅ ካለችበት መኪና ውስጥ ገብተው ከቦታው ለቀው ሄዱ። ለምን እንደሆነ ባያውቅም ኢትኤል ይህቺን ሴት ውስጡ አልወደዳትም ነበር።

*** ፉ – ፉ ***

*ፐ/ር እሴ ወደ መቀሌ የሚወስደውን መንገድ ይዘው መንገድ እንደጀመሩ በስልካቸው የታደለ ሮባን ዘፈን ‹ከኢንተርኔት ሰርቾ› አድርገው አወረዱና በመኪናው ስፒከር ከፈቱት።*

*♫ እኔስ አልምልም በቁሳር... ሃገሬ ምልቶ ስንት ኢድባር*

*ንጉስ አክሱም ሮማይ...ኢድርጎ አነፀኝ የበላይ፥*
*...ጣሊያን ሃገር ፒያዛ...ለስልሳ ዘመን በዋዛ*
*ዛሬስ ናፈቀኝ መሬቱ...የማርያም ፅዮን ታቦቱ፤*
*ባገሬ ነበር መነኩሴ... ማልዶ የሚየምቀኝ ቅዳሴ*
*ስንቱን አሳየኝ አቤቱ.. ዋ ምስሎኒ ሃገሮቱ!*

***

*ከካሌብ መንበር ኢዛና... ኩዱሊስ ጥንተ ገናና*
*በቢላል ቅዱስ መንገዱ... ጠራኝ ነጃሺ ማስጊዱ፤*
*ሲኖር ምናሬ ቢሺየት... ታሪኬን ጥሎ ቢተከለኝ*
*ሃገር ተዋግቶ መለሰኝ... አንቶናም ደጀ ኢደረሰኝ።*

*ቻው ቻው ሲኞር ሲኞሬ... ገባሁኝ በቃ ሃገሬ..." እያለ ይቀጥላል፡፡*

***

*"Finally we are going to Axum, time to solve the secret! Aren't you excited? (በስተመጨረሻ አክሱም ልንሄድ ነው፤ ሚስጥሩንም ልንፈታው፤ ደስ አላለህም?)"*

*"Yeah, I am... but something is bothering me! (አዎ... ግን የሆነ ነገር ግራ እያጋባኝ ነው!)"*

*"What is that? (ምን ይሆን?)"*

*"I am not sure how the security agency found out about my communication with those boys so quickly!" (የደህንነት ሰዎቹ እነዚህን ልጆች ማግኘቴን እንዴት በዚህ ፍጥነት ሊያውቁ እንደቻሉ አልገባኝም!)" አሏት በጥርጣሬ እየተመለከቷት፤*

"Yeah that is a mystery (አዎ የሚገርም እንቆቅልሽ ነው፡፡)" አለችና በመኪናው መስታወት ውጭ ውጪን ማየት ጀመረች፡፡

ፐ/ር እሴ ፍሬድሪካ ከእዚህ ጀርባ እጇ እንዳለበት ጠርጥረዋል፡፡ ቴዎድሮስን እንግሊዞች መድፍ እንሰራለን ብለው እንደካዱት፣ አፄ ምኒሊክን በቋንቋ ሸውደው መሬት ለመውሰድ እንደሞከሩት ጣሊያኖች፤ አጼ ኃይለ ስላሴን አባይ ላይ ግድብ እንሰራለን ጅቡቲንም እንመልስለን ብለው እንዳድበሰበሱት ሁሉ፤ ሁቱና ቱትሲዎችን ‹‹ነፃ ናችሁ!››... ‹‹ወጥተንላችኋል›› ብለው ሲያበቁ ደግሰውት በሄዱት የዘር ፍጅት ላይ ጋዝ እያርከፈከፉ፤ ሁቱዎች ቱትሲዎችን እንዲገድሉ በሂሊኮፕተር ገጀራና መጥረቢያ ጭነው ሲያከፋፍሉ የነበሩ ምዕራባውያንን ማመን በእርግጥም ትልቅ ስህተት ነው፡፡ የእነርሱ ተቀጣሪ ልትሆን የምትችል ሰው ይዞ ሃገር ለመለወጥ መምጣቱ ስህተት መሆኑን ቀድሞ አለመረዳታቸው አበገናቸው፡፡ በውስጣቸው የተፈጠረውን የስሜት መረበሽ ሸሽገው ወደ አክሱም መኪናቸውን አከነፉት፡፡

ከታደለ ሮባ ዘፈን ቀጥሎ በሞባይላቸው ምርጫ መሰረት የቴዲ አፍሮ ሙዚቃ መሠማት ጀመረ...

*♫ "አንተ አብርሃም የአሪት ስብሃት*
*የነእስማኤል የይስሃቅ አባት...*
*ልክ እንደ አክሱም ራስ ቀርፀሃት ራሴን*
*በፍቅር ቧፍ ለኩሳት ነፍሴን..."*

*** ፉ – ፉ ***

# ምዕራፍ ፲፩............✷የራማ ከፍታ✷

**"መዝሙረ-ዳዊት፤ ምዕራፍ 87"**

*"1፤ መሰረታቸው በተቀደሱ ተራሮች ነው፤*
*2፤ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ፣ እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወዳቸዋል::*
*3፤ የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፥ በአንቺ የተከበረ ነገር ይባላል!*
*4፤ የሚያውቁኝን ረዓብንና ባቢሎንን አስባቸዋለሁ፡ እነሆ፡*
*ፍልስጥኤማውያን ጢሮስም* ***የኢትዮጵያም*** *ሕዝብ፥ እነዚህ በዚያ ተወለዱ::*
*5፤ ሰው እናታችን ፅዮን ይላል፥ በውስጥዋም ሰው ተወለደ፡ እርሱ ራሱም*
*ልዑል መሰረታት::*
*6፤ እግዚአብሔር ለህዝቡ፥ በውስጥዋም ለተወለዱት አለቆችዋ በመፅሐፍ*
*ይነግራቸዋል::*
*7፤ በአንቺ የሚኖሩ ሁሉ ደስ እንደሚላቸው ይነግራቸዋል::"*

*** ዩ – ዩ ***

*"የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እናንተ ለእኔ እንደ* ***ኢትዮጵያ*** *ልጆች አይደላችሁምን?"* .............. *(ትንቢተ አሞፅ ምዕራፍ፡ 9:7)*

*** ዩ – ዩ ***

***አመሻሽ ላይ የመጨረሻዋ የባቱ ጡንቻ ሃይል ተንጠባጥባ ሲታልቅ ይታወቀኛል:: . . .*** ወደ ራማ ኪዳነ-ምህረት የሚያደርሰው ዳገታማ፣ 3 ሰዓታት ገደማ የሚፈጅ መንገድ እየፈተናቸው ነው:: ኢትኤል እግሮቹ አልታዘዝህ ብለውታል፤ መርየምን ከማዘል ባልተናነሰ ደግፏት የሚጓዘው አብርሃም ነፍሱ ልትወጣ ደርሳለች:: ከሦስቱ ትንሽ ጠንከር ያለው ናዖድም ለድካም እጅ ወደ መስጠቱ እየተቃረበ ነው::

ከወልዲያ ቆቦ ከተጓዙ በኋላ አንዲት መኪና ተባብራቸው በስተቀኝ ወደ አፋር መስመር እየተጓዙ ግዙፉን ተራራ ዞረው እንዳበቁ በግራ በኩል ወደ ራማ ኪዳነ ምህረት የሚወስደው መገንጠያ ጋር ሲደርሱ ወረዱ:: ይህን መገንጠያ ይዘውም ነበር የእግር ጉዞውን የጀመሩት። በመንገዳቸው በአንድ እግር ብቻ ውሃ ላይ ቆመው ለኢትዮጵያ ለዓመታት የፀለዩትን የአቡነ ተክለሃይማኖትን ከዚያም የቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያንም አልፈው ነበር የራማን ተራራ መውጣቱን የተያያዙት። ወደ ቤተ-ክርስቲያኒቱ እየተጠጉ ሲመጡ ጆሯቸው አንድ የሚማርክ ዜማ መስማት ጀመረ:: በደንብ በቀረቡ ቁጥር ዜማውም እየጠራ መጣ::

*♫ ነይ ነይ እምዬ ማርያም፥*

*ነይ ነይ ቤዛዊት ማርያም... የሚሉ የንዑዳን ሰልፎች ዝማሬ ከተሰማ በኋላ የዘማሪ ሃዋዜን መዝሙር ሁሉም በአንድ ድምፅ አሳምረው መዘመር ጀመሩ::*

*♫ ማርያም ብዬ እዘምራለሁ - እንደ አባቶቼ እጠራታለሁ*

*በያሬድ ዜማ በአዲሱ ቅኔ - ልዘምርላት በኢድሜ ዘመኔ፤*
*ማርያም ብዬ!... በእሳት መታጠቂያ ታጥቋል ባለ ቅኔው፥*
*ማርያም ብዬ!... መንፈስ ይማርካል ማህሌት ተገልጦ*
*ማርያም ብዬ!... በወርቁ ፅዋ ላይ አርጓል ፀሎቴ፥*
*ማርያም ብዬ!... በአማኑኤል እናት በእንቺ በእመቤቴ::*

እነኢትኤል ቤተ-ክርስቲያኒቱ ጋር ደረሱ፤ ቀና ብለውም ተመለከቷት:: በእንጨት የተሰራች ነች፤ ከላይዋ ከጣሪያው ደጋን ስር አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ተሰቅሏል:: በወርቀ ዘቦ ያጌጠ የክህነት ልብሶች የለበሱ ዘማሪዎች ከሰገነቷ ላይ ይታያሉ:: አብርሃም ነጠላ ለብሰው ከሚያጨበጭቡት ሰዎች መካከል እየተጠጋ አባ ኤልካኖን የሚባሉ አባትን ማግኘት ይችል እንደሆነ ቢጠይቅ እንደማያውቋቸው ነገሩት:: ሌሎች ሰዎችንም እየተዟዟረ ቢያጠያይቅ አውቃቸዋለሁኝ የሚል ሰው ግን አላገኘም:: ግራ በመጋባት ውስጥ ቆመው ሳለ አንድ ጥቁር ቀሚስ ያጠለቀ ከበላዩም ጥቁር ኩታ የደረበ

መነኩሴ ከኋላቸው መጥቶ የአብርሃምን ጀርባ ቸብ ቸብ አደረገው፡፡ አብርሃም ዞረ፤

"እነ ኢትኤል ማለት እናንተ ናችሁ?" አለው፤

"አዎ ነን፡፡" አለ አብርሃም፤ ሁሉም ዞረው ሰላምታ ሰጡት፤

"የእግዚአብሔር ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን፤ አባ ኤልካና እርሳቸው ወዳሉበት እንድወስዳችሁ ልከውኝ ነው፡፡" አለ ወጣቱ መነኩሴ፤

"እንዴ እስካሁን እርሳቸውን የሚያውቅ ሰው ፈልገን ፈልገን አላገኘንም ነበር፡፡" አለ አብርሃም፤

"አዎ እርሳቸውን የሚፈልጉ ሰዎች ከመጡ እንደማታውቁቁ ተናገሩ ብለው ስላዘዙ ማንም ሰው ስለእርሳቸው እዚህ ገዳም መገኘት አይመሰክርም፡፡ እንዲህ እንደናንተ አይነት የሚጠብቁት እንግዳ ከመጣ ራሳቸው ለእኔ ነግረውኝ እኔ ነኝ የማገናኛቸው፡፡ ለማንኛውም ኑ ተከተሉኝ፡" አለና ዞሮ ወደ ጫካው አመራ፤

እነ ኢትኤል ፊታቸው ላይ የደስታና የድካም ስሜት እየተደባለቀ፡ እርስ በርስ ተያዩና ተከተሉት፡፡

ወጣቱ መነኩሴ በባዶ እግሩ እሾህ እንኳን ሳይፈራ በዛፎቹ መሃል እየተሽሎከሎከ፣ ቁጥቋጦዎችን እየረገጠ ሲጓዝ ተገርመዋል፡፡ ብርዳማ ከሆነው የራማ አምባ በስተግራ በኩል ካለው ጥሻ ውስጥ ትንሽ ከተጓዙ በኋላ አንዲት እንደ ነገሩ የተቀለሰች፤ መለስተኛ ጎተራ የምትመስል የሳር ዳስ ጋር እየተቃረቡ ሳለ ወጣቱ መነኩሴ፤ እርምጃውን ገታ አድርጎ "ያውላችሁ፡ የአባ ኤልካና ማደሪያ… ለነገሩ ለስሙ የእርሳቸው ማደሪያ ተባለ እንጂ እርሳቸውስ በዓመት ውስጥ ወርም የሚሞላ ጊዜ አያድሩበት! ብቻ ዛሬ እናንተን ለማግኘት ነው መሰል ቤታቸው ተገኝተዋል፡፡ ለማንኛውም አድርሳቸውና ተመለስ ስለሆነ ያሉኝ እኔ በዚሁ እመለሳለሁኝ እናንተ ዝለቁ፡፡" አላቸውና በመጣበት ብርታትና ፍጥነት ተመለሰ፡፡

እነ ኢትኤል ወደ ዳሷ እየተጠጉ ሲመጡ ሌላ ዜማ ማድመጥ ጀመሩ፡፡ ኃልዮት አከሊል ያላበሳቸው አንድ ቢጫ ቀሚስና ወደቡኒ የተጠጋ ቆብ ያጠለቁ፤ በእጃቸውም ትልቅ መቁጠሪያን የያዙ አባት፡ ጀርባቸውን ሰጥተው፡ ከዳሱ በር ደጃፍ በትራቸውን ደገፍ ብለው ሲዘምሩ ነበር ያገኟቸው፡፡ የከበሮ ድለቃ ድምፅ ይሰማል፤ ከበሮ የሚመታ ሰው ግን የለም፡፡ በገና ይደረደራል፤ በገናው ግን ካለደርዳሪ ተቀምጧል፡፡ ፅናፅሉ ካለረጋጅ ይንሸዋሸዋል፤ አዛውንቱ ባህታዊ ግን በሚያምር አባታዊ ለዛ፡ መዝሙረ እዮብን ያንቆረቁሩታል፡፡ አንቱን ለማየት የጓጓው ኢትኤል ከኋላቸው ዞሮ ሰላምታ

ሊያቀርብላቸው ሲል አብርሃም እጁን ያዝ አደረገውና "ቆይ ይጨርስ" አለው፤ የመጽሐፈ ኢዮብ - ምዕራፍ 28 ቃላት በሚያምር ዜማ ይፈስ ነበር፡፡

♫1፤ በእውነት ብር የሚወጣበት፥ ወርቅም የሚነጠርበት ስፍራ አለ።

2፤ ብረት ከመሬት ውስጥ ይወሰዳል፤ መዳብም ከድንጋይ ይቀለጣል።

3፤ ሰው ለጨለማ ፍጻሜን ያደርጋል፤ የጨለማውንና የሞት ጥላን ድንጋይ እስከ ወሰኑ ድረስ ይፈላልጋል።

4፤ ሰው ከሚኖርበት ርቀው መውረጃ ይቆፍራሉ፤ ከሰውም እግር ተረሱ፥ ከሰዎችም ርቀው እየተንጠለጠሉ ይወዛወዛሉ።

5፤ እንጀራ ከምድር ውስጥ ይወጣል፤ በእሳትም እንደሚሆን ታችኛው ይገለበጣል።

6፤ ድንጋይዋ የሰንፔር ስፍራ ነው፥ የወርቅም ድቃቂ አለው።

7፤ መንገድዋን ጭልፊት አያውቀውም፥ አሞራም ዓይን አላየውም።

8፤ የትዕቢት ልጆች አልረገጡአትም፥ ደቦል አንበሳ አላለፈባትም።

9፤ ሰው ወደ ቡላድ ድንጋይ እጁን ይዘረጋል፥ ተራራውንም ከመሠረቱ ይገለብጣል።

10፤ ከድንጋይ ውስጥ መንዶልዶያ ይወቅራል፤ ዓይኑም ዕንቍን ሁሉ ታያለች።

11፤ ፈሳሹም እንዳይንጠባጠብ ይገድባል፤ የተሰወረውንም ነገር ወደ ብርሃን ያወጣል።

12፤ ነገር ግን ጥበብ የምትገኘው ወዴት ነው? የማስተዋልስ ስፍራ ወዴት ነው?

13፤ ሰው መንገድዋን አያውቅም፤ በሕያዋን ምድር አትገኝም።

14፤ ቀላይ። በእኔ ውስጥ የለችም ይላል፤ ባሕርም። በእኔ ዘንድ የለችም ይላል።

15፤ በምዝምዝ ወርቅ አትገኝም፥ ብርም ስለ ዋጋዋ አይመዘንም።

16፤ በኦፊር ወርቅ፥ በከበረም መረግድና በሰንፔር አትገመትም።

17፤ ወርቅና ብርጭቆ አይወዳደሩአትም፥ በጥሩ ወርቅም ዕቃ አትለወጥም።

18፤ ስለ ዛጐልና ስለ አልማዝ አይነገርም። የጥበብ ዋጋ ከቀይ ዕንቍ ይልቅ ይበልጣል።

19፤ የኢትዮጵያ ቶጳዝዮን አይተካከላትም፥ በጥሩም ወርቅ አትገመትም።

20፤ እንግዲያስ ጥበብ ከወዴት ትመጣለች? የማስተዋልስ ስፍራ ወዴት ነው?

21፤ ከሕያዋን ሁሉ ዓይን ተሰውራለች፥ ከሰማይ ወፎች ተሸሽጋለች።

22፤ ጥፋትና ሞት። ወሬዋን በጆሮቻችን ሰማን ብለዋል።

23፤ እግዚአብሔር መንገድዋን ያስተውላል፥ እርሱም ስፍራዋን ያውቃል።

24፤ እርሱም የምድርን ዳርቻ ይመለከታል፥ ከሰማይም በታች ያለውን ሁሉ ያያል።

25፤ ለነፋስ ሚዛንን ባደረገለት ጊዜ፥ ውኆችንም በስፍር በሰፈረ ጊዜ፥

26፤ ለዝናብም ሥርዓትን፥ ለነጐድጓድ መብረቅም መንገድን ባደረገ ጊዜ፥

27፤ በዚያን ጊዜ አያት፥ ገለጣትም፤ አዘጋጃትም፥ ደግሞም መረመራት።

28፤ ሰውንም። እነሆ፥ እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው፤ ከኃጢአትም መራቅ ማስተዋል ነው አለው።

አባ ኤልካኖ ዝማሬያቸውን ጨርሰው ሲዞሩ፣ ኢትኤል፣ ናዖድ፣ አብርሃምና መርየም ከጀርባቸው እንደቆሙ አስተዋሉ:: እምር ብለው ተነሱና ኢትኤልን እቅፍ አደረጉት::.."የእህቴ ልጅ... ትንሹ ኢታ አሁን እንዲህ ትልቅ ሆነኸ በማየቴ ፤ ልዑል አምላክ ምስጋና ይድረሰው::" አሉና ከእቅፋቸው አውጥተው ትከሻዎቹ ላይ ግራና ቀኝ እጃቸውን ጣል አድርገው ትከ ብለው ተመለከቱት:: "እውነት ነው የምነግርህ፣ የቃል-ኪዳኑ መፈፀም ባንተ ትከሻ ላይ ሲጣል ጥርጣሬ አድሮብኝ ነበር:: በጠንቋይ ምክር የሚመሩት እህቴና አባትህ በወጉ ሳያሳድጉህ፣ ከእግዜር ሊያርቁህ ይችላሉ ብዬ ፈርቼም ነበር:: አንተ ግን የነበሩብህን ፈተናዎች ከእነዚህ ድንቅ ጓደኞችህ ጋር ሆነህ በመወጣት እዚህ ደርሰሃል::" አሉና በአሸናፊነት ስሜት ፈገግ አሉ፣ እነአብርሃምንም እያቀፉ ‹‹እንኳን ደህና መጣችሁ፣ ወደ ውስጥ ዝለቁ፣›› አሏቸውና እርሳቸው ኢትኤልን አቅፈው ቀድመው ገቡ::

ኢትኤል፣ ናዖድ፣ አብርሃምና መርየም በጠባቧ ዳስ ውስጥ ካለ አጭር መደብ ላይ ጎን ለጎን ተጣብቀው ተቀመጡ:: ከመቅረዝ ላይ የተሰኩት ሦስት የበሩ ሻማዎች ጨለማውን አሸንፈውታል:: ከመደቡ ፊት ለፊት የሳር ፍራሽ ተቀምጧል:: ከጎኑ ካለው ከርካሳ ሳጥን ላይ እጅግ በርካታ የብራናና የወረቀት መጽሐፍት ተደርድረው ጣሪያውን ለመንካት ይንጠራራሉ:: አባ ኤልካኖ መፅሐፎቹን አንድ በአንድ ማውረድ ሲጀምሩ እነኢትኤል አንዳች ነገር ሊያሳዩቸው መስሏቸው ነበር:: እርሳቸው ግን ሁሉንም መፅሐፍት ተራ በተራ አውርደው ከጨረሱ በኋላ ከርካሳውን ሳጥን ከፈቱት:: ከውስጡም ሁለት የተጣጠፉ ባናዎችን አውጥተው ዘረጓቸው:: አንዱን ባና የኢትኤልና ናዖድ ትከሻ ላይ ሌላውን ባና ደግሞ በአብርሃምና መርየም ትከሻ ላይ ጣል አደረጉት::

"ውይ አባ አያስፈልግም ነበር እኮ፣" አለ አብርሃም አፈር እያለ፣

"በደንብ ነው እንጂ የሚያስፈልግ ልጄ፣" አሉ አባ ኤልካኖ ሳጥኑን ዘግተው መፅሐፍቶቹን ወደ ቦታቸው እየመለሱ:: "እናንተ እኮ እንደኛ የዚህን ተራራ ብርድ አልተለማመዳችሁትም:: ስጋችን በጊዜ ሂደት ካልሆነ፣ ነገሮችን በቶሎ መልመድ ይከብደዋል::" አሉ:: ድርደራቸውን እንደጨረሱም ከሳጥኑ ጎን ካለው ሌማት ውስጥ ሙሉሙል አውጥተው 4 ቦታ ከፋፈሉና በተላላጠ ነጭ የብረት ሳህን አቀረቡላቸው:: ከዚያም ወጣ ብለው ጥቂት የደረቁ ቅጠሎችንና እንጨቶችን ይዘው ተመለሱ:: ከጠፍር አልጋቸውም ቁጭ ብለው ምድጃው ላይ እሳት ለማያያዝ ሲሞከሩ መርየም ከተቀመጠችበት ተነሳችና ምድጃውን ይዛ ወደ ውጭ ወጣች::

"አንቺ ልጅ ምን ማለትሽ ነው? እንግዳን ማስራት ወጋችን አይደለም::" አሉ፣

"ኧረ ችግር የለውም ወላሂ፤ እኔ ደግሞ እሳት ሳቀጣጥል ጎበዝ ነኝ::" አለችና በፍጥነት እሳቱን አቀጣጥላ አመጣች:: ማንቆርቆሪያውንም በሚገባ አጥባ ውሃ ጣደች::

"ተባረኪ ልጄ! ስሟን ይዘሽ የምትጠሪባት ድንግል ማርያም ፀጋ ካንቺ ጋር ይሁን፤" ካሉ በኋላ ወደእነ አብርሃም ዞረው፤... "ብሉ እንጂ ልጆቼ! ወይስ ሻዩን እየጠበቃችሁ ነው::" አሏቸው::

"አይጨነቁ እንበላለን እትቴ፤ እርሶስ አይበሉም እንዴ?" አለ ኢትኤል፤

"አይ እኔ እንኳን ይቅርብኝ ልጄ፤ የእናንተ መምጣት ከምታስቡት በላይ አጥግቦኛል... ለመሆኑ እህቴና እባትህ ደህና ናቸው?"

"አዎ ደህና ናቸው... ምን ይሆናሉ ብለው ነው፤" አለ ኢትኤል እያቀረቀረ፤

"የፈጣሪ ያለህ ካየኋቸው እኮ ስንት ዘመን ሆነ... ለነገሩ ሁሌም በፀሎቴ ሳላስባቸው ቀርቼ አላውቅም::" አሉና ተከዝ ብለው መፅሐፍቶቻቸውን ያዩ ገቡ፤.. በዚህ አጋጣሚ ናዖድ በውስጡ ሲመላለስ የነበረውን ጥያቄ አቀረበ፤

"ይህን ሁሉ መጽሐፍ ግን አንብበውታል?"

"አይ ልጄ! ድሮ መቼ እንዲህ እንዳሁኑ ቀርፋፋ ሆንኩኝና፤ መፅሐፍ ከያዝኩኝ ፉት ነበር የማደርጋት:: ታዲያ ይህ የማንበብ ተሰጥኦዬም ነው፤ ለዚህ መንፈሳዊ መንገድ የረዳኝ:: አዋቂ ነኝ እልበት ከነበረው ጠባብነቴ አውጥቶ ያሰፋኝ:: እናም ልጄ ይህ ሁሉ የምታየውን ማንበቤ ሊገርምህ አይገባም ምክንያቱም የሰው ልጅ ጥበብ እንደረጋች ትንሽዬ ኩሬ ነች:: የእግዚአብሔር ጥበብ ግን አህጉራትን አቋርጦ ከሚፈስ ወንዝ ይልቃል::"

"ይህንን ህይወት እንዲመርጡ ያደረጎት ንባብ ነው እያሉን ነው እትቴ?" አለ ኢትኤል በመገረም::

"መንግስተ ሰማይ ብሩህ ልቦና ነች›› እንዲሉ አረጋዊ፤ ከንባቤ በላይ ልቦናዬን የመራውን አምላክ አመሰግነዋለሁኝ:: ግን ንባቤም አስተዋጽኦ እንዳደረገልኝ አልክድም::" አሉ አሁንም መጽሃፍቶቻቸውን በስስት እያዩ::

መርየም የፈላውን ሻይ በቀካ ኩባያ እየቀዳች ለሁሉም አከፋፈለች::

"ለምን ይሆን ይህንን ቦታ የመረጡት?" ጠየቀ ናዖድ፤ ሙልሙሉን ገምጦ መርየም በሰጠችው ሻይ እያራሰ፤

"ያኔ ገና በወጣትነቴ መንፈሳዊ መጽሐፎችን ሳነብ ‹‹ራማ›› የሚለው ቃል ለየት ያለ ትርጉም ይሰጠኝ ነበር:: ብዙ ስለ ቃሉ ባጠናው ቁጥርም፤ እኔ ለቃሉ ትርጉም ያለኝ ስፍራ እየሰፋ መጣ::" አሉና ከሻዩ አንዴ ተጎነጩለት::

"የማትስለቱ ከሆነ ትርጉሙን ልንገራችሁ?" አሉ ተራ በተራ እየተመለከቷቸው፤

"ኧረ አንስለችም አባ... እዚህ ድረስ የመጣነው ለእውቀት እንጂ ሌላ ለምን ሆነና!" አለ አብርሃም፡፡

"እሺ እንግዲያውስ ***ራማ*** ወይም ***ራዕማ*** ወይም ደግሞ ***ራህማ*** ስለሚለው ቃል ከብዙ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች አንጻር ሰፊ ጥናት ስላደረኩኝ ሰፋ አድርጌ ልነግራችሁ እችላለሁኝ፡፡ ራማ በጥቅሉ የስጋ፣ የነፍስና የመንፈስ ከፍታ የሚያሳይ ቃል ሲሆን ከላይ የመንግስተ-ሰማይ ስፍራ፤ የዝማሬ ቅዱስ ቦታ ስምም እንደሆነ ቅዱሳን መፅሐፍት ይዘግባሉ፡፡

በምንወደው አማርኛ ቋንቋችን መሰረት "ራ'ማ" ማለት ከራብዕ ፊደላት ድምፆች ‹‹ቅናት››ነት (ወደላይ ከፍ ማለት) ጀምሮ እንደምንረዳው ወደላይ መውጣት፤ ከፍታ ላይ መድረስ ወይም መነሳትን የሚገልፅ ቃል ነው፡፡ የኢትዮጵያ መፅሐፍ-ቅዱስ ማህበር ያዘጋጀው የመፅሐፍ-ቅዱስ መዝገበ ቃላት "ራ'ማ" የሚለውን ቃል፤ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳንን አጣቅሶ "ከፍታ" ሲል ይተረጉመዋል፡፡ በእብራይስጥ ቅዱስ መፅሐፍት ዘፍጥረት 10፤7 ላይ በሽርፍታ እንደሚታየው ደግሞ "ራዕማ" የኩሽ ልጅ ሲሆን ቃሉም፤ የህዋ አምላክ መብረቃዊ ነፀብራቅ ወይም ጥቁር ደንዳና አቋም የሚሉትን ሊወክል ይችላል፡፡ ከዚህም በኋላ በኢትዮጵያ የነገሰውን ታላቅ መሪ ንጉስ ራህማይ ወይም የእስያኤል ስም ሆኖም ቃሉን እናገኘዋለን፡፡

የቃሉን ፊደላት ቀጥታ ወስደን ራማ `Rama` የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል ብናይ ደግሞ Aries(ኤሪየስ) ለሚለው ቃል ቀጥታ ተተኪ ሆኖ እናገኘዋለን፤ "ኤሪየስ" ማለት ደግሞ በኮኮብ ቆጠራ መሰረት የእሳት ምልክት የሚሰጠውን የከዋክብት ስድር ይወክላል፡፡

ወደ አረ-ቢያ በረሀ ወርደን የቃሉን አረብኛ ፍቺ ካየነው ውበት የሞላባትን ሴት ልጅ ወይም አስደናቂ ሙቀትን ይገልፃል፡፡ በእነ መርየም ቅዱስ-ቁርዓን አንፃር ደግሞ *ራማ* ወይም *ራህማ* የሚለው ቃል እዝነትና ምህረት የሚገልፅ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- "አ‹ራህማ›ን" ከ99ኙ የአላህ ስሞች አንዱ ሲሆን ታላቅ የሆነ ምህረትን ይወክላል፡፡ ምህረት ደግሞ የተቀሩትና የፈጣሪ ባህሪያትን አሸንፎ ከበላይ እንደሆነ ይገልፃል፤ ***ራማዳን*** የሚባለው ቅዱስ-ቁርዓን እንደወረደበት የሚታመነው ወርም የስያሜው ቀጥተኛ ትርጉም የሚያንፀባርቅ ብርሃን እንደማለት ነው፡፡ መፀሐፍ ቅዱስም ቢሆን ምህረትን የሚያስበልጥበትና ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጥበት ጥቂት የማይባሉ ጥቅሶች አሉ፡፡ በእኛም ሀገር ሙስሊም ማህብረሰብ ዘንድ እንደሚታወቀው "***ከራማ***" ማለት

ለየት ያለ አልያም በላጭ የሆነ መንፈሳዊ ሁኔታ ላይ መገኘትን ያሳያል:: ይህም አንድ ሰው "ከራማው መጥቷል" ከተባለ መንፈሳዊ ምጥቀት ውስጥ ገብቷል ማለት ነው::" አሉና ለማስታወስ በሚመስል ሁኔታ ለአፍታ ዝም አሉና ቀጠሉ::

"ከአረቢያ ባህረ ሰላጤ ወደምስራቅ አቅጣጫ በስሱ ስንሻገር የዓለማችንን ቀደምት ከሆኑት አንዱ ሃይማኖት፣ ሂንዲዩዝምን እናገኛለን:: በዚህ እምነት መሰረት "ራዕማ" የሚለው ቃል ከነሱ ሶስት ዋና ዋና አማልክቶቻቸው አንዱ የሆነው የቪሽኑ ሌላኛው መጠሪያ እንደሆነ እንገነዘባለን:: ከቪሽኑ ውጪ ያሉት ሁለቱ አማልክት መካከል አንደኛው ብራህማ (በ - ራህማ) ሲባል የመፍጠር ባለቤት ተደርጎ ይወሰዳል፤ ሁለተኛው ሺቫ የሚሉት ደግሞ የጥፋት(ሞት) ፈራጅ እንደሆነ ያምናሉ:: እንግዲህ ቪሽኑ (ራዕማ) የሚሉት በሁለቱ አምላኮች መካከል ሚዛንን እንዳይዛባ እያደረገ (እያመጣጠነ) ህይወት ፍሰቷ እንድትቀጥል የሚያደርግና የሚያቻችል ነው ብለው ያምናሉ:: የእነሱን ትርጉም ለእነርሱ ትተን ቢያንስ ግን ቃሉ ጥንታዊና ጥልቅ ትርጉም እንዳለው፤ እንደሚጠቁም እንረዳ::

ከላይ እያጣቀስን ባየናቸው የቃሉ ትርጉም መሰረት *ራዕማ* ማለት የዝማሬ ሰማያዊ ግዛትን፣ የኩሽን ልጅ፣ ከፍታን፣ ከዚያም ታላቁ ንጉስ እስያኤልን፣ ልዩ የሚያበራ ፍላፃን፣ ምህረትን፣ ... ልዩ የሆነ ልቅናን እንደሚገልፅ እንደተረዳችሁ ፅኑ እምነቴ ነው::" አሉ ሁሉንም በተራ ተራ እየተመለከቱ፣ እነኢትኤል አንገቶቻቸውን በአዎንታ ነቀነቁ፤

"እንዲሁ ደግሞ **'ኤቶጵም ከራማ ተራራ ይመጣል'** እንዲል ቃላቸው... እውነት ቢዳፈንም ላይጠፋ... የመንፈሳዊ ምጥቀት ማማ ቅድስት ሀገራችን ፣ እስካሁንም ድርስ ይህቺም ገዳም ‹‹**ራማ**›› ተራራ ላይ ከመገኘቷም በላይ፤ ከአደዋ ባሻገር ‹‹**ራማ**›› የሚባል መንደር መኖሩ ለዚህ ትርጓሜ አንዱ ማሳያ ነው:: ከመሬትም በላይ በአርያም ምድር መንፈሳዊ ዳር ድንበር ያላት **ኤቶዮጵያ** ተምሳሌት ኢትዮጵያ መሆኗን ማወቃችን ለኛም ፀጋ፣ ለታላቅ ማንነትም መነሳሻ ሊሆነን ይገባል:: የ**ራማ**ም ተራራ የከፍታችን መገለጫ የሆነ የጥበብ ቦታ ነው::" አሉ፤

"ይገርማል... ስለዚህ ‹‹በዚህ የመንፈስ ከፍታ መገለጫ በሆነ ቦታ ደስታን አገኘ ዘንድ ነው የመጣሁት›› እያሉን ነው አባታችን?" አለ አብርሃም ሻዩን ጨርሶ ኩባያውን እያስቀመጠ፤

"ምክንያቴ እንኳን ከዚያም በላይ ነው:: የእግዚአብሔር ጥሪ ደግሞ ምክንያት አያሻውም:: ነገር ግን ከፍታችን ከእግዚአብሔር እግር ስር ዝቅ

ከማለት ነው ሊነሳ የሚገባው፡፡ ከፍ ከፍ ያለች ሁሉ ዝቅ ተደርጋ ትብያ ላይ እንደምትጣል ሁሉ፤ የህይወትም ሚስጥር እንዲሁ ይመስላል፡፡ ለዚህም ነው ጠቢባን በአንድ ድምፅ 'መንፈሳዊነት የሌለበት ምድራዊ ከፍታና ደስታ፤ ጥልቅና ዘላቂ አይደለም' ሲሉ የሚናገሩት፡፡ ይህም ሆኖ ግን ለሰው ልጅ ትካዜና ጥርስ ማፏጨትን፤ ከማቅረብ ይልቅ ደስታን መስጠቱ የተሻለ ይሆናል፡፡

"ሁሉም የከንቱ ከንቱ፤ ከንቱ ነው ንፋስንም እንደመከተል ነው" ያለው ጠቢቡ ሰለሞንም መልሶ ደግሞ "ሰው ደስ ከሚለውና በሕይወት እስካለ፤ መልካምን ነገር ከሚያደርግ በቀር፤ መልካም ነገር እንደሌለ አወቅሁ" ያለው ለዚህ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ከፍታ ቦታ ሆነን ለሰው ልጅ እውነተኛ ደስታና ሰላም ይሰጥ ዘንድ እግዚአብሔርን እንለምነዋለን፡፡" አሉና በገናቸውን አንስተው በሚያምር ድምፅ የዕዝራን መዝሙር ይዘምሩ ገቡ፤ እነኢትኤል በመገረም ውስጥ ሆነው ያዳምጧቸዋል፡፡

*"♪ ♫ በብርታት አለ በግርማ*

*…….በክብር በላይ በራማ*
*ከቋንቋ በላይ ነህና ይድረስህ ምስጋና /2x/*
*ውኖቹን በሰለፋ - በተራሮች አቁመህ*
*የምድርንም መሰረት - በጥልቁ ላይ መስርተህ፤*
*ከህሊና መረዳት - ከቃላት ጉልበት በላይ*
*ያልሰራኸው ቢጠፋ - ስመህ ሆነ ኤልሻዳይ፡፡*

ዝማሬአቸውን ገቱና ወደነኢትኤል ዞሩ፤ "አረፍ ካላችሁ ዘንዳ ከእኔ ሽታችሁ የመጣችሁትን ማረጋገጫ እነግራችኋለሁኝ፡፡ ልጆቼ እንዳትረሱ አይንን የምታበራ ጥበብ ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት። ሰይጣን እግዚአብሔር ለኛ የሰጠንን ጥበብ፤ በኛ በጎ ፍቃድ በኩል ተጠቅሞ እያጣመመ ከፉ ከማድረግ በቀር ከራሱ አንዳችም ጥበብ ሊፈጥር አይቻለውም። ሰይጣን እኛን ለማጥቃት የሚያደርገው ተግባር አንገቱ ላይ ሰንሰለት ታስሮበት እንደሚጮህ፤ ከማስፈራራት ውጪ እኛን ሊነከስ በማይችል ውሻ ይመስላል። እኛም በቸልተኝነታችን የእምነት ብርሃናችንን ሳናበራ በጭለማ ከተጓዝን ሰይጣን እንደ ውሻው መታሰሩን አናውቅም፤ የታሰረበትንም ሰንሰለት አናይም፤ እየጮኸ ሲያጓራም አጠገባችን መጥቶ የሚነክሰን ይመስለንና እንፈራለን። ፈርተንም ደንብረን እንሮጣለን። በማናውቀው የስሜት መንገድ በጭፍን ስንፈረጥጥም ካስቀመጠልን ወጥመዶች ውስጥ እንወድቃለን።"

"ወጥመዱ ምን ይሆን አባ?"… አለ አብርሃም።

"ወጥመዶቹማ ብዙ ናቸው ልጄ። የሥጋችንም ፈተና ዋናው መለያው ነው፣ ሐዋሪያው ጳውሎስ ወደ ገላትያ ሰዎች በላከው መልዕክት ምዕራፍ 5 ቁጥር 19 ጀምሮ እንደፃፈው "የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኩሰት፥ (20፤) መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ (21፤) መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካርና ከልክ ያለፈ ፈንጠዝያ፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። (22፤) የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። (23፤) እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። (24፤) የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።" ብሎ ይነግረናል:: ከዚህም በተጨማሪ ትዕቢት፣ ተንኮል፣ ክፋት፣ ገንዘብ አምላኪነት፣ እኔ ብቻ ነኝ የሚል ትምክህተኝነት፣ ዘረኝነት፣ ጭካኔ እና ስግብግብነትን መጥቀስ ይቻላል::

ታዲያ እነዚህ እና መሰል ወጥመዶች ውስጥ ከወደቅንለት በኋላ ሰይጣን ወደታሰረበት ቤቱ እንገባለታለን። በቤቱ ደግሞ አይኖቻችን ታውረው በዋዛ እየተነዳን እንገዛለታለን ፤ እሱም እንዳሻው ይገዛናል። ያኔ በእሱ የሃጢያት ቤት፣ የቁም ገሃነም ውስጥ የውሸት ደስታን ስንቃርም እንዋትታለን።" አሉና እንደመተከዝ ብለው ከቆዩ በኋላ፤ "ልጆቼ ሃይማኖት ማለት እነዚህ ወጥመዶች ውስጥ እንዳንገባ የምናይበት ላምባዲና እንጂ እንዳሁኑ የሚያጣላ ትብታብ አይደለም:: አንድ መሆኛና የሰው ልጅን ወደከፍተኛ የስነ-ምግባር ልቀት ማድረሻ አሰንሳር ነበረ::

ነገር ግን የዚህ ዘመን ሃይማኖት ለጥላቻና ለብር መጠቀሚያ ሆነ:: በሃይማኖት መሪዎች ልብ ሳይቀር ክህደትና ቸልተኝነት ተንሰራፋ:: ወንድና ወንድ ተጋባ፤ ሴትና ሴት ተጋባ፤ ሰውና እንስሳት ተጋባ፣ ሰውና ሃውልት ተጋባ፣ ስንቱ የእግዜር ፍጥረት ተረግጦ እየታለፈ ለሮቦት ሰብዓዊ መብት ተሰጠ፤ ለሰይጣን ማምለኪያ ቤት ተሰራ፣ በአደባባይም ሰይጣን ክብር ተሰጥቶት ተመለከ:: የሰው ልጅ ወደ እንስሳነት ደረጃ ወረደ:: በአደባባይ መስቀል ተረገጠ፣ ቁርዓንና መፅሐፍ ቅዱስ ተቃጠለ፤ እውነተኛ ካህናት ተናቁ አልባሌ ቃላትን የሚዘፍኑ ግብዞች እጅግ ከፍ ከፍ ተደረጉ:: የዘመኑ ጣዖታትም እነዚሁ አላዋቂ ታዋቂዎች፣ ብርና መሳሪያ፤ ሃያል ሆኑ:: መስከርና መዘሞት እንደ ስልጣኔ ተቆጠረ፤ ወዲህ አምላኪው ተመለከ፤ ወዲያ ደግሞ ኢ-አማኝ ሰው አምላክ የለም እያለ በኩራት የሚጓዝበት ዓለም ተፈጠረ::" አሉና አንገታቸውን ወደ መሬት ደፍተው ከቆዩ በኋላ ለዘብ ባለ ድምፅ ቀጠሉ...

"ይህ የጥፋት ማዕበል ዓለምን አዳርሶ፤ የቅድስት ምድራችንን ደጆች እያንኳኳ ነው፤ ዳሩ ግን መሃሪው አምላካችን፤ የማይተኛው እረኛችን፤ መቼም ቢሆን ህዝቡን አይረሳምና ይገለጣል፡፡ እኛም እለት ተእለት የበደል ልብሶቻችንን እያጠብን፤ እያነፃን እንዘጋጃለን። እምነታችንን በተግባር እያስረገጥን እንጠብቀዋለን፡፡"

"እምነት ምንድነው አባት?" አለ ናዖድ፤ ተግባርና እምነትን እኩል መጥራታቸው አልተዋጠለትም ነበርና፡፡

"ልጄ ናዖድ፤ እምነት ባዶ ብርጭቆ ይዞ ከሰማይ የሚመጣን ዝናብ እንደምትጠብቅ የዋህ ህጻን ልጅ ትመሰላለች፡፡

የደመናው ጠብታ ብርጭቆዋን እንደሚሞላላት አምና በርግጠኛነት ትጠብቃለች፤ ብርጭቆዋን ግን ሳትለቅ ጥብቅ አድርጋ ይዛለች፡፡

ኢ-አማኝነት በወርቅ የተሞላ በርሜል ይዞ፤ ሌላ ሀገር ለመሸጥ በረሃ አቋርጦ በሚሄድ ቆንቋና የወርቅ ነጋዴ ይመሰላል፡፡ የያዘው ውሃ አልቆበት በበረሃው ውስጥ የውሃ ጥም እያንገበገበው የሚሄድ፤ ፈጣሪ ችግሩን አይቶ ዝናብ ከሰማይ ቢልክም በርሜሉን ከፍቶ ከመቅዳት ፋንታ ወርቁን ጎርፍ እንዳይወስድበት በርሜሉን ጠርቅሞ በሚቆልፍ፤ ዝናቡ ካባራ በኋላም የውሃ ጥሙ በርትቶበት የሚነግድበት ከተማ ሳይደርስ ወርቁን እንዳቀፈ ከበረሃው እንደሚሞት ነጋዴ ይመሰላል፡፡ ስለዚህ ልጄ እምነት በመስማት ነው፤ መስማትም በቃሉ ነው እንዲል፤ እምነት መስማትና በማወቅ ይጀምራል፤ በልቦና ማስረጽም ይከተላል፣ በቃል መመስከርም ይሰልሳል ከሁሉም በላይ ግን በተግባር በመኖር ይገለጻል፡፡ እምነት ካለ ተግባር፤ ደመና ካለ ዝናብ፣ ፀሐይ ካለ ሙቀትና ብርሃን ወይም ይሄ የያዝከው ስልክ ካለ ባትሪና ኔትዎርክ እንደማለት ነው፡፡ በያዕቆብ መልዕክት ምዕራፍ 2 ቁጥር 17 ላይ "እንደዚሁም ስራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው፡፡" እንዲል «አምኛለሁኝ፣ ጌታን እወዳዋለሁኝ» ብሎ የሚል ሰው በተግባሩ ማሳያት አለበት፡፡ ጌታችን መድሐኒታችን እየሱስ ክርስቶስም "የምትወዱኝስ ብትሆኑ ትዕዛዛትን አክብሩ!" እንዳለን በእሱ ማመንህ፣ እሱን መቀበልህና መውደድህ ትርጉም የሚኖረው ስነ-ምግባርህ የተሟላ፣ ከኃጢያትም የራቅህ ስትሆን ብቻ ነው፡፡" ብለው ናዖድን አዩትና ወደነኢትኤል ዞሩና ንግግራቸውን ቀጠሉ፤

ናዖድ እስካሁን ከመጣበት መንገድ በሙሉ የሚጠቅመውን ምክር ያገኘው አሁን ነበር፡፡ አዕምሮው ውስጥ አሁን እየተሰማው ያለው የእርሳቸው ንግግር ሳይሆን የሚወደው፤ ሁሌም ለየት ያለ ስሜት የሚሰጠው የእየሩሳሌም ነጊያ መዝሙር ነበር፤

*"♫ በልቤ ፅላት ላይ ጻፍኩት ህግሕን*
*ከትዕዛዛትህ ፈቀቅ እንዳልል፣*
*አቤቱ እንዳልበድልህ ቃልህን በልቤ አኑር*
*አምላኬ እንዳልበድልህ ቃልህን በልቤ አኑር፤*
*በአፍህ ጥበብ በህግሕ ፍሬ*
*ጎተራዬ ይሙላ አይጉደል ከቤቴ፥*
*ረቂቅ እውቀትህ ከአንቁ ትበልጣለች*
*ወደ ማስተዋልህ ነፍሴ አዘንብላለች፤*
*…ህጌን ልብ በል አስተውል ልጄ ሆይ*
*ጥበቤን አግኝት ከአፏ ዞር አትበል*
*እድሜን የሚያረዝም በጎ ተግሳፅ አለ፥*
*በጎ ምክሬን ስማ በህይወት ትኖራለህ*
*የቃሉ ፍቺ ያበራል ህፃናትን አስተዋይ ያደርጋል*
*የቃሉ ፍቺ ያበራል አዕምሮ ለጎደለው ማስተዋል ይሰጣል።"*

"ልጅ ናዖድ ከእኛ ጋር ነህን?" አሉት በሃሳብ መንጎዱን ያስተዋሉት አባ ኤልካኖ፤ "አዎ አንድ ሃሳብ ውስጥ ተመስጬ ነው…" አለና ወደነኢትኤል ዞሮ፤ "ኢታ፣ አብርሽና መርየም፣ ይቅርታ አድርጉልኝ… አሁኑኑ መሄድ አለብኝ።" አለ።

"እንዴ ምን ማለትህ ነው?" አለ አብርሃም በድንጋጤ፤

"ከእኔ ብዙ የቤት ስራ እንደሚጠበቅብኝ የተረዳሁት ዛሬ ነው! አሁኑኑ ሄጄ ማስተካከል ያለብኝ ነገሮች አሉ።" ብሎ፤ ለመነሳት ሲዳዳም፤

"ተው አሁን መውጣት አትችልም!" አሉት አባ-ኤልካኖ ጠበቅ አድርገው… "ሰዓቱ መሽቷል፤ በዚህ ሰዓት ጫካውን ማቋረጥ አደጋ አለው። ታገስና ዛሬን እዚቼ አድረህ ጥዋት ትወጣለህ።" አሉት። ናዖድም በሃሳባቸው ተስማምቶ ተቀመጠ፤ እርሳቸውም ንግግራቸውን ካቆሙበት ቀጠሉ።

"… እናም ልጆቼ እግዚአብሔር ስንዴውን ከገለባው የሚለይበት መንሽ በእጁ ነው። ተዓምራትን በሚያደርጉና የቅርብ የቅርቡን ነገር በሚገምቱ ሰዎች፤ ስለምን ትገረማላችሁ? አመንዝራ ትውልድ ምልክትን እንደሚሻ ሁሉ ምልክትን የሚያበዙ የሐሰት ነብዮች እንደሚመጡ ጌታችን መናገሩን አታስተውሉምን? ምድራዊ ሃይልና ሃብት የእምነት መገለጫ እንዳልሆነም እወቁ። የዘመኑ ሃያላን በብረታ ብረትና ኬሚካል ቅመማ፤ ትላልቅ ኒዩክሊዬር ቦንቦችን ቢሰሩም እግዚአብሔርን ካልያዙ ግን ሃይላቸው በሙሉ እንደትንኝ ከንፍ ትቀጥናለች።

አዎ አሁንም ንቁ! ሃይማኖቶች እንደ ኮከቦች ናቸው:: እንደ ኮከቦች ብርሃንም የተለያየ ቅርጽን መወከያ ምስላቸው ያደርጋሉ:: እርግጥም ሃይማኖቶች በትክክለኛው ሀዲድ ከተጓዙ ወደ ጥበብና መንቃት የሚያመሩ የኮከብ ብርሀኖች ይሆናሉ:: ያ! ሳይሆንና ‹‹እኔ ብቻ አዋቂና ትክክል ብለው ሌላውን የሚንቁና የሚያጠቁ›› ከሆነ ደግሞ የሞተ ኮከብ ሆነው ወደ ‹‹ብላክ ሆልነት›› በመቀየር የተጠጋቸውን በሙሉ የሚያጠፉ ሰይፎች ይሆናሉ::

... ነገር ግን በሃይማኖትም ያልተገደቡ ምክሮቼን ስሙና አስተላልፉ፤ ምንም ነገር በራሱ መጥፎ አልያም ጥሩ አይደለም:: እኛ ያንን ነገር የምንጠቀመው ወይም የምናደርገው መቼ? የት? እንዴት? ለምን? እና ወዘተ የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው የዚያን ነገር ፋይዳ የሚለዩት:: በመሰረቱ እ/ር ሁሉንም ነገር ለበጎ እንጂ ለክፉ እንዲውል አልፈጠረም:: ትልቁ ስህተታችን የሚጀምረው አንድን ፍጥረት፣ ስም፣ ቅርፅ ወይም ስዕል አንስተን የሰይጣን ነው ማለት የጀመርን ጊዜ ነው:: **‹ስዋስቲካ›፣ ‹የአጥቢያ ኮከብ›፤ ‹የይሁዳም ባለ ስድስት ኮከብ›፤ ‹ጨረቃና ባለ 5 ኮከብ ቅርጽ›፤ ‹የሚበራ ቸቦ›፤** ሁሉም የእግዚአብሔር ፍጥረታትና የጥበቡ መገለጫዎች ናቸው:: ቅድም እንደነገርኳችሁ ሰይጣን እግ/ር ለኛ የሰጠንን ጥበብና የእርሱ መገለጫዎች የሆኑትን ነገሮች በኛ በጎ ፍቃድ በኩል ተጠቅሞ እያጣመመ ከፉ ከማድረግ በቀር ከራሱ አንዳችም ጥበብ ሊፈጥር አይቻለውም። እኛ ግን የሰይጣን ምልክት ብለን እውቅና በሰጠነው ቁጥር ስውሩ አላማው ተሳካ ማለት ነው:: አንዳንድ የዋህ ሰዎች የሰይጣንን ስውር ስራ ያጋለጡ መስሏቸው ‹‹ኃያል ነው›› እያሉ ለደካማው ሰይጣን እውቅና ይሰጣሉ:: እኛ በእምነት ለተሰለፍን ግን ሰይጣን ማለት የገለባ ታህል እንኳን አቅም የሌለው ፍጡር ነው::”

“ነገር ግን ሰይጣን የኛን በጎ ፍቃድ ካገኘ እጅግ ታላላቅ ጥፋቶችን በምድር የማድረግ አቅምን ያገኛል:: ይህ መሰሪ ስራው ደግሞ ዓለምን አጥለቅልቋል:: ለዚህም መፍትሔ ይሰጥ ዘንድ የጌታ መገለጥ ደርሷል::

“እነሆ ትንቢት የተነገረላት ጋለሞታይት ሃገር በዓለም ነግሳለች:: የዓለም መንግስታትንም፤ ከኃጢያት ፅዋ ለማጠጣት እየታተረች ነው:: አሁን ልብ ያለው ልብ ይበል!! በማስተዋልም አሁን ምድር ላይ የነገሰችውን ከተማ በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 17 ትንቢት ከተነገረላት ከተማ ጋር ያነፃፀር:: ራእዩም እንዲህ ይላል!

*ቁጥር 1፤ ‹‹ሰባቱንም ጽዋዎች ከያዙ ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ። ና በብዙም ውኃዎች ላይ የተቀመጠችውን የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ፡›› ይላል*

ይህም ገና የሚፈጸም ነገርን መልዓኩ ለቅዱስ ዮሐንስ ኢያሳየው ሲሆን ውኃ የሚለው ቃል ብዙ ህዝብና ጭፍራ፡ ስልጣንና ተሰሚነት ያላት መሆኑን አመላካች ነው::

በቁጥር 2 ደግሞ ‹‹የምድርም ነገሥታት ከእርስዋ ጋር ሴሰኑ በምድርም የሚኖሩ ከዝሙትዋ ወይን ጠጅ ሰከሩ ብሎ ተናገረኝ።›› ይላል:: ከራሷ አልፎ ለሌሎች ሃገራት መሪዎች፣ የከፋት ምንጭ የሆነች፣ እንደ ማሳየም በአሁኑ ዘመን በባዕድ አምልኮ ላይ የተሰማራች፣ ለሰይጣን ቤተ-አምልኮ የሰራች፣ ልቅ ወሲብን ከራሷ አልፎ ለዓለም የምታሰራጭ፣ ግብረ-ሰዶማዊነትንም ኢያበረታታች በብልግና ቪድዮዎች ዓለምን ያጥለቀለቀች፣ ሀገርን አመልካች ነው::

በቁጥር 3፤ ‹‹በመንፈስም ወደ በረሀ ወሰደኝ፤ የስድብም ስሞች በሞሉበት፥ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ባሉበት በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ።›› ያለው ቃል የሚያሳየው ሰባት ነገስታትን/የሀገር መሪዎችን ሲሆን፣ አስሩ ቀንዶችም፣ አስር የዓለም አቀፍ ተቋማትንም ይወከላል:: ህዝቦቿ በአፋቸው ላይ የእናትን ክብር የሚያጎድፉ፣ የሴትን ልጅ ክብር ወደ ውሻና ሴተኛ አዳሪነት የሚያወርድ ስድቦችን በብዛት የሚጠቀሙባት፣ ለምሳሌ ‹‹ሆሊ-ሺት›› ኢያሉ ቅድስናን በእርከሰት ስድብ የሚተኩ ሰዎችን ያፈራች::

በቁጥር 4 ላይ ደግሞ ‹‹ሴቲቱም በቀይና በሐምራዊ ልብስ ተጐናጽፋ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች በዕንቁችም ተሸልማ ነበር፥ በእጅዋም የሚያስጸይፍ ነገር የዝሙትዋም ርኵሰት የሞላባትን የወርቅ ጽዋ ያዘች፤›› ተብሎ የሰፈረ ሲሆን ከውጭ ስትታይ ኢያማለለች ከፋቷን እንዲዘነጋ የምታደርግ፣ ይህቺ ቀይና ሰማያዊ/ሐምራዊ ቀለም ያለው አርማ ያላት ሃገር፤ እነዚህ ቀለማት አንዲት የጋለሞታነት መለያ ሴት የእርኩሰት ምልከት የሆነላትን ችቦ ይዛ በስራም፣ በሃውልት ደረጃም የገነባች፤

በቁጥር 5ና 6 ላይ "በግምባርዋም ምስጢር የሆነ ስም። ታላቂቱ ባቢሎን፥ የጋለሞታዎችና የምድር ርኵሰት እናት ተብሎ ተጻፈ። 6፤ ሴቲቱም በቅዱሳን ደምና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ አየኋት። ባየኋትም ጊዜ እጅግ ታላቅ ድንቅ ኢደነቅሁ።" ተብሎ ተከትሏል፤ የጋለሞታዎችና የምድር ርኩሰት እናት ሆና በስራዋ፤ ሌሎች የሃጢያት ተባባሪዎችን የምታፈራ፤ በቅኝ ግዛትና በዓለማት ጦርነት ስም፤ የሚሊዮኖች ንጹሃንን ደም ያፈሰሰችና፣ አሁንም ኢያፈሰሰች ያለች:: የኢየሱስ ምስክሮች የሆኑትን ለድሃ፣ ለባሪያና ለደካማ ወግነው የቆሙትን በአደባባይ ያስገደለችና በደማቸው የሰከረች ከተማን ይወከላል::በቁጥር 7 ላይ፤ "መልአኩም አለኝ። የምትደነቅ ስለ ምንድር ነው? የሴቲቱን ምስጢርና የሚሸከማትን፥ ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ያሉትን የአውሬውን ምስጢር እኔ እነግርሃለሁ።" ይልና ቀጥሎም በቁጥር 8 እና 9... 8፤ ያየኸው አውሬ አስቀድሞ ነበረ፥ አሁንም የለም፥ ከጥልቁም ይወጣ ዘንድ አለው፥ ወደ ጥፋትም ይሄዳል፤ ስሞቻቸውም ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ አውሬው አስቀድሞ እንደነበረ አሁንም እንደሌለ፥ ነገር ግን ወደፊት እንዳለ ሲያዩ ያደንቃሉ። 9፤ ጥበብ ያለው አእምሮ በዚህ ነው። ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራራዎች

*ናቸው፥" ብሎ ይነግረናል፡፡.... ይኸም* ***ባቢሎን*** *የምትባለው ታላቅ ግዛት ከጌታችን ከእየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት የነበረችና የጠፋች ሀገር ተምሳሌት ስትሆን፤ ባለራእዩ ዮሐንስ በኖረበት ዘመን የሌለች ነገር ግን እሱ ካለፈ በኋላ ወደፊት የምትነሳ መንግስት እንደሆነች ይተነብያል፡፡ ወረድ ብሎ በቁጥር 18 ደግሞ ‹‹ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት የምትነግስ ታላቅ ከተማ ናት›› ብሎ በግልፅ በምድር ላይ የምትሰለጥን ከተማ እንደሆነች ፍቺውን ይነግረናል፡፡ በምዕራፍ 18፡4 ላይ ደግሞ ከዚህች ከተማ እንድንወጣ ያዘንና በቁ.6 ላይ ደግሞ በሰጠች መጠን ብድራትን እንድንመልስላት ያዘናል፡፡ እነሆ እኔ ደግሞ ይህቺ የባቢሎን መንግስት በኛ ዘመን እንደተነሳች እመሰክራለሁኝ፡፡"* አሉና በረጅሙ ተነፈሱ፤ ሁሉም በሙሉ ትኩረት እያደመጧቸው ነበር፤ ናዖድ ግን ስለነገ ጉዞውና ያወቀውን ለሌሎች የማስተላለፊያ መንገድ እያሰላሰለ አብዛኛውን ንግግራቸውን አልሰማም ነበር፡፡"… ለዛሬ ይህን ካወቃችሁና በልባችሁ ካሳደራችሁ በቂ ነው፡፡ እንግዲህ መርየምን ከመደቡ ቦታ ስጧትና፤ እናንተ አጉዛ አንጥፉችሁ ተጠጋግታችሁ ተኙ፡፡ እኔ ማስቀደስ ስላለብኝ ወደ ቤተ-ክርስቲያኒቱ እሄዳለሁኝ..." አሉና ከመደባቸው ወርደው… "በሉ በቸር እደሩልኝ፤" ብለዋቸው ወጡ፡፡ ኢትኤል በፍጥነት የግጥም ደብተሩን አውጥቶ ለዚህች በትንቢት ለተጠቀሰች የኃጥያት ሃገር ገጠመላት፤

*✍…ዳግማዊ ባቢሎን*

*በስልጣኔያቸው - ተኩራርተው ሲመኩ*
*አምላክ የለም" ብለው በስላቅ ሲያሽካኩ*
*የበላዩን ጌታ በብረት ጋጋታ - በጉራ ሲተኩ*
*ሶዶማዊያን በዝተው- ከገደቡ ሲያልፉ*
*ወሲብና ሱስን ለዓለም ሲሰብኩ*
*እርቃን ጣዖታትን አድንቀው ሲያገዝፉ*
*ከልክ በላይ ሀብትን ደምረው ሲያመልኩ*
*ሀገርን ከሀገር - ህዝብን ከህዝብ -ብሔርን ከብሔር*
*በድብቅ መሳሪያ ኖረው ሲያነካኩ*
*አልሳካ ካለም የቦንብ ናዳ ጥለው*
*በእሳት ውርጅብኝ ህፃናት ሲገሉ*
*የሊላውን ጥሪት በገሀድ ሊዘርፉ*
*ቫይረሱን ፈብርከው ሰቆቃ ሲፈጥሩ፥*
*ሰው ልጅን ለማጥፋት ኑክሊየር ሲያብላሉ*
*በጦር መሳሪያቸው ሊገዙ ሲያሴሩ*
*እግዚአብሔር ተቆጣ ተነሳ በትሩ - ሙብረቅ የለኮሠው እሳት ነበልባሉ*
*ውሀውም ታዘዘው ቧይት አውሎ ንፋሱ - ለዘሩት እልፍ ሃጢያት በመዓቱ ተሙቱ፡፡*

*** ዶ – ዶ ***

T/C እሴና ፍሬድሪካ ከግዙፉ ፒራሚድ ስር እንደተገናኙባት ልክ እንደዚያች ቀን ሁሉ ዛሬም፤ ከረጅሙ የአክሱም ሃውልት ስር ቆመዋል:: ‹‹ንፋስ መውጫ›› ተብሎ ከሚጠራው ግዙፉ ሃውልት ስር ቆመዋል::
"Have you ever wondered how they erected this stele weighing 500,000 kilogram at that time? (እነዚህን 500.000 ኪ.ግ የሚከብዱ ሃውልቶች በዚያን ጊዜ እንዴት እንደዚህ ማቆም እንደቻሉ ጥያቄ ፈጥሮብሽ አያውቅም?)"
"Yeah, but I think they used elephants and man power to do so! (ያውቃል ግን ያው ዝሆኖችንና የሰው ጉልበትን ተጠቅመው ያቆሙት ነው የሚመስለኝ፤)" አለች ፍሬድሪካ፤
"You and I know that is not possible, even in the current modern time we are facing difficulties to keep it upright... rather I believe they used the power of winds to erect it. (እኔም አንቺም ያ ሊሆን እንደማይችል ጠንቅቀን እናውቃለን:: ይልቅስ የንፋስ ኃይላትን ተጠቅመው እንዳቆሟቸው አምናለሁኝ::)" አሏት፤
"How is that possible, you know we have no such wind turbines even upto these days? (እንዴት ሆኖ? አሁን በዚህ ዘመን እንኳን ያን ያህል ሃይል ያለው የንፋስ ግፊት መፍጠር የሚችሉ ተርባይኖች እንደሌሉን ታውቃለህ)" አለቻቸው::
"They didn't use turbines, they used spiritual powers. (ተርባይን ሳይሆን መንፈሳዊ ሃይልን ነው የተጠቀሙት!)" ሲሏት ሳቀችና፤
"You must be kidding proffesor, anyways let's forget that, we are here now, where is the treasure? Let's find it, open it with the secret key and see for our selves. (እየቀለድክ መሆን አለበት ፕሮፌሰር፤ ለማንኛውም አሁን እርሱን እንርሳውና እዚህ የመጣንበት ምክንያት የሆነው ድብቁ ሃብት የት ነው? በሚስጥር መክፈቻ ቁልፉችን እንክፈተውና እናረጋግጥ::") አለች:: ቸኩላለች!

ምንም ሳይመልሱላት ከሃውልቱ አጠገብ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ፤ ወደታች በሚያስወርድ ደረጃ በኩል፤ ከአክሱሙ ስር ወደሚገኝ ምድር ቤት

ወረዱ:: በሰንፔር እና ጥቁር ወጥ ከቡር ድንጋይ የተሰራው እጅግ ከባድ ሃውልት ስር በሚያምር ሁኔታ የተገነባው ኪነ-ህንጻ፤ እውነትም ከዚህ ሃውልት ጀርባ መንፈሳዊ ሃይል እንዳለ ጽኑ ምስክር ነው:: የአክሱም ሃውልትን የተሸከመው ወጥ አለት፤ ስፋቱ 20 ሜትር፤ ወርዱ 7 ሜትር ይሆናል:: ከስሩ የተገነባው፤ ይህ መሿለኪያ የሚመስል የዋሻ ህንጻ፤ የአለቱን ጣሪያ ጨምሮ፤ 3ቱም ማዕዘኖች ብርሃንና ንፋስ የሚያስገቡ 4 ማዕዘን መስኮቶች አሉት:: የምድር ቤቱ ግርግዳዎች፤ አለት እንደ ሰም የሚያቀልጥ በሆነ እብነ-አድማስ በተሰኘ ማዕድን በተሰሩ፤ መሳሪያዎች ድንጋዮቹ ተከርክመው ከተሰካኩ ኋላ በብረት ዘንጎች ተለጥፈዋል:: የወደቀው ረጅም ሃውልት በስተምዕራብ ያለውን የህንጻውን መንገድ ዘግቶታል:: እንደ መሰላል የተቀረጹ የደጋን ቅርጾች በእነዚሁ የከበሩ ድንጋዮች፤ ድርድር የተዘጋ ቦታ ጋር ሲደርሱ፤ ፐ/ር እሴ ቀጥ ብለው ቆሙ:: ጭለማው አይናቸውን ጋርዷቸው ማለፊያ የሌለው ቢመስላቸውም፤ ከጥግ ያለውን ግርግዳ ዳበሳ ዳበስ ሲያደርጉ ግን በአንዱ ጎን ያሉ የተጠበሱ ድንጋዮች የሚመስሉ ብሎኬቶችና ከግርግዳው መካከል 1 ሜትር የሚጠጋ ስፋት መኖሩን አወቁ:: ፐ/ር እሴ በትከሻቸው በኩል ሸርተት ብለው በዚህ ከፍተት በኩል ወደ ውስጥ ገቡ፤ ፍሬድሪካም ተከተለቻቸው:: በገቡበት እልፍኝ ውስጥ የገጠማቸው ነገር ግን እጅግ አስገራሚ ነበር:: ከቅድሙ መሿለኪያ ቤት ሰፋ ያለ የዋሻ ክፍል ሲሆን በአራቱም ጥጎች የፈረስ ኮቴ ቅርጽ ያላቸው ግዙፍ የሰንፔር ሰገነቶች ነበሩበት፤

"I know this horse shoe shaped arches somewhere, (እነዚህን የፈረስ ኮቴ የሚመስሉ ቅስት ግንቦች የሆነ ቦታ አውቃቸዋለሁኝ፤)"

"Really? ... Where? (የእውነትህን ነው?... የት?)" አለች ፍሬድሪካ፤

"Hmmm... Yeah! I remember! I once participated in a seminar at California, it was about Indian history, an excavation done in Southern India and I have seen the same shapes, discovered there by archeologists. (ምም... አዎ! አስታወስኩኝ! በአንድ ወቅት ካሊፎርኒያ ላይ በህንድ ታሪክ ጥናት ዙሪያ በደቡባዊ ህንድ በተደረገ ጥናት የተገኙ ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸው ቤተ-መቅደሶችን አይቼ ነበር::)" ... አሉና ወደ ዋሻው መሀከለኛ ስፍራ ተጠጉ፤ ከዋሻው አማካይ ስፍራ ላይ አንድ በጠባቡ የተከፈተ ጉድጓድ በድንጋይ ተዘግቶ ይታያል::

ፕ/ር አሴ በዝግታ ወደ ጉድጓዱ ተጠጉ… እናው ጉድጓድ ላይ ያለውን የድንጋይ አቧራ ጎንበስ ብለው አራገፉት:: ከድንጋዩ ላይም በሱባ (የሳባውያን) ቋንቋ የተቀረጸ ፅሁፍ ወለል ብሎ ታየ::

*"This is the key of the location of the treasure I told you about!* (ይሄ ነው የነገርኩሽ ድብቅ ሐብት ያለበት ቦታ፤)" አሏት ፈገግ ብለው፤ ፍሬድሪካ በጉጉት ተጠግታ የስልኳን የፍላሽ ብርሃን በጉድጓዱ ላይ አበራች:: ነገር ግን ምንም አይነት ወርቅና ዕንቁም ይሁን የተቆለፈ ሳጥን ያሌለበት፤ በአራቱም ማዕዘን የተደፈነና አንድ ድንጋይ ቢደፍነውም ወደ ውጭ የሚያስወጣ ጠባብ መሿለኪያ ብቻ ያለው ጉድጓድ ሆኖ ነበር ያገኘችው:: ተናደደች፤ "What is this? Where is the treasure? Where is the secret key? (ይሄ ምንድነው?.. ድብቁ ሐብትስ?.. የሚስጥሩ ቁልፍስ?)"

"There is no secret key or treasure… I knew your plan from the beginning but accept the truth; we are here to open a closed path not a box of gold… let me read this for you… (ምንም አይነት የሚስጥር ቁልፍም ሆነ ድብቅ ሃብት የለም፤ እቅድሽን ከመጀመሪያውም አውቄው ነበር:: ለማንኛውም እውነታውን ተቀበይ፤ በወርቅ የተሞላ ሳጥን ለመክፈት ሳይሆን የተዘጋ መንገድ ልንከፍት ነው የመጣነው!)" ፤አሉና በረጅም ጊዜ የሳባውያን ቋንቋ ጥናታቸው መሰረት ድንጋዩ ላይ የተቀረጹትን ጽሑፎች በማስታወሻ ደብተራቸው መዘገቡና ወደ አማርኛ ቃላት ቀየሯቸው:: ነገር ግን ለማረጋገጥ እንጂ የፅሑፉን ትርጉም ቀድመውም ያውቁታል:: ቃላቶቹም የሚከተሉት ነበሩ፤

**"በዋዜባ የአምልኮ ቡድን፣ በስውሩ እጅ ላይ ለጎልጎሮት የተሰጠ፤ በልዑላዊው የኢዛና እጆች የተሰራ፤ ይህንን የእርግማን ሸለቆ አትክፈቱት!"**

"What does it say? (ምንድነው የሚለው?)፤" አለች በችኮላ፤

***‹‹The Cult of Wazeba, on the other hand, is a cult dedicated to GolGoroth. By the hand of Royal Ezana, open not this cursed/doomed/ tunnel.››***

"What does this mean? What are you upto? Don`t play with me professor! (እኮ ይሄ ምን ማለት ነው?… እቅድህስ ምንድነው?… አትጫወትብኝ እንጂ ፕሮፌሰር!)" አለች ቆጣ ብላ::

"I am not playing, (እየተጫወትኩብሽ አይደለም!)" አሏት፤ ለመፃፍ ካጎነበሱበት ቀና እያሉ፤ … "Did you know the origin of most of the

hurricanes which hit U.S and western countries? (አብዛኛዎቹ አሜሪካና ምዕራባዊ ሃገራትን የሚመቱ አውሎ ንፋሶች መነሻቸው ከየት እንደሆነ ታውቂያለሽ?)" ብለው ጠየቋት፤

ፍሬድሪካም ትንሽ አሰበች… በቅርቡ የሰማችው የዜና መግለጫም ታወሳት፤ "I heard news recently that most hurricanes are from the northern mountains of Ethiopia and Mediteranean Sea. (በቅርቡ ዜና ላይ እንደ ሰማሁት የአብዛኛዎቹ አውሎ ንፋሶች መነሻ የኢትዮጵያ ሰሜን ተራሮችና ሜዲትራኒያን ባህር ናቸው፡፡)"

"Well; this is the source & that is why they called it… <<The Gate-way of the Wind! >>… So I am here to open the tunnel & defend my country and the weak from all the evil deeds of your people that will happen in the future! (እንግዲህ እወቂው የቧይት ንፋሶቹ መነሻቸው ይህ ቦታ ነው፡፡ ለዚያም ነው! ‹‹ንፋስ መውጫ›› ብለው የሚጠሩት፡፡ እኔም እዚህ የመጣሁት ይህንን የተዘጋ መስመር ለመክፈትና ሃገሬንና ደካማ ህዝቦችን ካንቺ ሰዎች ቀጣይነት ካለው ሰይጣናዊ ጥቃት ለመከላከል ነው፡፡)" አሉና መስመሩን የዘጋውን ድንጋይ መግፋት ጀመሩ፡፡

"What are you doing? STOP! (ምን እያደግህ ነው? … አቁም!)" አለች ፍሬድሪካ፤ መልስ ሳይሰጧት ድንጋዩን ማንቋቀቁን ቀጠሉበት፡፡ ፍሬድሪካ ትዕግስቱ አልነበራትም፤

ኤጀንት ሶፊያ ወይም ፕ/ር እሴን ስታጠምድ በተሰጣት ስም መሰረት ፍሬድሪካ የእስራኤሉ የስለላ ቡድን ሞሳድ አባል ነች፡፡ እኚህን ፕ/ር እንድትከታተል ተልዕኮ ከተሰጣት ሁለት ዓመታት ሞልተዋል፡፡ የተመደበችውም እኚህን ስለ ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ በርብረው ያጠኑ ፕሮፌሰር ከኢትዮጵያውያን ሆን ብለው የተደበቁ ታሪኮችን እንዳያወጡ መከታተል ነበር፡፡ በዚሁ ተልዕኮዋ ውስጥ እያለችም የተደበቀ ሃብት አግኝቻያለሁኝ ሲሏት አዲስ እቅድ አወጣች፡፡ ይህም በአስመሳይነት ፕ/ሩ ያሉት ድብቅ ሃብት ድረስ መሄድና ሃብቱንም ካገኙ በኋላ እርሳቸውን በመርዝ መግደል፤ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ሃብት ደግሞ ወደ እስራኤል ይዞ መኮብለል፡፡ ይህም እቅዷ ከተሳካ የማዕረግ እድገት እንደሚያስገኝላት አምና ነበር፡፡ ፕ/ሩ ባሉት ሚስጥራዊ ስፍራ የተቀበረ ወርቅ፤ እርሱም ባይሆን የብራና ጽሑፎችና ጥንታዊ ቅርሶች የያዘ ሳጥን ይኖራል ብላ ነበር ያመነችው፡፡ እርሳቸው ግን በማይጨበጥ ነገር ሲያስለፏት መክረማቸው ሳያንስ ካሰበችውም በላይ የሷን

ሃገርና አሜሪካን ችግር ውስጥ ሊከት የሚችል ነገር ሊያደርጉ እንደሆነ ስታስብ ከዚህ በላይ መታገሱ ዋጋ እንደሌለው ተረዳች:: ድምጽ ማፈኛ የተገጠመለት ሽጉጧን ከጀርባዋ መዛ አወጣች::

"Don't move Professor Essei! (ፐ/ር እሴ እንዳትንቀሳቀስ!)" የሚል ቀጭን ትዕዛዝ አስተላለፈች፤ ድንጋዩን ለመከፈት አጎንብሰው ሲታገሉ የነበሩት ፐ/ር እሴ ቀና ብለው ከፍሬድሪካ የተደቀነባቸውን የሽጉጥ አፈሙዝ ተመለከቱ:: ልባቸው በድንጋጤ ስንጥቅ አለች፤ ውስጣቸው ጥርጣሬ ተፈጥሮ የነበረ ቢሆንም ይህን ያህል ደረጃ የሚደርስ ጭካኔ ግን አልጠበቁም ነበር::

*"Don't try to do anything stupid! I will not hesitate to shot and down in this doom there won't be any witness;* (ምንም አይነት የሞኝ ነገር አደርጋለሁኝ ብለው እንዳያስቡ፤ ለመተኮስ አላንገራግርም! በዚህ ጭለማ ውስጥ ብገሎትም ምንም ምስክር አይኖርም::)" አለች፤

"Okay, but Fredricka I don't think this is your true Identity? I trust you are... (እሺ ግን ይሄ ትክክለኛ ማንነትሽ አይመስለኝም ፍሬድሪካ፤ አምናለሁኝ አንቺ...)" ፤ብለው ንግግራቸውን ሳይጨርሱ፤

"Stop the bullshit! (የማይመስል ወሬህን አቁም!)" ብላ አንባርቃ አቋረጠቻቸው፤ "I will ask you for one last time, where is the treasure you were mentioning? ... Show me?"(ለመጨረሻ ጊዜ ነው የምጠይቅህ! አለ ስትል የነበረው ድብቅ ሃብት የት ነው?,,, አሳየኝ?)"

*"You see this is your problem, you always want to see, touch and prove something before you call it a treasur, you have no faith, and you have no value for the unseen sentiment,,,* (አየሽ፤ የእናንተ ችግር ይሄ ነው አንድን ነገር ሃብት ከማለታችሁ በፊት ማየት፣ መንካት እና ማረጋገጥ ትፈልጋላችሁ:: እምነት የላችሁም፤ በአይን ለማይታይ ሃይል ዋጋ አትሰጡም::"

"Whatever, you have missed your last chance! Sorry! (ምንም ዋጋ የለውም፤ የመጨረሻ እድልህን አበላሽተሃል:: አዝናለሁኝ፤)" ብላ ሌባ ጣቷን የሽጉጡ ቃታ ላይ አሳርፋ ለመሳብ ተዘጋጀች::

"Drop your weapon! (መሳሪያሽን ጣይ!)" የሚል ትዕዛዝ ከኋላዋ ተሰማ፤ ፐ/ር እሴ ቀና ሲሉ አከሎማ መሳሪያውን ፍሬድሪካ ላይ ደቅኖ

ተመለከቱት:: ፍሬድሪካ እርሳቸው ላይ ደቅናው የነበረውን ሽጉጥ በፍጥነት ወደ አክሎግ አዙራ ተኮሰች፤ አክሎግም አፀፋውን መለሰ::

ፕ/ር እሴ በድንጋጤ እንደተሞሉ ሁለቱንም ተራ በተራ ተመለከቱ:: የማቃሰት ድምፅ በዋሻው ውስጥ ተሰማ:: አክሎግ በቆመበት የቀኝ ክንዱን ጭምቅ አድርጎ ይዞ ደሙን ለማቆም ሲሞክር አዩት፤ የሚያቃስተው ግን እሱ አልነበረም::

ግራ ደረቷ የተቦረተፈው ፍሬድሪካ ግርግዳውን ተደግፋ እያቃሰተች ተቀምጣለች:: ተዝለፍልፋ ወደ መሬት ልትወድቅ ስትል ፈጠን ብለው ከስር ገቡና አቀፏት:: "Was it a false promise? (የውሸት ቃል ኪዳን ነበር ማለት ነው?)" አለቻቸው በለሆሳስ፤ መልስም ሳይሰጧት በሃዘን ተሞልተው፤ አይናቸው በሀዘን ቡዝዝ እንዳለ ተመለከቷት:: ድክምክም ብላ ከደረታቸው ተጋደመች:: ቁልቁል ተመለከቷት፤ ደም በደም ሆና ወደ ዘላለም ቤቷ ልትሄድ እያቃተተች ነው:: የሃገር ነገር ሆኖ እንጂ አብረዋት ሲሆኑ ደስ ይላቸው ነበር:: ላትመለስ ስታልፍም ማዘናቸው አልቀረም… "እኛም በራሳችን፤ እነርሱም በራሳቸው መኖር ሲችሉ እጅ ጣልቃ ማስገባት ለምን? ቦርጫቸውን አቅፈው ውስኪ የሚጨልጡ ባለስልጣናት እስከ መቼ ድረስ በምስኪን ወታደሮች እየተጠቀሙ ህቡዕ አላማቸውን ያሳካሉ?…

*** ፆ – ፆ ***

ወ/ሮ ቤዛዊት በባዶ እግራቸው እየከነፉ ነበር ፖሊስ ጣቢያ የሄዱት:: የቡታጅራ አውራጃ ፖሊስ መምሪያ አባላት ልጄ ጠፋችብኝ የሚሉትን እኚህ ሰው ተከትለው ሀረ-ሼይጣን ሐይቅ ድረስ ሄዱ:: ነገር ግን ፅዮን ስለተባለችው ልጅም ይሁን ስለ ደብተራው ሰው ምንም አይነት መረጃ ሊያገኙ አልቻሉም ነበር:: ለሦስት ቀናት ያህል ክትትልና ምርመራ ከተደረገ በኋላ ምንም ፍንጭ ስላልተገኘ ወ/ሮ ቤዛዊትም ብዙ ጊዜ ‹‹ወደ ሐይቁ እገባለሁኝ›› እያሉ እያስቸገሩ ስለ ነበር የአዕምሮ ህመምተኛ ተብለው፤ በፖሊሶች አስገዳጅነት አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ አማኑኤል የአዕምሮ ህሙማን ሆስፒታል እንዲገቡ ተደረገ:: በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ ያጋጠማቸውን ሰው ሁሉ እያስቆሙ ‹‹ልጄን አምጡልኝ?›› እያሉ ይለማመናሉ፤ እንባቸውንም ይዘራሉ::

*** ፆ – ፆ ***

*"መኖሪያቸውንም የተዉትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል።"… **(የይሁዳ መልዕክት፤ ምዕ 1:6)***

*** ፆ – ፆ ***

"እንግዲህ ፐ/ር፤ እደራ ዛሬ የሆነው ነገር በሙሉ በእርሶና በእኔ መካከል የሚቀር ነው::" አለ አክሎግ አስረግጦ፤ ጉድጓዱን የዘጋውን ድንጋይ አንስተው ከአንዱ ጥግ አጋድመው ከዋሻው እየወጡ ሳለ፤… አክሎም፤ "እኔ ትናንት በአሰርኳቹ ጊዜ በምርመራ ወቅት የነገሩኝ ነገርና ያስነበቡኝን የአባ ገዳውን ደብዳቤ ስላመንኩኝ ነው ይህን ያደረግኩት:: አንድ የእስራኤል ደህንነት መግደል ማለት ከእነሱ የተገዳይነት ታርጌት ውስጥ መግባት እንደሆነ ጠፍቶኝ አይደለም:: ነገር ግን እርስዎ ለሃገር እጅግ ጠቃሚ እውቀትን ይዘው እንደመጡ ስላመንኩኝ ነው::" አላቸው፤

"ወንድሜ አክሎግ ይህንን ጉዳይ ባጋልጥ የመጀመሪያው ተጠርጣሪ እኔው መሆኔ እንዴት ይጠፋሃል:: በዚህ ዙሪያ ምንም ሃሳብ እንዳይገባህ::" አሉ ፐ/ር እሴ ነገሩን ቆንጠጥ አድርገው::

"አዎ አውቃለሁኝ፤ ግን መርሳት የሌለቦት የፍሬድሪካ ሰዎች ከፍተኛ ክትትል ያደርጉብናል:: እኔ ግን እስከምችለው እጠብቆታለሁኝ:: ይሄን የማደርገውም እውቀቶን እንዲያካፍሉ ጊዜ እንዲያገኙ ነው፤ ነገር ግን ይዋል ይደር እንጂ፤ ምሳድ ፈልፍሎ እንደሚደርስብን አይጠራጠሩ::" አለ::

ፐ/ር እሴና አክሎግ ከምድር ቤቴ ወጡና ወደ አክሎግ ፒክ አፕ ደብል ጋቢና መኪና አቀኑ:: ፐ/ር እሴ ለፍሬድሪካ ባይነግሯትም ያንን ዕለት ከሰዓት በአክሱም ዩንቨርሲቲ ንግግር ለማድረግ ቀጠሮ ተይዞላቸው ነበር:: በአክሎግ መኪና ወደ አክሱም ዋናው ግቢ አመሩ::

"ግን ምን አይነት ጥቅም ቢኖረው ነው ያንን ድንጋይ ስታስገፉኝ የዋሉት?" አለ አክሎግ፤ ቅድም ጉድጓዱን ለመክፈት ሲታገል የቆሸሸውን የሸሚዙን ኮሌታ እየቆለፈ::

"መስማት ከፈለግከማ እነግርሃሁኝ:: የአክሱም ሃውልቶች ብዙሃኖቻችንን ፈረንጆቹ ለማሳመን እንደቻሉት የመቃብር ስፍራዎች ወይም በወንድ ብልት ቅርፅ የተሰሩ አይደሉም:: ሃውልቶቹን ልብ ካልካቸው ከስራቸው በጥሩ ሁኔታ የተቀረጸ በር ያላቸው፤ በየእርከኑም ውብ የመስኮት ምስል የተቀረፀባቸው ናቸው:: እነዚህን ቅርፆች በእነዚህ ጥቁር ሰንፔር ድንጋዮች ላይ ከሽኖ መሳል ራሱ የአሁን ዘመን ሳይንቲስቶች ያልፈቱት ጥበብ ነው::"

"ይገርማል! ነገር ግን ሃውልቶቹ በወንድ ብልት ቅርፅ የተሰሩ ወይም መቃብር ስፍራዎች ካልሆኑ ታድያ ምንድናቸው፤" አለ አክሎግ፤ መሪውን እየዘወረ፤

"በቅድሚያ ሃውልቶቹ የወንድ ብልት ማሳያ ነው የሚሉት ከቅርፁ በመነሳት ሲሆን ይህም ልክ እንዳልሆነ የሃውልቶቹ ቅርጽ ራሱ ይመሰክራል፡፡ ከታች ሰፍተው ወደ ላይ የሚጠቡ ረጃጅም ታዛዎች ከመሆናቸው ባሻገር በሮችና መስኮቶች የተቀረጸባቸው ናቸው፡፡... እስኪ የየትኛው ወንድ ብልት ነው በርና መስኮት የተቀረፀበት?" ብለው ሲጠይቁት አከሎግ በሳቅ ፈነዳ፤

"የምር ቀለዱብን እኮ፤..." ብለው ፐ/ር እሴም ፈገግ አሉና ቀጠሉ "ሁለተኛውና ብዙሃኑ የሚያስቀምጡት መከራከሪያ ደግሞ የመቃብር ስፍራዎች ናቸው የሚል ሲሆን ይህም ከሃውልቶቹ ስር ካለው ስፍራ በተገኙ የነገስታት ቅሪተ አካላት ላይ ተመስርተው የሚሰጡት መላ ምት ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ቅሪተ አካላት መጀመሪያ በዚያ ስፍራ በመንፈሳዊነት ሲጸልዩ እድሜያቸውን የፈጁና በኋላም እዚያው ያረፉ አባቶቻችን ናቸው፡፡ ሌሎቹ አጽሞች ደግሞ ወደ ጥፋት የገቡ ነገስታቶቻችን እ/ር ፊቱን አዙሮባቸው፤ በአክሱም ላይ ይገለጥ የነበረውን መንፈሳዊ ሃይል ስለተለያቸው እንዲታረቃቸውና በዘላለም መንግስቱ እንዲያኖራቸው ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ሃብት ንብረታቸውንም ጭምር ይዘው ከሃውልቶቹ ስር ይቀበሩ ስለነበር ነው፡፡

ነገር ግን የአክሱም ሃውልቶች ከዚህም የጠለቀ ታላቅ ትርጉም አላቸው፡፡ ከጫፎቻቸው ላይ ያሉት የደጋን ቅርጾች በሰው ልጅ ራስ ይመሰላሉ፡፡ ይህም የሰው ልጅ ህሊናና አዕምሮውን አበርትቶ የታችኛው ስሜቱን እንደ ሚቆጣጠር ሁሉ፤ ይህም የደጋን ወይንም ...

የማግኔት )))) ቅርፅ ያለው የአክሱም ራስ መጥፎ ነገሮችን በሙሉ እየሳበ ወደራሱ የሚያስገባ ማግኔትን ይመሰላል፡፡ በሌላ አባባል የሞቱ ኮከቦች ምርት የሆነው ጥቁር-አዘቅት (ብላክ-ሆል) የብርሀን ጨረሮችን እንደሚውጥ ሁሉ የአክሱም ግማሽ ጨረቃ መሳይ ቅርፅም ጠሊቀ-ብርሀን ሆኖ ፅልመትንና መከራን እየሳበ ያስወግዳል፡፡ የድሮ ቅዱሳን የታችኛውን የስጋ ፍሬያቸውን እያሸነፉ በአክሱም በር ይገቡና በቅድስናቸው መጠን ወደላይኛዎቹ እርከኖች እየወጡ በአክሱም ባሉት መስኮቶች በኩል እንደማንኮራኩር እየመጠቁ የፈለጉት ቦታ ድረስ ይጓዙ ነበር፡፡ የላይኛው ጫፍ ደጋን ላይ የደረሱ ፃድቃን ደግሞ በዚህ ፖርት ተጠቅመው አንደኛውና ሁለተኛው ሰማይ ድረስ እየወጡ ነብያትን ያገኙ እንደ ነበር አፈ-ታሪኮች ይነገራሉ፡፡

ታዲያ ምድር ላይ የስጋ ፍሬዎች ከተንሰራፉ አክሱም የተቀበለውን ተንቀልቃይ ሃጢያትም እየናረ ሲመጣ ንፋስ መውጫ በሚባለው መስመር በኩል በሰው ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ጥፋት ይወጣ ነበር፡፡ አባቶቻችንም በጸሎት እየታገዙ ዓለምን የሚበከሉ ኃጥያተኞችን የሚያጠፉ መቅሰፍት

ይልኩ ነበር:: እናም አክሎግ ልጄ እኛ እንደሌሎቹ ኃያላን ኒዩክሊዬር ማብላላት ባንችልና ዘመናዊ መሳሪያዎችም ባይኖሩንም የማይነጥፈው የአምላክ ሃይልና ጥበብ አለን:: እነዚያ ያየሃቸው ሽቅብ የጎኑ የአክሱም ሃውልቶች ከየትኛውም ሚሳኤልና ሮኬት የላቁ መሳሪያዎቻችን ናቸው፤ ከእኛ የሚጠበቀው ማመን ብቻ ነው:: አክሱም ስር ያለውን በር መክፈት ማለትም የእያንዳንዳችንን እምነት በር መክፈት ነው::"

አፉን ከፍቶ እያዳመጣቸው የነበረው አክሎግ አክሱም ዩንቨርሲቲ በመድረሱ በጣም ነበር የከፋው::

*** ዮ – ዮ ***

ፕ/ር እሴ ወደ አዳራሹ ሲገቡ በደማቅ ጭብጨባ ነበር ታዳሚው የተቀበላቸው:: ዝናቸውን የሰሙ ተማሪዎች የእርሳቸውን ትምህርት ለመከታተል ከመቐለና ከአዲግራት ዩኒቨርሲቲም የመጡ ተማሪዎች ነበሩ:: በጭብጨባ እንደታጀቡ ከመድረኩ ወጡና ወደ መናገሪያው ማይክራፎን ተጠጉ፤ አቦ አራርሳ በላኩላቸው ደብዳቤ ላይ ተመስርተው የጻፉትን ጽሑፍ ማንበብም ጀመሩ::

"ዛሬ ወንድምና እህቶቼ **‹‹እኛ አንድ ካልሆንን ያጠፉናል!››** እላችኋለሁኝ:: እንደ ጥንት አባቶቻችን በህብረት ሆ! ብለን ካልታገልን ከፋፍለው ይገዙናል!" ብለው በኃይለ ቃል ነበር ንግግራቸውን የጀመሩት፤ "አዎ! እንደ አባቶቻችን አንድ እንሁን፤ ምክንያቱም የታሪክ ጀግናዎቹ ኮሎኔል አብዲሳ አጋና ራስ ጎበና… የታገሉት ለኢትዮጵያ ልዕልና እንጂ ኦሮሞ ብሄርን ብቻ ወክለው አልነበረም፤ጀግናው በላይ ዘለቀ ከጣልያን ጋር የተጠዛጠዘው.. አፄ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ ጥይት የጠጣው ለአማራነቱ ሳይሆን ለሚወዳት ኢትዮጵያ ሀገሩ ክብር ነበር። እነ ንጉስ ኢዛና ታላቅ ግዛት የገነቡት.. ፣ አጼ ዮሀንስና ጀግናው አሉላ በፍጹም መሰጠት የተዋደቁት ለኢትዮጵያ ነፃነት እንጂ በጭራሽ ለትግሬነታቸው አልነበረም፤ የሌሎችም ብሔሮች ታላላቅ ጀግኖች ለዚህች ውድ ምድር ክቡር ደማቸውን አፍስሰዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን እነሶሪያ፣ የመን፣ ሊብያ… በምዕራባውያን የማያጠግብ የስመ ዴሞክራሲ የህልም እንጀራ ተመርተው የሰሩትን ቀይ ስህተት እንደማንደግም አምናለው፥ ምክንያቱም እኛ የጥንቱ የእውቀትና ማስተዋል ፈርጥ፤ የኢትኤል ኤቶዮጵ ወራሾች… ፍቅር የወለደን ጀግኖች፤ የዘራችን ሐረግ አንድ ግንድ ሆኖ በብሔር ቅርንጫፎቻችን ውበት የምናጌጥ፤ ስመ ሀይማኖት በሌሎች ሃገራት ላይ የጋረደውን የመለያየትና የጥላቻ ግንብ ያፈረስን ውህዶች፤ ዥንጉርጉር ሐበሾች፤ ኢትዮጵያውያኖች ነንና…" አሉና

ከውሃው ተጎነጩለት፤ ቀጠሉ… "አሁን ያለንበት ዘመን ኢትዮጵያ ፈተና መቋጫ ነው! ኢትዮጵያ እርግጥ ነው ተፈትናለች እውነትም ደግሞ የሚወደውን ሰውም አምላክ ይፈትናል። ወላጅም ልጁን የሚቆጣው ትልቅ ቦታ እንዲደርስ ነውና። ሆኖም በፈተናና መከራ መካከል ግን ትልቅ ልዩነት እንዳለ ልብ በሉ። መከራ ቅጣት ነው! ፈተና ግን ሰው የተሻለ ለመሆን መሻገር ያለበት ድልድይ እንደማለት ነው። …ኢትዮጵያ የፈጣሪ ቅድስት ምድር እንደመሆኗ ብዙ ዜጎቿን ለፈተና ታስቀምጣለች። የጥንቶቹ የነ ኤቶጵና ዮቶር ትውልዶች ፈተናውን ነቅንቀው እያለፉ ከመንፈሳዊ ህይወታቸው ባሻገር በዓለምም ላይ ነግሰዋል።

ለዚህም ዋነኛ መሳሪያቸው ደግሞ እውቀት፣ እምነት፣ ፍቅርና ተግባር ነበር! ይህንንም የፀደቀ ታላቅነታቸውን አውቀው በወቅቱ ብዙዎች ተጠቅመዋል። ሙሴ ከኢትዮጵያዊ አማቹ ጥበብ ወርሷል፤ ድንግል ማርያም እየሱስ ክርስቶስን እንዳትወልጂ ብሎ የገዛ እስራኤላዊ ወገኗ ሲያባራት እዚህ ደግ ህዝብ ጋር መጥታ ተጠግታለች፤ ነብዩ ሙሐመድ ጣዖት አምላኪ አረብ ሲያሳድዳቸው ተከታዮቻቸውን ሂዱ ያሉት ወደሮምና ፈረንሳይ ሳይሆን ወዳኛይቱ ኢትዮጵያ ነበር!. . .ሁሉም የፅድቅ መሬት እንደሆነች ያውቁ ነበር። ከስጋ ባሻገር የዘላለማዊ የነፍስ ብልፅግና እንደነበራት ተገንዝበዋል! የመጀመሪያ ‹‹ነፃ›› አውጪዎች አግዓዚያን ከጠቢቡ ሰሎሞን ልጅ ከምኒሊክ ቀዳማዊ ጋር የመጡት የኢትዮጵያን ሃገር ከፀሐይ አምልኮ ነጻ ለማውጣት እንጂ ሌላ ግዛት ለመመስረት አልነበረም፡፡

… ከዚያ ዘመን በኋላ በተለይ በተለይ ደግሞ በቅርብ ምዕተ ዓምታት ታሪኮቻችን ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያን ግን እነዚህን የፅድቅና ፈተናዎችን ማለፍ ተስኗቸዋል። ህይማኖት፣ ብሔርና ሀብትን ከእምነት፣ አንድነትና ፍቅር አብልጠው ይዘዋል። ጎራ ለይተውም ደም ተፋሰዋል።

እነሆም ተግባራዊ እውቀትና ልቅና በወሬና ማስመሰል ተተክቷል!

.. እንግዲህ ፈተናን ላለፈ ሽልማት እንዳለው ሁሉ ለወደቀም ቅጣት አለውና እኛም ጥላቻን ወርሰን የመከራን ፅዋ እየተጋትን ነው! ርሀብ፣ ድህነት፣ በሽታ፣ ጦርነት፣ ስደት ወ.ዘ.ተ… ወርሶን ቆይቷል! ከሁሉም በላይ ደግሞ ማንነት አልባና ነጭ አምላኪ ሆነናል። ስጋዊ ፈተናዎች እምነታችንን በጥርጣሬ በጣጥሠውት ተጫውተውብናል። ‹‹ማርክሲስት ሌኒንስት›› እያልን እግዚአብሔርን ከደን በሰራችን ሰንመካ ወድቀን መከራን አይተናል፡፡ ዛሬ ስራውም መንፈሳዊነቱም ተመናምኖ በስንፍና ቆመናል፡፡ ሲቶቻችን ጥንት በቅድስና ኖረው፤ በክብር ተድረው፤ ከየትም ሃገር በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ልዕልትና ንግስት ሆነው እንዳልተከበሩ፤ ሃገር እየመሩ ባዕዳን እንላርበደበዱ

አሁን ግን የማንም አረብና አውሮፓዊ አምላክን የካዱ ዱርዬዎች አገልጋይ ለመሆን በምድር፣ በአየርና በባህር ይተማሉ::

"እናም የአክሱም ዩንቨርሲት ተማሪዎችና ሰራተኞች ዛሬ የምነግራችሁ...እንደ ህዝብ ለሚያጋጥሙን ችግሮች መፍትሄው ተስፋ መቁረጥ አለመሆኑን ማወቅ አለብን! ፍቅርና እምነት ሰንቀን ለለውጥ ከዘመትን! ለኪስና ለማስመሰል ሳይሆን ፈጣሪን አስበን ከተባበርን ፈተናዎች ሁሉ ይታለፋሉ። እነሆ እስላምም የሃገር ሰላም፣ መስቀልም በክርስቶሳዊ ፍቅር ውስጥ የተደመረ ህብረትን ያስተምር::

ያኔ ሀዘናችን ይከስማል!

....ያኔ ማጎንበስ ቀርቶ ከማንም በላይ አንገታችን ቀና ይላል!

.........ያኔ ኢትዮጵያ እንደ በፊቱ የመንፈሱም የስጋውም ዓለም ንግስት ትሆናለች! ይህ ደግሞ የኔ ቃል አይደለም... ይሄ እግዚአብሔርም በሉት ያህዋ፣ አላህም ብላችሁ ጥሩት ኤሎሄ... ያ ምድርና ሰማይን የፈጠረው አምላካችን ጥብቅ ቃል-ኪዳን ነው።።"

...አሉና ከመድረኩ ወረዱ፤ አዳራሹ በደማቅ ጭብጨባ ተሞላ:: ፕ/ር እሴም እያመሰገኑ ወረዱና በዩኒቨርስቲው የታሪክ መምህር የሆኑትን ፕ/ር አጽበሐን አቀፏቸው:: እንደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕ/ር ዳግማዊና የወልዲያው ዶ/ር አያሌው ሁሉ ይህን መድረክ ያዘጋጁላቸው እርሳቸው ነበሩ::

"እውነት ለመናገር ንግግርህ ደም ስሬ ውስጥ ገብቶ ነው የተሰማኝ... እውነታውን በአጭር መንገድ ቁጭ አድርገኸዋል::" አሉ ፕ/ር አጽበሐ፤

"እኔም እውነት ለመናገር አብዛኛው የእኔ ንግግር አልነበረም፤" አሉ፤

"እና የማን ንግግር ነው?"

"የአንድ አባ ገዳ መልዕክት ነው::"

"እየቀለድክ ነው ወይስ የምርህን ነው::"

"የምሬን ነው፤ ሻይ ቡና እያልን ታሪኩን አጫውትሃለሁኝ::" አላቸውና አብረው ወደ ካሌብ ካፌና ሬስቶራንት አመሩ:: ከካፌው ደርሰው ወንበር ስበው ተቀመጡና ፕ/ር እሴ ለፕ/ር አጽበሐ ታሪኩን በሙሉ አጫወቷቸው::

"እና ይሄንን እውነታ ለማጋለጥ እስራኤላዊት ደህንነት ሞታለች ነው የምትለኝ?" አሉ ፕ/ር አጽበሐ ደንገጥ ብለው፤

"ኧረ ቀስ ብለህ አውራ በፈጠረህ! ሰው እንዳይሰማ!... ይህንንም አንተ ስለሆንክ፣ ስለማልዋሽህ ነው እንጂ የነገርኩህ ሚስጥር እኮ ነው::"

"እመነኝ ለማንም ትንፍሽ አልልም፤ ግን ቀጣዩ ጉዞህ ወዴት ነው የሚሆነው?" አለ ፕ/ር አጽበሐ፤ ፕ/ር እሴም ጺማቸውን እያሹ ከቆዩ በኋላ፡
"አባ ገዳው በላኩልኝ ደብዳቤ መሰረት ቀጣይ መዳረሻዬ ራማ የሚባል ከአደዋ ከተማ ማዶ ያለ ሰፈር እንዲሆን ነግረውኛል፤ እዚያም አንድ ነገር ይገለጽልሃል ብለውኝ ነበር:: ነገር ግን ቦታውን እንኳን ሄጀበት በስም እንኳን የማላውቀው ቦታ ስለሆነ ለመሄድ ውስጤ ፕርጣሬ ገብቶታል::" አሉ፡
"እንዴ የራማን አካባቢ እንዴት አታውቀውም፤ እኔ ከአንድም ሁለት ሦስቴ ሄጀበታለሁኝ..." አሉና ፕ/ር አጽበሐ ትንሽ አሰብ ካደረጉ በኋላ... "እንዲያውም ነገ አብረን እንሄዳለን::" አሏቸው፤
"የምርህን ነው?"
"አዎ!... አንተን ከመርዳቴ ባሻገር የነገርከኝ ታሪክ ውስጤ ላይ ጥያቄዎችን ስለፈጠረ አብሬህ ሄጄ ብሳተፍ ደስ ይለኛል::"
"እኔም ደስ ይለኛል::"... እያሉ እያወሩ ሳለ በካፌው በተሰቀለ የቴሌቪዥን መስኮት አንድ በቅርቡ ወደ ስልጣን የወጣ፤ ባለ ግርማ ሞገስ፡ ሰው ሰው፡ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሚሸት! አንድ የካህን፤ የወልይና መጋቢ ግርማ ሞገስ ያለው ሰው ይናገር ጀመር::
"እኛ ስንኖር ኢትዮጵያዊ፤ ስንሞት ደግሞ ኢትዮጵያ ነን..." እያለ፡ ፕ/ር እሴና ፕ/ር አጽበሐ እርስ በርስ ተያዩ፤ በአግራሞት ራሳቸውን ከመወዝወዝ ውጪ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም::

*** ፉ – ፉ ***

በማግስቱ ለናፆድ ሽኝት ከተደረገ በኋላ ኢትኤል፡ አብርሃምና መርየም የመጨረሻውን ወግ ለመስማት ከበራቸው ደጃፍ ከሚንዘላፈለው ቁጠማ አረፍ ያሉትን አባ ኤልካኖን ከበው ተቀመጡ:: አብዛኛውን የሌሊቱን ክፍል ሲጸልዩ ያደሩት አባ ኤልካኖን ፊታቸው በድካም ሳይሆን በጥዋት ጸዳል እንደተሞላ እንዲህ ሲሉ መናገር ጀመሩ::

"አዎ ልጆቼ እመኑኝ፤ ጽዮን ኢትዮጵያ ናት፡ የቅድስት ድንግል ማርያም ማደሪያ፤ የኪዳነ-ምህረት ወዳጅ ንዑዳን ህዝብ መኖሪያ፡ ጌታችን መድሐኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ያደገባት የዋል ደባ ገዳም መገኛ፡ በብርሃን ሰረገላ መልዓኩ ዑራኤል ለድንግል ማርያም እንዳሳየት ሁሉ እግዚአብሔር የሰጣት የርስት መሬቶች ያሉባት ደብር ነች::

ቃል ኪዳንም አላትና በሷ ላይ ይገለጻል:: እነሆ የካቲት 23/ 2010 ዓመት የቃል ኪዳኑ መፈፀም ማሳያ የሆነ ቀስተ ደመና በኢትዮጵያ ምድር በብዙ ስፍራዎች ተገለጠ:: ጥቁር ቀለም የደባለቅ ታላቅ ቀስተ ደመና ፀሐይን

በሰፊው ከበበ፡፡ ይህም ጥቁሩ በትዕግስት ውስጥ ትንሳዔውን የጠበቀ ትጉህ ህዝብን አመልካች ሲሆን፣ ከዚያም ቀስተ-ደመናው እየሰፋ መሄዱ በፍካሬ ትንቢት መሰረት በዓለም ላይ ላሉ ሰዎች ምልከትና **‹‹ከጽዮን ግንብ ስር ተሰብሰቡ››** የሚል መልዕከት ነው፡፡

በትንቢተ ኢሳይያስ በምዕራፍ 18፡ ቁጥር 7፤ "በዚያን ዘመን ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር - ከረጅምና ለስላሳ ወደሆነ ሕዝብ፥ ከመጀመሪያውም አስደንጋጭ ከሆነ ወገን፥ ከሚሰፍርና ከሚረግጥ ህዝብ፤ ወንዞችም ምድራቸውን ከሚከፍሉት ሕዝብ ዘንድ እጅ መንሻ የሆነ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ስም ወደሚገኝበት በጽዮን ተራራ ይሰፍራል፡፡" ብሎ ነግሮናል፡፡ ትንቢቱን ስገልጽላችሁም ‹‹ለስላሳ›› ሲልም የዋህና ደግ ሕዝብ ማለት ሲሆን፤ ‹‹ከመጀመሪያውም ስሙ አስደንጋጭ ከሆነ ወገን፥ ከሚሰፍርና ከሚረግጥ ሕዝብ›› ሲልም የሕዝቡን እየሰፈረ ስጪነት በከፋት ከመጡበት ግን ጠላጡን አስደንጋጭ ጀግንነቱን ለመግለጽ ነው፡፡ ወንዞችም ምድሩን ከሚከፍሉት ሲል ደግሞ ግዮን፣ ዋቢ ሸበሌና አዋሽን መሰል ወንዞች የሚከፍሏት ሃገራችንን ይወከላል፡፡

ስለሆነም የአምላካችን መንፈስ በኢትዮጵያ የመገለጫው ወቅት ደርሷልና፤ ገና በግንቦት 2ትም ታላቅ የብርሃን ጸዳል በፃድቃኒ ማርያም ላይ እንደሚገለጥ እናምናለን፡፡ ዓለም ዙሪያ ያላችሁ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆችም የጥሪውን መለከት ስትሰሙ ወደሷ ተሰብሰቡ እያልን እንጣራለን፡፡ የእግዚአብሔርም ብርሃን አእላፋትን ተሻግሮ ለሁሉም ይታያልና፡፡" አሉና አባ ኤልካና… "አይደለም እንዴ?" ብለው ጠየቋት፤ ፈገግ ብለው ወደ መርየም እየዞሩ፡፡

"ይመስለኛል… አላሁ ዓለም (እግዚአብሔር ያውቃል)"አለች፤ እሷም ፈገግ እያለች፤

"መርየም ልጄ ስልክሽ ላይ የቁርዓን ቃል ጭነሽበታልን?" አሏት በጥሞና እየተመለከቷት፤

"አዎን፡፡" አለች መርየም፤ ለአብርሃም ስለ ማርያም ምዕራፍ ለመናገር ‹‹ዳውን ሎድ›› አድርጋ በስልኳ ላይ የጫነችውን ቁርዓን እያስታወሰች፡፡

"ቴክኖሎጂም ቢሆን ለበጎ ካዋልነው መፅሐፍ ቅዱስና የሙስሊሞችን ቁርዓን ጨምሮ ብዙ ብዙ የሃይማኖትና የቅድስና መጽሐፍትን በቀላሉና በፍጥነት ለማግኘት ይረዱናል፡፡ ይሄ ጌም የምትሉትን ነገር መጫወታችሁ ባይከፋም እንደዚህ ለመሰሉ ቁም ነገሮችም ብታውሉትም መልካም ነው እላለሁኝ፡፡

ለማንኛውም እስኪ ቁርዓንሽን ከፈቺና ሱራ-አንኑር ቁ. 25ን የአማርኛውን ትርጉም አንብቢልን፤" አሏት፡፡

እሷም ከፍታ ማንበብ ጀመረች፤ *"አላህ የሰማያትና የምድር አብሪ ነው፡፡ የብርሃኑ ምሳሌ በውስጧ መብራት እንዳለባት (ዝግ) መስኮት፣ መብራቱ በብርጭቆ ውስጥ የኾነ፣ ብርጭቆይቱ ፍፁም ሉላዊ ኮከብ የምትመስል፣ ምሥራቃዊም ምዕራባዊም ካልኾነች ከተባረከች የወይራ ዛፍ ዘይቷ(የበራች)፣ እሳት ባይነካውም እንኳ ሊያበራ የሚቀርብ ከኾነች (ዘይት) (ይበልጥ) የሚቃጠል እንደሆነ (መብራት) ነው፡፡ (ይህ) በብርሃን ላይ የኾነ ብርሃን ነው፡፡ አላህ ወደ ብርሃኑ የሚሻውን ሰው ይመራል፡፡ አላህም ለሰዎች ምሳሌዎችን ያቀርባል፡፡ አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡"* ብላ ጨረሰች፤

"ይህ ቃል በእናንተም እውነተኛ ብርሃን አምላክ ብቻ እንደሆነ ያስመስክራል፡፡ ከዚያም ባለፈ የሚሻውን ሰው ወደዚህ ብርሃን እንደሚመራ ይናገራል፡፡ እስኪ እውነትን እንደምናገር የሚጠራጠሩኝ ካሉ በእኛ መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ምስክርነት ደግሞ እንዲያውቁ አብርሃም ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 1 ቁጥር 28ን አንብብልን"፡፡ አሉ ወደ አብርሃም ዞረው፡፡

እርሱም በስልኩ ላይ የሚገኘውን መጽሐፍ-ቅዱስ ከፍቶ ማንበብ ጀመረ፡፡ "(28፤) በዝናብ ቀን በደመና ውስጥ እንደ ቀስተ ደመና አምሳያ፥ እንዲሁ በዙሪያው ያለ ፀዳል አምሳያ ነበረ። የእግዚአብሔር ክብር ምሳሌ መልክ ይህ ነበረ። ባየሁም ጊዜ በግምባሬ ተደፋሁ፥ የሚናገርንም ድምፅ ሰማሁ።" ብሎ እንዳነበበ አባ ኤልካኖ ተቀብለው ቀጠሉ፡፡ "እንግዲያውስ እውነታው ይህ ነውና የአምላካችን ጸዳል ብርሃን የቀስተ ዳመና አምሳያ ነው፡፡ ቀጣዩን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከማንበብህ በፊት የሦስት ቃላትን ትርጉም ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አመሳክሬ እነግራችኋለሁኝ፡፡ የመጀመሪያው ቃል ‹‹ኢያስጲድ›› ሲሆን የዚህም ቃል ትርጉሙ ‹‹አረንጓዴ›› ቀለም ያለው ዕንቁ ነው፤ ሁለተኛው ‹‹ዮጵ›› ሲሆን ይህም ቢጫ ቀለም የተላበሰ ምድራዊ ‹‹ወርቅ›› ነው፤ ሦስተኛው ቃል ደግሞ ‹‹ሰርዲኖን›› ሲሆን ቀይ መልክ ያለው የእርያም ዕንቁ ነው፡፡ ይህን ካወቃችሁ ዘንዳ" አሉና ወደ አብርሃም ዞረው፤ "በል! የዮሐንስ ራእይ፤ ምዕራፍ አራት ሙሉውን አንብብልን፡፡" አሉትና ወደኋላቸው ደገፍ ብለው ተቀመጡ፡፡ አብርሃም በስልኩ ላይ ከተጫነው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያሉትን ቦታ ከፍቶ ማንበብ ጀመረ፡፡

*"(1፤) ከዚያ በኋላም አየሁ፥ እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ፥ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ። ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ አለ።*

*(2፤) ወዲያው በመንፈስ ነበርሁ፤ እነሆም፥ ዙፋን በሰማይ ቆሞአል በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ፤*

*(3፤) ተቀምጦም የነበረው በመልኩ **የኢያስጲድንና የሰርዲኖን ዕንቍ** ይመስል ነበር። በመልኩም መረግድን የመሰለ ቀስተ ደመና በዙፋኑ ዙሪያ ነበረ።*

*(4፤) በዙፋኑ ዙሪያም ሀያ አራት ዙፋኖች ነበሩ፥ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ሀያ አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ነበር።*

*(5፤) ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ ነጐድጓድም ይወጣል፤ በዙፋኑም ፊት ሰባት የእሳት መብራቶች ይበሩ ነበር፥ እነርሱም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።*

*(6፤) በዙፋኑም ፊት ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ። በዙፋኑም መካከል በዙፋኑም ዙሪያ፥ በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንስሶች ነበሩ።*

*(7፤) ፊተኛውም እንስሳ አንበሳን ይመስላል፥ ሁለተኛውም እንስሳ ጥጃን ይመስላል፥ ሦስተኛውም እንስሳ እንደ ሰው ፊት ነበረው፥ አራተኛውም እንስሳ የሚበረውን ንስር ይመስላል።*

*(8፤) አራቱም እንስሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሉአቸው፥ በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዓይኖች ሞልተውባቸዋል፤ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የነበረውና ያለ የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም።*

*(9፤) እንስሶቹም በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ከዘላለምም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው ለእርሱ ክብርና ውዳሴ ምስጋናም በሰጡት ጊዜ፥*

*(10-11፤) ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ። ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።(የዮሐ. ራእይ፤ ምዕ.4)*

ኢትኤል፣ አብርሃምና መርየም በጣም ተገርመው እርስ በእርስ ተያዩ፤

"አረንጓዴና ቀይ ቀለም ያለው ከሆነ ‹ዮጵ› የተሰኘውስ የቢጫ ቀለም የት አለ?" አለ ኢትኤል ግራ በመጋባት.. ባህታዊው አባ ኤልካኖ በልዩ ፈገግታ አይተውት፤ መልስ ሳይሰጡት ተነስተው ሄዱ።፡

ወዲያውም በራማ ተራራ እንዳሉ የብርሃን ጸዳል ፊታቸው ላይ ሲያንጸባርቅ፡፡ ኢትኤል፣ አብርሃምና መርየም ወደ ሰማዩ ቀና አሉ፡፡ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ደማቅ ቀስተ ደመና ሰማዩ ላይ ተዘርግቶ ነበር፡፡

»»ቶላና አባ ገዳው አቦ አራርሳ … ከኦሮሞ መንደር፤

ዘይኔና ወልዩ ሸህ ከድር … ከቁራኒ ማዶ፤

ዮሴፍና ራስታው በመርሳ … የእፅ ሜካ ውስጥ፤

ፕ/ር እሴና ፕ/ር አጽበሐ… ወደ አድዋ እየነዱ፤

ናያድ ደግሞ በሽገር እንዳለ ሁሉም ወደ ሰማይ ተመለከቱ፤ እነሆም እጅግ ደማቅ ቀስተ-ዳመና ሰማዩን ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ አሸብርቆት አዩ፡፡ አረንጓዴው በየዋህነትና ደግነት የተመሰረተ፣ ከልምላሜ ውስጥ የፈለቀ

ተፈጥሯዊ የህይወት መንገድ፤ በቢጫ ወርቃማ አንጡራ ሃብት፣ የማርያም መቀነት ሽብ በተደረገበት ፍቅርና ምህረት የሚመስል፣ ከኖኅ የተሰፋ ቃል ኪዳን የዘለቀ የእምነት አብነት፤ በቀይ አቶን እሳት የሚብበለበል ወኔና ንቃት እስከ ደም መሰዋዕትነት ድረስ ተከፍሎላት የቆመች ታላቅ ሃገር፣ የሰማዕቶች ምድር… ***ኢትዮጵያ፤***

**** ፆ – ፆ ****

*♫ "በቀስተ ዳመና - ሰማይ መቀነቱን - ባንዲራሽን ታጥቆ፣*
*አርማሽ የታተመ እንኳን በዓለም መዳፍ በአርያም ታውቆ*
*የተራሮች እናት ዘብ የቆሙልሽ የአክሱሟ ራስ ቶጲያ፣*
*የፍጥረት በር ነሽ የክብ ዓለም ምዕራፍ ዞሮ መጀመሪያ…*
*በሰማዩ ላይ ቢታይ ቀለም … የሷ ነው እንጂ ሌላ አይደለም!*
*የመጪው ዘመን ፊት ናት መሪ… ዛሬ ዓለም ቢላት ኋላ ቀሪ*
*ተዉኝ ይውጣልኝ ልጥራት ደጋግሜ… ኢትዮጵያ ማለት ለእኔ አይደል ወይ ስሜ*
*ቢጎል እንጀራው ከመሶቡ ላይ… እናት በሌላ ይቀየራል ወይ?*
*የሷን ውለታ ከፍሎ ሳይጨርሰው… ኢትዮጵያ ሲባል አብሮ አይልም ወይ ሰው?*
*‹‹ኢትዮጵያ›› … ‹ኢትዮጵያ›… ሃገሬ… ሃገሬ… ባንቺ አይደል ወይ ክብሬ፣*
*ባልፍም ኖሬ - ስለእናት ምድሬ - እሷ ናት ክብሬ - ኧረ እኔስ ሃገሬ!*
*ስንት የሞቱልሽ ለክብር[illegible]ብ ኢድረው*
*አልፈው ሲነኩሽ ባህርሽ [illegible]ተሻግረው፣*
*የጀግኖች አገር የአዳም እግር አሻራ ፥ ፈለገ ግዮን ያንቺ ስም ሲጠራ፣*
*እንኳን ሰማይ ላይ ባንዲራሽን አይቶ፣*
*ኢትዮጵያ ሲባል ማን ዝም ይላል ሰምቶ!*
*የሰለሞን እጽ ነሽ ፥ የቅዱሳን ዕንባ ፥ ያበቀለሽ ቅጠል*
*ዛሬ አዲስ አይደለም ፥ በለኮሰው እሳት ፥ የነካሽ ሲቃጠል*
*ሳይወሰን ዝናሽ ፥ በቅርሶችሽ ድርሳን ፥ በኢድባራት ታሪኩ፣*
*ነብዩ አይተው ከሩቅ ፥ ያሉልሽ በመፅሐፍ ፥ ኢትዮጵያን አትንኩ፣*
*በሰማዩ ላይ ቢታይ ቀለም… የሷ ነው እንጂ ሌላ አይደለም!*
*የመጪው ዘመን ፊት ናት መሪ… ዛሬ ዓለም ቢላት ኋላ ቀሪ*
*ተዉኝ ይውጣልኝ ልጥራት ደጋግሜ ፥ ኢትዮጵያ ማለት ለእኔ አይደል ወይ ስሜ*
*ቢጎል እንጀራው ከመሶቡ ላይ ፥ እናት በሌላ ይቀየራል ወይ፣*
*የሷን ውለታ ከፍሎ ሳይጨርሰው ፥ ኢትዮጵያ ሲባል አብሮ አይልም ወይ ሰው*
*‹‹ኢትዮጵያ!››… ‹‹ኢትዮጵያ!»… <<ሃገሬ»… ‹‹ሃገሬ»ባንቺ አይደል ወይ ክብሬ?!*
*በሰሜን በደቡብ በምስራቅ በምዕራብ ላይ ሙሉ ይሁን ያንቺ ሲሳይ*
***… ይራቅ ይራቅ ችግር ከምድርሽ - ሙሉ ሙሉ ይሁን ሲሳይሽ፤"***
***(ቴዎድሮስ ካሳሁን)***

# ምዕራፍ - ፲፪ …… «ኤቶዮጵ»

*"ኤቶዮጵም ከ√ማ ተራራ (Ω) ይመጣል - በግዮንም(⊕) ዙሪያ ይሰፍራል።"*

**«መዝሙረ ዳዊት —— ምዕራፍ፤ 69»**

33፤ እግዚአብሔር የተቸገሩትን ሰምቷል፤ እስረኞቹንም አልናቀምና።

34፤ ሰማይና ምድር፣ ባህርም በእርሷም የሚንቀሳቀስ ሁሉ ያመስግኑታል

35፤ እግዚአብሔርም ፅዮንን ያድናታልና፥ የይሁዳንም ከተሞች ይሠራልና፤ በዚያም ይቀመጣሉ ይወርሷትማል።

36፤ የባሪያዎቹ ዘር ይኖሩባታል። ስሙንም የሚወዱ በዚያ ይቀመጣሉ።

**** ቶ – ቶ ****

*አንድ ሰው አትሁን አንድም አይደለህም፥*

*ደጋን ሁን… ቀስት ሁን… ከቡ መሃል ገብተህ ከከቡ ተነጠል፤*
*የንስር አይኖች ያሉት አውሬን አዳኝ ምሰል*
*ፍዝ ኮከብ ስበር… ወደዚህ ነህ ሲሉህ ወደዚያ ተስፈንጠር፤*
*ከሰነፎች መሀል ቀስት ሆነህ ተወርወር*
*የደጋኑን ገመድ ወደኋላ ሳበው*
*ያልሳብከው ቀስት ነው እግርህ ስር 'ሚውድቀው።*

*(✍ ባለቅኔ ኤፍሬም ስዩም)*

**** ቶ – ቶ ****

***ዘ -ፍጥረተ እውነት...*** ሁለት ለአይንም ማራኪ፣ ለመብላትም የሚያጓጉ የንቃተ-አዕምሮ ፍሬን ያንጠለጠሉ ዛፎች በኤደን ገነት ውስጥ ቆመዋል፡፡ ኤደንን ባካበበው የግዮን ወንዝ ውሃ ላይጠወልጉ ፈክተዋል፡፡ መልዓክቶች ቁብም ሳይሰጧቸው እንዳላዩ ሁሉ ነበር የሚያልፏቸው፤ መብል ለእነርሱ ምናቸውም ነበር፡፡ ለሁለት የገነት ኑዋሪዎች ዘንድ ግን እነዚህ ዛፎች ልዩ የሆነ ስሜት ይፈጥርባቸው ነበር፤ ለአዳምና አጋሩ ለሆነችው ሴት፡፡

የመጀመሪያው ዛፍ፤ የእውቀት ዛፍ ሲሆን የአዕምሮን መልካምንና ክፉን የመለየት ዓይን የሚከፍቱ ፍሬዎችን ያፈራል፡፡ ፍሬዋም የእውቀት፣ የማስተዋል፣ የጥበብና ውሳኔዎችን በራስ በጎ-ፍቃድ የመወሰን ችሎታን እንዲይዝ ተደርጎም ነበር የተፈጠረው፡፡

ሁለተኛው ዛፍ፤ የህይወት ዛፍ ሲሆን የህይወት ፍሬዎችን ያመርታል፡፡ ይህን ፍሬ የበላም በህያውነት ለዘላለም እንዲኖር የሚያስችል ሆኖ ነበር የተፈጠረው፡፡ ይህንን ፍሬም የበላ አይሞትምም፡፡

ከኤደን ገነት በመባረሩ ቁጭት ያንገበገበው ሰይጣን እነአዳምን እንዴት እንደሚያሳስታቸው መላ ፈየደ፡፡ እነሆ በምድር ላይ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው እንስሳት በሙሉ እባብ ተንኮለኛና መሰሪ ነበር፡፡ ሰይጣንም ራሱ ወደ ኤደን ገነት እንዳይገባ ቢለለከልም እባብን መልዕክተኛው አድርጎ እየላከ አዳምና ሴትን ከእነዚህ ዛፎች እንዲበሉ መወስወስ ጀመረ፡፡ በጆሯቸውና ልቦናቸው እየመጣ ማንሾካሾኩን ሳያሰልስ ቀጠለ፡፡ ተንኮለኛው እባብ ሴትን "ከገነት ዛፎች በሙሉ እንድትበሉ ተፈቅዶላችኋልን?" ብሎ ጠየቃት፤

እርሷም "ከዚያች ዛፍ በስተቀር ሁሉንም መብላት እንደምንችል አዳም ነግሮኛል፡፡ እንዳለኝ ከሆነ ከዚያች ፍሬ ከበላን ሞት የሚባል ነገር ያገኘናል" ብላ መለሰችለት፤

እባቡም ሰይጣን ባለው መሰረት "ይህ ስህተት ነው፤ እ/ር ከዚያች ፍሬ እንዳትበሉ ያላችሁ እንደእሱ ሃያልና ሁሉን አዋቂ፤ መልካምና ክፉን የመለያ ጥበብም እንዳይኖራችሁ ነው፡፡" አላት፤

"እውነትህን ነው እንደዚያ አይነት እውቀት ይሰጣል?" አለች ሴት በጥርጣሬ፤

"እየነገርኩሽ! በዚያ ላይ እንደምታይው አዳም እኮ ላንቺ ጊዜ አይሰጥሽም፡፡ ካንቺ በላይም እግዚአብሔርን ይወዳል፡፡ ያቺን የእውቀት ዛፍ ፍሬ ቢበላ ግን ካንቺ እቅፍ አይወጣም፤ ውበትሽንም የሚያይበት ወንድነቱ ይገለጣል፡፡" ካንቺ እቅፍ አይወጣም፤ ውበትሽንም የሚያይበት ወንድነቱ ይገለጣል፡፡"

በዚህም ተደጋጋሚ ውስወሳው ሴት ተሸወደች፤ ፍሬዋንም ለመብላት ተመኘች፣ ጎመጀች፡፡ ምኞቷንም ተከተለች፤ ለዚህም ሄዋን ተባለች/ በኦሮምኛ ቋንቋ ሃዊ ማለትም ምኞት እንደማለትም ነው፡፡ እነሆም ሄዋን ተንጠራርታ

ከእውቀት ዛፍ አፀ-በለስ አወረደችና ገመጠች፤ ለአዳምም ሰጠችው:: ቀድሞውንም ፍሬዋን የሙብላት ፍላጎት በውስጡ ተፈጥሮ የነበረው አዳምም ተቀብሎ በላ:: ስኳርም፣ ጨውም፣ ዳማከሴም፣ ሎሚም አቀላቅሎ የህይወትን ስጋዊ ጠዓም እንደ መቅመስ ያለ ስሜት ሰጣቸው፤ ከመቅፅበትም አይነ-ስሜታቸው ተከፈተ:: ሃፍረተ-ስጋዎቻቸውንም ተያይተው ተፋፈሩ:: በዙሪያቸው የነበረው ነገር ሁሉ በአዲስ መንገድ ተገለጠላቸው:: ውስጠ ህሊናቸው ግን የሰሩት ነገር ልክ እንዳልሆነ እየነገራቸው ነበር:: በእርግጥም በተገለጠላቸው የማሰብ መንገድ በኩል ራቁታቸውን መሆናቸው ልክ እንዳልሆነ ገብቷቸዋል:: የሰው ልጆች የመጀመሪያ የፈጠራ ውጤት የሆነውን የቅጠል ልብስም ቆርጠው አገለደሙ::

አዳምና ሄዋን ቅጠሎቻቸውን አገልድመው ከዚህ በፊት በማያውቋቸው የፍርሃትና የፀፀት ስሜት እንደተሸረቡ ከእግዚአብሔር መደበቅ የሚችሉበት ቦታ መፈለግ ያዙ:: ሁሉን የሚያይና ሁሉን የሚያውቅ አምላክም የሰሩትን በሙሉ ያውቅ ነበርና ድምፁን ላከባቸው፤ እነርሱም በሰሙ ጊዜ መሸሸጊያ ፍለጋ ወዲህ ወዲያ ተራወጡ::

እ/ርም ይህን የሞኝ ሽሽታቸውን አይቶ፤ "ወዴት ነው የምትሸሸጉት?" ብሎ ጠየቃቸው፤

አዳምም መለሰ፤ "ድምፅህን ሰማሁኝ፤ እራቆቴንም ስለሆንሁ ፈራሁኝና ተሸሸግሁኝ፤"

"እራቁትህን መሆንህን ያወቅከው ከዚያች አትብላ ካልኩህ ፍሬ በልተህ አይደለምን?"

አዳምም አለ:: "ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርሷ ሰጠችኝና በላሁኝ::"… እግዚአብሔርም ሴቲቱን ለምን እንዲህ እንዳደረገች በጠየቃት ጊዜ እርሷ ደግሞ "እባብ አሳተኝና በላሁኝ::" አለች:: እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው። ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ፤ በሆድህም ትሄዳለህ፥ አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ትበላለህ።

በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።

ለሴቲቱም አላት። "በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፥ እርሱም ገዥሽ ይሆናል።"

አዳምንም አለው። "የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፤ እሾህንና አሜከላን

ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ፤ ወደ ወጣህበት መሬት እስከትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና፥ ወደ አፈርም ትመለሳለህ።"

እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥ አለበሳቸውም። እግዚአብሔር አምላክም አለ። **"እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፥ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፥ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፤" አለ፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክ ከዔድን ገነት አስወጣው፥ የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ። አዳምንም አስወጣው፥ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ።"**

›››››››››››››››››››› (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ፤3፡ 1-24) /(ሱራ አዕራፍ፤ 7፡27)

**** ቶ – ቶ ****

"እግዚአብሔር አምላክ አዳምና ሔዋንን ትዕዛዝ ባለማክበራቸው ከዔደን ገነት ሲያባራቸው የዘላለም ህይወት የሚሰጠውን የህይወት ፍሬ እንዳይበሉ መንገዱን በምትገለባበጥ የኪሩቤል ነበልባል ሰይፍ እንደዘጋው መጽሐፍ ቅዱሳችን ይነግረናል፡፡ ብዙሃኑ ሰው የነበልባል ሰይፍ ሲባል ግዙፍ የሆነ የሚነድ ጎራዴን ያስባል፡፡ የቅዱስ ቃሉ ሚስጥር ግን ሌላ ነው፡፡" አሉ አባ ኤልካኖን፤ ሦስተኛውና የመጨረሻውን ማብራሪቸውን እየጀመሩ፤ ኢትኤል፣ አብርሃምና መርየም ለመጨረሻው ትምህርታቸው ተደርድረው ቁጭ ብለዋል፡፡

"ወደ ማብራሪያው ስገባ የህይወት ዛፍ ማለት በራሱ ይሄ እኛ የምንተክለውን ዛፍ ሳይሆን ጥበብን የማስተዋል እና የጽድቅን ፍሬ የሚያሳይ ነው፡፡ በመጽሐፈ ምሳሌ11፡30 "የጻድቅ ፍሬ የሕይወት ዛፍ ናት ፤ ነፍሶችንም የሚሰበስብ እርሱ ጢቢብ ነው፡፡" ብሎ የሕይወት ዛፍን ይገልጻትና በምዕራፍ 15 ቁጥር 24 ደግሞ "በታች ካለው ከሲኦል ያመልጥ ዘንድ የሕይወት መንገድ አስተዋዩን ሰው ወደላይ ይወስደዋል፡፡" ብሎ ይህ የህይወት መንገድ ከሲያል አርቆ ወደ ዔደን ገነት የሚወስድ እንደሆነ ይመሰክራል፡፡ የኪሩቤልን እውነተኛ ትርጉም ለመረዳት እንድትችሉ በትንቢተ ሕዝቅኤል - ምዕራፍ 10 ከቁጥር 13 ጀምሮ ያለውን ቃል ላንብብላችሁ፡፡ አሉና ሦስት ጊዜ አማትበው ጸሎት ካደረሱ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ ከፍተው ማንበብ ጀመሩ፡፡... "13፤ መንኰራኵሮችም እኔ እየሰማሁ ጌልጌል ተብለው ተጠሩ።

14፡ ለእያንዳንዱም አራት አራት ፊት ነበሩት፤ አንደኛው ፊት የኪሩብ ፊት፣ ሁለተኛውም የሰው ፊት፣ ሦስተኛው የአንበሳ ፊት፣ አራተኛውም የንስር ፊት ነበረ።
15፤ ኪሩቤልም ከፍ ከፍ አሉ፤ ይህ በኮቦር ወንዝ ያየሁት እንስሳ ነው።
16፤ ኪሩቤልም ሲሄዱ መንኰራኵሮቹ በአጠገባቸው ይሄዱ ነበር፤ ኪሩቤልም ከምድር ከፍ ከፍ ይሉ ዘንድ ክንፎቻቸውን ሲዘረጉ መንኰራኵሮች ደግሞ ከአጠገባቸው ፈቀቅ አይሉም ነበር።
17፤ ሕይወት ያላቸው የእንስሶች መንፈስ በመንኰራኵሮች ውስጥ ነበረና እነዚህ ሲቆሙ እነዚያ ይቆሙ ነበር፥ እነዚህም ከፍ ከፍ ሲሉ እነዚያ ከእነርሱ ጋር ከፍ ከፍ ይሉ ነበር።
18፤ የእግዚአብሔርም ክብር ከቤቱ መድረክ ላይ ወጥቶ በኪሩቤል ላይ ቆመ።"

እነዚህን የእንስሳት ውክልናዎች ጠበብት አባቶቻችን ጠልሰም ይሏቸዋል፡፡ ትርጓሜያቸውም አምሳል፣ ውክልና እንዲሁም ስራን ማስዋብ እንደማለት ነው፡፡ ጠልሰም የተለየ ኃይል ያለው ጥበብ ነው፡፡ ይህም ሰይጣንን ፈተና አንኮታኩቶ የኪሩቤልን ድልድይ የማሻገር ኃይል ያለው ጥበብ ሲሆን ከእግዚአብሔር ለአባታችን ለሄኖክ የተገለጠ ነው፡፡ ይህም የጠልሰም ሰምና ወርቅ ያለው ጥበብ ልክ እንደኪሩቤል ሁሉ በአራት ምስሎች ይገለፃል፡፡ እነዚህም 4 ምስሎች ሰው፣ አንበሳ፣ ንስርና ላም ሲሆኑ የሰው ልጅም የተፈጠረባቸው 4 መሰረቶች መንፈስ፣ አዕምሮ፣ ነፋስና ስጋ ተተኪዎች ናቸው፡፡ እንግዲህ የኪሩቤልን ተተካኪ ፈተናዎችን ተሻግሮ ህያውነትን የተላበሰ ‹‹ሰው›› እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ከበታች ካለው የሲኦል ስቃይ መንጥቆ መንፈሳዊ ልቅናንም ይሰጠዋል፡፡... ታዲያ ይህን ዋጋው ልዩ የሆነ ጥበብ አሁን አብራራላችኋለሁኝ፡፡ እስከዚህም ተጉዛችኋልና ይህ የትዕግስተኞች በሙሉ ሽልማት ነው፡፡" ብለው በፈገግታ ቀጠሉ፤

"የመጀመሪያው የህይወት መንገድን የሚዘጋ ምስል ኪሩብ ላምን በሚመስል እንስሳ ይወከላል፡፡ ይህም የስጋ አካላችንና ልቦናችን የተሰራባት የዓለም/ የአፈር ምልክት ነው፡፡ በዚህም ስጋችን መልካችንና ቁሳዊ ሃብታችን ይጠበቃል፡፡ ይህንን የኪሩቤል ሰይፍ ለማለፍ ደግሞ ስጋችንን ለመቆጣጠርና በስሜት ከሚነዳ አውሬያዊ ስሜቶች ለመዳን የሚረዱን ፆም፣ ስግደትና ጥልቅ ሃሳብ ናቸው፡፡ ለዚህም ትጥቃችን ጤንነት (ከጤና እክሎች መራቅ)፣ እውቀት(ማንበብና ማጥናት)ና፣ ፅናት(እቅድን ማስመር) ናቸው፡፡

ሁለተኛው የንስር አሞራ ምስል ነው፡፡ ይህም እንደ ንፋስ ነፃነትን የተቸረው የነፍሳችን መገለጫ ሲሆን እስትንፋስ (ኦክስጅን) ላይ ያለው እንቅስቃሴያችን በሙሉ በዚህ ይመራል፡፡ ይህንን ንስርነታችንን በእኛ ስር አድርገን ለመብረርና ከኪሩቤል ሰይፎች ለማለፍ ደግሞ በመልካም ተግባር ልምምድ መኖር ዋናው መንገድ ሲሆን፤ በጥልቅ ተመስጦ ውስጥ ገብቶ እግዚአብሔርን ማሰብና ተስፋን ሰንቆ መጓዝ የዚህ የነፍሳችንን ጠልሰም ቅኔ መፍቻ ቁልፎች ናቸው፡፡

ሦስተኛው ምስል የአንበሳ ሲሆን መደቡም የእሳት ምልክት መገለጫ ነው፡፡ ይህም በአዕምሯችን ኃይል ባዘሉ ቃላቶቻችን ይገለጻሉ፡፡ ይህም የሃይልና የመነቃቂያ ተፈጥሮ የሚገራው በጥልቅ ምርምርና ትዕግስት ተመርቶ፣ በፈሪሃ እግዚአብሔር፣ በመተናነስና በትህትና የሚገኝ ጥበብን ሲይዙ ነው፡፡

አራተኛውና ከላይ የጠቀስኩላችሁን 3 ማንነቶች ከተጎናጸፉ በኋላ የሚደርሱበት ደረጃ ደግሞ የሰውነት ምስልን ይዞ ይገኛል፡፡ ይህም በውሃና በመንፈስ የሚገለፅ፣ የህያውነትና ዘላለማዊነት ደረጃ ሲሆን እምነት፣ ስነምግባር፣ ትዕግስት፣ ምህረት፣ ፅድቅና ሁሉንም የመቀበል የፍቅር ደረጃ ላይ ሲደርስ የሚገኝ ነው፡፡

ታዲያ እነዚህን አራቱን ምስሎች ከራሱ ያዋሃደ ሰው የኪሩቤልን ሰይፎች አልፎ የሕይወትን ፍሬ ይበላታል፤ ወደ እግዚአብሔር መንግስትም መግቢያውን ያበጃል፡፡ ይህንን መንገድ ለኛ ለማቅናት ሲል ስቃይና መከራን ለመቀበል ወደኋላ ያላለው ጌታችን መድሐኒታችን እየሱስ ክርስቶስም በወንጌሉ ‹‹የዘላለም ህይወትን አገኝ ዘንድ ምን ላድርግ?›› ብለው ሲጠይቁት በጌታ **ማመንን** (ዮሐ 14፡1)፤ አምላክህን በፍጹም **ልብህ** በፍጹም **ነፍስ**ህና በፍጹም **ኃይልህ** መውደድንና (ሉቃ 10፡ 25-30)፣ ሰውን **መውደድ**ን (ዮሐ 13፡ 34) እና **ትዕዛዛ**ትን ማክበር (ማር 17፡ 17-21) (ማቴ 1916፤ -22) እንደሆኑ ይነግረናል፡፡ የእነዚህን የኪሩቤል ተምሳሌት ስናዋህድም የዘላለም ህይወትን እንድናገኝ ማረጋገጫን ሰጥቶናል፡፡" አሉና አንጋጠው ወደ ሰማይ ከተመለከቱ በኋላ፤ ቀጠሉ……

"እነሆ ‹‹ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች›› (መዝ፤ 68፡31)፤ ወደ እግዚአብሔር የተዘረጉ እጆችም ባዷቸውን አይመለሱም፡፡ የፖለቲካውን ጦርነት እ/ር ፀሎታችንን ሰምቶ በቶዌድሮስ እየመለሰልን ነው፡፡ የሄኖክና የፍካሬ እየሱስ 10 ትንቢቶች ነበሩ 7ቱ ተፈፅመዋል፤ 3ቱም ይቀራሉ፡፡ ከእነዚህም አንዱ በስተመጨረሻ የእግዚአብሔርን ፍትህ ሳያጓድል ኢትዮጵያን የሚመራ ቅን መሪ መምጣቱ ነው፡፡ የተቀሩት ደግሞ የክርስቶስ መምጣትና አርማጌድዮን ናቸው፡፡ ይህም ንጉስ ከኢትዮጵያ አልፎ የዓለምን

ጭለማ እንደሚዋጋ ስለሚያውቁ ምዕራባውያኑ በየገዳሙ ፍለጋቸውን አጧጡፈውት ነበር:: በመሰረተ ልማት ስምም ገዳማትን እስከ ማፍረስ ድረስ እየሄዱ ፈልገውታል፤ እርሱ ግን ካልጠበቁት ስፍራ ተነስቶ ይነግስባቸዋል::

እንኳን እነርሱ የእኛም ህዝብ ባየይገባውም ኃይለ ስላሴ ግን ተናግረዋል፤ እነሆ ከሙስሊም አባት ይወለዳል፤ ተሰሚነት ባላቸውም፣ ት/ትን በተማሩ ምሁራን አፍ ይታገዛል:: እናንተ በዚህ ዘመን ህይወታቸውን እስከ መስጠት የሚደርሱ፣ ሰይፍ የሆነ ምላስ ያላቸው ጋዜጠኞች፣ ጠማሪዎችና ‹አክቲቪስቶ›ች ብላችሁ የምትጠሯቸው ትንታጎች አሏችሁ:: በእውቀትና በጥበብም ይመክራሉ፤ እናንተ ግን ትንቢቱን አታስተውሉምና ሌላ ቦታ ታማትራላችሁ:: እነሆ የኤልያስ መንፈስ ግን እውነትን ይመሰክራል:: የሀይማኖት ተቋሞቻችሁን የበግ ለምድ ለብሰው ጥቅምን ከሚያሳድዱ ተኩላዎች አጥሩ:: በአሁኑ ሰዓት ፓትሪያርክና ካህን መስለውም ቤተ-መቅደሳችን ድረስ ገብተዋል:: የመጣብንን ህቡዕ ጠላት ካላወቅነው ጉዳታችን የከፋ ነው:: ጸሎቴን የጠየቀህን እስረኛ ጨምሮ ብዙዎች በሀሰት የተወነጀሉ እስረኞች በቅርቡ ይለቀቃሉ:: ዋናዎቹ የጭለማ ግዞት አሳሪዎች ግን ገና ከደጃችን ቆመዋል:: ዶግማውንና ቀኖናውንም ሊቀይሩ ደፋ ቀና ማለት ጀምረዋል:: ፍቅር የሞላውን የኢትዮጵያ እስልምና በአክራሪ ገመድ የሚገዘግዙ ጠባቦች በየመስጊዱ ተሰግስገዋል::

አሁንም ከሃውልቱ ይልቅ ሃውልቱን እንድንሰራ ያደረገንን አምላክ ካልታመንን፤ ዋቄ ፈታዎችም ከዛፉ ይልቅ ዛፉን የፈጠረውን አንድ ዋቃ ካላከበሩ፤ ሙስሊሞቻችንም የካዕባን ዙሪያ በአንፖል ከማሽቆጥቆጥ ይልቅ የልባቸው ኢማን በብርሃን ፀዳል ማንቆጥቆጥ ካልቻሉ፤ እኛ ክርስቲያኖችም አንገታችን ላይ ማህተማችንን እንደምናስረው ሁሉ በልባችን መደብ ላይ የሚወከለውን የጽድቅ ህይወት ማህተም ካላተምን፤ እምነትን በነፍሳችን አንገት ላይ ካላሰርን እግዚአብሔርን እንደማናገኘው እንወቅ:: ድንጋዩም፣ ሃውልቱም፣ ዛፉም፣ እንጨቱም ከአንዱ እግዚአብሔር ተፈጥሯልና፤ አንዱንም እግዚአብሔር ያወድሳልና መመኪያችንም የእሱ መንፈስ-ቅዱስ ይሁን:: እነሆ የደጓ እናታችን ድንግል ማርያም ልጅ እየሱስ ክርስቶስ መምጫው ቅርብ ነው:: የራማዋ ኪዳነ ምህረት ድንግል ማርያም ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ታስብ፤ እግዚአብሔር አምላክም በቸርነቱና ምህረቱ ይጠብቀን:: አሜን፤ እነሆ ቃልኪዳኑን ፈፅሚያለሁኝ" አሉና የ‹፻› ቅርጽ ያለውን መቋሚያቸውን ደገፍ ብለው ከተቀመጡበት ተነሱ:: ቆመውም በመቋሚያው መሬቱን 3 ጊዜ መቱ፤ ይህው ዘንጋቸውን አስቀድመው እየተራመዱም በዝግታ ሄዱ::

***ፕ ተ***

በማግስቱ በጥዋት ጎህ ከመቅደዱ በፊት አባ ኤልካኖ ኢ.ትኤልን ከተኛበት ነቅነቅ ነቅነቅ አድርገው ቀሰቀሱት።
"ልጅ ኢ.ትኤል ና እስኪ ተከተለኝ።" አሉትና ተነስተው ከዳሱ ወጡ፤ በቅጡ እንኳን ሳይነቃ ቀልጠፍ ብሎ ቆመና ተከትሏቸው ወጥቶ ደረሰባቸው። አስር ያህል እርምጃዎችን ከዳሱ ርቀው ከተጓዙ በኋላ እጃቸውን ትከሻው ላይ አድርገው ቆሙ። በቅጡ ያልነጋ ጨለማ ሰማይ ላይ የጉሙ ጭጋግ ተጨምሮ ፊታቸውን በቅጡ ማየት አልቻለም ነበር።
"ያኔ የኔ እህት፤ ያንተ እናት እመቤት አንተን እርጉዝ ሳለች ከጎኗ ማልጠፋ ወንድሟ ነበርኩኝ። ታዲያ የምትወልድበት ቀን ደርሶ ምጧ ይመጣና እኔና አባትህ ደግፈናት በችኮላ ወደ ሆስፒታል ወሰድናት። ታዲያ በእግርህ በኩል መጥተህ ኖሮ ምጧ ረጅም ሰዓታትን ነበር የፈጀው። እኔና አባትህ ሳአል ከማዋለጃ ክፍሉ ደጃፍ ሆነን በጭንቀት እንንቆራጠጥ ነበር። ሌሊት 10:00 ሰዓት ገደማ ከማዋለጃ ክፍሉ ውጭ ላይ ባለ አግዳሚ ወንበር ላይ እንደተቀመጥኩኝ እንዴት እንደሆነ ሳላውቀው እንቅልፍ ጣለኝ።" አሉና እጃቸውን ከትከሻው ላይ አውርደው መቋሚያቸውን እየተመረኮዙ… እየተራመዱ ትረካውን ቀጠሉ።
"እናም ይገርምሃል እዚያችው አግዳሚ ወንበር ላይ እንደተኛሁኝ ነበር አንተ እንደምትወለድ በህልሜ የተገለጠልኝ። መወለድህም ብቻ ሳይሆን ስምህም ‹‹ኢ.ትኤል›› እንደሚባል፤ ባንተም ላይ ምልክት እንዳለ፤ የኪዳኑ ጊዜ ሲደርስም ወደ ራማ ተራራ እንደምትጓዝና ‹‹ኤቶዮጵ›› ተብለህ እንደምትጠራ፤ ለኢትዮጵያ ትንሳኤ ሲደርስ ለሚነሳው ንጉስ ባለራዕይና የጥበብ ገላጭ እንደምትሆን ሁሉ በህልሜ አየሁኝ።" ብለው በፈገግታ ወደ እሱ ዞሩ፤ ኢ.ትኤል የሚነግሩት ነገር እውን መሆኑን ማመን አቅቶት ያያቸዋል። "እነሆ የህልሙ መፈቻ ወቅት ደርሶ የነዮቶርን ጥበብ የተላበሰው መሪ በኢትዮጵያ ላይ ተሹሟል። አዎ! እግዚአብሔር ፊቱን ወደ'ኛ አዙሯልና የፍትሕ፣ የሃብትና አንድነት ጥያቄያችንን ሣልሳዊውን ቶዌድሮስ ይመልስልናል። ይህ ግን የመጀመሪያው ምዕራፍ ጦርነት ድል ብቻ ነው።… ከባዱ መንፈሳዊ ጦርነት ገና እየጠበቀን ነውና በታላቅ እምነትና ንቃተ ህሊና አብረን መቆም አለብን። እውቀት ተስፋና ፅናትን ታጥቀን እንዝመት። የኢትዮጵያ ትንሳኤ አሁን ነው። ኢትዮጵያ እንኳን ለራሷ ህዝቦች ለሌላም የምትተርፍበት፤ ለዓለም ሁሉ የፅድቅና የሰላም ምሳሌ የምትሆንበት፣ ህዝቧም በአንድ ልብ ሆኖ አምላኩን በእውነት የሚያመልከበትና የሚያስደስትበት፤ ውሸት ተሸንፎ እውነት የምትነግስበት፤ ተውሃዶ በእውነተኞችና ቅኖች ትከሻ ከፍ የምትልበት ጊዜው አሁን ነው። በተቃራኒው የሃገራችንን ትንሳኤ

የማይፈልጉ ውስጣዊም ሆኑ ውጫዊ ኃይሎች የሚተጉበት ነውና ከጽዮን ተራራ ተሰብስበን በንቃት መጠብቅ፤ በምህረት ኪዳናችን ፀንተን በራማ ጥላ ስር ሆነን ለሚመጣው ሁሉ መዘጋጀት አለብን::" አሉና እርምጃቸውን ገቱ፤ የኢትኤልን ክንድ ይዘውም፤ "ዝግጁ ነህ?" አሉት::

"ለምኑ?" አለ ኢትኤል ግራ እየተጋባ፤... "ለኤቶዮጵነት?" አሉት፤

"ለኢትዮጵያዊነትማ ድሮም ኢትዮጵያዊ ነኝ፤" አለ የሚሉት ያልገባው ኢትኤል፤ ሳይፈልጉ አሳቃቸው::

"ልክ ብለሃል ልጄ... ሁላችንም ድሮም፣ አሁንም ወደፊትም ኢትዮጵያዊ ነን... ደግ እንግዲያውስ ስለ ኤቶጵ ማንነትህ፣ ‹ቶ› ተዋህዶና ‹ዮጵ› ውበትህ ማወቅ ያለብህን ነግሬህ ስምህን ትረከባለህ::" አሉትና በቅርብ ከሚገኝ ከተጋደመ የዛፍ ግንድ ላይ ሄደው ተቀመጡ፤ ኢትኤልም ሄዶ ከጎናቸው ተቀመጠ::... "ምን መሰለህ የኔ ልጅ አንድ የሚነገር ታሪክ አለ:: ይህም ፍጥረታት በተፈጠሩ በመጀመሪያው ዓመት በአራተኛው ቀን ላይ በመላዕክት መካከል ግጭት መፈጠሩን የሚያትት ነው:: በዚህ ግጭትም አንጻራዊው ሳጥናኤልና ግብረ ሃይሉ ተምሳሌታውያኑን ቅዱሳን መልዓክት ገጠሟቸው:: በሁለት ተከታታይ ውግያዎችም አየሉባቸው:: በሦስተኛውና ታላቅ በሚባለው ጦርነት ግን ቅዱሳኑ ዳግመኛ እንዳይተናኮላቸው አድርገው ሳጥናኤልና ሃይሎቹን ቀጠቀጧቸው:: ይህም በዮሀንስ ራእይ ምዕ 12 ቁጥር 7 ላይ "በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ሚካኤልና መልዓክቱም ዘንዶውን ተዋጉ:: ዘንዶውም ከመላዕክቱ ጋር ተዋጋ... አልቻላቸውምም::" ተብሎ የተዘገበ ሲሆን ሙሉ ሐተታው ግን በመጽሐፍ ቅዱስ አንድምታ ላይ ይገኛል:: ሊቃውንት አባቶችም በዚህ ሦስተኛው ጦርነት ላይ ቅዱሳኑ ድል አድራጊ የሆኑት ልዑል እግዚአብሔር ክንፎቻቸው ላይ ልዩ ኃይል ያለውን የ ‹‹ ቶ ›› ምልክትን ቀርፆ ስላጎናጸፋቸው እንደሆነ ይመሰክራሉ:: ጥንት የነበሩ አባቶችም ለውጊያ ሲወጡ ይህንኑ ምልክት ይዘው ጠላቶቻቸውን ድባቅ ይመቱበት ነበር::"

"ይህ የ«**ቶ**» ምልክት ምንድነው ትርጉሙ?" አለ ኢትኤል ከፍተኛ የማወቅ ፍላጎት እየተነበበት:: ማስረዳታቸውን ጀመሩ..."ከ **‹T›** ዘንግ ላይ ያለችው የ **‹o›** የራስ ምልክት ወይም **‹የሰው ልጅ›** ሲሆን ይህም ልክ እንደ አክሱም ደጋን ከሰው ልጅ መንፈሳዊነት የሚፈልቅን ታላቅ **«ወጋግን»** ይወከላል:: በእየሱስ ክርስ**ቶ**ስ ስምም ውስጥ ተካቶ የሚገኘው **‹ቶ›** በኤፌ. 4:15 "ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን፤ በነገር ሁሉ **ራስ** ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤" እንዲል ቃሉ ወደ

ራስነት የሚያድግ የሰው ልጅን ያመላክታል፡፡ አንድ ግለሰብ እግሮቹን ገጥሞ፣ ሁለት እጆቹን ዘርግቶ የመስቀል ቅርፅ ሰርቶ ቢቆም የ‹ቶ›ን ቅርጽ ይይዛል፤ ይህም በመስቀል «✝» በመሰዋዕትነት እንደመጣ ህብረት የመደመር «+» ብቻ ሳይሆን በመዋሃድ የተሳሰረ አንድነትን መፍጠር ያሳያል፡፡ ከዚህ ትርጉም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ የወንድ መለያ« ♀ » ሲሆን ከዚህ ቀድመው ግን የድሮ አባቶቻችን አንድ ወንድ ሰው በሁሉም ረገድ አድጎ ወደ ሙሉ ሰውነት ሲደርስ ‹ኣቶ› ብለው መጥራታቸው የጥበቡን ቀደምት ባለቤትነታችንን ያመላክታል፡፡ በጥንታዊ የኑቢያና ሱባ ህውልቶች ላይም ተቀርጾ የሚገኘው ይህ የ ‹ቶ› ፊደል ብዙ የፍጥረትን ሚስጥር ስላዘለ የተለያዩ አጥኚዎች፣ ከንፋን ዘርግቶ ከቆመ ንስር፣ ከሻማ ብርሃን፣ ከዛፍ ቅርፅና ከመሳሰሉት ጋር እያያዙ ማብራሪያዎችን ያቀርባሉ፡፡ ይህም የሆነው ምስሉ የሁሉም ፍጥረታትን ህግ ያዘለ ታላቁ የተዋህዶ እግዚአብሔር በ፯/7 ቁጥር ላይ የገለጠው ሃይል ስለሆነ ነው፡፡ "በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች መካከልም በሽማግሌዎችም መካከል እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ፤ ሰባትም ቀንዶችና ሰባት አይኖች ነበሩት፤ እነርሱም ወደ ምድር የተላኩ ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው፡፡" *(የሐንስ ራእይ፤ 5፡6)* ተብሎ እንደተጻፈው «7» ቁጥር የፍጥረት ህግና ሚስጥራትን ያዘለ ድብቅ ሚስጥር አለው፡፡ ለዚህም ምሳሌ የሚሆኑት ሰባት ሰማያትን፣ ሰባት ምድርን፣ ሰባት ዓለማትን በሰባት ወቅቶች (ቀኖች) ስብኃት ለአብ በመፍጠሩ ሚስጥር 7ተኛው ቀን «ሰንበት» መከበሩ ነው፡፡ እግዚአብሔር በራሱ ምሳሌ መሰረት በሰባት መሰረት ላይ አዋህዶ የተፈጠረውን የሰው ልጅ ያመለክታል፡፡" አሉትና አንድ ጥቅ ል ዘርግተው ሰጡት፤ ምስሉን እያጣቀሰ ጊዜ ወስዶ አጠናው፡፡



*ይህም ምስል ከላይ ካለው **ራስ** ፣ 7ባተኛው ፍቅር ወሊድ፡*
*ከፈጣሪያችን የመገናኛ በር የሆነው **ንቁ ህሊናችን** ጀምሮ ሲወርድ፡*
*6ኛው የማይለዋወጥ ፅኑ ሃሳብ ያዘለ ማንነታችን መለያ እውን የሆነው **ልቦናችን**፡*
*5ኛው በአስተዋይነት ራእይ ማየት መቻል በነፃፍታድ በ**እጅ** ሚሰራ ስኑ ምግባር፡*
*4ኛው **ተመስጦን** ተጠቅመን በማሰላሰል የምናልመውን የምንሆንበት ግባችን*
*3ኛ በማስታወስና በጥናት አእምሯችንን ተጠቅመን የምናገኘው ማዕረግና **መልክ**፡*
*2ኛ በስማችን ተጠቅመን በአንደበተ ርቱዕ ንግግር፣ ዜማና ቋንቋ መካሊታችን*
***(ምላስ)** እስከ ታችኛው (ሆድ)*
*የስረኛው 1ኛ ደረጃ ላይ ያለው ስሜትና ጥርጣሬ ወለድ የሜንቅላት ምርምር የሚተርከው ተረት ተረታችን ድረስ ያሉንን የሰውነታችንን መሰረቶች የሚገልፅ ነው፡፡ **(ከብልቶች ፣ ከእግር ስር ወደ ምድር የሚጣል ሲጋዊ ጉድፍ)***

"የሰው ልጅ የነፃ ምርጫ ባለቤት ነው፤ ካሻው ወደ አውሬነት ደረጃም የመውረድ፣ ሰውም የመሆን፣ ታላቅ መንፈስም የመሸከም በጎ ፍቃድ አለውና አሁን የ«ቶ»ን ሚስጥር ካወቅህ ወደ ራስህ ተመልከት:: «ቶ» ማለትም አንተ ራስህ ነህና የታችኛውን የስሜታዊነት በር ዘግተህ በህሊናና አዕምሮ ንቃት ወደ «ራስ» ነት ደረጃህ ስታድግ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ትዋሃዳለህ::" አሉትና ኮስተር ብለው ተመለከቱት፤ በእስማማለሁኝ አንገቱን አነቃነቀላቸው::

"እንግዲያውስ የ«ቶ» ማንነትህን ከተረዳህ አሁን ደግሞ ስለ **«ዮጵ»** እነግርሃለሁኝ:: **«ዮጵ»** ወይም **«ዮጴ-ዝዮን»** ወይም **«የግዮን ወርቅ»** ማለት እንዳንተው ኢትኤል ይባል የነበረው የኢትዮጵያውያኖች ሁሉ የዘረ ምንጭ የሆነ ካህንና ንጉስ ለአምላኩ እግዚአብሔር ያቀረበው ስጦታ ነው:: ይህን ስጦታ ካቀረበ በኋላም **«ኤቶዮጵ»** ተብሎ ይህቺም ሃገር **ኢት-ዮጵ-ያ** ተብላ ተጠራች፤ ትርጉሙም **«የወርቅ ስጦታ ለእግዚአብሔር»** እንደ ማለት ነው::

ነገር ግን ይህ ስጦታ እንደሚመስልህ ወርቅ ብቻ ተሸክሞ ለፈጣሪ ማቅረብ አይደለም፤ ይሄ የሰሙ ትርጉም ነው:: የወርቁ ትርጉም ግን ኢትኤል አባታችን በጣም የጠለቀ የቋንቋ፣ የስነ-ግጥም፣ የቅኔ፣ የሙዚቃና የውዝዋዜ ጠበብት መሆኑ ነው:: ይህንም ሰምና ‹‹**ወርቅ**›› ያለው ለአምላኩ ከሚያቀርበው ‹‹**ዮጵ**›› ወርቅ በአብሮነት የሚያቀርበው የዝማሬና ቅዳሴ፣ የዜማ ትርጉሙም ‹‹ስጉ›› ብሎ ምስጋና ማቅረብ ሲሆን፤ የእግዚአብሔርን ውበት የሚገልጽ ጥልቅ ዜማና ግጥምም ነበር:: ከዚሁ ዜማው ጋር በዝማሜና ውዝዋዜ ሲንቀሳቀስ የሰዎችን ልብ የሚያቀልጥ ስለሆነ ‹‹በከዋክብት ስድር ላይ የሚደንስ የፀሐይ ልጅ›› ብለው ሰይመውት ነበር:: ከዚህም አልፎ ይህ ውብ ኪነቱ የከዋክብት ‹‹ኮዝሞዎቹ››ን እና መልዓክትን ይማርክ እንደነበር ይነገራል:: ለዚህም የአርያም ዜማዎችንና ምቶችን ከመላዕክትም ይገለጥለት ነበር:: ከዚህ የኤትዮጵ ታሪክ ጋር እጅግ የሚመሳሰል አንድ ከተወሰኑ ክፍለ ዘመናት በፊት በኢትዮጵያ የተነሳ ቅዱስ ሰው ነበር::

ቅዱስ ያሬድ ‹‹ዋይ ዜማ ዘሰማዕኩ እም ሰማይ ዘመላእክት ግናይ›› ብሎ ‹‹የቅዱሳን መላዕክትን ዜማ ሰማሁኝ›› ብሎ እንደመሰከረና ከየትኛውም የሙዚቃ ኖታ በፊት ‹‹ግእዝ›› ብሎ በር የከፈተ አግዓዚ ዜመኛ፣ ‹‹እዝል›› ብሎ የመንፈስ ምግብን አዝሎ፣ ‹‹አራራይ›› እያለ ልብን የሚያራራ ዝማሬን በ‹‹ድፋት›› እንደ ጌታችን ጎንበስ እያለ እግር እንዳጠበው፣ እንደተገረፈው ሁሉ ዝቅ እያለ፤ በ‹‹ሂደት››ም እንደ ውሃ ኩልል ብሎ እየፈሰሰ፣ እንደ

‹‹ቅናት››ም አንገቱን ቀና አድርጎ አምላኩን እየለመነ፣ በ‹‹ይዘት››ም ክርስቶስ ካለ ሃጢያቱ እንደተያዘው ሁሉ በሂደቱ ላይ ቀጥ ብሎ እየቆመ፣ ‹‹ቁርጥ›› ምልክት ላይ ሲደርስም እንደ ጌታ የአብን ፍቃድ ለመፈጸም መቁረጥ ንቅናቄውን ቆርጦ እያቆመ፣ ከዚያም ‹‹በጭረት›› ዘንግና በትር በመሰለ ቅርፅ ተደግፎ እንደመቆም ቃሉን ጎተት አድርጎ ቀና እየተባለ፣ ከዚያም እንደ የውሃና ደም ጠብታው በሚመስለው ‹‹ርክርክ›› ታረክርካለህ፣ ከዚያም የሰው ልጅ ከወደቀበት አፈፍ ብሎ ሲነሳ እንዳለው ቅርፅ የተሳለው ‹‹ደረት›› ምልክት መሰረት ጌታ ሁሉን እንደፈጸመ በከብርና በይባቤ መላእከት ወደ ላይ እንዳረገ ሁሉ እርሱም ብድግ እያለ፡፡ እንግዲህ በእነዚህ መመሪያዎች መሰረት በ‹‹ቅኝት›› እየተቃኘ፣ ማኅሌታዊያን በኅብረት እየተቀበሉት፣ በመቋሚያ እያዘመመ በመርገድ ያጸናጽል ነበር፡፡ ታዲያ ይህ ቅዱስ ያሬድ 50 ዋልያዎችና 70 ተማሪዎችን አስከትሎ ራሱ ከቆረቆረው በራስ ዳሸን ተራራ ከሚገኝ ጸለመት አጠገብ ባለ ሐዊ ገዳም እያስተማረ ሳለ እንደ ሄኖከና ኤልያስ ሳይሞት እንተሰወረ ገድሉ ላይ ተጽፏል፣ በገዳሙ ያሉ ቅዱስ አባቶችም ይመሰክራሉ፡፡

ታዲያ ለዚህ ለቅዱስ ያሬድ የተገለጠ ጥበብ ለቅም ቅም…እያቱ ከሆነው ካህኑ ንጉስ ኤቶዮጵ ቀድሞ የተገለጸው ነው፡፡ ይህንን የቋንቋ ዜማና ስነ-ግጥም እውቀቱን ተጠቅሞ ለወለዳቸው ልጆች የተለያዩ አይነት መንፈሳዊና ዓለማዊ ቋንቋዎችን፣ ዜማዎችንና ጭፈራዎችን አውርሶ በብሔር ልዩነት የተዋበን ጉራማይሌዎች አድርጓል፡፡ እንግዲህ የእነዚህን ሙዚቃዎችና ግጥሞች ውስጠ ሚስጥር ማጥናት ካንተ የሚጠበቅ የቤት ስራ ነው፡፡ ከልጅነት እ/ር ውስጥህ ባሳደረው የስነ-ጽሑፍ ፍቅር ገጣሚ መሆንህን ስትነግረኝ ገርሞኛል፡፡ እነሆ የግጥም መድብልህንም በመንፈሳዊነት አስተምህሮ አዋዝተህ ለህዝብ ታደርሳለህ፡፡ ደግሞም ብዙ ፀሐፍትና የጥበብ ሰዎች ከሚፈሩባት ትውልድ ነህና!… አንተ እንደ እኔ የልጅነት እድሜ ሁሉ አንተም የሙዚቃና የ‹‹ሬጌ›› ውዝዋዜን እንደምትወድም አውቃለሁኝ፣ ደግነትም በልብህ ውስጥ እንዳለ አይቻለሁኝ፡፡ ስለዚህ ይህንን ዝንባሌህን ተጠቅመህ ይህቺን የግጥም መፅሐፍህን ከማሳተምም ባሻገር ብዙ የነፍስ ምግቦችን ለህዝቡ እንደምታደርስ አምናለሁኝ፡፡ ዜማውንም አጥንተህ ጥልቅ ትርጉም ያላቸውን ስራዎች እንደምትሰራ ተስፋ አለኝ፡፡ የያሬዳዊ ዜማን አጥንተህ በውበት አዚም፣ የጥንቱን ኤቶዮጵን አድማስ ትረዳ ዘንድ የባህልና ዘመናዊ ሙዚቃዎችንም አጥንተህ የየትኛውንም ብሔረሰብ ባህል ሳትንቅ ለሁሉም ተደራሽ የሚያደርግ ስራ የጥበብ አከናፋት ይኑሩህ፡፡ የቦብ ማርሊይና ቶዌድሮስ ካሳሁንን ጥሩውን ተሞክሮ ውሰድ፡፡ ሰዎቹ 55000 ባፕቲስት ቸርች ለመስራት ፍቃድ አግኝተው በሃገርህ ላይ ተበትነዋልና የሚጠብቅህ ፈተና

ቀላል እንዳይመስልህ:: ግና እነዚህን ሁሉ ለማሳካት እንደምትጥርና ይህን የቤት ስራ በሚገባ እንደምትወጣ አምናለሁኝ... ለዚህ የቤት ስራ ዝግጁ ነህን?" አሉት ትከሻው ላይ እጃቸውን አኑረው:: "አዎን አንቴ!" አለ፤... "ስመ ክህነትህን ለመቀበልስ ዝግጁ ነህን?" አሉት፣ በድጋሚ "አዎን አንቴ!" አለና ከእግራቸው ስር በርከክ አለ::

"ስለዚህ ልጅ ኢትኤል ከዚህች ሰዓት ጀምሮ አንተ የ‹‹**ኤቶዮጵ**››ን መንፈስ አንግበሃል::" አሉትና ከቀሚሳቸው ‹ወርቀማ የ‹‹ ቶ ›› ምስል ያለው ማህተም አውጥተው በአንገቱ ዙሪያ አሰሩለት:: እንዲህም አሉት:: "(20) ልጄ ሆይ የአባትህን ትእዛዝ ጠብቅ የእናትህንም ህግ አትተው፤ (21) ሁል ጊዜ በልብህ አኑረው በአንገትህም እሰረው፤ (22) ስትሄድም ይመራሃል፤ ስትተኛ ይጠብቅሃል፤ ስትነሳ ያነጋግርሃል፤ (23) ትእዛዝ መብራት፤ ሕግ ብርሃን ነውና የተግሣጽ ንግግርም የህይወት ብርሃን ነው::" (መ.ምሳሌ ምዕ 6፤ 20-23) ተብሎ እንደተፃፈው እናትና አባትህ እውቀትን ባያወርሱህም እኔ አንትህ አሁን አስተምሬሃለሁኝና ህግና ትዕዛዝን በልብህ አኑረው፣ በነፍስህ ቀንዲል ላይም እሰረው እነሆም ይህንን ማህተምህንም አታውልቅ:: ከአጋንንት ጋር ለሚጠብቅህ ከባድ መንፈሳዊ ውጊያ ያግዝሃልና፤" ... "የምን አጋንንት?" አለ ኢትኤል እንደተንበረከከ፤

"ወዳጅህን ፅዮንን ወጥረው የያዟትን እርኩስ መንፈሶች ነዋ::" አሉትና ከተንበረከከበት እያነሱት፤

"ምን?... ፅዮንን አጋንንት?!" ኢትኤል ደነገጠ፤ "እሺ አሁን የት ነው ያለችው?" አላቸው፤ ወዳለችበት ሊከንፍ እየተዘጋጀ፤

"ባህር ሃጠራ ነው ያለችው፤" አሉት አባ ኤልካኖ መቋሚያቸውን እየወለወሉ፤

"በቃ ቶሎ በታውን አጠያይቄ ወደ ባህር ሃጠራ መሄድ አለብኝ::" አለና ሊሄድ ሲል ከንዱን ያዝ አድርገው አስቀሩት::

"ከየትኛውም መጓጓዣ የፈጠነ መጓጓዣ እኛ ዘንድ አለ:: ያላችሁበት ድረስ ስንመጣ በአውቶብስ እንዳይመስልህ፤ አሁን ፅዮን ያለችበት ባህር ሃጠራ ድረስ ስወስድህ ሚስጥሩን ራስህ ትመሰክራለህ::" አሉና መቋሚያቸውን ጠቆሙት፤... "ምን ላድርግ? አለ ኢትኤል፤

"በእምነት ተሞልተህ ያዘው!" አሉት:: ኢትኤል እጆቹን ዘርግቶ ዘንጉን ያዘ:: ግን ምንም የተፈጠረ ነገር የለም:: "እመን ልጅ ኢትኤል፤ እመን እንጂ አትፍራ:: ስለሚጠብቅህ ውጊያም አትጨነቅ በትንቢተ ዳንኤል 12፡1 "ላይ በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል

ይነሳል::" ተብሎ እንደተጻፈው እርሱ ያድብኻል፤ አንተ ከፊት በአምነት ቅደም እንጂ ከኋላህ አልፍ የብርሃን ስራዊት ይከተልሃል:: እኛም በቻልነው አቅም ሁሉ እንዋጋልሃለን:: ግን አስታውስ ዋናው ጦርነት አንተና ፅዮን ከአጋንንቱ ጭፍራ ጋር የምታደርጉት ነው::"

ኢትኤል ያሉትን በሙሉ ከሰማ በኋላ አይኑን ጨፍኖ ፅዮንን እያሰበ ዱላውን ጭምቅ አድርጎ ያዘው… አንገሉን እንደማዞርና እግሩም ውትርትር አለበት:: የእርሳቸው ድምጽም ራቀው፤ ሰውነቱን ይበርደው ጀመር:: አይኑን ሲገልጥ ራሱን ‹‹ባህር ሃጠራ›› አጠገብ ነበር ያገኘው::

*** ቶ – ቶ ***

## «ባህር ሃጠራ…»

እጅግ እየተደመመ ሰውነቱን መደባበስ ጀመረ፤ አዎ ህልምም አልነበረም:: ብዙ ኪሎ-ሜትሮችን በአይን ጥቅሻ ተሻግሯል:: ዙሪያውን ለማስተዋል ሲሞክር አንዲት ሴት ከእሱ በቅርብ ርቀት ላይ እየተርበተበተች ከባህሩ አጠገብ ቆማ አየ:: ቀስ እያለ እየተጠጋ ሲመለከታት ከባህር ሃጠራ በመረብ ተጠምዳ እንደተያዘች ዓሳ እየታገለች ነበር:: ልብ ብሎ ሲያስተውል ያቺው ምስኪኗ የልጅነት ጓዱ፣ የአሁኗ ፍቅሩ ፅዮን መሆኗን አረጋገጠ:: ነፃነቷን እንዳታውጅ እንቅፋት የሆነባት ነገር እንዳለ ተረድቷል::

ወደ እሷ ሊጠጋ ሲል ግን አንዳች እንደ አሳ-ነባሪ ጭራ የሚራገጥ ግርዶሽ መንገዱን ዘጋበት:: እየጮኸ በስሟ ቢጠራትም ፅዮን ግን አልዞረችም:: ወድያው አንድ መፍትሄ አሰበ፤ ስልኩን ከኪሱ አወጣና ወደ ቁጥሯ ደወለላት፣ አይጠራም:: ወዲያው ግን ስልኩን ይዞ በቆመበት ኢትኤል ራሱን ታዘበ፣ ከዚህ ሁሉ ተዓምራዊ ረጅም ጉዞ በኋላ በልቡ የተዘራውን የፈጣሪ ቃል ሃይል ዘንግቶ፤ አሁንም መንፈሳዊ ጦርነቱን በዓለማዊ መሳሪያ ብቻ ለማሸነፍ መሞከሩ ምን ያህል ሞኝነት እንደሆነ አሰበና በራሱ ስራ ፈገግ አለ:: ወዲያውም ከስልኩ ላይ የዘይኔ፣ የቶላ፣ የአብርሃም፣ የመርየምና የዮሴፍን ስልኮች መርጦ ለሁሉም እንዲህ የሚል ተመሳሳይ የፅሑፍ መልዕክት ላከላቸው::

*‹‹ውድ ጓደኞቼ እኔና ፅዮን ትልቅ ፈተና ውስጥ ስለሆንን በያላችሁበት በጸሎት አስቡን"*

ከዚያም ስልኩን መልሶ ወደ ኪሱ ከተተና ተንበርክኮ በፀሎት መትጋቱን ተያያዘው… እግዚአብሔር ሰይጣን የዘረጋውን ወጥመድ እንዲበጣጥስ ጠያቀ:: በዚያው መንፈስ ከአንበርክኮ ተነስቶ፣ አባ ኤልካኖ የሰጡትን ማህተም ከልብሶቹ ውስጥ አወጣ፤ ግርዶሹን ማለፍ እንደሚችል አምኖም

ወደ ፅዮን ሸመጠጠ፣ እንደ ማዕበል ላይ ተንሳፋፊዎች(ሰርፈርስ) በመንፈስ ሃሴት እያደረገ ግርዶሹን በሳው:: ልክ በልጅነት አባሮሽ ጨዋታቸው ወቅት ጉንፋናሙን ሰኢዶ ሸውዶ እንዳስፈታት ሁሉ ግርዶሹን በጥሶት እጇን ያዛት… ፅዮን ግን ገና አልተፈታችም ነበር::

*** ቶ – ቶ ***

*የሳጥናኤልን ጋንታ አገዛ ያገኙት ሱቃኤልና አዛዝኤል፣ ባህር ሃጠራ ደርሰው ቆሙ፤ ቅድም ያባረሯቸው ቅዱሳንም ከመቅፀበት ከቦታው ደረሱ፤ እነአዛዝኤል* እኩል እንደ ሞገድ የሚመጣባቸውን ቅዱስ ግብረ-ሓይል ተመለከቱ:: አሁን ግን ከጎናቸው ሳጥናኤል ስላለ ከመሸሽ ይልቅ መዋጋትን መረጡ::… የሚመጡት በአካል ሶስት አባ ኤልካኖ፣ ሼህ ከድርና አቦ አራርሳ፤ አሁን ግን ከቅድሙ በተለየ አንድ ወጣት አጅበው ነው የመጡት::

በመንፈስ ግን የትየለሌ ናቸው፤… አመጣጣቸው ያስደነግጣል… ግርማቸው ያስፈራል!

በህያው መንፈስ ተሞልተው… በመታዘዝ ቅዱስ ግብር-ኤል፣ "እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም!" ብሎ በታጠቀው ሚካ-ኤል መንፈስ ታጅበው እየነጎዱ ነው:: ለማዳን ጥሪው፤ ሚካውን እየሰነጠቀ ወደ እነአዛዝኤል ገሰገሱ:: ሱቃኤልና አዛዝኤል እርስ በርሳቸው በፍርሃት ተያዩ:: ቀና ሲሉ ሳጥናኤል የትምክህትን ሰይፍ ይዞ ለጦርነቱ ሲሰናዳ አዩት:: ወጣቱ ሰው እየገሰገሰ መጥቶ በሃይማኖት አክራሪነትና በዘረኝነት ብሎኬቶች ከሰሩት ግርዶሽ ጋር ተጋጭቶ ሲመለስ ፍርሃታቸው ትንሽ ረገብ ብሎ በፈገግታ ተያዩ:: ነገር ግን ወጣቱ ሰው አንዳች ነገር እንደተገለጠለት ሁሉ ፈገግ አለና ከአንገቱ ላይ ያቺን የማይወዷትን ምልክት አኖረ፣ በእምነት ሰይፍም ከፉኛ ያዳክማቸው ጀመር:: የተለያየ ሃይማኖት ያላቸው ጓደኞቹን በማፀለይም የሰሩትን ግርዶሽ አንኮታኮተው… እንደ ጦርም በጣጥሶት ወደ ውስጥ ዘልቆ የፅዮንን እጆች ያዛቸው:: እነሱቃኤል በድንጋጤ ክው እንዳሉ ሳጥናኤል ለፍልሚያው ወደታች ሲምዘገዘግ አዩት:: ለአልሞት ባይ ተጋዳይ ትግሉም እነርሱም ተከተሉት:: ወጣቱን አጅበው የመጡት ታላቅ የብርሃን ሰራዊቶችም ለጦርነቱ ከነሙሉ ግርማቸው ተሰለፉ::

*በፅዮን ሃገር፣ ከኢትዮጵያ አውድማ ለሚደረግ ታላቅ መንፈሳዊ ውጊያ ምገዶች ተርገበገቡ!*

*** ቶ – ቶ ***

"ጠላት በከንፈሩ ይሰጣል በልቡ ግን ተንኮልን ያኖራል" እንዲል ቃሉ የአባቷን የሙት መንፈስ አሳይሻለሁኝ በሚል የውሸት ተስፋ ተሸውዳ የተያዘች ፅዮን እየታገለች ቆማለች፤ እጆቿን የያዘው ማን እንደሆነ ለማወቅ ዞራ መመልከት ፈልጋለች። በደም ስሮቿ ውስጥ ሰርፆ የገባው ያ… ህቡዕ መንፈስ ግን እንደማጅራት ገትር አንገቷን ወጥሮ ይዞ እንዳትዞር ከለከላት። የነፍሷ አይን ግን በአንገት ሸንበቆ ሳይሆን እንደ ንፋስ ነፃ በሆነ ሃይል ይገፋልና ከጎኗ የቆመው ማን እንደሆነ ከማየት አልታገደም። በፍቅር ብርሃን የማይፈካ ጭለማ፤ የማይሸፈን ቦታ የለምና እጆቿን የያዘው የልቧን ግዛት ቀድሞ በፍቅር የያዘው ኢትኤል እንደሆነ አውቃለች። መናገር ጀምሮ የናፈቃትን ድምፁን ስትሰማ ደግሞ የተስፋ ብርሃን ውስጧ ይበራ ጀመረ፤ እሱም ወደእሷ ተጠግቶ አቀፋትና በጆሯዋ ያንሾካሹካል፦

"ፅዮን አይዞሽ!… አውቃለሁኝ እየሰማሽኝ እንደሆነ፡ በከለለሽ የጉም ጭለማ ውስጥ አንቺነትሽ እንዳለ አውቃለሁኝ። ንጋቱ ቅርብ ነው፤ ከጭለማም በኋላ ወጋገን ይወጣል፤ ጮራ ይፈነጥቃል። አዎ! ንጋቱ ቅርብ ነው። ነገር ግን አይኖችሽን ከፍተሽ ብርሃኑን ለማየት አትታገይ፡ ይልቅስ ይበልጥ ጨፍኚውና ወደ ውስጥሽ ብርሃን ጥለቂ፤ ውስጥሽን በእምነት ማዕበል አላውሺው። በጭለማው ውስጥ እውነተኛውን ብርሃን ወደ ሚሰጠው እግዚአብሔር ተጣሪ፤ እርሱም በነፍስሽ ላይ የመንቃትን ችቦ ለኩሶ የተስፋ መቁረጥን ጨለማ ይገፋል። መጠጊያ አምላክሽን ድምፅሽን ጮኸሽ ባታወጪም በዝምታ ውስጥ አነጋግሪው፤ "የሚረዳኝ የለምና ከእኔ አትራቅ!" ብለሽ ለምኚው።" አለና እጆቿ ይበልጥ ጭምቅ አድርጎ ይዞ በመንፈስ ኔትወርክ፤ በፍቅር ሰንሰለት መናገሩን ቀጠለ።

"አዎን በእሱ እመኚ እንጂ አትፍሪ ፅዮኔ! ንጋቱ ቅርብ ነውና። ብርሃንም ይወጣል፤ ጮራ ይፈነጥቃል፤ ድልሁ ሰማይ በፀሐይ ይወግጋል… ላጠፋም ላለማም አዲስ እድል ይሰጣል። ላንቺም እንደዚያው ነው ከውሸቱ ጨለማ ፈክተሽ እንድትወጪ፤ ከጥላቻ በቀል ምህረትን ምረጪ። የበደሉሽን ሁሉ "የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው!" ብለሽ ፀልይላቸው። ባንቺ የይቅርታ ፀበል ከነርሱ በላይ ላንቺ ታላቅ ዋጋ አለሽና፤ የይቅርታ አምላክ ላንቺም ታላቅ ፀጋን ያፈስልሻልና።"

"አውቃለሁኝ ፅዮኔ፡ አውቃለሁኝ ከልጅነት ጀምሮ እስከ አውቀት ሳይመችሽ በችግርና ፈተና የኖርሽ ልጅ እንደሆነሽ አውቃለሁኝ። የእኔው ቤተሰቦች ቤተሰቦችሽ ላይ ባስደገሙት መተት በድህነት ኖረሽ፤ የምትወጂው አባትሽን ለምርቃትሽ ደርሶ እንኳን ወግ ማዕረግሽን ሳያይ እንዳጣሽው አውቃለሁኝ።" ... ይህንን ሲላት እንባ በአይኑ ግጥም ብሎ ሞልቶ ነበር። "የኔ ምስኪን ከርታታ፣ የኔው ድሃዋ፣ ተውተርታሪ ታታሪዋ፣ እኔም ያንቺው አንቺም የኔዋ። አዎን አውቃለሁኝ፤ ከልጅነትጅ ጀምሮ ለኔ ብለሽ መገረፍሽን፤ እኔን ብለሽ መሰቃየትሽን፤ ከየዋህ የልጅነት ዘመናችን ጀምሮ የኔን ፍቅር አዝለሽ ማደግሽን አውቃለሁኝ፤ እኔ ግን አይኔን መክፈት ተስኖኝ አልተረዳሁሽም፤ በድዬሻለሁኝ። ሀዘንሽና ፈተናሽ ቢበዛ፣ ከጎንሽ የኔ የምትይው ሰው ብታጪ እጅሽን ለእነዚህ እርኩሶች እንደሠጠሽ አውቃለሁኝ። አሁን ግን እኔም ይሄው ያስተማርሽኝ ፍቅር፤ ገንዘብ ባይኖርሽም በልብሽ ባለው ሃብት በሰጠሽኝ እውነተኛ ደስታ፤ ያስጠናሽኝ ንፁህ የህይወት ትምህርት ማዕዛው ጠርቶኝ፤ በምስኪን ማንነትሽ ስታጠጪኝ የነበረው የቆርኪ ቡናሽ ናፍቆኝ መጥቻለሁኝ፤ ምክንያቱም የፍቅርን ትርጉም ባላውቅ ነው እንጂ አንቺንስ ነፍስ ካወቅኩባት ቀን ጀምሮ አፍቅሬሻለሁኝ። ሁሉም የገባኝ ግን በህይወቴ ውስጥ እ/ርን ካስገባው በኋላ ነው። ምክንያቱም የፍቅር ትርጉሙም እ/ር ነውና። ስለዚህ የኔ ፍቅር እኔንም ይቅር በይኝ። ቢዘገይም እንደምወድሽ አሁን ልንገርሽ። አዎ የኔ እናት ለኔ የፍቅር ትርጉሙ አንቺ ነሽ። ካላንቺ ያለፈውም የሚመጣውም ህይወቴ ሙሉ ደስታን አያገኝም።

*ስለዚህ ለሌሎቹ ብቻ ሳይሆን ለእኔም ይቅርታሽን ለግሺና አብረን ነፃ እንውጣ። ፍቅርሽን ከፍቅሬ አሳኪና ልክ እንደ ልጅነታችን የአቡሰንበቴ ጨዋታ እጆችሽን ይዤ ነፃ እንዳወጣሽ ፍቀጂልኝ። አንቺም የሥጋ እጅሽን ሳይሆን የመንፈስ ክንፎችሽን ዘርጊና ተቀበይኝ። ምክንያቱም ያኔ አባራሪያችን ምስኪኑ ዋሴ ነበር። አሁን ግን አሳዳጃችን ነፍስንም ለማሰር የሚታትረው ዲያቢሎስ ነው። ነገር ግን በእምነትና በአንድነት ነቅተን ከታገልነው ምንም አቅም የሌለው ጠላታችን ነውና እናሸንፈው፤ በይ ንቂ የኔ ፂያ፤ ፍቅር በወለደው እምነት ውስጥ ሆነን ይህንን እስር ቤት እናፍርሰው። ንቂ ፂያ! ንቂ!... እኔም ከጎንሽ አለው አሸንፈሽ ውጪ!.. ውጪ!" እያለም ይወተውታት*

ነበር፡፡... ወዲያውም ጨለማው ሙሉ ለሙሉ ለፀሐይ እጅ እየሰጠ፣ ወጋገን ወገገ፣ ጎህ ቀደደ፣ ጮራ ፈነጠቀ፡፡

*** ፉ – ፉ ***

ከሼህ ከድር ጋር ያለው ዘይኔ ኢትኤል በላከለት መልዕክት ሲነቃ ጎህ ሲቀድ ተመለከተ፤ እንዲህም ሲል ለፅዮን ዱዓ አደረገ፡፡ "(1) ፀሐይን በሚያፈልቅ የጎህ ጌታ እጠበቃለሁኝ፡፡ ከፈጠረው ፍጡር ሁሉ ክፋት፡፡ በውድቅት ላይ በጭለማው ጊዜ፤ በተበተቡት ክሮች ላይ ተፊዎች ከሆኑት (መተተኛ) ሴቶችም ክፋት፡፡ ከምቀኛም ምቀኝነት በእርሱ (እጠበቃለሁኝ)፡፡" (ቅ.ቁርዓን፤ የተፈልቃቂው ምዕራፍ፡ 113፤ 1-5)

*** ፉ – ፉ ***

ከባህታዊው አባ ኤልካኖን ጋር ያለው አብርሃምም ከዳሱ ወጥቶ ወጋገኗን ባየ ጊዜ ይህንን ቃል አንብቦ ፀሎቱን አደረሰ፡፡ "ለቅኖች ብርሃን በጨለማ ወጣ፤ መሃሪና ይቅር ባይ ጻዲቅም ነው፡፡" (መ. ዳዊት 112፤ 4)

*** ፉ – ፉ ***

ከአቦ አራርሳ ጋር ያለው ቶላ ጮራ ሲፈነጥቅ ባየ ጊዜ እንዲህም አለ፤ "ዱኬኒራ ኢፋኒ ሂን ባኢ/ ራህ ሆይ ብርሃንህን ጨለማው ላይ አብራ፤ ያ ዋቄ ፈታ ሆይ ይህቺን ልጅ ከታሰረችበት የድግምት ትብታብ ፍታ፤"

*** ፉ – ፉ ***

መርየም፣ ናዖድና ዮሴፍም በያሉበት ለፅዮን ጸሎታቸውን አደረሱ፡፡

*** ፉ – ፉ ***

ፅዮን የኢትኤል ድምፅ ከውሃ ሿሿታ ጋር ተቀላቅሎ ይሰማት ጀመር፡፡ አይኖቿ የንጋቱን ወጋገን ለማየት ዳዱ፡፡ ለራሷም አለች፤ "የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ የከፋት ፅልመትን ሁሉ የምታሸንፍ ታላቅ ብርሃን ነህ፡፡ ጨለማም ካንተ ዘንድ ነውና አንተን ሊያሸንፍ የሚችል ፅልመት የለም፡፡ አንተ ኤልሻዳይ ሁሉን ቻይ ነህና በአንተ ምህረትና ይቅር ባይነት ውስጥ ኢድሬ ያስከፋኝን፣ ያሴሩብኝን፣ የጎዱኝን በሙሉ ይቅር ብያለሁኝ፡፡ በአንተ ታላቅነት አሁንም፣ ወደፊትም ሁሉንም ከፋት አሸንፋለሁኝ፡፡ አሜን!"

*** ቶ – ቶ ***

## እነሆ ፅዮን ኒቃች!፤ ፈጣሪዋም ከጠላቶቿ እጅ ተቤዣት፤

የአነ ሱቃኤል ለረጅም ጊዜ የተሸረበ ሴራም በአንድ ንጋት ተበጣጠሰ፡፡ የሳጥናኤል ሰይፍ በብርሃን ሰራዊት ተርበደበደ፡፡ ሰይጣን የሰው ልጅን ፈትኖ ሲያሸንፈው ያ ሰው በሚያገኘው ፅድቅ እየተቃጠለ ባልፈተንኩት ኖሮ ብሎ በፀፀት ይበግናል፡፡ ዛሬም ፅዮን ነጻ ስትወጣ በፀፀት ጥርሱን እያፋጨ ወደ ጥልቁ ወረደ፡፡ ዛሬ ታላቅ ጦርነትን ቢሸነፍም ግን የሰው ልጅን ለመፈተን መትጋቱን አያቆምም!… ኤቶዮጵ፣ የእሷ ኢትኤል ፈጠን ብሎ አቀፋት፤ ፅዮን በኢትኤል፣ ኢትኤልም በፅዮን አንገት ስር ገብተው ስቅስቅ ብለው አለቀሱ፡፡

በፍጥነት ይዟት ወጣና ወደ አዲስ አበባ በሚሄድ መኪና ተሳፈሩ፡፡ ጉዞውን እንደጀመሩ ከፍተኛ ድካም ውስጥ የነበረችው ፅዮን ትከሻውን ደገፍ እንዳለች እንቅልፍ ጣላት፡፡ በስስት አይኖች አያትና ግንባሯን ሳም አደረጋት፡፡

"ነገሮች የማይታለፉ ቢመስሉም እግዚአብሔር ግን ለካ ሁሉንም በምክንያት ነው የሚያደርገው፤ መገናኘታችንና መለያየታችንም ለካስ ለምክንያት ነበር፡፡ ያ እሷን በማሰብ በሃሳብ ተወጥሮ ያሳለፈውን ጊዜ አሰበው፡፡ ከባድ ጊዜ ቢሆንም ከምንም በላይ እግዚአብሔር እነአብርሃምን የመሰለ ውድ ጓደኞች ስለሰጠው እድለኛነት ተሰማው፡፡ እርግጥም ጓደኝነት ልዩ ነው፡፡ ፅዮንን እንዳይቀሰቅሳት እየተጠነቀቀ የሚወደውን የግጥም ደብተሩን አወጣና እነሆ ስለ ጓደኝነት፤ ስንኝ መቋጠር ጀመረ፡፡

✍ ___ #ጓደኛ_ልዩ_ነው!!!_____

በዘር ዝራ አዝዕርት - በደም ያልተሰጠ
በንዋይ ድሪቶ - በጥቅም ያልተገኘ፥
ድንበር ተሻጋሪ ሰፍራ ያልገደበው
ከእምነት ብሔር አልፎ ፍቅር የወለደው
የኑሮ እስትንፋስ ጓደኛ ልዩ ነው፤

… ጓደኛ ልዩ ነው! ሁሉንም ይልቃል፥
ብታዘም ደግፎ ብትወድቅ ያነሳል
ባንተ ቦታ ሆኖ ችግር ይካፈላል
ማስመሰል አያውቅ - ሀዘንን ያቀላል፣
እንባህን ቀልዶ በሳቅ ይቀይራል፤

*… ፍፁም እንድትሆን ከቶ መች ጠብቆ!*
*ስተህ ብታጠፋም መቼ ቂምን ቋጥሮ!*
*ስታብድ አብሮህ አብዶ …*
*ከህመምህ ስቃይ አብሮ ይፈወሳል*
*ከራሱ አስበልጦ በደስታህ ይፈካል፤*

*…እውነት ምርጥ ነገር ፈጣሪ የላከው!*
*ቅኔው የጠበቀ ሚስጥሩን ያጣነው፥*
*መወለድ ቋንቋ ሆኖ በቃል ያልገለፀው…*
*የጓደኛ ዋጋው ትርጉሙ ልዩ ነው!!*

ኢትኤል የጻፈውን ግጥም እነአብርሃምን እያሰበ አነበበውና ፈገግ አለ፡፡ ዞር ሲልም ፅዮን ትከሻውን ደገፍ ብላ ተኝታለች፤ በስስት አያትና ግንባሯን ሳማት፡፡ ቀና ሲል አንድ በመኪናው ውስጥ የተለጠፈ አባባል ቀልቡን ገዛው፤ እንዲህ ይላል…

«ትዕግስትና ፅናት ካለ የማይታለፍ ፈተና፣ የማይፈታ ችግር የለም፡፡»

*ኢትኤልና ፅዮንን የያዘው መኪና ወደ አዲስ አበባ ገሰገሰ፡፡*

**** ፍ – ፍ ****

# ምዕራፍ ፲፫ ... አንድ-ፍቅር ፩♥

*"ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላከኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ።" "እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፤ በአንድ ፍፁማን እንዲሆኑ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደላከኝ በወደደኸኝም መጠን እነርሱንም እንደወደድካቸው ያውቃሉ::"..... (የዮሐንስ ወንጌል 17:20-23)*

*"የአምላካችሁን የአንድነት ገመድ ሁላችሁም ያዙ፤ አትለያዩም:: ጠበኞችም በነበራችሁ ጊዜ በእናንተ ላይ የዋልነው ውለታችንን አስታውሱ:: በልቦቻችሁም መካከል መስማማትን አድርገናልናና:: በፀጋውም ወንድማማቾች ኾናችሁ:: በእሳት ጉድጓድ አፋፍም ላይ ነበራችሁ፤ ከእርስዋም አዳናችሁ:: እንደዚሁ ትመሩ ዘንድ አምላክ ለእናንተ አንቀጾቹን ያብራራል::" .......... (ሱራ አል-ኢምራን፤ 3 : 103)*

**** ቶ – ቶ ****

ዛሬ ላይ የጥንቱን ረስተን - ካንድነት ከፍቅር ከስተን
ከትዕግስት ከመቻል ሳስተን፥
በነገድ በቋንቋ ህመም በስቃይ የምንታመም
ሀይማኖት አንድነት ቀርቶ ለመለያየት ሲሰበክ
ያኔ ነው የነገር ውድቀት ምእመን ይዘን ይንበርከክ፤
የፈጣሪ ማህረቱ ቀርቦን- መዓቱ ደግሞ እንዲርቀን
እርስ በእርስ ከመጠላላት ከከንቱ ሽብር ርቀን፥
በተንኮለኛ ሴራ በክፉ ምክሩ ሳንያዝ
በቀድሞ ፍቅራችን መጥቀን በአብሮነት ሰላም... በኢስላም!
በክርስትናም ረቀን የማንጨበጥ ትንታጎች
መሰረታችን ወደ ውስጥ ግንባችንንም አርቀን
ቆፈርንና ገንብተን የቆየውን አንድነት፥
ከፖለቲከኛ ደብቀን- መተሳሰባችን ሳይነቅዝ እስኪያልፍ ክፉ ቀን፤
በመሀተባችን እንፅና ለዲናችን እንመለስ
የመለያየት፣ የመጠላላት፣ የመጠፋፋት መርዞ
በአዛን በሶላት ይፍረስ...
የፍቅር አዋይ ቅሪቱ በአባታችን ሆይ ይቀደስ!

*(♥✍ ገጣሚና ፀሐፌ-ተውኔት **አበባው መላኩ**)*

***ቶ - ቶ***

*ከአንቅልፋቸው ሲነቁ ኢ.ትኤልና አባ ኤልካኖን ወዴት እንደገቡ ግራ ገብቷቸው ሲወዛገቡ የነበሩት መርየምና አብርሃም ከዳሱ በራፍ እንደተቀመጡ በጥቂት ሜትሮች ርቀት ላይ ቅጽበታዊ ብልጭታ አዩ:: …ወዳዩት ብልጭታም ተያይዘው ሄዱ፤ ከቦታው ሲደርሱ አባ ኤልካኖንና ሼህ ከድርን አብረው ቆመው አገኟቸው::*

በተለይ የሼህ ከድር እዚህ መገኘት እያስገረማቸው ተጠጉ፡ ቀድመው የተመለከቷቸው አባ ኤልካኖን፤ "ልጆች ደህና አደራችሁ?" አሏቸው የጥዋት ፈገግታ እየለገሷቸው፤

"ደህና እግዚአብሔር ይመስገን፤" አለ አብርሃም፡

"ሁሉም ዲየግ ነው እንግዲያው፤" አሉ ሼህ ከድር፡

"እንኳን ደስ አላችሁ።" አሉ አባ ኤልካኖን እየሳቁ፡ "ጓደኛችሁ ፅዮንን የአሁኑ ‹ኤቶዮጵ› የድሮው ‹ኢትኤል› የአጋንንት መንጋዎችን በአምላከ ፍቃድ ድል ነስቶ ነጻ አውጥቷታል::"

አብርሃምና መርየም በደስታ ተሞልተው ተቃቀፉ::

"አዎ አልሃምዱሊላህ! የሸይጣን ወጥመድ ተበጣጠሷል::" አሉ ሼህ ከድር፡ አከለውም… "እንግዲህ የነፅዮን ድል አስደስቶናል አሁን ደግሞ የእናንተን ደስታ የምናይበት ጊዜ ላይ ደርሰናል::" ሲሉ፤ መርየምና አብርሃም ግራ በመጋባት ውስጥ ሆነው እርስበርስ ተያዩ፤

ከዚያም አባ ኤልካኖ መናገር ጀመሩ፤ "አንተም ልጄ አብርሃም መጀመሪያ ያገኘሁ ቀን ስለ መርየም ስጠይቅህ ‹‹ለምን ይሆን?›› ብለህ ስትጨነቅ ነበር። አንቺም ‹‹ቤተሰቦቼና ሙስሊም ጓደኞቼ ምን ይሉኛል?›› ብለሽ በስጋትና በጭንቀት ይሄንን ግንኙነትሽን እያስኬድሽ እንደሆነ እናውቃለን። ዛሬ ግን እኛ የምንነግራችሁ እውነት አለና ስሙን።" አሉና ወደ ሼህ ከድር ዞሩ፡

ሼህ ከድርም ተራቸውን መናገር ጀመሩ፡ "አዎ አባ ኤልካኖን እውነት ብለዋል፤ በእናንተ መካከል የተፈጠረው ቁርኝት ፍቅር ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ምክንያቱም የተጣመራችሁት ‹‹ገንዘብን ብላችሁ ነው›› እንዳይባል ሁለታችሁም ገና ሃብት ያላፈራችሁ ተማሪዎች ናችሁ። ‹‹ስጋዊ ፍላጎትን ብላችሁ›› እንዳልሆነም፤ እስካሁን ሳትነካኩ፡ መዋደዳችሁ፡ ምስክር ነው:: ‹‹ለታይታ ነው›› እንዳይባልም፡ ስትገናኙ በድብቅ ነው፡ ‹‹በመላመድና በተመሳሳይ አስተሳሰብ በተፈጠረ ህብረት ነው አብራችሁ የሆናችሁት›› እንዳይባል ሁለታችሁም ሃይማኖት ከሚለያይ ቤተሰብ ተወልዳችሁ አስተዳደጋችሁም ለየቅል ነው። ስለዚህ እናንተ መሃል

የተፈጠረው የአል-ሙሂቡ የተሰጠ እውነተኛ ፍቅር፤ የአል-ወልዩ ወዳጅነት፣ የአል-ወዱዱ መዋደድ የሆነ ስጦታ ነው:: ለዚህም በእናንተ ግንኙነት ላይ ምንም ፍርሃት ሊኖርባችሁ አይገባም:: ሁለታቹ የሃገራችንን ሙስሊም እና ክርስቲያን ህዝብ ፍቅር ትወክላላችሁ:: የፍቅራችሁን ቁርኝት ጋብቻ የፈቀድኩት እኔ ወይም የወሎ ህዝብ ሳይሆን ራሱ የፍቅር አምላክ የሆነው ጀሊሉ ነው:: በሱረቱል ማዒዳህ ምዕ. 5 ቁ. 5 እንዲህ ይላልና…
*"ዛሬ መልካሞች ሁሉ ለናንተ ተፈቀዱ:: የእነዚያም መጽሐፍት የተሰጣቸው ሰዎች (የኦሪትና የወንጌል መፅሐፍትን የያዙና የሚከተሉ ክርስቲያኖችና አይሁዶች) ያረዱት ምግብም ለእናንተ የተፈቀደ ነው:: (እናንተ ያረዳችሁት) ምግባችሁም ለእነርሱ የተፈቀደ ነው:: ከምእመናት ጨዋዎችም ከእነዚያ ከእናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡት (ክርስቲያኖችና አይሁዶች) ሴቶች ጨዋዎቹም፤ ዝሙተኞች እና የምስጢር ወዳጅነት ሳትመሰርቱ በጨዋ ወግ ኾናችሁ መህሮቻቸውን ከሰጣችኋቸው በኋላ (ሊታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው):: (ካገባ በኋላ ግን) ከእምነትም የሚመለስ ሰው በእርግጥ ሥራው ተበላሸ:: በመጨረሻም ቀን እርሱ ከከሳሪዎቹ ነው::"* ይላል:: በእርግጥ ቃሉ ጥምረትን የሚፈቅደው ሙስሊም ወንድ ከክርስቲያን ሴት ጋር ቢሆንም ለፍቅር ነውና አንተም በሃይማኖቷ ጣልቃ ሳትገባ እየደገፍካት፣ አንቺም በሃይማኖቱ ጣልቃ ሳትገቢ እየደገፍሽው አብራችሁ በጋብቻ መተሳሰር ትችላላችሁና ዛሬ ቃልንም ትገባባላችሁ::" አሉ ሼህ ከድር፤ አባ ኤልካናም ቀበል አድርገው "እነሆ በፍቅር አምላክ እግዚአብሔር ፊት እነሆ ዛሬ ቃል ትገባባላችሁ። በሉ አንተም የእሷን፣ አንቺም የእሱን እጅ ያዙ::" ሲሉ አብርሃምና መርየም ልባቸው እንደጉድ እየመታ፣ በደስታ፣ በመገረምና በግራ መጋባት ስሜቶች እንደተዋጡ፤ እጅ ለእጅ ተያያዙ:: ወድያውም በልብሰ ክህነት ያጌጡ ወጣቶች ከኋላቸው መጥተው ለሁለቱም ካባ አለበሷቸው፤ በዙሪያቸውም ቁጤማ ጎዘጎዙ፤ ልዩ ማዕዛ ያለው እጣን አካባቢውን አወደው::… እነሆም አባ ኤልካኖ ቅዱስ ቁርዓን ይዘው ከመርየም ፊት ቆሙ፣ ሼህ ከድር ደግሞ መፅሐፍ ቅዱስ ይዘው ከአብርሃም ፊት ቆሙ። "ዛሬ ላትለያዩ ቃል ትገባባላችሁ፣ በተክሊል ትዋባላችሁ፣ ኒካም ታስራላችሁ። እኛም እንደ ፈጣሪ ፍቃድ ከቤተሰቦቻችሁ ዘንድ እንደ ሽማግሌ ሆነን ሄደን የሰርጋችሁን ነገር እንደምናቃና ቃላችንን እንሰጣችኋላን:: እውነተኛ ቃል ኪዳንም በቀለበት ጣት ሳይሆን በልቦናችሁ ላይ የሚጠልቅ የከበረ እንቁ ነው፤ ለዚያ ማሳያ የሆኑ ቀለበቶችን ግን አዘጋጅተንላችኋል:: አንደኛው ትንሽ የመስቀል ምልክት የተቀረጸበት መርየም በአብርሃም ጣት ላይ የምታጠልቀው ሲሆን ሁለተኛው የትንሽ ጨረቃና ኮከብ ምልክት የተቀረጸበት ደግሞ አብርሃም በመርየም ጣት ላይ

የሚያጠልቅላት ይሆናል፡፡ እጆቻችሁን በእነዚህ ቅዱስ መጽሐፍቶች ላይ ጭናችሁ፤ የምንላችሁን በሉ።" አሏቸው፤ በቅድሚያ ሼህ ከድር የሚሉትን አብርሃም እየደገመ አለ፡፡

"እኔ አብርሃም ገ/ኪዳን፣ ከጎኔ የቆመችውን መርየም ኑርሑሴንን፤ ለቅዱሱ ፍቅር ዋጋ ስል አብሪያት እስከ ህይወቴ ፍጻሜ ልቆይ፤ በህመሟ፣ በችግሯም ይሁን በእርጅናዋ ወቅት በወረት ተሞልቼ ላልርቃት፤እግዚአብሔር እሷን ስለሰጠኝ ከማመስገንና እሷን ለማስደሰት ከመሞከር ውጪ ላላማርና ላልጨቃጨቃት፣ ላዳምጣትና ሃሳቧን ልረዳት በፍቅርና መተሳሰብ አብሪያት ልሆን በእግዚአብሔር ፊት ቃል እገባለሁኝ፡፡" አለና ቀለበቱን አጠለቀላት፡፡

መርየምም አባ ኤልካኖን ያስባሏትን ተመሳሳይ ቃላትን፣ ደግማ፣ "በአላህ ፊት ቃል እገባለሁኝ፤" አለችና በተራዋ ቀለበቱን አጠለቀችለት፡፡ ከዚያም ሁለቱ ጥንዶች ተቃቀፉ፡፡ ልክ በዚህች ቅፅበት የቤተ-ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ከበሮዎችን እየመቱ፤ በእልልታና በጭብጨባ ገና በጥዋት ብርድ የተፈጸመውን የቀለበት ስነ-ስርዓት ሞቅ አድርገው ካደማመቁት ኋላ፣ አባ ኤልካኖን የእጅ ምልክት ሲያሳዮቸው ሁሉም ዝም አሉ፡፡

አባ ኤልካኖን መናገር ጀመሩ፡፡

"አሁንም ስሙኝ የዘመኑ ወጣት በፍቅር ተጣማሪዎች ሆይ! ልምከራችሁ፣ ፍቅር እስር ቤት አይደለም። ፍቅር በኃላፊነትና ግዴታ በሁለት እጆች ላይ የሚቆለፍ ካቴናም አይደለም። ፍቅር ማለት "ካጣሁሽ ሞቼ እገኛለሁኝ!" ብለው የሚያስፈራሩበት የጥገኝነት ኑሮም አይደለም። ፍቅር የውዴታ ግዴታም አይደለም። ፍቅር ማለት ነፃነት ነው። የፍቅር ምንጩ እግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔር ፀጋ ደግሞ ሁሉን ያካበበና ሰፊ እንጂ ጠባብ እስር ቤት አይደለም። አፍቃሪ ሰው የራሱን ፍላጎትና ጥቅም ረግጦ ለሚወደው ሰው ደስታና የተሻለ ህይወት እንዲኖር መስዋዕትነት ይከፍላል። ይህም መስዋዕትነት ከሚወደው ሰው ሊያራርቀው የሚችል ደረጃ ይደርሳል። አንድ የእውነት አፍቃሪ ወንድ፤ የፍቅር አጋሩ ለተሻለ የትምህርት ዕድል፣ ለተሻለ የሃይማኖት ብልፅግና ወይም ግቧን የምታሳካበት ጥሩ አጋጣሚ አግኝታ ወደሌላ ሃገር መሄድ ካለባት "አይሆንም... ስለምትናፍቂኝ እዚሁ ቅሪ!" ብሎ የሙጥኝ አይልም። አሁንም እደግመዋለሁኝ ፍቅር ነፃነት ነው። 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ምዕራፍ 13:4 ላይ፤ *"ፍቅር ይታገሣል፣ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፥ 5፣ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፥ 6፣ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፥ 7፣ ሁሉን ይታገሣል፣ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል፡፡"* ይላልና፣ ስለዚህም ልጅ አብርሃምና

መርየም ይህን ቃለ ኪዳን በልቦናችሁ አስፍሩ::" ብለው ንግግራቸውን በሙሉ ፈጸሙ፤ ከዚያም ሺህ ከድር ቀበል አድርገው መናገር ጀመሩ

"ፍቅር፣ መዋደድና አንድነት በአላህ ዘንድ እጹብ ድንቅ ዋጋ ነው ያለው:: የገንዘብ፣ የዘና ጥማትና ጥቅማ ጥቅሞችን የማግኘት ግዴታዎች ሳይኖሩበት ከአላህ የሙሃባ ወንዝ እየጨለፉ በሁለትና ከዚያ በላይ ሰዎች መካከል የሚመሰረት የጓደኝነት ንጹህ ፍቅር በመጨረሻው የፍርድ ቀን ከታላቅ የሙቀትና ቃጠሎ ቅጣት የሚያስጠልልና የሚጠብቅ ታላቅ ዋጋ እንዳለው ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በሀዲሳቸው ተናግረዋል::

ለዚህም በፍቅርና አንድነት የሚያምን፤ የመጣውን ሁሉ በእንግዳ ወዳጅነት የመቀበል ምሳሌነት ያለው የኛው የኢትዮጵያ የፍቅር ህዝብ ነው:: በዘመናት ሂደት አዲስ ሃይማኖት ሲመጣ ለመቀበል ያለመዳዳቱ የሚያሳየውም ህዝቡ ሃይማኖትን ለይስሙላ ያልያዘና፣ ከስመ ተከታይነት ይልቅ እምነቱ ላይ የፀና ከመሆኑ የተነሳ እውነት ይሆናል ብሎ ያሰበውን ነገር ለመመርመር የማይለግም በመሆኑ ነው:: ለዚያም ነው ይህ የኢትዮጵያ ልዩ የፍቅር ህዝብ ፈረዖኖች ያሳደዱትን ሙሳ(ዐ.ሰ) ያስጠጋው፣ ንጉስ ሳዑል ሊገለው የሚፈልገውን ነብዩ ዳውድ (ዐ.ሰ) ከጥቅጥቁ ጫካቸን አስገብቶ የደበቀው፤ አይሁዶች ከሙሴ በኋላ የሚመጣው ነብይ እንዴት ካለአባት ሊወለድ ይችላል ብለው በርካሽ ቃላት የጠሯትን፤ የሮም ንጉስ ልጇን ሊያርድ ያሳደዳትን ቅድስት ድንግል መርየም ኢሳ(ዐ.ሰ) ስትወልድ መርቀው የባረኩት፣ ለልጇም ጥላ ሆነው ያሳደጉት:: ለዚህም ነው የአረብ አላዋቂዎች (ጃሂሎች) በድንጋይ የወገሯቸውን የውዱን ነብያችንን ሙሐመድን(ዐ.ሰ) ባልደረቦች በፍቅር አይን አይተው፤ እንግድነት ተቀብለው ያስተናገዱት::… እናም የእኔና የአባ ኤልካኖም የመጨረሻ መልዕክት እንዲሆን የምንሻው ይህ የአንድነትና የፍቅር ትልቅ መንፈሳዊ ቅድስናን ያዘለ ችቦ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍ ብሎ መንደዱን እንዳያቆም ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ በትጋት እንድትሰሩ ነው:: የዓለም ተምሳሌት የሆነችው የሙሃባና የፍቅር ሃገራችን ኢትዮጵያ አሁንም ከራማ ተራራ የአል-ራህማን የምህረትና ፍቅር መገለጫ ሆና ትኖራለች::" አሉና የመጨረሻውን ምክራቸውን ጨርሰው ዘጉ:: ሲጠብቋቸው ከነበሩት አባ ኤልካኖን ጋርም ተቃቀፉ፤ እርግጥም ያሰቡት ታላቅ ራዕይ ተሳክቶላቸዋል:: ለቀጣዩ የኢትዮጵያ ትውልድም የጥበብና የፍቅር ችቦ አስረክበዋል፤ ታሪክና እውቀትን አውርሰዋል…

***….ስራቸውን ፈፅመዋል!***

ሁለቱ እምነት አባቶች፤ መቋሚያቸውን እየተደገፍ ተሰናብተው ድጋማ ላይመለሱ ከነአብርሃም በተቃራኒው አቅጣጫ ነጎዱ፡፡ አብርሃምና መርየምም፤ እጆቻቸው ሳይላቀቅ የእጮኝነት ዘመናቸውን ቀደሱት፡፡

*** ♀ – ♀ ***

ከኢትዮጵያ ቅድስት ማንነት ጋር ተያይዞ ኢትኤል በእዚህ አድካሚ ረጅም ጉዞው ውስጥ የተረዳውን ታላቅ እውነት ቢኖር በክርስትናና እስልምና መካከል ያለውን የጠለቀ ቁርኝት ነው፡፡ ይህንን አስደማሚ እውነታ ሳይከትብ ማለፍ አላስቻልህ አለውና ድጋሚ የሚወደውን የግጥም ደብተሩን አወጣ… ርዕሱንም **ተውሃዶ እና ተውሂድ** አለውና ስንኞቹን እንዲህ ደረደራቸው፡፡

### ✝ *ተውሃዶና ☪ ተውሂድ*

*✍ ተውሃዶና ተውሂድ - አሀደ ..ሁለተ - ዘውጅና ሰልስቱ*

*ምን ልዩ ቢመስል - ደንቡና ስርዓቱ፥*
*የውሃው አወራረድ - ፍቅር ወለድ ውህደቱ*
*የገሀ.. ራሀ.. ካሀ.. ዋሀ.. ላሀ.. ገፀ - በረከቱ፤*
*የሳይኛው ምንጩ የሰማየ ሰማያቱ*
*አንድ ስነ - ፍጥረት - የእግዜር የጀ ርቱዕ፤*
*የጸበል መነሻው - ስብኃተ ራህመቱ*
*ከራማ ፈሳሿ - ዜማም ዘምዛሚቱ*
*ካም ላከ መለኮት - ማሊከል ሙሊኩ*
*ረቡኒ ረቡ - ኤሎሄ ኢል አላሁ*
*ውስጡ ተመሳሳይ - ቢለያይም መልኩ*
*ድሮ ገና ድሮ… ከገዳ ከ‹ጋዱ› - ኩዋቂ ነው እውቀቱ፤*
*ከገዳም ቡራኬ - ድርሳነ ትምህርቱ፥*
*ከግዕዙ ብራና እስከ ኪታብ ርስቱ*
*የወረደ ራሁዕይ - ሚስጥረ ፍጥረቱ፤*
*ከአሊፈል አልፋው - አላፊ ትንቢቱ*
*ኦ ሜጋውም ግሩም - ሀያው ነው የህዋዉ*
*አንደ ወል ቤት ወሊይ - ቅዱሳን አባቱ*
*መነኩሴና ሼሁ - የገቡት ውል ገፁ፥*
*ዘልቀው ለተረዱት… ለተሸለሙቱ*
*ተውሃዶና ተውሂድ!*
*የእምነት መሰረቱ - አንድ ነው እውነቱ!!*

*** ♀ – ♀ ***

አዲስ አበባ እንደ ደረሱ ፅዮንን ይዞ ወደቤተሰቡ የመኖሪያ ቅጥር ግቢ ነበር ያመራው:: እንደደረሰም የግቢውን በር ማንኳኳት ጀመረ:: ለረጅም ደቂቃዎች ግቢውን በሃይል ሲያንኳኳ ከቆየ በኋላ ወ/ሮ እመቤት መጥተው በሩን ከፈቱት:: በሩ ላይ የቆመው ልጃቸው እንደሆነ ሲያዩ በታላቅ ደስታ ተሞልተው ሽጉጥ አድርገው አቅፈውት፤ ለረጅም ሰአት አለቀሱ:: መኪናው ውስጥ ከኢትኤል ከንድ ደገፍ ብላ ብትተኛም፤ ድካሙ በቅጡ ያለቀቃት ፅዮን የግቢውን የበር አውታር ተደግፋ ቆማለች፤ የኢትኤል እናት ወ/ሮ እመቤት ልጃቸውን ከእቅፋቸው አወጡና፤ እንባ ባደፈረሰው አይናቸው አይኖቹን እያዩ፤ ‹‹መጣህልኝ ልጄ!›› አሉት:: ‹‹እኔማ ትተኸኝ የሄድክ መስሎኝ፤ ነገር ዓለሙ ዞሮብኝ ነበር:: አንተን ካጣው፤ መኖሬ ምኑ ላይ ሆኖ ልጄ!›› አሉት:: ኢትኤል የእናቱን እንባ ሲያይ ቢከፋውም፤ የመጣበትን አላማ ላለመርሳት፤ ቆፍጠን አለና፤ ‹‹ፅዮኔ ሰላም አትባልም እማ?›› አላቸው:: ወ/ሮ እመቤት፤ ሲያይዋት ድንግጥ አሉና፤ እልህ እየተናነቃቸው፤ ፅዮንን እንደነገሩ ጨበጧት:: ‹‹አባስ ቤት አለ?›› ጠየቀ ኢትኤል

«አዎ አለ»፤ ብለውት እጁን ይዘው ወደ ውስጥ ሲዘልቁ፤ ኢትኤልም በግራ እጁ የፅዮን እጅ ጨብጦ፤ ይዟት ገባ:: ሳአሌ.....ሳአሌ እልልልልል.. ልጃችን መጥቷል እያሉ፤ ከሰገነቱ ጋረ እንደደረሱ፤ አቶ ሳአል ካቦርታቸው ላይ የደረቡትን ኩታ አፈፍ አድርገው ከሳሎን ወጡና፤ ልጃቸውን በፈገግታ እየተቀበሉ፤ ወደ ደረታቸው አስጠግተው አቀፉት:: ወዲያው ግን ከአጠገቡ ያለችው ሴት ፅዮን መሆኗን ሲያስተውሉ፤ ፊታቸው በአንዴ ተቀያየረ፤ "ምነው አባ ፊትህ ተለዋወጠሳ?... ያቸው ከልጅነት ጀምሮ የምታውቃት፤ አብሬያት እንዳልጫወት የምትከለክለኝ፤ አባቷ ላይ በስውር መተት አሰርተህ ያጎሳቆልካት ጓደኛዬ ፅዮን እኮ ናት::" የአቶ ሳአል ፊት በንዴት ደም ለበሰ፤ ‹‹ተው ልጄ እንደዚህ የሚዋጉ ቃላቶችን አትሰንዝር›› አሉ ወ/ሮ እመቤት በጭንቅ እየተወጠሩ.. እውነቱን መናገሬ ሊገርማቹ አይገባም፤ ይልቅስ በስውር የተበተባችሁት የጥንቆላ ወጥመድ፤ በእምነት ሰይፍ መበጣጠሱን እወቁት:: ይልቅ ከአሁን ሰአት ጀምሮ ይህ ሴራና የባእድ አምላኮ ከእናንተ እንድታርቁ ልነግራችሁ ነው የመጣሁት:: ህያው የሆነ አምላክ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና፤ ከርሱ ለምኑ:: ይህን ከንቱ፡ ከሞት ወዲያ፤ የማይዘልቅን ጉዞ ግን ታቆማላችሁ! ስሙኝ! ያሳደፋችሁትን የቤቱን ክብር ወደቀድሞ መልሱ:: አሁኑኑ ዘንዶውን ግደሉ:: በሀሳቤ የማትስማሙ ከሆነ ግን፤ ከአሁን በኋላ ከእናንተ ጋር ስለማልተባበር፤ ልጅነቴን እሽራለሁኝ::

.... አቶ ሳአል ግን ልባቸው ደንድኖ፤ ለመሸነፍ አሻፈረኝ እያሉ ቆመው እንዳሉ ለአመታት ሲቀለብ የከረመው ዘንዶ እነሆ ድንገት ከተፍ ብሎ በአቶ ሳአል

ሰውነት ላይ ተጠመጠመ፤ ወ/ሮ ቤዛዊት ባሉበት ደንዝዘው ቀሩ፤ ከቤታቸው ደጃፍ ሮጠው ከሰው እርዳታ እንዳይማፀኑ፤ እግራቸው ተሳስሮ አላራምድ አላቸው፤ ባሉበት አምርረው ጮኹ፤ መንደሩን አናወጡት፡፡ አቶ ሳአል ላይ የተጠመጠመው ዘንዶ፤ የሰውነት አካላቸውን ይበልጥ እየጨመቀ ትንፋሽ አሳጣቸው፡፡ ኢትኤል፤ ይህን ባየ ጊዜ ህይወታቸውን ለማትረፍ መሳሪያ ፍለጋ ተራወጠ፡፡ ከዘንዶው ኮብራ ክፍል አጠገብም ለእሱ ለሚታረዱ በጎች አጥንት መከትከቻ ካራ ተቀምጦ ስለነበር በፍጥነት አንስቶ መጣና ማጅራቱን በሃይል ወጋው፡፡ የቆሰለው ዘንዶው ‹ኮብራ›ም ቀስ በቀስ ከአባቱ ሰውነት ተላቀቀ፡፡ ጭራውን እንደ እንዝርት እያሾረ፤ተምዘግዝጎ ወረደና በድንጋጤና ፍርሀት ውስጥ ሆና ወደቆመችው ፅዮን መሳብ ጀምረ፡፡ ይህንን ያስተዋለው ኢትኤል፤ ካራውን ድጋሚ ወደ ዘንዶው ቢሰነዝር፤ በበረንዳው የመቋምያ ምሰሶ ታጥፎ ዞረና ለጥቂት አመለጠው፡፡ ወደሷ እየተመዘዘ ያለውን ዘንዶ የተመለከተችው ፅዮን በበኩሏ ራሷን የምትከላከልበትን መሳርያ ለማግኘት ዙሪያዋን አማተረች፡፡ ባቅራቢያዋ ካለው የአትክልት ስፍራ የተቀመጠን፣ የአትክልት መኮትኮቻ አይታ፤ ከማንሳቷ በፊት ግን ዘንዶው ቀድሞ እግሯ ስር ደረሰ፡፡

ዘንዶው ተሽከርክሮ ሊጠመጠምባት ሲል ግን አባቷ ያሳደገው ውሻ አላዛር፣ ከየት መጣ ሳይባል ዘሎ ዘንዶው ላይ ተከመረበት፡፡ በዚያው ቅፅበት ኢትኤል ደርሶ ካራውን የዘንዶው ጀርባ ላይ ሰነገው፡፡ ፅዮንም ተንደርድራ መኮትኮቻውን አመጣችና ግንባሩ ላይ ሰካችበት፡፡ የተዳከመው ዘንዶ እየተውተረተረ ሳለ የወ/ሮ ቤዛዊትን የይድረሱልኝን ጩኸት የሰሙ ሰፈርተኛና መንገደኞች ፤ተደፍሮ ወደማያውቀው ግቢ ተከታትለው ዘለቁና ባገኙት ነገር ሁሉ እየተፈራረቁ ስኮናውን ቀጥቅጠው ዘንዶውን ገደሉት፡፡ ኢትኤል፣ ፅዮንና እናቱ እመቤት አቶ ሳዖልን ይዘው ወደ ሆስፒታል ሄዱ፡፡

*** ዖ – ዖ ***

*አቶ ሳኦል ከመታፈንና የደረት አጥንቶቻቸው ላይ ከደረሰባቸው መቀጥቀጥ በስተቀር የከፋ ጉዳት እንዳልደረሰባቸው ሐኪሞቹ ሲነግሯቸው ወ/ሮ እመቤት ታላቅ የሆነ እፎይታ ነበር የተሰማቸው፡፡ ሃብታምነትን በአቋራጭ ለማግኘት ብለው የሄዱት የተሳሳተ መንገድ ልጃቸውና ባለቤታቸውን እስከማጣት የሚደርስ ዋጋ እንደሚያስከፍላቸው አልተረዱም ነበር፡፡*

*አቶ ሳኦል ከተኙበት ክፍል ሲወጡ ኢትኤልና ፅዮንን ከአስታማሚዎች መጠበቂያ አግዳሚ ወንበር ላይ ትቅፍቅፍ ብለው ቁጭ ብለው ተመለከቷቸው፡፡ ልባቸው በሃዘን ተነካ፣ እስከ ዛሬ ድረስ አላምንም ብለው*

*ሲታገሉት የነበረው፤ የእነዚህን ሁለት ልጆች በኢድሜና በፈተና ያልወደቀ አብሮነት አሸንፋቸው:: ተንደርድረው ሄደው ከፅዮን እግር ስር ተንበረከኩ…*

“ማሪኝ ልጄ ማሪኝ… አንቺንም ቤተሰብሽንም የበደልኩትን ሁሉ ይቅር በይኝ፤ ይሄ የጨለማ መንገድ አስቶኝ እንጂ መሬቱስ ለሁላችንም በቂ ነበር:: አሁንም ይቅርታሽን ብቻ ስጪኝ እንጂ ሁሉን ነገር አስተካክላለሁኝ::” እያሉም ተማጸኗት፤

ፅዮን ከእግሯ ስር የተንበረከኩትን ወ/ሮ እመቤት ደግፋ አነሳቻቸው:: ኢትኤል ሁለቱን በሕይወቱ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸውን ሴቶች አንድ ላይ አቀፋቸው… የደስታ እንባ እያፈሰሰ ነበር::

*** ቶ – ቶ ***

ፐ/ር እሴና ፐ/ር አፅበሐ ለነፃነት ክብር፣ በጥቁር አንበሳ ብርታት፣ ጥቁር ንጉስ፡ ጥቁር ኢትዮጵያዊ ጀግኖችን እየመራ ታሪክ የሰራባትን ስም ባዘለችው አደዋ ሆቴል አድረው፤ ወደ ራማ ከተማ የሚወስደውን የኮረኮንች መንገድ በማለዳ ነበር የጀመሩት። ወደ ከተማዋ በተጠጉ ቁጥር ነፋሻው አየርና የአካባቢውን ለምነት እየጨመረ መምጣቱን የታዘቡት ፐ/ር እሴ ወደ ፐ/ር አፅበሐ ዞረው፤

"በጣም ለም ነች እንዴ ራማ ከተማ?" አሏቸው፤

"በጣም እንጂ… ከሁሉም የትግራይ አካባቢዎች በላይ ለም አፈር ያለባት ከተማ ስትሆን አብዛኛው የክልሉ የፍራፍሬና አትክልት ፍጆታም ከዚህች ከራማ ከተማ የሚመረት ነው።" አሉ ፐ/ር አፅበሐ፤

"ታዲያ ለምንድነው ቢያንስ መንገዱ አስፓልት ያልሆነው?" አሉ ፐ/ር እሴ ከመኪናው ጋር አብረው እየተንገጫገጩ፤

"ወይ አንተ አስፓልት ትላለህ፤ ይሄ መንገድ በሙሉ በደርግ፣ በሻቢያና ወያኔዎች መካከል በተደረጉ ተደጋጋሚ ጦርነቶች ፤ ከዚያም በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት በተቀበሩ ፈንጂዎች ተሞልቶ ለማለፍ ራሱ የሚያስጋ ነበር። በአጠቃላይ እዚህ አካባቢ እርስ በርሳችን ስንፋጅ የፈሰሰው የኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ደም ቀላል እንዳይመስልህ። ይሄ መነሻውን የረሳ ስርዓት ጥቂት የቀን ጅቦችንና ቤተሰቦቻቸውን በኛ ትግሬዎች ስም ቦርጫቸውን እንዲወጥሩና ውስኪ እንዲራጩ ከማድረግ ባሻገር የድሃውን የትግራይ ህዝብ ውሃ፣ መንገድና መብራት የመሳሰሉትን መሰረተ ልማቶች ለማዳረስ እንኳን የረባ ስራ አልሰራም::" አሉ ፐ/ር አፅበሐ በትካዜ

ተውጠው። ፕ/ር እሴ፤ የፕ/ር አፅበሐ ስሜት ሲለዋወጥ ስላስተዋሉ ሌላ ጥያቄ አላከሉም ነበር።

በአጭር ጊዜ ውስጥ መድረስ ቢቻልም በመንገዱ አለመመቻቸት ምክንያት ጉዟቸው ትንሽ ተጓቶ ነበር። በስተመጨረሻ 8000 ገደማ ኗሪዎች ያሏት፣ ከባህር ጠለል በላይ 1400 ሜትር ከፍታ ላይ በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል ላይ የምትገኝ፤ አምባዋ ራማ ከተማ ሲደርሱ ልዩ ሰላም ነበር የተሰማቸው።

"ራማ ከተማ እንደገባሁኝ በቅድሚያ ማየት ያለብኝ ቦታ ይኖር ይሆን እንዴ?" አሉ፤ ፕ/ር አፅበሐን ፈገግ ብለው እያዩ፤

"ትልቁ የመስኖ ስራ፣ በቅርቡ የተጀመረው የሶላር ሲስተም የኤሌክትሪክ ፕሮጀክት... እምም... ብቻ ብዙ ማየት የሚችሉት ቦታ አለ፡፡ በተለይ ግን የቆር ነብር ሚካኤል ቤተ-ክርስቲያንን ማየት አለብህ፣" አሉ ፕ/ር አፅበሐ፣ "ነብር" የሚለው ቃል "ትግረ" (Tiger) ለሚለው ቃል ተተኪ መሆኑን የሚያውቁት ፕ/ር እሴ "የኢትዮጵያ ጠላቶች በመጡ ቁጥር ቀድመው የሚወሩት ይህንን አካባቢ ስለሆነ ለሃገራቸው ቅድሚያ መስዋዕትነት ከፍለው ነፃ የሚያወጡ አግዓዚ ትግራዋዮች እንደ ነብር ከቋጥኝ ቋጥኝ እየተፈናጠጡ ተዋግተው፤ በጀግንነት ማለፋቸውን የሚያሳይ መስሎ ተሰማቸው። ቆር ነብር ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ደርሰው ከተሳለሙ በኋላ ቤተ-ክርስቲያኑን ከመንብኖታቸው በፊት እረፍት ለማድረግ ተስማሙና ከቅጥር ግቢው በሚገኝ ውብ የአትክልት ስፍራ ላይ አረፍ አሉ።

"ይህን ቦታ ከዚህ በፊት አይተሃል?" አሏቸው ፕ/ር አፅበሐን እየተመለከቷቸው።

"አዎ በጣት ለሚቆጠሩ ጊዜያት መጥቻለሁኝ፤... እዚህ ስፍራ በመጣሁኝ ቁጥር ግን ልቤን ልዩ የሆነ ሰላም የሚሰጥ ሀሴት ነው የሚሰማኝ።" አሉና ፕ/ር አፅበሐ አከለውም "እነዚያ ግዙፍ ተራሮች ይታዩሃል?" አሉ እጃቸውን ወደ ሰሜን አቅጣጫ እየሰበቁ፤ ፕ/ር እሴ የእጃቸውን አቅጣጫ ተከትለው ሲመለከቱ እንደ ግዙፍ ከቡር ዘበኞች ኢትዮጵያን ከበው የቆሙ የተራራ ሰንሰለቶችን አስተዋሉ።

"እነዚህን ተራሮች ላይ ሁሌም ሁለት ፅሑፎች ትዝ ይሉኛል" አሉና ፕ/ር አፅበሐ ሁለት አውሮፓዊ የታሪክ ፀሐፊዎች ስለነዚህ ተራሮች የሰጡትን ምስክርነት በእንግሊዘኛው ማንበብ ጀመሩ፣ Balthasar Telles (Tellez 1710: 31) የተባለ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ የፖርቱጋል ታሪክ ጸሐፊ እነዚህን ተራሮች ሲገልፅ፣

"Some of these mountains, which the natives call **Ambas**, stand by themselves apart from all others, are prodigious high, as it were in an impregnable fortress. . . ."(እነዚህ የመንደሩ ሀገር በቀል ኗሪዎች አምባዎች ብለው የሚጠሯቸው ተራራዎች ለየት ብለው፣ በታላቅ ቁመት ተመዘው፣ የማይደፈሩ የጦር ምሽጎች ይመስላሉ!)`` ይላቸዋል:: የአባይን ምንጭ ለማግኘት በሚል የውሸት ምክንያት ኢትዮጵያ መጥቶ ‹‹መፅሐፈ ሄኖክን›› ጨምሮ ብዙ የብራና መጽሐፍትን ከኢትዮጵያ ሰርቆ የሄደው እንግሊዛዊው አሳሽ (ሌባ) ጀምስ ብሩስ ስለ እነዚህ ተራሮች ግን መዋሸት አልተቻለውም ነበር:: በታሪክ መዝገቡም እንዲህ ብሎ አስፍሯል:: *"It is not the extreme height of the mountains in Abyssinia that occasion's surprise, but the number of them, and the extraordinary forms which they present to the eye. Some of them Are flat, thin and square, in the shape of a hearth-stone, or slab, that scarce would seem to have base sufficient to resist the action of the winds. Some are like pyramids, others like obelisks or prisms, and some, the most extraordinary of all the rest, pyramids pitched upon their points, with the base uppermost, which, if it was possible, as it is not, they could have been so formed in the beginning, would be strong objections to our received ideas of gravity"*.(በአቢሲኒያ የሚገኙትን ተራሮች አስገራሚ የሚያደርጋቸው የቁመታቸው መርዘም ብቻ ሳይሆን መብዛታቸውና ለአይን እንግዳ የሆኑ ቅርጾችን መያዛቸው ነው:: አንዳንዶቹ ጠፍጣፎች፣ ሌሎቹ ሾጣጣና 4 ማዕዘን ቅርፅ ያላቸው ሲሆኑ፣ ምድጃና ቆራጣ ድንጋዮችን የሚመስሉም አሉ:: የንፋስን ኃይል የሚቋቋሙ እንደ ፒራሚድ እና ሌሎች እንደ ሳጥንና እንደ ሃውልትም ይመስላሉ፤ እጅግ ትንግርትን የሚፈጥሩት እንደ ሳጥንና... ▼ ያላቸው እና ደግሞ ተገልብጠው በጫፋቸው የቆሙ የፒራሚድ ቅርፅ ▼ ያላቸው እና የመሬት ስበት ህግን የሚጣረሱት ናቸው::)" ብሎ ዘግቦታል፤

"በጣም ይገርማል!" አሉ ፕ/ር እሴ::

"እነዚህን ተራሮች ስመለከት በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ ተራራማ ሃገር እያለ የሚጠቅሰው ኢትዮጵያን እንደሆነ አንዳች ጥርጣሬ አያድርብኝም:: ከሩቅ ሆኜ ሳማትራቸውም በዚህና በወንድሞቻችን ኤርትራ ሃገር መካከል ያለችውን 7 ኪ.ሜ ተራምጄ አልፌ ከስራቸው ቆሜ የማያቸው

ቀን እናፍቃለሁኝ፤ መቼ ይሆን በቤተ-ጊዮርጊስ፣ በቤተ-ፅዮንና በቤተ-ገብርኤል ደብሮች ስር ቆሜ የምፀልየው ብዬም እመኛለሁኝ፡፡ አስመራም ናፍቃኛለች፡፡" አሉ ፕ/ር አፀበሐ በትካዜ እንደተዋጡ፤ ድንገት ግን ስልካቸው ጠራና ከሃሳባቸው አነቃቸው፡፡

"ይቅርታ ፕ/ር ይህቺን ስልክ ማናገር አለብኝ" አሉና ፕ/ር አፀበሐ ስልኩን ለማናገር ፈንጠር ብለው ቆሙ፡፡፡..ፕ/ር እሴ አሁን ፕ/ር አፀበሐ የነገሯቸውን እያሰላሰሉ ቁጭ ብለዋል... ንፁህ አየር እየተንከላወሰ መጥቶ አፍንጫቸውን ያውደው ጀመር፤ አይኖችን የሚስብ አረንጓዴ 3D ሸራ ላይ በሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የተሳሉ የሚመስሉ አበቦች ጠላቸውን ያንጠባጥባሉ። በዚህ መመሰጥ ውስጥ ሳሉ... አንድ ጉንዳን እግራቸውን ንክስ አደረጋቸው፤ ዝቅ ብለው ሲመለከቱ እግራቸው ረጅም የጉንዳኖችን መንገድ ዘግቶ እንደገደባቸውና ነካሽ ጉንዳኑም ይህ ተግባራቸው ያናደደው የጉንዳን ወታደር መሆኑን ተረዱ፡፡ ጉንዳኑን ጀርባውን ይዘው ከቆዳቸው አላቀቁት፡፡ የጉንዳኖቹን የሰልፍ ጉዞ ስላስገረማቸው ተከትለውት ተጓዙ፡፡ ልክ ኩልል ብሎ እንደሚፈስ ወንዝ ጉንዳኖቹም በስርዓት ነበር የሚተሙት፡፡ በአይናቸው የፍሰታቸውን መስመር ተከትለው ሲያዩ አንድ የሚገርም ነገር ተመለከቱ፡፡ ይህም የእነዚህ ጉንዳኖች የጉዞ መስመር ከአካባቢው ካለ ጅረትም ሳይገደብ መቀጠሉ ነበር፡፡ ነገሩ ትንግርት ሆኖባቸው ሚስጥሩን ለማወቅ ወደ ጅረቱ አመሩ፡፡ ከጅረቱ አጠገብ ሲደርሱም ጉንዳኖቹ ወራጅ ውሃውን ለመሻገር የመረጡት ሰፊው ጅረት ግራና ቀኝ ላይ ያሉ አለቶች የፈጠሩትን ጠባብ መሿለኪያ እንደሆነ አስተዋሉ፡፡ ያም ሆኖ ግን መሿለኪያው ስርም የውሃውን ፍሰት ያስቀጠለ ክፍተት እንዳለ አዩና፤ ጉንዳኖቹ ይህንን ክፍተት እንዴት እንዳለፉት ለማጣራት አተኩረው ሲያዩ ነበር ፕ/ር እሴ እጅግ አስገራሚ ነገር የተመለከቱት፡፡ ይህንን ክፍተት ለማለፍ ጉንዳኖቹ ድልድይ ሰርተው ነበር፡፡ ይበልጥ አስገራሚው ነገር ደግሞ ድልድዩ በእንጨት ወይም በቅጠል ሳይሆን በራሳቸው በጉንዳኖቹ መሰራቱ ነበር፡፡ ከጅረቱ በዚህና በዚያኛው ጥግ ያሉ ሁለት አለቶች ላይ የተወሰኑ ጠብደል ጠብደል ጉንዳኖች በእግራቸው ድንጋዩን ተቆናጠው፤ የድልድዩ መሰረት ሆነው ቆመዋል፡፡ እነዚህም ጉንዳኖች፤ የሌሎችን ጉንዳኖች ወገብ ጥብቅ አድርገው ነክሰው የያዙ ሲሆን እነዚያ ጉንዳኖች ደግሞ በተራቸው ሌሎች ጉንዳኖች ይዘው የጉንዳኖች ድልድይ ሰርተዋል፡፡ ይህንን የመስዋዕት ጉንዳኖች ድልድይ ተጠቅመውም ሌሎቹ ጉንዳኖች ከአንዱ ጎን ወደ ሌላው ይሻገራሉ፡፡ ይሄ በጉንዳኖች የተሰራ ድልድይ አንድነት ምን ያህል መስዋዕትነት እንደሚያስከፍል ታላቅ ምሳሌ ነው፡፡ ለጓዶቻቸው፣ ለወገኖቻቸው ትልቅ ፍቅር ያላቸው ጀግኖች ሁሌም ሰማዕት እየሆኑ ትውልድን አሻግረዋልና..." ፕ/ር እሴ በሃሳብ ጎዳና ነጉዱ፤

"አዎ አንድነትና መተባበር ታላቅ ኃይል ነው:: አሮሞ፣ አማራ፣ ጉራጌ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ ትግሬ፣ አጋሜ፣ ኤርትራዊ ወዘተ እያልን እርስ በእርስ በብሔር ከምንበላላ፣ ደርግ፣ ኢሰፓ፣ ኤሃፓ፣ ሻዕቢያ፣ አነግ፣ ወያኔ፣ ግንቦት 7 ወዘተ እያልን በድርጅት ከምንዋጋና ቅዱሳን ተራሮቻችንን በደም ከምንበክል እጅ ለእጅ ተያይዘን ብንጓዝ የት በደረስን? እኔም እንደመጣሁት ሌሎችም በዓለም ዙሪያ ያሉ ኢትዮጵያውያንን ይህንን የመጻረርና የጥላቻ ግንብ አፍርሰው ት/ትና ልምዳቸውን ይዘው ቢመጡ ሃገራቸውንና ይህንን ምስኪን ህዝብ ምን ያህል በጠቀሙት::

አዎ እንኳንስ ተለያይተንላቸው፤ ወትሮም እኛን ለማጥቃት አርፈው የማይተኙ ጠላቶቻችንን በአንድነት ከንዳችን የምናሳፍርበት ወቅት ላይ ነው ያለነው:: በችግር ሊፈትኑን ቢጥሩ፤ እየተረዳዳን እኛ አንቸገርም:: ‹የህዝብ ቁጥር ንሯል መኖር አይቻልም› እያሉ ሊያስጨንቁን ቢጥሩ በእምነታችን ጸንተን እኛ አንጨነቅም፤ አሉባልታ እየነዙ እርስ በርሳችን ሊያጣሉን ቢጥሉ ከፍቅር ዋርካ ስር በአንድነት ስር ተጠልለን እኛ አንበተንም፤ ይህ ሁሉ አቅቷቸው በጉልበተኛ ክንድ ሊገዙን ቢመጡ በኢትዮጵያዊ ፍም ተመን እንሞታለን እንጂ ለእነሱ እጅ አንሰጥም:: አዎ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያን ለመግደል ሳይሆን ለማዳን የሚያስፈልገውን መሰዋዕትነት በሙሉ ለመከፈል ዝግጁ ነንና:: እኛ አንድ ከሆንን ከኤርትራ ጋር አንድ መሆን ብቻ ሳይሆን የጥንቲቷን ምስራቅ አፍሪካና የመንን አጠቃላ የገዛች ታላቅ ኢትዮጵያን የማንመሰርትበት ምንም ምክንያት የለም:: በአንድነት ሁሉም ይቻላል::"
ፕ/ር አፀበሐ የስልክ ንግግራቸውን ጨርሰው ተመልሰው ኖሮ ስማቸውን ሲጠሯቸው ፕ/ር እሴ መቆሚያ ከሌለው የጉንዳኖች የአብሮነት ጉዞን ከመሰለ የሃሳብ ወንዛቸው ነቁ::

*** ቶ – ቶ ***

ወ/ሮ እመቤት አቶ ሳዖል ወደ ተኙበት ክፍል ተመልሰው ገቡ:: ፅዮን ተመልሳ ከኢትኤል ላይ ደገፍ አለችና እንቅልፍ ወሰዳት፤ ኢትኤል የግጥም ደብተሩን አወጣ........ *ተጀመረ እንዳልል ቀድሞ ተጨርሷል*

*ተፈፀመ እንዳልል ሲቆረጥ ቀጥሏል፥*
*አልፋና አሜጋ ሊከፈት ሚዘጋ*
*የፍቅር ጎዳና በሁለት ሜፍ ሚላጋ፤*
*አንድም ከላይ ወርዶ ከመሬት ይፈልቃል*
*ከግራ እየተኛ በቀኝ ጎን ይነቃል፥*
*ሞተ አበቃ ሲሉት በሞት ላይ ይኖራል*
*ለተሻለ አሚሚት ዳግም ነፍስ ይዘራል::*

የመጨረሻው ግጥሙ የመጨረሻ ስንኝ መዝጊያ አራት ነጥቦች ከኢትኤል ብዕር ተንጠባጥበው አረፉ:: የሚወደውን የግጥም መፃፊያ ደብተሩን ከደነና ከጎኑ፣ ከሆስፒታሉ አግዳሚ ወንበር ላይ አስቀመጠው:: ድፍን 5 ዓመታትን የፈጀበት የጥበብ ስራው፣ የበኩር ልጁ አልቋል፣ የ'ሱ የህይወት መንገድ፣ የፍቅሩ ጥማት፣ የኑሮ ፈተናው ውጤት ግን ገና አላበቃም… ጥፋቱ አልተሻረም፣ ፍቅሩን አልገለፀምና!

"አሁን እንዴት ነሽ ፂ?… በደንብ ተነቃቃሽ?" አላት፣ ከስሩ ሽጉጥ ብላ ተኝታ የነበረችው ፅዮን ስትነቃ አስተውሎ፣

"ደህና ነኝ እ/ር ይመስገን፣ ትንሽ ብቻ የእናቴ ሁኔታ እያስጨነቀኝ ነው እንጂ፣" አለች ፅዮን የአይኖቿን ሽፋሽፍቶች አጣጥፋ ሽቅብ እያየችው፣

"ችግር የለውም ስለእርሳቸው አታስቢ፣ አሁን እናትና አባቴን እንደተሰናበትን የምናመራው እርሳቸው ጋር ነው::"

"የት ነው ያለችው?" አለች ፅዮን፣

"በኋላ እወስድሻለሁኝ፣ በቅድሚያ ግን እኔና አንቺ ምናወራው ነገር አለ::" አላት ኢትኤል እንዴት ብሎ እንደሚጀምር ግራ እየገባው፣

"ምንድነው የምንነጋገረው ነገር?" አለች ፅዮን፣ ኢትኤል ከጎኗ ተነሳና ጉልበቷ ስር በርከክ አለ… አይኑ ላይ ለመውደቅ የተዘጋጁ የእንባ ዘለላዎች ተከምረዋል፣… "በድዬሻለሁኝ ፂያ! ካንቺ ንፁህ ፍቅር ርቄ የሌላ ገላ አቅፌያለሁኝ፣ ያንን ሁሉ ንጹህ ፍቅርሽን አጉድፌዋለሁኝ::…" ብሎ ያዘጋጀውን የይቅርታ የቃላት ድርድር ከመጀመሩ ፅዮን ጣልቃ ገባችና

"ምንም ለመናገር አትፍራ… ያደረከውን ነገር በሙሉ አውቀዋለሁኝ::" አለች ፅዮን አንገቷን ወደ መሬት እንደ ደፋች፣

"እ… እንዴት አወቅሽ?" አለ ኢትኤል ግራ እየተጋባ፣

"ቢታንያ ደውላ ሁሉንም ነግራኛለች፣" ብላ ስትነግረው ኢትኤል በንዴት ወንበሩን በቡጢ ነረተና ስልኩን እየነካካ ከሆስፒታሉ ወጣ፣ ፅዮን ልታስቆመው ብትሞክርም አልቻለችም ነበር:: እንደወጣ የቢታንያ ስልክ ላይ ደወለ፣ አነሳች…

"አንቺ ቆይ ለምን ህይወቴን መበጥበጥሽን አታቆሚም!፣" አለ ኢትኤል፣

"ምን አድርጌ ነው ደግሞ ያንተን ህይወት የበጠበጥኩት… ወይስ ገና ለገና ወዳኛለች ብለህ የኔን ህይወት መበጥበጥህን መናገርህ ነው፣" አለች የአሽሙር እየሳቀች፣"አትሳሳቴ፣ አንቺ ከእኔ ጋር እልህ ነው እንጂ ፍቅር አልያዘሽም:: አሁንም ደግሜ ልንገርሽ ፍቅርን ከፈለግሽ ፍቅርን መስጠት የሚችል ማንነት

ይኑርሽ፡፡ ከብርሽን በምግብ፣ ልብስና ቁሳቁስ የምታስተመኚ ሴት አትሁኚ፡፡ አንቺ ለራስሽ ያልሰጠሽውን ከብርና ፍቅር መልከሽን አይቶ ሌላ ወንድ እንዲሰጥሽ አትጠብቂ፡፡ ወርቅም ቢሆን ከተራ አርቴፊሻል ጌጣጌጦች ዘንድ ተደርድር ከተሸጠ ዋጋው የአርቴፊሻል ጌጣጌጥ እንደሚሆን አትርሺ..."

"ምንድነው የምትለው...?"

"እሱ ቀስ ብሎ ይገባሻል፤ ለማንኛውም ከዚህ በኋላ እኔና ፅዮን መካከል እንዳትገቢ፤ እኔና እሷን ለመጣላት ከምትደከሚ የራስሽ የሆነው ሰው እንዳያመልጥሽ የሚቀርቡሽን ወንዶች ሁሉ በኪሳቸው መተመንሽን አቁሚ፡፡" አለ ኢትኤል

"ደስ የሚለኝ ግን ምን እንደሆነ ታውቃለኽ?" አለች ቢታንያ በንዴት "ያን ቀን ሴክስ ሳናደርግ ማደሬ ነው፤ መቼም ቢሆን ደግሞ እንደማታገኘኝ አወቀው!"

"ምን ማለትሽ ነው ሴክስ ሳናደርግ ማለት?... አላደረግንም እንዴ?" አላት ኢትኤል ግራ እየተጋባ፤

"ጥንብዝ ብለህ ስከረህ ልብስህን እንኳን ማውለቅ አቅቶህ ነው የተኛከው... አሁንም ቢሆን ሲያምርህ ይቀራል!..." ሳትጨርስ ስልኩ ተዘጋ፤

ኢትኤል ስልኩን ዘግቶ ሲዞር ፅዮን ከጎኑ ደርሳ ቆማ ነበር፡፡ ፊቱ በፈገግታ እንደተሞላ አቀፋት፡፡

*** ቶ – ቶ ***

ስልኩ ጆሮዋ ላይ የተጠረቀመባት ቢታንያ ውስጧ በንዴትና እልህ እየተንጨረጨረ ሞባይሏን በሃይል ወረወረችው፡፡ የተወረወረው ሞባይል በአየር ላይ እየተምዘገዘገ ሄዶ ያ... እንደ ግል ጣዖቷ የምታየው፣ ሲነካ እንኳን የሚያንገበግባት ፣ መስታወቷ ላይ አረፈ፡፡ አይኗ እያየ መስታወቷ ተሰነጣጥቆ ረገፈ፡፡ በንዴት ውስጥ ሆና ከመስታወቱ ፊት ለፊት መቀመጧን ዘንግታው ነበር፡፡ ውስጧ ግን የሃዘንና የንዴት ሳይሆን የሆነ የእፎይታና የግልግል ስሜት ነበር የተሰማት፡፡ ኢትኤል ሲመክራት እንዳልገባት ለመሆን ብትሞክርም ቃላቶቹ ግን ውስጧ ሰርስረው እየገቡ ነበር፡፡ ... ከመስታወቱ ስባሪዎች መካከል አንዱን አነሳችና ራሷን ተመለከተች፡፡ በትልቁ መስታወቷ ውስጥ ታየው የነበረው መልኳ አሁንም ከነ ሙሉ ውበቱ አለ፡፡ ትልቁ መስታወት ቢሰበርም፣ ሜካፕ ባትቀባም፣ በማስካራ ሽፋሽፍቷን ባታደምቅም፣ ሂል ጫማ ላይ ባትንጠለጠልም ቢታንያ ግን ቢታንያ ናት፤ በትልቅ መስታወትም፣ በትንሽ ሰባራ መስታወትም ቆንጆ ነች፡፡" ከራሷ ጋር በሃሳብ ያደረገችውን ምልልስ ስትጨርስ ፈገግ አለች፡፡ መናደድ ሲገባት ፈገግ ማለቷ ለራሷም ገርሟታል፡፡

*** ዩ – ዩ ***

# … ከ 2 ዓመታት በኋላ፤

እነ ኢትኤል ፅዮንን ለማስመረቅ ከተኮናተሩት መኪና ውስጥ ተቀምጠዋል፡፡ ከዘይኔና ኢትኤል በስተቀር ሁሉም የጀሮ ማዳመጫዎቻቸውን ሰክተዋል፤

♫ ታዲያ ምኑ ላይ ነው የኛ እርቆ ማሰብ?

አንድ የሆነውን ዘር ካቃተን መሰብሰብ፤.... አቤት አቤት!

እስላሙም ክርስቲያኑም- ያጣውም ያገኘውም
አንድ አድርገን ጌታ፤ አንድ አድርገን ጌታ፤..." የሚለው የሙዚቃዋ ንግስት አስቴር አወቀን ዘፈን የሚያዳምጠው ዮሴፍ ነበር፡፡

ከጎኑ የተቀመጡት አብርሃምና ናዖድ ሲሆኑ ከናዖድ ስልክ ላይ በተሰካው የጆሮ ማደመጫ አንድ አንድ ጆሮ አጥልቀው የቢኒያም ዋለን እንያያዝ የሚለውን መዝሙር በጋራ ያዳምጣሉ፤

♫ እስኪ እንያያዝ እንያያዝ ተሰጥቶናል የፅድቅ እውነት

አንዱ መንፈስ በሁሉ አድሮ ሰበሰበን ልጆቹ አድርጎ፤
ሳይኖር መሀላችን ከፍቅር ሌላ እዳ
ጠላት ከፍተት ሲያጣ መሹለኪያ ቀዳዳ፥
ህይወት በረከትም እንደ ወንዝ ሲቀዳ
ማየት እንዴት ያምራል ጥላቻ ሲመታ፡፡"

ከእነሱ ኋላ የተቀመጠው ቶላ ደግሞ የኦሮምኛ ሙዚቃ ንጉሱን አሊ ቢራ ሙዚቃ ያዳምጣል....

♫ "ረቢ ሞ ናሙማ ከን ሴራ ሜሊሴ ዋቃ ሞ፥

ነሙማ ከን ሴራ ሜሊሴ ሃቲ ቴኛ ታካ ማልቱ
አደን ኑ ባሴ ሃቲ
ቴኛ ታካ ማልቱ አደን ኑ ባሴ"
(እ/ር ነው ወይስ ሰው ማነው ህግን የጣሰው?
እ/ር ነው ወይስ ሰው ማነው ህግን የጣሰው?
እናታችን አንድ ናት ማነው የለያየን?
እናታችን አንድ ናት ምንድነው የለየን?``...)

ኢትኤል ከጎኑ የተቀመጠው ዘይኔ ሙዚቃውን አብሮ ሲዘፍን ተመለከተውና፤ "እንዴት ነው ግን የዜማና የሙዚቃ ጉዳይ በእስልምና ውስጥ ያለው ቦታ?" ብሎ ጠየቀው፤

ዘይኔም ፈገግ አለና፣ “የሐበሻው ቢላል አዛን የሚለየው እኮ የሚያምር ድምጽና ዜማ ስለነበረው ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ቁርዓን እንኳን ስንቀራ በዜማ እንድንቀራ ነው ያዘዙን፡፡ በዚያ ላይ አንሷር የሚባሉት፣ የመዲና ሰዎች ‹‹ለኛም ጨረቃ ወጣልን!›› እያሉ እየዘመሩ፣ ድቤ እየመቱ ሲቀበሏቸው ደስ አላቸው እንጂ አልተቆጡም ነበር፡፡ አንድ ሐዲሳቸው ላይም ለሰርግ የሚሄዱ ሰዎች ሙዚቀኛም ይዘው እንዲሄዱ አዘዋል፡፡ ሌላው ቢቀር በቅዱስ ቁርዓን እኮ ዳውድ (ዐ.ሰ) ወይም ዳዊት ሲዘምር ተራራዎችም አብረውት ይዘምሩ እንደነበር ይናገራል፡፡ ከሌሎቹ ዓለማት በተለየ ደግሞ ኢትዮጵያዊ እስልምና ከዜማ ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው፡፡ የዜማ ሃገር በሆነችው ኢትዮጵያ ያሉ ሙስሊሞች በድቤ የደመቀ፣ በጥልቅ ግጥሞችና ነፍስን በሚያገማሽሩ መንዙማዎች የረቀቀ፣ በወልዮች መቅቡል ዱኣ የሸቀቀ፣ በአብሮ መኖር ህብር የተዋበ፣ በመውሊድ በዓል አከብሮ በረካው የላቀ እስልምና ነው ያለን፡፡ ያም ሆኖ ግን ወደ አርካሽ ሃጢያቶች የሚመሩና ከአላህ የሚያጣሉ ግጥሞችና መልዕክቶች ያሏቸውን ሙዚቃዎች ማዳመጥ የለብንም፣ ለዚህም ደግሞ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡” አለና ዘይኔ ነገሩን በሰፊው አብራርቶ ነገረው፡፡

“እውነት ተናግረሃል ዘይንሻ!” አለ ኢትኤል “ሙዚቃ ከሰው ልጅ ጋር ያላት ቁርኝት እጅግ የላቀ ነው፡፡ ብላቴው ‹‹ሙዚቃ ህይወቴ›› ብሎ የዘፈነው ካለ ምክንያት እንዳይመስልህ፣ አበባዎች እንኳን ጥሩ ሙዚቃን ሲሰሙ ቶሎ እንደሚፈኩ ጥናቶች አሳይተዋል፡፡ ፡፡ ባይገርምህ ሰሞኑን ልብ ብዬ ሳስተውል ያኔ የአካላት አወቃቀር ‹‹አናቶሚ›› ስንማር ያየኋቸው የመካከለኛው የጆሮ ክፍል አካላት ቲምፓኒና 3ቱ አጥንቶች በራሳቸው የኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ጋር እጅግ የሚመሳሰል ቅርፅ እንዳላቸው አስተውያለሁኝ፡፡ የ‹‹ቲምፓኒ›› ከበሮ መምሰል ባንቀበል እንኳን የ‹‹ማሊዮለስን›› ማሲንቆ መምሰል፣ የ‹‹ኢንከስ››ን መለከት መምሰልና፣ የ‹‹ስቴፐልስ››ን ፅናፅል መምሰል መካድ አንችልም፡፡ ይህም የሙዚቃ መሳሪያዎችን የፈለሰፈልን ቀደምት አባታችን ኤቶዮጵ በሰው ልጆች አካላዊና መንፈሳዊ መስተጋብሮች ላይ የጠለቀ እውቀት ስለነበረው ይመስለኛል፡፡ ይህ አባታችን ኤቶዮጵም ለልጆቹ በተለያዩ የጭፈራና የዜማ ስልቶች ያወረሳቸው የሁሉም ብሔሮች ዜማዎችና ጭፈራዎች ሲወራረሱ መጥተው አሁን ላይ ደርሰዋል፡፡ በእሱ ህም ላይ የተመሰረተ የሀመር ጭፈራ የሆሜር መነሻ ቢሆን አንገረም፣ የኛን የውዳሴ ስርዓት ቀለም ቀባብተው የግሪክ ኦዲሴ ቢሉት አይገርምም፣ የእኛን የኦሮምኛ ዝላይ፣ ሶም ሶማና ዱብ ዱብ ሬጌ ብለው ቢያደምቁት፣ የጎጃም እንቅጥቅጥና ድለቃ የሂፕ ሆፕ መሰባበር ዳንስ ቢቀይሩት፣ የወላይታና የሲዳማ ዳለ ' መቀመጫ ላይ በይበልጥ ያተኮረ

ውዝዋዜ ትወርከና ዳንሶል እያሉ እንደ እንግዳ ሊያስጠኑን ቢሞክሩ ብርቅ ሆኖብን ልንገረም አይገባም:: ራሳችን ማየት ብንችል አባቶቻችን ጥለውልን ያለፉት ገና ብዙ ብዙ ያልተነኩ፣ የማይዳሰሱ ሃብቶች አሉን::" አለና ኢትኤል በረጅሙ ተነፈሰ… ሳያስበው ብዙ አውርቶ ነበር::

"እውነትህን እኮ ነው ኢታ፤ እኛ ወደ ራሳችን ችግሮች መመልከት ካልቻልን ችግራችንን መፍታት አይቻለንም:: አላህ በቁርዓኑ ‹‹ኢነላሀ ላ ዩገይሩ ማ ቢቀውሚን ሀታ ዩገይሩ ማ ቢአንፉሰሁም›› (13:11) ብሎ ‹‹የሰው ልጆች በውስጣቸው ያለውን አመለካከትና አስተሳሰብ መርምረው እስካልቀየሩ ድረስ እንደ ህዝብ ያሉበትን ሁኔታ እንደማይቀይር ይነግረናል:: ይህም የሚያሳየው እንደ ህዝብ ለውጥ ማምጣት ካለብን እያንዳንዳችን ወደ ራሳችን መመልከትና መለወጥ እንዳለብን ነው::" አለ ዘይኔ፤

"አዎ እስማማለሁኝ:: ጥሩ ጥሩ ባህሎቻችንን በወጉ ማድነቅና ማበልጸግ ይገባናል:: በአንድ ግርግዳ የተለያዩ መስጊድና ቤተ-ክርስቲያኖች ያሉን፣ ‹‹ወደ ቤት ወደ ቤት ወደ ማድቤት፤ አንድ እንጀራ ለእኛ ሌላው ለጎረቤት›› እያልን እየዘመርን መረዳዳትን ገና በልጅነት እድሜ እየተማርን የምናድግ፣ ‹‹እቴሜቴ የሎሚ ሽታ››፣ ‹‹ሆያ ሆዬ››፣ ‹‹እንቁጣጣሽ›› ወዘተ እያልን ገና ከለጋነታችን ስነ-ቃል ስንደረድር የምናድግ መሆናችን፤ ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ቆም ብለን ማስተዋልና ባህላችንን ጠብቀን ለቀጣዩ ትውልድ ማውረስ አለብን:: ጥሩ ሙዚቃና የዝማሬን ኃይል፤ በቀን ተቀን ህይወታችን መተግበርም ይገባናል:: እመነኝ ረጅም የታክሲ ሰልፍ ላይ ብትቆምም ሞባይልህን አውጣና አንዲት ጥሩ መልዕክት ያላትን መዝሙር፣ መንዙማ ወይም ዘፈን በጆሮ ማደመጫኸ አዳምጥ እስኪ… ሰልፉ ያጥርልሃል፣ ምሬትህ ይበንልሃል:: ረጅም ሰዓታትን የሚፈጅ ቀዶ ጥገናህን እስኪ በክላሲካል ሙዚቃ አጅበው፣ ስራህን ያስወበዋል፣ ድካምህን ያቀለዋል:: ከአድካሚ ስራህ ወደ ቤትህ ስትገባ ከራር ደርድር፤ የአስቤዛ ከርከር አስናድታ የጠበቀችህ ባለቤትህ በዜማው ከፊትህ ቆማ ትደንሳለች:: አዎ! በየቀኑ የህይወቱን ቅኝት እያስተካከለ በተለያዩ ዜማዎች ውስጥ የሚያስውብ ሰው የደስታ ቧንቧን ከቤቱ ደጃፍ ድረስ እንደቀጠለ ሰው ይመስላል::" አለ ኢትኤል፤

"በጣም ነው ግን የሚገርመው!" አለ ዘይኔ ቀበል አድርጎ፤

"አዎ ሙዚቃ ይገርማል!" ጨመረ ኢትኤል፤

"እሱ ብቻ አይደለም፤" አለ ዘይኔ፤… "እና ሌላ ምንድነው የገረመህ?"

"ከዚያ ጉዟችን በኋላ በጣም ተለውጠኸብኛል ወላሂ፤ የምትናገረው ነገር ሁሉ በጣም ይገርማል::" አለው ዘይኔ… ኢትኤል የአሁኑ ኤቶዮጵ ሳይመልስ

በዝምታ አንዳለ!... ከመመረቂያው አዳራሽ ሲደርሱ የተመራቂ ቤተሰቦች ለጉድ ተኮልኩለው ነበር የጠበቋቸው፡፡ ኢትኤል የዛሬ አመት እሱና ጓደኞቹም እንዲህ በክብር መመረቃቸውን ሲያስብ ፊቱ በፈገግታ ተሞላ፡፡

*** ቶ – ቶ ***

*የዳቼላን ፍርሃት በአምነት ያሸነፈችው ጽዮን ጥቁር የመመረቂያ ካባዋን ለብሳ ስትወጣ ፊቷ እንደ ፀዳል ያበራ ነበር። በስተቀኟ የቆመው ኢትኤል በወርቀ-ዘቦ ያጌጠ፣ ከጉልበቱና ከክርኖቹ በታች እንደ ዮጵ ወርቅ በሚያንጸባርቅ ሀር የተጠለፉ ዘርፎች ያሉት የሚያመር ዘመነኛ የእጅ ጥበብ ለብሷል፡፡ ከአጠገቧ በግራዋ በኩል የቆሙት እናቷ ወ/ሮ ቤዛዊትም በውድ የሃገር ልብስ ቀሚስ ተውበው ከጽዮን በላይ ፊታቸው በደስታ ፈክቶ ይታያሉ፡፡ ከጎናቸው ደግሞ ወ/ሮ እመቤት ከርሳቸው ባልተናነሰ ዘንጠው ስልክ እያናገሩ ቆመዋል፡፡ አቶ ሳዖል እንደተለመደው በሙሉ ሱፍ ሽክ ብለው አንገታቸው ላይ ባንጠለጠሉት ካሜራ አንድ በአንድ ፎቶዎችን ያነሳሉ፡፡ መርየምና ጽዮን ተቃቅፈው ፎቶ ከተነሱ በኋላ አብርሃም፣ ዘይኔ፣ ቶላ፣ ናዖድና ዮሴፍ በየተራ ለጽዮን የአበባ እቅፎችን እየሰጡ «እንኳን ደስ አለሽ» አሏት፡፡ በመሀል ግን አንድ ትንሽ ልጅ እየሮጠ መጣና ለጽዮን፣ ለኢትኤል፣ ለአብርሃም፣ ለመርየም፣ ለዘይኔ፣ ለናዖድና ለቶላ አንዳንድ ጥቅል ወረቀቶች ሰጣቸው፡፡ ከዚህ ሌላ ግን አንድ ተለቅ ያለ ጥቅል ለኢትኤል ሰጥቶት እየሮጠ ሄደ፡፡ ሁሉም በየተራ የተሰጣቸውን ጥቅል ፈቱት፣*

***ራማ*** ------- ***የኢትዮጵያዊያን የከፍታ ማህበር (ኤቶዮጵ)***
***ዮቶር*** -------*የታሪክ ምርምርና ታላቅ ስብዕና ማሰልጠኛ ተቋም (አብርሃም)*
***ገዳ*** ----------*የሃገር በቀል እምነቶች ምርምርና ማበልጸጊያ (ቶላ)*
***መርየም***—— *የሴቶች ማህበረሰባዊ ተሳትፎ ማጎልበቻ ተቋም (መርየም)*
***ጽዮን*** -------*የስነ ምግባርና ራስን የመሆን ክህሎት ግንባታ ት/ቤት (ፅዮን)*
***ጺጋ*** ---------*የመንፈሳዊ እውቀት ተግባሪዎች የመረዳጃ ህብረት (ናዖድ)*
***ወል*** ---------*የአንድነትና ፍቅር ሰባኪዎች ልዩ መድረክ (ዘይኔ)*
***ራሶች*** ------*የጥቁሮች መብት ተሟጋች ዓለም አቀፍ ኔትወርክ (ዮሴፍ)*

............ በመጨረሻም ኢትኤል ለሱ ብቻ የተሰጠውን ትልቅ ጥቅል ዘርግቶ ማንበብ ጀመረ... **ከአባ ኤልካና፣ ከሼህ ከድርና አቦ አራርሳ** የተላከ ይላል...

## ደህረ - ታሪክ

»እውነቱን ሊደብቁን ብለው ብዙ ቢሞክሩም፤ እዎ ጽዮን ኢትዮጵያ ናት፣ የቅድስት ድንግል ማርያም ማደሪያ፣ የኪዳኑ ምህረት ወዳጅ ንዑዳን ህዝብ መኖሪያ፤ ከዋልድባ ገዳም የብርሃን ሰረገላ የሚነሳባት፣ የመልዓኩ ኡራኤል መገለጫ፤

»»በቅዱስ ቁርዓንና በነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) አፍም የተመሰከረላት፣ የእስልምና የመጀመሪያ ተቀባይ ሀገር/ እልፍ ሙሂቦች መገኛ፣ የኡሙ-ኢይመን/ የድምጸ መረዋው ቢላልና የሰሚው ንጉስ ነጋሲ ፍትሃዊ የፅድቅ ሀገር፤

»»የእየሱስ ክርስቶስ ጠባቂና አሳዳጊ እናት/ የንጉስ ባዜን ግዛት/ የሰብዓ ሰገል ቅድስት ምድር/ የግማደ መስቀሉና የቅዱስ ፅዋው መገኛ/ የትጉህ ደጋግ አባቶች ደብር፤

»»የአክሱማይ ዘላጋ ሃውልቶች አግዓዚ መፈክር/ የላሊበላ አናፂ የተዓምር ውቅር፤ ረጃጅም ጋራዎች ዘብ የቆሙላት የነብሮችና የአንበሶች መገኛ ዱር፤

»»የሰለሞን በትረ መንግስት ወራሽ/ የንግስተ ሳባ ኢትያኤል እፅ/ የይሁዳ አንበሳ ስርዉመንግስት መቆሚያ/ በጭቆና ቀንበር ውስጥ ለነበሩ ጥቁሮች የተስፋ ምልክት፣ የራሱ ተፈሪያኖች የቃል-ኪዳኒቱ ምድር፤

»»የኢትዮጵያዊቷ የዳዊት ሴት እናት ኢዴል በጎ እድል ምሳሌ፣ ገድ የሚቀናው ጋድ የሚባል የነበረው በኋላም ሙሉ ምዕራባውያን የአምላክ ስም አርገው ‹ጋድ› ባሉት የንጉስ ዳዊት አማካሪ ካህን አቡ ገዳ… የቃሉ አሪሳ ገዳም፤

»»እስያን፣ አውሮፓና አረብን የገዛ ታላቅ ንጉስ የእስያኤል እናት/ የራማያናና ክሪሽና ሂንዱ ጥቁር ንጉስ መነሻ/ የጉግ ማንጉትችን በር የዘጋ ዙል ቀርኒን፣ የቻይናና ህንድ ስልጣኔ መነሻ ቺን/ቂን/ ቅንና ሃያል ንጉስ ዜንግ ቂን ወላጅ እናት፤

»»»ሙሴን ያስጠጋና ትዕግስትና ጥበብን ያስተማረ ታላቁ ካህን ዮቶር-አብ (ግሪኮች ቶር ብለው እስከማምለክ የደረሱት) የዋቄ ጉራቻ ክብር፣ የሰፊ ኦዳ የአደባር ዛፍ መብቀያ፣ የገዳ ሚስጥር / የታቦተ ፅላቱ ጠባቂ ሀገር፤

»»የ ‹ጣ› አምራውያን ተራራማዋ ሃገር፣ የራሀ ብርሃን መፍለቂያ የኮሬብ ተራራ መገኛ!

…ኢትኤል ለአምላኩ እግዚአብሔር ቢጫ ወርቅ ስጦታን አቅርቦ፣ በቅኔ አዚሞ ፅድቅን ያፈሰብሽ ምድር/ የኤቶጵ ሚስጥር የአምላክ ወዳጆች መንበረ-ፀባዖት፣

›››አብርሃም አስራት ያስገባለት የነበረው የዘላለም ካህኑ መልከ ፃዴቅ መገኛ አፈር፤ የሰላምና ፍቅር ንጉስ ልጆች መስፈሪያ ምድር፤

›››የዝዮን ፒራሚዳዊ ስልጣኔ መስራች፣ የ‹ቶ› ጥበብ ምንጭ መፍሰሻ፣ ግብፆች የሰገዱላቸው/ ግሪኮች ‹ዚየስ› ብለው እስከማምለክ የደረሷቸው ነገስታት፣ የዞዮናውያን፣ የግዮናውያን፣ የአቢሲኒያዎች ግዛት፤

›››የኖህ መርከብ ከውሃ ጥፋት በኋላ በእ/ር መራራት የቆመባቸው የአራራት ተራራዎች መገኛ/ የሰሜን ተራሮች ምድር/ የኖህ ቃልኪዳን የሆነው ቀስተ ዳመና ደማቅ ቀለሞች የሚውለበለቡባት ትንቢት ያላት የራማ ከፍታ፤

›››ነብዩ ሄኖክ ከአነ ሀይወቱ እስካረገባት ቀን ድረስ በቅድስና የኖረባት/ የመጀመሪያ የመፃፍ ጥበብ ሲገለጥለት የሱባውያንን ቋንቋ የከተበብሽ የሳባውያን ምድር፤

›››ኤደን ገነትን ባካበበው የግዮን ወንዝ ውሃ ተለውሶ ከአፈርሽ የተቦካው አዳም የመጀመሪያ እግር አሻራ ያረፈብሽ ቅድስት ምድር፣ በእግዚአብሔር የተመረጥሽ ለመሆንሽ ምንም ጥያቄ ማይቀርብልሽ ጽዮን ሃገሬ ኢትዮጵያ ነሽ፡፡ የዓለም ሃይማኖቶችና ጥበቦች ሁሉ ቋት አንቺ ነሽና፡፡

የዚህች ኢትዮጵያ ልጆች! ሳጥናኤልም ስኬትን የሚሰበስበው ፍርሀትና ጥላቻ በዝተው ፍቅርና እምነት በዓለም ሲመናመኑ ነውና ይህን እንዲያደርግ አትፍቅዱለት፡፡ በእምነትና በፍቅር ጸንተን እየሱስ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ የንግስናን ሃገር አዘጋጅተን እንጠብቀዋለን፡፡

"ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማል ፥ እርሱም ባል ንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚል ነው!" ...... (ወደ ገላትያ ሰዎች 5:14)ይህም የህጎች ሁሉ መጠቅለያ "ወንድምህን እንደራስህ ውደድ ነው" እንጂ የሚለው ኦርቶዶክስ፣ ሙስሊም፣ ፕሮቴስታንት፣ ካቶሊክ፣ የህዋ-ምስክር አልያም አይሁድ የሆነውን ወንድምህን እንደራስህ ውደድ አይደለም፡፡ ስለዚህም በአንድ ልብ ተነስታችሁ የሰይጣን መጎልመሻ የሆኑ፣ በየቦታው የተሰገሰጋችሁን ጠንቋይ ቤቶች አፍርሱ፡፡

ከባህር ስር ውሁ-አቅላሚዎች (አልጌዎች) እስከ አማዞን ጫካ ግዙፍ ዛፎች ድረስ የፈጣሪን መኖር ይመሰክራሉና፡፡ ሰማይና ምድር ያልፋሉ፣ ስጋም ሩጫውን ጨርሶ "ወራጅ አለ!" ማለቱ አይቀርምና በመንፈስ ተሞልተን ዘላቂውን ጉዞ እንቀላቀላለን፡፡ እናም ተጓዥ የሰው ልጅ ነው፤ ሃይማኖት መንገድ ነው፣ እምነት መኪና ነው፤ ነዳጁም ትዕግስት ነው፤ በኢትዮጵያዊነት መንጃ-ፍቃድ እንደመንዳት ያለ ፀጋም የለም፡፡

*** ☥ – ☥ ***


*** ዩ – ዩ ***

*"እንዲህም ከሆነ፥ እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።" (1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 13:13)*
*ምህረት፣ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር ና አንድነትን ይዞ ለተጓዘ ሁሉ ሁሌም የእውነት መዳረሻ የሆነው፤ የእውነተኛው ጭለማም፣ የእውነተኛው ብርሃንም ባለቤት የሆነው የፍቅር አምላክ፤ የዘላለም ሰላም የተጎናፀፈው፣ በራማ ያለው የዓለማት ጌታ ሃገራችን ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይባርክ፤*

***ዝንቱ መጽሐፍ፤ አሜን ወ አሚን፣ ሊይኩን ወ ይሁን።።***

♥ ፍቅር... ያሸንፋል ♥

‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹**ተፈፀመ**›››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››



1፤ መሠረታቸው በተቀደሱ ተራሮች ነው፤
2፤ ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ፥
እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወዳቸዋል።
3፤የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፥ በአንቺ
የተከበረ ነገር ይበላል።
4፤ የሚያውቁኝን ረዓብንና ባቢሎንን
አስባቸዋለሁ፤እነሆ፤ ፍልስጥኤማውያን
ጢሮስም የኢትዮጵያም ሕዝብ፥ በዚያ
ተወለዱ።
5፤ ሰው እናታችን ጽዮን ይላል፥
በውስጥዋም ሰው ተወለደ፤ እርሱ ራሱም
ልዑል መሠረታት።
6፤ እግዚአብሔር ለሕዝቡ፥ በውስጥዋም
ለተወለዱት አለቆችዋ በመጽሐፍ
ይነግራቸዋል።
7፤ በአንቺ የሚኖሩ ሁሉ ደስ እንደሚላቸው
ይነግራቸዋል።
(መ.ቅዱስ ፡፡፡፡፡፡ መዝሙረ ዳዊት፤ ምዕራፍ-87)

..."እነዚያ በምድር ላይ ሃያል የሚሆኑት አይሁዶችንለአማኝሙስሊሞች በጠላትነት ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ የበረቱ ኾነው በእርግጥ ታገኛቸዋለህ።እነዚያ፤ «እኛ ክርስቲያኖች ነን!» የሚሉት ደግሞ ለአማኝ ሙስሊሞች በወዳጅነት በእርግጥ ይበልጥ የቀረቧቸው ኾነው ታገኛቸዋለህ። ይህም የሆነው ከእነሱ (ከእውነተኛ ክርስቲያኖች) መሃል (ጥሩ) ቀሰውስትናዓለምንየናቁመነኮሳት በመኖራቸው፤ እነርሱም የማይኮሩ (ትሁቶች) በመሆናቸው ነው።"
(ቅ.ቁርዓን ፡፡፡፡፡ የማዕድ-ምዕራፍ፤ ቁ82)

ዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አእምሮ፥ እንደ ሩሲያዊው ደራሲ አንቷን ቼኮቭ በሙያው ሀኪም ነው። ሆኖም ለስነጽሁፍ ባለው ፍቅር ጊዜውን አጣቦ እየፃፈ ሁለት መፃፍትን በእንግሊዘኛና በአማርኛ ከዚህ ቀደም አስንብቦናል። አሁን ደግሞ በዚህ አስገራሚ ልብወለድ መጥቷል።

ይህ መጽሀፍ የማይነኩና የማይደፈሩ ጥልቅ መንፈሳዊ ጉዳዮችን ያዘለ ነው። አእምሮው በሳይንስ ለተቀረጸ ምሁር ከሳይንስ ተጻራሪ የሆነ ይዘትን ማውጠንጠኑ ብዙም ያልተለመደ ነገር ነው።

የኢትዮጵን የልጅነት ስም ኢትኤልን ለዋናው በለታሪክ ሰጥቶ እና ሌሎች ከእሱ ጋር የሚጓዙ ጽዮን፣ አብርሃም፣ መርየም፣ ቶላ፣ ናያድ፣ ቢታንያ፣ ዘይኔና ዮሴፍ የተሰኙ ባህርያትን ፈጥሮ ታሪኩን በሀክምና ትምህርት በተሰማሩ ተማሪዋች መሀል አስናስሎ ጀምሮ እንደ ፕ/ር እሴና ዶ/ር ሳሙኤል ባሉ ምሁሮች አጅቦ እስከ አስገራሚዎቹ ባህታዊ፣ ወልዮችና አበ-ገዳዎች ድረስ አዋዝቶ ያዳርሰዋል።

ደራሲው ከሚያነሳቸው ርእሶች ውስጥ ዛሬ የኢትዮጵያን ኅብረተሰብ የተበተበው የጥንቆላ አስከፊነት አንዱን ስፍራ ይዟል። በተጨማሪም ገናናውን የኢትዮጵያ ታሪክ ፣ የገዳ ስርዓትና የ<ቶ> ጥበብን ይዳስሳል። ከዚህ ሁሉ በላይ በጠቅላላው የኢትዮጵያዊ ሙስሊሞች እና ክርስትያኖች ጥንታዊ ግንኙነትና ወዳጅነት፥ እንዲሁም በእስልምና እና ክርስትና ሀይማኖቶች መሀል ያሉትን ተመሳሳይነት፥ አንድነት እና ኅብረት አጉልቶ ያንጸባርቃል።

ታሪኩም ምስጢራዊ እና መንፈሳዊ ሆኖ፥ እያጓጓ እና እየተሽቆለቆለ ይፈስሳል። ቃላቱና አ/ነገሮቹም በቦታቸው ገብተው እርስበርሳቸው ተዋህደዋል። ይህን መጽሀፍ ሁሉም ሰው ቢያነበው የፈንጠዝያው(inspiration)ን እና የአእምሮውን አድማስ ያሰፋል ብዬ አምናለሁኝ። ******(ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ)

ዋጋ 131.00 ብር